ትምህርት
እና
ቃል ኪዳኖች

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች

ይህም ለነቢዮ ለጆሴፍ ስሚዝ
የተሰጡ ራእዮችን እና በእርሱ

ተተኪ በሆኑት የቤተክርስቲያኗ አመራር
ጥቂት የተጨመሩትን የያዘ ነው

ማውጫዎች

መግቢያ 5

የዘመን ቅድመ ተከተል. 9

ክፍሎች . . . . ፩

አስተዳደሪያዊ አዋጆች. . . . . ፪፻፺፫

መግቢያ

ትምህርት እና ቃልኪዳኖች፣ በመጨረሻው ቀናት የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለማቋቋም እና ለማስተዳደር መለኮታዊ ራእዮች እና የተነሳሱ ምሪት የተሰጡ አዋጆች ስብስብ ነው። ምንም እንኳን አብዛኞቹ ክፍሎች የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላትን የሚመለከቱ ቢሆኑም፣ መልእክቶቹ፣ ማስጠንቀቂያዎቹ፣ እና ማበረታቻዎቹ ለሰው ዘር በሙሉ ጥቅም ናቸው፤ እንዲሁም በሁሉም ቦታ ላሉት ሰዎች ሁሉ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ድምጽ ለጊዜአዊ ጥቅማቸውና ለዘለአለማዊ ደህንነታቸው ሲናገራቸው እንዲሰሙ ግብዣን የያዙ ናቸው።

በዚህ ጥራዝ ውስጥ ያሉት አብዛኞዎቹ ራዕዮች በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ነቢይ እና ፕሬዘደንት በነበረው በጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ አማካኝነት የተሰጡ ነበሩ። ሌሎቹ በአመራሮቹ ውስጥ የእርሱ ተተኪ በሆኑት በኩል የተሰጡ ነበሩ (የክፍል ፻፴፭፣ ፻፴፮፣ እና ፻፴፰፣ እና የአስተዳደሪያዊ አዋጆች ፩ እና ፪ ርዕሶችን ተመልከቱ)።

መፅሐፈ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ይፋ ከሆኑት የቤተክርስቲያኗ ጽሁፎች፣ ከመጻሐፍ ቅዱስ፣ ከመጻሐፈ ሞርሞን፣ እና የታላቅ ዋጋ ዕንቁ፣ መካከል አንዱ ነው። ሆኖም ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች የጥንት ጽሁፍ ትርጉም ባለመሆኑ ልዩ ነው፣ ነገር ግን ዘመናዊ ግኝት ነው እናም በእግዚአብሔር በተመረጡ ነቢያት አማካኝነት ለቅዱስ ስራው ዳግመኛ መመለስ እና በእነዚህ ዘመናት የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለማቋቋም የተሰጠ ነበር። በራዕዮቹ ውስጥ ለስላሳ ነገር ግን ፅኑ የሆነው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ በዘመን ፍጻሜ እንደገና ሲነገር ይደመጣል፤ እናም በዚህ ውስጥ የተጀመረው ስራ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያት የተነገሩትን ቃላት በማሟላት እና በማስማማይ ለዳግም ምፅዓት መዘጋጂያ ነው።

ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ በሻሮን፣ ዊንድሰር አውራጃ፣ ቨርሞንት ውስጥ በታህሳሥ ፳፫፣ ፲፰፻፭ (እ.አ.አ.) ተወለደ። በህይወቱ መጀመሪያ ላይ ከቤተሰቦቹ ጋር በምዕራብ ኒው ዮርክ በሚገኘው በዚህ ዘመን ማንቸስተር ወደሚባለው ሄደ። በዚያ አቅራቢያ እየኖረ ሳለ፣ በ፲፰፻፳ (እ.አ.አ.) ጸደይ፣ የአስራ አራት አመት ልጅ በነበረበት ወቅት ነበር የመጀመሪያውን ራእዩን የተቀበለው፣ በዚሁም በግል በእግዚአብሔር በዘለአለማዊው አባት፣ እና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ተጎብኝቶ ነበር። በእዚህ ራእይ በአዲስ ኪዳን የተመሰረተችው እና ሙላተ ወንጌልን ስታካሂድ የነበረችው እውነተኛይቷ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንደማትገኝ ተነግሮት ነበር። በብዙ መላዕክት ትምህርት እንዲሰጠው የተደረገበት ሌሎች መለኮታዊ መገለጦችም ተከትለው ነበር፤ እግዚአብሔር በምድር ላይ የተለየ ስራ ለእርሱ እንዳለው እናም በእርሱ አማካኝነት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዳግመኛ ወደ ምድር ተመልሳ እንደምትመጣ እንዲያይ ተደርጎ ነበር።

ከጊዜ በኋላም፣ ጆሴፍ ስሚዝ በመለኮታዊ እርዳታ መጽሐፈ ሞርሞንን እንዲተረጉምና እንዲያሳትም ይችል ዘንድ ተደርጎ ነበር። በዚያም ጊዜ እርሱ እና ኦሊቨር ካውድሪ በግንቦት ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በመጥምቁ ዮሐንስ ወደ አሮናዊ ክህነት ተሹመው ነበር (ት. እና ቃ. ፲፫ን ተመልከቱ)፣ እናም ብዙም ሳይቆይ፣ በጥንቶቹ ኃዋሪያት በጴጥሮስ፣ በያዕቆብ እና በዮሐንስ ወደ መልከ ጼዴቅ ክህነት ተሹመው ነበር (ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፪ን ተመልከቱ)። ሌሎችም ሹመቶች ተከትለው ነበር፣ በዚህም በሙሴ፣ በኤልያስ እና በኤልያ፣ እንዲሁም በብዙ የጥንት ነቢያት የክህነት ቁልፎች ተስጥቷቸው ነበር (ት. እና ቃ. ፻፲፤ ፻፳፰፥፲፰፣ ፳፩ን ተመልከቱ)። እነዚህ ሹመቶች በእርግጥም ለሰው ልጅ የመለኮታዊ ስልጣኖች ዳግመኛ የተመለሱባቸው ናቸው። በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በመለኮታዊ አመራር መሰረት፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ቤተክርስቲያኗን አደራጀ፣ እንዲህም እውነተኛዋ የኢየሱስ ክርስቶስ

ቤተክርስቲያን ዳግመኛ በሰዎች መካከል እንደ እምነት ተቋም ወንጌልን ለማስተማር እና የደህንነት ስርዓቶችን ለማከናወን በስልጣን ስራዋን ጀመረች። (ት. እና ቃ. ፳ን እና የታላቅ ዕንቁ ዋጋ፣ የጆሴፍ ስሚዝ—ታሪክ ፩ን ተመልከቱ)።

እነዚህ የተቀደሱ ራዕዮች ችግር በነበረበት ጊዜ የተቀበሉት የጸሎት መልስ ነበሩ፣ እናም የመጡትም እውነተኛ ሰዎች ከተሳተፉበት ከገሀዱ የህይወት ጉዳዮች ነበር። ነቢዩ እና ተባባሪዎቹ የመለኮታዊ ምሪትን ፈልገው ነበር፣ እና እነዚህ ራዕዮችም እነርሱ ይህን እንደተቀበሉ ያረጋግጣሉ። በራዕዮቹም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ዳግመኛ መመለሱንና መገለጡን፣ እናም የዘመኑ ፍጻሜም የተቃረበ መሆኑን አንድ ሰው ለመመልከት ይችላል። የቤተክርስቲያኗ ከኒው ዮርክ እና ፔንሲላቫኒያ ወደ ኦሃዮ፣ ወደ ሚዙሪ፣ ወደ ኢሊኖይ፣ እና በመጨረሻም ወደ ታላቁ የምዕራብ አሜሪካ ሸለቆ ከነበራት የምዕራብ እንቅስቃሴ፣ እና በአሁኑ ዘመን ቅዱሳን ፅዮንን ለመገንባት የሞከሩበትን ትግል በእነዚህ ራዕዮች ውስጥ ተመልክተዋል።

ቀደም ብለው ያሉት አብዛኞቹ ክፍሎች ስለመጽሐፈ ሞሮሞን መተርጎም እና ህትመት የተመለከቱ ነገሮችን ያካተቱ ናቸው(ክፍል ፫፣ ፭፣ ፲፣ ፲፯፣ እና ፲፱ን ተመልከቱ)። ወደኋላ ያሉት አንዳንዶቹ ክፍሎች የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተነሳሳ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ስራውን የሚያንጸባርቁ ናቸው፣ በዚህም ጊዜ አብዛኞቹ ታላላቅ የትምህርት ክፍሎች ተገልጸዋል (ለምሳሌ ክፍል ፵፯፣ ፷፬፣ ፸፫፣ ፸፮፣ ፸፯፣ ፹፮፣ ፺፩ እና ፻፴፮ን ተመልከቱ፣ እያንዳንዳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር አንዳንድ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው)።

በራዕዮቹ ውስጥ፣ የአምላክ ስነ-ፍጥረትን፣ የሰው ልጅ አጀማመርን፣ የሰይጣን መኖርን፣ የምድራዊ ህይወት ዓላማን፣ የመታዘዝን አስፈላጊነት፣ የንስሃን አስፈላጊነት፣ የመንፈስ ቅዱስ ስራዎችን፣ ደህንነትን የተመለከቱ ስርዐቶችና አፈጻጸሞችን፣ የምድር ዕጣ ፈንታን፣ ከትንሳኤ በኋላ የሚኖረው የሰው ልጅ ሁኔታ እና ፍርድን፣ የጋብቻ ግንኙነት ዘላለማዊነትን፣ እናም የቤተሰብ ዘለአለማዊ የመሆን ሁኔታን በሚመለከት መሰራታዊ ነገሮች መግለጫ በመስጠት የወንጌል ትምህርቶች ተገልጸዋል። እንደዚሁ ከኤጲስ ቆጳሳት፣ ከቀዳሚ አመራር፣ ከአስራ ሁለቱ ቡድን፣ እና ከሰባዎቹ እና ከሌሎች የአመራር ሹመቶች እና ቡድኖች ጥሪዎች ጋር በሂደት የተገለጸው የቤተክርስቲያኗ አስተዳደራዊ ቅርጾች ተገልጸዋል። በመጨረሻም ስለኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊነት፣ ግርማው፣ ፍጹምነቱ፣ ፍቅሩ፣ እና የማዳን ኃይሉ የተሰጠው ምስክርነት ይህንን መጽሐፍ ለሰው ልጆች ቤተሰብ ታላቅ ዋጋ ያለው እና "ለቤተክርስቲያኗም ከምድር ሀብት ሁሉ የበለጠ ዋጋ እንዲኖረው" ያደርገዋል (የት. እና ቃ. ፸ መግቢያ ተመልከቱ)።

ራዕዮቹ በመጀመሪያ የተመዘገቡት በጆሴፍ ስሚዝ ጸሀፊዎች ነበር፣ እናም የቤተክርስቲያኗ አባላት በእጅ የተጻፉ ቅጂዎችን እርስ በእርስ በደስታ ይካፈሉ ነበር። ቋሚ መዝገብ ለመፍጠር፣ ጸሀፊዎች እነዚህን ራዕዮች ባልታተሙ የመዝገብ መፅሀፎች ውስጥ በቅጂ አዘጋጁ፣ እነዚህንም የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ራዕዮችን ለማተም ለማዘጋጀት ተጠቀሙባቸው። ጆሴፍ ስሚዝ እና የመጀመሪያ የቤተክርስቲያኗ አባላት እነዚህን ራእዮች ቤተክርስቲያኗ በተመለከቱበት ሁኔታ ይመለከቷቸው ነበር፥ ህያው፣ ለውጥ የሚፈጥር፣ እና በተጨማሪ ራዕይ ለመጣራት የሚችል። ራዕዮችን በሚቀዱበት ጊዜ እና ለመታተም በሚዘጋጁበት ጊዜ ሳይታወቅ ስህተቶች ሊገቡባቸው እንደሚችሉም አውቀው ነበር። ስለዚህ፣ የቤተክርስቲያኗ ጉባኤ በ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ጆሴፍ ስሚዝ "በመንፈስ ቅዱስ በኩል ሊያገኛቸው የሚችላቸውን እነዚያን ጉድለቶች እና ስህተቶች እንዲያስተካክል" ጠየቁት።

ራዕዮች ከተገመገሙ እና ከተስተካከሉ በኋላ፣ የቤተክርስቲያኗ አባላት በምዙሪ ውስጥ የነቢዩን ብዙ የመጀመሪያ ራዕዮች የያዘውን፣ *A Book of Commandments for the Government of the Church of Christ* (በርዕስ መጽሐፈ ትእዛዛት ለክርስቶስ ቤተክሪስቲያን አስተዳደር) የሚባለውን መፅሀፍ ማተም ጀመሩ። ነገር ግን፣ በሀምሌ ፳፣ ፲፰፻፴፫

(እ.አ.አ.) በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ የነበረውን የቅዱሳንን የእትመት ቢሮ በመደምሰሳቸው፣ ራዕዮችን ለማተም የተደረገው የመጀመሪያ ጥረት ቆመ።

የምዙሪ የእትመት ቢሮ እንደተደመሰሰ በሰሙበት ጊዜ፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ሌሎች የቤተ ክርስቲያኗ መሪዎች ራዕዮችን በከርትላንድ ኦሀዮ ለማተም ዝግጅት ጀመሩ። እንደገና ስህተቶችን ለማስተካከል፣ አባባሎችን ለመግለጽ፣ እና የቤተክርስቲያኗ ትምህርት እና ድርጅትን ለማሳወቅ፣ ጆሴፍ ስሚዝ የአንዳንድ ራዕዮችን ጽሁፎች የማረም ስራን በመቆጣጠር እነዚህን በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) እንደ *Doctrine and Covenants of the Church of the Latter Day Saints* (መጽሐፈ ትእዛዛት ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ቤተክሪስቲያን አስተዳደር) ለማሳተም አዘጋጀ። ጆሴፍ ስሚዝ የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ሌላ ቅጂ እኒድታተም ፈቃድ ሰጠ፣ ይህም የታተመው በ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) ከነቢዩ ሰማዕትነት ጥቂት ወሮች ካለፉ በኋላ ነበር።

የመጀመሪያዎቹ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ለራዕዮቹ ታላቅ ዋጋ ሰጧቸው እናም እንደ እግዚአብሔር መልእክቶች ይመለከቷቸው ነበር። በ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.)፣ አንድ ጊዜ፣ ብዙ የቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ጌታ በነፍሳቸው እነዚህ ራዕዮች እውነት እንደሆኑ እንደመሰከረላቸው የክብር ምስክራቸውን ሰጥተው ነበር። ይህ ምስክርነት በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) የትምህርት እና ቃል ኪዳን ቅጂ ውስጥ በአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት የተጻፈ ምስክር በመባል ታትሞ ነበር።

የመጽሐፈ ትምህርት እና ቃል ቃል ኪዳኖች እውነተኛነትን በተመለከተ የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ምስክርነት

በቤተክርስቲያኗ ድምጽ ለዚህ ዓላማ በተመደበው ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ አማካኝነት ለቤተክርስቲያኗ የሰጠውን ትዕዛዛት፣ ይኸውም የጌታ ትእዛዛት መጽሐፍን በተመለከተ የምስክሮች ምስክርነት፥

ስለዚህ እኛ በአለም ለሚገኙ ለሰው ዘር በሙሉ፣ በምድር ገጽታ ላይ ላሉ ፍጡራን ሁሉ፣ እነዚህ ትእዛዛት በእግዚአብሔር ምሪት ለሰዎች ሁሉ ጥቅም እንደተሰጡ እና እውነት መሆናቸውን ጌታ ለነፍሳችን እንደመሰከረልን፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነትም እንዳፈሰሰልን ምስክርነታችንን ለመስጠት ፈቃደኞች ነን።

ጌታ እረዳታችን ሆኖ፣ ይህን ምስክርነት ለዓለም እንሰጣለን፤ እናም ለዓለም ምስክርነታችንን እድንሰጥ ይህንን ዕድል እድናገኝ የተፈቀደልን በእግዚአብሔር አብ፣ እና በልጁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነው፣ እኛም የሰው ልጆችም ሁል ጊዜ በዚህ ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ለጌታ እየጸለይን፣ በዚሁ ምስክርነት እጅግ በጣም ተደስተናል።

የአስራ ሁለቱ ስም ዝርዝር፥

ቶማስ ቢ ማርሽ
ዴቪድ ደብሊው ፓተን
ብሪግሃም ያንግ
ሂበር ሲ ኪምቦል
ኦርሰን ሀይድ
ዊሊያም ኢ መክለልን
ፓርለይ ፒ ፕራት
ሉክ ኤስ ጆንሰን
ዊሊያም ስሚዝ
ኦርሰን ፕራት
ጆን ኤፍ ቦይንቶን
ላይማን ኢ ጆንሰን

በተከታታይ የትምህርት እና ቃልኪዳኖች ቅጂዎች፣ ተጨማሪ ራእዮች እና ሌሎች መረጃዎች ብቁ በሆኑ ተሰብሳቢዎች ወይም በቤተክርስቲያኗ ጉባዔ ሲስተናገዱ እና ተቀባይነትን ሲያገኙ እንዲጨመሩ ተደርገዋል። በብሪገም ያንግ አመራር ስር በሽማግሌ ኦርሰን ፕራት የተዘጋጀው የ፲፰፻፸፰ (እ.አ.አ.) ቅጂ፣ ራዕዮችን በዘመን ቅድመ መከተል እና አዲስ ርዕሶችንና ታሪካዊ መግቢያዎች በመስጠት አዘጋጀ።

ከ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ቅጂ ጀምሮ፣ ሰባት የመንፈሳዊ ትምህርት ትምህርቶች ተካተው

ነበር፤ *Lectures on Faith* (የእምነት ንግግሮች) የሚል ርዕስ ተሰጥቷቸው ነበር። እነዚህ ከ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) እስከ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ፣ ኦሃዮ፣ ለነቢያት ትምህርት ቤት መጠቀሚያ የተዘጋጁ ነበሩ። ለትምህርት እና መመሪያ ቢጠቀሙም፣ ከ፲፱፻፳፩ (እ.አ.አ.) ቅጂ ጀምሮ እነዚህ ንግግሮች ከትምህርትና ቃል ኪዳኖች ውስጥ እንዲወጡ ተደርገዋል፣ ምክንያቱም አጠቅላይ ቤተክርስቲያኗን በሚመለከት የተሰጡ ወይም የቀረቡ ራእዮች ስላልሆኑ ነው።

በትምህርት እና ቃል ኪድኖች የ፲፱፻፹፩ (እ.አ.አ.) በእንግሊዝኛው ቅጂ ውስጥ ሶስት መረጃዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ተጨምረው ነበር። እነዚህም የመታን ደህንነት መሰረታዊ መርሆችን የሚመሰርቱት ክፍሎች ፻፴፯ እና ፻፴፰፣ እና ያለዘር እና የቀለም ልዩነት ብቁ የቤተክርስቲያኗ ወንድ አባላት ለክህነት ለመሾም እንደሚችሉ ያስተዋወቀው የአስተዳደራዊ አዋጅ ፪ ነበሩ።

እያንዳንዱ የትምርት እና ቃል ኪዳን ቅጂ የድሮ ስህተቶችን አስተካክለዋል እና አዲስ መረጃዎችን፣ በተለይም በክፍል ርዕሶች የታሪክ ክፍሎችን፣ ጨምረዋል። የዚህ ጊዜ ቅጂ ቀናትን እና የቦታ ስምችን ያጣራል እና ሌሎችንም በተጨማሪ ያስተካክላል። እነዚህ ለውጦች የተደረጉት ጽሁፎችን ከብዙዎቹ ትክክለኛው ታሪካዊ መረጃዎች ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ነው። በዚህ አዲስ ቅጂ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ልዩ ነገሮችም ራዕዮች የተቀበለበትን ቦታዎች የሚያሳዮ ካርታዎችን የተከለሱበት፣ በተጨማሪውም የቤተክርስቲያኗን ታሪካዊ ፎርትዎች፣ ማጣቀሻዎችን፣ የክፍል ርዕሶችን፣ እና የርዕስ ማጠቃለያዎችን የተሻሻሉበት ነበሩ፤ ሁሉም ማሻሻያዎች የተደረጉት አንባቢዎች በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የተሰጡትን መልእክቶች እንዲረዱና እንዲደሰቱበት ለመርዳት ነበር። በክፍል ርዕሶች ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችም የተወሰዱት ከቤተክርስቲያኗ ታሪክ ያልታተመ ፅሁፍ እና ከታተመው ከ*History of the Church* [የቤተክርስቲያኗ ታሪክ] (እነዚህም በርዕሶች ውስጥ አንድ ላይ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ተብለው ይጠራሉ) እና ከ *Joseph Smith Papers* [የጆሴፍ ሚዝ ፅሁፍ] ውስጥ ነበር።

የማውጫዎች የዘመን ቅድመ ተከተል

ቀን (እ.አ.አ.)		*ቦታ*	*ክፍሎች*
፲፰፻፳፫	መስከረም	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፪
፲፰፻፳፰	ሐምሌ	ሀርመኒ፣ ፔንሲላቬኒያ	፫
፲፰፻፳፱	የካቲት	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፬
	መጋቢት	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፭
	ሚያዝያ	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፮፣ ፯፣ ፰፣ ፱፣ ፲
	ግንቦት	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፲፩፣ ፲፪፣ ፲፫*
	ሰኔ	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፲፬፣ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰
	በጋ	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፲፱
፲፰፻፴		ዌይን አውራጃ፣ ኒው ዮርክ	፸፬
	ሚያዝያ	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፳*፣ ፳፩
	ሚያዝያ	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፳፪፣ ፳፫
	ሐምሌ	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፳፬፣ ፳፭፣ ፳፮
	ነሐሴ	ሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ	፳፯
	መስከረም	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፳፰፣ ፳፱፣ ፴፣ ፴፩
	ጥቅምት	ማንችስተር፣ ኒው ዮርክ	፴፪
	ጥቅምት	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፫
	ህዳር	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፬
	ታሕሣሥ	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፭*፣ ፴፮*፣ ፴፯*
፲፰፻፴፩	ጥር	ፈየት፣ ኒው ዮርክ	፴፰፣ ፴፱፣ ፵
	የካቲት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፵፩፣ ፵፪፣ ፵፫፣ ፵፬
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፵፭፣ ፵፮፣ ፵፯፣ ፵፰
	ግንቦት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፵፱፣ ፶
	ግንቦት	ቶምሰን፣ ኦሃዮ	፶፩
	ሰኔ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፶፪፣ ፶፫፣ ፶፬፣ ፶፭፣ ፶፮
	ሐምሌ	ጽዮን፣ ጃክሰን አውራጃ፣ ሚዙሪ	፶፯
	ነሐሴ	ጽዮን፣ ጃክሰን አውራጃ፣ ሚዙሪ	፶፰፣ ፶፱
	ነሀሴ	ኢንድፔንደንስ፣ ሚዙሪ	፷
	ነሀሴ	የምዙሪ ወንዝ፣ ሚዙሪ	፷፩
	ነሐሴ	ቻሪቶን፣ ሚዙሪ	፷፪
	ነሐሴ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፷፫
	መስከረም	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፷፬
	ጥቅምት	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፷፭፣ ፷፮
	ህዳር	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፩፣ ፷፯፣ ፷፰፣ ፷፱፣ ፸፣ ፻፴፫
	ታህሳስ	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፸፩
	ታህሳስ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፸፪
፲፰፻፴፪	ጥር	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፸፫
	ጥር	አምኸርስት፣ ኦሃዮ	፸፭
	የካቲት	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፸፮
	መጋቢት	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፸፯፣ ፸፱፣ ፹፣ ፹፩

*በተጠቀመው ቦታ ላይ ወይም አቅራቢያ

ቀን (እ.አ.አ.)		*ቦታ*	*ክፍሎች*
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፸፰
	ሚያዝያ	ኢንድፔንደንስ፣ ሚዙሪ	፹፪፤ ፹፫
	ነሀሴ	ሐይረም፣ ኦሃዮ	፺፱
	መስከረም	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፹፬
	ህዳር	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፹፭
	ታህሳሥ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፹፮፤ ፹፯*፤ ፹፰
፲፰፻፴፫	የካቲት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፹፱
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፺፤ ፺፩፤ ፺፪
	ግንቦት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፺፫
	ሰኔ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፺፭፤ ፺፮
	ነሐሴ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፺፬፤ ፺፯፤ ፺፰
	ጥቅምት	ፔሪስበርግ፣ ኒው ዮርክ	፻
	ታህሣሥ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፩
፲፰፻፴፬	የካቲት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፪፤ ፻፫
	ሚያዝያ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፬*
	ሰኔ	ፊሺንግ ወንዝ፣ ሚዙሪ	፻፭
	ህዳር	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፮
፲፰፻፴፭	ሚያዝያ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፯
	ነሐሴ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፴፬
	ታህሳስ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፰
፲፰፻፴፮	ጥር	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፴፯
	መጋቢት	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፱
	ሚያዝያ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፲
	ነሃሴ	ሴለም፣ ማሳቹሴትስ	፻፲፩
፲፰፻፴፯	ሐምሌ	ከርትላንድ፣ ኦሃዮ	፻፲፪
፲፰፻፴፰	መጋቢት	ፋር ዌስት፣ ሚዙሪ	፻፲፫*
	ሚያዝያ	ፋር ዌስት፣ ሚዙሪ	፻፲፬፤ ፻፲፭
	ግንቦት	ስፕሪንግ ሂል፣ ዴቪስ አውራጃ፣ ሚዙሪ	፻፲፮
	ሐምሌ	ፋር ዌስት፣ ሚዙሪ	፻፲፯፤ ፻፲፰፤ ፻፲፱፤ ፻፳
፲፰፻፴፱	መጋቢት	ልብርቲ እስር ቤት፣ ክለይ አውራጃ፣ ሚዙሪ	፻፳፩፤ ፻፳፪፤ ፻፳፫
፲፰፻፵፩	ጥር	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፻፳፬
	መጋቢት	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፻፳፭
	ሐምሌ	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፻፳፮
፲፰፻፵፪	መስከረም	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፻፳፯፤ ፻፳፰
፲፰፻፵፫	የካቲት	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፻፳፱
	ሚያዝያ	ራመስ፣ ኢሊኖይ	፻፴
	ግንቦት	ራመስ፣ ኢሊኖይ	፻፴፩
	ሐምሌ	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፻፴፪
፲፰፻፵፬	ሰኔ	ናቩ፣ ኢሊኖይ	፻፴፭
፲፰፻፵፯	ጥር	ዊንተር ኳርተርስ (የአሁኑ ነብራስካ)	፻፴፮
፲፰፻፺	ጥቅምት	ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ	አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩
፲፱፻፲፰	ጥቅምት	ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ	፻፴፰
፲፱፻፸፱	ሰኔ	ሶልት ሌክ ሲቲ፣ ዩታ	አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪

*በተጠቀመው ቦታ ላይ ወይም አቅራቢያ

ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች

ክፍል ፩

በህዳር ፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ በቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ልዮ ጉባዔ ወቅት በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የተሰጠ ራዕይ። ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ብዙ ራእዮች ከጌታ ተሰጥተው ነበር፣ እናም እነዚህ ራዕዮች በመጽሐፍ መልክ ተጠርዘው እንዲታተሙ በጉባኤው ውሳኔ ከተሰጠባቸው ዋነኛ ሐሳቦች መካከል አንዱ ነበር። ይህ ክፍል በዚህ ዘመን የተሰጡትን ትምህርቶች፣ ቃል ኪዳኖች፣ እና ትዛዛትን በተመለከተ የጌታን መግቢያ የያዘ ነው።

፩–፯፣ የማስጠንቀቂያው ድምጽ ለሁሉም ሰው ነው፤ ፰–፲፮፣ ክህደትና ክፋት ዳግም ምፅዓትን ይቀድማሉ፤ ፲፯–፳፫፣ ጆሴፍ ስሚዝ የጌታን እውነት እና ሀይል በምድር ዳግመኛ እንዲመልስ ተጠርቷል፤ ፳፬–፴፫፣ መፅሐፈ ሞርሞን መጥቷል እናም እውነተኛ ቤተክርስቲያን ተመስርታለች፤ ፴፬–፴፮፣ ሰላምም ከምድር ይወሰዳል፣ ፴፯–፴፱፣ እነዚህን ትዛዛት መርምሩ።

ከፍ ብሎ የሚኖረው እና [ሀ]አይኖቹንም በሁሉም ሰዎች ላይ የሆነው፣ የእርሱ ድምፅ አቤቱ እናንት [ለ]የቤተክርስቲያኔ ሰዎች ሆይ አድምጡ ይላል፣ አዎን እውነት እላለሁ፥ እናንት በሩቅ ያላችሁ፣ በባህር ደሴቶች ላይ ያላችሁ [ሐ]ስሙ፣ በአንድነትም አድምጡ።

፪ በእውነት የጌታ [ሀ]ድምጽ ለሁሉም ሰው ነውና፣ እናም [ለ]ማንም አያመልጥም፤ እናም የማያይ አይንም ሆነ የማይሰማ ጆሮ፣ ወይም የማይጣስ [ሐ]ልብ አይኖርም።

፫ እናም [ሀ]አመጸኞች በብዙ ሐዘን ይወጋሉ፤ ኃጢአታቸውም በቤቶች አናት ላይ [ለ]ይነገራሉ፣ የሚስጥር ተግባሮቻቸውም ይገለጣሉ።

፬ እናም [ሀ]በመጨረሻዎቹ ቀናት፣ እኔ በመረጥኳቸው ደቀመዛሙርቶቼ አንደበት፣ የማስጠንቀቂያው [ለ]ድምጽ ለሁሉም ህዝብ ይሆናል።

፭ እናም እነርሱም ወደፊት ይሄዳሉ፣ ማንም አያግዳቸውም፣ እኔ ጌታ አዝዣቸዋለሁና።

፮ እነሆ አቤቱ! የምድር ነዋሪዎች፣ ለእናንተ [ሀ]እንዲያሳትሙት የሰጠዋችሁ ይህ የእኔ [ለ]ስልጣን፣ እንዲሁም የአገልጋዮቼ ስልጣን፣ እናም ለመፅሐፈ ትእዛዛቴ መቅድም ነው።

፯ ስለዚህ፣ [ሀ]ፍሩ እናም ተንቀጥቀጡ፣ አቤቱ! እናንት ሕዝቦች ሆይ፣ እኔ ጌታ በእነርሱ ያወጅኩት [ለ]ይፈጸማልና።

፰ እናም እውነት እላችኋለሁ፣ ይህንን የምስራች ይዘው ወደ ምድር ነዋሪዎች የሚሄዱ፣ ለእነርሱ በምድርም ሆነ በሰማይ፣

፩ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፯–፰።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ለ ፫ ኔፊ ፳፯፥፫፤
ት. እና ቃ. ፳፥፩።
ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ሐ ዘዳግ. ፴፪፥፩።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፲፮።
ለ ፊልጵ. ፪፥፱–፲፩።
ሐ ቅ.መ.መ. ልብ።
፫ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ሉቃ. ፰፥፲፯፤ ፲፪፥፫፤
፪ ኔፊ ፳፯፥፲፩፤
ሞር. ፭፥፰።
፬ሀ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ለ ሕዝ. ፫፥፲፯–፳፩፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥፴፯።
ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ፤ የሚስዮን ስራ።
፮ሀ ት. እና ቃ. ፸፪፥፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስልጣን።
፯ሀ ዘዳግ. ፭፥፳፱፤
መክ. ፲፪፥፲፫።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፴፰።

የማያምኑትን እና [ሀ]አመጸኞችን [ለ]የማሰር ኃይል ተሰጥቷቸዋል፤

፱ አዎን፣ እውነት፣ የእግዚአብሔር [ሀ]ቁጣ [ለ]በክፉዎች ላይ ያለልክ የሚወርድበት ቀን እስከሚመጣ ድረስ እንዲያስሯቸው—

፲ ጌታ መጥቶ ለእያንዳንዱን ሰው [ሀ]እንደ የስራው [ለ]መጠን [ሐ]እስኪመልስ እና ሁሉም ሰው ለባልንጀራው በሰፈረበት መጠን እስከሚሰፍርበት [መ]ቀን ድረስ የማሰር ኃይል ተሰጥቷቸዋል።

፲፩ ስለዚህ የሚሰማ ሁሉ ይሰማ ዘንድ፣ የጌታ ድምጽ እስከ ምድር ዳርቻ ነው፥

፲፪ ለሚመጣው ተዘጋጁ ተዘጋጁ፤ ጌታ ተቃርቧልና፤

፲፫ እናም የጌታ [ሀ]ቁጣ ተቀጣጥሏል፣ እናም [ለ]ሰይፉም በሰማይ ታጥቧል፣ እንዲሁም በምድር ነዋሪዎችም ላይ ይወርዳል።

፲፬ እናም የጌታ [ሀ]ክንድ ይገለጣል፤ የጌታን ድምጽ ሆነ ያገልጋዮቹን ድምጽ [ለ]ከማይሰሙ፣ ለነቢያት እና ለኃዋሪያት ቃላት [ሐ]ትኩረት ከማይሰጡ ሰዎች መካከል [መ]የሚገለሉበት ቀን ይመጣል፣

፲፭ [ሀ]ከስርዓቴ [ለ]እርቀዋል፣ እናም [ሐ]ዘለአለማዊ ቃል ኪዳኔን [መ]አፍርሰዋልና፤

፲፮ ጽድቁን ለመመስረት ጌታን [ሀ]አይፈልጉም፣ ነገር ግን ሁሉም ሰው [ለ]በገዛ [ሐ]መንገዱ፣ እናም ቁሳቁሱ የጣኦት በሆነው፣ [መ]አምሳያውም የአለም በሆነው፣ [ሠ]አርጅቶም [ረ]በባቢሎን በሚጠፋው፣ እንዲሁም በምትወድቀው በታላቂቷ ባቢሎን እንደ አምላኩ ምስል ይጓዛል።

፲፯ ስለዚህም እኔ ጌታ በምድር [ሀ]ነዋሪዎች ላይ የሚመጣውን መቅሰፍት በማወቁ፣ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን ጠራሁት እናም ከሰማይም ተናገርኩት እንዲሁም ትእዛዛትን ሰጠሁት፤

፲፰ እናም ደግሞ ይህንን የምስራች ለአለም እንዲያውጁ፣ እናም ይህን ሁሉ ያደረኩትም በነቢያቶች የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ ለሌሎችም ትእዛዛትን ሰጥቻለሁ—

፲፱ የአለም [ሀ]ደካማ ነገሮች ወደፊትም ይወጣሉ ብርቱውን እና ጠንካራውን ይሰብራሉ፣ ሰው ባልጀራውን መምከር አይገባውም፣ በስጋ ክንድ [ለ]መመካት አይኖርበትም—

፳ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው የአለም አዳኝ በሆነው በጌታ እግዚአብሔር ስም [ሀ]ይናገር ዘንድ፤

፳፩ ደግሞም እምነትም በምድር ይበዛ ዘንድ፤

፳፪ ዘለአለማዊ [ሀ]ቃልኪዳኔ ይመሰረት ዘንድ፤

፳፫ [ሀ]የወንጌሌ ሙላት [ለ]በደካሞች እና በተራ ሰዎች አማካይነት በነገስታት እና በገ

፰ ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ቅ.መ.መ. ማተም፤ ማስተሳሰር።
፱ ሀ ራዕ. ፲፱፥፲፭–፲፮፤ ፩ ኔፊ ፳፪፥፲፮–፲፯።
ለ ሞዛያ ፲፮፥፪፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፩፤ ፶፭።
፲ ሀ ምሳ. ፳፬፥፲፪፤ አልማ ፱፥፳፰፤ ፵፩፥፪–፭፤ ት. እና ቃ. ፮፥፴፫።
ለ ማቴ. ፯፥፪።
ሐ ሕዝ. ፯፥፬፤ ት. እና ቃ. ፶፮፥፲፱። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
መ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፮።
ለ ሕዝ. ፳፩፥፫፤ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፬።
፲፬ ሀ ኢሳ. ፶፫፥፩።
ለ ፪ ኔፊ ፱፥፴፩፤ ሞዛያ ፳፮፥፳፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፩፥፪።
መ የሐዋ. ፫፥፳፫፤ አልማ ፶፥፳፤ ት. እና ቃ. ፶፥፰፤ ፶፮፥፫።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ለ ኢያ. ፳፫፥፲፮፤ ኢሳ. ፳፬፥፭።
ሐ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
መ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፲፮ ሀ ማቴ. ፮፥፴፫።
ለ ኢሳ. ፶፫፥፮።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፪፥፮።
መ ዘፀአ. ፳፥፬፤ ፫ ኔፊ ፳፩፥፲፯። ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
ሠ ኢሳ. ፶፥፱።
ረ ት. እና ቃ. ፷፬፥፳፬፤ ፻፴፫፥፲፬። ቅ.መ.መ. ባቢሎን፤ አለማዊነት።
፲፯ ሀ ኢሳ. ፳፬፥፩–፮።
፲፱ ሀ የሐዋ. ፬፥፲፫፤ ፩ ቆሮ. ፩፥፳፯፤ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፫፤ ፻፴፫፥፶፰–፶፱። ቅ.መ.መ. ገር፤ ገርነት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፰፥፴፩። ቅ.መ.መ. መታመን።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. መመስከር።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፱፥፲፩። ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን፤ አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ፩ ቆሮ. ፩፥፳፯–፳፱።

ዝርዎች ፊት እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ [ሐ]ይታወጅ ዘንድ ተሰጥቷቸዋል።

፳፬ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ እኔም ተናግሬዋለሁ፤ እነዚህ [ሀ]ትእዛዛት ከእኔ ዘንድ ናቸው፣ በድክመታቸው፣ [ለ]እንደ ቋንቋቸው ወደ [ሐ]መረዳት ይመጡ ዘንድ ለአገልጋዮቼ ተሰጥተዋቸዋል።

፳፭ እናም ስህተትን እስከፈጸሙ ድረስ ስተታቸውን እንዲታወቁ፤

፳፮ እናም [ሀ]ጥበብንም እስከፈለጉ ድረስ ያንኑ ይማሩ ዘንድ፤

፳፯ እናም ኃጢአትን እስከሰሩ ድረስ [ሀ]ንስሀ እንዲገቡ [ለ]ይገሰጹ ዘንድ፤

፳፰ [ሀ]ትሁት እስከሆኑ ድረስ እንዲበረቱ እና ከላይም እንዲባረኩ፣ እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ [ለ]እውቀትንም ይቀበሉ ዘንድ ነው።

፳፱ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊም ቢሆን የኔፋውያንን መዝገብ ከተቀበለ በኋላ፤ አዎን በእግዚአብሔር ምህረት፣ በእግዚአብሔር ኃይል [ሀ]መፅሐፈ ሞርሞንን የመተርጎም ኃይል ይኖረው ዘንድ ነው።

፴ እናም ደግሞ እነዚህ ትእዛዛት የተሰጣቸው በምድር ገጽ ላይ ሁሉ ብቸኛ እውነተኛ እና ህያው የሆነችውን [ሀ]ቤተክርስቲያን፣ እኔም ጌታ በጣም [ለ]የተደሰትኩባትን የእዚህችን [ሐ]ቤተክርስቲያን መሰረት የመጣል፣ እና [መ]ከጭለማ እና ከተደበቀችበት የማውጣት [ሠ]ኃይል ይኖራቸው ዘንድ ነው። እነዚህን ነገሮች ለቤትክርስቲያኗ ስናገር በጋራ እንጂ በተናጠል አይደለም—

፴፩ እኔ ጌታ [ሀ]ኃጢአትን በዝቅተኛ ደረጃ መመልከት አይቻለኝምና፤

፴፪ ሆኖም፣ ንስሀ የሚገባ እና የጌታን ትእዛዛት የሚጠብቅ [ሀ]ይቅርታን ይቀበላል፤

፴፫ እናም [ሀ]ንስሀ የማይገባ፣ የተቀበለውም ብርሀን ቢሆን እንኳን ከእርሱ [ለ]ይወሰድበታል፤ [ሐ]መንፈሴም ከሰው ጋር ዘወትር [መ]አይሆንምና፣ ይላል የሰራዊት ጌታ።

፴፬ እናም ደግሞ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አቤቱ የምድር ነዋሪዎች ሆይ፥ እኔ ጌታ እነዚህን ነገሮች ለስጋ ለባሽ [ሀ]ሁሉ ለማሳወቅ ፍቃደኛ ነኝ፤

፴፭ እኔም ለሰዎች [ሀ]አላደላም፣ እናም [ለ]ቀኑ በፍጥነት እንደመጣ ሁሉም ሰው ያውቀው ዘንድ ፍቃዴ ነው፤ [ሐ]ሰላም ከምድር የሚወሰድበት፣ እና [መ]ዲያብሎስም በግዛቱም ላይ ኃይል የሚያገኝበት ሰዓት አልደረሰም ነገር ግን ተቃርቧል።

፴፮ እናም ደግሞ ጌታ [ሀ]በቅዱሳኑ ላይ ኃይል ይኖረዋል፣ እናም [ለ]በመካከላቸውም [ሐ]ይነግሳል እናም [መ]በኢዱሜአ ወይም በአለም ላይ [ሠ]በፍርድ ይወርዳል።

፳፫ሐ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፳፬ሀ ፪ ኔፊ ፴፫፥፲–፲፩፤ ሞሮኒ ፲፥፳፯–፳፰።
ለ ፪ ኔፊ ፴፩፥፫፤ ኤተር ፲፪፥፴፱።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፥፲፪። ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፳፮ሀ ያዕ. ፩፥፭፤ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፰። ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፳፯ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፳፰ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀት።
፳፱ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
፴ሀ ኤፌ. ፬፥፭፤ ፲፩–፲፬። ቅ.መ.መ. የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ምልክቶች።
ለ ት. እና ቃ. ፴፰፥፲።
ሐ ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፤ የወንጌል ዳግም መመለስ።
መ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ሠ ት. እና ቃ. ፩፥፬–፮፤ ፲፯–፲፰።
፴፩ሀ አልማ ፵፭፥፲፮፤ ት. እና ቃ. ፳፬፥፪። ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
፴፪ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፵፪–፵፫። ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፴፫ሀ ሞዛያ ፳፮፥፴፪።
ለ አልማ ፳፬፥፴፤ ት. እና ቃ. ፷፥፪–፫።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
መ ዘፍጥ. ፮፥፫፤ ፪ ኔፊ ፳፮፥፲፩፤ ሞር. ፭፥፲፮፤ ኤተር ፪፥፲፭፤ ሞሮኒ ፱፥፬።
፴፬ሀ ማቴ. ፳፰፥፲፱፤ ት. እና ቃ. ፩፥፪፤ ፵፪፥፶፰።
፴፭ሀ ዘዳግ. ፲፥፲፯፤ የሐዋ. ፲፥፴፬፤ ሞሮኒ ፰፥፲፪፤ ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፮።
ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፯፥፩–፮። ቅ.መ.መ. ሰላም፤ የጊዜዎች ምልክቶች።
መ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፴፮ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ለ ዘካ. ፪፥፲–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፩፤ ፹፬፥፻፲፰–፻፲፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት።
መ ቅ.መ.መ. አለም።
ሠ ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።

፴፯ እነዚህን [ሀ]ትእዛዛት መርምሩ፣ የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና፣ እናም በውስጣቸው ያሉት ትንቢቶች እና [ለ]የተስፋ ቃላት ሁሉ ይፈጸማሉ።

፴፰ እኔ ጌታ የተናገርኩትን፣ ተናግሬያለሁ፣ እናም አላመካኝም፤ ሰማያትና ምድር ቢያልፉም [ሀ]ቃሌ ግን አያልፍም፣ ነገር ግን ሁሉም [ለ]ይፈጸማል፣ በእኔ [ሐ]ድምጽ ሆነ [መ]በአገልጋዮቼ ድምጽ፣ ያም [ሠ]አንድ ነው።

፴፱ ስለሆነም፣ እናም አስተውሉ፣ ጌታ አምላክ ነው፣ [ሀ]መንፈስም ይመሰክራል፣ እናም ምስክርነቱም እውነት ነው፣ እናም [ለ]እውነት ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ይኖራል። አሜን።

ክፍል ፪

በመስከረም ፳፩፣ ፲፰፻፳፫ (እ.አ.አ.) ምሽት በማንችስተር፣ ኒው ዮርክ በነቢዩ አባት ቤት ውስጥ ከመልአኩ ሞሮኒ ለጆሴፍ ስሚዝ ከተሰጡ ቃላት ከጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ውስጥ የተውጣጣ ምንባብ። በአሁኑ ወቅት መፅሐፈ ሞርሞን በመባል በአለም ፊት ያለውን ጽሁፍ ከጻፉት ረጅም የታሪክ ጸሀፊያን ሀረግ ሞሮናይ የመጨረሻው ነበር (ሚልኪያስ ፬፥፭–፮፤ እንዲሁም ክፍሎች ፳፯፥፱፤ ፻፲፥፲፫–፲፮፤ እና ፻፳፰፥፲፯ን አነጻጽሩ።)

፩፣ ኤሊያስ ክህነትን ይገልጣል፤ ፪–፫፣ የአባቶች የተስፋ ቃል በልጆች ልብ ይተካላል።

፩ እነሆ [ሀ]ታላቁና የሚያስፈራው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት በነቢዩ [ለ]ኤሊያስ እጅ ክህነትን እገልጥላችኋለው።

፪ እናም ለአባቶች የተገባውን [ሀ]የተስፋ ቃል በልጆች ልብ [ለ]ይተክላል፣ እናም የልጆቹም ልብ ወደ አባቶቻቸው ይመለሳል።

፫ እንዲህ ባይሆን ኖሮ፣ መላው ምድር በምጽአቱ በጠፋ ነበር።

ክፍል ፫

ሐምሌ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ ፔንስልቬንያ ውስጥ መፅሐፈ ሌሒ ተብሎ ይጠራ የነበረውን የተተረጎመበት ፻፲፮ የመፅሐፈ ሞርሞን ገጾች የመጀመሪያ ክፍል መጥፋት በተመለከተ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩ በቸልተኛነት እነዚህን ገጾች ለጥቂት ጊዜ የመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ጸሐፊ በመሆን ያገለግል

፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ ት. እና ቃ. ፶፰፥፴፩፤ ፷፪፥፯፤ ፹፪፥፲።
፴፰ ሀ ፪ ነገሥ. ፲፥፲፤ ማቴ. ፭፥፲፰፤ ፳፬፥፴፭፤ ፪ ኔፊ ፱፥፲፮፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፭።
ለ ት. እና ቃ. ፻፩፥፳፬።
ሐ ዘዳግ. ፲፰፥፲፰፤ ት. እና ቃ. ፲፰፥፴፫–፴፰፤ ፳፩፥፭።
ቅ.መ.መ. ራዕይ፤ ድምፅ።
መ ቅ.መ.መ. ነቢይ።
ሠ ቅ.መ.መ. ስልጣን፤ የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ።
፴፱ ሀ ፩ ዮሐ. ፭፥፯፤ ት. እና ቃ. ፳፥፳፯፤ ፵፪፥፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. እውነት።
፪ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፴፬፥፮–፱፤ ፵፫፥፲፯–፳፮።
ለ ሚል. ፬፥፭–፮፤ ፫ ኔፊ ፳፭፥፭–፮፤ ት. እና ቃ. ፻፲፥፲፫–፲፭፤ ፻፳፰፥፲፯፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፰–፴፱። ቅ.መ.መ. ኤልያስ፤ የክህነት ቁልፎች።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት፤ ማተም፣ ማስተሳሰር።
ለ ት. እና ቃ. ፳፯፥፱፤ ፺፰፥፲፮–፲፯።

ለነበረው ማርቲን ሀሪስ አሳልፎ ሰጠ። ራዕዩ በኡሪምና ቱሚም አማካይነት የተሰጠ ነው። (ክፍል ፲ን ተመልክቱ።)

፩–፬፣ የጌታ ጎዳና አንድ እና ዘለአለማዊ ዙሪያ ነው፤ ፭–፲፭፣ ጆሴፍ ስሚዝ ንስሀ መግባት ወይም የመተርጎም ስጦታውን ማጣት አለበት፤ ፲፮–፳፣ መፅሐፈ ሞርሞን የሌሒ ዘሮችን ለማዳን ይመጣል።

፩ የእግዚአብሔር [ሀ]ስራ፤ ጥበብ፤ እና ዓላማ ሊከሸፍም ሆነ ከንቱ ሊሆን አይችልም።

፪ [ሀ]እግዚአብሔር በተጣመመ መንገድ አይጓዝም፣ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ አይዞርም፣ የተናገረውንም አይለውጥም፣ ስለዚህ መንገዱ ቀጥተኛ ነው፣ [ለ]ጎዳናውም አንድ እና ዘለአለማዊ ዙሪያ ነው።

፫ አስታውሱ፣ አስታውሱ የሚሰናከለው የሰው ስራ እንጂ የእግዚአብሔር [ሀ]ስራ አይደለም፤

፬ ሰው ብዙ ራዕይ ቢቀበል፣ እናም ብዙ ታላላቅ ነገሮችን ለመስራት ሀይል ቢኖረውም፣ ነገር ግን በራሱ ጥንካሬ [ሀ]ቢታበይ፣ የእግዚአብሔርን [ለ]ምክር ከንቱ ቢያደርግ እናም [ሐ]በስጋው እና በራሱ ፈቃድ ቢመራ፣ ውድቀትንና የእግዚአብሔርን [መ]በቀል በራሱ ላይ ማምጣት አለበት።

፭ እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች ተሰጥተውሀል፣ ነገር ግን የተሰጡህ ትእዛዛቶች እንዴት የጠበቁ ነበሩ፤ እናም ካልተላለፍካቸው፣ ለአንተ የተገባልህን የተስፋ ቃላት እንዲሁ አስታውስ።

፮ እናም እነሆ፣ ምን ያህል ጊዜ የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ህግጋት [ሀ]ተላልፈሀል፤ እናም በሰዎችም [ለ]ሀሳብ ምን ያህል ሄደሀል።

፯ ስለሆነም እነሆ ሰውን ከእግዚአብሔር አስበልጠህ [ሀ]ፍርሀት አልነበረብህም። ምንም እንኳን ሰዎች የእግዚአብሔርን ምክር ከንቱ ቢያደርጉም እናም ቃሉንም [ለ]ቢንቁ—

፰ ነገር ግን ታማኝ መሆን ነበረብህ፤ እናም እጁን ዘርግቶ [ሀ]ከጠላትም ክፉ [ለ]ፍላፃ ይደግፍህ ነበር፤ እናም [ሐ]በመከራህ ጊዜ ሁሉ ከአንተ ጋር ይገኝ በነበር።

፱ እነሆ አንተ ጆሴፍ ነህ፣ እናም የጌታን ስራ እንድትሰራ ተመርጠሀል፣ ነገር ግን በመተላለፍህ ምክንያት ካልተጠነቀቅህ ትወድቃለህ።

፲ ነገር ግን አስታውስ፤ እግዚአብሔር መሀሪ ነው፤ ከሰጠሁህ ትእዛዛት ተጻራሪ የሆነውን ለሰራህበት ንስሐ ግባ፣ እናም አሁን የተመረጥህ ነህ፣ እናም ለስራው ዳግም ተጠርተሀል፤

፲፩ ይህን ካላደረግህ በቀር፣ ትተዋለህ እናም እንደሌሎችም ሰዎች ትሆናለህ፣ እና ስጦታም አይኖርህም።

፲፪ እናም እግዚአብሔር የሰጥህን [ሀ]የመተርጎም መንፈሣዊ ብርሀንና ሀይል አሳልፈህ በሰጠህ ጊዜ፣ የተቀደሰውን ነገር በኃጢአተኛ [ለ]ሰው እጅ ውስጥ እንዲገባ አሳልፈህ ሰጥተሀል፣

፫ ፩ [ሀ] መዝ. ፰፥፫–፱፤
ት. እና ቃ. ፲፥፵፫።
፪ [ሀ] አልማ ፯፥፳።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
[ለ] ፩ ኔፊ ፲፥፲፰–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፴፭፥፩።
፫ [ሀ] የሐዋ. ፭፥፴፰–፴፱፤
ሞር. ፰፥፳፪፤
ት. እና ቃ. ፲፥፵፫።
፬ [ሀ] ት. እና ቃ. ፹፬፥፸፫።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
[ለ] ያዕቆ. ፬፥፲፤
አልማ ፴፯፥፴፯።
ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)፤
የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
[ሐ] ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
[መ] ቅ.መ.መ. በቀል።
፮ [ሀ] ት. እና ቃ. ፭፥፳፩፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፳፰–፳፱።
[ለ] ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፱፤
፵፮፥፯።
፯ [ሀ] መዝ. ፳፯፥፩፤
ሉቃ. ፱፥፳፮፤
ት. እና ቃ. ፻፳፪፥፱።
ቅ.መ.መ. መበርታት፣
ብርቱነት፤
ፍርሀት።
[ለ] ዘሌዋ. ፳፮፥፵፪–፵፫፤
፩ ኔፊ ፲፱፥፯፤
ያዕቆ. ፬፥፰–፲።
፰ [ሀ] ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
[ለ] ኤፌ. ፮፥፲፮፤
፩ ኔፊ ፲፭፥፳፬፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፯።
[ሐ] አልማ ፴፰፥፭።
፲፪ [ሀ] ት. እና ቃ. ፩፥፳፱፤ ፭፥፬።
[ለ] ት. እና ቃ. ፲፥፮–፰።

፲፫ የእግዚአብሔርንም ምክር ከንቱ ላደረገ ሰው፣ እና በእግዚአብሔር ፊት የተደረገውን በጣም የተቀደሱ ቃል ኪዳኖችን ላፈረሰና፣ በራሱ ፍርድ ላይ ለሚመካና በራሱም ጥበብ [ሀ]ለሚታበይ ሰው አሳልፈህ ሰጥተሀል።

፲፬ እናም በዚህ መክንያት ነው ለጊዜው ስጦታህን ያጣኸው—

፲፭ ምክንያቱም [ሀ]የመሪህን ምክር ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዲረገጥ አድርገኃልና።

፲፮ ሆኖም፣ ስራዬ ወደፊት ይቀጥላል፣ [ሀ]የአዳኝ እውቀት ወደ አለም በአይሁዶች [ለ]ምስክርነት እንደመጣ እንዲሁ፣ የአዳኝ [ሐ]እውቀት ወደ ህዝቤ ይመጣል—

፲፯ እንዲሁም [ሀ]ለኔፋውያን፣ እናም ለያዕቆባውያን እናም ለዮሴፋውያን እናም ለዞራማውያን በአባቶቻቸው ምስክርነት ይመጣል—

፲፰ እናም ይህ [ሀ]ምስክርነት በአባቶቻቸው ክፋት ምክንያት እምነት በማጣት [ለ]ወደ መነመኑት፣ ጌታ ወንድሞቻቸው ኔፋውያንን፣ በኃጢአታቸው እና በእርኩስነታቸው የተነሳ፣ [ሐ]እንዲጠፉ ወዳደረጋቸው፣ ወደ [መ]ላማናውያን እና ልሙኤላውያን እና እስማኤላውያን እውቀት ይመጣል።

፲፱ በዚህ [ሀ]ዓላማ ምክንያት ነው ጽሁፎቹን የያዘው ይህ [ለ]ሰሌዳ የተጠበቀው—ጌታ ለህዝቦቹ የገባው [ሐ]የተስፋ ቃል ይፈጸም ዘንድ፤

፳ እናም [ሀ]ላማናውያን ወደ አባቶቻቸው እውቀት ይመጡ ዘንድ፣ እናም የጌታን የተስፋ ቃል ያውቁ ዘንድ፣ እናም ወንጌልንም [ለ]ያምኑ ዘንድ፣ እናም በኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ስራ [ሐ]ይመኩ ዘንድ፣ እናም በእምነት በስሙ [መ]ይከብሩ ዘንድ፣ እናም በንሰሀቸው ይድኑ ዘንድ ነው ሰሌዳው የተጠበቀው። አሜን።

ክፍል ፬

የካቲት ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ ፔንስልቬንያ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለአባቱ ለጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ የተሰጠ ራዕይ።

፩–፬፣ የጌታን አገልጋዮች የጀግና አገልግሎት ያድናቸዋል፤ ፭–፮፣ አምላካዊ ባህሪያት ላገልግሎቱ ብቁ ያደርጋቸዋል፤ ፯፣ የእግዚአብሔር ነገሮች መሻት አለባቸው።

፩ አሁን እነሆ፣ በሰዎች ልጆች መካከል [ሀ]ድንቅ ስራ ሊመጣ ነው።

፪ ስለዚህ እናንት በእግዚአብሔር [ሀ]አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ የጀመራችሁ፤ በመጨረሻው ቀን በእግዚአብሔር ፊት [ለ]ያለ ወቀሳ ትቆሙ ዘንድ፣ በሙሉ [ሐ]ልባችሁ፤ ኃይላችሁ፣ አዕምሮአችሁ እና ጉልበታችሁ [መ]እንደምታገለግሉት አረጋግጡ።

፫ ስለዚህ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል

፲፫ሀ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፭ሀ ይህም ጌታ ማለት ነው።
፲፮ሀ ቅ.መ.መ. አዳኝ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፳፫–፳፭፤
፪ ኔፊ ፳፱፥፬–፮።
ሐ ሞዛያ ፫፥፳።
፲፯ሀ ፪ ኔፊ ፭፥፳–፱።
፲፰ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ለ ፪ ኔፊ ፳፮፥፲፭–፲፮።
ሐ ሞር. ፳፥፪–፫።
መ ፪ ኔፊ ፭፥፲፬፤
ኢኖስ ፩፥፲፫–፲፳።
፲፱ሀ ፩ ኔፊ ፱፥፫፤ ፭።
ለ ቅ.መ.መ. የወርቅ ሰሌዳዎች።
ሐ ፫ ኔፊ ፭፥፲፬–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፲፥፵፮–፶።
፳ሀ ፪ ኔፊ ፴፥፫–፮፤
ት. እና ቃ. ፳፰፥፳፤
፵፱፥፳፬።
ለ ሞር. ፫፥፲፱–፳፩።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፱፤
ሞሮኒ ፮፥፬።
መ ሞሮኒ ፯፥፳፮፤ ፴፳።
፬ ፩ሀ ኢሳ. ፳፱፥፲፬፤
፩ ኔፊ ፲፬፥፯፤ ፳፪፥፰፤
ት. እና ቃ. ፮፥፩፤ ፲፰፥፵፬።
ቅ.መ.መ. የወንጌል
ዳግም መመለስ።
፪ሀ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
ለ ፩ ቆሮ. ፩፥፰፤
ያዕቆ. ፩፥፲፱፤
፫ ኔፊ ፳፯፥፳።
ሐ ቅ.መ.መ. ልብ፤
አዕምሮ።
መ ኢያ. ፳፪፥፭፤
፩ ሳሙ. ፯፥፫፤
ት. እና ቃ. ፳፥፲፱፤ ፸፮፥፭።

ፈቃድ ካላችሁ ወደስራው [ሀ]ተጠርታችኋል፤

፬ ስለሆነም እነሆ [ሀ]እርሻው ነጭ ቷል [ለ]አዝመራውም ዝግጁ ነው፤ እናም አስተውሉ፣ በጥንካሬው የሚያጭድ እንዳይጠፋ ዘንድ [ሐ]በጎተራው ይከምራል፣ ነገር ግን ለነፍሱ ደህንነትን ያመጣል፤

፭ እናም [ሀ]እምነት፣ [ለ]ተስፋ፣ [ሐ]ለጋስነትና [መ]ፍቅር፣ ሙሉ [ሠ]አይኑን ወደ እግዚአብሔር [ረ]ክብር ከማድረግ ጋር ለስራ ብቁ ያደርጉታል።

፮ እምነት፣ [ሀ]ምግባረ በጎነት፣ ዕውቀት፣ ራስን መግዛት፣ [ለ]ትዕግስት፣ ወንድማዊ ደግነት፣ አምላካዊነት፣ ልግስና፣ [ሐ]ትህትና፣ [መ]ትጋትን አስታውሱ።

፯ [ሀ]ለምኑ፣ እናም ይሰጣችኋል፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችኋል። አሜን።

ክፍል ፭

መጋቢት ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ በማርቲን ሀሪስ ጥያቄ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ።

፩–፲፣ ይህ ትውልድ የጌታን ቃል በጆሴፍ ስሚዝ በኩል ይቀበላል፤ ፲፩–፲፰፣ ሶስቱ ምስክሮች ስለ መፅሐፈ ሞርሞን ይመሰክራሉ፤ ፲፱–፳፣ እንደ ቀድሞው ጊዜ የጌታ ቃል ይረጋገጣል፤ ፳፩–፴፭፣ ማርቲን ሀሪስ ንስሀ ይግባና ከምስክሮቹ አንዱ ይሁን።

፩ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ አንተ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ምስክርነትህን የሰጠህባቸውን [ሀ]ስሌዳዎችን ከእኔ እንደተቀበልህ አገልጋዬ [ለ]ማርቲን ሀሪስ ከእኔ ምስክርነትን ፈልጓል፤

፪ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ለእርሱም እንዲህ ትለዋለህ—ለአንተ የተናገረህ፣ እንዲህ ብሎሀል፥ እኔ ጌታ አምላክ ነኝ፣ እናም እነዚህን ነገሮች ለአንተ፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ሰጥቻለሁ፣ እናም ለእነዚህም ነገሮች [ሀ]ምስክር ሆነህ እንድትቆም አዝዤሀለሁ፤

፫ እናም እኔ ላዘዝኩህ [ሀ]ሰዎች ካልሆነ በስተቀር እንዳታሳያቸው ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን እንድትገባ አድርጌሀለሁ፤ በእነርሱም ላይ እኔ ካልሰጠሁህ በስተቀር ምንም አይነት [ለ]ስልጣን የለህም።

፬ እናም ስሌዳዎቹን የመተርጎም ስጦታ አለህ፤ እናም ይህም በአንተ ላይ ካደረኩት የመጀመሪያው ስጦታ ነው፤ በዚህ አላማዬ እስኪሟላ ድረስ ሌላ ስጦታ እንዳለው እንዳታስመስል አዝዤሀለሁ፤ ይህም እስኪያልቅ ድረስ ሌላ ምንም ስጦታ አልሰጥህምና።

፭ እውነት፣ እልሀለው፣ ቃላቴን [ሀ]የማያ

፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፩፥፬፣ ፲፭፤
ፙ፮፥፭፤ ፷፫፥፶፯።
ቅ.መ.መ. ጥሪ፣
በእግዚአብሔር መጠራት፣
የተጠራበት።
፬ ሀ ዮሐ. ፬፥ፙ፭፤
አልማ ፳፮፥፫–፭፤
ት. እና ቃ. ፲፩፥፫፤
ፙ፫፥፫፣ ፯።
ለ ቅ.መ.መ. መከር።
ሐ ፩ ጢሞ. ፭፥፲፰።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ሐ ቅ.መ.መ. ልግስና።
መ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ሠ መዝ. ፻፵፩፥፰፤
ማቴ. ፮፥፳፪፤ ሞር. ፰፥፲፭።
ረ ቅ.መ.መ. ክብር።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. በጎነት።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ሐ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
መ ቅ.መ.መ. ትጋት።
፯ ሀ ማቴ. ፯፥፯–፰፤ ፪ ኔፊ ፴፪፥፬።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፭ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. የወርቅ ስሌዳዎች።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥፳፫–፳፬፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፳፩።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክር።
፫ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲፫። ደግሞም
“የሶስቱ ምስክሮች
ምስክርነት”ን እና
“የስምንቱ ምስክሮች
ምስክርነት”ን በመፅሐፈ
ሞርሞን የመጀመሪያ ገጾች
ውስጥ እመልከቱ።
ለ ፪ ኔፊ ፫፥፲፩።
፭ ሀ ኤር. ፳፮፥፬–፭፤
አልማ ፭፥ፙ፯–ፙ፰፤
ት. እና ቃ. ፩፥፲፬።

ደምጡ ከሆነ በምድር ነዋሪዎች ላይ ዋይታ ይመጣል፤

፮ ስለዚህ ከአሁን በኋላ [ሀ]ትሾማለህና ሂድ እናም [ለ]ቃሌን ለሰዎች ልጆች አድርስ።

፯ እነሆ፤ ቃላቴን [ሀ]የማያምኑ ከሆን፤ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ የሚቻል ሆኖ ለአንተ የሰጠሁትን ነገሮች ሁሉ ብታሳያቸውም፣ አንተን አያምኑህም።

፰ አቤቱ፣ ይህ [ሀ]የማያምን [ለ]አንገተ ደንዳና ትውልድ—ቁጣዬ በእነርሱ ላይ ተቀጣጥሏል።

፱ እነሆ፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ ለአንተ በአደራ የሰጠሁህን እነዚህን ነገሮች [ሀ]የጠበኩት በጥበብ አላማዬ ምክንያት ነው፣ እና ይህም ወደፊት ለሚመጡት ትውልዶች እንዲታወቅ ይደረጋል፤

፲ ነገር ግን ይህ ትውልድ በአንተ አማካይነት ቃሌን ያገኛል፤

፲፩ እናም ከአንተ ምስክርነት በተጨማሪ ጠርቼም የምሾማቸው፣ እነዚህንም ነገሮች የማሳያቸው የሶስቱ አገልጋዬቼ [ሀ]ምስክርነት እናም በአንተ አማካይነት የተሰጡትን ቃሎቼን ይዘው ወደፊት ይጓዛሉ።

፲፪ አዎን፣ እነዚህ ነገሮች በእርግጥም እውነት እንደሆኑ ያውቃሉ፣ ምክንያቱም ከሰማይ እኔ አውጅላቸዋለሁና።

፲፫ እነዚህን ነገሮች እንዳሉ እና ማየት ይችሉ ዘንድ ሀይልን እሰጣቸዋለሁ፤

፲፬ እናም [ሀ]እንደጨረቃ የጠራች፣ እንደ ጸሀይ መልከ መልካም፣ ሰንደቅ ዓርማን እንዳነገበ ወታደር የምታስፈራው [ለ]ቤተ ክርስቲያኔ ከምድረበዳ በምትነሳበት እና መምጣት በምትጀምርበት ጊዜ፣ ይህን አይነት ምስክርነት፣ ይህን ሀይል፣ በዚህ ትውልድ መካከል እንዲቀበል ለሌላ [ሐ]ለማንም አልሰጥም።

፲፭ እናም ስለቃሌ የሶስቱን [ሀ]ምስክሮችን ምስክርነት እልካለሁ።

፲፮ እናም እነሆ፣ ቃሌን [ሀ]የሚያምኑ ሁሉ [ለ]በመንፈሴ [ሐ]መገለጥ [መ]እጎበኛቸዋለሁ፤ እናም ከእኔ፣ እንዲሁም ከውሀ እና ከመንፈስ [ሠ]ይወለዳሉ—

፲፯ እናም ገና [ሀ]ስላልተሾማችሁ ለትንሽ ጊዜ መቆየት አለባችሁ—

፲፰ እናም በእነርሱ ላይ ልባቸውን ካደነደኑ ምስክርነታቸውም ይህንን ትውልድ [ሀ]ይኮንን ዘንድ ይሄዳል፤

፲፱ በምድር ነዋሪዎች መካከል [ሀ]ጥፋትና መከራ ይመጣል፣ [ለ]ንስሀ ካልገቡም ምድር [ሐ]ባዶ እስክትሆን ድረስ ከጊዜ ወደ ጊዜ መውረዱ ይቀጥላል፣ እንዲሁም የምድር ነዋሪዎች [መ]በምፅዓቴም ብርሀን ይበላሉ እናም ፈጽሞ ይጠፋሉ።

፳ እነሆ፣ በኢየሩሳሌም መጥፊያ ጊዜ [ሀ]እንደነገርኳቸው ህዝብ፣ እነዚህን ነገሮች እነግርሀለሁ፤ በዚያም ጊዜ [ለ]ቃሌ እንደ ተረጋገጠ ሁሉ በዚህም ጊዜ ይረጋገጣል።

፳፩ እናም አሁን አገልጋዬ ጆሴፍ በፊቴ

፮ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፪–፫።
ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፱፥፯።
፯ ሀ ሉቃ. ፲፮፥፳፯–፴፩፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥፯–፲፪።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።
ለ ሞር. ፰፥፴፫።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
፱ ሀ አልማ ፴፯፥፲፰።
፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲፪፤
ኤተር ፭፥፫–፬፤
ት. እና ቃ. ፲፯፥፩–፭።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፴፫፥፭፤
፻፱፥፸፫።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተክርስቲያን፤
የወንጌል ዳግም መመለስ።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲፫።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፲፯።
ቅ.መ.መ. የመፅሐፈ
ሞርሞን ምስክሮች።
፲፮ ሀ ኤተር ፬፥፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ት. እና ቃ. ፰፥፩–፫።
መ ፩ ኔፊ ፪፥፲፮።
ሠ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ
ስጦታ፤
ዳግመኛ መወለድን፣
ከእግዚአብሔር መወለድ፤
ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት፤
ስልጣን።
፲፰ ሀ ፩ ኔፊ ፲፬፥፯፤
ት. እና ቃ. ፳፥፲፫–፲፭።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፰፤
፴፭፥፲፩፤ ፵፫፥፲፯–፳፯።
ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣
የኋለኛው ቀናት፤
የጊዜዎች ምልክቶች።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ሐ ኢሳ. ፳፬፥፩፣ ፭–፮።
መ ኢሳ. ፷፮፥፲፭–፲፮፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፶፩።
ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፳ ሀ ፩ ኔፊ ፩፥፲፰፤
፪ ኔፊ ፳፭፥፱።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፴፰።

በቅንነት እንድትራመድ፣ ንሰሀ እንድት ግባ፣ እናም ከዚህ በኋላ በሰዎች ሀሳብ እን ዳትወሰድ አዝህለሁ፤

፳፪ እናም ያዘዝኩህ ትእዛዛት [ሀ]በመጠበቅ ጠንካራ እንድትሆን አዝህለሁ፤ እናም ይህ ንን ካላደረግህ [ለ]ብትገደልም እንኳን ዘለአ ለማዊ ህይወትን እሰጥሀለሁ።

፳፫ እናም አሁን፣ ዳግም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ ምስክርነትን ስለሚፈልገው [ሀ]ሰው እናገርሀለሁ—

፳፬ እነሆ እንዲህ እለዋለሁ፣ ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል እና እራሱን በብቃት በፊቴ ዝቅ አያደርግም፤ ነገር ግን እራሱን በታላቅ ጸሎት እና እምነት ከልብ በሆነ ፈቃድ ዝቅ የሚያደርግ ከሆነ ማየት የሚሻውን ነገሮች [ሀ]እይታ አሰጠዋለሁ።

፳፭ እናም ለዚህ ትውልድ እንዲህ ይላል፥ እነሆ ጌታ ለጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ያሳ የውን ነገሮች አይቻለሁ እናም በእርግጥም እውነት እንደሆኑ [ሀ]አውቃለሁ፣ ምክንያ ቱም ተመልክቻቸዋለሁና፣ በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ሀይል አይቻቸዋለሁና።

፳፮ እናም እኔ ጌታ አገልጋዬን ማርቲን ሀሪስን እነዚህን ነገሮች በተመለከተ ተመ ልክቻቸዋለሁ፣ በእግዚሐብሔር ሀይል አይቻቸዋለሁ ከማለት በስተቀር ምንም ተጨማሪ ነገር እንዳይነግራቸው አዝዘዋ ለሁ፤ እናም የሚናገራቸው ቃላት እነዚ ህን ናቸው።

፳፯ ነገር ግን ይህን ከካደ ቀደም ብሎ ከእኔ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያፈርሳል እናም እነሆ፣ ይኮነናል።

፳፰ እናም እራሱን ዝቅ አድርጎ እናም የሰ ራውን ስህተት ካልተቀበለ እና ትእዛዛቴን ለመጠበቅ ከእኔ ጋር ቃል ካልገባ፣ እና በእኔ ካላመነ በስተቀር፣ እነሆ፣ እንዲህ እለዋለሁ ምንም አይነት እይታ አይኖረውም፣ የተና ገርኳቸውን ነገሮች እይታ አልሰጠውምና።

፳፱ እናም ነገሩ ይህ ከሆነ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ካሁን በኋላ ምንም ነገር እንደማይ ሰራ እንዲሁም ስለዚህም ነገር ካሁን በኋላ እንዳያታክተኝ እንድትነግረው አዝህለሁ።

፴ ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ እነሆ እንዲህ እል ሀለሁ ጆሴፍ፣ ጥቂት ገጾችን ከተረጎምህ በኋላ፣ ዳግም ትተረጉም ዘንድ ዳግመኛ እስከማዝህ ድረስ ለጥቂት ጊዜ ታቆማለህ።

፴፩ እናም ይህንን ካላደረግህ በስተቀር፣ ምንም ስጦታ አይኖርህም እናም የሰጠሁ ህን ነገሮች እወስዳቸዋለሁ።

፴፪ እናም፣ ምክንያቱም አንተን ለማጥ ፋት የታለመውን ዕቅድ አስቀድሜ ማየት ስለምችል፣ አዎን አገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ ራሱን ዝቅ የማያደርግ ከሆነ እና ምስክር ነትን ከእጄ የማይቀበል ከሆነ ወደመተላ ለፍ እንደሚወድቅ አስቀድሜ አይቻለሁ፤

፴፫ እናም ሌሎች ብዙ አንተን ከምድር ላይ [ሀ]ለማጥፋት የሚያቅዱ አሉ፤ እናም በዚህ ምክንያት ቀኖችህ ይራዘሙ ዘንድ ለአንተ እነዚህን ትእዛዛት ሰጥቻለሁ።

፴፬ አዎን፣ በዚህ ምክንያት እንዲህ ብያ ለሁ፣ እስከማዝህ ድረስ አቁም እናም ባለህ በት ሁን፣ እናም ያዘዝኩሁን ነገሮችን የም ታከናውንበትን ሁኔታዎች [ሀ]አዘጋጃለሁ።

፴፭ እናም ትእዛዛቴን በመጠበቅ [ሀ]ታማኝ ከሆንህ፣ በመጨረሻው ቀን [ለ]ከፍ ትላለህ። አሜን።

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ አልማ ፷፥፲፫፤ ት. እና ቃ. ፮፥፴፤ ፻፴፭።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፩።
፳፬ ሀ "የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት"ን በመፅሐፈ ሞርሞን መጀመሪያ ገጾች ውስጥ ተመልከቱ።
፳፭ ሀ ኤተር ፭፥፫።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፥፮፤ ፴፰፥፲፫፣ ፳፰።
፴፬ ሀ ፩ ኔፊ ፫፥፯።
፴፭ ሀ ዘፀአ. ፲፭፥፳፮፤ ት. እና ቃ. ፲፩፥፳።
ለ ዮሐ. ፮፥፴፱–፵፤ ፩ ተሰ. ፬፥፲፯፤ ፫ ኔፊ ፲፭፥፩፤ ት. እና ቃ. ፱፥፲፬፤ ፲፯፥፰፤ ፸፭፥፲፮፣ ፳፪።

ክፍል ፮

ሚያዚያ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለኦሊቨር ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ። በሚያዚያ ፯፣ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) ኦሊቨር ካውድሪ የመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ጸሐፊ በመሆን ማገልገል ጀመረ። የመፅሐፈ ሞርሞን መዛግብት የተቀረጹበትን ሰሌዳዎች በተመለከተ ስለነቢዩ ምስክርነት እውነትነት ቀደም ብሎ መለኮታዊ መገለጥን ተቀብሎ ነበር። ነቢዩ በኡሪምና ቱሚም ጌታን ጠየቀ እናም ይህን መልስ ተቀበለ።

፩–፮፣ በጌታ የእርሻ ስፍራ የሚያገለግሉ ሰራተኞች ደህንነትን ያገኛሉ፤ ፯–፲፫፣ ከደህንነት ስጦታ የበለጠ ስጦታ የለም፤ ፲፬–፳፯፣ የእውነት ምስክርነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይመጣል፤ ፳፰–፴፯፣ ወደ ክርስቶስ ተመልከቱ እናም ሁልጊዜ መልካምን አድርጉ።

፩ ታላቅ እና [ሀ]ድንቅ ስራ ወደ ሰዎች ልጆች ሊመጣ ነው።

፪ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ፈጣን እና ሀያል፣ ሁለት ስለት ካለው ሰይፍ ይልቅ [ሀ]የተሳለ፣ መገጣጠሚያን እና መቅኔን እስኪለይ ድረስ የሚሰራውን [ለ]ቃሌን አድምጡ፤ ስለዚህ ቃሎቼን አድምጡ።

፫ እነሆ፣ [ሀ]የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ አዝመራው ዝግጁ ነው፣ ስለዚህ፣ ለነፍሱም ዘለአለማዊ ደህንነት በእግዚአብሔር መንግስት ያከማች ዘንድ መሰብሰብ የሚሻ በኃይሉ ይጨድ እናም ቀኑም እየመሸ ሳለም ይሰብስብ።

፬ አዎን፣ ማንኛውም [ሀ]የሚያጭድ እናም የሚሰበስብ፣ እንዲሁ በእግዚአብሔር የተጠራ ነው።

፭ ስለዚህ፣ እኔን [ሀ]ብትጠይቁኝ ትቀበላላችሁ፣ ካንኳኳችሁ ይከፈትላችኋል።

፮ አሁን፣ እንደጠየቃችሁት፣ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ትእዛዛቴን ጠብቁ እናም [ሀ]የፅዮንን አስተሳሰብ ለማምጣት እና ለመመስረት [ለ]እሹ፤

፯ [ሀ]ጥበብን እንጂ [ለ]ሀብትን [ሐ]አትሹ፣ እናም እነሆ፣ የእግዚአብሔር [መ]ሚስጥራት ይገለጡላችኋል፣ እናም ባለጠጋም ትሆናላችሁ። እነሆ፣ [ሠ]ዘለዓለማዊ ሕይወት ያለው እርሱም ባለጠጋ ነውና።

፰ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ ላደርግላችሁ እንደምትሹ እንዲሁ ይሆንላችኋል፤ የምትሹ ከሆነም ካላችሁ፣ በዚህ ትውልድ ውስጥ ለብዙ መልካም ነገሮች መከናወን መሳሪያ ትሆናላችሁ።

፱ ለዚህ ትውልድ [ሀ]ከንስሀ በቀር ሌላ ምንም አትናገሩ፤ ትእዛዛቴን ጠብቁ፣ እናም ስራዬን በትእዛዛቴ መሰረት ለማምጣት እርዱ፣ እናም ትባረካላችሁ።

፲ እነሆ ስጦታ አላችሁ፣ እናም በስጦታችሁም የተነስ የተባረካችሁ ናችሁ። [ሀ]ይህም የተቀደሰ እና ከላይ የመጣ መሆኑን አስታውሱ—

፮ ፩ ሀ ኢሳ. ፳፱፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፬፤ ፲፰፥፵፬።
፪ ሀ ሔለ. ፫፥፳፱፤
ት. እና ቃ. ፴፫፥፩።
ለ ዕብ. ፬፥፲፪፤
ራዕ. ፩፥፲፮፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥፩።
፫ ሀ ዮሐ. ፬፥፴፭፤
ት. እና ቃ. ፴፩፥፬፤
፴፫፥፫፤ ፻፩፥፷፬።
፬ ሀ ራዕ. ፲፬፥፲፭–፲፱፤
አልማ ፳፮፥፭፤
ት. እና ቃ. ፲፩፥፫–፬፤ ፳፯።
፭ ሀ ማቴ. ፯፥፯–፰።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፯።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ፩ ነገሥ. ፫፥፲–፲፫፤
ማቴ. ፲፱፥፳፫፤
ያዕቆ. ፪፥፲፰–፲፱።
ቅ.መ.መ. ሀብቶች፤
አለማዊነት።
ሐ አልማ ፴፱፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፷፰፥፴፩።
መ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፩፤ ፷፭።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ሠ ት. እና ቃ. ፲፬፥፯።
፱ ሀ አልማ ፳፱፥፱፤
ት. እና ቃ. ፲፭፥፮፤ ፲፰፥፲፬–፲፭፤ ፴፬፥፮።
ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፤
የሚስዮን ስራ።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፳፫፥፳፬።

፲፩ እናም [ሀ]ከጠየቅህ፣ ታላቅ እና ድንቅ የሆኑ [ለ]ሚስጥራትን ታውቃለህ፤ ስለዚህም ሚስጥራትን ታውቅ ዘንድ፣ ብዙዎችንም ወደ እውነት እውቀት ታመጣ ዘንድ፣ አዎን፣ የተሳሳተ መንገዳቸውን ሁሉ እንዲተው [ሐ]ታሳምናቸውም ዘንድ [መ]ስጦታህን ትጠቀምበታለህ።

፲፪ በአንተ እምነት ውስጥ ካልሆኑ በስተቀር ስጦታህን ለማንም አታሳውቅ። [ሀ]በተቀደሱ ነገሮች አትቀልድ።

፲፫ መልካምን ካላደረግህ፣ እናም እስከ [ሀ]መጨረሻም [ለ]በእምነት [ሐ]ከጸናህ ከእግዚአብሔር የስጦታዎች ሁሉ የበላይ በሆነው በእግዚአብሔር መንግስት ትድናለህ፤ [መ]ከደህንነት በላይ የሆነ ምንም ስጦታ የለም።

፲፬ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ባደረግኸው የተባረክህ ነህ፤ ምክንያቱም እኔን [ሀ]ጠይቀኃል እናም በጠየቅኸው መጠን የመንፈሴን መመሪያ ተቀብለኃል። ይህ ባይሆን ኖሮ አሁን ያለህበት ስፍራ ባልደረስህ ነበር።

፲፭ እነሆ፣ እንደጠየቅኸኝ ታውቃለህ እናም [ሀ]አዕምሮህን አብርቻለሁ፤ እናም አሁን በእውነት መንፈስ መረዳትን እንዳገኘህ ታውቅ ዘንድ እነዚህን ነገሮች እነግርሀለሁ፤

፲፮ አዎን፣ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም ሀሳብህንና [ሀ]የልብህን ፈቃድ እንደማያውቅ [ለ]እንድታውቅ ዘንድ እነግርሀለሁ።

፲፯ እየጻፍህ ያለው ቃላት ወይም ስራ [ሀ]እውነት እንደሆነ—ለአንተ እንደምስክርነት እነዚህን ነገሮች እነግርሀለሁ።

፲፰ ስለዚህ [ሀ]ትጉህ ሁን፤ በታማኝነት፣ ለቃሉ ሲል በሚገጥመው በማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ከአገልጋዬ ከጆሴፍ ጎን [ለ]ቁም።

፲፱ በስህተቱም ገስጸው፣ እናም ከእርሱም ተግሳጽን ተቀበል። ትዕግስተኛ ሁን፤ የተረጋጋህ ሁን፣ ራስህን ግዛ፣ ትዕግስት፣ እምነት፣ ተስፋ እና ልግስና ይኑርህ።

፳ እነሆ፣ አንተ ኦሊቨር ነህ፣ እናም በፈቃድህ ምክንያት ተናግሬሀለሁ፤ ስለዚህ እነዚህን ቃላት በልብህ [ሀ]አከማች። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ ታማኝ እና ትጉህ ሁን፣ እናም በፍቅሬ እቅፍ ውስጥም አደርግሀለሁ።

፳፩ እነሆ፣ እኔ [ሀ]የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ። [ለ]የእኔው ወደሆኑት የመጣሁት እናም የራሴም ያልተቀበሉኝ እኔው ነኝ። እኔ በጭለማም የማበራ [ሐ]ብርሀን ነኝ፣ እናም [መ]ጭለማውም አይገነዘበውም።

፳፪ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ተጨማሪ ምስክርነትን ከፈለግህ፣ ስለ እነዚህ ነገሮች [ሀ]እውነትነት ታውቅ ዘንድ በልብህ ወደ እኔ የጮህክበትን ምሽት አስታውስ።

፳፫ ይህንን ነገር በተመለከተ ለአእምሮህ [ሀ]ሰላምን አልተናገርኩምን? ከእግዚአብሔር ከመጣ ምስክርነት ይልቅ ምን አይነት [ለ]ምስክርነት ትፈልጋለህ?

፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥፳፫፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፲፰፣ ፳፮።
ለ ማቴ. ፲፩፥፳፭፤ ፲፫፥፲–፲፩፤
አልማ ፲፪፥፱።
ሐ ያዕ. ፭፥፳፤
አልማ ፳፪፥፵፭፤
ት. እና ቃ. ፲፰፥፵፬።
መ ቅ.መ.መ. ስጦታ፤
የመንፈስ ስጦታዎች።
፲፪ ሀ ማቴ. ፯፥፮።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መፅናት።
ለ ሞዛያ ፪፥፵፩፤
ኤተር ፬፥፲፱፤
ት. እና ቃ. ፶፩፥፲፱፤
፸፫፥፵፯።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፭፥፳፬።
መ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
፲፮ ሀ ፩ ነገሥ. ፰፥፴፱።
ለ ፩ ዜና ፳፰፥፱፤
ማቴ. ፲፪፥፳፭፤
ዕብ. ፬፥፲፪፤
ሞዛያ ፳፬፥፲፪፤
፫ ኔፊ ፳፰፥፮።
ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥፪።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፺፭–፺፮።
፳ ሀ ኤተር ፫፥፳፩፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፹፭።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ለ ዮሐ. ፩፥፲–፲፪፤
የሐዋ. ፫፥፲፫–፲፯፤
፫ ኔፊ ፱፥፲፮፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፰።
ሐ ዮሐ. ፩፥፭፤
ት. እና ቃ. ፲፥፶፰።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
መ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ለ ፩ ዮሐ. ፭፥፱፤
ት. እና ቃ. ፲፰፥፪።

፳፬ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ምስክርነትን ተቀብለሀል፤ ሌላ ሰው የማያውቃቸውን ነገሮች ነግሬህ ምስክርነትን አልተቀበልክምን?

፳፭ እናም፣ እነሆ፣ ከእኔም የምሻ ከሆነ ልክ እንደ አገልጋዬ ጆሴፍ [ሀ]ትተረጉም ዘንድ ስጦታን እሰጥሀለሁ።

፳፮ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ በሰዎች [ሀ]ኃጢአት የተነሳ ያስቀረኋቸው አብዛኛውን ወንጌሌን የያዙ [ለ]ጽሁፎች አሉ።

፳፯ እናም አሁን አዝሀለሁ፥ ለራስህ ሀብትን በሰማይ የማከማቸት ፈቃድ የሆነ መልካም ፈቃድ ካለህ፣ ከዚያም፣ በኃጢአት የተነሳ ተደብቀው የነበሩትን [ሀ]ቅዱሳን መጻህፍቴን በስጦታህ ወደ ብርሀን በማምጣት ትረዳለህ።

፳፰ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ለአንተ እና ለአገልጋዬ ለጆሴፍ ይህንን አገልግሎት ወደ ብርሀን የሚያመጣውን ስጦታ ቁልፍ እሰጣችኋለሁ፤ በሁለት ወይም በሶስት [ሀ]ምስክር አንደበት ሁሉም ቃል ይጸናል።

፳፱ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ቃሌን እና የዚህን የወንጌል ክፍል እናም አገልግሎቴን የማይቀበሉ ከሆኑ፣ የተባረካችሁ ናችሁ፣ ምክንያቱም በእኔ ላይ ካደረጉብኝ በላይ ሊያደርጉባችሁ አይችሉምና።

፴ እናም በእኔ ላይ እንዳደረጉት እንዲሁ በእናንተ ላይ [ሀ]ቢያደርጉም እንኳን፣ የተባረካችሁ ናችሁ፣ ከእኔም ጋር [ለ]በክብር [ሐ]ትኖራላችሁና።

፴፩ ነገር ግን በሚሰጠው [ሀ]ምስክርነት የሚጸናውን ቃሌን [ለ]ካልተቃወሙ፣ የተባረኩ ናቸው፣ እና ከዚያም በስራችሁ ፍሬ ትደሰታላችሁ።

፴፪ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ልክ ለደቀመዛሙርቴ እንደተናገርሁት፣ ሁለት ወይም ሶስት ሆነው በስሜ፣ አንድን ነገር በተመለከተ፣ [ሀ]በሚሰበሰቡበት፣ በዚያም [ለ]በመካከላቸው እሆናለሁ፣ እንዲሁም በመካከላችሁ ነኝ።

፴፫ ልጆቼ፣ መልካምን ለማድረግ [ሀ]አትፍሩ፣ [ለ]የዘራችሁትን ያንኑ መልሳችሁ ታጭዳላችሁ፤ ስለዚህ መልካምን ከዘራችሁ ያንኑ መልካም የሆነውን እንደ ደመወዝ ታጭዳላችሁ።

፴፬ ስለዚህ፣ አትፍሩ፣ እናንት ትንሽ መንጋዎች፣ መልካምን አድርጉ፤ ምድርና ገሀነም ቢቀናጁባችሁም፣ በእኔ [ሀ]ዐለት ላይ ከተገነባችሁ ሊቋቋሟችሁ አይችሉምና።

፴፭ እነሆ፣ አልኮንናችሁም፤ በመንገዳችሁ ሂዱ እናም ዳግምም [ሀ]ኃጢአትን አትስሩ፤ ያዘዝኳችሁን ስራ በርጋታ እከናውኑ።

፴፮ ባሰባችሁት ነገር ሁሉ ወደ እኔ [ሀ]ተመልከቱ፤ አትጠራጠሩ፣ አትፍሩ።

፴፯ ጎኔ ላይ የተወጋሁት ቁስል፣ እናም በእጄ እና በእግሬ ላይ ያሉትን [ሀ]የምስማር ምልክቶች [ለ]አስቧቸው፤ እናም እምነት ይኑራችሁ፣ ትእዛዛቴን ጠብቁ፣ እናም [ሐ]መንግስተ ሰማያትን [መ]ትወርሳላችሁ። አሜን።

፳፭ ሀ ሞዛያ ፰፥፲፫፤ ት. እና ቃ. ፭፥፬፤ ፱፥፩–፭፤ ፲።

፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፉት።

ለ ት. እና ቃ. ፰፥፩፤ ፱፥፪። ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—እንደሚመጡ የተተነበዩ ቅዱሣት መጻህፍት።

፳፯ ሀ ት. እና ቃ. ፴፭፥፳።

፳፰ ሀ ዘዳግ. ፲፱፥፲፭፤ ፪ ቆሮ. ፲፫፥፩፤ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲፪–፲፬፤ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፫።

፴ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፳፪፤ ፻፴፭። ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።

ለ ቅ.መ.መ. ክብር።

ሐ ራዕ. ፫፥፳፩።

፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።

ለ ፫ ኔፊ ፲፮፥፲–፲፬፤ ት. እና ቃ. ፳፥፰–፲፭።

፴፪ ሀ ማቴ. ፲፰፥፲፱–፳። ቅ.መ.መ. አንድነት።

ለ ት. እና ቃ. ፳፱፥፭፤ ፴፰፥፯።

፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. መበርታት፣ ብርቱነት።

ለ ገላ. ፮፥፯–፰፤ ሞዛያ ፯፥፴–፴፩፤ አልማ ፱፥፳፰፤ ት. እና ቃ. ፩፥፲።

፴፬ ሀ መዝ. ፸፩፥፫፤ ማቴ. ፯፥፳፬–፳፭፤ ፩ ቆሮ. ፲፥፬፤ ሔለ. ፭፥፲፪፤ ት. እና ቃ. ፲፥፷፱፤ ፲፰፥፬፡ ፲፯፤ ፴፫፥፲፫፤ ሙሴ ፯፥፶፫። ቅ.መ.መ. አለት።

፴፭ ሀ ዮሐ. ፰፥፫–፲፩።

፴፮ ሀ ኢሳ. ፵፭፥፳፪፤ ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፬።

፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. መስቀል።

ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ክርስቶስ ከሟችነት በኋላ መገለጡ።

ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።

መ ማቴ. ፭፥፫፡ ፲፤ ፫ ኔፊ ፲፪፥፫፡ ፲።

ክፍል ፯

ሚያዚያ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝና ኦሊቨር ካውድሪ በኡሪምና ቱሚም ተወዳጁ ደቀመዝሙር ዮሐንስ በስጋ መኖርና አለመኖርን በተመለከተ ለጠየቁት ጥያቄ የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ በዮሐንስ በብራና ላይ ተጽፎ በራሱ ተደብቆ ከነበረው ጽሁፍ ላይ የተተረጎመው ነው።

፩–፫፣ የተወደደው ዮሐንስ እስከ ጌታ ምፅዓት ድረስ ይኖራል፤ ፬–፰፣ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የወንጌልን ቁልፍ ይዘዋል።

፩ እናም ጌታ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ የምወድህ [ሀ]ዮሐንስ ሆይ፣ ምንን [ለ]ትሻለህ? የፈለግኸውን ብትጠይቅ እሱም ይሰጥኃል።

፪ እናም እኔም እንዲህ አልኩት፥ ጌታ እንድኖርና ነፍሳትን ወደ አንተ እንዳመጣ [ሀ]በሞት ላይ ስልጣንን ስጠኝ አልኩት።

፫ እናም ጌታም እንዲህ ይላልኝ፥ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ይህንን ስለፈለግህ እኔ [ሀ]በክብር እስክመጣ ድረስ [ለ]ትኖራለህ እናም በሀገሮች፣ በነገዶች፣ በቋንቋዎች፣ እና በህዝብም ፊት [ሐ]ትተነብያለህ።

፬ በዚህም ምክንያት ጌታ ጴጥሮስን እንዲህ ይላልው፥ እኔ እስክመጣ እንዲኖር ብፈቅድ ያ ለአንተ ምንድን ነው? እርሱ ወደ እኔ ነፍሳትን ለማምጣት ፈልጓል፣ ነገር ግን አንተ በቶሎ ወደ እኔ [ሀ]በመንግስቴ መምጣትን ፈልገሀል።

፭ ጴጥሮስምሆይ ለአንተ እንዲህ እልሀለሁ፣ ይህ መልካም ፈቃድ ነበር፤ ነገር ግን የምወደው እርሱ ተጨማሪ፣ ወይም ቀደም ብሎ ካደረገው የበለጠ ስራ በሰዎች መካከል ያደርግ ዘንድ ፈለገ።

፮ አዎን፣ ታላቅ የሆነን ስራ ወስዷል፤ ስለዚህ እንደነበልባል እሳት እና እንደ [ሀ]አገልጋይ መልአክ አደርገዋለሁ፤ እርሱም [ለ]በምድር ለሚኖሩ የደህንነት [ሐ]ወራሾችን ያገለግላል።

፯ እናም ለእርሱና ለወንድምህ ለያዕቆብ እንድታገለግል አደርግሀለሁ፤ እናም ለእናንተ ለሶስታችሁም እኔ እስክመጣ ድረስ ይህን ስልጣን እና የአገልግሎቱን [ሀ]ቁልፍ እሰጣችኋለሁ።

፰ እውነት እላችኋለሁ፣ ሁለታችሁም እንደመሻታችሁ ይሆንላችኋል፤ ሁለታችሁም በፈለጋችሁት ነገሮች [ሀ]ትደሰታላችሁና።

ክፍል ፰

ሚያዝያ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለኦሊቨር ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ። በመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ሂደት በጸሀፊነት በማገልገል የነቢዩን ቃል እየጻፈ የቀጠለው ኦሊቨር፣ የትርጉም ስጦታ እንዲሰጠው ፈለገ። ጌታም ይህን እራይ በመስጠት ለልመናው መልስ ሰጠው።

፯ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ዮሐንስ፣ የዘብዴዎስ ልጅ።
ለ ፫ ኔፊ ፳፰፥፩–፲።
፪ ሀ ሉቃ. ፱፥፳፯።
ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. ክብር፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ዮሐ. ፳፩፥፳–፳፫።
ቅ.መ.መ. የተቀየሩ ሰዎች።
ሐ ራዕ. ፲፥፲፩።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፥፭።
ለ ዮሐ. ፲፥፰–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፸፯፥፲፬።
ሐ ት. እና ቃ. ፸፮፥፹፮–፹፰።
፯ ሀ ማቴ. ፲፮፥፲፱፤
የሐዋ. ፲፭፥፯፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፸፪።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።

፩–፭፣ ራዕይ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እማካኝነት ይመጣል፤ ፮–፲፪፣ የእግዚአብሔር የሚሥጥራት እውቀት እና የጥንት መዛግብትን የመተርጎም ኃይል የሚመጣው በእምነት ነው።

፩ [ሀ]ኦሊቨር ካውድሪ፣ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ጌታ አምላክህንና ቤዛህ ህያው እንደሆነ፣ ጥንታዊ የሆኑትን በመንፈሴ [ለ]መገለጥ የተነገሩትን የቅዱስ መጻህፍቴ ክፍል የሆኑትን የቆዩ [ሐ]መዛግብት ጽሁፎችን [መ]እውቀት እንደምትቀበል በማመን በታማኝ ልብ፣ በእምነት [ሠ]የጠየከውን ሁሉ እውቀት ትቀበላለህ።

፪ አዎን፣ እነሆ፣ በአንተ ላይ በሚሆነው እና [ሀ]በልብህም በሚኖረው [ለ]በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአዕምሮህ እና በልብህ [ሐ]እነግርሀለሁ።

፫ አሁን፣ እነሆ፣ ይህ የራዕይ መንፈስ ነው፤ እነሆ ይህም ሙሴ የእስራኤልን ልጆች [ሀ]በቀይ ባህር ውስጥ በደረቅ ምድር ያሻገረበት መንፈስ ነው።

፬ ስለዚህ ይህ ያንተ ስጦታ ነው፣ ተጠቀምበት፣ እናም ከጠላቶችህ እጆች ስለሚያወጣህ የተባረክ ነህ፣ ይህ ባይሆን ኖሮ ይገድሉህ እንዲሁም ነፍስህንም ወደጥፋት ባመጡት ነበር።

፭ አቤቱ፣ እነዚህን [ሀ]ቃላት አስታውስ፣ እናም ትእዛዛቴን ጠብቅ። ይህ ስጦታህ እንደሆነ አስታውስ።

፮ ስጦታህ ይህ ብቻም አይደለም፤ የአሮን ስጦታ የሆነው ሌላም ስጦታ አለህ፤ እነሆ፣ ይህም ብዙ ነገሮችንም ነግሮኃል፤

፯ እነሆ፣ ከእግዚአብሔር በስተቀር ይህንን የአሮንን ስጦታ ካንተ ጋር እንዲሆን የሚያደርግ ምንም ኃይል የለም።

፰ ስለዚህ፣ አትጠራጠር፣ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና፤ እናም በእጅህም ትይዘዋለህ፣ እናም ድንቅም የሆነ ስራ ትሰራለህ፤ ከእጅህም ምንም አይነት ኃይል ሊወስደው አይችልም፣ የእግዚአብሔር ስራ ነውና።

፱ እናም፣ ስለዚህ በእነዚህ መንገዶች እንድነግርህ የምትጠይቀኝን፣ ይህንንም እሰጥሀለሁ፣ እናም እርሱን በተመለከተ እውቀት ይኖርሀል።

፲ ያለ [ሀ]እምነት ምንም ማድረግ እንደማትችል አስታውስ፤ ስለዚህ በእምነት ጠይቅ። በእነዚህም ነገሮች አትቀልድ፤ የማያስፈልጉህን ነገሮች [ለ]አትጠይቅ።

፲፩ የእግዚአብሔርን ሚስጥራት ታውቅ ዘንድ፣ እናም ተደብቀው ያሉትን የተቀደሱ ጥንታዊ መዛግብትን [ሀ]መተርጎም፣ እንዲሁም ከእነርሱም እውቀት ማግኘት ትችል ዘንድ ጠይቅ፤ እናም እንደ እምነትህ ይደረግልሀል።

፲፪ እነሆ፣ እኔ ነኝ የተናገርኩት፤ እናም ከመጀመሪያው ጀምሮ የተናገርኩህ እኔው ራሴው ነኝ። አሜን።

ክፍል ፱

ሚያዚያ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለኦሊቨር ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ። ኦሊቨር ትዕግስተኛ እንዲሆን ተገሰጸ

፰ ፩ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፷፮። ቅ.መ.መ. ካውደሪ፣ ኦልቨር።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥፲፮።
ሐ ት. እና ቃ. ፮፥፳፮–፳፯፤ ፱፥፪።
መ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ሠ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ልብ።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ት. እና ቃ. ፱፥፯–፱። ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፫ሀ ዘፀአ. ፲፬፥፲፫–፳፪፤ ዘዳግ. ፲፩፥፬፤ ፩ ኔፊ ፬፥፪፤ ሞዛያ ፯፥፲፱። ቅ.መ.መ. ቀይ ባህር።
፭ሀ ዘዳግ. ፲፩፥፲፰–፲፱።
፲ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፫–፷፭።
፲፩ሀ ት. እና ቃ. ፱፥፩፣ ፲።

እናም ለመተርጎም ከመሞከር ይልቅ ለጊዜው የተርጓሚውን ቃላት በመጻፍ እንዲደሰት ተመከረ።

፩–፮፣ ሌሎች ጥንታዊ መዛግብት ገና ይተርጎማሉ፤ ፯–፲፬፣ መፅሐፈ ሞርሞን በጥናት እና በመንፈሳዊ ማረጋገጫ ተተረጎመ።

፩ እነሆ፣ ልጄ ሆይ እንዲህ እልሀለሁ፣ ከእኔ በፈለከው መሰረት [ሀ]ስላልተረጎምህ እናም ዳግም ለአገልጋዬ፣ ለጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ [ለ]መጻፍን በመጀመርህ ምክንያት በእርሱ ላይ እምነት የጣልኩበትን መዝገብ እስክትጨርስ ድረስ እንድትቀጥል እፈልጋለሁ።

፪ እና ከዚያም እነሆ፣ [ሀ]ሌሎች [ለ]መዛግብቶች አሉኝ፣ ያንንም በመተርጎም እንድትረዳ ኃይል እሰጥኃለሁ።

፫ ልጄ ትዕግስተኛ ሁን፣ ይህ በእኔ ዘንድ ጥበብ ነውና፤ እናም በአሁኑ ጊዜ መተርጎምህ አስፈላጊ አይደለም።

፬ እነሆ፣ እንድታደርገው የተጠራህበት ስራ ለአገልጋዬ ለጆሴፍ እንድትጽፍ ነው።

፭ እናም፣ እነሆ፣ ይህንም እድል ከአንተ የወሰድኩብህ መተርጎም በጀመርህ ጊዜ እንደ ጀመርኸው ባለመቀጠልህ ምክንያት ነው።

፮ [ሀ]አታጉረምርም፣ ልጄ ሆይ፣ ከአንተ ጋር በዚህ ሁኔታ ይህን ማድርጌ ጥበብ ነው።

፯ እነሆ፣ አልተረዳህም፤ እኔን ከመጠይቅህ በስተቀር ምንም ሳታስብበት፣ እንደምሰጥህ ገምተህ ነበር።

፰ ነገር ግን እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ በአእምሮህ ውስጥ [ሀ]ልታጠናው ይገባል፤ ከዚያም ትክክለኛ መሆኑን [ለ]ልትጠይቀኝ ይገባል፣ እናም ትክክለኛ ከሆነ [ሐ]ውስጥህም [መ]እንዲቃጠል አደርጋለሁ፤ ትክክል እንደሆነም [ሠ]ይሰማሀል።

፱ ነገር ግን ትክክል ካልሆነ እንደዚህ ያሉ ስሜቶች አይሰሙህም፣ ነገር ግን የተሳሳተ ነገርን የሚያስረሳ [ሀ]የሀሳብ ብዥታ ይሆንልሀል፤ ስለዚህ፣ ከእኔ ካልተሰጠ በስተቀር ቅዱስ የሆነውን መጻፍ አትችልም።

፲ አሁን፣ ይህን አውቀህ ቢሆን ኖሮ [ሀ]መተርጎም በቻልህ ነበር፤ ሆኖም፣ አሁን መተርጎምህ አስፈላጊ አይደለም።

፲፩ እነሆ፣ በጀመርህበት ጊዜ አስፈላጊ ነበር፤ ነገር ግን [ሀ]ፈራህ፣ እናም ጊዜውም አለፈ፣ እናም አሁን አስፈላጊ አይደለም፤

፲፪ የጠፋውን ጊዜ ለመተካት ለአገልጋዬ [ሀ]ጆሴፍ በቂ ጥንካሬን አብጅቼ እንደሰጠሁት አታይምን? እናም ማናችሁንም ቢሆን አልኮነንኩም።

፲፫ እንድታደርግ ያዘዝኩህን አድርግ፣ እናም ትበለጽጋለህ። ታማኝ ሁን፣ እናም [ሀ]ለፈተና ራስህን አታጋልጥ።

፲፬ አንተን [ሀ]ለጠራሁበት [ለ]ስራ ጸንተህ ቁም፣ እናም ከራስ ጠጉርህ አንዲት አትጠፋም፣ እናም በመጨረሻውም ቀን [ሐ]ከፍ ትላለህ። አሜን።

፱ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፰፥፩፣ ፲፩።
ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፰፯።
፪ ሀ ስለተጨማሪ ትርጉም ስራ፣ እንዲሁም ኦሊቨር ካውድሪ እንደ ጸሀፊ ረጂ የነበረባቸውን የጆሴፍ ስሚዝ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም እና የመፅሀፈ አብርሐም የሚያመለክት። ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
ለ ት. እና ቃ. ፮፥፳፮፤ ፰፥፩።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ማጉረምረም።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ሉቃ. ፳፬፥፴፪።
መ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ ምስክርነት።
ሠ ት. እና ቃ. ፰፥፪–፫።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፲፥፪።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፰፥፲፩።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥፰።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፮፥፲፫።
ሐ አልማ ፲፫፥፳፱፤ ት. እና ቃ. ፲፯፥፰።

ክፍል ፲

ምንም እንኳን ከፊሎቹን በበጋ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) አካባቢ የተቀበላቸው ሳይሆን ባይቀርም፣ በሚያዝያ ፲፰፻፳፰ (እ.አ.አ.) አካባቢ በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጌታ ክፉ ሰዎች ከመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ፻፲፮ ገጽ የሌሒ መጽሐፍ የእጅ ጽሁፍ ላይ ስላደረጉት ለውጥ ለጆሴፍ ነገረው። እነዚህ የእጅ ጽሁፎች ለጊዜው በአደራ ተሰጥተውት ከነበረው ከማርቲን ሀሪስ እጅ ነበር የጠፉት። (የክፍል ፫ ዐርስትን ተመልከቱ።) የክፉት ዓላማውም በጠፉት ገጾች ላይ ያሉት እስኪተረጎሙ መጠበቅ እና በተለወጠው ነገር የተነሳ ትርጓሚው አመኔታን እንዲያጣ ለማደረግ ነበር። ይህ የክፉት ዓላማ በክፉው ተጠንስሶ ነበር እንዲሁም ሞርሞን የጥንቱ የኔፋውያን ባለ ታሪክ ሰሌዳዎቹን አሳጥሮ እየጻፈ ሳለ በጌታ ይታወቅ እንደነበር በመፅሐፈ ሞርሞንም ውስጥ ይታያል (የሞርሞን ቃላት ፩፥ ፫–፯ን ተመልከቱ)።

፩–፳፮፣ የጌታን ስራ እንዲቃወሙ ክፉ ሰዎችን ሰይጣን ያነሳሳል፣ ፳፯–፴፫፣ እርሱም የሰዎችን ነፍስ ለማጥፋት ይሻል፣ ፴፬–፶፪፣ ወንጌል በመፅሐፈ ሞርሞን አማካይነት ለላማናውያን እና ለሁሉም ህዝብ ይዳረሳል፤ ፶፫–፷፫፣ ጌታ ቤተክርስቲያኑን እና ወንጌሉን በሰዎች መካከል ይመሰርታል፤ ፷፬–፸፣ የንስሀ ልብ ያላቸውን ወደ ቤተክርስቲያኑ ይሰበስባል እናም ታዛዦቹን ያድናል።

፩ አሁን፣ እንዲህ፣ እልሀለሁ፣ [ሀ]በኡሪም እና ቱሚም አማካኝነት ለመተርጎም ኃይል የተሰጡህን ጽሁፎች [ለ]ለክፉ ሰው እጅ አሳልፈህ በመስጠትህ አጥፍተሀቸዋል።

፪ እናም ስጦታህንም አብረህ አጥተሀል፣ እናም [ሀ]አእምሮህ ጨልሟል።

፫ ሆኖም፣ አሁን [ሀ]ዳግመኛ ተመልሶልሀል፤ ስለዚህ ታማኝ መሆንህን ተመልከት እናም እንደጀመርኸው የቀረውን የትርጉም ስራ ለመጨረስ ቀጥል።

፬ ለመተርጎም እንዲያስችልህ ከተዘጋጀልህ [ሀ]ብርታት እና መንስዔ በላይ [ለ]በፍጥነት አትሂድ ወይም አትስራ፤ ነገር ግን እስከመጨረሻው [ሐ]ትጉህ ሁን።

፭ ድል ታደርግ ዘንድ፤ አዎን፣ ሰይጣንን ድል ታደርግ ዘንድ፣ እናም የእርሱን ስራ ከሚደግፉት የሰይጣን አገልጋዮች እጆች ታመልጥ ዘንድ ዘወትር [ሀ]ጸልይ።

፮ እነሆ፣ እነርሱ [ሀ]ሊያጠፉህ ፈልገዋል፤ ያመንከው [ለ]ሰው እንኳን ሊያጠፋህ ፈልጓል።

፯ እምነት የተጣሉብህን ነገሮች ለመውሰድ ስለፈለገ፤ እናም እንዲሁም ስጦታህን ለማጥፋት ስለፈለገ፣ ክፉ ሰው ነው ያልኩት በዚህ ምክንያት ነው።

፰ እናም ጽሑፎቹን በእጁ አሳልፈህ በመስጠትህ ምክንያት፣ እነሆ፣ ክፉ ሰዎች ከአንተ ወስደዋቸዋል።

፱ ስለዚህ፣ አዎን፣ የተቀደሱትን፣ ለክፉት አሳልፈህ ሰጥተሀቸዋል።

፲ እናም፣ እነሆ፣ እንዲጻፉ ያደረግሀቸውን ወይም አንተ የተረጎምካቸውን፣ ከእጅህ የወጡትን ጽሁፎች፣ እንዲለወጡ [ሀ]ሰይጣን ክፉትን በልባቸው ውስጥ አስቀምጧል።

፲ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
ለ ት. እና ቃ. ፫፥ ፩–፲፭።
፪ሀ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፫፥ ፲።
፬ሀ ዘፀአ. ፲፰፥ ፲፫–፳፮።
ለ ሞዛያ ፬፥ ፳፯።
ሐ ማቴ. ፲፥ ፳፪።
ቅ.መ.መ. ትጋት።
፭ሀ ፫ ኔፊ ፲፰፥ ፲፭–፳፩።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፮ሀ ት. እና ቃ. ፭፥ ፴፪–፴፫፤ ፴፰፥ ፲፫።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥ ፩–፪።
፲ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።

፲፩ እናም እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ ቃላቶቹን በመለወጣቸው ምክንያት፣ ከተረጎምካቸው እና እንዲጻፉ ካደረካቸው ተጻራሪ የሆነን ነገር ያነባሉ፤

፲፪ እናም፣ በዚህ ምክንያት ዲያብሎስ ይህን ስራ ለማጥፋት የብልጠት ዕቅድ ለማሳካት ፈልጓል።

፲፫ ለመተርጎም አስመስለህ በነበሩት ቃላት ውስጥ [ሀ]ያዝንህ ብለው በሀሰት በመናገር፣ ይህንን እንዲያደርጉ በልባቸው ውስጥ አስቀምጧልና።

፲፬ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ሰይጣን የክፉት እቅዱን እንዲያከናውን አልፈቅድም።

፲፭ እነሆም፣ ዳግም ለመተርጎም በመጠየቅ ጌታ አምላክህን እንድትፈትን በልባቸው ውስጥ ይህን አስቀምጧል።

፲፮ እናም ከዚያም፣ እነሆ፣ እግዚአብሔር ለመተርጎም ኃይልን እንደሰጠው እናያለን፤ ይህም ከሆነ ዳግም እንዲሁ ኃይልን ይሰጠዋል ይላሉ እናም በልባቸውም ይህንን ያስባሉ፤

፲፯ እናም ዳግም እግዚአብሔር ኃይልን የሚሰጠው ከሆነ፣ ወይም ዳግም የሚተረጉም ከሆነ፣ ወይም በሌላ አባባል፣ ዳግም አንድ አይነት ቃላት የሚያመጣ ከሆነ፣ እነሆ፣ ከእኛም ዘንድ እንዲህ አይነት አለን፣ እናም ለውጠናቸዋል፤

፲፰ ስለዚህም አይስማሙም፣ እናም በእነዚህ ቃላት ዋሽቷል፣ እናም ስጦታም የለውም፣ እናም ኃይልም የለውም እንላለን፤

፲፱ ስለዚህ እርሱንም እናም ደግሞ ስራውን እናጠፋለን፤ እናም ይህን የምናደርገው በመጨረሻ እንዳናፍር፣ እናም የአለምን ክብር እንድናገኝ ነው።

፳ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ሰይጣን በልባቸው ውስጥ ታላቅ ስፍራ ይዟል፤ መልካም በሆነው ላይ [ሀ]በክፉት እንዲነሱ [ለ]ያነሣሳቸዋል፤

፳፩ እናም ልቦቻቸው [ሀ]ተበላሽተዋል፣ እናም [ለ]በክፉት እና በርኩሰት ተሞልተዋል፤ እናም [ሐ]ምግባሮቻቸው ርኩሰት በመሆናቸው ምክንያት ከብርሀን ይልቅ [መ]ጨለማን [ሠ]ይወዳሉ፤ ስለዚህም እኔን አይጠይቁም።

፳፪ ነፍሳቸውን ወደ ጥፋት [ሀ]እንዲመሩ [ለ]ሰይጣን ያነሣሳቸዋል።

፳፫ እናም ስለዚህ የእግዚአብሔርን እቅድ ለማጥፋት አጨበርባሪ ዕቅድ አስቀምጧል፤ ነገር ግን ይህንን ከእጃቸው እጠይቃለሁ፣ [ሀ]በፍርድ ቀንም ወደ እፍረታቸው እና ወደ ኩነኔያቸው ይለውጣል።

፳፬ አዎን፣ በዚህ ስራ ላይ ልባቸው በቁጣ እንዲነሳሳ ያደርጋል።

፳፭ አዎን፣ እንዲህም አላቸው፥ ማጥፋት ትችሉ ዘንድ፣ አታልሉ እናም ለመያዝ አድፍጡ፤ እነሆ ይህም ጉዳት አይደለም። እናም እንዲህ በማለት ይሸነግላቸዋል፣ እንዲሁም ውሸታምን ሰው ይዞ ለማጥፋት [ሀ]መዋሸት ኃጢአት አይደለም ይላቸዋል።

፳፮ እናም ስለዚህ ይሸነግላቸዋል፣ እናም ነፍሳቸውን ወደ [ሀ]ገሀነም ጎትቶ እስኪጥል ድረስ [ለ]ይመራቸዋል፤ እናም እንደዚህ እራሳቸው በራሳቸው [ሐ]ወጥመድ ውስጥ እንዲያጠምዱ ያደርጋል።

፳፯ እናም ስለዚህ የሰዎችን ነፍስ [ሀ]ለማጥፋት በምድር ላይ ወደላይ እና ወደታች፣ [ለ]ወዲህ እና ወዲያው ይመላለሳል።

፳፰ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ሌላው [ሀ]ለማታለል ይዋሻል ብሎ ለማታ

፲፫ ሀ ኤር. ፭፥፳፮።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
ለ ፪ ኔፊ ፳፰፥፳–፳፪።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፳፫–፳፬።
ለ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፉት።
ሐ ዮሐ. ፫፥፲፰–፳፩፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥፵፭።
መ ሞዛያ ፲፭፥፳፮።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ሠ ሙሴ ፭፥፲፫–፲፰።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ፪ ኔፊ ፪፥፲፯–፲፰።
፳፫ ሀ ሔለ. ፰፥፳፭፤
ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፳፫–፳፭።
፳፭ ሀ ፪ ኔፊ ፪፥፲፰፤ ፳፰፥፰–፱፤
አልማ ፲፥፲፯፤
ሙሴ ፬፥፬።
ቅ.መ.መ. ሐሰት።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ሲዖል።
ለ ቅ.መ.መ. ክህደት።
ሐ ምሳ. ፳፱፥፭–፮፤
፩ ኔፊ ፲፬፥፫።
፳፯ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፥፲፱–፳፫፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፳፰–፳፱።
ለ ኢዮብ ፩፥፯።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሸንገላ (ውሸት)፣
መዋሸት፣ ማታለል።

ለል ለሚዋሽ ወዮለት፣ እንደዚህ እይነቶቹ ከእግዚአብሔር [ለ]ፍትህ አያመልጡምና።

፳፱ አሁን፣ እነሆ ሰይጣን አታሏችኋል ስላላቸው እነዚህን ቃላት ለውጠዋል—እናም በዚህ የተነሳ አንተ ጌታ አምላክህን [ሀ]እንድትፈታተን፣ ኃጢአት እንዲያደርጉ ይሸነግላቸዋል።

፴ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ ከእጅህ የወጡትን ዳግመኛ አትተረጉምም፤

፴፩ ስለሆነም በእነዚህ ቃላት ላይ በመዋሸት የክፋት እቅዳቸውን አያከናውኑም። ስለሆነም ዳግም ተመሣሳይ ቃላት ብታመጣ ዋሽተሀል እናም ለመተርጎም አስመስለሀል ነገር ግን ራስህን ተቃውመሀል ይላሉ።

፴፪ እናም እነሆ፣ ይህንንም ያሰራጫሉ እናም ሰይጣን ሰዎች በአንተ ላይ በቁጣ እንዲነሱ፣ ቃላቴን እንዳያምኑ ልባቸውን ያደነድናል።

፴፫ ስለዚህ ስራው በዚህ ትውልድ መካከል እንዳይመጣ [ሀ]ሰይጣን በዚህ ትውልድ ያለህን ምስክርነት ለማሸነፍ ያስባል።

፴፬ ነገር ግን እነሆ፣ ጥበብ ይኸው ነው፣ እናም ለአንተ [ሀ]ጥበብን ስላሳየሁህ እናም እነዚህን በተመለከተ፣ ምንም ማድረግ እንደሚገባህ፣ ትእዛዛትን ስለሰጠሁህ፣ የትርጉሙን ስራ እስክታጠናቅቅ ድረስ ለአለም እንዳታሳይ።

፴፭ ጥበብ ይኸው ነው፣ ለአለም እንዳታሳየው ስላልኩህ አትደነቅ—ለአለም እንዳታሳየው ያልሁህ ምክንያት አንተን ለማዳን ነው።

፴፮ እነሆ፣ ለጻድቃንን አታሳያቸው አላልኩም፤

፴፯ ነገር ግን ዘወትር [ሀ]ጻድቁን ለመፍረድ ስለማትችል፣ ወይም ክፉን ከጻድቁ ዘወትር ለመለየት ስለማትችል፣ ስለዚህ እንዲህ እልሀለሁ፣ ነገሩን በተመለከተ ለአለም እስካሳውቅ ድረስ [ለ]ዝም በል።

፴፰ እናም አሁን፣ እውነት እልሀለሁ፣ ከእጅህ የወጡት የጻፍካቸው [ሀ]ነገሮች መዝገብ [ለ]በኔፊ ሰሌዳዎች ላይ ተቀርጸው ይገኛሉ፤

፴፱ አዎን፣ እናም በእነዚህ ጽሁፎች ውስጥ የበለጠ ዝርዝር በኔፊ ሰሌዳ ላይ ተሰጥቷል መባሉን አስታውስ።

፵ እናም አሁን፣ በኔፊ ሰሌዳ ላይ የተቀረጸው ታሪክ በጥበቤ በዚህ ታሪክ ውስጥ ላሉት ህዝብ ከማመጣው እውቀት አንጻር በቀረበ በመሆኑ ምክንያት—

፵፩ ስለዚህ፣ [ሀ]በኔፊ ሰሌዳዎች ላይ ያሉትን ጽሁፎች እስከ ንጉስ ቢንያም አገዛዝ ድረስ፣ ወይም ተርጉመህ በእጅህ እስከ አስቀረሀቸው ድረስ ትተረጉማለህ፤

፵፪ እናም እነሆ፣ እንደ ኔፊ መዝገብ ታሳትመዋለህ፤ እና እንደዚህም ቃላቴን የለወጡትን አምታታቸዋለሁ።

፵፫ ሥራዬን ያጠፉ ዘንድ አልፈቅድም፤ አዎን፣ ጥበቤ ከአጋንንት ብልጠት የላቀ መሆኑንም አሳያቸዋለሁ።

፵፬ እነሆ፣ አጥሮ የተጻፈውን ወይም አነስተኛውን የኔፊ ታሪክን ብቻ ነው ያገኙት።

፵፭ እነሆ፣ በወንጌሌ ላይ ታላቅ መረዳትን የሚያስገኙ ብዙ ነገሮች በኔፊ ሰሌዳ ላይ ተቀርጸው ይገኛሉ፤ ስለዚህ፣ ይህን የኔፊ ቅርጾች የመጀመሪያ ክፍሎችን መተርጎምህ እናም ይህንም ስራ መላክህ በእኔ ዘንድ ጥበብ ነው።

፵፮ እናም፣ እነሆ፣ የቀሩት እነዚህ [ሀ]ስራዎች የእኔ ቅዱሳን ነቢያቶች፣ አዎን፣ እናም እንዲሁም ደቀመዛሙርቴ በጸሎታቸው ለዚህ ህዝብ እንዲመጣ [ለ]የፈለጉትን [ሐ]የወንጌሌን ክፍሎች የያዘ ነው።

፳፰ ለ ሮሜ ፪፥፫።
ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፳፱ ሀ ማቴ. ፬፥፯።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፴፯ ሀ ማቴ. ፳፫፥፳፰።
ለ ዘፀአ. ፲፬፥፲፬።
፴፰ ሀ በመፅሐፈ ሞርሞን የመጀመሪያ እትም መግቢያ ውስጥ፣ በ፻፲፮ ገጾች ውስጥ የነበረው መረጃ “መፅሀፈ ሌሂ” ተብሎ ከተጠራው ሰሌዳዎች ላይ የተተረጎሙ ክፍል እንደነበረ ነቢዩ ገልጿል።
ለ ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
፵፩ ሀ ቃላት ፩፥፫–፯።
፵፮ ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ለ ኢኖስ ፩፥፲፪–፲፰፤
ሞር. ፰፥፳፬–፳፮፤
፱፥፴፬–፴፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ወንጌል።

፵፯ እናም እንዲህ አልኳቸው፣ በጸሎታቸው ባላቸው [ሀ]እምነት መጠን [ለ]ሊሰጣቸው ይገባል፤

፵፰ አዎን፣ እናም ይህም እምነታቸው ነበር፣ በጊዜያቸው እንዲሰብኩ ለእነርሱ የሰጠኋቸውን ወንጌል ለወንድሞቻቸው [ሀ]ለላማናውያን እናም ደግሞ በመገንጠላቸው ምክንያት ላማናውያን ለሆኑት ሁሉ ይመጣ ዘንድ ነበር።

፵፱ አሁን፣ ይህ ብቻም አይደለም—ሌሎች ህዝብ ይህን ምድር እንዲይዙ የሚቻል ቢሆን፣ ይህ ወንጌል እንዲሁ ይታወቅ ዘንድ የጸሎት እምነታቸው ነበር፤

፶ እናም ስለዚህ በዚህ ምድር ላይ በዚህ ወንጌል የሚያምን ሁሉ ዘለአለማዊ ህይወት ይኖረው ዘንድ፣ በዚህ ምድር ላይ በጸሎታቸው በረከትን ትተዋል፤

፶፩ አዎን፣ ለማንኛውም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ ወይም ህዝብ ሁሉ ይህ ነጻ ይሆን ዘንድ በጸሎታቸው በረከትን ትተዋል።

፶፪ እና፣ አሁን፣ እነሆ በጸሎታቸው ውስጥ ባለው እምነት የተነሳ የዚህን የወንጌሌን ክፍል ወደ ህዝቦቼ እውቀት አመጣለሁ። እነሆ፣ የሚመጣው የተቀበሉትን ለመሻር ሳይሆን፣ ነገር ግን ለመገንባት ነው።

፶፫ እናም በዚህ ምክንያት እንዲህ ብያለሁ፥ ይህ ትውልድ ልቡን የማያደነድን ከሆነ፤ ቤተክርስቲያኔን በመካከላቸው እመሰርታለሁ።

፶፬ አሁን ይህንን የምለው ቤተክርስቲያኔን ለማፍረስ አይደለም፣ ነገር ግን ቤተክርስቲያኔን ለመገንባት ነው።

፶፭ ስለዚህ፣ የቤተክርስቲያኔ ሰው የሆነ ሁሉ [ሀ]መፍርሀት የለበትም፣ እንደዚህ አይነቱ [ለ]መንግሥተ ሰማይን [ሐ]ይወርሳልና።

፶፮ ነገር ግን [ሀ]የማይፈሩኝ፣ ትእዛዛቴን የማይጠብቁ ነገር ግን ለራሳቸው [ለ]ጥቅምን ለማግኘት [ሐ]ቤተክርስቲያንን የሚገነቡ፣ አዎን፣ እርኩሰትን የሚያደርጉ ሁሉ እናም የአጋንንትን መንግስት የሚገነቡ—አዎን፣ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ አውካቸዋለሁ፣ እና መላ ሰውነታቸው እንዲርበተበት እና እንዲቀጠቀጥ አደርጋለሁ።

፶፯ እነሆ፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ [ሀ]የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ። የእኔው ወደሆኑት መጣሁ፣ የራሴም አልተቀበሉኝም።

፶፰ እኔ በጭለማ የማበራ [ሀ]ብርሀን ነኝ፣ እናም በጨለማም ያሉት አይረዱትም።

፶፱ ለደቀመዛሙርቴ ከዚህ በረት ያልሆኑ [ሀ]ሌሎች [ለ]በጎች አሉኝ ያልሁት እኔው ነኝ። እናም [ሐ]ያልተረዱኝ ብዙ ነበሩ።

፷ እናም ለዚህ ህዝብ [ሀ]የያዕቆብ ቤት ቅርንጫፍም እንደነበሩ፤ እና ሌሎች በጎች እንዳሉኝ አሳያቸዋለሁ፤

፷፩ እናም በስሜ የሰሩትን ድንቅ ስራዎቻቸውን ወደ ብርሀን አመጣለሁ፤

፷፪ አዎን፣ እናም ለእነርሱ አገልግሎት የዋለውን ወንጌሌን ወደ ብርሀን አመጣዋለሁ፣ እናም እነሆ፣ እናንት የተቀበላችሁትን አይክዱም ነገር ግን ይገነቡታል፣ እናም [ሀ]የትምህርቴን እውነተኛ ነጥቦች፣ አዎን፣ በእኔ ያለውን ብቸኛ ትምህርት ወደ ብርሀን ያመጡታል።

፷፫ እናም ወንጌሌን እመሰረት ዘንድ፣ ብዙ ፀብ እንዳይኖር ዘንድ ይህንን አደርጋለሁ፤ አዎን፣ የትምህርቴ ነጥቦች በተመለከተ [ሀ]ሰይጣን የሰዎችን ልብ [ለ]ለፀብ ያነሣሳል፤ በዚህም ስህተት ይሰራሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን [ሐ]ያጣምማሉ እናም አይረዷቸውም።

፵፯ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ፫ ኔፊ ፭፥፲፫–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፫፥፲፱–፳።
፵፰ ሀ ሞሮኒ ፲፥፬–፭፤
ት. እና ቃ. ፻፱፥፷፭–፷፰።
፶፭ ሀ ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
ሐ ማቴ. ፭፥፲።
፶፮ ሀ መክ. ፲፪፥፲፫–፲፬።
ለ ፬ ኔፊ ፩፥፳፮።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—
የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
፶፯ ሀ ሮሜ ፩፥፬።
፶፰ ሀ ት. እና ቃ. ፮፥፳፩።
፶፱ ሀ ዮሐ. ፲፥፲፮።
ለ ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፭፥፲፮–፲፯።
፷ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
፷፪ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፴፩–፵።
፷፫ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ሐ ፪ ጴጥ. ፫፥፲፮።

፷፬ ስለዚህ፣ ይህንን ታላቅ ሚስጥር እገልጽላቸዋለሁ፤

፷፭ ስለሆነም፣ ልባቸውን የማያደነድኑ ከሆኑ፣ ዶሮ ጫቹቶቿን በክንፎቿ እንደምትሰበስብ እንዲሁ እኔም [ሀ]እሰበስባቸዋለሁ፤

፷፮ አዎን፣ ከመጡ [ሀ]ከህይወት ውሀ በነፃ ይጠጣሉ።

፷፯ እነሆ፣ ይህ ትምህርቴ ነው—ንስሀ የሚገባ እና ወደ እኔ [ሀ]የሚመጣ ሁሉ [ለ]የቤተክርስቲያኔ ሰው ነው።

፷፰ በዚህ ላይ ጨምሮ ወይም ቀንሶ [ሀ]የሚያውጅ ሁሉ ከእኔ አይደለም፣ ነገር ግን [ለ]ተቃዋሚዬ ነው፤ ስለዚህ ከቤተክርስቲያኔም አይደለም።

፷፱ እናም አሁን፣ እነሆ፣ የቤተክርስቲያኔ የሆነ ሁሉ እናም በቤተክርስቲያኔ እስከመጨረሻው የሚጸና [ሀ]በአለቴ ላይ የምመሰርተው እርሱን ነው እናም [ለ]የሲዖል ደጆችም አይቋቋሙትም።

፸ የአለም [ሀ]ብርሀን እና ህይወት የሆነውን፣ የአዳኛችሁን፣ [ለ]የጌታችሁን እና የአምላካችሁን ቃላት አስታውሱ። አሜን።

ክፍል ፲፩

ግንቦት ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለወንድሙ ለሀይረም ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ይህም ራዕይ የተሰጠው በኡሪም እና ቱሚም አማካይነት ለጆሴፍ ልመናና ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነበር። ይህ ራዕይ የአሮናዊ ክህነት ዳግመኛ ከተመለሰ በኋላ መሰጠቱን የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ያሳስባል።

፩–፮፣ በወይኑ ስፍራ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ደህንነትን ያገኛሉ፤ ፯–፲፬፣ ጥበብን እሹ፣ ንስሐን አውጁ፣ በመንፈስ ታመኑ፤ ፲፭–፳፪፣ ትዕዛዛቱን ጠብቁ፣ እናም የጌታን ቃል አጥኑ፤ ፳፫–፳፯፣ የራዕይን እናም የትንቢትን መንፈስን አትካዱ፤ ፳፰–፴፣ ክርስቶስን የሚቀበሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ።

፩ በሰዎች ልጆች መካከል ታላቅ እና [ሀ]ድንቅ ስራ ሊመጣ ነው።

፪ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ፈጣን እና [ሀ]ሀያል፣ ሁለት አንደበት ካለው ሰይፍ ይልቅ [ለ]የተሳለ፣ መገጣጠሚያን እና መቅኔን የሚለየውን [ሐ]ቃሌን [መ]አድምጥ፤ ስለዚህ ቃሌን እድምጥ።

፫ እነሆ፣ የእርሻው ስፍራ [ሀ]ነጭ ሆኖ አዝመራው ዝግጁ ነው፤ ስለዚህ፣ መሰብሰብ የሚሻ ሁሉ ኃይሉ ይጨድ፣ እናም ለነፍሱም [ለ]ዘለአለማዊ ደህንነት በእግዚአብሔር መንግስት [ሐ]ያከማች ዘንድ ቀን ሳለ ይሰብስብ።

፷፭ ሀ ሉቃ. ፲፫፥፴፬፤
፫ ኔፊ ፲፥፬–፮፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፳፬።
፷፮ ሀ ቅ.መ.መ. ህያው ውሀ።
፷፯ ሀ ማቴ. ፲፩፥፳፰–፴።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፷፰ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፵።
ለ ሉቃ. ፲፩፥፳፫።
፷፱ ሀ ቅ.መ.መ. አለት።
ለ ማቴ. ፲፮፥፲፰፤
፪ ኔፊ ፬፥፴፩–፴፪፤
ት. እና ቃ. ፲፯፥፰፤
፻፳፰፥፲።
፸ ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
፲፩ ፩ ሀ ኢሳ. ፳፱፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፬።
ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፪ ሀ አልማ ፬፥፲፱፤ ፴፩፥፭።
ለ ሔለ. ፫፥፳፱–፴፤
ት. እና ቃ. ፮፥፪።
ሐ ዕብ. ፬፥፲፪።
መ ፩ ኔፊ ፲፭፥፳፫–፳፭፤
ት. እና ቃ. ፩፥፲፬፤
፹፬፥፵፫–፵፭።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፪፥፫።
ለ ፩ ጢሞ. ፮፥፲፱።
ሐ ሉቃ. ፲፰፥፳፪፤
ሔለ. ፭፥፰።

፩ አዎን፣ ማንኛውም [ሀ]የሚያጭድ እናም የሚሰበስብ ሁሉ እንዲሁ በእግዚአብሔር የተጠራ ነው።

፳ ስለዚህ፣ እኔን [ሀ]ከጠየቅህ ትቀበላለህ፤ ካንኳኳህ ይከፈትልሀል።

፯ አሁን፣ እንደጠየቅኸው፣ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ ትእዛዛቴን ጠብቅ እናም [ሀ]የፅዮንን አስተሳሰብ ለማምጣት እና ለመመስረት ፈልግ፤

፯ [ሀ]ጥበብን እንጂ [ለ]ባለጠግነትን አትሻ፤ እናም፣ እነሆ፣ የእግዚአብሔር ሚስጥራት ይገለጡልሀል፣ እናም ባለጠጋም ትሆናለህ። እነሆ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወት ያለው ሰው ባለጠጋ ነው።

፰ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ላደርግልህ እንደምትሻው እንዲሁ ይደረግልሀል፤ እናም፣ ፈቃድህም ከሆነ፣ በዚህ ትውልድ ውስጥ የብዙ መልካም ስራ መከናወን መንስኤ ትሆናለህ።

፱ ለዚህ ትውልድ [ሀ]ከንስሀ በቀር ሌላ ምንም [ለ]አትናገር፤ ትእዛዛቴን ጠብቅ፣ እናም ስራዬን በትእዛዜ [ሐ]መሰረት እንዲከናወን እርዳ፣ እናም ትባረካለህ።

፲ እነሆ፣ [ሀ]ስጦታ አለህ፣ ወይም በእምነት፣ [ለ]በታመነ ልብ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሀይል፣ ወይም አንተን በሚናገርህ ሀይሌ በማመን ከእኔ ከፈለግህ ስጦታ ይኖርሀል፤

፲፩ ስለሆነም፣ እነሆ፣ የምናገረው እኔ ነኝ፣ በጭለማ የማበራው [ሀ]ብርሀን እኔ ነኝ፣ እናም ለአንተ እነዚህን ቃላት [ለ]በሀይሌ እሰጥሀለሁ።

፲፪ እናም አሁን፣ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ወደ መልካም፣ አዎን፣ በትክክል ለመስራት፣ [ሀ]በትህትና [ለ]ለመራመድ፣ በጽድቅ [ሐ]ለመፍረድ፣ በሚመራው [መ]መንፈስ ላይ [ሠ]እምነትህን አድርግ፤ እና መንፈሴም ይህ ነው።

፲፫ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ከመንፈሴ [ሀ]አእምሮህን [ለ]እንዲያበራ፣ ነፍስህን [ሐ]በደስታ እንዲሞላ እሰጥሀለሁ፤

፲፬ እናም ከዚያም ታውቃለህ፣ ወይም [ሀ]የጽድቅን ነገሮች በተመለከተ ከእኔ የምትሻቸውን ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ በእምነት በእኔ በማመን እንደምትቀበል በዚህ ታውቃለህ።

፲፭ እነሆ፣ እስከምትጠራ ድረስ ለመስበክ [ሀ]እንደተጠራህ አድርገህ ማሰብ እንደሌለብህ አዝሀለሁ።

፲፮ የትምህርቴን እርግጠኝነት ታውቅ ዘንድ ቃሌን፣ [ሀ]አለቴን፣ ቤተክርስቲያኔን እናም ወንጌሌን እስክትቀበል ድረስ፣ ለጥቂት ጊዜ ጠብቅ።

፲፯ እናም ከዚያም፣ እነሆ እንደመሻትህ፣ አዎን፣ እንደ እምነትህም እንዲሁ ይደረግልሀል።

፲፰ ትእዛዛቴን ጠብቅ፤ ዝም በል፤ ለመንፈሴ መቃቀትን አድርግ፤

፲፱ አዎን፣ የተነገሩትን ነገሮች ወደብርሀን በማምጣት ትረዳ ዘንድ፣ በሙሉ ልብህ ወደ እኔ [ሀ]ጽና—አዎን፣ የስራዬን ትርጉም፤ እስከምታጠናቅቅም ድረስ ትዕግስተኛ ሁን።

፳ እነሆ፣ አዎን፣ በሙሉ ሀይልህ፣ አዕ

፩ ሀ ራዕ. ፲፬፥፲፭፤
ት. እና ቃ. ፲፬፥፫–፬።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፯ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፯–፰፤
ት. እና ቃ. ፰፯፥፲፩።
ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ፩ ነገሥ. ፫፥፲፩–፲፫፤
፪ ኔፊ ፳፯፥፴፩፤
ያዕቆ. ፪፥፲፯–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፱።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፥፳፩–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፭፥፭።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፵፯፥፰–፲፪።
ለ ሉቃ. ፰፥፲፭።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ቅ.መ.መ. መራመድ፣
ከእግዚአብሔር ጋር
መራመድ (መሄድ)።
ሐ ማቴ. ፯፥፩–፭፤
አልማ ፵፩፥፲፬–፲፭።
መ ሮሜ ፰፥፩–፱፤
፩ ዮሐ. ፬፥፩–፯።
ሠ ት. እና ቃ. ፹፬፥፪፲፯።
ቅ.መ.መ. መታመን።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
ለ ት. እና ቃ. ፸፯፥፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
፲፭ ሀ እ.አ. ፩፥፭።
ቅ.መ.መ. ስልጣን፤
ጥሪ፣ በእግዚአብሔር
መጠራት፣ የተጠራበት።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፯፥፵፬።
ቅ.መ.መ. አለት።
፲፱ ሀ ያዕቆ. ፯፥፭፤
ት. እና ቃ. ፯፰፥፲፩።

ምሮህ እናም ጉልበትህ፣ ትእዛዛቴን [ሀ]መጠበቅ ይህ የአንተ ስራ ነው።

፳፩ ቃሌን ለማወጅ አትፈልግ፣ ነገር ግን አስቀድመህ ቃሌን [ሀ]ለማግኘት ፈልግ፣ እናም ከእዚያ አንደበትህ ይፈታል፤ ከዚያም፣ ፈቃድህ ከሆነ፣ አዎን፣ ሰዎችን ለማሳመን የእግዚአብሔር ሀይል የሆነውን ቃሌን እና መንፈሴን ትቀበላለህ።

፳፪ ነገር ግን አሁን ዝም በል፤ አዎን፣ በዚህ ትውልድ ለሰው ልጆች [ሀ]የምሰጠውን እስክትቀበል ድረስ፣ በሰዎች መካከል የሄደውን [ለ]ቃሌን [ሐ]አጥና እናም ደግሞም በሰዎች መካከል የሚመጣውን [መ]ቃሌን፣ ወይም አሁን እየተተረጎመ ያለውን አጥና፣ እናም ሁሉም ነገሮች በዚያ ላይ ይጨመራሉ።

፳፫ እነሆ አንተ ልጄ [ሀ]ሀይረም ነህ፣ የእግዚአብሔርን መንግስት [ለ]ፈልግ፣ እናም እንደ ፅድቅ መሰረት ሁሉም ነገሮች ይጨመራሉ።

፳፬ [ሀ]አለቴ በሆነው [ለ]በወንጌሌ ላይ ታነፅ፤

፳፭ [ሀ]የራዕይ መንፈስንም ሆነ፣ [ለ]የትንቢትን መንፈስ አትካድ፣ ይህንን ለሚክድ ለእርሱ ወዮለት፤

፳፮ ስለዚህ፣ በእኔ ጥበብ እስክትወጣ ድረስ በልብህ ቃሌን [ሀ]አከማች።

፳፯ እነሆ፣ መልካም ፈቃድ ላላቸው፣ እናም [ሀ]በማጭዳቸው ለመሰብሰብ ለሚያጭዱ ሁሉ እናገራለሁ።

፳፰ እነሆ፣ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ [ሀ]ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ። እኔ የአለም ህይወት እና [ለ]ብርሀን ነኝ።

፳፱ የእኔም ወደሆኑት መጥቼ የእኔም ያልተቀበሉኝ እኔው ራሴው ነኝ፤

፴ ነገር ግን እውነት፣ እውነት፣ እልህለሁ፣ ለተቀበሉኝ ሁሉ፣ በስሜ ለሚያምኑት እንኳን፣ ለእነርሱ የእግዚአብሔር [ሀ]ልጆች ይሆኑ ዘንድ [ለ]ስልጣንን እሰጣቸዋለሁ። አሜን።

ክፍል ፲፪

ግንቦት ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለጆሴፍ ናይት ቀዳማዊ፣ የተሰጠ ራዕይ። የመፅሐፈ ሞርሞንን ሰሌዳ መያዙን እና በሂደት ላይ ያለውን የትርጉም ስራ በተመለከተ ጆሴፍ ስሚዝ የሰጠውን መግለጫ ጆሴፍ ናይት አመነ እናም መተርጎም እንዲቀጥሉ ያስቻላቸውን የቁሳቁስ እርዳታ፣ ለጸሐፊው እና ለጆሴፍ ስሚዝ ብዙ ጊዜ ሰጥቶ ነበር። በጆሴፍ ናይት ጥያቄ፣ ጆሴፍ ስሚዝ ጌታን በመጠየቅ ራእዩን ተቀብሏል።

፩–፮፣ በወይኑ ስፍራ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ደህንነትን ያገኛሉ፤ ፯–፱፣ የሚሹ እና ብቁ የሆኑ ሁሉ በጌታ ስራ ውስጥ መርዳት ይችላሉ።

፩ በሰዎች ልጆች መካከል ታላቅ እና [ሀ]ድንቅ ስራ ሊመጣ ነው።

፪ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ፈጣን እና ሀያል፣ ሁለት አንደበት ካለው ሰይፍ

፳ ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፳፩ ሀ አልማ ፲፯፥፪–፫፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፹፭።
፳፪ ሀ ይህም መፅሐፍ ቅዱስ
ማለት ነው።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት—የቅዱሣት
መጻህፍት ዋጋዎች።
ሐ ይህም መፅሐፈ ሞርሞን
ማለት ነው።
መ አልማ ፳፱፥፰።
፳፫ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፬።
ለ ማቴ. ፮፥፴፫።
፳፬ ሀ ማቴ. ፯፥፳፬–፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ራዕ. ፲፱፥፲።
ቅ.መ.መ. ትንቢት፣
መተንበይ።
፳፮ ሀ ዘዳግ. ፲፩፥፲፰፤
ት. እና ቃ. ፮፥፳፤ ፹፬፥፹፭፤
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፯።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
ለ ዮሐ. ፩፥፲፪።
፲፪ ፩ ሀ ለእንደዚህ አይነት
ማጣቀሻዎች ት. እና ቃ.
፲፩፥፩–፮ ተመልከቱ።

ይልቅ የተሳለ፣ መገጣጠሚያን እና መቅኔን የሚለየውን ቃሌን አድምጥ፤ ስለዚህ ቃሎቼን እድምጥ።

፫ እነሆ፣ የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ አዝመራው ዝግጁ ነው፣ ስለዚህ፣ ለነፍሱ ዘለአለማዊ ደህንነትን በእግዚአብሔር መንግስት ያከማች ዘንድ፣ መሰብሰብ የሚሻ በኃይሉ ይጨድ፣ እናም ቀን ሆኑም እያለ ይሰብስብ።

፬ ማንኛውም የሚያጭድ እናም የሚሰበስብ፣ እርሱ በእግዚአብሔር የተጠራ ነው።

፭ ስለዚህ፣ ብትጠይቀኝ ትቀበላለህ፣ ብታንኳኳ ይከፈትልሀል።

፮ አሁን፣ እንደጠየከው፣ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ ትዛዛቴን ጠብቅ እናም የፅዮንን እንቅስቃሴ ለመፈጸም እና ለመመስረት ፈልግ፤

፯ እነሆ፣ ለአንተ እና እንዲሁም ይህንን ስራ ለመፈጸምና ለመመስረት ለሚሹ ሁሉ እናገራለሁ።

፰ በሀላፊነት እምነት በተጣሉበት ነገሮች ሁሉ ራሱን ገዝቶ፣ [ሀ]በእምነት፣ [ለ]በተስፋና [ሐ]በለጋስነት፣ እናም እራሱን [መ]ትሁት በማድረግና [ሠ]በፍቅር ተሞልቶ ካልሆነ በቀር፣ ማንም ሰው በዚህ ስራ ውስጥ መርዳት አይችልም።

፱ እነሆ፣ እነዚህን ቃላት የምናገረው እኔ የአለም ብርሀን እና ህይወት ነኝ፣ ስለዚህ ባለህ ሀይል አድምጥ እናም ከዚያም ትጠራለህ። አሜን።

ክፍል ፲፫

በግንቦት ፲፭፣ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቬንያ አጠገብ ስለነቢዩ እና ኦሊቨር ካውድሪ የአሮናዊ የክህነት ሹመት ሥርዓት አፈፃጸም ታሪክን የሚናግር ከጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ውስጥ የተውጣጣ ምንባብ። የሹመቱ ስርዓት የተከናወነው በአዲስ ኪዳን መጥምቁ ዮሐንስ ተብሎ ይጠራ በነበረው፣ እራሱን ዮሐንስ ብሎ በገለጸው መልአክ እጅ ነበር። መልአኩ ይህንን ስርዓት ያከናወነው የመልከ ጼዴቅ ክህነት የሚባለውን የታላቁን ክህነት ቁልፍ በያዙት ጴጥሮስ፣ ያእቆብ፣ እና ዮሐንስ ተብለው በተጠሩት የጥንት ኃዋሪያት ስር በመሆን እንደነበረ ገልጿል። በተገቢው ጊዜ ይህ ከፍተኛ ክህነት እንደሚሰጣቸው ለጆሴፍ ስሚዝ እና ለኦሊቨር ካውድሪ የተስፋ ቃል ተሰጥቷቸው ነበር። (ክፍል ፳፯፥፯–፰፣ ፲፪ን ተመልከቱ።)

የአሮናዊ ክህነት ቁልፎች እና ሀይላት ተዘርዝረዋል።

፩ አገልጋይ ባልንጀሮቼ፣ [ሀ]የመላእክትን፣ እና [ለ]የንስሀን ወንጌል፣ እና ለኃጢአት ስርየት በማጥለቅ [ሐ]የማጥመቅ አገልግሎት ቁልፎች የያዘውን [መ]የአሮንን ክህነት በመሲሁ ስም ለእናንተ [ሠ]እሰጣችኋለሁ፤ እናም [ረ]የሌዊ ወንድ ልጆች ዳግም መስዋዕት ለጌታ [ሰ]በጽድቅ እስኪሰዉ ድረስ ይህ ከምድር ላይ ዳግመኛ በፍጹም አይወሰድም።

፰ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ሐ ቅ.መ.መ. ልግስና።
መ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ሠ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
፲፫ ፩ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ሐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
መ ት. እና ቃ. ፳፯፥፰፤ ፹፬፥፲፰–፴፬።
ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
ሠ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፷፰–፸፭።
ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ረ በጆሰፍ ስሚዝ—ታሪክ መጨረሻ ላይ ስለአሮናዊ ክህነት ዳግም መመለስ ኦሊቨር ካውደሪ የሰጠውን ታሪክ ተመልከቱ።
ዘዳግ. ፲፥፰፤ ፩ ዜና ፮፥፵፰፤
ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፳፬።
ሰ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።

ክፍል ፲፬

ሰኔ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በፌየት፣ ኒው ዮርክ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለዴቪድ ዊትመር የተሰጠ ራዕይ። በመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ላይ የዴቪድ ዊትመር ቤተሰቦች የላቀ ፍላጎት አድሮባቸው ነበር። የትርጉሙን ስራ እስኪያጠናቅቅ ድረስ እና በሚመጣው የመጽሐፉ የባለቤትነት መብት በህግ ጥበቃን እስከሚያገኝ ድረስ ነቢዩ መኖሪያውን በፒተር ዊትመር ቀዳማዊ ቤት መስርቶ ነበር። ሶስቱ የዊትመር ወንድ ልጆች፣ እያንዳንዳቸው የስራውን እውነትነት ምስክርነት ስላገኙ፣ የእያንዳንዳቸውን ሀላፊነት በተመለከተ ይበልጥ አሳሰቧቸው ነበር። ይህ እና ከዚህ የሚቀጥሉት ሁለቱ ራዕዮች (ክፍል ፲፭ እና ፲፮) የተሰጡት በኡሪም እና ቱሚም አማካይነት ለተጠየቀው መልስ ነበር። በኋላም ዴቪድ ዊትመር ከሶስቱ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክሮች አንዱ ሆነ።

፩–፮፣ በወይኑ ስፍራ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ደህንነትን ያገኛሉ፤ ፯–፰፣ ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ውስጥ ዘለአለማዊ ህይወት ከሁሉም በላይ ታላቅ ነው፤ ፱–፲፩፣ ክርስቶስ ሰማይ እና ምድርን ፈጠረ።

፩ በሰዎች ልጆች መካከል ታላቅ እና [ሀ]ድንቅ ስራ ሊመጣ ነው።

፪ እነሆ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ፈጣን እና ሀያል፣ ሁለት አንደበት ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ፣ መገጣጠሚያን እና መቅኔን የሚለየውን ቃሌን አድምጥ፤ ስለዚህ ቃላቴን እድምጥ።

፫ እነሆ፣ የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ አዝመራው ዝግጁ ነው፣ ስለዚህ፣ ለነፍሱ ዘለአለማዊ ደህንነትን በእግዚአብሔር መንግስት ያከማች ዘንድ መሰብሰብ የሚሻ በኃይሉ ይጨድ፣ እናም ቀን ሆኑም እያለ ይሰብስብ።

፬ አዎን፣ ማንም የሚያጭድ እናም የሚሰበስብ፣ እርሱ በእግዚአብሔር የተጠራ ነው።

፭ ስለዚህ፣ ብትጠይቀኝ ትቀበላለህ፣ ብታንኳኳም ይከፈትልሀል።

፮ ፅዮንን ወደፊት ለማምጣት እና ለመመስረት ፈልግ። በነገሮች ሁሉ ትእዛዛቴን ጠብቅ።

፯ እናም፣ ትእዛዛቴን [ሀ]ብትጠብቅ እናም እስከመጨረሻው [ለ]ብትጸና ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ሁሉ ታላቅ ስጦታ የሆነውን [ሐ]ዘለአለማዊ ህይወት ይኖርሀል።

፰ እናም እንዲህም ይሆናል፣ ለዚህ ትውልድ ንስሀ ታውጅ ዘንድ እናም [ሀ]ስለምትሰማው እና ስለምታየው [ለ]ምስክር ሆነህ ትቆም ዘንድ፣ ቃልን የሚሰጥህን [ሐ]መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በማመን በእምነት በስሜ አባቴን ትጠይቃለህ።

፱ እነሆ፣ ሰማያት እና [ሀ]ምድርን፣ [ለ]ጨለማም ሊጋርደው የማይችል [ሐ]ብርሀንን [መ]የፈጠርኩ እኔ [ሠ]የህያው እግዚአብሔር [ረ]ልጅ [ሰ]ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ።

፲፬ ፩ ሀ ለእንደዚህ አይነት ማጣቀሻዎች ት. እና ቃ. ፲፩፥፩–፮ ተመልከቱ።
፯ ሀ ዘሌዋ. ፳፮፥፫–፲፪፤ ዮሐ. ፲፭፥፲፤ ሞዛያ ፪፥፳፪፤ ፵፩፤ ት. እና ቃ. ፶፰፥፪።
ለ ቅ.መ.መ. መፅናት።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፩፥፳፤ ት. እና ቃ. ፮፥፲፫። ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፰ ሀ በመፅሐፈ ሞርሞን የመጀመሪያ ገጾች ውስጥ “የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት”ን ተመልከቱ።
ለ ሞዛያ ፲፰፥፰–፲። ቅ.መ.መ. ምስክር።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፱ ሀ አብር. ፬፥፲፪፤ ፳፬–፳፭።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ሐ ፪ ሳሙ. ፳፪፥፳፱። ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
መ ዮሐ. ፩፥፩–፫፣ ፲፬፤ ፫ ኔፊ ፱፥፲፭፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፩። ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
ሠ ዳን. ፮፥፳፮፤ አልማ ፯፥፮፤ ት. እና ቃ. ፳፥፲፱።
ረ ሮሜ ፩፥፬።
ሰ ሞዛያ ፬፥፪፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፳–፳፬።

፲ ስለዚህ፣ የወንጌሌን [ሀ]ሙላት [ለ]ከአህዛብ ወደ እስራኤል ቤት ላመጣ ይገባኛል።

፲፩ እናም እነሆ፣ አንተ ዴቪድ ነህ፣ አንተም ለመርዳት ተጠርተሀል እናም ይህንም ብታደርግ እና እምነትም ቢኖርህ በጊዜአዊ እና በመንፈሳዊ በረከቶች ትባረካለህ እናም ደመወዝህም ታላቅ ይሆናል። አሜን።

ክፍል ፲፭

ሰኔ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለጆን ዊትመር የተሰጠ ራዕይ (የክፍል ፲፬ ርዕስን ተመልከቱ)። ይህ በቅርበት እና በሚገርም ሁኔታ የግል መልዕክት ነው፣ ጌታ በጆን ዊትመር እና በራሱ ብቻ የሚታወቀውን ይናገራል። ጆን ዊትመር በኋላም ከስምንቶቹ አንዱ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክር ሆነ።

፩–፪፣ የጌታ ክንድ በምድር ላይ ሁሉ ነው፤ ፫–፮፣ ወንጌልን መስበክ እና ነፍሳትን ማዳን ታላቅ ዋጋ ያለው ነገር ነው።

፩ አድምጥ፣ አገልጋዬ ጆን እናም የጌታህን እና የአዳኝህን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃላት አድምጥ።

፪ ስለሆነም እነሆ፣ ክንዴ በምድር ሁሉ ላይ ስለሆነ፣ በስልጣን እና [ሀ]በሀይል እናገርሀለሁ።

፫ እናም ከእኔ እና ከአንተ ብቻ በቀር ማንም ሰው የማያውቀውን ነገር እነግርሀለሁ—

፬ ስለሆነ ብዙ ጊዜ ላንተ ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ምን እንደሆነ ከእኔ ለማወቅ ፈልገሀል።

፭ እነሆ፣ ስለ እነዚህ ነገሮች፣ እናም የሰጠሁህን ቃላቴን በትእዛዛቴ መሰረት ስለተናገርህ የተባረክ ነህ።

፮ እናም አሁን፣ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ ለአንተ ታላቅ ዋጋ ያለው ነገር፣ ነፍሳትን ወደ እኔ ታመጣ ዘንድ ከእነርሱም ጋር [ሀ]በአባቴ [ለ]መንግስት [ሐ]ታርፍ ዘንድ ለዚህ ህዝብ ንስሀን [መ]ማወጅ ይሆናል። አሜን።

ክፍል ፲፮

ሰኔ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለፒተር ዊትመር ዳግማዊ፣ የተሰጠ ራዕይ። (የክፍል ፲፬ ርዕስን ተመልከቱ)። በኋላም ፒተር ዊትመር ዳግማዊ ከስምንቶቹ አንዱ የመፅሐፈ ሞርሞን ምስክር ሆነ።

፩–፪፣ የጌታ ክንድ በምድር ላይ ሁሉ ነው፤ ፫–፮፣ ወንጌልን መስበክ እና ነፍሳትን ማዳን ታላቅ ዋጋ ያለው ነገር ነው።

፩ [ሀ]አድምጥ፣ አገልጋዬ ፒተር እናም የጌታህን እና የአዳኝህን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃላት አድምጥ።

፪ ስለሆነም እነሆ፣ ክንዴ በምድር ሁሉ

፲ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፰–፱፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፬።
ለ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
፲፭ ፪ሀ ሔለ. ፫፥፳፱–፴።
ቅ.መ.መ. ሀይል።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. የሰማይ አባት።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
ሐ ቅ.መ.መ. እረፍት።
መ ት. እና ቃ. ፲፰፥፲፭–፲፮።
ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፲፮ ፩ሀ ለእንደዚህ አይነት
ማጣቀሻዎች ት. እና ቃ.
፲፭ ተመልከቱ።

ላይ ስለሆነ፣ በስልጣን እና በሀይል እናገርሀለሁ።

፫ ከእኔ እና ከአንተ ብቻ በቀር ማንም ሰው የማያውቀውን ነገር እነግርሀለሁ—

፬ ስለሆነ ብዙ ጊዜ ለአንተ ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ምን እንደሆነ ከእኔ ለማወቅ ፈልገሀል።

፭ እነሆ፣ ስለ እነዚህ ነገሮች፣ እናም የሰጠሁህን ቃላቴን በትእዛዛቴ መሰረት ስለተናገርክ የተባረክ ነህ።

፮ እናም አሁን፣ እነሆ እንዲህ እልሀለሁ፣ ለአንተ ታላቅ ዋጋ ያለው፣ ነፍሳትን ወደ እኔ ታመጣ ዘንድ፣ ከእነርሱ ጋር በአባቴ መንግስት ታርፍ ዘንድ፣ ለዚህ ህዝብ ንስሀን ማወጅ ይሆናል። አሜን።

ክፍል ፲፯

ሰኔ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የመፅሐፈ ሞርሞንን ታሪክ የተቀረጸበትን ሰሌዳዎች ከማየታቸው በፊት ለኦሊቨር ካውድሪ፣ ዴቪድ ዊትመር እና ማርቲን ሀሪስ የተሰጠ ራዕይ። ጆሴፍ ስሚዝ እና ጸሀፊው፣ ኦሊቨር ካውድሪ፣ ሶስት ልዩ ምስክሮች እንደሚመረጡ ከመፅሐፈ ሞርሞን ሰሌዳ ትርጉም ተገንዝበው ነበር (ኤተር ፭፥፪–፬፤ ፪ ኔፊ ፲፩፥፫፤ ፳፯፥፲፪ን ተመልከቱ)። ኦሊቨር ካውድሪ፣ ዴቪድ ዊትመር እና ማርቲን ሀሪስ በልዩ መሻት በመነሳሳት ሶስቱ ምስክሮች መሆንን ፈልገው ነበር። ነቢዩ ጌታን ጠየቀ፣ እናም ይህ ራዕይ በኡሪም እና ቱሚም አማካይነት የተሰጠ መልስ ነበር።

፩–፬፣ ሰሌዳዎቹ እና ሌሎች የተቀደሱ ነገሮችን ሶስቱ ምስክሮች በእምነት ይመለከታሉ፤ ፭–፱፣ ስለ መፅሐፈ ሞርሞን መለኮታዊነት ክርስቶስ ምስክርነቱን ሰጠ።

፩ እነሆ፣ በቃሌ ላይ መደገፍ አለባችሁ እላችኋለሁ፣ ዓላማም በተሞላበት ልብ ካደረጋችሁ፣ [ሀ]ሰሌዳዎቹን፣ እንዲሁም ጥሩርን፣ [ለ]የላባንን ሰይፍ፣ ከጌታ ጋር [ሐ]ፊት ለፊት በተነጋገርንበት ጊዜ ለያሬድ [መ]ወንድም የተሰጡትን [ሠ]ኡሪም እና ቱሚም፣ እናም [ረ]በቀይ ባህር ዳርቻ በምድረበዳ ለሌሒ የተሰጠውን [ሰ]ተዓምረኛ ጠቋሚ [ሸ]ትመለከታላችሁ።

፪ እናም እነርሱን የምትመለከቱት በእምነታችሁ፣ እንዲሁም ጥንታዊ ነቢያት በነበራቸው አይነት እምነት ነው።

፫ እምነት ካገኛችሁ እና በአይኖቻችሁ ካያችኋቸው በኋላ በእግዚአብሔር ሀይል ስለእነርሱ [ሀ]ትመሰክራላችሁ፤

፬ እናም አገልጋዩ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እንዳይጠፋ ዘንድ፣ በዚህ ስራ ለሰው ልጆች የጽድቅ አላማዬን አመጣ ዘንድ ይህንን ታደርጋላችሁ።

፭ እናም አገልጋዩ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እንደተመለከታቸው ሁሉ፤ እናንተም እንዲሁ እንደተመለከታችሁ ትመሰክራላችሁ፣ እናም እርሱም የተመለከታቸ

፲፯ ፩ ሀ ሞር. ፮፥፮፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፶፪።
ቅ.መ.መ. ሰሌዳዎች።
ለ ፩ ኔፊ ፬፥፰–፱፤
፪ ኔፊ ፭፥፲፬፤
ያዕቆ. ፩፥፲፤
ሞዛያ ፩፥፲፮።
ሐ ዘፍጥ. ፴፪፥፴፤
ዘፀአ. ፴፫፥፲፩፤ ሙሴ ፩፥፪።
መ ኤተር ፫።
ሠ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።
ረ ፩ ኔፊ ፪፥፭።
ሰ ፩ ኔፊ ፲፮፥፲፣ ፲፮፣ ፳፮–፳፱፤
አልማ ፴፯፥፴፰–፵፯።
ሸ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲፪፤
ኤተር ፭፥፪–፬፤
ት. እና ቃ. ፭፥፲፭።
ደግሞም በመፅሐፈ ሞርሞን የመጀመሪያ ገጾች ውስጥ “የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት”ን ተመልከቱ።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. መመስከር፤ ምስክር።

ውም በእኔ ኃይል ነው፣ ምክንያቱም እምነት ስለነበረው ነበር።

፮ እና እርሱም [ሀ]መፅሐፍን፣ እንዲሁም እኔ ያዘዝኩትን [ለ]ክፍል፣ ተርጉሟል፣ እናም ጌታ እና አምላካህ ህያው እንደሆነ ይህም እውነት ነው።

፯ ስለዚህ ልክ እንደ እርሱ አንድ አይነት ሀይል፣ እናም አንድ አይነት እምነት፣ እናም አንድ አይነት ስጦታ ተቀብላችኋል፤

፰ እናም የሰጠኋችሁን የመጨረሻ ትእዛዛቴን ከፈጸማችሁ የሲዖል [ሀ]ደጆችም አይቋቋማችሁም፣ [ለ]ጸጋዬ ለእናንተ በቂ ነውና፣ እናም በመጨራሻው ቀን [ሐ]ከፍ ትላላችሁ።

፱ እናም ለሰው ልጆች የጽድቅ አላማዬን አመጣ ዘንድ፣ እኔ [ሀ]ጌታችሁና አምላካችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ተናግሬዋለሁ። አሜን።

ክፍል ፲፰

ሰኔ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ኦሊቨር ካውድሪ፣ እና ዴቪድ ዊትመር የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩ እንዳለው፣ ይህ ራዕይ እንዲታወቅ የተደረገው “ስለአስራ ሁለት ሐዋሪያት በእነዚህ በኋለኛው ቀናት መጠራት ነበር፣ እና ደግሞም ቤተክርስቲያኗን ለመገንባት መመሪያዎችን ስለመስጠት ነበር።”

፩–፭፣ ቅዱሳን መጻህፍት ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚገነባ ያሳያሉ፤ ፮–፰፣ አለም በኃጢአት እየበሰለ ነው፤ ፱–፲፮፣ የነፍሳት ዋጋ ታላቅ ነው፤ ፲፯–፳፭፣ ደህንነትን ለማግኘት ሰዎች የክርስቶስን ስም በላያቸው ላይ መውሰድ አለባቸው፤ ፳፮–፴፮፣ የአስራ ሁለቱ ጥሪ እና ተልዕኮ ተገልጧል፤ ፴፯–፴፱፣ ኦሊቨር ካውድሪ እና ዴቪድ ዊትመር አስራ ሁለቱን መፈለግ ይገባቸዋል፤ ፵–፵፯፣ ደህንነትን ለማግኘት ሰዎች ንስሀ መግባት፣ መጠመቅ፣ እና ትእዛዛቶቹን መጠበቅ አለባቸው።

፩ አሁን፣ እነሆ፣ አንተ አገልጋዬ፣ ኦሊቨር ካውድሪ ከእኔ ለማወቅ በምትሻው ነገር ምክንያት፣ እነዚህን ቃላት ለአንተ እሰጥሀለሁ፥

፪ እነሆ፣ አንተ የጻፍካቸው ነገሮች [ሀ]እውነት እንደሆኑ፣ በብዙ አጋጣሚ በመንፈሴ ገልጬልሀለሁ፤ ስለዚህም እውነት እንደሆኑ ታውቃለህ።

፫ እናም እውነት እንደሆኑ ካወቅህ፣ እነሆ፣ [ሀ]በተጻፉት ላይ እንድትደገፍ፣ ትእዛዛትን ለአንተ እሰጥሀለሁ፤

፬ ስለሆነ በውስጣቸው የቤተክርስቲያኔን፣ [ሀ]የወንጌሌን፣ እና [ለ]የአለቴን መሰረት በተመለከተ ሁሉም ነገሮች ተጽፈዋል።

፭ ስለዚህ፣ በወንጌሌ እና በአለቴ መሰረት ላይ ቤተክርስቲያኔን ከገንባህ የሲዖል ደጆችም አይቋቋሙህም።

፮ እነሆ፣ [ሀ]አለም በኃጢአት እየበሰለ ነው፣ እናም የሰው ልጆች፣ [ለ]አሕዛብ እና ደግሞም የእስራኤል ቤት፣ ለንስሀ መነሳሳት አለባቸው።

፮ሀ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ለ ፪ ኔፊ ፳፯፥፳፪፤
፫ ኔፊ ፳፮፥፯–፲።
፰ሀ ማቴ. ፲፮፥፲፰፤
፫ ኔፊ ፲፩፥፴፱፤
ት. እና ቃ. ፲፥፷፱።
ለ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፯፤
፫ ኔፊ ፳፯፥፲፬–፲፭፣ ፳፪፤
ት. እና ቃ. ፱፥፲፬።
፱ሀ ቅ.መ.መ. ጌታ።
፲፰ ፪ሀ ት. እና ቃ. ፮፥፲፭–፲፯።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፺፰፥፲፩።
ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሣት መጻህፍት ዋጋዎች።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ቅ.መ.መ. አለት።
፮ሀ ቅ.መ.መ. አለም።
ለ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።

፯ ስለዚህ፣ እኔ ባዘዝኩት መሰረት በአገልጋዬ በጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እጅ [ሀ]እን ደተጠመቅህ ሁሉ፣ ያዘዝኩትን ነገር ፈጽሚል።

፰ በእኔ ለሚታወቀው አላማ፣ ለአላማዬ ስለጠራሁት አትደነቅ፤ ስለዚህ፣ ትእዛዛቴን [ሀ]በመጠበቅ [ለ]ትጉህ ከሆነ፣ በዘለአለም ህይወት [ሐ]ይባረካል፤ ስሙም [መ]ጆሴፍ ነው።

፱ እናም አሁን፣ በትእዛዝ መልክ ለአንተ ለኦሊቨር ካውድሪ እናም እንዲሁም ለዴቪድ ዊትመር እናገራለሁ፤ ስለሆነም፣ እነሆ፣ በሁሉም ስፍራ ሁሉም ሰዎች ንስሀ እንዲገቡ አዝዛለሁና፣ እናም እርሱ በተጠራበት ጥሪ ስለተጠራችሁ እንደ [ሀ]ኃዋሪያዬ ጳውሎስ እናገራችኋለሁ።

፲ [ሀ]የነፍስ [ለ]ዋጋ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ እንደሆነ አስታውሱ፤

፲፩ ስለሆነም፣ እነሆ ጌታ [ሀ]አዳኛችሁ የስጋ [ለ]ሞትን ሞተ፤ ስለዚህ ሰዎች ንስሀ ገብተው ወደ እርሱ ይመጡ ዘንድ የሰዎችን ሁሉ [ሐ]ህመም [መ]ተሰቃየ።

፲፪ እናም [ሀ]በንስሀ ብቻ ሰዎችን ሁሉ ወደ እርሱ ያመጣ ዘንድ፣ ከሞት ዳግም [ለ]ተነሳ።

፲፫ እናም ንስሀ በሚገባ ነፍስ [ሀ]ደስታው እንዴት ታላቅ ነው!

፲፬ ስለዚህ፣ ለዚህ ህዝብ ንስሀን [ሀ]እንድትጮሁ ተጠርታችኋል።

፲፭ እናም በቀኖቻችሁ ሁሉ ንስሀን ወደ እነዚህ ህዝብ በመጮህ ብታገለግሉ፣ እናም አንድም ነፍስ ቢሆን እንኳን ወደ እኔ ዘንድ ብታመጡ፣ በአባቴ መንግስት ከእርሱ ጋር [ሀ]ደስታችሁ እንዴት ታላቅ ይሆናል!

፲፮ እናም አሁን፣ ወደ አባቴ [ሀ]መንግስት ባመጣችሁት አንድ ነፍስ ደስታችሁ ታላቅ ከሆነ፣ ወደ እኔ ብዙ ነፍሳትን [ለ]ብታመጡ [ሐ]ደስታችሁ ምን ያህል ታላቅ ይሆናል!

፲፯ እነሆ፣ ወንጌሌ፣ እና አለቴ፣ እናም [ሀ]ማዳኔም በፊታችሁ ነው።

፲፰ እንደምትቀበሉ በማመን በእምነት አባቴን [ሀ]በስሜ [ለ]ጠይቁ፣ እናም ለሰው ልጆች [ሐ]አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ የሚገልጠው መንፈስ ቅዱስ ይኖራችኋል።

፲፱ እናም [ሀ]እምነት፣ [ለ]ተስፋ፣ እናም [ሐ]ለጋስነት ከሌላችሁ፣ ምንም ነገር ማድረግ አትችሉም።

፳ [ሀ]የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን ካልሆነ በስተቀር ከማንም ቤተክርስቲያን ጋር [ለ]አትከራከሩ።

፳፩ የክርስቶስ [ሀ]ስም በላያችሁ ላይ ውሰዱ እናም እውነትን [ለ]በቅንነት [ሐ]ተናገሩ።

፳፪ እናም ስሜ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉ ንስሀ የሚገቡና [ሀ]የሚጠመቁ እናም እስከመጨረሻው ድረስ [ለ]የሚጸኑ፣ እንዲሁ ይድናሉ።

፯ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፷–፸፩።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ሐ ቅ.መ.መ. መባረክ፣
የተባረከ፣ በረከት።
መ ፪ ኔፊ ፫፥፲፬–፲፭።
ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ጆሴፍ ዳግማዊ።
፱ ሀ ሮሜ ፩፥፩።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ነፍስ።
ለ ቅ.መ.መ. ነፍስ—
የነፍሶች ዋጋ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
ለ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
ሐ ኢሳ. ፶፫፥፬–፭።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
መ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣
ማዳን፣ ቤዛነት።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፥፬–፲፰።
ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፫ ሀ ሉቃ. ፲፭፥፯።
፲፬ ሀ አልማ ፳፱፥፩–፪፤
ት. እና ቃ. ፴፬፥፭–
፮፤ ፳፫፥፶፯።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ነፍስ—
የነፍሶች ዋጋ።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
ሐ አልማ ፳፮፥፲፩።
ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፲፰ ሀ ዮሐ. ፲፭፥፲፮።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፫–፷፭።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ሐ ቅ.መ.መ. ልግስና።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—
የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
ለ ፪ ጢሞ. ፪፥፳፫–፳፬፤
፫ ኔፊ ፲፩፥፳፱–፴።
፳፩ ሀ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፫፤
ሞዛያ ፭፥፰፤
፫ ኔፊ ፳፯፥፭፤
ት. እና ቃ. ፳፥፴፯።
ለ ሮሜ ፲፪፥፫።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፥፭–፰።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ለ ቅ.መ.መ. መፅናት።

፳፫ እነሆ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ የተሰጠ [ሀ]ስም ነው፣ እናም ሰው ሊድንበት የሚችል የተሰጠ ሌላ ስም የለምና፤

፳፬ ስለዚህ ይህን፣ ከአብ የተሰጠውን ስም ሁሉም ሰዎች በራሳቸው ላይ ሊወስዱ ይገባል፣ በመጨረሻውም ቀን በዚያ ስም ይጠራሉና፤

፳፭ ስለዚህ፣ የሚጠሩበትን [ሀ]ስም የማያውቁ ከሆነ፣ በአባቴ [ለ]መንግስት ስፍራ ሊኖራቸው አይችልም።

፳፮ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ለአይሁድ እና [ሀ]ለአህዛብ ወንጌሌን እንዲያውጁ የተጠሩ ሌሎች አሉ።

፳፯ አዎን፣ እንዲሁም አስራ ሁለቱ፤ እናም [ሀ]አስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርቴ ይሆናሉ፣ እናም በላያቸው ላይ [ለ]ስሜን ይወስዳሉ፤ እናም አስራ ሁለቱም ዓላማ በተሞላ ልብ ስሜን በላያቸው ለመውሰድ ፈቃድ ያላቸው ናቸው።

፳፰ እናም አላማ በተሞላ ልብ ስሜን በላያቸው ላይ ሊወስዱ ፈቃድ ካላቸው፣ ወደ [ሀ]አለም ሁሉ በመሄድ [ለ]ወንጌሌን [ሐ]ለፍጥረታት ሁሉ ለማወጅ ተጠርተዋል።

፳፱ እናም በተጻፈው መሰረት በስሜ [ሀ]ለማጥመቅ የተሾሙት እነርሱ ናቸው፤

፴ እናም የተጻፈው በፊታችሁ አለላችሁ፤ ስለዚህ፣ በተጻፉት ቃላት መሰረት ልታከናውኑት ይገባል።

፴፩ እናም ለእናንተ [ሀ]ለአስራ ሁለቱ እናገራለሁ—እነሆ፣ ጸጋዬ ለእናንተ በቂ ነው፤ በፊቴ በቅንነት ተራመዱ እናም ኃጢአትንም አታድርጉ።

፴፪ እናም፣ እነሆ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ እናም እግዚአብሔር ለሰዎች በሰጠው [ሀ]ጥሪ እና ስጦታ [ለ]መሰረት ካህናትን እና መምህራንን [ሐ]እንድትሾሙ፣ እና ወንጌሌንም እንድታውጁ ዘንድ፣ በእኔ የተሾማችሁት እናንተ ናችሁ፤

፴፫ እናም እኔ፣ ጌታችሁ እና አምላካችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ተናግሬዋለሁ።

፴፬ እነዚህ [ሀ]ቃላት የእኔ እንጂ የሰው ወይም የሰዎች አይደሉም፤ ስለዚህ፣ የሰው እንዳልሆኑ እናም የእኔ እንደሆኑ ትመሰክራላችሁ፤

፴፭ ለእናንተ እነዚህን የሚናገራችሁ [ሀ]ድምፄ ነው፤ ለእናንተም የተሰጧችሁ በመንፈሴ ነው፣ እናም በኃይሌም አንዳችሁ ለሌላኛችሁ ልታነቧቸው ትችላላችሁ፤ እናም በሀይሌ ካልሆነ በስተቀር እነርሱ ሊኖሯችሁ ባትችሉም ነበር፤

፴፮ ስለዚህ፣ ድምፄን እንደሰማችሁ እና ቃላቴን እንደምታውቁ [ሀ]መመስከር ትችላላችሁ።

፴፯ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ለአንተ ለኦሊቨር ካውድሪ እና እንዲሁም ለዴቪድ ዊትመር የተናገርኩት ነገር ፈቃድ ያላቸውን አስራ ሁለቱን ኃዋሪያት እንድትፈልጉ ኃላፊነትን ሰጥቻችኋለሁ፤

፴፰ እናም በፍላጎታቸው እና [ሀ]በስራቸው ታውቋቸዋላችሁ።

፴፱ እናም ባገኛችኋቸው ጊዜ እነዚህ ነገሮች ታሳይዋቸዋላችሁ።

፵ እናም ትሰግዳላችሁ እናም አባቴን በስሜ [ሀ]ታመልካላችሁ።

፵፩ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ንስሀ ሊገቡ እንደሚገባ እና መጠመቅም እንዳለባቸው በማለት ለአለም መስበክ ይኖርባችኋል፤

፵፪ ሁሉም ወንዶች ንስሀ መገባት እና

፳፫ ሀ ሚል. ፩፥፲፩፤
የሐዋ. ፬፥፲፪፤
ሞዛያ ፫፥፲፯፤
ሔለ. ፫፥፳፰–፳፱።
፳፭ ሀ ሞዛያ ፭፥፱–፲፬።
ለ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፺፥፰–፱፤ ፻፲፪፥፬።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
ለ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፪።
፳፰ ሀ ማር. ፲፮፥፲፭–፲፮።
ለ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፥፪፤ ፵፪፥፶፰።
፳፱ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፳፩–፳፰፤
ት. እና ቃ. ፳፥፸፪–፸፬።
፴፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፳፫–፴፭።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፳፯።
ለ ፪ ጴጥ. ፩፥፳፩፤
ት. እና ቃ. ፷፰፥፫–፬።
ሐ ሞሮኒ ፫፤
ት. እና ቃ. ፳፥፷፤ ፻፯፥፶፰።
ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
፴፭ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፴፰።
ቅ.መ.መ. ድምፅ።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. መመስከር።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
፵ ሀ ቅ.መ.መ. ማምለክ።

መጠመቅ አለባቸው እናም ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ ነገር ግን ሴቶች፣ እናም [ሀ]ለተጠያቂነት እድሜ የደረሱ ልጆች ሁሉ ንስሀ መግባት እና መጠመቅ አለባቸው።

፵፫ እናም፣ አሁን፣ ይህንን ከተቀበላችሁ በኋላ፣ በሁሉም ነገሮች [ሀ]ትእዛዛቴን መጠበቅ አለባችሁ።

፵፬ እናም፣ ወደ ንስሀ እንዲመጡ ብዙ ኃጢዓቶቻቸውንም [ሀ]በማሳመን፣ ወደ አባቴ መንግስት ይመጡ ዘንድ፣ በእጃችሁ [ለ]ድንቅ ስራን በሰዎች ልጆች መካከል እሰራለሁ።

፵፭ ስለዚህ፣ የምሰጣችሁ በረከቶች ከሁሉም ነገሮች [ሀ]በላይ ናቸው።

፵፮ እናም ይህን ነገር ከተቀበላችሁ በኋላ፣ ትእዛዛቴን [ሀ]የማትጠብቁ ከሆነ በአባቴ መንግስት አትድኑም።

፵፯ እነሆ፣ እኔ፣ ጌታችሁ እና አምላካችሁ እና አዳኛችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈሴ ሀይል ይህን ተናግሬዋለሁ። አሜን።

ክፍል ፲፱

በበጋ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) አካባቢ በማንቼስተር ኒው ዮርክ በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የተሰጠ ራዕይ። በታሪኩ ውስጥ፣ ነቢዩ ይህን “ለማርቲን ሀሪስ በሰው ሳይሆን ዘለአለማዊ በሆነው በእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝ” ብሎ አስተዋወቀ።

፩–፫፣ ክርስቶስ ሁሉም ስልጣን አለው፤ ፬–፭፣ ሰዎች ሁሉ ንስሀ መግባት አለባቸው ወይም ይሰቃያሉ፤ ፮–፲፪፣ ዘለአለማዊ ቅጣት የእግዚአብሔር ቅጣት ነው፤ ፲፫–፳፣ ንስሀ ቢገቡ እንዳይሰቃዩ ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ ተሰቃየ፣ ፳፩–፳፰፣ የንስሀን ወንጌል ስበክ፤ ፳፱–፵፩፣ የምስራችን ቃል አውጅ።

፩ እኔ [ሀ]አልፋና ኦሜጋ፣ ጌታ [ለ]ክርስቶስ ነኝ፤ አዎን፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እናም የአለም ቤዛ የሆንኩት እኔ ነኝ።

፪ ነገሮችን ሁሉ ለእኔ [ሀ]ይገዙ ዘንድ ይህንንም በማድረግ፣ የእርሱ የሆንኩት አብ ለእኔ ያለውን ፈቃድ አከናውኛለሁ እናም [ለ]ጨረሻለሁ፤

፫ ሰይጣንን እና ስራዎቹን በአለም [ሀ]ፍጻሜ [ለ]ለማፍረስ፣ እና እያንዳንዱን ሰው [ሐ]በተግባሩ መሰረት [መ]በመፍረድ በዚያ በሚኖሩት ላይ እንድፈርድባቸው ዘንድ [ሠ]ሀይልን እና የመጨረሻ ታላቅ የቅጣት ቀንን በመያዝ የአብን ፈቃድ አከናውናለሁ።

፬ እናም እያንዳንዱ ሰው [ሀ]ንስሀ መግባት አለበት ወይም [ለ]ይሰቃያል፤ እኔ እግዚአብሔር [ሐ]መጨረሻ የለኝምና።

፭ ስለዚህ የማሳልፈውን ፍርድ [ሀ]አልሽርም፣ ነገር ግን፣ አዎን፣ [ለ]በግራዬ ለሚሆኑት ዋይታ፣ [ሐ]ልቅሶ እና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፸፩፤
፳፱፥፵፯፤ ፷፰፥፳፯።
ቅ.መ.መ. መልስ
መስጠት፣ ሂሳብ፣
ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ትእዛዛት።
፵፬ ሀ አልማ ፴፮፥፲፪–፲፱፤
፷፪፥፵፭።
ለ ኢሳ. ፳፱፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፬፥፩።
፵፭ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፭–፴፰።
፵፮ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፫።

፲፱ ፩ሀ ራዕ. ፩፥፰፣ ፲፩፤
፫ ኔፊ ፱፥፲፰፤
ት. እና ቃ. ፴፭፥፩፤ ፷፩፥፩።
ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
፪ሀ ዮሐ. ፲፯፥፬፤
፫ ኔፊ ፲፩፥፲፩።
ለ ፊልጵ. ፫፥፳፩።
፫ሀ ቅ.መ.መ. አለም—
የአለም መጨረሻ።
ለ ኢሳ. ፲፬፥፲፪–፲፯፤
፩ ዮሐ. ፫፥፰፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፳፮፤

ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፩–፻፲፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
መ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
ሠ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፬ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ለ ሉቃ. ፲፫፥፫፤
ሔለ. ፲፬፥፲፱።
ሐ ሙሴ ፩፥፫።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥፬፤ ፶፰፥፴፪።
ለ ማቴ. ፳፭፥፵፩–፵፫።
ሐ ማቴ. ፲፫፥፵፪።

፮ ምንም እንኳን፣ ይህ ስቃይ ማብቂያ እንደሌለው [ሀ]ባይጻፍም፣ ነገር ግን [ለ]ገደብ የለሽ ስቃይ ተብሎ ተጽፏል።

፯ ዳግም፣ [ሀ]ዘለአለማዊ ኩነኔ ተብሎ ተጽፋል፤ ስለዚህ በአንድ ላይ ለስሜ ክብር በሰዎች ልጆች ልብ ላይ ይሰራ ዘንድ ከሌሎች የቅዱስ መጻሕፍት ጽሁፎች በበለጠ ግልጽ ነው።

፰ ስለዚህ፣ ይህንን ሚስጥር ለአንተ እገልጽልኃለሁ፣ አንተም እንደ እኔ ኃዋርያቴ ታውቅ ዘንድ ስለሚገባ ነውና።

፱ አንድ ሆናችሁ ወደ [ሀ]እረፍቴ ትገቡ ዘንድ ለዚህ ስራ ለተመረጣችሁት ለእናንተ እናገራለሁ።

፲ ስለሆነም፣ እነሆ፣ የአምላክነት [ሀ]ሚስጥር እንዴት ታላቅ ነው! ስለሆነም፣ እነሆ፣ እኔ መጨረሻ የለኝም፣ እናም ከእጄ የሚሰጠው ቅጣት መጨረሻ የሌለው ቅጣት ነው፣ ስሜም [ለ]መጨረሻ የሌለውም ነውና። ስለዚህ—

፲፩ [ሀ]ዘለአለማዊ ቅጣት የእግዚአብሔር ቅጣት ነው።

፲፪ መጨረሻ የሌለው ቅጣት የእግዚአብሔር ቅጣት ነው።

፲፫ ስለዚህ፣ ንስሀ እንድትገባ እና በስሜ ከአገልጋዬ ከጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ እጅ የተቀበልካቸውን [ሀ]ትእዛዛት እንድትጠብቅ አዝኃለሁ፤

፲፬ እናም እነዚህንም በኃያሉ ኃይሌ ነው የተቀበልከው፤

፲፭ ስለዚህ ንስሀ እንድትገባ አዝሀለሁ—ንስሀ ግባ አለበለዚያ በቁጣዬ እናም በንዴቴ እናም በአፌ በትር እመታሀለሁ እናም [ሀ]ስቃይህ መራር ይሆናል—ምን ያህል መራር እንደሆነ አታውቅም፣ ምን ያህል እንደሚጎዳህ እንደሆነ አታውቀውም፣ አዎን፣ ምን ያህል ለመሸከም እንደሚከብድ አታውቀውም።

፲፮ ስለሆነም፣ እነሆ፣ [ሀ]ንስሀ ከገቡ [ለ]እንዳይሰቃዩ ዘንድ እኔ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ለሁሉም [ሐ]ተሰቃይቻለሁ፤

፲፯ ነገር ግን ንስሀ ካልገቡ እኔ እንደተሰቃየሁት [ሀ]መሰቃየት አለባቸው፤

፲፰ ይህም ስቃይ የሁሉም ታላቅ የሆንኩትን እኔን እግዚአብሔርን፣ ከስቃዩ የተነሳ እንድንቀጠቀጥ እናም ከእያንዳንዱ ቀዳዳ እንድደማ እናም በአካል እና በመንፈስ እንድሰቃይ እናም መራራውን ጽዋ [ሀ]እንዳልጠጣ እንድፈልግ እና እንድሸማቀቅ ያደረገኝን ነው።

፲፱ ሆኖም፣ ለአብ ክብር ይሁን፣ እናም ጠጥቼዋለሁ እናም ለሰዎች ልጆችም ዝግጅቴን [ሀ]ጨርሻለሁ።

፳ ስለዚህ፣ ዳግም ንስሀ እንድትገባ አዝሀለሁ፣ አለበለዚያም በኃያሉ ኃይሌ ትሁት አደርግሀለሁ፤ እናም ሰለዚህ ኃጢአትህን [ሀ]ተናዘዝ፣ አለበለዚያም የተናገርኩትን፣ አዎን፣ መንፈሴን ካንተ በወሰድኩበት ጊዜ በአነሰ ደረጃ የቀመስከውን፣ ቅጣቴን ትሰቃያለህ።

፳፩ እናም ከንስሀ በቀር ምንም [ሀ]እንዳትሰብክ አዝሀለሁ፣ እናም በእኔ ጥበብ እስኪሆን ድረስ እነዚህን ነገሮች ለአለም [ለ]እንዳታሳይ።

፳፪ ስለሆነም፣ ስጋን አሁን [ሀ]መሸከም አይችሉም፣ ነገር ግን [ለ]ወተትን መቀበል

፮ ሀ ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፭–፻፮፤
፻፴፰፥፶፱።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፴፫፣
፵፬–፵፰።
፯ ሀ ሔለ. ፲፪፥፳፭–፳፮፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥፵፬።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. እረፍት።
፲ ሀ ያዕቆ. ፬፥፰፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፲፬–፻፲፮።
ለ ሙሴ ፩፥፫፤ ፯፥፴፭።
ቅ.መ.መ. ማለቂያ የሌለው።
፲፩ ሀ ማቴ. ፳፭፥፵፮።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፪፤
፲፥፮–፯፤ ፲፯።
፲፭ ሀ አልማ ፴፮፥፲፩–፲፱።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ አልማ ፲፩፥፵–፵፩።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን
መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፯።
፲፰ ሀ ሉቃ. ፳፪፥፵፪–፵፬።
፲፱ ሀ ዮሐ. ፲፯፥፬፤ ፲፱፥፴።
፳ ሀ ዘኍል. ፭፥፮–፯፤
ሞዛያ ፳፯፥፳፱፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፵፫፤
፷፬፥፯።
ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፲፩፥፱።
ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፵፪።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፲፯–፲፰።
ለ ዕብ. ፭፥፲፩–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፶፥፵።

አለባቸው፤ ስለዚህ እንዳይጠፉ እነዚህን ነገሮች ማወቅ የለባቸውም።

፳፫ ከእኔ ተማር፣ እናም ቃላቴን አድምጥ፤ በመንፈሴ [ሀ]በትህትና [ለ]ተጓዝ፣ እናም በእኔ [ሐ]ሰላምን ታገኛለህ።

፳፬ እኔ [ሀ]ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ፣ በአብ ፈቃድ መጥቻለሁ፣ እናም ፈቃዱንም አደርጋለሁ።

፳፭ እናም ዳግም፣ የባልንጀራህን [ሀ]ሚስትም ሆነ የባልንጀራህን ህይወት [ለ]እንዳትመኝ አዝህለሁ።

፳፮ እናም ዳግም የራስህንም ንብረት እንዳትመኝ፣ ነገር ግን በለጋስነት [ሀ]እውነትን እና የእግዚአብሔርን ቃል የያዘውን መፅሐፈ ሞርሞንን ለማሳተሚያ ይሆን ዘንድ እንድትሰጥ አዝህለሁ—

፳፯ ይህ [ሀ]ለአህዛብ የተሰጠ፣ እንዲሁ በቅርቡ ላማናውያን የእነርሱ [ለ]ቅሪት በሆኑት [ሐ]አይሁዳውያን ወንጌልን ያምኑ ዘንድ እናም የመጣውን [መ]መሲህ ይመጣል ብለው እንዳይጠብቁ ወደእነርሱ የሚሄደው ቃሌ ነው።

፳፰ እናም ዳግም፣ ድምጽህን አውጥተህ፣ እንዲሁም በልብህ አዎን በአለም ፊት፣ እንዲሁም በስውር፣ በአደባባይ እንዲሁም በግል [ሀ]በድምጽ [ለ]እንድትጸልይ አዝህለሁ።

፳፱ እናም የምስራችን ቃል ታውጃለህ፣ አዎን፣ በተራራዎችም ላይ፣ እናም በሁሉም ከፍታ ስፍራዎች ላይ፣ እናም ልታያቸው በተፈቀደልህ ህዝብ መካከል ሁሉ [ሀ]ታውጃለህ።

፴ እናም፣ በእኔ [ሀ]በመታመን፣ ክፋትን ለሚናገሩህ ክፋትን ባለመናገር በሙሉ ትህትና ታደርገዋለህ።

፴፩ እናም [ሀ]የተወሳሰበ የቤተክርስቲያን ትምህርቶችን አትናገር፣ ነገር ግን ንስሀን እናም በአዳኛችን [ለ]እምነትን፣ [ሐ]በጥምቀት እናም [መ]በእሳት አዎን እንዲሁም [ሠ]በመንፈስ ቅዱስ ኃጢአት [ረ]እንደሚሰረይ አውጅ።

፴፪ እነሆ፣ ይህንን ነገር በተመለከተ የምሰጥህ ይህ ትልቅ እና የመጨረሻ [ሀ]ትእዛዝ ነው፤ ምክንያቱም ይህ ለዕለት ተዕለት እርምጃህ እስከ ህይወትህ ፍጻሜ በቂ ነው።

፴፫ እናም ይህንን [ሀ]ምክር ችላ የምትል ከሆነ ስቃይን ትቀበላለህ፣ አዎን፣ በአንተ እና በንብረትህ ላይ ቢሆን እንኳን ጥፋትን ትቀበላለህ።

፴፬ የንብረትህን ክፍል፣ አዎን፣ የምድርህን ክፍል ቢሆንም እንኳን፣ እናም ለቤተሰብህ ከሚያስፈልግህ በቀር ሁሉንም ንብረትህን [ሀ]ሽጥ።

፴፭ ከአሳታሚው ጋር የገባኸውን [ሀ]ውል [ለ]እዳ ክፈል። [ሐ]ከባርነት ራስህን ነፃ አውጣ።

፴፮ ቤተሰብህን ለማየት ስትፈልግ ካልሆነ በስተቀር ቤትህን እና መኖሪያህን [ሀ]ተው፤

፴፯ እናም በነፃነት ለሁሉም [ሀ]ተናገር፤ አዎን፣ በከፍተኛ ድምጽ ቢሆንም እንኳን፣ ሆሳዕና፣ ሆሳዕና፣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን! በማለት ስበክ፣ ምክር፣ [ለ]እውነትን አውጅ።

፴፰ ዘወትር [ሀ]ጸልይ፣ እናም መንፈሴን

፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ለ ሞሮኒ ፯፥፫–፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
፳፭ ሀ ዘፀአ. ፳፥፲፯፤
፩ ቆሮ. ፯፥፪–፬።
ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
ለ ቅ.መ.መ. መመኘት።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. እውነት።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
ለ ኦምኒ ፩፥፲፬–፲፱፤
ሞዛያ ፳፭፥፪–፬፤
ሔለ. ፰፥፳፩፤
፫ ኔፊ ፪፥፲፪–፲፮።
ሐ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
መ ቅ.መ.መ. መሲህ።
፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፵፯፣
፶፩፤ ፳፫፥፮።
ለ ፩ ጢሞ. ፪፥፰።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. መታመን።
፴፩ ሀ ፪ ጢሞ. ፪፥፳፫–፳፬።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
መ ማቴ. ፫፥፲፩።
ሠ ቅ.መ.መ. የመንፈስ
ቅዱስ ስጦታ።
ረ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፮–፳፱።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ትእዛዛት።
፴፬ ሀ የሐዋ. ፬፥፴፬–፴፭።
፴፭ ሀ ይህም ለመፅሐፈ ሞርሞን
የመጀመሪያ እትመት
መክፈል ማለት ነው።
ለ ቅ.መ.መ. እዳ።
ሐ ምሳ. ፳፪፥፯።
፴፮ ሀ ማቴ. ፲፱፥፳፱።
፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፵፯፤
፷፰፥፰፤ ፸፩፥፯።
ለ ት. እና ቃ. ፸፭፥፬።
፴፰ ሀ ሉቃ. ፲፰፥፩፤ ፪ ኔፊ ፴፪፥፱፤
ት. እና ቃ. ፲፥፭።

በአንተ ላይ [ለ]አፈሳለሁ—አዎን፣ የምድርን ሀብት እናም የሚጠፋን ነገር ሁሉ ብታገኝም እንኳን በረከትህ ከዚህ የበለጠ ታላቅ ይሆናል።

፴፱ እነሆ፣ ሳትደሰት እና ልብህን ለደስታ ሳታነሳሳ ይህን ማንበብ አትችልምን?

፵ ወይም እውር መሪ የሚሮጠውን ያህል መሮጥ አትችልምን?

፵፩ ወይም በጥበብ ራስህን በፊቴ [ሀ]ዝቅ ማድረግ እና ትሁት ማድረግ ትችላለህ? አዎን፣ ወደ እኔ ወደ አዳኝህ [ለ]ና። አሜን።

ክፍል ፳

ስለቤተክርስቲያን አደረጃጀት እና አስተዳደር፣ በፈየት፣ ኒው ዮርክ ወይም በዚያ አካባቢ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። የዚህ ራዕይ ክፍሎች የተሰጡት በበጋ ፲፰፻፳፱ (እ.አ.አ.) አካባቢ ሳይሆን አይቀርም። በዚያ ጊዜ አንቀጾች እና ቃል ኪዳኖች ተብሎ የሚታወቀው ሙሉ ራዕዩ የተመዘገበው በሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴ (ቤተክርስቲያኗ በተደራጀችበት ቀን) ሳይሆን አይቀርም። ነቢዩ እንደጻፈው፥ “በትንቢት እና ራዕይ መንፈስ ከእርሱ [ከኢየሱስ ክርስቶስ] የሚከተለውን ተቀበልን፤ ይህም ብዙ መረጃዎችን ብቻ ሳይሆን የሰጠን፣ ነገር ግን እንደ እርሱ ፈቃድ እና ትእዛዝ መቼ የእርሱን ቤተክርስቲያን ዳግም በምድር ላይ ማቋቋም እንደሚገባን ጠቁሞናል።”

፩–፲፮፣ መፅሐፈ ሞርሞን የኋለኛው ቀን ስራን መለኮታዊነት ያረጋግጣል፤ ፲፯–፳፰፣ የፍጥረት፣ የውድቀት፣ የኃጢአት ክፍያ፣ እናም የጥምቀት ትምህርቶች ተረጋግጠዋል፤ ፳፱–፴፯፣ ንስሀ፣ መፅደቅን፣ ቅድስናን፣ እና ጥምቀትን የሚያስተዳድሩ ህጎች ተገልጸዋል፤ ፴፰–፷፯፣ የሽማግሌዎች፣ የካህናት፣ የመምህራን፣ እናም የዲያቆናት ሀላፊነቶች በአጭር ተጠቃለዋል። ፷፰–፸፬፣ የአባላት ሀላፊነቶች፣ ልጆችን መባረክ፣ እና ጥምቀት የሚከናወንበትም ዘዴዎች ተገልጠዋል፤ ፸፭–፹፬፣ የቅዱስ ቁርባን ጸሎቶች እና የቤተክርስቲያን አባልነትን ማስተዳደሪያ ደንቦች ተሰጥተዋል።

፩ በእነዚህ በኋለኞቹ ቀናት የክርስቶስ [ሀ]ቤተክርስቲያን [ለ]መነሳት፣ ጌታችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ አመት ሲሆን፣ ቤተክርስቲያኗም በእግዚአብሔር ፈቃድ እና ትእዛዝ ሚያዝያ በሚባለው በአራተኛው ወር በስድስተኛው ቀን ለአገራችን ህግ ዘወትር ተስማሚ በሚሆን ሁኔታ [ሐ]ተደራጅታ ተመስርታለች—

፪ እነዚህም ትእዛዛት የተሰጡት በእግዚአብሔር [ሀ]ለተጠራው፣ እና የዚህች ቤተክርስቲያን መጀመሪያ [ለ]ሽማግሌ በመሆን የኢየሱስ ክርስቶስ [ሐ]ሐዋርያ እንዲሆን ለተሾመው ለጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ ነበር፤

፫ እናም በእግዚአብሔር፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ሀዋሪያ፣ የዚህች ቤተክርስቲያን ሁለተኛ ሽማግሌ እንዲሆን ለተጠራው እና በእርሱ እጅ ለተሾመው ለኦሊቨር ካውድሪ ነው፤

፴፰ለ ምሳ. ፩፥፳፫፤ የሐዋ. ፪፥፲፯።

፵፩ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።

ለ ማቴ. ፲፩፥፳፰–፴።

፳ ፩ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፥፩–፰። ቅ.መ.መ. የቤተክርስቲያን ስም፤ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።

ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፪።

ሐ ት. እና ቃ. ፳፩፥፫።

፪ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።

ለ ቅ.መ.መ. ስልጣን፤ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።

ሐ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።

፬ ይህም እንደጌታችን እና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ነው፣ ለእርሱም አሁንም ለዘለዓለምም ክብር ይሁን። አሜን።

፭ ይህ የመጀመሪያው ሽማግሌ የኃጢአት ስርየት እንደተቀበለ በእውነት ከተገለጸለት በኋላ፣ በአለም ከንቱነት ውስጥ ደግሞም [ሀ]ተጠላለፈ፤

፮ ነገር ግን ንስሀ ከገባ፣ እናም በእምነት እራሱን በቅንነት ትሑት ካደረገ በኋላ፣ [ሀ]መልኩ እንደ መብረቅ ብሩህ፣ እናም ልብሱ ከንጣቶች ሁሉ በላይ ንጹ እና ነጭ በነበረው ቅዱስ [ለ]መልአክ በኩል እግዚአብሔርም አገለገለው፤

፯ እና ያነሳሱትን ትዕዛዛትንም ሰጠው፤

፰ እናም መፅሐፈ ሞርሞንን ለመተርጎም ቀደም ብሎ በተዘጋጁት [ሀ]መንገዶች በኩል ከላይ ሀይልን ሰጠው፤

፱ ይህም የወደቁትን ሰዎች መዝገብ፣ እናም ለአህዛብና ለአይሁድ ሁሉ [ሀ]ሙሉ የኢየሱስ ክርስቶስን [ለ]ወንጌል የያዘ ነው፤

፲ በሚያነሳሳ መንፈስ የተሰጠ፣ እናም በመላእክት አገልግሎት [ሀ]ለሌሎችም የተረጋገጠ፣ እና በእነርሱም ለአለምም [ለ]የተገለጸ ነው—

፲፩ ይህ ቅዱሳን መጻህፍት [ሀ]እውነት እንደሆነ እናም በዚህ እድሜና ዘመን እንደ ቀደሙት ትውልዶችም እግዚአብሔር የእርሱን ቅዱስ [ለ]ስራ እንዲያከናውኑ ሰዎችን [ሐ]እንደሚያነሳሳ እና እንደሚጠራ በማረጋገጥ ነው።

፲፪ በዚህም እርሱ ትላንትናም ዛሬም እናም ለዘለአለም [ሀ]አንድ አይነት አምላክ እንደሆነ በማሳየት ነው። አሜን።

፲፫ ስለዚህም፣ በጣም ታላቅ ምስክርነቶች ስላሏቸው፣ ዓለም ሁሉ፣ እንዲሁም ከዚህ በኋላ ወደዚህ እውቀት የሚመጡት ሁሉ፣ በእነርሱ ይፈረድባቸዋል።

፲፬ እናም በእምነት የሚቀበሉት ሁሉ፣ እናም [ሀ]ፅድቅን የሚሰሩ፣ የዘለአለማዊ ህይወት [ለ]አክሊልን ይቀበላሉ፤

፲፭ ነገር ግን [ሀ]ባለማመን ልባቸውን የሚያደነድኑ፣ እናም ለሚያስወግዱት፣ ወደ ኩነኔያቸው ይለወጣል—

፲፮ ጌታ እግዚአብሔር ተናግሮታልና፣ እናም እኛ የቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች፣ በላይ ያለውን የከበረ ግርማዊ ቃላቶቹን ሰምተናል እናም ምስክርነታችንን እንሰጣለን፣ ለእርሱም ክብር ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ይሁን። አሜን።

፲፯ በእነዚህ ነገሮች መጨረሻ የሌለውና ዘለአለማዊ የሆነው፣ ሰማይና ምድርን እናም በውስጣቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረ ከዘለአለም እስከዘለአለም ያው የሆነ የማይቀየር አምላክ [ሀ]እግዚአብሔር በሰማይ ውስጥ እንደሚገኝ [ለ]እናውቃለን፤

፲፰ እርሱም ሰውን፣ ወንድና ሴትን፣ [ሀ]በመልኩ እና በአምሳሉ [ለ]ፈጠራቸው፤

፲፱ እናም እውነተኛውን እና ህያው የሆነውን እግዚአብሔርን ብቻ [ሀ]እንዲወዱና [ለ]እንዲያገለግሉ እናም [ሐ]የሚያመልኩት

፭ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፳፰–፳፱።

፮ ሀ ማቴ. ፳፰፥፪–፫።

ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴–፴፭። ቅ.መ.መ. መላእክት።

፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።

፱ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፬።

ለ ቅ.መ.መ. ወንጌል።

፲ ሀ ሞሮኒ ፯፥፳፱–፴፪፤ ት. እና ቃ. ፭፥፲፩።

ለ በመፅሐፈ ሞርሞን የመጀመሪያ ገጾች ውስጥ “የሶስቱ ምስክሮች ምስክርነት”ን እና “የስምንቱ ምስክሮች ምስክርነት”ን ተመልከቱ።

፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሣት መጻህፍት ዋጋዎች።

ለ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።

ሐ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት።

፲፪ ሀ ዕብ. ፲፫፥፰፤ ፩ ኔፊ ፲፥፲፰–፲፱፤ ሞር. ፱፥፱–፲፤ ት. እና ቃ. ፴፭፥፩፤ ፴፯፥፩–፬።

፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።

ለ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት፤ የዘለዓለም ህይወት።

፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።

፲፯ ሀ ኢ.ያ. ፪፥፲፩። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።

ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፳፪–፳፫።

፲፰ ሀ ዘፍጥ. ፩፥፳፮–፳፯፤ ሞዛያ ፯፥፳፯፤ ኤተር ፫፥፲፬–፲፯።

ለ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።

፲፱ ሀ ዘዳግ. ፲፩፥፩፤ ማቴ. ፳፪፥፴፯፤ ሞሮኒ ፲፥፴፪፤ ት. እና ቃ. ፶፱፥፭–፮።

ለ ዘዳግ. ፮፥፲፫–፲፭። ቅ.መ.መ. አገልግሎት።

ሐ ቅ.መ.መ. ማምለክ።

እርሱን ብቻ እንዲሆንም ትእዛዛትን ሰጣቸው።

፳ ነገር ግን እነዚህን ቅዱስ ህጎችን በመተላለፍ ሰው [ሀ]ስጋዊና [ለ]አጋንንታዊ ሆነ፣ እናም [ሐ]የወደቀ ሆኑ።

፳፩ ስለዚህ፣ ለእርሱ በሰጠው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ስለእርሱ እንደተጻፈው፣ ሁሉን የሚገዛው እግዚአብሔር [ሀ]አንድያ ልጁን ሰጠ።

፳፪ እርሱም [ሀ]በፈተናዎች ተሰቃየ ነገር ግን እራሱን አሳልፎ አልሰጠም።

፳፫ እርሱም [ሀ]ተሰቀለ፣ ሞተ፣ እናም በሶስተኛውም ቀን ዳግም ከሞት [ለ]ተነሳ፤

፳፬ እናም [ሀ]በአብ ቀኝ በኩል ለመቀመጥ፣ እና እንደአብ ፈቃድ በፍጹም ሀይል ለመንገስ ወደሰማይ [ለ]አረገ፤

፳፭ ይህም በእርሱ ቅዱስ ስም [ሀ]አምነው እና ተጠምቀው፣ እናም እስከመጨረሻም ድረስ በእምነት [ለ]የጸኑት ሁሉ ይድኑ ዘንድ ነው—

፳፮ በስጋ ከመጣበት [ሀ]ከመካከለኛው ዘመን በኋላ የሚያምኑት ብቻ ሳይሆን፣ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ፣ እንዲሁም ከመምጣቱ አስቀድሞ፣ በመንፈስ ቅዱስ [ለ]ስጦታ ተነሳስተው [ሐ]ቅዱሳን ነቢያት ስለእርሱ በሁሉም ነገሮች [መ]በመመስከር በተናገሯቸው ቃላት ያመኑት ሁሉ ዘለአለማዊ ህይወትን ያገኛሉ፣

፳፯ ስለአብና ወልድ [ሀ]በሚመሰክረው መንፈስ ቅዱስ በኩል በሚመጡት በእግዚአብሔር [ለ]ስጦታዎች እና ጥሪዎች የሚያምኑት ከእርሱ በኋላ የሚመጡትም እንዲሁም ይሆንላቸዋል፤

፳፰ አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅዱስ መጨረሻ የሌላቸውና ዘለአለማዊ [ሀ]አንድ አምላክ ናቸው። አሜን።

፳፱ እናም ሁሉም ሰው [ሀ]ንስሀ መግባትና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም [ለ]ማመን፣ እናም አብን በእርሱ ስም ማምለክ፣ እናም በስሙ እስከፍጻሜው መጽናት እንዳለባቸው እናውቃለን፣ ወይም በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ [ሐ]መዳን አይችሉም።

፴ እናም በጌታችንና አዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ [ሀ]ጸጋ በኩል የምናገኘው [ለ]ፅድቅ ፍትሀዊ እና እውነተኛ እንደሆነ እናውቃለን፤

፴፩ እናም በጌታችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ በኩል የሚገኘው [ሀ]ቅድስና በሙሉ [ለ]ሀይላቸው፣ አዕምሮአቸው፣ እናም ጉልበታቸው እግዚአብሔርን ወድደው ለሚያገለግሉት ሁሉ ትክክል እና እውነተኛ እንደሆነ እናውቃለን።

፴፪ ነገር ግን ሰው ከጸጋ [ሀ]ወድቆ ከህያው እግዚአብሔር ለመለየት የሚያስችለው ሁኔታም አለ፤

፴፫ ስለዚህ [ሀ]በፈተና እንዳይወድቁ፣ ቤተ ክርስቲያኗ ትጠንቀቅ እና በየጊዜውም ትጸልይ፤

፴፬ አዎን፣ እንዲሁም የተቀደሱትም ቢሆኑም እንኳን ይጠንቀቁ።

፳ ሀ ቅ.መ.መ. ስሜታዊ፣ ስሜታዊነት።
ለ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሐ ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።
፳፪ ሀ ማቴ. ፬፥፩–፲፩፤ ፳፯፥፵።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ፤ የሰማይ አባት።
ለ ቅ.መ.መ. ወደ ሰማይ ማረግ።
፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፴፭፥፪፤ ፴፰፥፬፤ ፵፭፥፭፣ ፰፤ ፷፰፥፱፤ ፸፮፥፶፩–፶፫።
ለ ቅ.መ.መ. መፅናት።
፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፴፱፥፩–፫።
ለ ሙሴ ፭፥፶፰። ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ያዕቆ. ፬፥፬፤ ፯፥፲፩፤ ሞዛያ ፲፫፥፴፫።
መ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ እና ሞት ትንቢቶች።
፳፯ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፲፯።
ለ ት. እና ቃ. ፲፰፥፵፪።
፳፰ ሀ ዮሐ. ፲፯፥፳–፳፪፤ ፫ ኔፊ ፲፩፥፳፯፣ ፴፮። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሐ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ፤ ደህንነት።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ለ ቅ.መ.መ. ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ለ ዘዳግ. ፮፥፭፤ ሞሮኒ ፲፥፴፪።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ፤ ክህደት።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።

፴፭ እናም እነዚህ ነገሮች እውነተኛ እና ከዮሐንስ ራዕይ ጋር የሚግባቡ፣ [ሀ]ከቅዱስ መጻህፍቶችም፣ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ስጦታና ሀይል፣ በእግዚአብሔር [ለ]ድምጽ፣ ወይም በመላእክት አገልግሎት በኩል በሚመጡት የእግዚአብሔር ራዕዮች ላይም [ሐ]የማይጨምሩ እና የማይቀንሱ እንደሆኑ እናውቃለን።

፴፮ እናም ጌታ እግዚአብሔር ይህን ተናግሯል፤ እናም ክብር፣ ሀይል፣ እናም ግርማ ለቅዱስ ስሙ አሁን እናም ለዘለአለም ይሁን። አሜን።

፴፯ ደግሞም፣ የጥምቀትን ስርዓት በተመለከተ ለቤተክርስቲያኗ በትእዛዝ መልክ የተሰጠ—ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት ትሁት የሚያደርጉ፣ እናም [ሀ]ለመጠመቅ ከፈለጉ እናም [ለ]በተሰበረ ልብ እና በተዋረደ መንፈስ ከመጡ፣ እናም ከቤተክርስቲያኗ ፊት በእውነት ለኃጢአታቸው ሁሉ ንስሀ እንደገቡ ምስክር ካደረጉ፣ እናም እርሱን እስከመጨረሻ ድረስ ለማገልገል ፈቃድ ኖሯቸው የኢየሱስ ክርስቶስን [ሐ]ስም በራሳቸው ለመውሰድ [መ]ፈቃደኛ ከሆኑ፣ እናም የኢየሱስ ክርስቶስን መንፈስ ለኃጢአት [ሠ]ስርየት እንደተቀበሉ [ረ]በስራቸው በእውነት ካሳዩ፣ ወደ እርሱም ቤተክርስቲያን በጥምቀት ይወሰዳሉ።

፴፰ የሽማግሌዎች፣ የካህናት፣ የመምህራን፣ የዲያቆናት፣ እናም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ሀላፊነት። [ሀ]ሐዋርያ ሽማግሌ ነው፣ እናም [ለ]ማጥመቅም ለእርሱ የተሰጠ ጥሪ ነው፤

፴፱ እናም ሌሎች ሽማግሌዎችን፣ ካህናትን፣ መምህራንን፣ እናም ዲያቆናትን [ሀ]ለመሾም፤

፵ እናም የክርስቶስ ስጋና ደም ምልክቶች የሆኑትን ወይንን እና ዳቦን [ሀ]መባረክ—

፵፩ እና ቅዱሳት መጻህፍቱ እንደሚሉትም፣ ለእሳትና [ሀ]ለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት [ለ]እጆቻቸውን በመጫን ወደ ቤተክርስቲያኗ የተጠመቁትን [ሐ]ማጽናት፤

፵፪ እናም ማስተማር፣ ማብራራት፣ አጥብቆ መምከር፣ ማጥመቅ፣ እናም ቤተክርስቲያኗን መጠበቅ፤

፵፫ እናም እጆችን በመጫን ቤተክርስቲያኗንም ማጽናት፣ እናም መንፈስ ቅዱስንም መስጠት፤

፵፬ እናም በስብሰባዎች ሁሉ መሪነትን መያዝ ነው።

፵፭ ሽማግሌዎችም እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝና ራዕይ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስብሰባዎችን [ሀ]ማስተዳደር አለባቸው።

፵፮ [ሀ]የካህን ሀላፊነት መስበክ፣ [ለ]ማስተማር፣ ማብራራት፣ አጥብቆ መምከር፣ እናም ማጥመቅ፣ እናም ቅዱስ ቁርባንን መባረክ ነው፣

፵፯ እናም የእያንዳንዱን አባል ቤትን መጎብኘት፣ እናም በሚስጥር እና [ሀ]በድምፅ [ለ]እንዲጸልዩ እና [ሐ]የቤተሰብ ሀላፊነታቸውን እንዲያከናውኑ በጥብቅ ማበረታታት ነው።

፵፰ ሌሎች ካህናትን፣ መምህራንን፣ እናም ዲያቆናትን [ሀ]መሾምም ይችላል።

፵፱ እናም ሽማግሌ በሌለበትም ጊዜ ስብሰባዎችን ይመራል።

፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት።
ለ ት. እና ቃ. ፲፰፥፴፫–፴፮።
ሐ ራዕ. ፳፪፥፲፰–፲፱።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ለ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ሐ ሞዛያ ፭፥፯–፱፤ ፲፰፥፰–፲።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም
በራሳችን ላይ መውሰድ።
መ ቅ.መ.መ. መፅናት።
ሠ ያዕ. ፪፥፲፰።
ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ረ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
ለ ፫ ኔፊ ፲፩፥፳፩–፳፪።
፴፱ ሀ ሞሮኒ ፫፤
ት. እና ቃ. ፻፯፥፶፰።
፵ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. የመንፈስ
ቅዱስ ስጦታ።
ለ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ሐ ት. እና ቃ. ፴፫፥፲፭፣
፲፬–፲፭፤ ፶፭፥፫።
፵፭ ሀ ሞሮኒ ፮፥፱፤
ት. እና ቃ. ፵፮፥፪።
፵፮ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፻፲፩፤
፻፯፥፷፩።
ቅ.መ.መ. ካህን፣
የአሮናዊ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ።
፵፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፥፴፰።
ለ ፩ ጢሞ. ፪፥፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ።
፵፰ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።

፶ ሽማግሌ ባለበት ጊዜ ግን፣ የእርሱ ተግባር መስበክ፣ ማስተምር፣ ማብራራት፣ አጥብቆ መምከር፣ እናም ማጥምቅ፣

፶፩ እናም የእያንዳንዱን አባል ቤት መጎብኘት፣ እናም በሚስጥር እና ድምጻቸውን አውጥተው እንዲጸልዩ እና የቤተሰብ ሀላፊነታቸውን እንዲያከናውኑ ማበርታት ብቻ ነው።

፶፪ አስፈላጊ ሲሆን ካህን በእነዚህ ሀላፊነቶቹ ሁሉ ሽማግሌውን [ሀ]ይረዳል።

፶፫ [ሀ]የመምህሩ ሀላፊነትም ቤተክርስቲያኗን ዘወትር [ለ]መጠበቅ፣ እና እነርሱን መርዳትና ማጠንከር ነው፤

፶፬ እናም ምንም ጥፋት በቤተክርስቲያኗ እንዳይኖር፣ እንዲሁም አባላቶቿ እርስ በራሳቸው [ሀ]እንዳይከፋፉ፣ እንዳይዋሹ፣ እንዳይተማሙ፣ ወይም [ለ]ክፉ እንዳይነጋገሩ መጠበቅ፤

፶፭ እናም ቤተክርስቲያንም በየጊዜው እንዲሰበሰቡ ማድረግ፣ እናም አባላቶቿ ሀላፊነታቸውን እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው።

፶፮ ሽማግሌ ወይም ካህን በማይኖሩበት ጊዜም የስብሰባውን መሪነት ይወስዳል—

፶፯ እናም አስፈላጊ በሚሆንም ጊዜ፣ በቤተክርስቲያኗ ሀላፊነቶቹ ሁሉ [ሀ]ዲያቆናት ይረዱታል።

፶፰ ነገር ግን መምህራንም ሆኑ ዲያቆናት የማጥመቅ፣ ቅዱስ ቁርባንን የመባረክ፣ ወይም እጆችን የመጫን ስልጣን የላቸውም፤

፶፱ ነገር ግን እነርሱ ማስጠንቀቅ፣ ማብራራት፣ ማበረታታት፣ እናም ማስተማር፣ እናም ሁሉንም ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ መጋበዝ አለባቸው።

፷ እያንዳንዱም [ሀ]ሽማግሌ፣ ካህን፣ መምህር፣ ወይም ዲያቆን ከእግዚአብሔር በተሰጠው ስጦታዎች እና [ለ]ጥሪዎች መሰረት ይሾም፤ እናም እርሱን በሚሾመው ውስጥ በሚገኝ መንፈስ ቅዱስ ሀይልም ይሾማል።

፷፩ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት ሽማግሌዎችም በሶስት ወር አንድ ጊዜ፣ ወይም ጉባኤው እንደሚመራውና እንደሚቀጥረው በጉባኤ ይሰብሰቡ፤

፷፪ እናም ይህም ጉባዔ በወቅቱ መሰራት ያለባቸውን ማንኛውም የቤተክርስቲያኗን ስራ መስራት አለበት።

፷፫ ሽማግሌዎች አባል ከሆኑበት ቤተክርስቲያን ወይም ከጉባዔው [ሀ]በምርጫ አማካይነት ከሌሎች ሽማግሌዎች ፈቃዳቸውን ይቀበሉ።

፷፬ በካህን የተሾመው እያንዳንዱም ካህን፣ መምህር፣ ወይም ዲያቆንም [ሀ]የምስክር ወረቀት በተሾመበት ጊዜ ከካህኑ መውሰድ ይችላል፣ ይህም የምስክር ወረቀት ለሽማግሌው በሚያቀርብ የጥሪውን ሀላፊነት ለማከናወን የሚያስችለው ስልጣን ይሰጠዋል፣ ወይም ይህን ከጉባኤ ሊቀበለው ይችላል።

፷፭ የዚህ ቤተክርስቲያን ቅርንጫፍ በተደራጀበት ስፍራ፣ ያለቤተክርስቲያኗ [ሀ]ምርጫ ማንም ሰው በቤተክርስቲያን ሀላፊነት [ለ]አይሾምም፤

፷፮ ነገር ግን የቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፍ ባለመኖሩ ምርጫ ሊጠራ በማይቻልበት ስፍራ፣ የሽማግሌዎች አመራር፣ ተጓዥ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ከፍተኛ አማካሪዎች፣ ሊቀ ካህናት፣ እና ሽማግሌዎች የመሾም መብት ሊኖራቸው ይችላል።

፷፯ እያንዳንዱ የታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት (ወይም የካህናት አመራር)፣ [ሀ]ኤጲስ ቆጶስ፣ ከፍተኛ አማካሪ፣ እናም [ለ]ሊቀ ካህናት [ሐ]በከፍተኛ ሸንጎ ወይም በአጠቃላይ ጉባኤ አመራር መሾም አለበት።

፶፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፲፩።
፶፫ ሀ ቅ.መ.መ. መምህር፣
የአሮናዊ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፶፬ ሀ ፩ ተሰ. ፭፥፲፩–፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. ክፉ መናገር።
፶፯ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያቆን።
፷ ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
ለ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣
በእግዚአብሔር መጠራት፣
የተጠራበት።
፷፫ ሀ ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።
፷፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፹፬፤
፶፪፥፵፩።
፷፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፮፥፪።
ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፷፯ ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
ለ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ሐ ቅ.መ.መ. ከፍተኛ ሸንጎ።

፷፰ አባላት ከተጠመቁ በኋላ ያለባቸው [ሀ]ሀላፊነት—[ለ]ቅዱስ ቁርባኑን ከመውሰዳቸውና ሽማግሌዎች [ሐ]እጆቻቸውን በመጫን ከሚያጸኗቸው በፊት፣ ሽማግሌዎች ወይም ካህናት ሰዎቹ [መ]እስኪገባቸው ድረስ ስለ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዲያብራሩላቸው ብቁ ጊዜን ማግኘት አለባቸው፣ ይህም ሁሉም ነገሮች በዕቅድ ይደረጉ ዘንድ ነው።

፷፱ እናም አባላቶቿ በቤተክርስቲያኗ ፊት እናም በሽማግሌዎች ፊት በአምላካዊ አካሄድ እና ንግግር ብቁ መሆናቸውን ያሳዩ፣ በጌታ ፊት [ሀ]በቅድስና በመሄድ ከቅዱስ መፅሀፍቶች ጋር የሚጣጣሙ [ለ]ስራዎች እና እምነት ይኑራቸው።

፸ ልጆች ያሏቸው እያንዳንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላትም ልጆቻቸውን በቤተክርስቲያኗ ፊት ወደ ሽማግሌዎች ያምጡ፣ እነርሱም እጆቻቸውን በክርስቶስ ስም ልጆቹ ላይ ይጫኑ፣ እናም በእርሱ ስም [ሀ]ይባርኳቸው።

፸፩ [ሀ]በተጠያቂነት እድሜ ላይ ካልደረሰ፣ እናም [ለ]ንስሀ ለመግባት ችሎታ ከሌለው፣ ማንም ሰው በክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን አይችልም።

፸፪ ንስሀ ለገቡት [ሀ]ጥምቀት ከእዚህ በሚከተለው ስነስርዓት ሁኔታ መሰጠት አለበት፥

፸፫ በእግዚአብሔር ተጠርቶ ለማጥመቅ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስልጣን ያለው ሰው፣ እራሱን ወይም እራሷን ለጥምቀት ካቀረበው ወይም ካቀረበች ሰው ጋር ወደ ውሀው አብሮ ይገባል፣ እናም እርሱን ወይም እርሷን በስም በመጥራት ይህን ይላል፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጠኝ ስልጣን መሰረት፣ በአብ፣ በወልድ፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሀለሁ (አጠምቅሻለሁ)። አሜን።

፸፬ ከዚያም እርሱን ወይም እርሷን ውሀ ውስጥ [ሀ]ያጥልቅ፣ እና ከውሀ ውስጥም በድጋሚ ያውጣ።

፸፭ ቤተክርስቲያኑም ዘወትር በአንድነት በመገናኘት ጌታ ኢየሱስን [ሀ]ማስታወስ ዳቦና ወይንን [ለ]መካፈላቸው አስፈላጊ ነው፤

፸፮ እናም ሽማግሌ ወይም ካህን ይህንንም ያድርግ፤ እና በዚህ [ሀ]መንገድም ይህን ያደርጋል—ከቤተክርስቲያኑ ጋር ተንበርክኮና በተረጋጋ ጸሎት ይህን በማለት አብን ይጥራ፥

፸፯ አቤቱ ዘለአለማዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን [ሀ]ዳቦ ለሚቋደሱት ነፍሳት ሁሉ የልጅህን አካል በማሰብ እንዲበሉት እና፣ አቤቱ ዘለአለማዊ አባት እግዚብሔር ሆይ፣ እነርሱ የልጅህን ስም በላያቸው ላይ [ለ]ለመውሰድ ፈቃደኞች መሆናቸውን፣ እና ሁልጊዜ እርሱን እንደሚያስታውሱና እርሱ የሰጣቸውን ትእዛዛት [ሐ]እንደሚጠብቁ ለአንተም [መ]ይመሰክሩ ዘንድ፣ በዚህም የእርሱ [ሠ]መንፈስ ሁልጊዜ እንዲኖራቸው ትባርከውና ትቀድሰው ዘንድ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቅሀለን። አሜን።

፸፰ ወይኑን የሚያስተላልፉበት [ሀ]መንገድም ይህ ነው—[ለ]ኩባያውን ወስዶ እንዲህ ይላል፥

፸፱ አቤቱ ዘለዓለማዊ አባት እግዚአ

፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሁለንተና።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
ሐ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
መ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፷፱ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ለ ያዕ. ፪፥፲፬–፲፯።
፸ ሀ ቅ.መ.መ. መባረክ፤ የተባረከ፤ በረከት—ልጆችን መባረክ።
፸፩ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥፵፪፤ ፳፱፥፵፯፤ ፷፰፥፳፭–፳፯። ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፤ ሂሳብ፤ ተጠያቂነት፤ ሀላፊነት፤ ጥምቀት፤ መጥመቅ—ለመጠመቅ ብቁነት።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፤ ንስሀ መግባት።
፸፪ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፳፪–፳፰።
፸፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፤ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ።
፸፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
ለ የሐዋ. ፳፥፯።
፸፮ ሀ ሞሮኒ ፬።
፸፯ ሀ ሉቃ. ፳፪፥፲፱።
ለ ሞዛያ ፭፥፰–፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፤ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
መ ሞዛያ ፲፰፥፰–፲፤ ት. እና ቃ. ፳፥፴፯።
ሠ ዮሐ. ፲፬፥፲፮።
፸፰ ሀ ሞሮኒ ፭።
ለ ሉቃ. ፳፪፥፳።

ብሔር ሆይ፣ ይህንን [ሀ]ወይን የሚጠጡት ነፍሳት ሁሉ ለእነርሱ የፈሰሰውን የልጅህን ደም በማስታወስ ያደርጉት ዘንድ፣ ሁልጊዜ እርሱን እንደሚያስታውሱ ለአንተም፣ አቤቱ ዘለዓለማዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ ይመሰክሩ ዘንድ፣ በዚህም የእርሱ መንፈስ ሁልጊዜ እንዲኖራቸው፣ ትባርከውና ትቀድሰው ዘንድ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቅሀለን። አሜን።

፹ በኃጢአት የሚወድቅ ወይም በጥፋት የሚወሰዱ ማንም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል፣ ቅዱሳት መጻህፍቱ እንደሚመሩት ይቀጣሉ።

፹፩ አንድ ወይም ብዙ መምህራንን በቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ወደሚደረገው ብዙ ጉባኤዎች ላይ እንዲገኙ መላክም የክርስቶስን ቤተክርስቲያን ክፍል የሆኑ ቤተክርስቲያናት ሀላፊነትም ነው፣

፹፪ በየወቅቱ የቤተክርስቲያኗ አባላት [ሀ]ስም ዝርዝር ሌሎች ሽማግሌዎች በየጊዜው በሚሾሟቸው በአንዱ ሽማግሌ በመዝገብ ይጠበቅ ዘንድ ሲመጡም ካለፈው ጉባኤ በኋላ ራሳቸውን የቤተክርስቲያኗ አባላት ጋር አንድ ያደረጉትን ሰዎች ስም ይዘው ይምጡ፤ ወይም በአንዳንድ ካህናት እጅም ይላኩ፤

፹፫ ደግሞም፣ ማናቸውም ከቤተክርስቲያኑ [ሀ]እንዲወጡ ቢደረጉም፣ ስማቸው ከቤተክርስቲያኑ ስም ዝርዝር ውስጥ እንዲሰረዙ ለማድረግ ነው።

፹፬ ወደ ማይታወቁበት ስፍራ አባላት ከሚኖሩበት ቤተክርስቲያን አካባቢ ሲሄዱም፣ ጥሩ የቤተክርስቲያን አባል እንደሆኑ የሚዘረዝር የምስክር ወረቀት በደብዳቤ ይዘው መሄድ ይችላሉ፣ ይህ የምስክር ወረቀት ደብዳቤውን የሚወስደው ሰው ከሽማግሌው ወይም ከካህኑ ጋር የሚተዋወቅ ከሆነ፣ ማንኛውም ሽማግሌ ወይም ካህን ሊፈርም ይችላል፣ ወይም ይህም በመምህራን ወይም በዲያቆናት መፈረም ይችላል።

ክፍል ፳፩

ሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ራዕዩ የተሰጠው ቤተክርስቲያኗ በተደራጀችበት ቀን በዴቪድ ዊትመር ቀዳማዊ፣ ቤት ውስጥ ነበር። ቀደም ብለው የተጠመቁት ስድስት ሰዎች ተሳትፈዋል። እነዚህ ሰዎች በአንድ ድምጽ እንደ እግዚአብሔር ትእዛዝ ለማቋቋም ፍላጎታቸውን እና ውሳኔያቸውን ገልጸዋል (ክፍል ፳ን ተመልከቱ)። ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን እና ኦሊቨር ካውድሪን እንደ ቤተክርስቲያኗ አመራር ለመቀበል መርጠዋል። እጅ በመጫን ጆሴፍ ኦሊቨርን ለቤተክርስቲያን ሽማግሌነት ሾሞታል ኦሊቨር በተመሳሳይ ሁኔታ ጆሴፍን ሾሞታል። ከቅዱስ ቁርባን ስርዐት በኋላ፣ ጆሴፍ እና ኦሊቨር በእያንዳንዱ ተሳታፊዎች ላይ እጅ በመጫን መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ አድርገዋል እንዲሁም እንደቤተክርስቲያን አባልነት አጽንተዋቸዋል።

፩–፫፣ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ባለራዕይ፣ ተርጓሚ፣ ነቢይ፣ ኃዋሪያ እና ሽማግሌ እንዲሆን ተጠራ፤ ፬–፰፣ የእርሱም ቃል የፅዮንን መነሻ ይመራል፣ ፱–፲፪፣ አጽናኝ በሆነው ሲናገር የሚናገረውን ቅዱሳን ያምናሉ።

፩ እነሆ፣ በመካከላችሁ [ሀ]መዝገብ ይቀመ

፸፱ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥ ፪–፬።
፹፪ሀ ሞሮኒ ፮፥ ፬።
፹፫ሀ ዘፀአ. ፴፪፥ ፴፫፤

አልማ ፭፥ ፶፯፤
ሞሮኒ ፮፥ ፯።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።

፳፩ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፵፯፥ ፩፤
፷፱፥ ፫–፰፤ ፹፭፥ ፩።

ጣል፤ እናም [ለ]ባለራዕይ፣ ተርጓሚ፣ ነቢይ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ [ሐ]ሐዋርያ፣ በእግዚአብሔር በአብ ፈቃድ እና በጌታህ በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ የቤተክርስቲያኗ ሽማግሌ ተብለህ ትጠራለህ፣

፪ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት መሰረቱን ለመጣል [ሀ]በመነሳሳት፣ እናም ወደተቀደሰ እምነት ትገነባው ዘንድ ተጠርተሀል

፫ [ሀ]ቤተክርስቲያኗ በጌታ ዓመት በአስራ ስምንት መቶ ሰላሳኛው ሚያዚያ ተብሎ በሚጠራው አራተኛው ወር በስድስተኛው ቀን [ለ]ተመሰረተች።

፬ ስለዚህ፣ በፊቴ [ሀ]በቅድስና በመራመድ የሚቀበላቸውን [ለ]ቃላቱን እና ትእዛዛቶቹን እናንተ የቤተክርስቲያኗ አባላት ታደምጣላችሁ፤

፭ [ሀ]ቃሉን ልክ ከእኔ አንደበት እንደወጣ አድርጋችሁ ሁሉ ትዕግስት እና እምነት ትቀበላላችሁ።

፮ ምክንያቱም ይህንን ስታደርጉ የሲዖል [ሀ]ደጆችም አያሸንፏችሁም፤ አዎን እናም ጌታ አምላክ [ለ]የጭለማን ኃይል ከላያችሁ ላይ ይገፋል እናም ለእናንተ ጥቅም እና ለስሙ [ሐ]ክብር ሰማያት [መ]እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋል።

፯ ጌታ አምላክ እንዲህ ይላል፥ ለአንዴ እና ለመጨረሻ [ሀ]የፅዮንን መሰረት ለማስፋት በታላቅ ኃይል አነሳስቼዋለሁ፣ እናም ትጋቱን አውቃለሁ፣ እንዲሁም ጸሎቱን ሰምቻለሁ።

፰ ለፅዮን የሚያለቅሰውን ልቅሶ ተመልክቼአለሁ፣ እናም ለእርሷ ካሁን በኋላ እንዳያዝን አደርገዋለሁ፣ ለኃጢአቱ [ሀ]ስርየት የሚደሰትበት እና በረከቴ በስራው ላይ የሚገለጥበት ቀን መጥቷል።

፱ ስለሆነም፣ እነሆ፣ [ሀ]በወይኑ ስፍራዬ የሚሰሩትን በታላቅ በረከት [ለ]እባርካቸዋለሁ፣ እና እነርሱም [ሐ]በኃጢአተኛ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ [መ]ለአለም ኃጢአት፣ አዎን፣ ኃጢአት ስርየት [ሠ]ልባቸውን ለሚያዋርዱ [ረ]እንደተሰቀለ በእኔ በኩል [ሰ]በአጽናኙ [ሸ]በሚሰጡት ቃሉ ያምኑታል።

፲ ስለዚህ በአንተ በሐዋሪያዬ በኦሊቨር ካውድሪ [ሀ]እንዲሾም ፍቃዴ ነው፤

፲፩ በ እሱ እጅ ሽማግሌ ስለሆንክ እርሱ ለአንተ [ሀ]የመጀመሪያ ስለሆነ ስሜን በመሸከም ለዚህች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሽማግሌ ትሆን ዘንድ ይህ ለአንተ ስርዐት ነው።

፲፪ እናም ለቤተክርስቲያኗ ለዚህ ቤተክርስቲያን፣ እናም በአለም ፊት፣ አዎን፣ በአህዛብ ፊት፤ የመጀመሪያ ሰባኪ ትሆን ዘንድ፤ አዎን፣ [ሀ]ለአይሁድም እንዲሁ ሰባኪ ትሆናለህ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። አሜን።

ክፍል ፳፪

ሚያዝያ ፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በማንችስተር፣ ኒው ዮርክ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ

፩ ለ ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
ሐ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ለ ት. እና ቃ. ፳፥፩።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
፭ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፴፰።
ቅ.መ.መ. ነቢይ፤ የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ።
፮ ሀ ማቴ. ፲፮፥፲፰፤
ት. እና ቃ. ፲፥፷፱።
ለ ቄላ. ፩፥፲፪–፲፫።
ሐ ቅ.መ.መ. ክብር።
መ ት. እና ቃ. ፴፭፥፳፬።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፭–፮።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፯፤
ያዕቆ. ፭፥፸–፸፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
መ ፩ ዮሐ. ፪፥፪።
ቅ.መ.መ. አለም—ትእዛዛትን የማያከብሩ ሰዎች።
ሠ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ረ ቅ.መ.መ. መስቀል።
ሰ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
ሸ ቅ.መ.መ. መመስከር።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፪።
፲፪ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፥፵፪፤
ት. እና ቃ. ፲፱፥፳፯፤
፺፥፰–፱።

በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የተሰጠው ቀደም ብለው የተጠመቁ ሰዎች ቤተክርስቲያኗን ያለዳግም ጥምቀት ለመዋሀድ በመፈለጋቸው ምክንያት ነው።

፩፣ ጥምቀት አዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ነው፤ ፪–፬፣ በስልጣን የተከናወነ ጥምቀት ያስፈልጋል።

፩ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ በዚህ ነገር ሁሉም [ሀ]የጥንት ቃልኪዳኖች እንዲሻሩ አድርጌ አለሁ፤ ይህ ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበረ [ለ]አዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ነው።

፪ ስለዚህ፣ ሰው መቶ ጊዜያት ቢጠመቅ ምንም አይጠቅመውም፣ ምክንያቱም [ሀ]በሙሴ ህግም ሆነ [ለ]በሞተ ስራዎቻችሁ በጠባቡ ደጅ መግባት አትችሉምና።

፫ ልክ እንደጥንቱ፣ ይህ የመጨረሻው ቃል ኪዳን ዳግመኛ እንዲመጣ እና ይህች ቤተክርስቲያን ለእኔ እንድትገነባ ያደረግሁት በሞቱ ስራዎቻችሁ ምክንያት ነው።

፬ ስለዚህ እንዳዘዝኳችሁ [ሀ]በደጃፉ ግቡ፣ እናም አምላካችሁን ለመምከር [ለ]አትሹ። አሜን።

ክፍል ፳፫

ሚያዝያ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በማንቸስተር፣ ኒው ዮርክ በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለኦሊቨር ካውድሪ፣ ለኃይራም ስሚዝ፤ ለሳሙኤል ኤች ስሚዝ፣ ለጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ፣ እና ለጆሴፍ ናይት ቀዳማዊ፣ የተሰጠ አምስት ተከታታይ ራዕዮች። ስማቸው የተጠቀሱት አምስት ሰዎች ሀላፊነታቸውን ለማወቅ በነበራቸው ፈቃድ ምክንያት፣ ነቢዩ ጌታን ጠይቆ ለእያንዳንዱ ሰው ራዕይን ተቀበለ።

፩–፯፣ እነዚህ ቀደምት ደቀ መዛሙርት ለመስበክ፣ ለመምከር፣ እና ቤተክርስቲያናን ለማጠንከር ተጠርተዋል።

፩ እነሆ፣ ኦሊቨር ለአንተ ጥቂት ቃላትን እናገራለሁ። እነሆ፣ አንተ የተባረክህ ነህ፣ እናም በምንም ኩነኔ ስር አይደለህም። ነገር ግን ወደ [ሀ]ፈተና እንዳትገባ [ለ]ትዕቢትን ተጠንቀቅ።

፪ ጥሪህን ለቤተክርስቲያኗ እና እንዲሁም በአለም ፊት እንዲታወቅ አድርግ፣ እናም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እናም ለዘለአለም እውነትን ለመስበክ ልብህ ይከፈታል። አሜን

፫ እነሆ፣ ለአንተ ለኃይራም ጥቂት ቃላትን እናገራለሁ፤ አንትም ብትሆን በምንም ኩነኔ ስር አይደለህም እናም ልብህ ተከፍቷል እናም አንደበትህ ተፈትቷል፤ እናም ጥሪህ ለመምከር እና ቤተክርስቲያናን በቀጣይነት [ሀ]ለማጠንከር ነው። ስለዚህ ሀላፊነትህ ለዘለአለም ለቤተክርስቲያኗ ነው፣ ይህም የሆነው በቤተሰብህ ምክንያት ነው። አሜን።

፬ እነሆ፣ ለአንተ [ሀ]ሳሙኤል ጥቂት ቃላትን እናገራለሁ፤ አንትም እንዲሁ በምንም ኩነኔ ስር አይደለህም እናም ጥሪህ ለመምከር እና ቤተክርስቲያናን በቀጣይነት ለማ

፳፪ ፩ሀ ዕብ. ፰፥፲፫፤
፫ ኔፊ ፲፪፥፵፯–፵፯።
ለ ት. እና ቃ. ፷፮፥፪።
ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን፤
አዲስ እና የዘለአለም
ቃል ኪዳን።
፪ሀ ገላ. ፪፥፲፮።
ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
ለ ሞሮኒ ፰፥፳፫–፳፮።
፬ሀ ማቴ. ፯፥፲፫–፲፬፤
ሉቃ. ፲፫፥፳፬፤
፪ ኔፊ ፱፥፵፩፤
፴፩፥፱፥ ፲፯–፲፰፤
፫ ኔፊ ፲፬፥፲፫–፲፬።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ለ ያዕቆ. ፬፥፲።
፳፫ ፩ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣
ፈተና።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፹፩፥፬–፭፤
፻፰፥፯።
፬ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፬።

ጠንክር ነው፤ እናም በአለም ፊት ለመስበክ ገና አልተጠራህም። አሜን።

፭ እነሆ፣ ለአንተ ጆሴፍ ጥቂት ቃላትን እናገራለሁ፤ አንተም በምንም ኩነኔ ስር አይደለህም እናም ጥሪህ ለመምከር እና ቤተክርስቲያኗን በቀጣይነት ለማጠንከር ነው፤ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እናም ለዘለአለም ይህ የአንተ ሀላፊነት ነው። አሜን።

፮ እነሆ ለአንተ ለጆሴፍ ናይት [ሀ]መስቀልህን እንድታነሳ፣ በዚህም [ለ]ድምጽህን አውጥተህ እንዲሁም በሚስጥር እናም በአለም ፊት፣ እናም በቤተሰብህ መካከል፣ እናም በባልንጀሮችህ መካከል፣ እናም በሁሉም ስፍራዎች [ሐ]እንድትጸልይ በእነዚህ ቃላት እገልጽልሀለሁ።

፯ እነሆም፣ የልፋትህን ዋጋ ትቀበል ዘንድ፣ ከእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ጋር [ሀ]አንድ መሆን እና ለመምከር ቃልህን ዘወትር መስጠት ይህ ስራህ ነው። አሜን።

ክፍል ፳፬

ሐምሌ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ፣ ፔንስልቫኒያ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለኦሊቨር ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ። ምንም እንኳን ቤተክርስቲያኗ ከተደራጀች አራት ወራት ቢያልፉም ስደቱ ጠንክሯል፣ እናም መሪዎች ራሳቸውን ለተወሰነ ጊዜ በመሰወር ደህንነትን መሻት ነበረባቸው። የሚቀጥሉት ሶስት ራዕይዎች በዚህ ጊዜ እነርሱን ለማጠንከር፣ ለማበረታታት፣ እና ለማስተማር የተሰጡ ናቸው።

፩–፱፣ ጆሴፍ ስሚዝ ቅዱሳን መጻህፍትን ለመተርጎም፣ ለመስበክ፣ እናም ለማብራራት ተጠርቷል ፲–፲፪፣ ኦሊቨር ካውድሪ ወንጌልን ለመስበክ ተጥርቷል፤ ፲፫–፲፱፣ ተአምራትን፣ እርግማንን፣ የእግርን ትቢያ ማራገፍን፣ ለመንገድ ከረጢት ሳይዙ መሄድን የተመለከተ ህግ ተገልጧል።

፩ እነሆ መፅሐፈ ሞርሞንን ለመጻፍ እናም ወደ አገልግሎቴ ተጠርተህ እናም ተመርጠህ ነበር፤ እናም ከስቃይህ ውስጥ ከፍ አድርጌሀለሁ፣ እናም መክሬሀለሁ፣ ከተጠላቶችህም ሁሉ ድነሀል እናም ከሰይጣን እና ከጨለማ ሀይል ታድጌሀለሁ!

፪ ሆኖም፣ [ሀ]በመተላልፍህ ይቅርታን አታገኝም፤ ሆኖም፣ ሂድ ከእንግዲህ ግን ኃጢአትን አትስራ።

፫ ተግባርህን [ሀ]አጉላ፤ እናም በምድርህ ከዘራህ እና ዋስትናውን ካስጠበቅህ በኋላ [ለ]በኮለስቪል፣ ፊየቴ፣ እናም ማንችስተር ወደሚገኙት ቤተክርስቲያኖች በፍጥነት ሂድ፣ እና እነርሱም [ሐ]ይደግፉሀል፤ እናም በጊዜያዊም ሆነ በመንፈሳዊ በረከት እባር ካቸዋለሁ፣

፬ ነገር ግን አንተን የማይቀበሉ ከሆነ፣ በበረከት ፈንታ እርግማንን እልክባቸዋለሁ።

፭ እናም ወደ እግዚአብሔር በስሜ መጣራትን፣ እናም [ሀ]በአጽናኙ የሚሰጡህን ነገሮች መጻፍን፣ እናም ለቤተክርስቲያኗ ቅድሷን መጻህፍትን ሁሉ ማብራራትህን ትቀጥላለህ።

፮ እናም በዚያኑ ጊዜ [ሀ]የምትናገረውን እና የምትጽፈው ይሰጥሀል፣ እናም ይሰ

፮ሀ ማቴ. ፲፥፴፰፤
፫ ኔፊ ፲፪፥፴።
ለ ት. እና ቃ. ፳፥፸፯፤ ፺፩።
ሐ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ—አስፈላጊ።

፳፬ ፪ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፴፩–፴፪።
፫ሀ ያዕቆ. ፩፥፲፱፤ ፪፥፪።
ለ ት. እና ቃ. ፳፮፥፩፤ ፴፯፥፪።
ሐ ት. እና ቃ. ፸፥፲፪።
፭ሀ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፮ሀ ዘፀአ. ፬፥፲፪፤

ማቴ. ፲፥፲፱–፳፤
ሉቃ. ፲፪፥፲፩–፲፪፤
ሔለ. ፭፥፲፰–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፹፭፤
፻፥፭–፰፤
ሙሴ ፮፥፴፪።

ሙታል፣ ወይም ከበረከት ይልቅ እርግማንን እልክባቸዋለሁ።

፯ በፅዮን ውስጥ [ሀ]አገልግሎትህን ሁሉ ታደርጋለህና፤ እና በዚህም ጥንካሬን ታገኛለህ።

፰ [ሀ]በስቃይህ [ለ]ታጋሽ ሁን፣ ብዙም ያጋጥምሀልና፣ ነገር ግን [ሐ]በጽናት አሳልፋቸው፣ እነሆም [መ]እስከመጨረሻዎቹ ቀኖችህም እንኳን እኔ ከአንተ ጋር ነኝ።

፱ ይህ የተጠራህበት ስላልሆነ፣ በጊዜያዊ ስራዎች ጥንካሬ አይኖርህም። [ሀ]ለጥሪህ ትኩረትን ስጥ እናም ተግባርህን የምታጎላበትንም፣ እናም ሁሉን ቅዱሳን መጻህፍት የምታብራራበት እናም እጅን መጫንን እና ቤተክርስቲያናቱን የምታጸናበት ሁኔታ ይኖርሀል።

፲ እናም ወንድምህ ኦሊቨር በአለም ፊት እንዲሁ በቤተክርስቲያኗ ስሜን መሸከምን ይቀጥላል። ስለእኔ በቂ ነገርን መናገር እችላለው ብሎ አያስብ፤ እናም፣ አስተውል፣ እኔ እስከመጨረሻው ድረስ ከእርሱ ጋር ነኝ።

፲፩ በድካም ሆነ፣ ወይም በብርታት፣ በእስራትም ሆነ በነጻነት በራሱ ሳይሆን፣ በእኔ ክብረን ያገኛል።

፲፪ እናም በሁሉም ጊዜያት እና በሁሉም ስፍራዎች አፉን ይከፍታል እናም [ሀ]እንደ መለከት ድምጽ በቀንና በማታ [ለ]ወንጌሌን ያውጃል። እናም በሰዎች መካከል የማይታወቅን አይነት ብርታት እሰጠዋለሁ።

፲፫ [ሀ]ዲያብሎስን [ለ]ከማስወጣት፣ የታመሙትን [ሐ]ከመፈወስ እናም [መ]መርዛምን እፉኝት፣ እናም ገዳይን መርዝ ከመቋቋውም በስተቀር እኔ [ሠ]ካላዘዝኳችሁ ሌሎች [ረ]ተአምራትን አትሹ፤

፲፬ እናም፣ ቅዱሳን መጻህፍት ይፈጸሙ ዘንድ፣ [ሀ]እነዚህን ነገሮች የሚፈልጓቸው ካልጠየቁህ በስተቅር አታደርጋቸውም፣ በተጻፈው መሰረት ታደርጋው ዘንድ ነውና።

፲፭ እናም [ሀ]በምትገቡበት ስፍራ ሁሉ በስሜ ካልተቀበሏችሁ፣ በበረከት ፈንታ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ የእግራችሁን ትቢያ [ለ]በማራገፍ እናም በመንግድ ዳር ላይ እግራችሁን በማጽዳት እርግማንን ትተዋላችሁ።

፲፮ እናም በአመጽም በእናንተ ላይ እጁን የሚያነሳ ሁሉ በስሜ ይመታ ዘንድ ታዛላችሁ፤ እናም እነሆ፣ እንደ ቃላቶቻችሁ በጊዜዬ እመታቸዋለሁ።

፲፯ እናም ከእናንተ ጋርም ወደ ህግ የሚሄዱትም በህጉ ይረገማሉ።

፲፰ ምንም አይነት [ሀ]ኮረጆም፣ ከረጢትም፣ በትርም ሆነ ሁለት እጅ ጠባብን አትውሰድ፣ ለምግብ፣ ለምትለብሰው፣ እናም ለመጫሚያ እናም ለገንዝብ እናም ለከረጢት የሚያስፈልግህን በዚያው ሰዓት ቤተክርስቲያኗ ትሰጥሀለችና።

፲፱ ስለሆነ በሀያል ግርዘት አዎን ለመጨረሻ ጊዜ፤ የወይን ስፍራዬን [ሀ]እንድትገርዝ ተጠርተሀል፤ እናም [ለ]የሾምካቸውም ሁሉ በዚህ መንገድ እንዲሁ ያደርጋሉ። አሜን።

፯ ሀ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ሐ ቅ.መ.መ. መፅናት።
መ ማቴ. ፳፰፥፳።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፬፥፮።
ለ ቅ.መ.መ. መስበክ።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ—ክፉ መንፈሶች።
ለ ማር. ፲፮፥፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።
መ የሐዋ. ፳፰፥፫–፱፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፷፭–፷፪፤ የ፳፬፥፯፰–፯፱።
ሠ ፩ ኔፊ ፲፯፥፶።
ረ ቅ.መ.መ. ምልክት፤ ተአምራት።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ለታመሙት አገልግሎት መስጠት።
፲፭ ሀ ማቴ. ፲፥፲፩–፲፭።
ለ ማር. ፮፥፲፩፤ ሉቃ. ፲፥፲፩፤ ት. እና ቃ. ፷፥፲፭፤ ፸፭፥፲፱–፳፪፤ ፺፱፥፬–፭።
፲፰ ሀ ማቴ. ፲፥፱–፲፤ ሉቃ. ፲፥፬፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፸፰–፸፱።
፲፱ ሀ ያዕቆ. ፭፥፳፩–፸፬፤ ት. እና ቃ. ፴፱፥፲፯፤ ፸፩፥፬።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።

ክፍል ፳፭

ሐምሌ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ ፔንስልቫኒያ በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የተሰጠ ራዕይ። (የክፍል ፳፬ ርዕስን ተመልከቱ)። ይህ ራዕይ ጌታ ለነቢዩ ሚስት ለኤማ ስሚዝ ያለውን ፈቃድ ይገልጣል።

፩–፮፣ ኤማ ስሚዝ፣ ባለቤቷን ለመርዳት እና ለማጽናናት የተጠራች የተመረጠች ሴት ነች፤ ፯–፲፩፣ እንዲሁም ለመጻፍ፣ ቅዱሳን መጻህፍትን ለማብራራት እና መዝሙሮችን ለመምረጥ ተጠርታለች፤ ፲፪–፲፬፣ የጻድቃን መዝሙር ለጌታ ጸሎት ነው፤ ፲፭–፲፮፣ በዚህ ራዕይ ውስጥ ያሉት የታዛዥነት መሰረታዊ መርሆች በሁሉም ዘንድ ተፈጻሚዎች ናቸው።

፩ ለአንቺ እየተናገርኩ ሳለ፣ ልጄ ኤማ ስሚዝ፣ የጌታ አምላክሽን ድምጽ አድምጪ፤ እውነት እልሻለሁ፣ ወንጌሌን [ሀ]የሚቀበሉ ሁሉ [ለ]በመንግስቴ ወንድ እና ሴት ልጆች ናቸው።

፪ ፈቃዴን በተመለከተ ራእዬን እሰጥሻለሁ፤ ታማኝ ከሆንሽ እና [ሀ]በምግባረ በጎነት መንገድ በፊቴ [ለ]የምትጓዢ ከሆነ፣ ህይወትሽን እጠብቀዋለሁ እናም በፅዮን [ሐ]ርስትን ትቀበያለሽ።

፫ እነሆ፣ [ሀ]ኃጢአቶችሽ ተሰርየውልሻል፣ እናም እኔ [ለ]የጠራሁሽ አንቺ የተመረጥሽ ሴት ነሽ።

፬ ስላላየሻቸው ነገሮች አታጉረምርሚ፣ ከአንቺ እና ከአለም ታግደዋል፣ ይህም ወደፊት በሚመጣው በእኔ ዘንድ ጥበብ ነው።

፭ የጥሪሽ ሀላፊነት ለባለቤትሽ ለአገልጋዬ ለጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ በመከራው ወቅት በአበረታች ቃላት፣ በትህትና መንፈስ፣ በመስጠት [ሀ]መጽናኛው እንድትሆኚው ነው።

፮ እናም በሚሄድበት ጊዜ አብረሽው ትሄጂያለሽ፣ እናም አገልጋዬን ኦሊቨር ካውድሪን ወደፈቀድኩበት ስፍራ እልከው ዘንድ፣ የሚጽፍለት ሰው ሳይኖር ለእርሱም ጸሀፊም ትሆኛለሽ።

፯ ቅዱሳን መጻህፍትን ለማብራራት እናም መንፈሴ እንደሰጠሽ ቤተክርስቲያኗን ታበረታቺ ዘንድ፣ በእርሱም እጅ [ሀ]ትሾሚያለሽ።

፰ [ሀ]እጁንም በራስሽ ላይ ይጭናል እናም መንፈስ ቅዱስን ትቀበያለሽ፣ እናም ጊዜሽ ለመጻፍ እና ብዙ ለመማር የተሰጠ ይሆናል።

፱ እናም ባለቤትሽ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለሚረዳሽ መፍርሀት የለብሽም፤ እንደ እምነታቸው፣ እንደ ፈቃዴ፣ ሁሉም ነገሮች [ሀ]ይገለጡላቸው ዘንድ፣ የእርሱ [ለ]ጥሪ ለእነርሱ ነው።

፲ እናም እውነት እልሻለሁ የዚህን [ሀ]አለም [ለ]ነገሮች ወደጎን ትተያቸዋለሽ እናም የተሻሉ ነገሮችን [ሐ]ትሺያለሽ።

፲፩ እናም እንዲሁም፣ በቤተክርስቲያኔ ውስጥ መኖራቸው ይህም ስለሚያስደስተኝ፣ እንደሚሰጥሽም መጠን የተ

፳፭ ፩ ሀ ዮሐ. ፩፥፲፪።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. በጎነት።
ለ ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፪፥፵፪፤ ፷፬፥፴፤ ፻፩፥፲፰።
ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፫ ሀ ማቴ. ፱፥፪።
ለ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
፮ ሀ ወይም መለየት።
ቅ.መ.መ. መለየት።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ፤ ትንቢት፣ መተንበይ።
ለ ቅ.መ.መ. ነቢይ፤ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. አለማዊነት።
ለ ቅ.መ.መ. ሀብቶች፤ መመኘት።
ሐ ኤተር ፲፪፥፬።

ቀደሱ [ሀ]መዝሙሮችን ትመርጪ ዘንድ ይሰጥሻል።

፲፪ [ሀ]ከልብ ከሆነ [ለ]ዝማሬ ነፍሴ ትደሰ ታለችና፣ አዎን የጻድቅን መዝሙር በእኔ ዘንድ ጸሎት ነው፣ በረከትንም በራሳቸው ላይ በማድረግ ይመለስላቸዋልና።

፲፫ ልብሽን አቅኚ እናም ተደሰቺ፣ እና ከገባሽውም ቃል ኪዳን ጋርም ተጣበቂ።

፲፬ [ሀ]በትህትና መንፈስ ቀጥዪ፣ እናም [ለ]ከትዕቢትም ተጠበቂ። ነፍስሽ በባልሽ እናም በእርሱ ላይ በሚመጣው ክብር ሀሴ ትን ታድርግ።

፲፭ ዘወትር ትእዛዛቴን ጠብቂ፣ እናም [ሀ]የጽድቅ [ለ]አክሊልን ትቀበያለሽ። ይህንን ባታደርጊ፣ እኔ ወዳለሁበት ስፍራ መም ጣት [ሐ]አትችዪምና።

፲፮ እናም እውነት፣ እውነት እልሻለሁ፣ ለሁሉም የሆነው ይህ የእኔ [ሀ]ድምጽ ነው። አሜን።

ክፍል ፳፮

በሐምሌ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ ፔንስልቫኒያ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ለኦሊቨር ካውድሪ፣ እና ለጆን ዊትመር የተሰጠ ራዕይ። (የክፍል ፳፬ ርዕስን ተመልከቱ)።

፩ ቅዱሳን መጻህፍትን እንዲያጠኑ እና እንዲሰብኩ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፤ ፪፣ የጋራ ስምምነት ህግ ጸደቀ።

፩ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ ወደ ምዕ ራብ የሚቀጥለውን ጉባዔ ለማድረግ እስ ክትሄዱ ድረስ ጊዜአችሁን በቅዱሳን መጻ ህፍት [ሀ]ጥናት፣ ስብከት፣ [ለ]በኮለስቪል ያለ ውን ቤተክርስቲያን በማጠንከር፣ በምድሩ ላይ ስራችሁን እንድታከናውኑ ይጠበቅባ ችኋል፣ እናም በመቀጠልም ምን እንደም ታከናውኑ ይነገራችኋል።

፪ እናም ሁሉም ነገሮች በቤተክርስቲያን [ሀ]በጋራ ስምምነት፣ በብዙ ጸሎት እና እም ነት ይከናወናሉ፣ ሁሉንም ነገሮች በእምነት ትቀበላላችሁ። አሜን።

ክፍል ፳፯

በነሀሴ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በሀርመኒ ፔንስልቫኒይ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። የዳቦ እና ወይን ቅዱስ ቁርባን ሀይማኖታዊ አገልግሎት ለመስጠት ለማ ዘጋጀት፣ ጆሴፍ ወይን ያገኝ ዘንድ ሄደ። የሰማይ መልአክም ተገናኘው እናም ይህንን ራዕይ ተቀበለ፣ የዚህም ራዕይ አማካይ ክፍል በወቅቱ ሲጻፍ ቀሪው በቀ ጣዩ ወር መስከረም የተጻፈ ነበር። በአሁን ወቅት በቤተክርስቲያኗ የቅዱስ ቁር ባን አገልግሎት ውስጥ በወይን ፋንታ ውሀ ጥቅም ላይ ውሏል።

፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. መዝሙር።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ልብ።
ለ ፩ ዜና ፲፮፥፱።
ቅ.መ.መ. መዘመር።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
ለ ቅ.መ.መ. አክሊል፤ ከፍተኛነት።
ሐ ዮሐ. ፯፥፴፬።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፴፰።
፳፮ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሣት መጻህፍት ዋጋዎች።
ለ ት. እና ቃ. ፳፬፥፫፤ ፴፯፥፪።
፪ ሀ ፩ ሳሙ. ፰፥፯፤ ሞዛያ ፳፱፥፳፮።
ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።

፩–፬፣ በቅዱስ ቁርባን ወቅት በምሳሌነት መውሰድ ያለባቸው ተገለጡ፤ ፭–፲፬፣ ክርስቶስ እና ከሁሉም ዘመናት ያሉ ደቀመዛሙርቱ ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ ይኖርባቸዋል፤ ፲፭–፲፰፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር እቃ ልበሱ።

፩ [ሀ]ፈጣን እና ኃያል የሆኑትን፣ የጌታህን፣ የአምላክህን እና የአዳኝህን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃላት አድምጥ።

፪ ስለሆነም፣ እነሆ፣ በአባቴ ፊት ለእናንተ የሰዋሁትን አካሌን እናም ለኃጢአታችሁ [ሀ]ስርየት የፈሰሰውን [ለ]ደሜን እያስታወሳችሁ ሙሉ አይናችሁን ወደ [ሐ]ክብሬ ካደረጋችሁ፣ [መ]ቅዱስ ቁርባንን ስትወስዱ የምትበሉት ወይም የምትጠጡት ነገር ለውጥ አያመጣም።

፫ ስለዚህ፣ ወይንም ሆነ ጠንካራ መጠጥ ከጠላቶቻችሁ እንዳትገዙ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ፤

፬ ስለዚህ፣ በመካከላችሁ፣ አዎን በምድር ላይ በሚገነባው በዚህ በአባቴ መንግስት፣ አዲስ ካልተሰራ በስተቀር ምንም ነገር እንዳትወስዱ፤

፭ እነሆ፣ ይህ በእኔ ዘንድ ጥበብ ነው፤ ስለዚህ፣ ከእናንተ ጋር እና ወደ እናንት የዘለአለም ወንጌሌን ሙላት የያዘውን መፅሐፈ ሞርሞንን እንዲገልጥ ከላኩት፣ የኤፍሬምን [ሀ]በትር ጽሁፍ ቁልፎች ከሰጠሁት [ለ]ከሞሮኒ ጋር በምድር ላይ የወይን ፍሬውን [ሐ]የምጠጣበት ሰዓት ስለሚመጣ አትደነቁ፤

፮ እናም እንዲሁም አለም ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያት አንደበት የመጨረሻውን ቀን በተመለከተ የተነገሩትን የሁሉም ነገሮች ዳግም መመለስ ቁልፍ ከሰጠሁት [ሀ]ከኢልያ ጋር፤

፯ እናም ደግሞ፣ እርሱ [ሀ](ኢልያ) የጎበኘው እና ልጅ እንደሚኖረው እና ስሙም ዮሐንስ እንዲሚሆን በኤልያስም መንፈስ እንደሚሞላ የተነገረለት የዘካሪያስ ልጅ ከሆነው [ለ]ዮሐንስም ጋር፤

፰ ይህም ዮሐንስ ለእናንተ ለአገልጋዮቼ፣ ለጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ እና ለኦሊቨር ካውድሪ እንደ [ሀ]አሮን እንድትጠሩ እና [ለ]እንድትሾሙ የተቀበላችሁትን የመጀመሪያውን [ሐ]ክህነትን እንድትቀበሉ የላክሁት ነው፤

፱ እናም እንዲሁም መላው ምድር በእርግማን እንዳይመታ የአባቶችን ልብ ወደልጆች፣ የልጆችን ልብ ወደአባቶች [ሀ]እንዲመልስ የሚያስችለውን የኃይል ቁልፍ ከሰጠሁት [ለ]ኤልያስ፤

፲ እንዲሁም [ሀ]ቃል ኪዳኖቹ በጸኑባቸው ከአባቶቻችሁ ከዮሴፍና ያዕቆብና፣ ይስሀቅና፣ አብርሐም ጋር፣

፲፩ እንዲሁም የሁሉም አባት፣ የሁሉም ልዑል፣ በዘመናት ከሸመገለው ከሚካኤል ወይም [ሀ]አዳም ጋር፣

፲፪ እናም [ሀ]ሐዋርያት ትሆኑ ዘንድ [ለ]በሾምኳችሁ እና ባጸደቅኩላችሁእናም የስሜ ልዩ [ሐ]ምስክሮች እንድትሆኑ እና የአገልግሎታችሁን እናም ለእነርሱ የገለጥኩላቸውን ተመሳሳይ ነገሮች ቁልፍ እንድትይዙ በላኳ

፳፯ ፩ ሀ ሔለ. ፫፥፳፱፤
ት. እና ቃ. ፮፥፪።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ለ ቅ.መ.መ. ደም።
ሐ ቅ.መ.መ. ክብር።
መ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
፭ ሀ ሕዝ. ፴፯፥፲፮።
ቅ.መ.መ. ኤፍሬም—የዮሴፍ ወይም የኤፍሬም በትር።
ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴–፴፬።
ሐ ማቴ. ፳፮፥፳፱፤
ማር. ፲፬፥፳፭፤
ሉቃ. ፳፪፥፲፰።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ኢልያ።
፯ ሀ ሉቃ. ፩፥፲፯–፲፱።
ለ ሉቃ. ፩፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፳፯–፳፰።
፰ ሀ ዘፀአ. ፳፰፥፩–፫፣ ፵፩፤
ት. እና ቃ. ፻፯፥፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፫።
ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. የትውልድ ሐረግ።
ለ ፩ ነገሥ. ፲፯፥፩–፳፪፤
፪ ነገሥ. ፩–፪፤
ት. እና ቃ. ፪፤ ፻፲፥፲፫–፲፮፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፰–፴፱።
ቅ.መ.መ. ኤልያስ።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. አዳም።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፸፪።
ቅ.መ.መ. የመልከጼዴቅ ክህነት።
ሐ የሐዋ. ፩፥፰።

ቸው ከጴጥሮስ፣ እና ከያእቆብ፣ እና ዮሐንስ ጋር፤

፲፫ ለእነርሱም በሰማይ እና በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ [ሀ]በአንድ በምጠቀልልበት [ለ]በዘመናት ሙላት፣ የዚህን [ሐ]የዘመነ ፍጻሜን [መ]ወንጌልንና የመንግስቴን [ሠ]ቁልፎች [ረ]ለመጨረሻው ጊዜ [ሰ]ከሰጠኋቸው ጋር፤

፲፬ እናም እንዲሁ አባቴ ከአለም [ሀ]ከሰጠኝ ሁሉ ጋር የምጠጣበት ሰዓት ስለሚመጣ አትደነቁ።

፲፭ ስለዚህ፣ ልባችሁን ከፍ አድርጋችሁ ተደሰቱ፣ ወገባችሁን አጥብቁ፣ ክፉውን ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ [ሀ]ለመቆም እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን [ለ]የጦር እቃ ሁሉ ልበሱ።

፲፮ ስለዚህ [ሀ]መላእክቴ እንዲሰጧችሁ ያደረኩትን፣ ወገባችሁን [ለ]በእውነት [ሐ]ታጥቃችሁ፣ [መ]የጽድቅንም [ሠ]ጥሩር ለብሳችሁ፣ [ረ]በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤

፲፯ የሚንበለበሉትን የክፉን [ሀ]ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ በማንሳት፤

፲፰ እናም የመዳንንም ራስ ቁር፣ እናም በእናንተ ላይ የማፈሰውን የመንፈስንም ሰይፍ እናም የምገልጥላችሁን ቃሌን ያዙ፣ እናም የምትጠይቁኝንም ነገሮች በተመለከተም ተስማሙ፣ እስከምመጣም ድርስ ታማኝ ሁኑ፣ እናም እናንተም እኔ ወደአለሁበት [ሀ]ትሆኑትም ዘንድ [ለ]ትነጠቃላችሁ። አሜን።

ክፍል ፳፰

በመስከረም ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈየት ኒው ዮርክ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለኦሊቨር ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ። የቤተክርስቲያን አባል የሆነው ሀይረም ፔጅ፣ አንድ የሆነ ድንጋይ ነበረው እናም በዚህ ድንጋይ በመረዳት የፅዮንን ግንባታ በተመለከተ እና የቤተክርስቲያኗን ስርዐት በተመለከተ ራዕይን እንደተቀበለ ተናገረ። በዚህም ብዙ አባላት ተታለሉ፣ እናም ኦሊቨር ካውድሪም መጥፎ ተጽዕኖ አደረበት። ከተቀጠረው ጉባዔ ቀደም ብሎ፣ ነቢዩ ጌታን ስለነገሩ በትጋት ጠየቀው፣ እና ይህም ራዕይ ተከተለ።

፩–፯፣ ጆሴፍ ስሚዝ የሚስጥሩን ቁልፍ ይዟል፣ እናም ለቤተክርስቲያኗ ራዕይ የሚቀበለው እርሱ ብቻ ነው፤ ፰–፲፣ ኦሊቨር ካውድሪ ለላማናውያን ይስበክ፤ ፲፩–፲፮፣ ሰይጣን ሀይረም ፔጅን አታለለው እናም የሀሰት ራእዮችን ሰጠው።

፩ እነሆ፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ [ሀ]ኦሊቨር፣ [ለ]በአጽናኙ የሰጠሁትን ራእዮች እና ትእ

፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፻።
ለ ኤፌ. ፩፥፱–፲፤
ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፴፤
፻፳፬፥፵፩።
ሐ ቅ.መ.መ. ዘመን።
መ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ሠ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ረ ያዕቆ. ፭፥፸፩፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፳፰–፴።
ሰ ማቴ. ፲፮፥፲፱።
፲፬ ሀ ዮሐ. ፮፥፴፯፤ ፲፯፥፱፣ ፲፩፤
፫ ኔፊ ፲፭፥፳፬፤
ት. እና ቃ. ፶፥፵፩–፵፪፤
፹፬፥፳፫።
፲፭ ሀ ሚል. ፫፥፪፤
ት. እና ቃ. ፹፯፥፰።
ለ ሮሜ ፲፫፥፲፪፤
ኤፌ. ፮፥፲፩–፲፰።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፱–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. እውነት።
ሐ ኢሳ. ፲፩፥፭።
መ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
ሠ ኢሳ. ፶፱፥፲፯።
ረ ፪ ኔፊ ፲፱፥፮።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፥፳፬፤
ት. እና ቃ. ፫፥፰።
፲፰ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፫።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፴፯፤
ት. እና ቃ. ፲፯፥፰።
፳፰ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፫።
ለ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።

ዛዛትን በተመለከተ [ሐ]የምታስተምራቸው ነገሮች ሁሉ በቤተክርስቲያን እንድትሰማ ለአንተ ይሰጥሀል።

፪ ነገር ግን፣ እነሆ፣ እውነት እውነት እልሀለሁ፣ በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከአገልጋዬ [ሀ]ከጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ በስተቀር [ለ]ማንም ሰው ትእዛዛትን እና ራእዮችን እንዲቀበል አይሾምም፣ እርሱም እንደ ሙሴ ሁሉ ይቀበላቸዋል።

፫ እና አንተም፣ ልክ እንደ [ሀ]አሮን፣ ለእርሱ ለምሰጣቸውን ነገሮች፣ በእምነት ትዛዛቱን እና ራእዮቹን በኃይል እና [ለ]በስልጣን ለቤተክርስቲያኗ ለማወጅ ታዛዥ ትሆናለህ።

፬ እናም [ሀ]ለመናገር ወይም ለማስተማር በአጽናኙ ወይም በሁሉም ጊዜ ለቤተክርስቲያኗ በትእዛዝ መልክ ከተመራህ፣ ይህንንም ልታደርገው ትችላለህ።

፭ ነገር ግን በጥበብ እንጂ በትእዛዝ መልክ አትጻፍ፤

፮ እናም የቤተክርስቲያኗ የበላይ እና ከአንተም የበላይ የሆነውን አታዝዘውም፤

፯ ስለሆነም በእርሱ ምትክ ሌላ አስክሾም ድረስ [ሀ]የሚስጥራትን [ለ]ቁልፎች እና የታተሙትን ራዕዮች ሰጥቼዋለሁ።

፰ እናም፣ እነሆ፣ እልሀለሁ [ሀ]ወደላማናውያን ሄደህ [ለ]ወንጌሌን ትሰብክላቸዋለህ፤ እናም ትምህርትህን በተቀበሉ መጠን በመካከላቸው ቤተክርስቲያኔን ትመሰርታለህ፤ እናም ራእዬን ትቀበላለህ ነገር ግን በትእዛዝ መልክ አትጻፋቸው።

፱ እናም አሁን፣ እነሆ፣ እልሀለሁ፣ ይህ አልተገለጠም፣ እናም [ሀ]የፅዮን [ለ]ከተማ የት እንዲሚገነባ ማንም አያውቅም፣ ነገር ግን ከዚህ በኋላ ይሰጣል። እነሆ እልሀለሁ፣ በላማናውያን ድንበር ላይ ይሆናል።

፲ ጉባዔው እስኪፈጸም ድረስ ከዚህ ስፍራ እንዳትሄድ፤ እናም አገልጋዬ ጆሴፍ በጉባኤውም ድምጽ ጉባዔውን እንዲመራ ይሾማል፣ እናም የሚልህን ሁሉ ትናገራለህ።

፲፩ እናም ዳግም፣ ወንድምህን ሀይረም ፔጅን ወስደህ በአንተ እና በእርሱ [ሀ]መካከል ብቻ ከድንጋዩ የጻፈው ነገሮች ከእኔ እንዳልሆኑ እና [ለ]ሰይጣንም [ሐ]እንዳታለለው ንገረው።

፲፪ ስለሆነም፣ እነሆ እነዚህ ነገሮች ለእርሱ አልተሰጡትም፣ ማናቸውም ነገሮች ቢሆኑ ለማንም የቤተክርስቲያን አባል የቤተክርስቲያኗን ቃል ኪዳን በሚጻረር መልክ አይሰጠውም።

፲፫ ስለሆነም ሁሉም ነገሮች በስራዐት እና በቤተክርስቲያኗ ውስጥ [ሀ]በጋራ ስምምነት፣ በእምነት ጸሎት መከናወን አለባቸው።

፲፬ እናም በላማናውያን መካከል ከመሄድህ በፊት እንደ ቤተክርስቲያኗ ቃል ኪዳን መሰረት ይህ ነገር እንዲረጋጋ ትረዳለህ።

፲፭ እናም ከምትሄድበት ጊዜ ጀምሮ እስከምትመለስበት ጊዜ ድረስ የምታከናውነው ነገር [ሀ]ይሰጥሀል።

፲፮ እናም ወንጌሌን በደስታ ድምጽ በማወጅ በሁሉም ጊዜ አንደበትህን መክፈት ይገባሀል። አሜን።

፩ሐ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ—በመንፈስ
ማስተማር።
፪ሀ ፪ ኔፊ ፫፥፲፩–፳።
ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ጆሴፍ ዳግማዊ።
ለ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፯–
፲፰፤ ፵፫፥፬።
፫ሀ ቅ.መ.መ. አሮን፣
የሙሴ ወንድም።
ለ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
፬ሀ ዘፀአ. ፬፥፲፪–፲፮፤
ት. እና ቃ. ፳፬፥፭–፮።
፯ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ሚስጥሮች።
ለ ት. እና ቃ. ፰፬፥፭፤
፹፬፥፲፱።
፰ሀ ፪ ኔፊ ፫፥፲፰–፳፪፤
ት. እና ቃ. ፴፥፭–
፮፤ ፴፪፥፩–፫።
ለ ት. እና ቃ. ፫፥፲፱–፳።
፱ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥፵፪–፵፫።
ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፫።
፲፩ሀ ማቴ. ፲፰፥፲፭።
ለ ራዕ. ፳፥፲።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፫፥፭–፯።
፲፫ሀ ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።
፲፭ሀ ፪ ኔፊ ፴፪፥፫፣ ፭።

ክፍል ፳፱

መስከረም ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈየት ኒው ዮርክ በስድስት ሽማግሌዎች ፊት በነቢዩ ጆሴፍ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የተሰጠው ከጉባዔው ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ፣ ከመሰከረም ፳፮፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) ጀምሮ ነው።

፩–፰፣ ክርስቶስ የመረጣቸውን ይሰበስባል፤ ፱–፲፩፣ ምፅአቱ አንድ ሺህ ዘመን እንዲጀምር ያደርጋል፤ ፲፪–፲፫፣ አስራ ሁለቱ መላው እስራኤልን ይፈርዳሉ፤ ፲፬–፳፩፣ ምልክቶች፣ መቅሰፍቶች፣ እና ውድመቶች ዳግም መፅአትን ይቀድማሉ፣ ፳፪–፳፰፣ የመጨረሻው ትንሳዔ እና የመጨረሻው ፍርድ አንድ ሺህ ዘመንን ይከተላሉ፤ ፳፱–፴፭፣ ሁሉም ነገሮች ለጌታ መንፈሳዊ ናቸው፤ ፴፮–፴፱፣ ሰይጣን እና ተከታዮቹ የሰውን ልጅ እንዲፈትኑ ከሰማይ ተወርውረዋል፤ ፵–፵፭፣ ውድቀቱ እና የኃጢአት ክፍያው መዳንን ያመጣሉ፤ ፵፮–፶፣ ህፃናት ልጆች በሀጢይት ክፍያው ድነዋል።

፩ ታላቁ [ሀ]እኔ ነኝ ያለውን፣ [ለ]የምህረቱ ክንድ [ሐ]ለኃጢአታችሁ ክፍያ የሆነውን፣ የአዳኛችሁን የኢየሱስ ክርስቶስን ድምጽ አድምጡ፤

፪ ድምጼን የሚያደምጡ እና ራሳቸውን በፊቴ [ሀ]ዝቅ የሚያደርጉ፣ እና ወደ እኔም በታላቅ ጸሎት የሚጣሩትን ህዝቦቹንም ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ [ለ]የሚሰበስበውን የእነርሱን ድምጽ አድምጡ።

፫ እነሆ እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ ጊዜ ለኃጢአታችሁ [ሀ]ይቅርታን አግኝታችኋል፣ ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ትቀበላላችሁ፤ ነገር ግን ከዚህ የሚብስ ነገር እንዳይመጣባችሁ ዳግመኛ ኃጢአት እንዳትሰሩ አስታውሱ።

፬ እውነት እላችኋለሁ፣ ልክ እንደ [ሀ]መለከትም ድምጽ፣ በደስታ ድምጽ ወንጌሌን ለማወጅ ከአለም ውስጥ ተመርጣችኋልና።

፭ እኔ [ሀ]በመካከላችሁ ስላለሁ እና በአብም ዘንድ [ለ]ስለማማልዳችሁ፣ ልባችሁን አንሱ እናም ተደሰቱ፤ እናም [ሐ]መንግስቱን ሊሰጣችሁ መልካም ፈቃዱ ነው።

፮ እናም፣ እንደተጻፈው—እንደ ትእዛዜ በጸሎት [ሀ]አንድ ሆናችሁ [ለ]በእምነት [ሐ]የምትጠይቁትን ማንኛውንም ነገር ትቀበላላችሁ።

፯ እናም በእኔ የተመረጡትን [ሀ]ለመሰብሰብ [ለ]ተጠርታችኋል፣ ምክንያቱም በእኔ የተመረጡት [ሐ]ድምጼን ይሰማሉ እና [መ]ልባቸውንም አያደነድኑም፤

፰ ስለዚህ ልባቸውን [ሀ]ለማዘጋጀት እና በክፉዎች ላይ በሚላክበትን [ለ]መከራ እና ጭንቀት ቀን ለመቃወም እንዲዘጋጁ፣ በዚህ ምድር ላይ በአንድ ስፍራ [ሐ]እንዲሰበሰቡ አዋጁ ከአብ ዘንድ ወጥቷል።

፱ እነሆ ሰዓቱ ተቃርቧል፣ ምድርም የም

፳፱ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ያለና የሚኖር።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ማቴ. ፳፫፥፴፯፤ ፫ ኔፊ ፲፥፬–፮።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፬ሀ አልማ ፳፱፥፩–፪፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፴፯፤ ፴፥፱።
፭ሀ ማቴ. ፲፰፥፳፤ ት. እና ቃ. ፮፥፴፪፤ ፴፰፥፯፤ ፹፰፥፷፪–፷፫።
ለ ቅ.መ.መ. አማላጅ።
ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
፮ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፥፩–፪፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፩።
ለ ማር. ፲፩፥፳፬።
ሐ ማቴ. ፳፩፥፳፪፤ ዮሐ. ፲፬፥፲፫።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ለ ማር. ፲፫፥፳፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፬። ቅ.መ.መ. ምርጦች።
ሐ አልማ ፭፥፴፯–፵፩።
መ ቅ.መ.መ. ልብ።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፮–፱፤ ፸፰፥፯።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥፲፱፤ ፵፫፥፲፯–፳፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፬–፷፮፤ ፶፯፥፩።

ትጠፋበትም ዳርሷል፤ እናም [ሀ]ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሰሩ ሁሉ [ለ]ገለባ የሚሆኑበት ይሆናሉ፤ በምድር ላይ ኃጢአት እንዳይኖር [ሐ]አቃጥላቸዋለሁ ይላል የሰራዊት ጌታ፤

፲ ሰዓቱ ተቃርቧል፣ እናም በኃዋሪያቴ የተነገረው መፈጸም አለበት፤ [ሀ]እንደተናገሩት እንዲሁ ይፈጸማልና፤

፲፩ ራሴን ከሰማይ በኃይል እና በታላቅ ክብር፣ በሰማይ [ሀ]ሰራዊት ጋር እገልጣለሁ፣ እና [ለ]በጽድቅም ከሰዎች ጋር በምድር ላይ ለአንድ [ሐ]ሺህ አመታት እኖራለሁ፣ እናም ኃጢአተኞችም መቆም አይችሉም።

፲፪ እናም ዳግም፣ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ በኢየሩሳሌም በአገልግሎቴ ከእኔ ጋር የነበሩት አስራ ሁለቱ [ሀ]ሐዋሪያቴ፣ [ለ]በእሳት አምድ በምመጣበት ቀን የጽድቅን ልብስ ለብሰው፣ አክሊልን በራሳቸው ላይ ደፍተው፣ ልክ እንደ እኔው [ሐ]በክብር፣ መላው እስራኤልን [መ]ለመፍረድ፣ እንዲሁም የወደዱኝ እና ትእዛዛቴን የጠበቁትን ብቻ ለመፍረድ፣ ከእኔ ጋር በቀኝ በኩል ይቆሙ ዘንድ በአብ ፈቃድ የጸና አዋጅ ወጥቷል።

፲፫ እነሆ ልክ እንደ ሲና ተራራ [ሀ]መለከትም በረጅም እና በጉልህ ይሰማል፣ እናም መላው ምድርም ይናወጣል፣ እናም አዎን በእኔ [ለ]የሞቱትም ሙታን የጽድቅን [ሐ]አክሊል ሊቀበሉ እናም ልክ [መ]እንደ እኔ ሊለብሱ፣ አንድ እንሆን ዘንድ ከእኔ ጋር እንዲሆኑ ወደፊትም [ሠ]ይመጣሉ።

፲፬ ነገር ግን፣ እነሆ እውነት እልሀለሁ ይህ ታላቅ [ሀ]ቀን ከመምጣቱ በፊት [ለ]ፀሀይ ትጨልማለች፣ እናም ጨረቃም ወደ ደምነት ትለወጣለች፣ እናም ከዋክብትም ከሰማይ ይረግፋሉ፣ እናም በላይ በሰማይና በታች በምድርም ታላቅ [ሐ]ምልክቶችም ይሆናሉ፤

፲፭ እናም በሰዎች መካካልም [ሀ]ለቅሶ እና ሐዘን ይሆናል፤

፲፮ እናም ታላቅ [ሀ]የበረዶ አውሎነፋስም የምድርን ሰብል ለማጥፋት ይላካል።

፲፯ እንዲህም ይሆናል፣ በአለም ኃጢአት የተነሳ፣ ንስሀም ስለማይገቡ፣ [ሀ]በኃጢአተኞች ላይ [ለ]በቀልን አደርጋለሁ፣ የቁጣ ጽዋዬም ሞልቷልና፤ ስለሆነም እነሆ፣ ካልሰሙኝ [ሐ]ደሜ አያነጻቸውም።

፲፰ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ አምላክ በውስጧ የሚኖሩትን ይይዙ ዘንድ በምድር ላይ ዝንቦችን እልካለሁ፣ እናም ስጋቸውንም ይበላሉ፣ በውስጣቸውም እጭ እንዲያዝ አደርጋለሁ፤

፲፱ እናም እኔን በመቃወም እንዳይናገሩ [ሀ]ምላሳቸው እንዳይንቀሳቀስ አደርገዋለሁ፤ ስጋቸው ከአጥንታቸው እናም አይኖቻቸው ከአይን ጉድጓዶቻቸው ላይ ይረግፋሉ።

፱ ሀ ፪ ኔፊ ፳፥ ፴፫፤ ፫ ኔፊ ፳፭፥ ፩። ቅ.መ.መ. ኩራት።

ለ ናሆ ፩፥ ፲፤ ሚል. ፬፥ ፩፤ ፩ ኔፊ ፳፪፥ ፲፭፣ ፳፫፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፴፯።

ሐ ት. እና ቃ. ፵፭፥ ፶፯፤ ፷፫፥ ፴፬፣ ፶፬፤ ፷፬፥ ፳፬፤ ፻፩፥ ፳፫–፳፭፤ ፻፴፫፥ ፷፬። ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት።

፲ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

፲፩ ሀ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥ ፴፯።

ለ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።

ሐ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት።

፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።

ለ ኢሳ. ፳፯፥ ፲፭–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፻፱፥ ፯፤ ፻፴፫፥ ፵፮።

ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር፤ ክብር።

መ ማቴ. ፲፱፥ ፳፰፤ ሉቃ. ፳፪፥ ፴፤ ፩ ኔፊ ፲፪፥ ፱፤ ሞር. ፫፥ ፲፰–፲፱።

፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፫፥ ፲፰፤ ፵፭፥ ፵፭።

ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥ ፺፯፤ ፻፴፫፥ ፶፮።

ሐ ቅ.መ.መ. አክሊል፤ ከፍተኛነት።

መ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፺፬–፺፭፤ ፹፬፥ ፴፭–፴፱።

ሠ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፶።

፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

ለ ኢዩ. ፪፥ ፲፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥ ፴፫።

ሐ ቅ.መ.መ. የጊዜዎች ምልክቶች።

፲፭ ሀ ማቴ. ፲፫፥ ፵፪።

፲፮ ሀ ሕዝ. ፴፰፥ ፳፪፤ ራዕ. ፲፩፥ ፲፱፤ ፲፮፥ ፳፩።

፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።

ለ ራዕ. ፲፮፥ ፯–፲፩፤ ፪ ኔፊ ፴፥ ፲፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥ ፶፫–፶፭። ቅ.መ.መ. በቀል።

ሐ ፩ ዮሐ. ፩፥ ፯፤ አልማ ፲፩፥ ፵–፵፩፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥ ፲፮–፲፰።

፲፱ ሀ ዘካ. ፲፬፥ ፲፪።

፳ እናም የጫካ [ሀ]አውሬዎች እናም የሰማይ አዕዋፋት ይበሏቸዋል።

፳፩ እናም ታላቋና [ሀ]የርኩሰት ቤተክርስቲያን፣ እነዚህ ገና ያልተፈጸሙትን ነገሮች ግን መፈጸም [ለ]የሚገባቸውን ነገሮች ነቢዩ ሕዝቅኤል እንደተናገረው፣ እና እኔ ህያው እንደሆንኩ፣ የምድር ሁሉ [ሐ]ጋለሞታ የሆነችው [መ]ወደምትበላ እሳት ትጣላለች፣ ምክንያቱም የረከሰ አይነግስምና።

፳፪ እናም ዳግም፣ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ አንድ [ሀ]ሺህ አመት ሲጠናቀቅ፣ እናም ሰዎች ዳግም አምላካቸውን መካድ ሲጀምሩ፣ ምድርንና የምተዋት [ለ]ለጥቂት ጊዜ ይሆናል።

፳፫ እናም [ሀ]መጨረሻው ይመጣል፣ እናም ሰማይ እና ምድር ይጠፋሉ እናም [ለ]ያልፋሉ፤ እንዲሁም አዲስ ሰማይ እና [ሐ]አዲስ ምድርም ይሆናል።

፳፬ እነሆ ሁሉም አሮጌ ነገሮች [ሀ]ያልፋሉ፣ ሁሉም ነገሮች፣ እንዲሁም ሰማይ እና ምድር እናም በውስጣቸው ያሉት ሁሉ፣ ሰዎች እና አራዊት፣ የሰማይ አዕዋፋት፣ እናም የባህር አሳዎች ሁሉ አዲስ ይሆናሉ፤

፳፭ እናም አንድ [ሀ]ጸጉርም ሆነ ጉድፍ ከፊታችሁ እንኳን አይጠፋም፣ የእጄ ስራ ነውና።

፳፮ ነገር ግን እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ምድር ከማለፏ በፊት፣ [ሀ]የመላእክቱ አለቃ [ለ]ሚካኤል [ሐ]መለከቱን ይነፋል፤ ከዚያም በኋላ [መ]የሞቱት ሁሉ ይነሳሉ፣ መቃብራቸው ይከፈታልና፣ እናም ወደፊትም [ሠ]ይመጣሉ—አዎን ሁሉም ወደፊት ይመጣሉ።

፳፯ እናም [ሀ]ጻድቃን ለዘለአለም ህይወት [ለ]በቀኜ ይሰበሰባሉ፤ እናም በግራዬ የሚገኙትን ኃጢአተኞችም በአባቴ ፊት የእኔ እንደሆኑ ለመናገር ያሳፍረኛል፤

፳፰ ስለዚህ እንዲህም እላችኋለሁ—እናንት የተረገማችሁ [ሀ]ለዲያብሎስ እና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ዘለአለማዊ [ለ]እሳት ከፊቴ [ሐ]ሂዱ።

፳፱ እናም አሁን፣ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ በፍጹም በማንኛው ጊዜ እንዲመለሱ በአፌ ተናግሬ አላውቅም፣ እኔ [ሀ]ወዳለሁበት መምጣት አይችሉም፣ ሀይል የላቸውምና።

፴ ነገር ግን አስታውሱ ሁሉም ፍርዶቼ ለሰዎች አልተሰጡም፤ ከአፌ ቃላት እንደወጡ እንዲሁ ይፈጸማሉ፣ የመንፈሴ ኃይል በሆነው በቃሌ ኃይል ከፈጠርኳቸው ነገሮች [ሀ]ፊተኞችም ኋለኞች፣ ኋለኞቸም ፊተኞች ይሆናሉ።

፴፩ በመንፈሴ ሀይል [ሀ]ፈጥሬአቸዋለሁና፤ አዎን፣ [ለ]መንፈሳዊ እንዲሁም ስጋዊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ—

፴፪ የስራዬ ጅማሬ የሆነው በቅድሚያ [ሀ]መንፈሳዊ፣ ሁለተኛ ጊዜአዊዊ፤ እናም ደግሞ የስራዬ ማብቂያ የሆነውን፣ በቅድሚያ ጊዜአዊው፣ እና ሁለተኛም መንፈሳዊው—

፴፫ ለእናንተ ስናገር በተፈጥሮ ትረዱ

፳ ሀ ኢሳ. ፲፰፥፮፤
ሕዝ. ፴፱፥፲፯፤
ራዕ. ፲፱፥፲፯–፲፰።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—
የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፴፰።
ሐ ራዕ. ፲፱፥፪።
መ ኢዩ. ፩፥፲፱–፳፤ ፪፥፫፤
ት. እና ቃ. ፺፯፥፳፭–፳፮።
ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ለ ራዕ. ፳፥፫፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፴–
፴፩፤ ፹፰፥፻፲–፻፲፩።
፳፫ ሀ ማቴ. ፳፬፥፲፬።
ቅ.መ.መ. አለም—
የአለም መጨረሻ።
ለ ማቴ. ፳፬፥፴፭፤
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር
የመጨረሻ ሁኔታ።
፳፬ ሀ ራዕ. ፳፩፥፩–፭።
፳፭ ሀ አልማ ፵፥፳፫።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. የመላእክት አለቃ።
ለ ቅ.መ.መ. ሚካኤል፤
አዳም።
ሐ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፶፪–፶፭።
መ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ፤
የማይሞት፣ አለሟችነት።
ሠ ዮሐ. ፭፥፳፰–፳፱።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
ለ ማቴ. ፳፭፥፴፫።
ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፫።
ሐ ማቴ. ፳፭፥፵፩፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥፵፩።
፳፱ ሀ ዮሐ. ፯፥፴፬፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፲፪።
፴ ሀ ማቴ. ፲፱፥፴፤
፩ ኔፊ ፲፫፥፵፪።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣
ፍጥረት።
ለ ሙሴ ፫፥፭–፯።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ፍጥረት።

ዘንድ ነው፤ ነገር ግን ለእኔ ለስራዬ [ሀ]መጨረሻም ሆነ መጀመሪያ የለውም፤ ነገር ግን ለእናንተ ተረዱት ዘንድ ተሰጥቷችኋል፣ ምክንያቱም እኔን ጠይቃችኋል እናም ተስማምታችኋልና።

፴፬ ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ ሁሉም ነገሮች ለእኔ መንፈሳዊ ናቸው፣ እናም በማንኛውም ጊዜ ቢሆን፣ ለሰው ወይም ለሰው ልጆች፣ ወይም እኔ ለፈጠርኩት ለአባታችሁ አዳምም፣ ጊዜያዊ የሆነ ህግ አልሰጠኋቸውም።

፴፭ እነሆ፣ ለእርሱ ራሱን [ሀ]እንዲወክል ሰጥቸዋለሁ፣ እናም [ለ]ትእዛዛትን ሰጠሁት ነገር ግን ጊዜአዊ ትእዛዝን አልሰጠሁትም፣ ትእዛዛቴ መንፍሳዊ ናቸውና፤ ተፍጥሯዊ ሆነ ጊዜያዊ፣ እንዲሁም ስጋዊ ወይም ስሜታዊ አይደሉም።

፴፮ እናም እንዲህም ሆነ፣ አዳም በዲያብሎስ በመፈተን—እነሆ፣ [ሀ]ዲያብሎስም በአዳም ፊት ነበርና፣ ምክንያቱም [ለ]ኃይሌ የሆነውን [ሐ]ክብርህን ስጠኝ በማለት በእኔ ላይ [መ]አምጿልና፤ እንዲሁም [ሠ]አንድ ሶስተኛውን የሰማይ [ረ]ሰራዊት [ሰ]በነጻ ምርጫቸው እኔን እንዲተው አደረገ፤

፴፯ እናም ወደታች ተጥለዋል፣ በዚህም የተነሳ [ሀ]ዲያብሎስ እና [ለ]መላእክቱ መጥተዋል፤

፴፰ እናም፣ እነሆ፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለእነርሱ ስፍራ ተዘጋጅቶላቸዋል፣ ይህም ስፍራ [ሀ]ሲኦል ነው።

፴፱ እናም ሰይጣን የሰዎችን ልጆች [ሀ]ይፈትን ዘንድ ግድ ነው፣ ይህ ካልሆነ በራሳቸው መምረጥ አይችሉምና፤ ምክንያቱም [ለ]መራራውን ካላወቁ ጣፋጩን ማወቅ አይችሉም ነበር—

፵ ስለዚህ፣ እንዲህም ሆነ ዲያብሎስ አዳምን ፈተነው፣ እናም የተከለከለውን [ሀ]ፍሬ በላ እናም ትእዛዙን ተላለፈ፣ በዚህም ለፈተና ራሱን አሳልፎ በመስጠቱ ምክንያት በሰይጣን ፈቃድ [ለ]ተገዢ ሆነ።

፵፩ ስለዚህ፣ እኔ፣ ጌታ አምላክ በመተላለፉ ምክንያት ከፊቴ [ሀ]ከዔደን ገነት [ለ]እንዲወጣ አደረግሁ፣ በዚህም የተነሳ የመጀመርያ ሞት በሆነው እንዲሁም የመጨረሻ [ሐ]ሞት በሚሆነው መንፈሳዊ በሆነው በኃጢአተኞችም ላይ እናንት [መ]የተረገማችሁ ወደዚያ ሂዱ በምልበት ጊዜ በሚከሰተው [ሠ]የመንፈስ ሞት ሞተ።

፵፪ ነገር ግን፣ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ እኔ፣ ጌታ አምላክ፣ [ሀ]ንስሀ እና [ለ]በአንድያ ልጄ ስም በእምነት [ሐ]መዳንን እንዲያውጁላቸው እኔ ጌታ አምላክ [መ]መላእክትን እስከ ምልክላቸው ድረስ [ሠ]በጊዜያው ሞት አዳም እና ዘሮቹ እዳይሞቱ አደረግሁኝ።

፵፫ እናም በዚህም የተነሳ እኔ ጌታ እግዚአብሔር የሰው ልጅ [ሀ]የሚሞከርበት ቀናቱን መደብኩኝ፣ በዚህም የሚያምኑትም ሁሉ፣ በስጋዊ ሞቱ ወደ [ለ]አለሚችነት እና [ሐ]በዘለአለማዊ ህይወት [መ]ለመነሳት እንዲችል እኔ ጌታ እግዚአብሔር ይህን አደረግሁ።

፴፫ ሀ መዝ. ፻፲፩፥፯–፰፤ ሙሴ ፩፥፬።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
፴፮ ሀ ት. እና ቃ. ፸፮፥፳፭–፳፮፤ ሙሴ ፬፥፩–፬።
ለ ኢሳ. ፲፬፥፲፪–፲፬፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፳፰–፳፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ክብር።
መ ቅ.መ.መ. የሰማይ ሸንጎ።
ሠ ራዕ. ፲፪፥፫–፬።
ረ ት. እና ቃ. ፴፰፥፩፤ ፵፭፥፩። ቅ.መ.መ. ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ሰ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ፪ ጴጥ. ፪፥፬፤ ይሁዳ ፩፥፮፤ ሙሴ ፯፥፳፮። ቅ.መ.መ. መላእክት።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሲዖል።
፴፱ ሀ ሙሴ ፬፥፫–፬። ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ሙሴ ፮፥፶፭።
፵ ሀ ዘፍጥ. ፫፥፮፤ ሙሴ ፬፥፯–፲፫።
ለ ፪ ኔፊ ፲፥፳፬፤ ሞዛያ ፲፮፥፫–፭፤ አልማ ፭፥፵፩–፵፪።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. ዔድን።
ለ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ሐ አልማ ፵፥፳፮።
መ ት. እና ቃ. ፳፱፥፳፯–፳፰፤ ፸፮፥፴፮–፴፱።
ሠ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
፵፪ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ሙሴ ፭፥፮–፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
መ አልማ ፲፪፥፳፰–፴።
ሠ ፪ ኔፊ ፪፥፳፩። ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
፵፫ ሀ አልማ ፲፪፥፳፬፤ ፵፪፥፲።
ለ ሙሴ ፩፥፴፱። ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሚችነት።
ሐ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
መ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።

፵፬ እናም የማያምኑት ወደ ዘለአለማዊ [ሀ]ጥፋት፣ ንስሀ ባለመግባታቸው ከመንፈሳዊ ውድቀታቸው አይድኑምና፤

፵፭ እነሆ ከብርሀን ይልቅ ጭለማን ይወዳሉ፣ እናም [ሀ]ስራቸውም እርኩስ ነው፣ እናም ለሚታዘዙለት ለዚያ [ለ]ደሞዛቸውን ይቀበላሉ።

፵፮ ነገር ግን፣ እላችኋለሁ፣ ህጻናት [ሀ]ልጆች ከአለም መጀመሪያ ጀምሮ በአንድያ ልጄ [ለ]ድነዋል፤

፵፯ ስለዚህ፣ ኃጢአትን ሊሰሩ አይችሉም፣ በእኔ ፊት [ሀ]ተጠያቂ እስኪሆኑ ድረስ ህጻናት ልጆችን [ለ]ለመፈተን ሰይጣን ሀይል አልተሰጠውምና፤

፵፰ ስለዚህ እንደ ፈቃዴ፣ እንደወደድሁ [ሀ]ከአባቶቻቸው እጅ ታላላቅ ነገሮችን እጠብቅባቸው ዘንድ ይህ ተሰጥቷቸዋል።

፵፱ እናም፣ ዳግም፣ እላችኋለሁ፣ እውቀት ያለው ሁሉ ንስሀ ይገባ ዘንድ አላዘዝሁምን?

፶ እናም [ሀ]መረዳት ለሌለው እርሱ፣ እንደ ተጻፈው ያደርግ ዘንድ ሀላፊነቱ የእኔ ነው። እናም አሁን በዚህ ጊዜ ለእናንተ ተጨማሪ ነገርን አላውጅም። አሜን።

ክፍል ፴

መስከረም ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈየት ኒው ዮርክ በነቢዩ ጆሴፍ አማካይነት ከሶስት ቀን ጉባዔ በኋላ፣ ግን የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ከመለያየታቸው በፊት፣ ለዴቪድ ዊትመር፣ ለፒተር ዊትመር ዳግማዊ፣ እና ለጆን ዊትመር የተሰጠ ራዕይ። ይህ ጽሁፍ በመጀመሪያ የታተመው እንደ ሶስት ራዕይዎች ነበር፣ ይህም በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ቅጂ ውስጥ በነቢዩ በአንድ ክፍል ውስጥ ተካትተው ነበር።

፩–፬፣ ዴቪድ ዊትመር በትጋት ባለመስራቱ ተገሰጸ፤ ፭–፰፣ ፒተር ዊትመር ዳግማዊ ከኦሊቨር ካውድሪ ጋር ወደላማናውያን ተልዕኮ ይሂድ፤ ፱–፲፩፣ ጆን ዊትመር ወንጌልን እንዲሰብክ ተጠራ።

፩ እነሆ፣ [ሀ]ዴቪድ እንዲህ እልሀለሁ፣ ሰውን [ለ]በመፍራት ለጥንካሬ በእኔ [ሐ]መደገፍ ያለብህን ያህል አልተደገፍክም።

፪ ነገር ግን አዕምሮህ በእኔ በፈጣሪህ ነገር እንዲሁም በተጠራህበት አገልግሎት ላይ ከመሆን ይልቅ [ሀ]በምድር ነገሮች ላይ ሆኗል፤ እናም መንፈሴን እና ከአንተ በላይ ስልጣን የተሰጣቸውን አላደመጥክም፣ ነገር ግን እኔ ባላዘዝኳቸው ተወስደሀል።

፫ ስለዚህ፣ ከእጄ ለራስህ እንድትጠይቅ ተትተሀል፣ እናም ስለተቀበልካቸውም ነገሮች [ሀ]አሰላስል።

፬ እናም ተጨማሪ ትእዛዛትን እስከምሰጥህ ድረስ መኖሪያህ በአባትህ ቤት ይሆናል። በቤተክርስቲያኗ ውስጥ እናም በአለም ፊት እና በአካባቢው ባሉት ዙሪያዎች [ሀ]አገልግሎትን ትሰጣለህ። አሜን።

፵፬ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፥፯–፲፪።
ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፵፭ሀ ዮሐ. ፫፥፲፰–፳፩፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፴፩–፴፪።
ለ ሞዛያ ፪፥፴፪–፴፫፤
አልማ ፫፥፳፮–፳፯፤
፭፥፵፩–፵፪፤ ፴፥፷።
፵፮ሀ ሞሮኒ ፰፥፰፤ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፴፰።
ቅ.መ.መ. ልጅ፣ ልጆች።
ለ ት. እና ቃ. ፸፬፥፯።
ቅ.መ.መ. ቤዛ፣
ማዳን፣ ቤዛነት።
፵፯ሀ ቅ.መ.መ. መልስ
መስጠት፣ ሂሳብ፣
ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ለ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
፵፰ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፳፭።
፶ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፯፥፯–፲።
ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፴ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ዊትመር፣
ዴቪድ።
ለ የሐዋ. ፭፥፳፱።
ሐ ፪ ዜና ፲፮፥፯–፱።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፳፭፥፲።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፬ሀ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።

፭ እነሆ [ሀ]ፒተር፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ ከወንድምህ ከኦሊቨር ጋር [ለ]ትጓዛለህ፤ ወንጌሌን ለማወጅ አንደበትህን ትከፍት ዘንድ ለእኔ አስፈላጊ የሚሆንበት [ሐ]ወቅት መጥቷል፤ ስለዚህ አትፍራ፣ ነገር ግን ወንድምህ የሚሰጥህን ምክር እና ቃላት [መ]አድምጥ።

፮ እናም በስቃዩ ሁሉ ከእርሱ ጋር ሁን፣ ለአንተ እና ለእርሱ ደህንነት በጸሎት እና በእምነት ዘወትር ልብህን ወደ እኔ አንሳ፤ [ሀ]በላማናውያን መካከል [ለ]ቤተክርስቲያኔን እንዲገነባ ኃይልን ሰጥቼዋለሁና፤

፯ እናም ከወንድሙ፣ ከጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ በቀር በእርሱ [ሀ]ላይ ማንንም የቤተክርስቲያኗን ነገሮች በተመለከተ የእርሱ አማካሪ እንዲሆን አልሾምኩም።

፰ ስለዚህ፣ እነዚህን ነገሮች አድምጥ እናም ትእዛዛቴን በመጠበቅ ትጋ፣ እናም በዘለአለማዊ ህይወት ትባረካለህ። አሜን።

፱ እነሆ፣ አገልጋዬ ጆን እንዲህ እልሀለሁ እንደመለከት [ሀ]ድምጽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ወንጌሌን [ለ]ማወጅ ትጀምራለህ።

፲ እናም አገልግሎትህም ከእዚያ እንድትሄድ ትእዛዝ እስክሰጠህ ድረስ በወንድምህ በፊልፕ በሮው ስፍራና በአካባቢው፣ አዎን፣ እንዲሁም ድምጽህ በሚሰማበት ስፍራ ሁሉ ይሆናል።

፲፩ እናም ከዚህ ጊዜ ጀምሮም በሙሉ ነፍስህ አገልግሎትህ ሁሉ በፅዮን ይሆናል፤ አዎን፣ [ሀ]ሰው ሊያደርግ የሚችለውን [ለ]ሳትፈራ ለእኔ ስራ ዘወትር አንደበትህን ትከፍታለህ፣ እኔም ዘወትር ከአንተ [ሐ]ጋር እሆናለሁና። አሜን።

ክፍል ፴፩

መስከረም ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለቶማስ ቢ. ማርሽ የተሰጠ ራዕይ። ወቅቱም የቤተክርስቲያኗ ጉባዔ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ነበር (የክፍል ፴ ርዕስን ተመልከቱ)። ይህ ራዕይ ከመሰጠቱ በፊት በወሩ መጀመሪያ ላይ የተጠመቀው ቶማስ ማርሽ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሽማግሌነት ተሹሞ ነበር።

፩–፮፣ ቶማስ ቢ. ማርሽ ወንጌልን እንዲሰብክ ተጠራ እናም ስለቤተሰቡ ደህንነት ማረጋገጫ ተሰጠው፤ ፯–፲፫፣ ትዕግስተኛ እንዲሆን፣ ዘወትር እንዲጸልይ እናም አጽናኙን እንዲከተል ተመከረ።

፩ ልጄ [ሀ]ቶማስ፣ በስራዬ ባለህ እምነት የተባረክህ ነህ።

፪ እነሆ፣ በቤተሰብህ የተነሳ ብዙ መከራን አይተሀል፤ ሆኖም፣ ቤተሰብህን እና አንተን አዎን፣ ህጻናት ልጆችህን እባርካቸዋለሁ፤ እናም የሚያምኑበት እና እውነትን የሚያውቁበት እንዲሁም ከአንተ ጋር በቤተክርስቲያኔ አንድ የሚሆኑበት ቀን ይመጣል።

፫ ልብህን አንሳ እናም ተደሰት፣ የተልዕኮህ ሰዓት መጥቷልና፤ እናም አንደበትህ ይፈታል፣ እናም የታላቅ ደስታን [ሀ]የምስራችንም ለዚህ ትውልድ ታውጃለህ።

፬ ለአገልጋዬ ለጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ የተገለጡለትን ነገሮች [ሀ]ታውጃለህ። ከዚህ

፭ ሀ ቅ.መ.መ. ዊትመር፣ ፒተር ዳግማዊ።
ለ ት. እና ቃ. ፴፪፥፩–፫።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፩፥፲፭።
መ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)፤ የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፫፥፳፤ ፵፱፥፳፬። ቅ.መ.መ. ላማናውያን።
ለ ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፯ ሀ ት. እና ቃ. ፳፰፥፪–፫።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፴፫፥፪።
ለ ት. እና ቃ. ፲፭፥፮።
፲፩ ሀ ኢሳ. ፶፩፥፯።
ለ ቅ.መ.መ. መበርታት፣ ብርቱነት፤ ፍርሀት።
ሐ ማቴ. ፳፰፥፲፱–፳።
፴፩ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማርሽ፣ ቶማስ ቢ።
፫ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፯፤ ሉቃ. ፪፥፲–፲፩፤ ሞዛያ ፫፥፫–፭።
፬ ሀ ሞዛያ ፲፰፥፲፱፤ ት. እና ቃ. ፵፪፥፲፪፤ ፶፪፥፴፮።

ጊዜ ጀምሮ መስበክ፣ አዎን፣ [ለ]ለነዶ ሊሆን የቀረበውን ሰብል መሰብሰብ ትጀምራለህ።

፭ ስለዚህ፣ በሙሉ ነፍስህ [ሀ]እጨድ፣ እናም ኃጢአትህም [ለ]ተሰርዮልሀል፣ እናም ብዙ [ሐ]ነዶም በጀርባህ ትሸከማለህ፣ [መ]ለሰራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና። ስለዚህ ቤተሰቦችህም በህይወት ይኖራሉ።

፮ እነሆ፣ እውነት እልሀለሁ፣ ከእነርሱ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ሂድ፣ እናም ቃሌን አውጅ፣ እናም ለእነርሱም ስፍራን አዘጋጅላቸዋለሁ።

፯ አዎን፣ የስዎቹን ልብ [ሀ]እከፍታለሁ፣ እናም ይቀበሉሀል። እና በእጀህም ቤተክርስቲያንን እመሰርታለሁ፤

፰ እናም [ሀ]ታጠነክራቸዋለህ እናም ለሚሰበሰቡበት ቀንም ታዘጋጃቸዋለህ።

፱ [ሀ]በስቃይ [ለ]ታጋሽ ሁን፣ ክፉ ለሚናገሩህ ክፉ አትመልስ። [ሐ]ቤትህን በትህትና ግዛ፣ እናም የጸናህ ሁን።

፲ እነሆ፣ ስለማይቀበሉህም ለአለም ሳይሆን ነገር ግን ለቤተክርስቲያኗ ሀኪም ትሆናለህ።

፲፩ እኔ ወደምፈቅደው ስፍራ ሁሉ ሂድ፣ እናም የምትሄድበት እና የምትሰራው [ሀ]በአጽናኙ ይሰጥሀል።

፲፪ [ሀ]ወደፈተና እንዳትገባ እና ደመወዝህን እንዳታጣ ዘወትር [ለ]ጸልይ።

፲፫ እስከ ፍጻሜው ድረስ [ሀ]ታማኝ ሁን፣ እኔም ከአንተ [ለ]ጋር ነኝ። እነዚህ ቃላት የሰውም ሆነ የሰዎች አይደሉም፣ ነገር ግን በአብ [ሐ]ፈቃድ የእኔ ያዳኛችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ናቸው። አሜን።

ክፍል ፴፪

ጥቅምት ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) መጀመሪያ አካባቢ በማንቸስተር፣ ኒው ዮርክ ውስጥ በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለፓርሊ ፒ ፕራት እና ለዚባ ፒተርሰን የተሰጠ ራዕይ። ቤተክርስቲያኗ በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በረከታቸው ቀደም ብሎ እንደተተነበየላቸው ስለተገነዘበቻቸው ላማናውያን በተመለከተ በሽማግሌዎች መካከል ታላቅ ፈቃድ እና አትኩሮት አድሮ ነበር። በዚህ የተነሳ ጌታ በምራዕብ ወዳሉት የኢንድያን ጎሳዎች ሽማግሌዎች እንዲሄዱ ፈቃዱ እንደሆነ ለመጠየቅ ታላቅ ጸሎት ተደረገ። ይህ ራዕይም ተከተለ።

፩–፫፣ ፓርሊ ፒ ፕራት እና ዚባ ፒተርሰን ከኦሊቨር ካውድሪ እና ፒተር ዊትመር ዳግማዊ ጋር በመሆን ለላማናውያን እንዲሰብኩ ተጠሩ፤ ፬–፭፣ ቅዱሳን መጻህፍትን ለመረዳት መጸለይ አለባቸው።

፩ እናም አሁን አገልጋዩን [ሀ]ፓርሊ ፒ ፕራትን በተመለከተ፣ እነሆ፣ እንዲህ እለዋለሁ፣ እኔ ህያው እንደሆንኩኝ፣ ወንጌሌን እንዲያውጅ እናም ከእኔም [ለ]እንዲማር እንዲሁም የዋህ እና ልበ ትሁት እንዲሆን ፍቃዴ ነው።

፪ እናም እኔ ለእርሱ የሰጠሁት ከአገልጋዮቼ፣ ከኦሊቨር ካውድሪ እና ከፒተር ዊት

፬ ለ ት. እና ቃ. ፬፥፬–፯።
፭ ሀ ራዕ. ፲፬፥፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
ሐ ት. እና ቃ. ፸፱፥፫።
መ ሉቃ. ፲፥፫–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፸፭፥፳፬።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፩፥፭፤ ፻፰፥፯።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—የወላጆች ሀላፊነቶች።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ አፅናኝ።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ፫ ኔፊ ፲፰፥፲፯–፳፩። ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መፅናት።
ለ ማቴ. ፳፰፥፳።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስልጣን።
፴፪ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ፕራት፣ ፓርሊ ፓርከር።
ለ ማቴ. ፲፩፥፳፰–፴።

መር ዳግማዊ፣ ጋር [ሀ]በላማናውያን መካከል ወደ ምድረበዳ [ለ]እንዲሄድ ነው።

፫ እናም [ሀ]ዚባ ፒተርሰን እንዲሁ ከእነርሱ ጋር ይሄዳል፤ እኔም ራሴ ከእነርሱ ጋር እሄዳለሁ፣ እናም [ለ]በመካከላቸውም እሆናለሁ፤ እናም ከአብ ዘንድ እኔ የእነርሱ [ሐ]አማላጅ ነኝ፣ እናም ምንም ነገር እነርሱን አይቃወምም።

፬ እናም ለተጻፉት [ሀ]ትኩረትን ይሰጣሉ፣ እናም ሌላን [ለ]ራዕይ ተቀበልን አይሉም፤ እናም እነዚህን ነገሮች [ሐ]እንዲገባቸው [መ]ግልጽ አደርግላቸው ዘወትር ይጸልያሉ።

፭ እናም ለእነዚህ ቃላት ያድምጣሉ እና በቀላሉም አይመለከቷቸውም፣ እናም እባርካቸዋለሁ። አሜን።

ክፍል ፴፫

ጥቅምት ፲፰፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በፈየት፣ ኒው ዮርክ በነቢዩ በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለእዝራ ታይር እና ኖርዝሮፕ ስዊት የተሰጠ ራዕይ። ይህንን ራዕይ በማስተዋወቅ፣ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚያረጋግጠው፣ “በእምነት ተግተው ለሚሹት ጌታ ሊያስተምራቸው ዘወትር ዝግጁ ነው።”

፩–፬፣ ሰራተኞች በአስራ አንደኛው ሰዓት ወንጌልን እንዲያውጁ ተጠርተዋል፤ ፭–፮፣ ቤተክርስቲያኗ ተመስርታለች፤ እና የተመረጡትም ይሰበሰባሉ፤ ፯–፲፣ ንስሀ ግቡ፣ መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና፤ ፲፩–፲፭፣ ቤተክርስቲያኗ በወንጌል አለት ላይ ተመስርታለች፤ ፲፮–፲፰፣ ለሙሽራው ምጽአት ተዘጋጁ።

፩ እነሆ፣ እንዲህ እልሀችኋለሁ፣ አገልጋዮቼ እዝራ እና ኖርዝሮፕ፣ ጆሮቻችሁን ክፈቱ እናም ፈጣን እና ሀያል፣ [ሀ]ቃሉ ሁለት አንደበት ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ፣ ነፍስንና መንፈስን፣ መገጣጠሚያን እና መቅኔን እስኪለይ ድረስ የሚሰራውን የጌታን ድምፅ አድምጡ፣ እናም የልብን ሐሳቦችና [ለ]ምኞቶች የሚያውቅ ነው።

፪ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ ድምጻችሁን እንደ መለከት [ሀ]ድምጽ ከፍ እንድታደርጉ እና ወንጌሌን በጠማማና በክፉ ትውልድ መካከል እንድታውጁ ተጠርታችኋልና።

፫ እነሆም፣ [ሀ]የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ አዝመራው ዝግጁ ነው፤ እናም [ለ]አስራ አደኛው ሰዓት፣ እና [ሐ]ለመጨረሻ ጊዜ ወደ እኔ የወይን ስፍራ አገልጋዮቼን የምጠራበት ጊዜ ነው።

፬ እናም አንዳች ፍሬ እንኳን ሳይቀር [ሀ]የወይን ስፍራዬም [ለ]ተበላሽቷል፤ እናም ከጥቂቶቹ በስተቀር [ሐ]መልካምን የሚያደርጉ የሉም፤ እናም ሁሉም ብልሹ አእምሮ [መ]በካህን ተንኮል ምክንያት በብዙ መንገዶች [ሠ]ጥፋት ላይ ወድቀዋል።

፭ እናም እውነት፣ እውነት፣ እላችኋ

፪ ሀ ት. እና ቃ. ፫፥ ፲፫–፳።
ለ ት. እና ቃ. ፳፰፥፰፤ ፴፥፭።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፰።
ለ ማቴ. ፲፰፥፳፤
ት. እና ቃ. ፮፥፴፪፤ ፴፰፥፯።
ሐ ቅ.መ.መ. አማላጅ።
፬ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፥፳፭፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፶፫–፶፬።
ለ ት. እና ቃ. ፳፰፥፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
መ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፸፬።
፴፫ ፩ ሀ ዕብ. ፬፥፲፪፤
ሔለ. ፫፥፳፱–፴።
ለ አልማ ፲፰፥፴፪፤
ት. እና ቃ. ፮፥፲፮።
፪ ሀ ኢሳ. ፶፰፥፩።
፫ ሀ ዮሐ. ፬፥፴፭፤
ት. እና ቃ. ፬፥፬፤
፲፪፥፫፤ ፲፬፥፫።
ለ ማቴ. ፳፥፩–፲፮።
ሐ ያዕቆ. ፭፥፸፩፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፳፰።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
ለ ፪ ኔፊ ፳፰፥፪–፲፬፤
ሞር. ፰፥፳፰–፵፩።
ሐ ሮሜ ፫፥፲፪፤
ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፪።
መ ቅ.መ.መ. የካህን ተንኮል።
ሠ ፪ ኔፊ ፳፰፥፲፬።

ለሁ፣ ይህችን [ሀ]ቤተክርስቲያን [ለ]መስርቻታለሁ እናም ከምድረበዳ እንድትወጣ ጠርቻታለሁ።

፮ እናም ምርጦቼን፣ እንዲሁም በእኔ የሚያምኑትን፣ እና ድምጼን የሚያዳምጡትን ሁሉ፣ [ሀ]ከአራቱም የምድር ማዕዘናት ቢሆንም [ለ]እሰበስባለሁ።

፯ አዎን፣ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ የእርሻው ስፍራ ነጭ ሆኖ አዝመራው ዝግጁ ነው፤ ስለዚህ፣ በማጭዶቻችሁ እጨዱ፣ እናም በሙሉ ኃይላችሁ፣ አዕምሮአችሁ፣ እናም ጉልበታችሁ ሰብስቡ።

፰ አንደበታችሁን [ሀ]ክፈቱ እንዲሁም ይሞላሉ፣ ከኢየሩሳሌም በምድረበዳ እንደተጓዘው፣ እንደጥንቱ [ለ]ኔፊም ትሆናላችሁ።

፱ አዎን፣ አንደበታችሁን ከፍታችሁ ከመናገር አትቆጠቡ፣ እናም [ሀ]ነዶንም በጀርባችሁ የተጫናችሁ ትሆናላችሁ፣ እኔም ከናንተ ጋር ነኝና።

፲ አዎን፣ አንደበታችሁን ክፈቱ እናም ይሞላሉ፣ እንዲህ በማለትም ተናገሩ፥ [ሀ]ንስሀ ግቡ፣ ንስሀ ግቡ፣ እናም የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ ጎዳናውንም አስተካክሉ፤ መንግሥተ ሰማይ ተቃርባለችና፤

፲፩ አዎን፣ ለኃጢአታችሁም ስርየት፣ እያንዳንዳችሁም ንስሀ ግቡ እና [ሀ]ተጠመቁ፤ አዎን፣ በውሀም ተጠመቁ፣ እናም በመቀጠልም የእሳት እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይመጣል።

፲፪ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ ይህ [ሀ]ወንጌሌ ነው፤ እናም በእኔ እምነት ከሌላቸው በስተቀር በምንም መንገድ ሊድኑ አይችሉም፤

፲፫ እናም በዚህ [ሀ]አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እገነባለሁ፣ አዎን፣ በዚህም አለት ላይ ተገንብታችኋል፣ እናም የምትቀጥሉም ከሆነ፣ [ለ]የሲዖል ደጆችም አያሸንፏችሁም።

፲፬ እናም የቤተክርስቲያኗን [ሀ]መመሪያዎች እና የተሰፋ ቃላትን መጠበቅ ታስታውሳላችሁ።

፲፭ እናም እምነት ያላቸውን ሁሉ በቤተክርስቲያኔ ውስጥ [ሀ]እጆቻችሁን በመጫን [ለ]ታጸኗቸዋላችሁ፣ እናም እኔም የመንፈስ ቅዱስን [ሐ]ስጦታን እሰጣቸዋለሁ።

፲፮ እናም መፅሐፈ ሞርሞን እናም [ሀ]ቅዱሳን መጻህፍት ለእናንተ [ለ]መማሪያነት ከእኔ ለእናንተ ተሰጥተዋል፤ እናም የመንፈሴም ኃይል ነገሮችን ሁሉ [ሐ]ህይወት ይሰጣል።

፲፯ ስለዚህ፤ [ሀ]ሙሽራው በሚመጣበት ጊዜ ዝግጁ መሆን እንድትችሉ፣ መብራታችሁን አስተካክላችሁ በመለኮስ እና ዘይታችሁን በመያዝ፣ ታማኝ ሁኑ፣ ዘውትርም ጸልዩ—

፲፰ እነሆም፣ እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ በቶሎም [ሀ]እመጣለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፭ ሀ ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ለ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፮ ሀ ፩ ኔፊ ፲፱፥፲፭–፲፮።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፹፩።
ለ ፪ ኔፊ ፩፥፳፮–፳፰።
፱ ሀ መዝ. ፻፳፮፥፮፤ አልማ ፳፮፥፫–፭፤ ት. እና ቃ. ፸፭፥፭።
፲ ሀ ማቴ. ፫፥፩–፫።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፲፪ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፥፲፫–፳፪።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. አለት።
ለ ማቴ. ፲፮፥፲፮–፲፱፤ ት. እና ቃ. ፲፥፷፱–፸።
፲፬ ሀ ይህም ት. እና ቃ. ፳ (የክፍል ፳ ርዕስን ተመልከቱ) ማለት ነው። ት. እና ቃ. ፵፪፥፲፫።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ለ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፥፵፩።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ ፪ ጢሞ. ፫፥፲፮።
ሐ ዮሐ. ፮፥፷፫።
፲፯ ሀ ማቴ. ፳፭፥፩–፲፫። ቅ.መ.መ. ሙሽራ።
፲፰ ሀ ራዕ. ፳፪፥፳። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

ክፍል ፴፬

ህዳር ፬፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈያት፣ ኒው ዮርክ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለኦርሰን ፕራት የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ ወንድም ፕራት አስራ ዘጠኝ አመቱ ነበር። ከስድስት ሳምንት ቀደም ብሎ ከታላቅ ወንድሙ፣ ከፓርሊ ፒ ፕራት ዳግም ስለተመለሰው ወንጌል ስብከት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰማ ተለወጠና ተጠመቀ። ይህ ራዕይ የተሰጠው በፒተር ዊትመር ቀዳማዊ ቤት ውስጥ ነበር።

፩–፬፣ በእምነት የተሞሉት በኃጢአት ክፍያው አማካይነት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ፤ ፭–፱፣ የወንጌል ስብከት የዳግም ምጽአትን መንገድ ያዘጋጃል፤ ፲–፲፪፣ ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ ሀይል አማካይነት ይመጣል።

፩ ልጄ [ሀ]ኦርሰን፣ እኔ ጌታ አምላክ፣ እናም እንዲሁም ቤዛህን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ የምንናገረውን ስማ እናም አድምጥ፣ እንዲሁም ተመልከት፤

፪ በጭለማ የሚያበራ እና ጭለማም የማይረዳውን፣ እኔ የአለም [ሀ]ብርሀን እና ሕይወት የሆንኩትን፤

፫ ያመኑ ሁሉ የእግዚአብሔር [ሀ]ልጆች ይሆኑ ዘንድ አለምን [ለ]በመውደድ [ሐ]እርሱ ህይወቱን አሳልፎ [መ]የሰጠውን ስማ እናም አድምጥ፣ እንዲሁም ተመልከት። ስለዚህም አንተ ልጄ ነህ፤

፬ እናም በማመንህ ምክንያት [ሀ]የተባረክ ነህ፤

፭ እናም ይበልጡን የተባረክ ነህ ምክንያቱም ወንጌሌን እንድትሰብክ በእኔ [ሀ]ተጠርተሀል—

፮ ለጠማማና ክፉ ትውልዶች፣ [ሀ]ለዳግም ምፅአቱ የጌታን መንገድ በማዘጋጀት [ለ]ንስሀን ጩህ እናም ረጅም እና ጉልህ እንደሆነው መለከት ድምጽ ድምጽህን ከፍ አድርግ።

፯ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ በኃይልና በታላቅ ክብር [ሀ]በደመና ውስጥ የምመጣበት [ለ]ጊዜ ተቃርቧልና።

፰ እናም ሁሉም ህዝብ [ሀ]ስለሚንቀጠቀጡ፣ የምጽአቴም ጊዜ [ለ]ታላቅ ቀን ይሆናል።

፱ ነገር ግን ያ ታላቁ ቀን ከመምጣቱ በፊት፣ ጸሀይ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ወደ ደምነት ትለወጣለች፤ እናም ከዋክብትም ብርሀናቸውን መስጠት ይከለክላሉ፣ አንዳንዶቹም ይወድቃሉ፣ እና ታላቅ ጥፋትም ኃጢአተኞችን ይጠብቃቸዋል።

፲ ስለዚህም፣ ጌታ እግዚአብሔር ስለተናገረ፣ ድምጽህን ከፍ አድርገህ ከመናገር [ሀ]አትቆጠብ፣ ስለዚህ ትንቢትን ተናገር፣ እና ይህም በመንፈስ ቅዱስ [ለ]ሀይል አማካይነት ይሰጣል።

፲፩ እናም እምነት ካለህ፣ እነሆ፣ እስከ ምመጣ ድረስ እኔም ከአንተ ጋር ዘወትር እሆናለሁ—

፲፪ እናም እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ በቶሎም እመጣለሁ። እኔ ጌታህ እና ቤዛህ ነኝ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፴፬ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ፕራት፣ ኦርሰን።
፪ሀ ዮሐ. ፩፥፩–፭።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፫ሀ ዮሐ. ፩፥፱–፲፪፤
ሮሜ ፰፥፲፬፣ ፲፮–፲፯፤
ሙሴ ፮፥፷፬–፷፰።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
ለ ዮሐ. ፫፥፲፮፤ ፲፭፥፲፫።
ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ሐ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
መ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣
ቤዛነት፤
የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣
የኃጢያት ክፍያ።
፬ሀ ዮሐ. ፳፥፳፱።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣
በእግዚአብሔር መጠራት፣
የተጠራበት።
፮ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ት. እና ቃ. ፯፥፱።
፯ሀ ሉቃ. ፳፩፥፳፯።
ለ ራዕ. ፩፥፫።
፰ሀ ኢሳ. ፷፬፥፪።
ለ ኢዩ. ፪፥፲፩፤
ሚል. ፬፥፭፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፯–፳፮።
ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፲ሀ ኢሳ. ፶፰፥፩።
ለ ፪ ጴጥ. ፩፥፳፩።

ክፍል ፴፭

በታህሳስ ፯፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ ወይም በአቅራቢያው፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለሲድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። በዚህን ጊዜ ነቢዩ ከሞላ ጎደል በየቀኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተጠምዶ ነበር። ትርጉሙ የተጀመረው በሰኔ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) መባቻ ላይ ነበር፣ እናም ኦሊቨር ካውድሪ እና ጆን ዊትመር እንደ ጸሀፊ በመሆን አገልግለው ነበር። ለሌላም ስራ ስለተጠሩ፣ ስድኒ ሪግደን በመለኮታዊ ምርጫ ለነቢዩ እንደ ጸሀፊ በመሆን እንዲያገለግል ተጠርቶ ነበር (አንቀጽ ፳ን ተመልከቱ)። ከዚህ ራዕይ አስቀድሞ እንደተጻፈው፣ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንዳሚገልጸው፣ “ በታህሳሥ ሲድኒ ሪግደን ከኦሀዮ ጌታን ለመጠየቅ መጣ፣ እናም ከእርሱ ጋርም ኤድዋርድ አብሮት መጥቶ ነበር።. . . ከእነዚህ ወንድሞች መድረስ ጥቂት ጊዜ በኋላ ጌታ ይህን ተናገረ።”

፩–፪፣ እንዴት ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች መሆን እንደሚችሉ፤ ፫–፯፣ ሲድኒ ሪግደን እንዲጠምቅ እና መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጥ ተጠርቷል፤ ፰–፲፪፣ ምልክቶች እና ታእምራት የሚሰሩት በእምነት ነው፤ ፲፫–፲፮፣ የጌታ አገልጋዮች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ህዝብን ያሄዷቸዋል፤ ፲፯–፲፱፣ ጆሴፍ ስሚዝ የሚስጥራቱን ቁልፎች ይዟል፤ ፳–፳፩፣ የተመረጡት ዳግም ምጽአትን ይታገሳሉ፤ ፳፪–፳፯፣ እስራኤል ትድናለች።

፩ [ሀ]አልፋና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያና የመጨረሻ፣ [ለ]መንገዱም አንድ ዘለአለማዊ ዙሪያ የሆነው፣ ዛሬም፣ ትላንት እንዲሁም ለዘለአለም [ሐ]አንድ አይነት የሆነውን [መ]የጌታ አምላካችሁን ድምጽ አድምጡ።

፪ እነርሱ የእግዚአብሔር [ሀ]ልጆች ይሆኑ ዘንድ፣ እንዲሁም እኔ በአብ እንዳለሁ እርሱም በእኔ [ለ]እንዳለ፣ እነርሱም በእኛ [ሐ]አንድ ይሆኑ ዘንድ ለአለም ኃጢአቶች፣ እንዲሁም በእኔ ስም [መ]ለሚያምኑ ሁሉ [ሠ]የተሰቀልኩት የእግዚአብሔር ልጅ የሆንኩት እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ።

፫ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት፣ ለአገልጋዬ ለስዲኒ እናገራለሁ፣ ስራዎችህን እና አንተን ተመልክቻለሁ። ጸሎቶችህን ሰምቻለሁ፣ እናም ለታላቅ ስራም አዘጋጅቼሀለሁ።

፬ ታላላቅ ነገሮችን ስለምታደረግ የተባረክ ነህ። እነሆ እንደ [ሀ]ዮሐንስ፣ በእኔ እና ከሚመጣው [ለ]ኤልያስ በፊትም መንገድን እንድታዘጋጅ ተልከሀል፣ እና መላክህንም አላወክም።

፭ ለንስሀ በውሀ ጠምቀሀል፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን [ሀ]አልተቀበሉም፤

፮ ነገር ግን አሁን በውሀ [ሀ]እንድታጠመቅ ትእዛዛትን እሰጥሀለሁ፣ እናም ልክ እንደ ጥንቶቹ ኃዋሪያት [ለ]እጆችን በመጫን [ሐ]መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ።

፯ እናም እንዲህም ይሆናል ሞኝነታቸውና አጸያፊ ስራቸው ለሁሉም ሰዎች አይን

፴፭ ፩ ሀ ራዕ. ፩፥ ፰።
ቅ.መ.መ. አልፋ
እና ኦሜጋ።
ለ ፩ ኔፊ ፲፥ ፲፱፤
ት. እና ቃ. ፫፥ ፪።
ሐ ዕብ. ፲፫፥ ፰፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥ ፩–፬፤
፴፱፥ ፩–፫።
መ ቅ.መ.መ. ጌታ።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ።
ሐ ዮሐ. ፲፯፥ ፳–፳፫።
ቅ.መ.መ. አንድነት።
መ ት. እና ቃ. ፳፥ ፳፭፤
፵፭፥ ፭፤ ፰።
ሠ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
፬ ሀ ሚል. ፫፥ ፩፤
ማቴ. ፲፩፥ ፲፤
፩ ኔፊ ፲፩፥ ፳፯፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፳፯–፳፰።
ለ ፫ ኔፊ ፳፭፥ ፭–፮፤
ት. እና ቃ. ፪፥ ፩፤
፻፲፥ ፲፫–፲፭።
፭ ሀ የሐዋ. ፲፱፥ ፩–፮።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ለ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ሐ ቅ.መ.መ. የመንፈስ
ቅዱስ ስጦታ።

ግልጽ ስለሚሆን፣ በምድሩ ላይ፣ እንዲሁም [ሀ]በአህዛቦችም መካከል ታላቅ ስራ ይሆናል።

፰ እኔ እግዚአብሔር ነኝና፣ እናም ክንዴም [ሀ]አጭር አይደለም፤ እናም [ለ]ተአምራትን፣ [ሐ]ምልክቶችን፣ እንዲሁም ድንቅ ስራዎችን በስሜ [መ]ለሚያምኑት ሁሉ አሳያለሁ።

፱ እና [ሀ]በእምነት በስሜ የሚጠይቁትም፣ [ለ]ዲያብሎስን [ሐ]ያስወጣሉ፣ የታመሙትንም [መ]ይፈውሳሉ፤ እውሮች ብርሀናቸውን እንዲያገኙ፣ ደንቆሮዎች እንዲሰሙ፣ እናም ዱዳዎች እንዲናገሩ፣ እናም ሽባዎች እንዲራመዱ ያደርጋሉ።

፲ እናም የሰዎች ልጆች ታላላቅ ነገሮችን እንዲያዩ የሚደረጉበት ጊዜ በቶሎ ይመጣል፤

፲፩ ነገር ግን [ሀ]የዝሙቷን ቁጣ ወይን ጠጅ ህዝብ እንዲጠጡ ካደረገችው [ለ]ባቢሎን [ሐ]ጥፋት በስተቀር፣ [መ]ያለእምነት ምንም ነገር እንዲታይ አይደረግም።

፲፪ እናም ለዚህ ትውልድ የላኩትን የወንጌሌን ሙላት ለመቀብል ከተዘጋጁት በስተቀር፣ መልካምን የሚያድርጉ [ሀ]የሉም።

፲፫ ስለዚህ፣ በመንፈሴ ኃይል ህዝብን እንዳውቃቸው [ሀ]ያልተማሩትን እና የተናቁትን፣ የአለም [ለ]ደካማ ነገሮችን እጠራለሁ።

፲፬ እናም ክንዳቸው የእኔ ክንድ ይሆናል፣ እናም [ሀ]ጋሻና መከታ እሆናቸዋለሁ፤ እናም ወገባቸውን አስርላቸዋለሁ፣ እናም ለእኔ በወንድነትም ይዋጋሉ፤ [ለ]ጠላቶቻቸው ከእግሮቻቸው ስር ይሆናሉ፤ ሰይፉንም ስለ እነርሱ [ሐ]እሰነዝራለሁ፣ እናም በንዴቴም [መ]እሳት እጠብቃቸዋለሁ።

፲፭ እናም [ሀ]ለድሆች እና [ለ]ትሁቶች ወንጌል ይሰበክላቸዋል፣ እናም የምጽአቴንም ጊዜ [ሐ]ይጠባበቃሉ፣ ይህም [መ]ተቃርቧልና—

፲፮ እናም አሁን የበጋም ወቅት ስለተቃረበ፣ [ሀ]የበለሱን ዛፍ ምሳሌ ትምህርት ይማራሉ።

፲፯ እናም የወንጌሌን [ሀ]ሙላት በአገልጋዬ [ለ]በጆሴፍ እጅ ልኬአለሁ፤ እናም በድክመቱም ባርኬዋለሁ፤

፲፰ እናም [ሀ]የታተሙትን የሚስጥራቱን [ለ]ቁልፎች፣ እንዲሁም አለም [ሐ]ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ያሉትን ነገሮች፣ እናም በእኔ የሚያምን ከሆነ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከእኔ ምጽአት ድረስ የሚመጡትን ነገሮች ሰጥቼዋለሁ፣ የማያምን ከሆነ በእርሱ ምትክ ሌላ ሰው አደርጋለሁ።

፲፱ ስለዚህ፣ ከእምነቱ እንዳይሰናከል ጠብቀው፣ እናም ሁሉንም ነገሮች በሚያውቀው [ሀ]በአጽናኙ [ለ]በመንፈስ ቅዱስ ይህም ይሰጣል።

፳ እናም ለእርሱም [ሀ]እንድትጽፍ ትእዛዝን እሰጥሀለሁ፤ እናም በልቤ ውስጥ ያሉትን

፯ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
፰ ሀ ኢሳ. ፶፥፪፤ ፶፱፥፩።
ለ ቅ.መ.መ. ተአምራት።
ሐ ቅ.መ.መ. ምልክት።
መ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ማር. ፩፥፳፭–፴፭።
ሐ ማር. ፲፮፥፲፯።
መ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።
፲፩ ሀ ራዕ. ፲፰፥፪–፬።
ለ ቅ.መ.መ. ባቢሎን።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፥፲፱–፳።
መ ት. እና ቃ. ፷፫፥፲፩–፲፪።
፲፪ ሀ ሮሜ ፫፥፲–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፴፫፥፬፤ ፴፰፥፲–፲፩፤ ፹፬፥፵፱።
፲፫ ሀ የሐዋ. ፬፥፲፫።
ለ ፩ ቆሮ. ፩፥፳፯፤ ት. እና ቃ. ፩፥፲፱–፳፫፤ ፻፳፬፥፩።
፲፬ ሀ ፪ ሳሙ. ፳፪፥፪–፫።
ለ ት. እና ቃ. ፺፰፥፴፬–፴፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬።
መ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፳፬።
፲፭ ሀ ማቴ. ፲፩፥፭።
ለ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ሐ ፪ ጴጥ. ፫፥፲–፲፫፤ ት. እና ቃ. ፵፱፥፳፫፤ ፵፭፥፴፱፤ ሙሴ ፯፥፷፪።
መ ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፫።
፲፮ ሀ ማቴ. ፳፬፥፴፪፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፴፮–፴፰፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፰። ቅ.መ.መ. የጊዜዎች ምልክቶች።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፲፪።
ለ ት. እና ቃ. ፻፴፭፥፫።
፲፰ ሀ ዳን. ፲፪፥፱፤ ማቴ. ፲፫፥፴፭፤ ፪ ኔፊ ፳፯፥፲–፲፩፤ ኤተር ፬፥፬–፯፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፭።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፱።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፰።
፲፱ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፲፮፣ ፳፮፤ ፲፭፥፳፮። ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፳ ሀ ነቢዩ በዚያ ጊዜ መፅሐፍ ቅዱስን በራዕይ በሚተረጉምበት ስራ ላይ ነበር፣ ለዚህም ስድኒ ሪግደን እንደ ጸሀፊ ተጠርቶ ነበር።

ቅዱሳን መጻህፍት እንኳን በእኔ [ለ]ለተመረጡት መዳን ይሆን ዘንድ ይሰጣል።

፳፩ [ሀ]ድምጼንም ይሰማሉ፣ እኔንም ያያሉ፣ እናም እንቅልፍም አይተኙም፣ እናም [ለ]የምጽአቴንም ቀን [ሐ]ይጠባበቃሉ፤ እኔም [መ]ንጽሁ እንደሆንኩት ሁሉ እነርሱም ንጹኃን ይሆናሉና።

፳፪ እናም አሁን [ሀ]ለአንተ እንዲህ እልሀለሁ፣ ከእርሱ ጋር ቆይ፣ እናም ከአንተ ጋርም ይጓዛል፤ አትተወው፣ እናም በእርግጥም እነዚህ ነገሮች ይፈጸማሉ።

፳፫ እስካልጻፋችሁ [ሀ]ድረስ፣ እነሆ፣ ለእርሱ እንዲተነብይ ይሰጠዋል፤ እና አንተም ወንጌሌን ትሰብካለህ እናም ለእርሱ በተሰጡ መጠን ቃላቶቹን ያረጋግጡ ዘንድ [ለ]ቅዱሳን ነቢያትን ትጠቅሳለህ።

፳፬ የታሰራችሁበትን ትእዛዛት እና ቃል ኪዳኖች [ሀ]ጠብቁ፤ እናም መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ ሰማያትን [ለ]አናውጣለሁ፣ እና [ሐ]ሰይጣንም ይንቀጠቀጣል እናም ፅዮንም በከፍታዎች ላይ [መ]ሀሴትን ታደርጋለች እናም ታብባለች፤

፳፭ እና [ሀ]እስራኤልም በእኔ ጊዜ [ለ]ትድናለች፤ እናም በሰጠሁት [ሐ]ቁልፎችም ይመራሉ፤ እናም ከአሁን በኋላ በፍጹምም አያፍሩም።

፳፮ ልባችሁን አቅኑ ሀሴትንም አድርጉ፣ [ሀ]መዳናችሁ ቀርቧልና።

፳፯ እናንተ ትንንሽ መንጎች፣ አትፍሩ፣ እስከምመጣ ድረስ [ሀ]መንግስቱ የእናንተ ነው። እነሆ፣ [ለ]በቶሎም እመጣለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፴፮

ታህሳሥ ፱፣ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ አቅራቢያ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለኤድዋርድ ፓርትሪጅ የተሰጠ ራዕይ (የክፍል ፴፭ ርዕስን ተመልከቱ)። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ስለኤድዋርድ ፓርትሪጅ እንደገለጸው "የቅድስና ምሳሌ፣ እና ከጌታ ታላላቅ ሰዎች አንዱ ነው።"

፩–፫፣ በስድኒ ሪግደን አማካይነት ጌታ እጁን በኤድዋርድ ፓርትሪጅ ላይ ጭኗል፤ ፬–፰፣ ወንጌልንና ክህነትን የሚቀበል ወንድ ሁሉ እንዲሄድ እና እንዲሰብክ ይጠራል።

፩ የእስራኤል [ሀ]ኃያል የሆነው፣ ጌታ አምላክ እንዲህ ይላል፥ እነሆ፣ አገልጋዬ [ለ]ኤድዋርድ እንዲህ እልሀለሁ፣ አንተ የተባረክህ ነህ፣ እናም ኃጢአትህም ተሰርዮልሀል፣ እንዲሁም እንደመለከት ድምጽ ወንጌሌን እንድትሰብክ ተጠርተሀል፤

፪ እናም በአገልጋዬ በስድኒ ሪግደን [ሀ]እጄን በአንተ ላይ እጭናለሁ፣ እናም የመንግስትን [ለ]የሰላም ነገሮች የሚያስተምርህን [ሐ]አጽናኝ የሆነውን መንፈሴን፣ መንፈስ ቅዱስን ትቀበላለህ።

፳ ለ ቅ.መ.መ. ምርጦች።
፳፩ ሀ ኢዩ. ፪፥፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፯–፳፭፤
፹፰፥፺፤ ፻፴፫፥፶–፶፩።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ሐ ሚል. ፫፥፪–፫።
መ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፥፱–፲፩።
፳፫ ሀ ይህም ስድኒ ሪግደን በመጻፍ ላይ ባልነበረበት ጊዜ ማለት ነው።
ለ ይህም ቅዱሳት መጻህፍት ማለት ነው።
፳፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፫፥፯።
ለ ፩ ኔፊ ፳፪፥፳፮።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፩፥፮።
መ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል።
ለ ኢሳ. ፵፭፥፲፯፤
፩ ኔፊ ፲፱፥፲፭–፲፮፤ ፳፪፥፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፳፮ ሀ ሉቃ. ፳፩፥፳፰።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ራዕ. ፳፪፥፳።
፴፮ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ያህዌህ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፩፥፱–፲፩።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፩።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ አፅናኝ።

ሳን እንዳይድገሉ፣ እንዳይሰርቁ፣ ሀሰትን እንዳይናገሩ፣ እንዳይመኙ፣ እንዳያመነዝሩ፣ ወይም በሌሎች ላይ ርኩሰትን እንዳይናገሩ ታዘዋል፤ ፴–፴፱፣ የንብረቶች ቅደሳን የሚመሩ ህግጋቶች ተሰጥተዋል፤ ፵–፵፪፣ ትዕቢት እና ስራ ፈትነት የተረገሙ ናቸው፤ ፵፫–፶፪፣ ህሙማን በአገልግሎት እና በእምነት ይፈወሳሉ፤ ፶፫–፷፣ ቅዱሳን መጻህፍት ቤተክርስቲያኗን ይገዛሉ እናም ለአለምም ይሰበካሉ፤ ፷፩–፷፱፣ የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ስፍራ እና የመንግስተ ሰማይ ሚስጥራት ይገለጣሉ፤ ፸–፸፫፣ የተቀደሱ ንብረቶች የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን ለመርዳት ጥቅም ላይ ይውላሉ፤ ፸፬–፺፫፣ ዝሙትን መፈጸም፣ አመንዝራነትን፣ ግድያን፣ ስርቆትን፣ ኃጢአትን መናዘዝን የሚገዙ ህግጋት ተሰጥተዋል።

፩ በስሜ ባመናችሁና ትእዛዛቴን በጠበቃችሁ መጠን፤ የአለም አዳኝ፣ የህያው እግዚአብሔር ልጅ በሆንኩት በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በስሜ ራሳችሁን ያሰባሰባችሁ አቤቱ እናንት የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ አድምጡ።

፪ ደግሞም እንዲህ እላችኋለሁ፣ አድምጡ ስሙ እንዲሁም በምሰጣችሁም [ሀ]ህግ ታዘዙ።

፫ እውነት እላለሁ፣ [ሀ]ባዘዝኳችሁ ትእዛዝ መሰረት ራሳችሁን አንድ ላይ እንዳሰባሰባችሁ፣ እናም ይህን አንድ ነገር [ለ]በተመለከተ ስለተስማማችሁ፣ እናም በስሜ አብን ስለ ጠየቃችሁ እንዲሁ ትቀበላላችሁ።

፬ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከአገልጋዮቼ ከጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ እና ከስድኒ ሪግደን በቀር ሁላችሁም በስሜ ወደፊት ትሄዱ ዘንድ ይህን የመጀመሪያ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፭ እናም ለእነርሱም ለተወሰነ ወቅት ይሄዱ ዘንድ ትእዛዝን እሰጣቸዋለሁ፣ እናም መቼ እንደሚመለሱም [ሀ]በመንፈስ ኃይል አማካይነት ይሰጣቸዋል።

፮ እናም እንደ መለከት ድምጽ ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ፣ ልክ እንደ እግዚአብሔር መላእክት ቃሌን በማወጅ፣ በመንፈሴ ኃይል ወንጌሌን በመስበክ [ሀ]ሁለት በሁለት በመሆን ወደፊት ትሄዳላችሁ።

፯ እናም ንስሀ ግቡ፣ ንስሀ ግቡ መንግስተ ሰማይ ተቃርባለችና በማለት በውሀ እያጠመቃችሁ ትሄዳላችሁ።

፰ እናም ከዚህም ስፍራ በምዕራብ አቅጣጫ ወዳሉ ክልሎች ትሄዳላችሁ፤ እናም የሚቀበሏችሁን ባገኞችኋቸው መጠን በሁሉም ክልሎች ቤተክርስቲያኔን ትገነባላችሁ—

፱ በአንድ [ሀ]ተሰብስባችሁ እናንት [ለ]ህዝቤ እኔም አምላካችሁ እሆን ዘንድ [ሐ]አዲሲቷም የኢየሩሳሌም [መ]ከተማ የምትዘጋጅበት ጊዜው ከላይ የሚገለጥበት ጊዜ እስከሚመጣ ድረስ ቤተክርስቲያኔን ትገነባላችሁ።

፲ እናም ዳግም፣ እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እንደሾምኩት ስራውን ያከናውን። እና እንዲህም ይሆናል፤ የሚተላለፈ ከሆነ በእርሱ ስፍራ [ለ]ሌላ ይሾማል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፲፩ ዳግም እላችኋለሁ፣ [ሀ]ስልጣን ባለው [ለ]ካልተሾመ፣ እና ስልጣንም እንዳለው በቤተክርስቲያኗ የሚታወቅ እና በቤተክርስቲያኗ መሪዎችም ዘንድ በትክክለኛው መን

፵፪ ፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፫።
ቅ.መ.መ. ህግ።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፪።
ለ ማቴ. ፲፰፥፲፱።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፮ ሀ ማር. ፮፥፯።
ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ለ ዘካ. ፰፥፰።
ሐ ኤተር ፲፫፥፪–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፮–፸፩፤ ፹፬፥፪–፭፤ ሙሴ ፯፥፷፪፤ እ.አ. ፩፥፲።
ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
መ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፪።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፵፩፥፱–፲፩፤ ፻፳፬፥፲፱።
ለ ት. እና ቃ. ፷፬፥፵።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ስልጣን፤ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት፤ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።

ገድ የተሾመ ካልሆነ በስተቀር፣ ለማንም ወንጌሌን [ሐ]እንዲሰብክ ወይም ቤተክርስቲያኔን እንዲገነባ አይሰጠውም።

፲፪ እናም ዳግም፣ የዚህች ቤተክርስቲያን [ሀ]ሽማግሌዎች፣ ካህናት እና መምህራን [ለ]በመፅሐፍ ቅዱስ እና [ሐ]የወንገሌ ሙላት በሚገኝበት [መ]በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ የሚገኙትን የወንጌሌን መሰረታዊ መርሆች [ሠ]ያስተምራሉ።

፲፫ እናም [ሀ]ቃል ኪዳኖቹን እና የቤተክርስቲያን መመሪያዎችን አክብረው ያድርጉ፣ በመንፈስ ሲመሩም፣ እነዚህ የእነርሱ ትምህርት ይሆናሉ።

፲፬ እናም በእምነት [ሀ]ጸሎትም መንፈስ ይሰጣችኋል፤ እናም [ለ]መንፈስን ካልተቀበላችሁ አታስተምሩምና።

፲፭ እናም [ሀ]የቅዱስ መጽሐፍቴ ሙላት እስኪሰጥ ድረስ ትምህርታችሁን በተመለከተ እንዳዘዝኳችሁ በማክበር ይህን ሁሉ አድርጉ።

፲፮ እናም [ሀ]በአጽናኙም አማካይነት ድምጻችሁን ከፍ ስታደርጉ፣ እኔን መልካም እንደመሰለኝ ትናገራላችሁ እናም ትተነብያላችሁ፤

፲፯ ስለሆነም፣ አጽናኙ ሁሉንም ነገሮች ያውቃል፣ እናም ስለአብ እና ስለወልድ ይመሰክራል።

፲፰ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ለቤተክርስቲያኗ እናገራለሁ። [ሀ]አትግደሉ፤ እናም [ለ]የሚገድል በዚህም አለም ሆነ በሚመጣው አለም ይቅርታን አያገኝም።

፲፱ እናም ዳግም፣ አትግደል እላለሁ፤ ነገር ግን የሚገድል እርሱ [ሀ]ይሞታል።

፳ [ሀ]አትስረቅ፤ የሚሰርቅ እና ንስሀ የማይገባ ወደውጭ ይጣላል።

፳፩ [ሀ]ሀሰትን አትናገር፤ ሀሰት የሚናገር እናም ንስሀ የሚይገባ ወደውጭ ይጣላል።

፳፪ ሚስትህን በፍጹም ልብህ [ሀ]ውደዳት፣ እናም ከሚስትህም በስተቀር ከማንም ጋር [ለ]አትጣመር።

፳፫ እናም ሴትን [ሀ]በምኞት የሚመለከት እምነትን ይክዳል፣ እናም መንፈስም አይኖረውም፤ እናም ንስሀ ካልገባ ወደውጭ ይጣላል።

፳፬ [ሀ]አታመንዝር፤ እናም የሚያመነዝር፣ እናም ንስሀ የማይገባ፣ እርሱ ወደ ውጭ ይጣላል።

፳፭ ነገር ግን የሚያመነዝር እና በፍጹም ልቡ [ሀ]ንስሀ የሚገባ፣ እናም የሚትውና ዳግም የማያደርገውን፣ እርሱን [ለ]ይቅርትሉታላችሁ፤

፳፮ ነገር ግን [ሀ]ዳግም የሚያደርገው ቢሆን፣ ይቅርታ አይደረግለትም፣ ነገር ግን ወደውጭ ይጣላል።

፳፯ በባልንጀራህ ላይ [ሀ]ክፉትን አትናገር፣ እንዲሁ ጉዳትንም አታድርግ።

፳፰ እነዚህን ነገሮች በተመለከተ በቅዱሳት መጻህፍቴ ውስጥ የተሰጡትን ህግጋቴን

፲፩ሐ ቅ.መ.መ. መስበክ።

፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።

ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፍ ቅዱስ።

ሐ ቅ.መ.መ. ወንጌል።

መ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን፤ ቅዱሳት መጻህፍት— የቅዱሣት መጻህፍት ዋጋዎች።

ሠ ሞዛያ ፲፰፥፲፱–፳፤ ት. እና ቃ. ፶፪፥፱፣ ፴፮። ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ።

፲፫ ሀ ይህም ት. እና ቃ. ፳ (የክፍል ፳ ርዕስን ተመልከቱ) ማለት ነው።

፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፷፬። ቅ.መ.መ. ጸሎት።

ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ ማስተማር፣ አስተማሪ— በመንፈስ ማስተማር።

፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፶፮–፶፰።

፲፮ ሀ ፩ ቆሮ. ፪፥፲–፲፬፤ ት. እና ቃ. ፳፰፥፪–፬። ቅ.መ.መ. አፅናኝ።

፲፰ ሀ ዘፀአ. ፳፥፲፫–፲፯፤ ማቴ. ፭፥፳፩–፴፯፤ ፪ ኔፊ ፱፥፴፭፤ ሞዛያ ፲፫፥፳፩–፳፬፤ ፫ ኔፊ ፲፪፥፳፩–፴፯።

ለ ቅ.መ.መ. ግድያ።

፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. የሞት ቅጣት።

፳ ሀ ቅ.መ.መ. መስረቅ።

፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሐሰት፤ ታማኝ፣ ታማኝነት።

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት፤ ፍቅር።

ለ ዘፍጥ. ፪፥፳፫–፳፬፤ ኤፌ. ፭፥፳፭፣ ፳፰–፴፫።

፳፫ ሀ ማቴ. ፭፥፳፰፤ ፫ ኔፊ ፲፪፥፳፰፤ ት. እና ቃ. ፷፫፥፲፮። ቅ.መ.መ. ምኞት።

፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።

፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።

ለ ዮሐ. ፰፥፫–፲፩። ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።

፳፮ ሀ ፪ ጴጥ. ፪፥፳–፳፪፤ ት. እና ቃ. ፹፪፥፯።

፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. አሉባልታ።

፫ እናም ሆሳዕና፣ ልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን በማለት፣ ከፍ ባለ ድምጽም ታውጀዋለህ።

፬ እናም አሁን ሰዎችን ሁሉ በተመለከተ፣ ይህን ጥሪና ትእዛዝ እሰጥሀለሁ—

፭ በአገልጋዮቼ በስድኒ ሪግደን እና በጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ ፊት ይህንን ጥሪና ትእዛዝ ተቀብለው የሚመጡት ሁሉ፣ [ሀ]ይሾማሉ እናም በአህዛብ መካከል ዘለአለማዊ ወንጌሌን [ለ]እንዲሰብኩ ይላካሉ—

፮ ንስሀንም በመጮህ፣ እንዲህ ይበሉ፥ ከዚህ ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን [ሀ]አድኑ፣ እናም ከእሳት ውስጥም ተነጥቃችሁ ውጡ፣ በረከሰ ስጋ የተበከለውንም [ለ]ልብስ ተጸየፉ።

፯ እኔ እንደተናገርኩት በአንድ ልብ ይህን የሚቀበል ሁሉ እንዲሾምና እንዲላክ ይህ ትእዛዝ ለቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ይሰጣል።

፰ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ፤ ስለዚህ ወገባችሁን እሰሩ እናም በድንገትም ወደ [ሀ]ቤተመቅደሴ እመጣለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፴፯

ታህሳሥ ፲፰፻፴ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ አቅራቢያ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ዘመን መሰባሰብን በተመለከተ የመጀመሪያው ትእዛዝ የተሰጠው በዚህ ውስጥ ነው።

፩–፬፣ ቅዱሳን በኦሀዮ እንዲሰባሰቡ ተጠሩ።

፩ እነሆ፣ ኦሀዮ እስክትሄዱ ድረስ [ሀ]መተርጎም መቀጠልህ ለእኔ አስፈላጊ አይደለም፣ እና ይህም የሚሆነው በጠላት ምክንያት እና ለአንተ ደህንነት ነው።

፪ እናም ዳግም እንዲህ እልሀለሁ፣ በእነዚያ ስፍራዎች ወንጌሌን እስክትሰብክ እናም ቤተክርስቲያኔ በሚገኝበት ስፍራ ሁሉ፣ በተለይም [ሀ]በኮለስቪል የሚገኘውን እስከምታጠነክር ድረስ አትሄድም፤ እነሆም፣ በታላቅ እምነትም ወደ እኔ ይጸልያሉና።

፫ እናም ዳግም፣ አገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ለሚመለስበት ጊዜ ለመዘጋጀት፣ [ሀ]በኦሀዮ አንድ ላይ መሰብሰባቸው አስፈላጊ እንደሆነ ትእዛዝን ለቤተክርስቲያኗ እሰጣለሁ።

፬ እነሆ፣ ጥበብ በእዚህ ይላል፣ እናም እኔ እስክመጣ ድረስ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ [ሀ]ይምረጥ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፴፰

ጥር ፪፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የተሰጠ ራዕይ። ወቅቱ የቤተክርስቲያን ጉባዔ የሚካሄድበት ነበር።

፭ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፯።
ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ለ ቅ.መ.መ. መስበክ።
፮ሀ የሐዋ. ፪፥፵።
ለ ይሁዳ ፩፥፳፫።
፰ሀ ሚል. ፫፥፩።
፴፯ ፩ሀ ይህም በመተርጎም ላይ ያለው መፅሐፍ ቅዱስ ማለት ነው።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፳፬፥፫፤ ፳፮፥፩።
፫ሀ ይህም የኦሀዮ ስቴት ማለት ነው። ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፩–፴፪።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።

፩–፮፣ ክርስቶስ ሁሉን ነገሮች ፈጠረ፤ ፯–፰፣ እርሱም በቅርብ በሚያዩት በቅዱሳኑ መካከል ነው፤ ፱–፲፪፣ ሁሉም ስጋ በእርሱ ፊት በስባሽ ነው፤ ፲፫–፳፪፣ ለጊዜአዊ እና ለዘለአለም የሚሆን የቃል ኪዳን ምድርን ለጻድቃኖቹ አስቀምጧል፤ ፳፫–፳፯፣ ቅዱሳን አንድ እንዲሆኑ እና እርስ በራሳቸው እንደ ወንድም እንዲተያዩ ታዘዋል፤ ፳፰–፳፱፣ የጦርነቶች ትንቢቶች ተነግረዋል፤ ፴–፴፫፣ ቅዱሳን ከላይ ስልጣን ይሰጣቸዋል እናም በሁሉም ህዘቦች መካከልም ይሄዳሉ፤ ፴፬–፵፪፣ ቤተክርስቲያኗ ድሆችን እና የተቸገሩን እንድትንከባከብ እና ዘለአለማዊ ሀብትን እንድሻ ታዛለች።

፩ ጌታ አምላካቹ፣ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ታላቁ [ሀ]እኔ ነኝ፣ አልፋ እና ኦሜጋ፣ [ለ]የመጀመሪያው እና የመጨረሻው፣ አለም ከመፈጠሩ [ሐ]አስቀድሞ [መ]በከፍታና በተቀደሰ ስፍራ ዘለአለማዊነትን እና ሁሉን የሰማይ ሱራፌላዊ [ሠ]ሰራዊትን የተመለከተው እንዲህ ይላል፤

፪ ሁሉንም ነገሮች [ሀ]የሚያውቀው እንዲህ ይላል፣ ምክንያቱም [ለ]ሁሉም ነገሮች በአይኖቼ ፊት ናቸውና፤

፫ የተናገርኩትም እኔ ነኝ፣ እናም አለም በእኔ [ሀ]ሆነ፣ እናም ሁሉም ነገሮች በእኔ መጡ።

፬ የሔኖክን [ሀ]ፅዮን ወደ እቅፌ የወሰድኩ እኔው ነኝ፤ እናም እውነት፣ እላለሁ፣ በስሜ [ለ]የሚያምኑ ሁሉ፣ እኔ ክርስቶስ በመሆኔ፣ በስሜ፣ ባፈሰስኩት [ሐ]ደም ምክንያት በአብ ፊት አማልጃቸዋለሁ።

፭ ነገር ግን እነሆ፣ በምድር ዳርቻ በሚመጣው እስከ ታላቁ [ሀ]ፍርድ ቀን ድረስ የቀሩትን [ለ]ኃጢአተኞች በጨለማ [ሐ]ሰንሰለት ውስጥ አስቀምጫቸዋለሁ።

፮ እናም ድምጼን የማይሰማው እና ግን ልባቸውን የሚያደነድኑት ጥፋተኞች እንዲሁ እንዲቀመጡ አደርጋለሁ፣ እናም ወዮላቸው ጥፋታቸው ይሆናል።

፯ ነገር ግን እነሆ፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]አይኖቼም በእናንተ ላይ ናቸው። እኔም [ለ]በመካከላችሁ ነኝ እናም እናንተም አታዩኝም፤

፰ ነገር ግን [ሀ]የምታዩኝም ቀን በቶሎ ይመጣል፣ እናም እኔም እንደሆንኩ ታውቃላችሁ፤ የጨለማም መጋረጃም ይገፈፋል፣ እናም [ለ]ያልነጻ እርሱ ቀኑን [ሐ]አይቋቋምም።

፱ ስለዚህ፣ ወገባችሁን ታጠቁ እናም ተዘጋጁ። እነሆ፣ [ሀ]መንግስትም የእናንተ ናት፣ እናም ጠላትም አይቋቋማችሁም።

፲ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]ንጹሐን ናችሁ፣ ነገር ግን ሁላችሁም አይደላችሁም፤ እናም ከእናንተ ሌላ [ለ]የተደሰትኩበት ማንም የለም፤

፲፩ በፊቴ ሁሉም [ሀ]ስጋ በስባሽ ነው፤ እናም በምድር ላይ፣ በሰው ልጆች መካከል፣ እና በሁሉም የሰማይ ሰራዊት ፊት [ለ]የጭለማው ሀይል እያሸነፈ ነው—

፴፰፩ሀ ቅ.መ.መ. ያለና የሚኖር።
ለ ራዕ. ፩፥፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
መ መዝ. ፺፥፪።
ሠ ት. እና ቃ. ፵፭፥፩።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፵፩፤ ሙሴ ፩፥፴፭። ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
ለ ምሳ. ፭፥፳፩፤ ፪ ኔፊ ፱፥፳።
፫ሀ መዝ. ፴፫፥፮–፱። ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
፬ሀ ጆ.ስ.ት. ዘፍጥ. ፲፬፥፳፭–፵ (ተጨማሪ)፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፲፩–፲፬፤ ፸፮፥፷፮–፷፯፤ ፹፬፥፺፱–፻፤ ሙሴ ፯፥፲፰–፷፱። ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፳፥፳፮፤ ፴፭፥፪፤ ፵፭፥፫–፭።
ሐ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ለ ቅ.መ.መ. ኃጢያተኛ፣ አመፃ።
ሐ ፪ ጴጥ. ፪፥፬፤ ይሁዳ ፩፥፮። ቅ.መ.መ. ሲዖል።
፯ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፩።
ለ ት. እና ቃ. ፮፥፴፪፤ ፳፱፥፭።
፰ሀ ራዕ. ፳፪፥፬–፭። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ሐ ሚል. ፫፥፪።
፱ሀ ሉቃ. ፮፥፳። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
፲ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ እና ርኩስ።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፴።
፲፩ሀ ኢሳ. ፩፥፫–፬፤ ት. እና ቃ. ፹፪፥፮።
ለ ሚክ. ፫፥፮፤ ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፳፫፤ ሙሴ ፯፥፷፩–፷፪።

፲፪ ይህም ዝምታ እንዲነግስ አደረገ፣ እናም ዘለአለማዊውም ሁሉ [ሀ]ተጎድቷል፣ እናም [ለ]መላእክትም [ሐ]ገለባውን ሰብስበው [መ]እንዲያቃጥሉ ምድርን [ሠ]የሚሰበሰቡበትን ታላቁን ትእዛዝ እየጠበቁ ናቸው፤ እናም፣ እነሆ ጠላትም ተባብሯል።

፲፫ እናም አሁን በጊዜ ሂደትም [ሀ]ጥፋታችሁ እንዲፈጸም፣ እልፍኝ ውስጥ ተቀምጦ የነበረውን አንድ ሚስጥርም አሳያችኋለሁ፣ እናም እናንተም አላወቃችሁትም፤

፲፬ ነገር ግን ይህን ለእናንተ እናገረዋለሁ፣ እና እናንተም የተባረካችሁት በኃጢአታችሁ ወይም በልባችሁ አለማመን ምክንያት አይደለም፤ አንዳንዶቻችሁ በፊቴ ጥፋተኞች ብትሆኑም፣ ነገር ግን ለድክመታችሁ ምህረትን አደርጋለሁ።

፲፭ ስለዚህ፣ ከአሁን ጊዜ ጀምሮ [ሀ]ብርቱዎች ሁኑ፤ [ለ]አትፍሩ፣ መንግስተ ሰማይ የእናንተ ናትና።

፲፮ እናም ለደህንነታችሁ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ፣ ጸሎታችሁንም ሰምቻለሁና፣ እናም [ሀ]ድሆችም በፊቴ አጉረምርመዋል፣ እናም [ለ]ባለጠጎችንም የሰራኋቸው እኔው ነኝ፣ ስጋ ለባሽ ሁሉ የእኔ ነው፣ እኔም ለማንም [ሐ]አላደላም።

፲፯ እናም ምድርን ባለጸጋ እንድትሆን አድርጌአለሁ፣ እናም እነሆ [ሀ]የእግሬ መረገጫ ናት፣ ስለዚህም ዳግምም እቆምባታለሁ።

፲፰ እናም ጌታ በሚመጣበት ጊዜ እርግማን የሌለበትን ማር እና ወተት የሚፈስበትን እንዲሁም የቃል ኪዳንን ምድር፣ ከሁሉም በላይ ታላቅ የሆኑትን ሀብቶች፣ እሰጣችሁ ዘንድ እጄን እዘረጋለሁ እናም ይህም ይሆን ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፲፱ እናም በሙሉ ልባችሁ የምትሹ ቢሆን የምትወርሱት ምድር እንዲሆን እሰጣችኋለሁ።

፳ እናም ይህም ከእናንተ ጋር ቃልኪዳኔ ይሆናል፣ ለዘለአለም፣ ምድርም እስከ ቆመች ድረስ፣ ይህ ለእናንተ [ሀ]ውርስ ምድር እናም ለልጆቻችሁም የውርስ ይሆንላችኋል፣ እናም ደግሞም ለዘለአለም ዳግም ላያልፍ የእናንተ ይሆናል።

፳፩ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ በዚያን ጊዜ [ሀ]ንጉስም ሆነ ገዢ አይኖራችሁም፣ እኔ ንጉሳችሁ እሆናለሁ እናም እጠብቃችኋለሁና።

፳፪ ስለዚህ፣ ድምጼን ስሙና [ሀ]ተከተሉኝ፣ እናም [ለ]ነፃ ህዝብም ትሆናላችሁ፣ እናም እኔ በምመጣበት ጊዜ ከእኔ ህግ በስተቀር ሌሎች ሕጎች አይኖሯችሁም፣ [ሐ]ህግን የምሰጣችሁ እኔ ነኝና፣ እናም እጄንስ ምን ያግደዋል?

፳፫ ነገር ግን፣ እላችኋለሁ፣ በሾምኳችሁ ስልጣን መሰረት እርስ በርስ [ሀ]ተማማሩ።

፳፬ እናም እያንዳንዱ ሰው ወንድሙን [ሀ]እንደራሱ ይመልከት፣ እናም በፊቴ [ለ]መልካምነትን እና [ሐ]ቅድስናን ተለማመዱ።

፳፭ እናም ዳግም እላችኋለሁ፣ ሁሉም ሰው ወንድሙን እንደራሱ ይመልከት።

፳፮ ከእናንተ መካከል አስራ ሁለት ልጆች ኖሮት፣ እነርሱም በታዛዥነት እያ

፲፪ ሀ ሙሴ ፯፥፵፰።
ለ ት. እና ቃ. ፹፮፥፫–፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፬፤ ፻፩፥፷፭–፷፮።
መ ማቴ. ፲፫፥፴።
ሠ ቅ.መ.መ. መከር።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፴፪–፴፫።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. መበርታት፣ ብርቱነት።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርሀት—ሰውን መፍራት።
፲፮ ሀ ሞዛያ ፬፥፲፮–፲፰።
ለ ፩ ሳሙ. ፪፥፯።
ሐ የሐዋ. ፲፥፴፬፤ ሞሮኒ ፰፥፲፩–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፩፥፴፬–፴፭።
፲፯ ሀ ፩ ኔፊ ፲፯፥፴፮፤ አብር. ፪፥፯።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፰።
፳፩ ሀ ዘካ. ፲፬፥፱፤ ፪ ኔፊ ፲፥፲፬፤ አልማ ፭፥፶።
፳፪ ሀ ዮሐ. ፲፥፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት።
ሐ ኢሳ. ፴፫፥፳፪፤ ሚክ. ፬፥፪፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፱።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፯–፸፱፣ ፻፲፰፣ ፻፳፪።
ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ።
፳፬ ሀ ዘዳግ. ፲፯፥፳፤ ፩ ቆሮ. ፬፥፮።
ለ ት. እና ቃ. ፵፮፥፴፫።
ቅ.መ.መ. በጎነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅድስና።

ገለገሉት፣ እናም ለአንዱ፥ ያማረ ልብሰ ለብሰህ እዚህም ተቀመጥ፤ ለሌላኛውም፥ ብጣሽ ልብስ ለብሰህ እዚህ ተቀመጥ በማለት በእነርሱ ላይ አድሎን የሚያደርግ ማን ሰው በመካከላችሁ አለ—እናም ልጆቹን ተመልክቶ እኔ ፍትሀዊ ነኝ የሚል ማን ነው?

፳፯ እነሆ፣ ይህን ለእናንተ እንደምሳሌ ሰጥኳችሁ፣ እናም እኔም እንዲሁ ነኝና። እንዲህ እላችኋለሁ፣ [ሀ]አንድ ሁኑ፤ እናም አንድ ካልሆናችሁ የእኔ አይደላችሁም።

፳፰ እናም ዳግም፣ ጠላትም በተሰውረ ስፍራ ሆኖ [ሀ]ሕይወታችሁን ይፈልጋል እላችኋለሁ።

፳፱ ሩቅም ከሆኑ ሀገሮች [ሀ]ጦርነትን ትሰማላችሁ፣ እናም ሩቅ ባሉ ሀገራትም ታላቅ ጦርነት በቅርቡም ይሆናል ትላላችሁ፣ ነገር ግን በምድራችሁ የሚገኙትን ህዝብ ልብ አታውቁም።

፴ በጸሎቶቻችሁ ምክንያት እነዚህ ነገሮችን እነግራችኋለሁ፤ ስለዚህ በልባችሁ [ሀ]ጥበብን [ለ]አከማቹ፣ አለበለዚያ የሰዎች ኃጢአት መሬትን በሚነቀንቅ እና ከፍ ባለ ድምጽ በጆሮቻችሁ በመናገር፣ በኃጢአታቸው እነዚህ ነገሮች እንዲገለጡ ያደርጉላችኋል፤ ነገር ግን ከተዘጋጃችሁ ፍርሀት አይኖራችሁም።

፴፩ እናም የጠላትን ኃይል ታመልጡ ዘንድ፣ እናም [ሀ]እንከን የሌላችሁ እና ያልነቀፉ ጻድቅ ህዝብ በመሆን ትሰበሰቡ ዘንድ—

፴፪ ስለዚህ፣ በዚህም ምክንያት ወደ [ሀ]ኦሀዮ እንድትሄዱ ትእዛዛትን ሰጥኳችሁ፤ በዚያም [ለ]ህጌን እሰጣችኋለሁ፤ እና በዚያም ከላይ የሚመጣ ኃይል [ሐ]ትቀበላላችሁ።

፴፫ እናም ከዚያም ስፍራ፣ ፍቃዴ የሆነላቸው በሁሉም ህዝብ መካከል [ሀ]ይሄዳሉ፣ እና ምን እንደሚያደርጉም ይነገራቸዋል፤ ያስቀመጥቁት ታላቅም ስራ አለኝና፣ እስራኤልም [ለ]ትድናለችና፣ እና ወደምፈልግ በትም ስፍራ እመራቸዋለሁ፣ እናም እጄን ምንም ኃይል [ሐ]አያግደውም።

፴፬ እናም አሁን፣ በዚህ ስፍራ ለምትገኘው ቤተክርስቲያን የተወሰኑ ሰዎች በመካከላቸው እንዲሾሙ ትእዛዝን እሰጣለሁ፣ በቤተክርስቲያኗም [ሀ]ድምጽ ይሾማሉ፤

፴፭ ድሆችን እና ችግረኞችን ይንከባከባሉ፣ እንዳይሰቃዩም [ሀ]በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ያገልግሏቸዋል፤ ወደ አዘዝኳቸውም ስፍራ እልካቸዋለሁ፤

፴፮ እናም የዚህች ቤተክርስቲያን ንብረት ጉዳይ ማስተዳደርም የእነርሱ ስራ ይሆናል።

፴፯ እናም ሊሸጥ የማይቻል የእርሻ ስፍራዎች ያሏቸው፣ መልካም እንደመሰላቸው ያከራዩት ወይም እንዲተዉ ያድርጉ።

፴፰ ሁሉም ነገሮች ተጠብቀው ያሉ መሆናቸውን አረጋግጡ፤ እናም ሰዎች ከላይ [ሀ]መንፈሳዊ ስጦታ ሲሰጣቸውና ወደፊትም ሲላኩ፣ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በቤተክርስቲያኗ እቅፍ ውስጥ ይሰበሰባሉ።

፴፱ እናም አብ ሊሰጣችሁ የፈቀደውን [ሀ]ሀብት ከፈለጋችሁ፣ ከሁሉም ሰዎች በላይ ባለጠጋም ትሆናላችሁ፣ የዘለአለም ሀብትም ይኖራችኋልና፤ እናም እሰጣቸው ዘንድ የምድር [ለ]ሀብት ሁሉ የእኔ ነው፤ ነገር ግን [ሐ]ከኩራት ተጠበቁ፣ አለበለዚያም እንደ ጥንቶቹ [መ]ኔፋውያን ትሆናላችሁ።

፵ እናም ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ እያንዳንዱ ሰው፣ ሽማግሌው፣ ካህኑ፣ መምህሩ፣

፳፯ ሀ ዮሐ. ፲፯፥፳፩–፳፫፤
፩ ቆሮ. ፩፥፲፤
ኤፌ. ፬፥፲፩–፲፬፤
፫ ኔፊ ፲፩፥፳፰–፴፤
ሙሴ ፯፥፲፰።
ቅ.መ.መ. አንድነት።

፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፴፫፤
፴፰፥፲፫።

፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፮፤ ፷፫፤
፹፯፥፩–፮፤ ፻፴፥፲፪።

፴ ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፯።

፴፩ ሀ ፪ ጴጥ. ፫፥፲፬።

፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፯፥፫።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪።
ሐ ሉቃ. ፳፬፥፵፱፤
ት. እና ቃ. ፴፱፥፲፭፤
፺፭፥፰፤ ፻፲፥፱–፲።

፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
ለ ኢሳ. ፶፬፥፲፯፤ ኤር. ፴፥፲፤
ት. እና ቃ. ፻፴፮፥፳፪።
ሐ ዳን. ፬፥፴፭።

፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።

፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።

፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ።

፴፱ ሀ ያዕቆ. ፪፥፲፯–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፲፩፥፯።
ለ ሐጌ. ፪፥፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩራት።
መ ሞሮኒ ፰፥፳፯።

እንዲሁም አባል ያዘዝኩትን፣ ባለው ሀይል ሁሉ እየተጓዘ [ሀ]በእጆቹ ስራዎች፣ እንዲዘጋጅ እና እንዲያከናውን ትእዛዛትን እሰጣችኋለሁ።

፵፩ እናም እያንዳንዱ ሰው ለባልጀራው በደግነት እና በትህትና ሆኖ፣ [ሀ]ስብከታችሁም [ለ]የማስጠንቀቂያ ድምጽ ይሁን።

፵፪ እናም ከኃጢአተኞችም መካከል [ሀ]ውጡ። ራሳችሁን አድኑ። የጌታን ዕቃ የምትሸከሙ ንፁህን ሁኑ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፴፱

ጥር ፭፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በፈየት ኒው ዮርክ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለጄምስ ኮቪል የተሰጠ ራዕይ። ለአርባ አመታት የሜተዲስት ቄስ የነበረው ጄምስ ኮቪል ጌታ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የሚሰጠውን ማንኛውንም ትእዛዝ ለማክበር ከጌታ ጋር ቃል ኪዳን ገባ።

፩–፬፣ ቅዱሳን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ኃይል አላቸው፤ ፭–፮፣ ወንጌልን መቀበል ክርስቶስን መቀበል ነው፤ ፯–፲፬፣ ጄምስ ኮቪል እንዲጠመቅ እና በጌታ የወይን ስፍራ እንዲሰራ ታዘዘ፤ ፲፭–፳፩፣ የጌታ አገልጋዮች ከዳግም ምጽአት በፊት ወንጌልን ይሰበኩ ፳፪–፳፬፣ ወንጌልን የሚቀበሉ ለጊዜአዊ እና ለዘለአለም ይሰባሰባሉ።

፩ [ሀ]ከዘለአለም እስከዘለአለም ህያው የሆንኩትን ታላቁ [ለ]እኔ ነኝን፣ እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስን ድምፅ አድምጥ እናም ስማ—

፪ በጨለማ የሚያበራውን እና በጨለማም ያሉት የማይረዱበት፣ የአለም [ሀ]ብርሀን እና ህይወት የሆነውን፤

፫ [ሀ]በመካከለኛው ዘመን የእኔ ወደሆኑት መጣሁ እና የእኔም የሆኑትም አልተቀበሉኝም፤

፬ ነገር ግን ለተቀበሉኝ ሁሉ [ሀ]ልጆቼ ይሆኑ ዘንድ ኃይልን ሰጠኋቸው፤ እናም ለሚቀበሉኝም እንዲሁ፣ ልጆቼ እንዲሆኑ ኃይልን እሰጣቸዋለሁ።

፭ እናም እውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣ ወንጌሌን [ሀ]የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እናም ወንጌሌን የማይቀበል እኔን አይቀበልም።

፮ እናም ይህ የእኔ [ሀ]ወንጌል ነው—የንስሀና የውሀ ጥምቀት፣ እናም በመቀጠል ሁሉን ነገሮችን የሚያሳየውንና የመንግስተ ስማይን ስላማዊ ነገሮችን [ለ]የሚያስተምረውና አጽናኝ የሆነው፣ [ሐ]የእሳት እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ይከተላል።

፯ እናም አሁን፣ እነሆ፣ አገልጋዬ [ሀ]ጄምስ እልሀለሁ፣ ስራዎችህን ተመልክቻለሁ እናም አውቅሀለሁ።

፰ እናም እውነት እልሀለሁ፣ በዚህ ወቅት ልብህ በፊቴ የቀና ነው፤ እናም፣ እነሆ፣ በራስህም ላይ ታላቅ በረከቶችን አድርጌአለሁ፤

፵ ሀ ፩ ቆሮ. ፬፥፲፪።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ።
ለ ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣
ማስጠንቀቂያ።
፵፪ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲፩።
፴፱ ፩ ሀ ዕብ. ፲፫፥፰፤
ት. እና ቃ. ፳፥፲፪፤
፴፭፥፩፤ ፴፰፥፩–፬።
ለ ዘፀአ. ፫፥፲፬።
ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፳፮፤
ሙሴ ፮፥፶፯፣ ፰፪።
፬ ሀ ዮሐ. ፩፥፲፪።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
፭ ሀ ዮሐ. ፲፫፥፳።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ
መግባት፤
ወንጌል፤
ጥምቀት፣ መጥመቅ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፩።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤
ዳግመኛ መወለድን፣
ከእግዚአብሔር መወለድ።
፯ ሀ ት. እና ቃ. ፵፥፩።

፱ ሆኖም፣ በመታበይ እና [ሀ]በአለም ነገሮች ምክንያት ብዙ ጊዜ ስላልተቀበልከኝ፣ ታላቅ መከራን አይተሀል።

፲ ነገር ግን፣ እነሆ፣ ተነሳና [ሀ]ተጠመቅ፣ እናም ስሜንም እየጠራህ ኃጢአቶችህን እጠብ፣ መንፈሴንና የማታውቀውን ታላቅ በረከትን ትቀበላለህ የሚለውን ድምጼንም የምታደምጥ ከሆነ የመዳንህ ቀናት መጥተዋል።

፲፩ እናም ይህን የምታደርግ ከሆነ፣ ለታላቅ ስራ አዘጋጅቼሀለሁ። በዚህ የመጨረሻው ቀናት የላክሁትን የወንጌሌን ሙላት፣ እንዲሁም የእስራኤል ቤት የሆኑትን ህዝቤን [ሀ]እንዲመለሱ ለማድረግ የላክሁትን ቃል ኪዳን ትሰብካለህ።

፲፪ እናም እንዲህም ይሆናል ኃይልም በአንተ ላይ [ሀ]ይሆናል፤ ታላቅ እምነትም ይኖርሀል፣ እናም ከአንተም ጋር እሆናለሁ፣ ከፊትህም እሄዳለሁ።

፲፫ በወይን ስፍራዬም [ሀ]እንድትሰራ፣ እናም ቤተክርስቲያኔን ትገነባ፣ እና በከፍታዎችም ላይ እንድታብብና ሀሴትንም [ለ]ታደርግ ዘንድ ፅዮንን [ሐ]ለማምጣት ተጠርተሀል።

፲፬ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ ወደ ኦሀዮ እንድትሄድ እንጂ፣ ወደ ምስራቅ ሀገሮች እንድትሄድ አልተጠራህም።

፲፭ እናም በኦሀዮ ህዝቤ ራሳቸውን እስካሰባሰቡ ድረስ፣ በሰዎች ልጆች መካከል የማይታወቅን [ሀ]በረከትን አስቀምጫለሁ፣ እናም በራሶቻቸውም ላይ ይፈሳል። ከዚያም ወንዶቹ [ለ]በህዝብ [ሐ]ሁሉ መካከል ይሄዳሉ።

፲፮ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት፣ እልሀለሁ፣ እጄን በፍርድ በህዝብ ላይ ከማድረግ እንደምቆጠብ በማሰብ፣ በኦሀዮ የሚገኙ ህዝብ በታላቅ እምነት ወደ እኔ ይጣራሉ፣ ነገር ግን ቃሌን አልከድም።

፲፯ ስለዚህ፣ ለመጨረሻም ጊዜ [ሀ]ይገረዝ ዘንድ፣ በታላቅ ኃይልህ ስራህን ጀምር እናም ታማኝ ሰራተኞችን ወደ ወይን ስፍራዬ ጥራ።

፲፰ እናም ንስሀ እስከገቡና የወንጌሌን ሙላት እስከተቀበሉ እንዲሁም እስከተቀደሱ ድረስ፣ እጄን [ሀ]በፍርድ ከማድረግ እቆጠባለሁ።

፲፱ ስለዚህም፣ ከፍ ባለ ድምጽም፣ መንግስተ ሰማይ ቀርባለች በማለት፥ ሆሳዕና! የልዑል እግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን ብለህ በመጮህ ወደፊት ሂድ።

፳ [ሀ]ለምፅዓቴም ቀን ከፊት ለፊቴ መንገድን በማዘጋጀት፣ በውሀ በማጥመቅ ወደ ፊት ሂድ፤

፳፩ ጊዜው ተቃርቧል፤ [ሀ]ቀኑን እና ሰአቱን ማንም ሰው [ለ]አያውቅም፤ ነገር ግን በእርግጥም ይመጣል።

፳፪ እና እነዚህንም ነገሮች የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እናም ለጊዜውና ለዘለአለም ወደ እኔ ይሰበሰባሉ።

፳፫ እናም ዳግም፣ እንዲህም ይሆናል በውሀ ባጠመቅሀቸው ሁሉ ላይ፣ [ሀ]እጆችህን ትጭናለህ፣ እናም የመንፈስ ቅዱስን [ለ]ስጦታ ይቀበላሉ፣ እንዲሁም [ሐ]የምጽአቴን ቀን ምልክቶች [መ]ይጠባበቃሉ እናም እኔንም ያውቃሉ።

፳፬ እነሆ፣ በቶሎም እመጣለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፱ ሀ ማቴ. ፲፫፥፳፪።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፵።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፲፪ ሀ ፪ ቆሮ. ፲፪፥፱።
፲፫ ሀ ማቴ. ፳፥፩–፲፮።
ለ ት. እና ቃ. ፻፲፯፥፯።
ሐ ኢሳ. ፶፪፥፰።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፪፤ ፺፭፥፰፤ ፻፲፥፰–፲።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፥፪።
፲፯ ሀ ያዕቆ. ፭፥፷፩–፸፭፤ ት. እና ቃ. ፳፬፥፲፱።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፳፩ ሀ ማቴ. ፳፬፥፴፮።
ለ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፵።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ለ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
ሐ ፪ ጴጥ. ፫፥፲–፲፬።
መ ራዕ. ፫፥፫፤ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፭፤ ፵፭፥፴፱–፵፬።

ክፍል ፵

ጥር ፮፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በፈየት፣ ኒው ዮርክ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለሲድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። ይህ እራይ ከመመዝገቡ ቀደም ብሎ፣ የነቢዩ ታሪክ እንደሚገልጸው፣ "ጄምስ [ኮቪል] የጌታን ቃል ስላልተቀበለ እና ወደ ቀድሞው መሰረታዊ መርሆችና ሰዎች ስለተመለሰ፣ ጌታ ለእኔ እና ለስድኒ ሪግደን ተከታዩን ራዕይ ሰጠን" (ክፍል ፴፱ን ተመልከቱ)።

፩–፫፣ የስደት ፍራቻ እና ለአለም መጨነቅ ወንጌልን አለመቀበልን ያመጣል።

፩ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ቃሌን ለመታዘዝ ቃል ኪዳንን ስለገባ፣ የአገልጋዬ [ሀ]የጄምስ ኮቪል ልብ በፊቴ መልካም ነበር።

፪ እናም ቃሉን በደስታ [ሀ]ተቀበለ፣ ነገር ግን ወዲያውኑ ሰይጣን ፈተነው፤ እናም [ለ]የስደት ፍራቻና ለአለም መጨነቅ ቃሉን [ሐ]እንዳይቀበል አደረገው።

፫ ስለዚህም ቃል ኪዳኔን አፈረሰ፣ እናም መልካም የመሰለኝን በእርሱ ላይ አደርግ ዘንድ ፍቃዴ ነው። አሜን።

ክፍል ፵፩

የካቲት ፬፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ፣ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት ለቤተክርስቲያኗ የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ ነቢዩን እና የቤተክርስቲያኗን ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን "ህግጋት" ለመቀበል እንዲጸልዩ ያስተምራል (ክፍል ፵፪ን ተመልከቱ)። ጆሴፍ ስሚዝ ከከርትላንድ ወደ ኒው ዮርክ ገና መድረሱ ነበር፣ እናም በቶምሰን ኦሀዮ የሚኖረው የቤተክርስቲያኗ አባል ሊመን ኮፐሊ "ወንድሞች ጆሴፍ እና ስድኒ (ሪግደን). . .ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ እና እርሱም ቤቶች እና ድጋፎች እንደሚሰጣቸው ጠየቀ።" የሚቀጥለው ራዕይ ጆሴፍ እና ስድኒ የት መኖር እንደሚገባቸው ይገልጻል እና ደግሞም ኤድዋርድ ፓርትሪጅን እንደ ቤተክርስቲያኗ የመጀመሪያ ኤጲስ ቆጶስ ጥሪን ይሰጣል።

፩–፫፣ ሽማግሌዎቹ ቤተክርስቲያኗን በራዕይ መንፈስ ያስተዳድራሉ፤ ፬–፮፣ እውነተኛ ደቀ መዛሙርት የጌታን ህግ ይቀበላሉ እናም ይጠብቃሉ፤ ፯–፲፪፣ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ ለቤተክርስቲያኗ ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሟል።

፩ የምትሰሙኝ፣ ከበረከቶች ሁሉ ታላቅ በሆነው [ሀ]በረከት ልባርካችሁ ደስተኛ የሆንኩት እናንት ህዝቤ ሆይ፣ አድምጡ እናም ስሙ ይላል ጌታ እና አምላካችሁ፤ እናም የማያደምጡኝን እና በከንቱ ስሜን [ለ]የጠሩትን ከእርግማኖች ሁሉ ከባድ በሆነው እርግማን [ሐ]እረግማቸዋለሁ።

፪ እኔ የጠራኋችሁ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ አድምጡ፣ እነሆ በቃላቴ ላይ [ሀ]እንድትስማሙና ራሳችሁን እድታሰባስቡ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፵ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፴፱፥ ፯–፲፩።
፪ ሀ ማር. ፬፥ ፲፮–፲፱።
ለ ማቴ. ፲፫፥ ፳–፳፪።
ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ሐ ቅ.መ.መ. ክህደት።

፵፩ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
ለ ት. እና ቃ. ፶፮፥ ፩–፬፤ ፻፲፪፥ ፳፬–፳፮።
ሐ ዘዳግ. ፲፩፥ ፳፮–፳፰፤ ፩ ኔፊ ፪፥ ፳፫።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. አንድነት።

፫ እናም ቤተክርስቲያኔን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባችሁ እንድታውቁ እና ነገሮችን ሁሉ በፊቴ መልካም ታደርጉ ዘንድ በእምነታችሁ ጸሎት [ሀ]ህጌን ትቀበላላችሁ።

፬ እናም እኔ [ሀ]በምመጣበት ጊዜ የእናንተ [ለ]ገዢ እሆናለሁ፤ እናም እነሆ፣ በቶሎም እመጣለሁ፣ ህጌም እንዲጠበቅ አድርጉ።

፭ ህጌን [ሀ]ተቀብሎ [ለ]የሚያደርገው፣ እርሱ ደቀ መዛሙሬ ነው፤ እናም ተቀብየዋለሁ የሚል እና የማያደርገው፣ እርሱ ደቀ መዛሙሬ አይደለም፣ እናም ከመካከላችሁ ወጥቶ [ሐ]ይጣላል፤

፮ የመንግስተ ስማይ ልጆች የሆኑ ነገሮችን ወስዶ፣ ብቁ ላልሆኑ ወይም [ሀ]ለውሾች ሊሰጥ አይገባም፣ ወይም [ለ]ዕንቁዎችም በእሪያዎች ፊት እንዳይጣሉ ዘንድ አይገባምና።

፯ እናም ዳግም፣ ለአገልጋዬ ለጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ የሚኖርበትና [ሀ]የሚተረጉምበት [ለ]ቤት ሊገነባለት ይገባል።

፰ እናም ዳግም፣ ትእዛዛቴን እስከጠበቀ ድረስ አገልጋዬ ሲድኒ ሪግደን መልካም እንደመሰለው ይኖር ዘንድ ይገባል።

፱ ደግሞም፣ አገልጋዬን [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅን ጠርቼዋለሁ፤ በቤተክርስቲያኗ ድምጽ እንዲመረጥ እና ለቤተክርስቲያኗ [ለ]ኤጲስ ቆጶስነት እንዲሾም እናም ንግዱን ትቶ ሙሉ ጊዜውን ለቤተክርስቲያኗ አገልግሎት [ሐ]እንዲያውል ትእዛዝን እሰጣለሁ፤

፲ ህግጋቴን በምሰጥ ጊዜ የሚሰጡትን ነገሮች ሁሉ በዚያው መሰረት እንዲያከናውንም ትእዛዝን እሰጣለሁ።

፲፩ እናም ይህም የሆነበት ምክንያት ልቡ በፊቴ ንጹህ ስለሆነ ነው፣ እሱ ለእኔ [ሀ]ተንኮል እንደሌለው እንደ ጥንቱ [ለ]ናትናኤል ነውና።

፲፪ እነዚህ ቃላት ለእናንተ ተሰጥተዋችኋል፣ እናም በፊቴም ንጹህ ናቸው፤ ስለዚህም፣ በፍርድ ቀን በነፍስህ ስለሚመለሱ፣ እንዴት እንደምትይዛቸውም ተጠንቀቅም። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፵፪

የካቲት ፱፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ፣ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት በሁለት ክፍል የተሰጠ ራዕይ። ቁጥር ፩ እስከ ፸፪ የያዘው የመጀመሪያው ክፍልም የተሰጠው በአስራ ሁለት ሽማግሌዎች ፊት እና "ህጉ" በኦሀዮ እንደሚሰጥ ጌታ የገባው የተስፋ ቃል እንዲፈጸም ነበር (ክፍል ፴፰፥፴፪ን ተመልከቱ)። ሁለተኛው ክፍልም ከቁጥር ፸፫ እስከ ፺፫ የሚያጠቃልል ነበር። ነቢዩ ይህ ራዕይ "የቤተክርስቲያኗን ህግ እንደሚያቅፍ" አመለከተ።

፩–፲፣ ሽማግሌዎች ወንጌልን ለመስበክ፣ የሚለወጡትን ለማጥመቅ፣ እና ቤተክርስቲያኗን ለመገንባት ተጠርተዋል፤ ፲፩–፲፪፣ ሊጠሩ እና ሊሾሙ እንዲሁም በቅዱሳን መጻህፍት ውስጥ የሚገኙትን መሰረታዊ መርሆች ያስተምሩ ዘንድ ይገባል፤ ፲፫–፲፯፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይተንብዩ እናም ያስተምሩ፤ ፲፰–፳፱፣ ቅዱ

፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ዘካ. ፲፬፥፱፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፱። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት።
፭ ሀ ማቴ. ፯፥፳፬።
ለ ያዕ. ፩፥፳፪–፳፭፤ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፥፰–፱። ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፮ ሀ ማቴ. ፲፭፥፳፮።
ለ ማቴ. ፯፥፮።
፯ ሀ ይህም መፅሐፍ ቅዱስን ተርጉም ማለት ነው። ት. እና ቃ. ፵፭፥፷–፷፩።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፸፩።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፴፮፥፩።
ለ ት. እና ቃ. ፸፪፥፱–፲፪፤ ፻፯፥፷፰–፸፭። ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፩።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ተንኮል።
ለ ዮሐ. ፩፥፵፯።

ታውቃላችሁ፤ ኃጢአትን የሚሰራና ንስሀ የማይገባ እርሱ ወደ ውጭ [ሀ]ይጣላል።

፳፱ [ሀ]ብትወዱኝ [ለ]ታገለግሉኛላችሁ እናም [ሐ]ትዛዛቴን ሁሉ ትጠብቃላችሁ።

፴ እናም እነሆ፣ [ሀ]ድሆችን ታስታውሳላችሁ፣ እናም ለእነርሱ [ለ]እርዳታ የምታካፍሏቸውን ንብረታችሁን ሊሰበር በማይችል ቃል ኪዳን እና ተግባር [ሐ]ትቀድሳላችሁ።

፴፩ ነገሮቻችሁንም [ሀ]ለድሆች [ለ]እስካካፈላችሁ ድረስ፣ ለእኔ ታደርጉታላችሁ፤ እና እነዚህም በቤተክርስቲያኔ [ሐ]ኤጲስ ቆጶስ እናም ለዚህ አላማ በሚሾማቸው ወይም በሾማቸው እና ለአገልግሎት [መ]በለያቸው በሁለቱ ሽማግሌዎች ወይም ሊቀ ካህናት አማካሪዎቹ ፊት ይቅረቡ።

፴፪ እናም እንዲህም ይሆናል፣ እነዚህም በቤተክርስቲያኔ ኤጲስ ቆጶስ ፊት ከቀረቡ በኋላ፣ እናም ስለቤተክርስቲያኔ ንብረቶች [ሀ]መቀደስ፣ ከትእዛዛቴ ጋር በመስማማት ከቤተክርስቲያኗ ለመወሰድ እንደማይቻሉም ምስክሮችን ከተቀበለ በኋላ፣ ሁሉም ሰው ለእኔ [ለ]ተጠያቂ ይሆናል፣ በንብረቱ ወይም በቅድስና ለእርሱና [ሐ]ለቤተሰቡ በበቂ ሁኔታ በተሰጠውም ላይ [መ]ጠባቂ ይሆናል።

፴፫ እናም ዳግም፣ ይህ ከመጀመሪያው በቅድስና ከተሰጠ በኋላ በቤተክርስቲያኗ እጆች ውስጥ ወይም በማንም ግለሰብ እጅ ውስጥ ለእርዳታቸው ከሚያስፈልጋቸው በላይ የሆነ ለኤጲስ ቆጶስ የሚቀደስ [ሀ]የቀረ ንብረት ካለ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለሌላቸው እንዲሰጥ፣ ለሚያስፈልገው እያንዳንዱ ሰው በበቂ ሁኔታ እንዲሰጠው እና እንደሚያስፈልገውም መጠን ይቀበል ዘንድ ይቀመጣል።

፴፬ ስለዚህ፣ በቤተክርስቲያኗ ከፍተኛ አማካሪዎች ጉባኤ እና በኤጲስ ቆጶስ እና በአማካሪዎቹ አመራር፣ የቀረው ለድሆች እና በችግር ላይ ላሉት ይሆን ዘንድ በጎተራዬ ይጠበቃል፤

፴፭ እናም ለቤተክርስቲያኗ የህዝብ ጥቅም፣ እናም የአምልኮ ቤት ለመገንባት፣ እናም ከዚህ በኋላ የምትገለጠውን [ሀ]አዲሲቷ ኢየሩሳሌምን ለመገንባት—

፴፮ ወደ [ሀ]ቤተ መቅደሴ [ለ]በምመጣበት በዚያን ቀን የቃል ኪዳን ህዝቤ በአንድ ላይ እንዲሰበሰቡ በግምጃ ቤቴ ይቀመጣል። እናም ይህን የማደርገው ለህዝቤ መዳን ነው።

፴፯ እናም እንዲህም ይሆናል፣ ኃጢአትን የሚያደርግ እና ንስሀ የማይገባ እርሱ ከቤተክርስቲያኗ ውጭ [ሀ]ይጣላል፣ እናም [ለ]በቅድስና ለቤተክርስቲያኔ ድሆች እና ችግረኞች የሰጠውን፣ ወይም በሌላ አባባል ለእኔ የሰጠውን፣ ዳግሞ አይቀበልም—

፴፰ ከሁሉ ለሚያንሱ ለእነዚህ [ሀ]ካደረጋችሁት፣ ለእኔ አድርጋችኋል።

፴፱ እንዲህም ይሆናል፣ በነቢያቴ አንደበት የተናገርኩት ይፈጸማል፤ የእስራኤል ቤት ለሆኑት ድሀ ህዝቤ ይሆን ዘንድ ከአህዛብ መካከል ወንጌሌን የሚቀበሉትን ሀብታቸውን እቀድሰዋለሁና።

፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፳፱ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፲፭፣ ፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
ሐ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፴ ሀ ሞዛያ ፬፥፲፮–፳፮፤ አልማ ፩፥፳፯።
ቅ.መ.መ. ደሀ።
ለ ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።
ሐ ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ።
ለ ሞዛያ ፪፥፲፯።
ቅ.መ.መ. ምፅዋት፣ የምፅዋት ስጦታ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
መ ቅ.መ.መ. መለየት።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፩፥፬።
ለ ት. እና ቃ. ፸፪፥፫–፲፩።
ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፩፥፫።
መ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፶፭፤ ፶፩፥፲፫፤ ፻፲፱፥፩–፫።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፤ ፅዮን።
፴፮ ሀ ሚል. ፫፥፩።
ለ ት. እና ቃ. ፴፮፥፰።
፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፵፩፥፭፤ ፶፥፰–፱።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።
ለ ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
፴፰ ሀ ማቴ. ፳፭፥፴፬–፵።
ቅ.መ.መ. ልግስና፤ በጎ ድርገት።

፵ እና ደግሞም፣ በልብህም [ሀ]አይታበይ [ለ]ልብሶችሁም በጣም ያላጌጡ ይሁኑ፣ እናም ውበታቸውም የእጆችህ ስራ ውበት ይሁን፤

፵፩ እናም ሁሉም ነገሮች በፊቴ በንጽህና ይሰሩ።

፵፪ [ሀ]ስራ ፈትም አትሁን፤ ስራ ፈት የሆነ እርሱ የሰራተኞችን እንጀራ አይበላም እንዲሁም ልብስንም አይለብስምና።

፵፫ እናም በመካከላችሁ [ሀ]የታመመ ሰው ቢኖር፣ እናም ለመፈወስ እምነት ባይኖረው፣ ነገር ግን ካመነ፣ በጠላት እጅ ሳይሆን በመልካም ርህራሄ፣ ቅጠላቅጠል እና ለስላሳ ምግብንም በመመገብ እንክብካቤ ይደረግለታል።

፵፬ እናም ሁለት ወይም ከዚያም በላይ የቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ይጠሩ፣ ለእነርሱም ይጸልዩ እናም እጆቻቸውን በስሜ በላያቸው ላይ [ሀ]ይጫኑ፣ ቢሞቱም ለእኔ [ለ]ይሞታሉ፣ ከኖሩም ለእኔ ይኖራሉና።

፵፭ በሞት ላጣችኋቸው፣ በተለይም የክብር ትንሳዔ [ሀ]ተስፋ ለሌላቸው፣ [ለ]ባለቀሳችሁ መጠን፣ በአንድ ላይ [ሐ]በፍቅር [መ]ትኖራላችሁ።

፵፮ እናም እንዲህም ይሆናል በእኔ የሚሞቱ [ሀ]ሞትን አይቀምሱም፣ ለእነርሱም [ለ]ጣፋጭ ትሆናለችና፤

፵፯ እና በእኔ የማይሞቱም፣ ወዮላቸው፣ ሞታቸውም መራራ ትሆናለችና።

፵፰ እናም ዳግም እንዲህም ይሆናል ለመፈወስ በእኔ [ሀ]እምነት ያለው፣ እና ለሞትም [ለ]ያልተሰጠ፣ እርሱ [ሐ]ይፈወሳል።

፵፱ ለማየት እምነት ያለው ያያል።

፶ ለመስማትም እምነት ያለው ይሰማል።

፶፩ ለመዘለል እምነት ያለው ሽባም ይዘላል።

፶፪ እናም እነዚህንም ነገሮች ለማድረግ እምነት የሌላቸው፣ ነገር ግን በእኔ የሚያምኑ፣ [ሀ]ልጆቼ ይሆኑ ዘንድ ኃይል አላቸው፤ እናም ህግጋቴን አስካላፈረሱ ድረስ ድካማቸውን [ለ]ትሸከማላችሁ።

፶፫ [ሀ]በመጋቢነት ስፍራችሁ ትቆማላችሁ።

፶፬ የወንድማችሁንም ልብስ አትውሰዱ፤ ከወንድማችሁ የተቀበላችሁትንም ክፈሉ።

፶፭ እናም ከምትጠቀሙበት በላይ [ሀ]ቢኖራችሁ፣ ሁሉም ነገሮች እንደተናገርኩት ይከናወኑ ዘንድ፣ [ለ]በኀተራዬ ስጡ፣

፶፮ ጠይቁ፣ እናም እንደመረጥኩትም [ሀ]ቅዱሳን መጽሐፍቴ ይሰጣሉ፣ እናም በመልካም ሁኔታ [ለ]ይጠበቃሉ፤

፶፯ እናም እነዚህን በተመለከተ ዝምታችሁ፣ እናም ሙሉ ሁሉ እስከምትቀበሏቸውም ድረስ ያለማስተማራችሁ ተገቢ ነው።

፶፰ ከዚያም ሁሉንም ሰዎች እነዚህን ታስተምሩ ዘንድ ለእናንተ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ፤ [ሀ]ሁሉም ህዝብ፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ እና ወገን እንዲማሯቸው ይደረጋልና።

፶፱ በቅዱሳትት መጻህፍቴ ህግ ሆነው የተሰጷችሁን ነገሮች ቤተክርስቲያኔን የሚያ

፵ ሀ ምሳ. ፲፮፥ ፲፰።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
ለ ቅ.መ.መ. መጠነኛነት።
፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥ ፴–፴፪።
ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣
ስራ ፈቺ።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሕመም፣
ታማሚነት።
፵፬ ሀ ቅ.መ.መ. ለታመሙት
አገልግሎት መስጠት፤
እጅን መጫን።
ለ ሮሜ ፲፬፥ ፰፤
ራዕ. ፲፬፥ ፲፫፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥ ፵፱።
፵፭ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥ ፲፱–፳፪።
ቅ.መ.መ. ተስፋ።
ለ አልማ ፳፰፥ ፲፩–፲፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
መ ፩ ዮሐ. ፬፥ ፲፮፣ ፳–፳፩።
፵፮ ሀ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
ለ ራዕ. ፲፬፥ ፲፫።
፵፰ ሀ ት. እና ቃ. ፵፮፥ ፲፱።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ መክ. ፫፥ ፩–፪፤
የሐዋ. ፲፯፥ ፳፮፤
ዕብ. ፱፥ ፳፯፤
ት. እና ቃ. ፻፳፪፥ ፱።
ሐ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣
ፈውሶች።
፶፪ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ወንድ እና ሴት ልጆች።
ለ ሮሜ ፲፭፥ ፩።
ቅ.መ.መ. ጓደኝነት።
፶፫ ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣
መጋቢነት።
፶፭ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥ ፲፯–
፲፱፤ ፻፲፱፥ ፩–፫።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፴፬፤
፶፩፥ ፲፫።
፶፮ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥ ፷–፷፩።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት
መጻህፍት—የቅዱሣት
መጻህፍት ዋጋዎች።
፶፰ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥ ፪።

ስተዳድሩ ህግ ይሆንላችሁ ዘንድ ትቀበሏቸዋላችሁ።

፷ እናም በእነዚህ ነገሮች መሰረት [ሀ]የሚያከናውን እርሱ ይድናል፣ የማያደርጋቸውና በእዚህም የሚቀጥል ከሆነም [ለ]ይጠፋል።

፷፩ ብትጠየቁ፣ [ሀ]ደስታንና የሚያመጡትን፣ ዘለአለማዊ ህይወትን የሚያመጡትን—[ለ]ሰላማዊ የሆኑ ነገሮችንና [ሐ]ሚስጥራትንም ታውቁ ዘንድ [መ]በራዕይ ላይ ራዕይን፣ [ሠ]በእውቀት ላይ እውቀትን ትቀበላላችሁ።

፷፪ ጠይቁ፣ እናም በራሴ ጊዜ [ሀ]አዲስቷ ኢየሩሳሌም የምትገነባበትምን ስፍራ ይገለጥላችኋል።

፷፫ እናም እነሆ፣ እንዲህም ይሆናል አገልጋዮቼ ወደ ምስራቅ እና ወደ ምዕራብ፣ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ይላካሉ።

፷፬ እናም አሁንም ቢሆን፣ [ሀ]ወደምስራቅ የሚሄደው የሚለወጡትን ወደ ምዕራብ እንዲሸሹ ያስተምር፣ እናም ይህም የሚሆነው ወደ ምድር በሚመጣው የተነሳ፣ እናም [ለ]በሚስጥር ሴራዎች ምክንያት ነው።

፷፭ እነሆ፣ እነዚህን ሁሉ ትጠብቃላችሁ፣ እናም ደመወዛችሁም ታላቅ ይሆናል፤ የመንግስቱን ሚስጥራት ታውቁ ዘንድ ለእናንተ ተስጥቷችኋል፣ ነገር ግን አለም እንዲያውቃቸው አልተሰጠም።

፷፮ የተቀበላችሁትን ህግጋት ትጠብቃላችሁ እናም ታማኞችም ትሆናላችሁ።

፷፯ እናም በዚህና በአዲስቷ ኢየሩሳሌም ራሳችሁን ታደራጁ ዘንድ በቂ የሆነ የቤተ ክርስቲያን [ሀ]ቃል ኪዳንን ከዚህ በኋላ ትቀበላላችሁ።

፷፰ ስለዚህ፣ [ሀ]ጥበብ የሚጎድለው፣ እኔን ይጠይቅ ሳልነቅፍ በነጻ እሰጠዋለሁ።

፷፱ ልባችሁን አንስታችሁ ተደሰቱ፣ [ሀ]መንግስት፣ ወይም በሌላ አባባል፣ የቤተ ክርስቲያኗ [ለ]ቁልፎች ለእናንተ ተሰጥተዋልና። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፸ እንደ አባላትም፣ [ሀ]ካህናት እና [ለ]መምህራን [ሐ]መጋቢነታቸውን ያገኛሉ።

፸፩ ኤጲስ ቆጶሱን በአማካሪነት በሁሉም ነገሮች እንዲረዱት የተሾሙት ሽማግሌዎች ወይም ሊቀ ካህናት፣ አስቀድሞ እንደተገለጸው ለድሆች ደህንነት፣ እና በሌላ ጉዳዮች፣ [ሀ]በቅድስና ለኤጲስ ቆጶሱ በተሰጡት ንብረቶች ቤተሰቦቻቸውን ይርዱ።

፸፪ ወይም ለመጋቢነት ወይም በሌላ ጉዳይ አገልግሎታቸው ሁሉ መልካም ይሆናል ተብሎ በታሰበው መንገድ ወይም በአማካሪዎቹና በኤጲስ ቆጶሱ ውሳኔ መሰረት ተገቢውን ክፍያ ያግኙ።

፸፫ ኤጲስ ቆጶሱም፣ እንዲሁ፣ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ለሚሰጠው አገልግሎት እርዳታውን ወይም ትክክለኛ ክፍያን ያግኝ።

፸፬ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ማንኛቸውም ሰዎች ከመካከላችሁ [ሀ]በአመንዝራነት ምክንያት ከባለቤታቸውን በፍቺ ቢለዩ፣ ወይም በሌላ አባባል፣ በፊታችሁ በዚህም ምክንያት በተዋረደ ልብ ቢመሰክሩ፣ ከመካከላችሁ አውጥታችሁ አትጣሏቸው፤

፸፭ ነገር ግን ባለቤታቸውን [ሀ]በአመንዝራ

፷ ሀ ት. እና ቃ. ፵፩፥፭። ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ሙሴ ፭፥፲፭። ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፷፩ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳፫። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
መ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ሠ አብር. ፩፥፪። ቅ.መ.መ. ምስክርነት፤ እውቀት።
፷፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፫።
፷፬ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፬።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
፷፯ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፩–፲፭።
፷፰ ሀ ያዕ. ፩፥፭። ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፷፱ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ማቴ. ፲፮፥፲፱፤ ት. እና ቃ. ፷፭፥፪። ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፸ ሀ ቅ.መ.መ. ካህን፣ የአሮናዊ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. መምህር፣ የአሮናዊ ክህነት።
ሐ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
፸፩ ሀ ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
፸፬ ሀ ቅ.መ.መ. በወሲብ የስነ ምግባር ጉድለት፤ ዝሙት መፈጸም።
፸፭ ሀ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።

ነት ምክንያት እንደተዉ፣ እናም እራሳቸው ስህተቱን የፈጸሙ እንደሆኑ፣ እናም ባለቤታቸው በህይወት መኖራቸውን ካወቃችሁ፣ ከመካከላችሁ [ለ]ይጣላሉ።

፸፯ ደግሞም፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ የተጋቡ ከሆኑ እንደዚህ አይነቶቹን ምንም እንዳትቀበሏቸው በብርቱ ጥያቄ [ሀ]የነቃችሁ እና የተጠነቀቃችሁ ሁኑ፤

፸፰ እና ካላገቡም፣ ለሁሉም ኃጢአታቸው ንስሀ ይግቡ አለበለዚያም አትቀበሏቸውም።

፸፱ እናም ዳግም፣ የዚህች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል የሆነ ሁሉም ሰው የቤተክርስቲያኗን ትእዛዛት እና ቃል ኪዳን ይጠብቅ።

፹ እናም እንዲህም ይሆናል፣ ከመካከላችሁ ማንም ሰው የሰውን [ሀ]ነፍስ ቢያጠፉ አሳልፋችሁ ስጧቸው እናም በምድሪቷ ህግ መሰረት ይቀጡ፤ ምክንያቱም እርሱ ይቅርታ እንደሌለው አስታውሱ፤ እና ይህም በምድሪቷ ህግጋት መሰረት ይረጋገጥ።

፹፩ እናም ማንም ወንድ ወይም ሴት ቢያመነዝር፣ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ፊት ይዳኙ ዘንድ ትቀርባለች ወይም ይቀርባል፣ እናም በጠላቶቹ ወይም ጠላቶቿ ሳይሆን፣ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የቤተክርስቲያን ምስክሮች ፊት እያንዳንዱ በእርሱ ወይም በእርሷ ላይ የሚሰጠው ቃል ይጸናል፣ ነገር ግን ከሁለት በላይ ምስክሮች መኖራቸው ይመረጣል።

፹፪ ነገር ግን በሁለት ምስክሮች አንደበት ይኮነናል ወይም ትኮነናለች፤ እናም ሽማግሌዎች ጉዳዩን በቤተርስቲያኗ ፊት ያቀርባሉ፣ እናም በእግዚአብሔር ህግ ይዳኙ ዘንድ ቤተክርስቲያኗም እጆቿን በእርሱ ወይም በእርሷ ላይ ታነሳለች።

፹፫ እናም፣ ቢቻል፣ ኤጲስ ቆጶሱ መገኘቱም አስፈላጊ ነው።

፹፬ እናም በፊታችሁ ለሚመጡ ጉዳዮች ሁሉ እንዲሁ ታደርጋላችሁ።

፹፭ እናም ወንድ ወይም ሴት ቢዘርፍ ወይም ብትዘርፍ፣ ለምድሪቷ ህግ ይሰጣል ወይም ትሰጣለች።

፹፮ እናም ከሰረቀ ወይም [ሀ]ከሰረቀች፣ ለምድሪቷ ህግ ይሰጣል ወይም ትሰጣለች።

፹፯ እናም ቢዋሽ ወይም [ሀ]ብትዋሽ፣ ለምድሪቷ ህግ ይሰጣል ወይም ትሰጣለች።

፹፰ እናም ማንኛውንም አይነት ኃጢአት ቢያደርግ ወይም ብታደርግ፣ የእግዚአብሔር ህግ ለሆነው ይሰጣል ወይም ትሰጣለች።

፹፱ እናም [ሀ]ወንድሞቻችሁ ወይም እህቶቻችሁ [ለ]ቢበድሏችሁ፣ ከእርሷ ወይም ከእርሱ ጋር በግል ተገናኙ፤ [ሐ]ከተናዘዘ ወይም ከተናዘዘችም እርቅን ታደርጋላችሁ።

፺ እናም ካልተናዘዘ ወይም ካልተናዘዘች፣ ለአባሎቹ ሳይሆን ለሽማግሌዎቹ፣ ለቤተክርስቲያን አልፎ ይሰጣል ወይም ትሰጣለች። እና ይህም በአለም ፊት ሳይሆን፣ በስብሰባ ይደረጋል።

፺፩ እናም ወንድምህ ወይም እህትህ ብዙዎችን ቢበድል ወይም ብትበድል፣ በብዙዎች ፊት [ሀ]ይገሰጻል ወይም ትገሰጻለች።

፺፪ እናም በግልጽ ማንም ሰው በግልጽ ቢበድል፣ ያፍርበት ወይም ታፍርበት ዘንድ በግልጽ ይገሰጻል ወይም ትገሰጻለች። እናም ባናዘዝባት ወይም ባትናዘዝባት፣ ለእግዚአብሔር ህግ አልፎ ይሰጣል ወይም ትሰጣለች።

፺፫ ማንም ሰው በስውር ቢበድል፣ ለበደለው ወይም ለበደለችው፣ እናም ለእግዚአብሔር በስውር ለመናዘዝ እድል ይኖረው ወይም ይኖራት ዘንድ፣ ቤተክርስቲያኗ በማስጠንቀቅ እንዳትናገረው ወይም እንዳ

፸፮ለ ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፸፯ሀ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፹ሀ ቅ.መ.መ. ግድያ።
፹፮ሀ ቅ.መ.መ. መስረቅ።
፹፯ሀ ቅ.መ.መ. ሐሰት፤ ታማኝ፣ ታማኝነት።
፹፱ሀ ቅ.መ.መ. እህት፤ ወንድሞች፣ ወንድም።
ለ ማቴ. ፲፰፥፲፭–፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
፺፩ሀ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።

ትናገራት ዘንድ፣ በስውር ይገሰጻል ወይም ትገሰጻለች።

፺፫ እናም ሁሉንም ነገሮች በዚህ መልክ ታከናውናላችሁ።

ክፍል፤ ፵፫

በየካቲት ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ አንዳንድ የቤተክርስቲያኗ አባላት ሰዎች በሀሰት ባለራዕይ ነን በሚሉ ሰዎች ተረብሸው ነበር። ነቢዩ ጌታን ጠየቀና ለቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ይህን መልስ ተቀበለ። የመጀመሪያው ክፍል ስለቤተክርስቲያኗ አመራር ጉዳይን የሚመለከት ነበር፤ የኋለኛው ክፍል ሽማግሌዎች ለአለም ህዝብ የሚሰጡትን ማስጠንቀቂያዎች የያዘ ነበር።

፩–፯፣ ራዕይ እና ትእዛዛት የሚመጡት በተመደበው በአንዱ በኩል ብቻ ነው፤ ፰–፲፬፣ ቅዱሳኑ የሚቀደሱት በጌታ ፊት በቅድስና በመስራት ነው፤ ፲፭–፳፪፣ ሽማግሌዎች ለንስሀ እንዲጮሁና ሰዎችን ለዚያ ለጌታ ታላቅ ቀን እንዲያዘጋጁ ተልከዋል፤ ፳፫–፳፰፣ ጌታ ሰዎችን የሚጠራው በራሱ ድምፅ እና በፍጥረት ሀይል ነው፤ ፳፱–፴፭፣ አንድ ሺ ዘመን እና ሰይጣን የሚታሰርበት ይመጣል።

፩ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ አድምጡ፣ እናም የምናገራችሁንም ቃላት ስሙ።

፪ እነሆ፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከእጄ ትእዛዛትን እና ራዕዮችን ለመቀበል በመደብኩት በእርሱ በኩል [ሀ]ትእዛዛትን እንደ ቤተክርስቲያኔ [ለ]ህግ ተቀብላችኋልና።

፫ እናም ይህንንም በእርግጥ ታውቃላችሁ—እርሱ በእኔ [ሀ]የሚያምን ቢሆን፣ እርሱ እስከሚወሰድ ጊዜ ድረስ ማንም ትእዛዛትን እና ራእዮችን ለመቀበል የሚመደብ የለም።

፬ ነገር ግን፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በእርሱ በኩል ካልሆነ በስተቀር [ሀ]ማንም ለዚህ ስጦታ አይመደብም፤ ይህም ከእርሱ ከተወሰደ በእርሱን ምትክ ሌላ ከመመደብ በስተቀር ምንም ሀይል አይኖረውምና።

፭ እናም፣ በፊታችሁ የሚመጡትን የማንንም እንደ ራእዮች እና ትእዛዛት እንዳትቀበሉ፣ ይህም ለእናንተ ህግ ይሆናል፤

፮ እና ይህንንም የምሰጣችሁ [ሀ]እንዳትታለሉ፣ እነርሱም ከእኔ እንዳልሆኑ ታውቁ ዘንድ ነው።

፯ እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ [ሀ]የተሾመ እርሱ [ለ]በበሩ ይገባል እናም የተቀበላችሁትን እና በመደብኩት በኩል የምትቀበሏቸውን ራዕዮች ለማስተማር፣ አስቀድሜ እንደነገርኳችሁ ይሾማል።

፰ አሁንም፣ እነሆ፣ ስትሰበሰቡ እርስ በራሳችሁ [ሀ]ትማማሩ እና ትተናነጹ ዘንድ፣ እንዴት እንደምትሰሩ እና ቤተክርስቲያኔን እንደምትመሩ፣ በሰጠኋችሁ ህጋዊ ነጥቦችና ትእዛዛት እንዴት እንደምትሰሩ በጥልቅ ታውቁ ዘንድ እሰጣችኋለሁ።

፱ በዚህም በቤተክርስቲያኔ ህግ መመሪያ ይሰጣችኋል፣ እናም በተቀበላችሁ

፵፫ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ፤
የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪።
፫ ሀ ዮሐ. ፲፭፥፬።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፰፥፪–፫።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፵፮፥፯።
ቅ.መ.መ. ሸንገላ (ውሸት)፤
መዋሸት፤ ማታለል።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፤ ሹመት።
ለ ማቴ. ፯፥፲፫–፲፬፤
፪ ኔፊ ፱፥፵፩፤
፴፩፥፱፤ ፲፯–፲፰፤
፫ ኔፊ ፲፬፥፲፫–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፳፪።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፯።

ትም [ሀ]ትቀደሳላችሁ፣ እናም በፊት ለፊቴም በቅድስና ለመሄድ ራሳችሁን ታስተሳስራላችሁ—

፲ ይህንም እስካደረጋችሁም ድረስ፣ ለተቀበላችሁት መንግስት ክብር [ሀ]ይጨመርላችኋል። ይህን ባታደርጉ ግን፣ የተቀበላችሁትም እንኳ [ለ]ይወሰድባችኋል።

፲፩ በመካከላችሁ ያለውን [ሀ]ክፋት አፅዱ፤ በፊቴም ራሳችሁን ቀድሱ፤

፲፪ የመንግስትን ክብሮች የምትሹ ከሆነ፣ አገልጋዬን ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን መድቡ፣ እናም በጸሎት እምነት በፊቴ [ሀ]ደግፉት።

፲፫ እና ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ የመንግስትን [ሀ]ሚስጥራት የምትሹ ከሆነ፣ ምግብና ልብሶች፣ እናም ያዘዝኩትን ስራዎች ያከናውነው ዘንድ የሚያስፈልጉትን ማናቸውንም ነገሮች ስጡት፤

፲፬ እናም ይህን ባታደርጉ፣ በፊቴ [ሀ]ንጹህ ህዝብን ለራሴ አስቀር ዘንድ፣ እርሱን ከሚቀበሉት ጋር ይቆያል።

፲፭ ደግሞም እላለሁ፣ የመደብኳችሁ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ አድምጡ፥ የተላካችሁት ልትማሩ አይደለም፣ ነገር ግን [ሀ]በመንፈሴ ሀይል በእጆቻችሁ የሰጠኋችሁን ነገሮች ለሰው ልጆች [ለ]ታስተምሩ ዘንድ ነው፤

፲፮ እናም ከላይ [ሀ]ትማሩ ዘንድ ይገባል። ራሳችሁን [ለ]ቀድሱ እና እንደተናገርኩት እንድትሰጡ ዘንድ፣ የሀይል [ሐ]መንፈሳዊ ስጦታም ይሰጣችኋል።

፲፯ አድምጡ፣ እነሆ፣ የጌታ [ሀ]ታላቅ [ለ]ቀን ቀርቧልና።

፲፰ ጌታ ከሰማይ [ሀ]ድምጹን የሚሰጥበት ቀን ይመጣልና፤ ሰማያት [ለ]ይንቀጠቀጣሉ እና ምድርም [ሐ]ትናወጣለች፣ እና ረጅም እና ጉልህ የሆነው የእግዚአብሔር [መ]መለከት ለሚያንቀላፉት ህዝብ እንዲህ ይላል፥ ቅዱሳን ሆይ [ሠ]ተነሱና ኑሩ፤ ኃጢአተኞች ሆይ ዳግም እስከምጣራ ድረስ [ረ]ባላችሁበት ሁኑ እናም [ሰ]ተኙ።

፲፱ ስለዚህ ራሳችሁን ከክፉዎች መካከል እንዳትገኙ ወገባችሁን ታጠቁ።

፳ ድምጻችሁንም ከፍ አድርጉ እናም አትቆጥቡ። ለወጣቶችም ሆነ ለአዛውንቱ፣ ለታሰሩትም ሆነ ነፃ ለሆኑት፣ እንዲህ በማለት ህዝብን ለንስሀ መግባት ጥሯቸው፥ ራሳችሁን ለጌታ ታላቅ ቀን አዘጋጁ።

፳፩ እኔ፣ ሰው የሆንኩት፣ ድምጼን ከፍ ባደርግ እና ለንስሀ ብጠራችሁ እና ብትጠሉኝ፣ ንስሀ ግቡ፣ እና ለጌታ ታላቅ ቀን ተዘጋጁ፣ በማለት ህያው ለሆኑት ጆሮዎች ሁሉ [ሀ]ነጎድጓዶችም ከምድር ዳርቻ በታላቅ በድምፅ የሚናገሩበት ቀን ሲመጣ፣ ምንስ ትላላችሁ?

፳፪ አዎን፣ ደግሞም፣ እነዚህም ቃላት—ንስሀ ግቡ፣ የጌታ ታላቅ ቀን መጥቷልና በማለት መብረቆች ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ሲታዩ፣ እናም ህያው ለሆኑት ሁሉ በድምጽ ሲናገሩ፣ እና የሚሰሙትን ጆሮዎች ሁሉ ሲሰነጥቁ፣ ምንስ ትላላችሁ?

፳፫ ደግሞም፣ ጌታ ከሰማይ ቃሉን እንዲህ በማለት ይሰጣል፥ የምድር ህዝብ ሆይ፣ አድምጡ እና የሰራችሁን የእግዚአብሔርን ቃላት ስሙ።

፱ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፲ ሀ አልማ ፲፪፥፲።
ለ ማር. ፬፥፳፭።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ—በመንፈስ ማስተማር።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ሉቃ. ፳፬፥፵፱፤ ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፪፤ ፺፭፥፰–፱፤ ፻፲፥፰–፲።
፲፯ ሀ ሚል. ፬፥፭፤ ት. እና ቃ. ፪፥፩፤ ፴፬፥፮–፱።
ለ ት. እና ቃ. ፳፱፥፰። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፲፰ ሀ ኢዩ. ፪፥፲፩፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፶።
ለ ኢዩ. ፪፥፲፤ ፫፥፲፮፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፵፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፹፯።
መ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፫፤ ፵፭፥፵፭።
ሠ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ረ ት. እና ቃ. ፸፮፥፹፭፤ ፹፰፥፻–፻፩።
ሰ ሞር. ፱፥፲፫–፲፬።
፳፩ ሀ ፪ ኔፊ ፳፯፥፪፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺።

፳፬ የምድር ህዝብ ሆይ፣ [ሀ]ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ስንት ጊዜ በአንድነት ሰበሰብኳችሁ፣ እናንት ግን [ለ]አልወደዳችሁም!

፳፭ [ሀ]በአገልጋዮቼ አንደበት፣ እና በመላዕክት [ለ]አገልግሎት፣ እና በራሴም ድምፅ፣ እና በነጎድጓድ ድምጽ፣ እና በመብረቅ ድምጽ፣ እና በማዕበል ድምጽ፣ በምድር በመናወጥ ድምጽ፣ እና በበረዶ ናዳ ድምጽ፣ እና [ሐ]በረሀብ እናም በሁሉም ዓይነት ቸነፈር ድምጽ፣ እና በታላቅ የመለከት ድምፅ፣ እና በፍርድ ድምጽ፣ እና ቀኑን ሙሉ [መ]ምህረት ድምፅ፣ እና በዘለአለማዊ ህይወት ክብር እና ባለጠግነት ድምጽ ስንት ጊዜ [ሠ]ጠራኋችሁ፣ እናም [ረ]በዘለአለማዊ ደህንነት አድናችሁም ዘንድ ወደድሁ፣ እናንት ግን አልተቀበላችሁኝም!

፳፮ እነሆ፣ የቁጣዬ ጽዋ የሚሞላበት ቀን መጥቷል።

፳፯ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ የጌታ አምላካችሁ ቃላት ናቸው።

፳፰ ስለዚህ፣ ስሩ፣ በወይን ስፍራዬ ለመጨረሻ ጊዜ [ሀ]ስሩ—ለመጨረሻም ጊዜ በምድር የሚኖሩትን ጥሩ።

፳፱ በጊዜዬ በምድር ላይ ለፍርድ [ሀ]እገለጣለሁና፣ እናም ህዝቤም ይድናሉ፣ እና ከእኔም ጋር በምድር ይነግሳሉ።

፴ በአገልጋዮቼ አንደበት የተናገርኩት ታላቁ [ሀ]አንድ ሺህ ዘመን ይመጣልና።

፴፩ [ሀ]ሰይጣን [ለ]ይታሰራልና፣ ደግሞም ሲፈታ [ሐ]ለጥቂት ጊዜ ብቻ ይነግሳል፣ ከዚያም [መ]የምድርም ፍጻሜ ይሆናል።

፴፪ እና [ሀ]በጽድቅ የሚኖረውም በቅጽበት [ለ]ይለወጣል፣ እና ምድርም በእሳት በሚመስል ሁኔታ ትጠፋለች።

፴፫ እና ክፉዎችም ወደ እቶኑ [ሀ]እሳት ይጣላሉ፣ እና በፊቴ [ለ]ለፍርድ እስከሚመጡም ድረስ፣ መጨረሻቸውን ማንም ሰው በምድር አያውቀውም፣ ወይም መቼም አያውቁትም።

፴፬ እነዚህን ቃላት አድምጡ። እነሆ፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የአለምሁሉ [ሀ]አዳኝ ነኝ። እነዚህን ነገሮች በልባችሁ [ለ]አኑሩዋቸው፣ እናም የዘለአለም [ሐ]ማስተዋልም [መ]በአዕምሮዎቻችሁ ላይ [ሠ]ይረፍ።

፴፭ [ሀ]የተረጋጋችሁ ሁኑ። ትእዛዛቴን ሁሉ ጠብቁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፵፬

በየካቲት መጨረሻ አካባቢ፣ በ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ውስጥ የቀረቡትን ትእዛዛት በማክበር፣ ቤተክርስቲያኗ በሚቀጥለው ሰኔ መጀመሪያ ላይ ጉባኤ እንዲኖር መደበች።

፳፬ ሀ ማቴ. ፳፫፥፴፯፤ ፫ ኔፊ ፲፥፬–፮።
ለ ቅ.መ.መ. አመጽ።
፳፭ ሀ ማቴ. ፳፫፥፴፬። ቅ.መ.መ. ነቢይ።
ለ ት. እና ቃ. ፯፥፮፤ ፻፴፥፬–፭።
ሐ ኤር. ፳፬፥፲፤ ዓሞ. ፬፥፮፤ ት. እና ቃ. ፹፯፥፮፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፳፱።
መ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሠ ሔለ. ፲፪፥፪–፬።
ረ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት፤ የዘለዓለም ህይወት፤ ደህንነት።
፳፰ ሀ ያዕቆ. ፭፥፸፩፤ ት. እና ቃ. ፴፫፥፫። ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፴፩ ሀ ፩ ኔፊ ፳፪፥፳፮። ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፭፤ ፹፬፥፻፤ ፹፰፥፻፲።
ሐ ራዕ. ፳፥፫፤ ያዕቆ. ፭፥፸፯፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥፳፪።
መ ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፶፩–፶፪፤ ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፩፤ ፻፩፥፴፩። ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፴፫ ሀ ማቴ. ፫፥፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. አዳኝ።
ለ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፬፥፹፭፤ ፻፥፯–፰።
መ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
ሠ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፴፭ ሀ ሮሜ ፲፪፥፫፤ ት. እና ቃ. ፲፰፥፳፩።

፩–፫፣ ሽማግሌዎች በጉባኤ ይሰብሰቡ፤ ፬–፮፣ በምድሪቷ ህግጋት መሰረት እናም ደሆችንም ይንከባከቡ ዘንድ ራሳቸውን ያደራጁ።

፩ እነሆ፣ ጌታ ለእናንተ ለአገልጋዮቼ እንዲህ ይላል፣ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ከምስራቅና ከምእራብ፣ ከሰሜንና ከደቡብ፣ በደብዳቤ ወይም በሌላ መንገድ፣ መሰብሰባቸው ፍቃዴ ነው።

፪ እናም እንዲህ ይሆናል ያልፉል፣ ታማኝ ቢሆኑ፣ እና በእኔም ያላቸውን እምነት ቢጠቀሙ፣ ራሳቸውን በሚሰበስቡበት ቀን [ሀ]መንፈሴን አፈስባቸዋለሁ።

፫ እናም እንዲህ ይሆናል በአካባቢው ክፍለ ሀገሮች ይሂዱ፣ እና ለህዝቡ ንስሀን መግባትን [ሀ]ይሰበኩ።

፬ እና፤ እንዲህም ሆኖ [ሀ]በሰው ህግጋት መሰረት ራሳችሁን ለማደራጀት ሀይልን እስካገኛችሁ ድረስ ብዙዎች [ለ]ይለወጣሉ፤

፭ [ሀ]ጠላቶቻችሁ በእናንተ ላይ ስልጣን እንዳይኖራቸው በሁሉም ነገሮች እንድ ትጠበቁ፣ ህግጋቴንም ለመጠበቅ እንድትችሉ፣ ጠላትም ህዝቤን ለማጥፋት የሚሻባቸው ስምምነቶች ይሰበሩ ዘንድ ራሳችሁን ለማደራጀት ሀይል ታገኛላችሁ።

፮ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ሁሉም ነገሮች በተቀበላችሁት ህጌ መሰረት እስከሚከናወኑ ድረስ ይጠበቁ ዘንድ፣ ደሆችንና ችግረኞችን [ሀ]ተንከባከቡ እና በሚያስፈልጋቸውም ነገሮች አገልግሏቸው። አሜን።

ክፍል ፵፭

በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በመጋቢት ፯፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለቤተክርስቲያኗ የተሰጠ ራዕይ። ስለ ራዕይ ጽሁፍ ማስረጃን ሲያስተዋውቅ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንዲህ ገልጿል፥ “በዚህ በቤተክርቲያኗ እድሜ፣ ሰዎች የጌታን ስራ እንዳይመረምሩና እምነቱንም እንዳያቅፉ ብዙ የሀሰት ዘገባዎችና ረብ የለሽ ታሪኮች ታትመውና ተሰራጭተው ነበር፤ ነገር ግን ለቅዱሳኑ ደስታ . . . ይህንን የሚከተለውን ተቀበልኩ”።

፩–፭፣ ክርስቶስ ከአብ ዘንድ አማላጃችን ነው፤ ፮–፲፣ ወንጌል የጌታን መንገድ በፊቱ የሚያዘጋጅ መልእክተኛ ነው፤ ፲፩–፲፭፣ ሔኖክንና ወንድሞቹን ጌታ ወደ እራሱ ተቀብሏቸዋል፤ ፲፮–፳፫፣ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ እንደተሰጠው ክርስቶስ የመምጫውን ምልክቶች ገለጠ፤ ፳፬–፴፰፣ ወንጌሉ ደግሞ ይመለሳል፣ የአህዛብ ጊዜያት ይፈጸማሉ፣ እና ምድርም በአስከፊ በሽታ ትሸፈናለች፤ ፴፱–፵፯፣ ተአምራት፣ ድንቃ ድንቅ፣ እና ትንሳኤ ዳግም ምፅአትን ያስከትላሉ፤ ፵፰–፶፫፣ ክርስቶስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ይቆማል፣ እና አይሁዶችም በእጆቹና እግሮቹ ላይ ያሉትን ቁስሎች ያያሉ፤ ፶፬–፶፱፣ ጌታም ለአንድ ሺ አመት ዘመንም ይነግሳል፤ ፷–፷፪፣ በጣም አስፈላጊ መረጃዎች እንዲታወቁ የሚደረግበትን አዲስ ኪዳንን ነቢዩ ለመተርጎም እንዲጀምር መመሪያ ተሰጥቶታል፤ ፷፫–፸፭፣ ቅዱሳን እንዲሰበሰቡ እና ከሁሉም አገሮች ተሰብስበው የሚመጡበትን አዲስቷን ኢየሩሳሌም እንዲገነቡ ታዝዘዋል።

፵፬ ፪ሀ የሐዋ. ፪፥ ፲፯።
፫ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፺፰፥ ፭–፯።
ለ ቅ.መ.መ. መቀየር፣ የተቀየረ።
፭ሀ ፪ ኔፊ ፬፥ ፴፫።
፮ሀ ያዕ. ፩፥ ፳፯።
ቅ.መ.መ. ርህራሄ፤ በጎ ድርገት።

፩ [ሀ]መንግስቱ የተሰጣችሁ፣ አቤቱ እናንት [ለ]የቤተክርስቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ አድምጡ፤ ምድርን የመሰረተውን፣ ሰማያትንና ሠራዊቱን ሁሉ [ሐ]የሰራውን፣ እና ህያው የሆኑትን፣ የሚንቀሳቀሱትን፣ እና የሚኖሩትን ሁሉ የፈጠረውን አድምጡ እና ስሙ።

፪ ደግሞም እንዲህ እላችኋለሁ፣ [ሀ]ሞት እንዳይመጣባችሁ ድምጼን አድምጡ፤ ባሰባችሁትም [ለ]ሰዓት በጋ ያልፋል፣ እና [ሐ]መኸሩ ይፈጸማል፣ እና መንፈሳችሁም አይድኑም።

፫ ከአብ ፊት [ሀ]አማላጅ የሆነውን፣ ፊቱም ስለእናንተ እንዲህ በማለት የሚማፀንላችሁን ስሙ—

፬ አባት ሆይ፣ [ሀ]ኃጢአት ያልሰራውን በእርሱም የተደሰትከውን [ለ]ስቃይና ሞት ተመልከት፤ የፈሰሰውን የልጅህን ደም ተመልከት፣ ስምህ [ሐ]ይከበር ዘንድ አንተ የሰጠኸውን የልጅህን ደም ተመልከት፤

፭ ስለዚህ፣ አባት ሆይ፣ በስሜ [ሀ]የሚያምኑትን ወደ እኔም መጥተው [ለ]ዘለአለማዊ ህይወት ይኖራቸው ዘንድ እነዚህ ወንድሞቼን አድናቸው።

፮ የቤተክርቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ አድምጡ፣ እና እናንት ሽማግሌዎችም አብራችሁ ስሙ፣ እና [ሀ]ዛሬ እየተባለ እስከሚጠራ ድረስ ድምጼን አዳምጡ፣ እና ልባችሁንም አታደንድኑ፤

፯ እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ [ሀ]አልፋና ዖሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፣ የአለም [ለ]ብርሀንና ህይወት—በጭለማም የማበራ ብርሀን ነኝ፣ በጨለማም ያሉት አይረዱትም።

፰ የእኔ ወደ ሆኑት መጣሁ እነርሱም አልተቀበሉኝም፤ ለተቀበሉኝ ሁሉ ግን፣ ለእነርሱ ብዙ [ሀ]ተዓምራት እንዲሰሩ፣ እናም የእግዚአብሔር [ለ]ልጆችም ይሆኑ ዘንድ [ሐ]ስልጣንን እሰጣቸዋለሁ፤ እና በስሜ [መ]ለሚያምኑትም [ሠ]ዘለአለማዊ ህይወት የሚያገኙበትንም ሀይል እሰጣቸዋለሁ።

፱ እና ይህም ቢሆንም በአለም ብርሀን እንዲሆን፣ እና ለህዝቤም [ሀ]መመሪያ እንዲሆን፣ እና [ለ]አህዛብም እንዲፈልጉት፣ እናም በፊቴም መንገድን የሚያዘጋጅልኝ [ሐ]መልእክተኛ እንዲሆን [መ]ዘለዓለማዊ [ሠ]ቃል ኪዳኔን ወደ አለም ልኬአለሁ።

፲ ስለዚህ፣ ወደ እርሱ ኑ፣ እናም ከመጡትም ጋር እንደ ቀደሙት ቀናት ከሰዎች ጋር እንዳደረግሁት አነጋግረዋለሁ፣ እና [ሀ]ጠንካራ ማስረጃዬንም እሳያችኋለሁ።

፲፩ ስለዚህ፣ በአንድነት አድምጡ እና ጥበቤን—[ሀ]የሔኖክና የወንድሞቹ አምላክ ነው ብላችሁ የምትሉትን የእርሱን ጥበብ ላሳያችሁ፣

፲፪ ከምድር [ሀ]ተለይተው የተወሰዱትን፣ እና በቅዱሳን ሰዎች ዘንድ ሁሉ ተፈልጋ የፅድቅ ቀን እስከሚመጣበት እስከ እዚያ ተጠብቃ ያለውን [ለ]ከተማ በክፋት እና በር

፵፭ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፶፥ ፴፭።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ሐ ኤር. ፲፬፥ ፳፪፤ ፫ ኔፊ ፱፥ ፲፭፤ ት. እና ቃ. ፲፬፥ ፱። ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
፪ሀ አልማ ፴፬፥ ፴፫–፴፮።
ለ ማቴ. ፳፬፥ ፵፬።
ሐ ኤር. ፰፥ ፳፤ ት. እና ቃ. ፶፮፥ ፲፮። ቅ.መ.መ. መከር።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፷፪፥ ፩። ቅ.መ.መ. አማላጅ።
፬ሀ ዕብ. ፬፥ ፲፭።
ለ ት. እና ቃ. ፲፱፥ ፲፰–፲፱። ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ሐ ዮሐ. ፲፪፥ ፳፰።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፳፥ ፳፭፤ ፴፭፥ ፪፤ ፴፰፥ ፬።
ለ ዮሐ. ፫፥ ፲፮።
፮ሀ ዕብ. ፫፥ ፲፫፤ ት. እና ቃ. ፷፬፥ ፳፫–፳፭።
፯ሀ ራዕ. ፩፥ ፰፤ ፳፩፥ ፮፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥ ፩።
ለ ዮሐ. ፩፥ ፭።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ተአምራት።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
ሐ ማቴ. ፲፥ ፩። ቅ.መ.መ. ሀይል።
መ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሠ ት. እና ቃ. ፲፬፥ ፯።
፱ሀ ፪ ኔፊ ፳፱፥ ፪።
ለ ኢሳ. ፵፪፥ ፮፤ ፪ ኔፊ ፲፥ ፱–፲፰።
ሐ ሚል. ፫፥ ፩።
መ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ሠ ኤር. ፴፩፥ ፴፩–፴፬፤ ሞር. ፭፥ ፳።
፲ሀ ኢሳ. ፵፩፥ ፳፩፤ ት. እና ቃ. ፶፥ ፲–፲፪።
፲፩ሀ ሙሴ ፯፥ ፷፱።
፲፪ሀ ጆ.ስ.ት. ዘፍጥ. ፲፬፥ ፴–፴፬ (ተጨማሪ)፤ ት. እና ቃ. ፴፰፥ ፬፤ ሙሴ ፯፥ ፳፩።
ለ ሙሴ ፯፥ ፷፪–፷፬። ቅ.መ.መ. ፅዮን።

ኩሰታቸው ምክንያት ለማግኘት ያልቻሉትን ቀን ነው፤

፲፫ እናም በምድሪቱም [ሀ]እንግዶችና መጻተኞች ነን ብለው የተናዘዙትን፤

፲፬ ነገር ግን ይህን እንደሚያገኙት እና በስጋም እንደሚያዩት [ሀ]ቃል ኪዳን ያገኙትን የሔኖክና የወንድሞቹን አምላክ የእነርሱን ጥበብ ላሳያችሁ።

፲፭ ስለዚህ፣ አድምጡ እናም ምክንያቴን እሰጣችኋለሁ፣ እና እንደ ቀደሙት ቀናት ሰዎችም አነጋግራችኋለሁ እናም እተነብያለሁም።

፲፮ ለደቀ መዛሙርቴ በስጋዬ በፊት ለፊታቸው ቆሜ [ሀ]እንዳሳየኋቸው ለእናንተም በግልፅ አሳያችኋለሁ፣ እና እንዲህም በማለት ነገርኳቸው፥ ለአባቶቻችሁ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ለሚሟላት፣ በክብር በሰማይ ደመና ስለምመጣበት [ለ]ቀን፣ ስለመመለሴ ምልክቶችን እንደጠየቃችሁኝ፣

፲፯ [ሀ]መንፈሳችሁ ከስጋችሁ [ለ]ስለመለያየቱን እንደ ምርኮ ስላያችሁት፣ የቤዛ ቀን እንዴት እንደሚመጣ እና ደግሞም [ሐ]የተበተኑትን እስራኤል [መ]መመለስንም አሳያችኋለሁ።

፲፰ አሁን የእግዚአብሔር ቤት ብላችሁ የምትጠሩትን በኢየሩሳሌም ውስጥ ያለውን ቤተመቅደስ ተመልከቱ፣ እና ጠላቶቻችሁም ይህ ቤት በምንም አይወድቅም ይላሉ።

፲፱ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ በማታ እንደሚመጣው ሌባ በዚህ ትውልድ ላይ ጥፋት ይደርሳል፣ እና ይህ ህዝብም ይጠፋሉ በሁሉም ሀገሮች መካከልም ይበተናሉ።

፳ እና ይህ አሁን የምታዩት ቤተመቅደስ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም።

፳፩ እና እንዲህም ይሆናል፣ ይሆናሉ ያልኳችሁ ጥፋቶች ከመከሰታቸው በፊት ይህ የአይሁድ ትውልድም አያልፍም።

፳፪ የአለም [ሀ]መጨረሻ እየመጣ እንደሆነ እናውቃለን ትላላችሁ፤ ምድርና ሰማይ እንደሚያልፉም እናውቃለን ትላላችሁ፤

፳፫ ስለዚህም እናንት በእውነት ትናገራላችሁ፣ ይህም ነውና፤ ነገር ግን እነዚህ የነገርኳችሁ ሁሉም ነገሮች እስከሚፈጸሙ ድረስ አያልፉም።

፳፬ እና ይህ የነገርኳችሁ ስለ ኢየሩሳሌም ነው፤ እናም ያ ቀን ሲመጣም፣ የቀሩትም በሁሉም አገሮች መካከል [ሀ]ይበተናሉ።

፳፭ ነገር ግን ደግሞም [ሀ]ይሰበሰባሉ፤ ነገር ግን [ለ]የአህዛብ ጊዜ እስከሚፈጸም ድረስ እንዲሁ ይቆያሉ።

፳፮ [ሀ]በዚያ ቀንም ስለ [ለ]ጦርነቶችና የጦር ወሬዎች ይሰማል፣ እና ምድር ሁሉም በሁከት ውስጥ ትሆናለች፣ እናም የሰዎች ልብ በፍርሀት [ሐ]ይደክማል፣ እና እስከ ምድር ጫፍም ድረስ ክርስቶስ መምጫውን [መ]አዘገየው ይላሉ።

፳፯ የሰዎች ፍቅርም ይቀዘቅዛል፣ እና ኃጢአትም ይበዛል።

፳፰ [ሀ]የአህዛብ ጊዜ ሲመጣም፣ በጨለማ ውስጥ ለተቀመጡትም [ለ]ብርሀን ይሆናል፣ እና ይህም ወንጌሉ ሙሉ ይሆናል፤

፳፱ ነገር ግን [ሀ]አይቀበሉትም፤ ብርሀኑን አይመለከቱትምና፣ እናም በሰዎች [ለ]አስተያየት ምክንያትም ልባቸውን ከእኔ [ሐ]ያዞራሉ።

፲፫ ሀ ዕብ. ፲፩፥፲፫፤ ፩ ጴጥ. ፪፥፲፩።
፲፬ ሀ ዕብ. ፲፩፥፰–፲፫፤ ሙሴ ፯፥፷፫።
፲፮ ሀ ማቴ. ፳፬፤ ሉቃ. ፳፩፥፯–፴፮፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥፶።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፥፲፪–፲፬። ቅ.መ.መ. እስራኤል— የተበተኑት እስራኤል።
መ ቅ.መ.መ. እስራኤል— የእስራኤል መሰብሰብ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. አለም— የአለም መጨረሻ።
፳፬ ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፥፲፭።
፳፭ ሀ ነሀ. ፩፥፱፤ ኢሳ. ፲፩፥፲፪–፲፬፤ ፩ ኔፊ ፳፪፥፲–፲፪፤ ፪ ኔፊ ፳፩፥፲፪–፲፬።
ለ ሉቃ. ፳፩፥፳፬።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ለ ት. እና ቃ. ፹፯፤ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፳፫።
ሐ ሉቃ. ፳፩፥፳፮።
መ ፪ ጴጥ. ፫፥፫–፲።
፳፰ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፥፲፫።
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፤ የወንጌል ዳግም መመለስ።
፳፱ ሀ ዮሐ. ፩፥፭።
ለ ት. እና ቃ. ፫፥፮–፰፤ ፵፮፥፯፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፲፱።
ሐ ማቴ. ፲፭፥፰–፱።

፴ በዚያ ትውልድም ውስጥም የአህዛብ ጊዜዎች ይፈጸማሉ።

፴፩ እናም ተከታታይ [ሀ]ቀሰፋዎችን ከማየታቸው በፊት የማያልፉ ሰዎች በዚያም ትውልድ ይኖራሉ፤ በሽታም ምድርም በአሰቃቂ በሽታ ትሸፈናለችና።

፴፪ ነገር ግን ደቀ መዛሙርቴ በተቀደሰ ስፍራዎች ላይ [ሀ]ይቆማሉ፣ እናም አይነቃነቁም፤ ነገር ግን ከክፉዎቹም መካከል፣ ሰዎች ድምጾቻቸውን አንስተው እግዚአብሔርን [ለ]ይረግማሉ እናም ይሞታሉ።

፴፫ የምድርም [ሀ]መናወጥ እናም ብዙ በዳማም በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤ ነገር ግን ሰዎች በእኔ ላይ ልባቸውን ያደነድናሉ፣ እናም እርስ በራሳቸው [ለ]ሰይፋቸውን ይማዘዛሉ፣ እናም ይገዳደላሉ።

፴፬ እና አሁንም፣ እኔ ጌታ እነዚህን ቃላት ለደቀ መዛሙርቴ ስነግራቸው ተጨንቀው ነበር።

፴፭ እናም እኔ እንዲህ አልኳቸው፣ [ሀ]አትጨነቁ፣ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሊሆኑ ግድ ስለሚሆን፣ ቃል የገባሁላችሁ ነገሮች ሁሉ እንደሚፈጸሙ ታውቃላችሁ።

፴፮ ብርሀንም መፈንጠቅ ሲጀምር፣ በምሳሌም እንደማሳያችሁ ለእነርሱም እንዲሁ ይሆናል—

፴፯ ተመልከቱ እና [ሀ]የበለስ ዛፎችንም እዩ፣ እናም በአይኖቻችሁም ተመልከቷቸው፣ እና ሲያቈጠቍጡ፣ እናም ቅጠሎቻቸውም ሲለመልሙ፣ በጋ አሁን እየቀረበ ነው ትላላችሁ፤

፴፰ እነዚህን ነገሮች ሁሉ በሚያዩበት በዚያ ቀንም እንዲህም ይሆናል፣ ከዚያም ሰአቱ እንደደረሰ ያውቃሉ።

፴፱ እና እንዲህም ይሆናል፣ እኔን [ሀ]የሚፈራ የጌታን መምጫ ታላቅ [ለ]ቀን፣ እንዲሁም [ሐ]የሰውን ልጅ መምጫ [መ]ምልክቶችን፣ [ሠ]ይጠብቃል።

፵ እናም ምልክቶችንና ተዓምራቶችን ያያሉ፣ ምክንያቱም በላይ ሰማይ እና በታች በምድርም ይታያሉና።

፵፩ እናም ደምን፣ [ሀ]እሳትን፣ እና የጢስ ጭጋግን ይመለከታሉ።

፵፪ እና የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊትም፣ [ሀ]ፀሀይ ትጨልማለች፣ እናም ጨረቃ ወደ ደምነት ትለወጣለች፣ እናም ክዋክብትም ከሰማይ ይረግፋሉ።

፵፫ እናም የቀሩትም በዚህ ስፍራ ይሰበሰባሉ፤

፵፬ ከዚያም እኔን ይሻሉ፣ እናም እነሆ፣ እኔም እመጣለሁ፤ እናም በሀይልና በሰማይ ደመና፣ በታላቅ [ሀ]ክብር ተሸፍኜ፣ ከሁሉም ቅዱሳን መላእክት ጋርም ያዩኛል፤ እናም እኔን [ለ]የማይጠብቀውም እርሱ ተለይቶ ይጠፋል።

፵፭ የጌታ ክንድ ከመውረዱ በፊት ግን፣ አንድ መልአክ [ሀ]መለከቱን ይነፋል፣ እናም አንቀላፍተው የነበሩት ቅዱሳንም [ለ]በደመናው እኔን ለመቀበል [ሐ]ይመጣሉ።

፵፮ ስለዚህ፣ [ሀ]በሰላም ብታንቀላፉ የተባረካችሁ ናችሁ፤ ምክንያቱም አሁን አይታችሁኝ እንዳወቃችሁኝ፣ እንዲሁም እና

፴፩ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፲፱–፳፤ ፺፯፥፳፪–፳፭።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፳፩–፳፪፣ ፷፬።
ለ ራዕ. ፲፮፥፲፩፣ ፳፩።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፹፫፥፲፰፤ ፹፰፥፹፯–፺።
ለ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፭።
፴፭ ሀ ማቴ. ፳፬፥፮።
፴፯ ሀ ማር. ፲፫፥፳፰፤ ሉቃ. ፳፩፥፳፱–፴፩።
፴፱ ሀ ት. እና ቃ. ፲፥፶፭–፶፮። ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ፤ ፍርሀት—እግዚአብሔርን መፍራት።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ሐ ቅ.መ.መ. የሰው ልጅ።
መ ቅ.መ.መ. የጊዜዎች ምልክቶች።
ሠ ፪ ጴጥ. ፫፥፲–፲፫፤ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፭–፲፮፤ ሙሴ ፯፥፷፪።
፵ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፬፤ ፹፰፥፹፯–፺።
፵፪ ሀ ኢዩ. ፪፥፲፤ ራዕ. ፮፥፲፪፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፹፯፤ ፻፴፫፥፵፱።
፵፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
ለ ማቴ. ፳፬፥፳፱–፴፩፤ ማር. ፲፫፥፳፬–፳፯።
፵፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፫፤ ፹፫፥፲፰።
ለ ፩ ተሰ. ፬፥፲፮–፲፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፮–፺፯። ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፵፮ ሀ አልማ ፵፥፲፪።

ንት ወደ እኔ [ለ]መጥታችሁ ነፍሶቻችሁም [ሐ]ህያው ይሆናሉና፣ እና ደህንነታችሁም ፍጹም ይሆናል፤ እና ቅዱሳንም ከአራቱ የምድር ማዕዘናትም ይመጣሉ።

፵፯ ከዚያም የጌታ [ሀ]ክንድ በአህዛብ ላይ ይወርዳል።

፵፰ ከዚያም ጌታ እግሩን በዚህ [ሀ]ተራራ ላይ ያቆማል፣ እና ተራራውም ለሁለት ይሰነጠቃል፣ እና ምድርም [ለ]ትንቀጠቀጣለችም፣ ወዲህና ወዲያም ትናወጣለች፣ እና ሰማያትም [ሐ]ይንቀጠቀጣሉ።

፵፱ እና ጌታም ድምጹን ያሰማል፣ እናም የምድርም ዳርቻ ሁሉ ይሰሙታል፤ እና የምድር ነገስታት ሁሉ [ሀ]ዋይ ዋይ ይላሉ፣ እና የሳቁትም ሞኝነታቸውን ያያሉ።

፶ አሽሟጣጩንም አደጋ ይሸፍነዋል፣ ፌዘኛውም ይጠፋል፤ እናም ለኃጢአትም ያደፈጡ ሁሉ ተቆርጠው ወደ እሳት ይጣላሉ።

፶፩ ከዚያም [ሀ]አይሁድም ወደ እኔ [ለ]ተመልክተው እንዲህ ይላሉ፦ በእጆችህ እና በእግሮችህ ያሉት እነዚህ ቍስሎች ምንድን ናቸው?

፶፪ ከዚያም እኔ ጌታ እንደ ሆንኩም ያውቃሉ፤ ምክንያቱም እኔ እንዲህ እላቸዋለሁና፦ እነዚህ [ሀ]ቁስሎች በወዳጆቼ ቤት የቆሰልኳቸው ቍስሎች ናቸው። እኔም ከፍ የተደረግሁት ነኝ። እኔም [ለ]የተሰቀለው ኢየሱስ ነኝ። እኔም የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ።

፶፫ እና ከዚያም በኃጢአቶቻቸው ምክንያትም [ሀ]ያለቅሳሉ፤ ከዚያም [ለ]ንጉሳቸውን ስላሰቃዩ በሰቆቃም ያዝናሉ።

፶፬ እና ከዚያም [ሀ]የአህዛብ አገሮችም ይድናሉ፣ እና ህግን የማያውቁትም በፊተኛው [ለ]ትንሳኤ ስፍራ ይኖራቸዋል፤ እና ለእነርሱም [ሐ]ይቀልላቸዋል።

፶፭ በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ምንም ስፍራ እንዳይኖረው [ሀ]ሰይጣንም [ለ]ይታሰራል።

፶፮ እናም በክብሬ በምመጣበት በዚያም [ሀ]ቀንም፣ ስለ አስሮቹ [ለ]ደናግል የተናገርኩት ምሳሌም ይፈጸማል።

፶፯ እነርሱ ጥበበኛ ናቸው እናም [ሀ]እውነትን ተቀብለዋልና፣ እና እንደ [ለ]መሪያቸውም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል፣ እና [ሐ]አልተታለሉም—በእውነት እንዲህ እላችኋለሁ፣ ቀኑን ይዋጃሉ እንጂ ተቆርጠው ወደ [መ]እሳቱ አይጣሉም።

፶፰ እና [ሀ]ምድርንም [ለ]ይወርሱ ዘንድ ይሰጣቸዋል እናም ተባዝተውም ብርቱዎች ይሆናሉ፤ እናም ልጆቻቸውም ያለኃጢአት ወደ [ሐ]ደህንነት [መ]ያድጋሉ።

፶፱ ጌታም ከእነርሱ [ሀ]መካከል ይገኛልና፣ እናም ክብሩም በእነርሱ ላይ ያርፋል፣ እናም እርሱም ንጉሳቸውና [ለ]ህግ ሰጪአቸው ይሆናል።

፷ እና አሁንም እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ፣ [ሀ]አዲስ ኪዳን እስከሚተረጎም ድረስ ስለዚህ ምዕራፍ ከዚህ ሌላ ታውቁ ዘንድ ምንም

፵፮ ለ ኢሳ. ፶፭፥፫።
ሐ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፵፯ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፪–፲፮።
፵፰ ሀ ዘካ. ፲፬፥፬።
ለ ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፰፤ ፹፰፥፹፯።
ሐ ኢዩ. ፫፥፲፮፤ ት. እና ቃ. ፵፱፥፳፫።
፵፱ ሀ ት. እና ቃ. ፹፯፥፮።
፶፩ ሀ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ለ ዘካ. ፲፪፥፲።
፶፪ ሀ ዘካ. ፲፫፥፮።
ለ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
፶፫ ሀ ራዕ. ፩፥፯።
ለ ሉቃ. ፳፫፥፴፫፤ ዮሐ. ፲፱፥፫፣ ፲፬–፲፭።
፶፬ ሀ ሕዝ. ፴፮፥፳፫፤ ፴፱፥፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሐ ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፪።
፶፭ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ራዕ. ፳፥፪፤ ፩ ኔፊ ፳፪፥፳፮፤ ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፩፤ ፹፰፥፻፲።
፶፮ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ማቴ. ፳፭፥፩–፲፫፤ ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፬።
፶፯ ሀ ቅ.መ.መ. እውነት።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፴፯።
መ ት. እና ቃ. ፳፱፥፯–፱፤ ፷፫፥፶፬፤ ፷፬፥፳፫–፳፬፤ ፻፩፥፳፪–፳፭።
፶፰ ሀ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ለ ማቴ. ፭፥፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
መ ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፩፤ ፻፩፥፳፱–፴፩።
፶፱ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፩፤ ፻፬፥፶፱።
ለ ዘፍጥ. ፵፱፥፲፤ ዘካ. ፲፬፥፱፤ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳፩–፳፪።
፷ ሀ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)። ደግሞም የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም መፅሐፍ ቅዱስ ምርጫዎችን ተመልከቱ።

አልሰጣችሁም፣ እና በውስጡም እነዚህ ሁሉ ነገሮች ይታወቃሉ፤

፷፪ ስለዚህ ወደፊት ለሚመጡት ነገሮች ትዘጋጅ ዘንድ፣ አሁን ይህን እንድትተረጉም ሰጥቼሀለሁ።

፷፫ በእውነት እንዲህ እላችኋላሁ፣ ታላላቅ ነገሮች ይጠብቋችኋልና፤

፷፫ በባዕድ ሀገሮችም [ሀ]ጦርነትን ትሰማላችሁ፣ ነገር ግን እነሆ እንዲህ እላችኋላሁ፣ እነዚህ ቅርብ ናቸው፣ እንዲሁም በበራችሁ ላይ ቀርበዋል፣ እና ብዙ አመታት ከማለፋቸው በፊትም ስለራሳችሁ ሀገርም ጦርነትን ትሰማላችሁ።

፷፬ ስለዚህ የቤተክርቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ እኔ ጌታ ከምስራቅ ሀገሮች ተሰብስባችሁ ውጡ እና በአንድነትም ራሳችሁን ሰብስቡ እላችኋለሁ፤ ወደ [ሀ]ምእራብ ሀገሮችም ሂዱ፣ በዚያም የሚኖሩትንም ንስሀ እንዲገቡም ጥሯቸው፣ እና ንስሀ ቢገቡም ቤተክርቲያኖችን ለእኔ ስሩልኝ።

፷፭ እና በአንድ ልብና ሀሳብ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለእናንተ የሚመደብላችሁን ውርስ [ሀ]ለመግዛት ትችሉ ዘንድ ሀብቶቻችሁን ሰብስቡ።

፷፮ ይህም [ሀ]አዲሲቷ ኢየሩሳሌም፣ [ለ]የሰላም [ሐ]ምድር፣ [መ]መሸሸጊያ ከተማ፣ የልዑሉ እግዚአብሔር ቅዱሳን ደህንነት ስፍራ ትባላለች፤

፷፯ እና የጌታ [ሀ]ክብርም በዚያ ይገኛል፣ እናም የጌታ ፍርሀትም በዚያ ይኖራል፣ በዚህ ምክንያትም ኃጢአተኞቹም ወደ እርሷ አይገቡም፣ እናም ፅዮንም ተብላ ትጠራልች።

፷፰ በኃጢአተኞቹም መካከል እንዲህም ይሆናል፣ ሰይፉን በጎረቤቱ ላይ የማያነሳው እያንዳንዱ ሰውም ለደህንነት ወደ ፅዮን መሸሽ ያስፈልገዋል።

፷፱ በዚያም ከሰማይ በታች ካሉ እያንዳንዱ ሀገርም ወደ እሷ [ሀ]ይሰበሰባሉ፤ እና እርስ በራሱ በጦርነት ላይ የማይሆን ህዝብም እርሱ ብቻ ይሆናል።

፸ በኃጢአተኞቹ መካከልም እንዲህ ይባላል፣ ከፅዮን ጋር ለመዋጋት አንሂድ፣ ምክንያቱም የፅዮን ኗሪዎች አስፈሪዎች ናቸውና፤ ስለዚህ ልንቋቋማቸው አንችልም።

፸፩ እናም እንዲህ ይሆናል ጻድቃን ከእያንዳንዱ ሀገሮች ተሰብሰበው ይወጣሉ፣ እና የዘለአለማዊ ደስታ መዝሙርንም እየዘመሩ ወደ ፅዮን ይመጣሉ።

፸፪ እና አሁንም እንዲህ እላችኋላሁ፣ ይህን ስራ በህዝቡ አይኖች፣ እና በጠላቶቻችሁ አይኖች እንድታከናውኑ፣ እና ያዘዝኳችሁንም ነገሮች እስከምታከናውኑ ድረስ ስራችሁን እንዳያውቁ ለእኔ አስፈላጊ ነው እስከምላችሁ ድረስ እነዚህ ነገሮች ወደ አለም እንዳይወጡ ጠብቁ፤

፸፫ ይህንንም ሲያውቁ፣ እነዚህን ነገሮች ያስተውሉ ዘንድ ነው።

፸፬ ጌታ ሲመጣም ለእነርሱ [ሀ]አስፈሪ ይሆናል፣ ፍርሀትም ይይዛቸዋል፣ እና በሩቅ ቆመውም ይንቀጠቀጣሉ።

፸፭ እናም በጌታ ፍርሀት እና በሀይሉ ችሎት ምክንያት ሁሉም አገሮች ይፈራሉ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፷፫ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳፱፤
፹፯፥፩–፭፤ ፻፴፥፲፪።
፷፬ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፬።
፷፭ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳፯።
፷፮ ሀ ኤተር ፲፫፥፭–፮፤
ሙሴ ፯፥፷፪፤
እ.አ. ፩፥፲።
ቅ.መ.መ. አዲሲቱ
ኢየሩሳሌም፤
ፅዮን።
ለ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፫።
መ ኢሳ. ፬፥፮፤
ት. እና ቃ. ፻፲፭፥፮።
፷፯ ሀ ት. እና ቃ. ፷፬፥፵፩–፵፫፤
፺፯፥፲፰–፲፱።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
፷፱ ሀ ዘዳግ. ፴፥፫፤
ኤር. ፴፪፥፴፯–፴፱፤
ት. እና ቃ. ፴፫፥፮።
፸፬ ሀ ሶፎ. ፪፥፲፩።

ክፍል ፵፮

በመጋቢት ፰፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለቤተክስቲያኗ የተሰጠ ራዕይ። በዚህ በቤተክርስቲያኗ ቀደምት ጊዜያት፣ የቤተክርስቲያኗን ስርዓቶች ለማከናወን አንድ ወጥ የሆነ የአሰራር ሁኔታ አል ነበረም። ነገር ግን፣ በቅዱስ ቁርባን ስብሰባዎች እና በሌሎች ጉባዔዎች የቤተ ክርስቲያኗን አባላትና በትጋት ቤተክርስቲያኗን እየመረመሩ ያሉትን የመቀበል ልምድ በመጠኑም ቢሆን ነበር። ይህ ራዕይ የስብሰባዎችን አካሄድና አመራር እና የመንፈስ ስጦታዎችን ስለመፈለግ እና ለይቶ ስለማወቅ ስላለው መመሪያ በተመ ለከተ የጌታን ፈቃድ ይገልጣል።

፩–፪፣ ሽማግሌዎች ሰብሰባዎችን መንፈስ ቅዱስ እንደመራቸው ማከናወን አለባቸው፤ ፫–፯፣ እውነትን የሚሹ ከቅዱስ ቁርባን ስብሰባዎች መገለል የለባቸውም፤ ፯–፲፪፣ እግዚአብሔርን ጠይቁ እናም የመንፈስ ስጦታዎችን ፈልጉ፣ ፲፫–፳፮፣ ከእነዚህም ስጦታዎች የጥቂቶቹ ዝርዝር፤ ፳፯–፴፫፣ የቤተክርቲያን መሪዎች የመንፈስን ስጦታዎች የመለየት ሀይል ተሰጥቷቸዋል።

፩ የቤተክርቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ አድምጡ፤ እውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች ለእናንተው የሚነገሯችሁ ለእናንተ [ሀ]ጥቅም እና ትምህርት ነውና።

፪ ነገር ግን ምንም እንኳን እነዚህ ነገሮች ቢጻፉም፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዲሁም ፍጻሜ እስከሚሆንበት ወቅት፣ ሁሉንም ስብሰባዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና አመራር [ሀ]እንዲያካሂዱ በሁሉም ጊዜያት ለቤተክርስቲያኔ [ለ]ሽማግሌዎች ተሰጥቷቸዋል።

፫ ሆኖም፣ በአለም ፊት ከሚደረጉት የህዝብ ስብሰባዎቻችሁ ውስጥ በፍጹም ማንንም [ሀ]እንዳታስወጡ ታዛችኋል።

፬ እንዲሁም ማንንም [ሀ]የቤተክርስቲያኗ አባል ከቅዱስ ቁርባን ስብሰባዎች እንዳታስወጡ ታዛችኋል፤ ሆኖም፣ ማንም በደልን ያደረገ ቢኖር እስኪያስተሰርይ ድረስ ቅዱስ ቁርባንን [ለ]እንዲወስድ አትፍቀዱለት።

፭ ደግሞም እንዲህ እላችኋለሁ፣ ማናቸውንም መንግስትን በትጋት እየፈለጉ ያሉትን ከቅዱስ ቁርባን ስብሰባዎቻችሁ አታስወጧቸው—ይህንን የምናገረውም በቤተክርቲያኗ አባል ስላልሆኑት ነው።

፮ ደግሞም እንዲህ እላችኋለሁ፣ [ሀ]በማረጋገጫ ስብሰባዎቻችሁ ውስጥ የቤተክርቲያን አባል ያልሆኑ፣ በፅኑ መንግስትን የሚሹ፣ የሚገኙ ቢሆን አታስወጧቸው።

፯ ነገር ግን በልግስና የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ስለሁሉም ነገሮች [ሀ]እንድ ትጠይቁት ታዛችኋል፤ እናም መንፈስ የሚመሰክርላችሁንም ሁሉ በልብ [ለ]ቅድስና፣ በፊቴ በቅንነት በመራመድ፣ የደህንነታችሁን ፍጻሜ [ሐ]እያሰባችሁ፣ ሁሉንም ነገሮች በጸሎትና [መ]በምስጋና በማድረግ፣ በክፉመናፍስት ወይም [ሠ]በአጋንንት ትምህርት ወይም በሰዎች [ረ]ትእዛዛት [ሰ]እንዳትወሰዱ የእኔ ፈቃድ ነው፤ አንዳ

፵፮ ፩ ሀ ፪ ጢሞ. ፫፥፲፮–፲፯።
፪ ሀ ሞሮኒ ፮፥፱፤ ት. እና ቃ. ፳፥፵፭።
ለ አልማ ፮፥፩።
፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፰፥፳፪–፳፭። ቅ.መ.መ. ጓደኝነት።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ለ ፫ ኔፊ ፲፰፥፳፮–፴፪። ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
፮ ሀ ይህም በቅርብ የተጠመቁትን ማረጋገጥ ማለት ነው።
፯ ሀ ያዕ. ፩፥፭–፮፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፫።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
መ መዝ. ፻፤ አልማ ፴፬፥፴፰። ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
ሠ ት. እና ቃ. ፫፥፮–፯፤ ፵፭፥፳፱።
ረ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሰ ፩ ጢሞ. ፬፥፩–፬፤ ት. እና ቃ. ፵፫፥፭–፯።

ንዶቹ ከሰዎች ሌሎቹ ደግሞ ከአጋንንት ናቸውና።

፯ ስለዚህ፣ እንዳትታለሉ ተጠንቀቁ፤ እና ዘወትር ለምን እንደተሰጧችሁ እያስታወሳችሁ፣ እንዳትታለሉም የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በፅኑ [ሀ]ፈልጉ፤

፰ በእውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ ለሚወዱኝ እና ሁሉንም ትእዛዛቴን ለሚጠብቁ እናም ይህን ለማድረግ ፈቃድ ላላቸው ለእነርሱ ጥቅም የተሰጡ ናቸው፤ ለምኞቶቻችሁ [ሀ]ማስፈፀሚያ በክፉ [ለ]ለምልክት ሳይጠይቁ፣ ከእኔ የሚሹት ወይም ይጠየቁበት ዘንድ እንዲጠቀሙበት ነው።

፲ እና ደግሞም በእውነት እላችኋለሁ፣ እነዚህ ለቤተክርቲያኗ የተሰጡት [ሀ]ስጦታዎች ምን እንደሆኑ፣ ሁል ጊዜም እንድታስታውሷቸውና [ለ]በአዕምሮአችሁ እንድትጠብቋቸው ፍቃዴ ነው።

፲፩ ብዙ ስጦታዎች አሉ፣ ሁሉም ስጦታዎች ለሁሉም አልተሰጡም፤ [ሀ]እያንዳንዱም ሰው አንድ ስጦታ በእግዚአብሔር መንፈስ ተስጥቶታል።

፲፪ ሁሉም በዚህም እንዲጠቀሙበት፣ ለአንዳንዶቹ አንድ ተሰጥቷል፣ እና ለሌሎችም ሌላ ተሰጥቷል።

፲፫ ለአንዳንዶቹ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፣ እና ለአለምም ኃጢአት እንደተሰቀለ [ሀ]እንዲያውቁ በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷቸዋል።

፲፬ በታማኝነትም ቢቀጠሉ ዘለአለማዊ ህይወት እንዲኖራቸው፣ ለሌሎችም በእነርሱ ቃላት [ሀ]እንዲያምኑ ተሰጥቷቸዋል።

፲፭ እናም ደግሞም፣ ለአንዳንዶቹ፣ አንዱን ጌታ እንደሚያስደስተው፣ እንደ ጌታ ፈቃድ፣ እንደ ሰው ልጆች ሁኔታዎች ምህረቱን በማመቻቸት፣ በመንፈስ ቅዱስ የአስተዳደርን [ሀ]ልዩነት እንዲያውቁ ተስጥቷቸዋል።

፲፮ ደግሞም፣ ለሌሎችም ስለ አሰራር ልዩነት፣ ከእግዚአብሔርም እንደሚመጡ፣ መንፈስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም እንደሚሰጠው፣ እንዲያውቁ በመንፈስ ቅዱስ ይሰጣቸዋል።

፲፯ እናም ዳግም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለአንዳዶቹ በእግዚአብሔር መንፈስ፣ [ሀ]የጥበብ ቃል ተስጥቷቸዋል።

፲፰ ለሌላም፣ ሁሉም ብልህ እንዲሆኑ እና [ሀ]እውቀት እንዲኖራቸው ይማሩ ዘንድ፣ የእውቀት ቃል ተስጥቷቸዋል።

፲፱ ደግሞም፣ ለአንዳንዶቹ ለመፈወስ [ሀ]እምነት እንዲኖራቸው ተሰጥቷቸዋል፤

፳ እናም ለሌሎች [ሀ]ይፈውሱ ዘንድ እምነት እንዲኖራቸው ተስጥቷቸዋል።

፳፩ ደግሞም፣ ለአንዳንዶቹ [ሀ]ተዓምራትን ማድረግ ተሰጥቷቸዋል።

፳፪ እና ለሌሎችም [ሀ]ትንቢትን መናገር ተሰጥቷቸዋል።

፳፫ እና ለሌሎችም መናፍስትን [ሀ]ለመለየት ተሰጥቷቸዋል።

፳፬ ደግሞም፣ ለአንዳንዶች [ሀ]በልሳን መናገር ተሰጥቷቸዋል።

፳፭ እና ለሌላውም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ተሰጥቶታል።

፳፮ እናም እነዚህ [ሀ]ስጦታዎች ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር [ለ]ልጆች ጥቅም፣ ከእግዚአብሔር የመጡ ናቸው።

፳፯ ለቤተክርቲያኗ [ሀ]ኤጲስ ቆጶስ፣ እናም ቤተክርቲያኗን እንዲጠብቁና የቤተክር

፯ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፪፥፴፩።
፰ ሀ ያዕ. ፬፥፫።
ለ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፬፥፲፪።
ቅ.መ.መ. የመንፈስ ስጦታዎች።
ለ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
፲፩ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፪፥፬–፲፩።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፲፬ ሀ ፫ ኔፊ ፲፪፥፪።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፲፭ ሀ ሞሮኒ ፲፥፰።
፲፯ ሀ ሞሮኒ ፲፥፱።
ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. እውቀት።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፵፰–፶፪።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ተአምራት።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
፳፫ ሀ ሙሴ ፩፥፲፫–፲፭።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. የልሳኖች ስጦታ።
፳፮ ሀ ሞሮኒ ፲፥፰–፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።

ቲያናና ሽማግሌዎች እንዲሆኑ በእግዚአብሔር ለተመደቡት እና ለተሾሙትም፣ ከመካከላችሁ ከእግዚአብሔር የመጣ ያል ሆኑትን ነገሮች ናቸው እንዳይሉ እነዚህን ስጦታዎች [ለ]ለይተው እንዲያውቁ ተሰጥቷቸዋል።

፳፰ እናም እንዲህ ይሆናል፣ [ሀ]በመንፈስ የሚጠይቅ እርሱ በመንፈስም ይቀበላል፤

፳፱ ለአንዳንዶቹ እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች የሚሰጧቸውም፣ መሪም እንዲኖር፣ እያንዳንዱ አባላት በዚህ ይጠቀሙበት ዘንድ ነው።

፴ [ሀ]በመንፈስ [ለ]የሚጠይቀው እርሱ እንደ እግዚአብሔር [ሐ]ፈቃድ ይጠይቃል፤ ስለዚህ እንደጠየቀውም ተደርጓለታል።

፴፩ ደግሞም፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ በመንፈስ ምንም ስታደርጉ፣ ሁሉም ነገሮች በክርስቶስ ስም መደረግ አለባቸው፤

፴፪ እናም ለማንኛውም የተባረካችሁባቸው በረከቶች [ሀ]ምስጋናን በመንፈስ ለእግዚአብሔር መስጠት አለባችሁ።

፴፫ እና በፊቴም [ሀ]መልካምነትንና [ለ]ቅድስናን ሁል ጊዜ መለማመድ አለባችሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፵፯

በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በመጋቢት ፰፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ከዚህ ጊዜ እንደ ነቢዩ ጸሀፊ ያገለግል የነበረው ጆን ዊትመር የታሪክ ምሁር እና መዝጋቢ ሆኖ በመሾም ኦሊቨር ካውደሪን ለመተካት አመንትቶ ነበር። እንዲህም ጻፈ፣ "ላደርገው አልፈልግም ነበር ግን የጌታን ፈቃድ በዚህ ጉዳይ አከብራለሁ፣ እናምእርሱ ከፈለገው፣ በገላጩ ጆሴፍ በኩል ይህን እንደሚገልጽ ፍላጎቴ ነው።" ጆሴፍ ስሚዝ ይህን ራዕይ ከተቀበለ በኋላ፣ ጆን ዊትመር ተቀበለ እናም በተመደበበት ሀላፊነት አገለገለ።

፩–፬፣ ጆን ዊትመር የቤተክርስቲያኗን ታሪክ እንዲጠብቅ እና ለነቢዩ ጸሀፊ እንዲሆን ተመድቧል።

፩ እነሆ፣ በሌላ ኃላፊነት እስኪጠራ ድረስ አጋልጋዩ ጆን ቀጣይነት ያለው [ሀ]ታሪክ እንዲጽፍና እንዲጠብቅ፣ እናም፣ አገልጋዩ ጆሴፍ፣ የሚሰጡህ ን ነገሮች ሁሉ በመጻፍ እንዲረዳህ በእኔ ዘንድ አስፈላጊ ነው።

፪ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ በስብሰባዎች ላይ እንዲሁ መናገር ይችላል።

፫ ደግሞም፣ እልሀለሁ የቤተክርቲያኗን መዝገብ እና ታሪክ በቋሚነት እንዲጠብቅም ይሾም፤ ኦሊቨር ካውድሪ ሌላ ሀላፊነት ተሰጥቶታልና።

፬ ስለዚህ፣ ታማኝ እስከሆነ ድረስ፣ እነዚህን ነገሮች እንዲፅፍ [ሀ]በአፅናኙ ይሰጠዋል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፳፯ ለ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፬–፷፭።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ለ ት. እና ቃ. ፶፥፳፱።
ሐ ፪ ኔፊ ፬፥፴፭።
፴፪ ሀ ፩ ዜና ፲፮፥፰–፲፭፤
፩ ተሰ. ፩፥፪፤
አልማ ፴፯፥፴፯፤
ት. እና ቃ. ፶፱፥፯፣ ፳፩።
ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. በጎነት።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፵፯ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፷፱፥፪–፰፤ ፹፭፥፩–፪።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ አፅናኝ።

ክፍል ፵፰

በመጋቢት ፲፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ቅዱሳኑ የሚሰፍሩበትን መሬት ማግኘት የሚችሉበትን ዘዴ ነቢዩ ጌታን ጠይቆ ነበር። ወደ ኦሀዮ እንዲሰበሰቡ ጌታ ያዘዛቸውን በማክበር፣ ከምስራቅ ዩናይትድ ስቴትስ በሚሰደዱት የቤተክርስቲያኗ አባላት ምክንያት ይህ አስፈላጊ ጉዳይ ነበር። ክፍል ፴፯፥፩–፫፤ ፵፭፥፷፬ን ተመልከቱ።

፩–፫፣ በኦሀዮ የሚገኙት ቅዱሳን ከወንድሞቻቸው ጋር መሬታቸውን ይካፈሉ፤ ፬–፮፣ ቅዱሳን ምድርን ይግዙ፣ ከተማም ይስሩ፣ እና የቀዳሚ አመራሮቻቸውንም ምክር ይከተሉ።

፩ ለአላችሁበት ሁኔታ አስፈላጊ ስለሆነ፣ አሁን በምትኖሩበት መቆየታችሁ ተገቢ ነው።

፪ መሬት እስካላችሁ ድረስ፣ በምስራቅ ካሉ ወንድሞቻችሁ ጋር [ሀ]ተካፈሉ፤

፫ መሬት ከሌላችሁም፣ መልካም በሚመስላቸው ስፍራዎች፣ በአካባቢያቸው ከሚገኙት በአሁንም ጊዜ ይግዙ፣ ምክንያቱም በዚህም ጊዜ መኖሪያ እንዲኖራቸው በጣም አስፈላጊ ነውና።

፬ በጊዜው መሬት፣ [ሀ]እንዲሁም ከተማ፣ ለውርስ [ለ]ለመግዛት እንድትችሉ፣ የምትችሉትን ያህል ገንዘብ ማጠራቀም እና የምትችሉትን ነገሮች በፅድቅ ማግኘታችሁ በጣም አስፈላጊ ነው።

፭ ስፍራው የሚገለጥበት ወቅት ገና ነው፤ ነገር ግን ወንድሞቻችሁ ከምስራቅ ከመጡ በኋላ [ሀ]አንዳንድ ሰዎች ሹመት ይሰጣቸው፣ እና ለእነርሱም ስፍራውን [ለ]እንዲያውቁ ይሰጣል፣ ወይም ለእነርሱ ይህ ይገለጣል።

፮ መሬቶችንም እንዲገዙ እና [ሀ]የከተማውን መሰረት እንዲጀምሩ ሀላፊነት ይሰጣቸዋል፤ እና ከዚያም እያንዳንዱ ሰው እንደ [ለ]ቤተሰቡ፣ እንደ ጉዳዮቹ፣ እና ከዚህ በፊት በተቀበላችሁትና ወደፊትም በምትቀበሉት ትእዛዝ በኩል በአመራሩና በቤተክርስቲያኗ ኤጲስ ቆጶስ እንደተወከሉለት፣ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር መሰብሰብ ትጀምራላችሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፵፱

በግንቦት ፯፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ ለስድኒ ሪግደን፣ ለፓርሊ ፒ ፕራት፣ እና ለሊመን ኮፕሊ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ሊመን ኮፕሊ ወንጌልን ተቀብሎ ነበር፣ ነገር ግን ቀደም ሲል አባል የነበረበትን የሼከሮቹን [የተወዛዋዦቹ] (ዩናይትድ ሶሳይቲ ኦፍ ብሊቨርስ እን ክራይስትስ ሰከንድ አፒሪንግ [በክርስቶስ ዳግም ምፅዓት የሚያምኑ የአንድነት ህብረተሰብ]) አንዳንድ ትምህርቶችን ይዞ ነበር። አንዳንዶቹ የሼከሮቹ እምነቶች የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቀደም ሲል እንደተከሰተ፣ እና አን ሊ በምትባል ሴት አምሳል እንደተገለጠ ነበር። የውሀ ጥምቀት እንደ አስፈላጊ ድርገት አይመለከቱትም ነበር። ጋብቻን አስወግደው፣ ግብረ ስጋ በማይፈጸምበት ኑሮ ያምኑ ነበር። አንዳ

፵፰ ፪ ሀ ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፭–፴፮፤ ፵፭፥፷፭–፷፮።
ለ ት. እና ቃ. ፶፯፥፬–፭።
፭ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፮–፰።
ለ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፫።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
ለ ት. እና ቃ. ፶፩፥፫።

ንድ ሼከሮችም ስጋ መብላትን ይከለክሉ ነበር። ለዚህ ራዕይ መቅድምም፣ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንዲህ ይገልጻል፣ "ስለ ርዕሱ ፍጹም እውቀት ለማግኘት፣ ጌታን ጠየቅሁ፣ እናም የሚከተለውን ተቀበልሁ።" ራዕዩም የሼከሮቹ ቡድን መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ያፈርሳል። ከዚህ በፊት የተጠቀሱት ወንድሞችም ይህን ራዕይ (ክሊቭላንድ ኦሀዮ አካባቢ ላለው) ወደ ሼከሮቹ ማህበረሰብ ወስዱት፣ እና ለእነርሱም ሁሉንም አነበቡላቸው፣ ነገር ግን አልተቀበሉትም ነበር።

፩–፯፣ የክርስቶስ ምጽአት ቀንና ሰአት እርሱ እስከሚመጣ ድረስ አይታወቅም፤ ፰–፲፬፣ ደህንነትን ለማግኘት፣ ሰዎች ንስሀ መግባት፣ በወንጌሉ ማመን፣ እና ስርዓቶችን ማክበር አለባቸው፤ ፲፭–፲፮፣ ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው፤ ፲፯–፳፩፣ ስጋን መመገብ የተፈቀደ ነው፤ ፳፪–፳፰፣ ከክርስቶስ የዳግም ምፅአት በፊት፣ ፅዮን ትበለፅጋለች እና ላማናውያንም እንደ ፅጌረዳ ያብባሉ።

፩ አገልጋዮቼ ስድኒ፣ ፓርሊ፣ እና ሊመን ቃሌን አድምጡ፤ እነሆም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የተቀበላችሁትን ወንጌሌን፣ እንደተቀበላችሁ እንዲሁ፣ ወደ ሼከሮቹ ሄዳችሁ [ሀ]እንድትሰብኩላቸው ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፪ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ሙሉ እውነትን ሳይሆን ከፊሉን ብቻ ለማወቅ ይሻሉ፣ ንስሀ መግባትም አለባቸው እና በፊቴ [ሀ]ትክክል አይደሉምና።

፫ ስለዚህ፣ አገልጋዮቼ ስድኒን እና ፓርሊን፣ ወንጌልን እንድትሰብኩላቸው እሰዳችኋለሁ።

፬ ከእነርሱ በተቀበላቸው ሳይሆን፣ በእናንተ በአገልጋዮቼ በኩል [ሀ]በሚማራቸው በኩል እነርሱን በሚገባ እንዲያስረዳ አገልጋዬ ሊመንም ለዚህ ስራ ይሾማል፤ ይህን በማድረግም እባርከዋለሁ፣ አለዚያም አይበለጽግም።

፭ ጌታ እንዲህም ይላል፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ እና አንድያ ልጄን ለአለም [ሀ]ቤዛነት ወደ አለም [ለ]ልኬአለሁ፣ እና እርሱን የሚቀበልው ይድናል፣ እናም እርሱንም ያልተቀበለው [ሐ]ይኮነናል ብዬ እደነግጋለሁና—

፮ እናም [ሀ]የሰውን ልጅም የወደዱትን ሁሉ አደረጉበት፤ እና ሀይሉንም [ለ]በክብሩ [ሐ]ቀኝ በኩል ወስዷል፣ እናም አሁንም በሰማያት ነግሷል፣ እናም በምድር ላይ ወርዶ ሁሉንም ጠላቶች ሁሉ ከእግሩ [መ]በታች እስከሚያደርጋቸው ጊዜ ድረስም ይነግሳል፤ እና ይህም ጊዜ ተቃርቧል—

፯ እኔ፣ ጌታ አምላክ፣ ይህን ተናግሬአለሁ፤ ነገር ግን ሰአቱንና [ሀ]ቀኑን የሰማይ መላእክትም ይሁን ሰው የሚያውቅ የለም፣ እስከሚመጣም ድረስ አያውቁትም።

፰ ስለዚህ፣ ለራሴ ካስቀረኋቸው፣ ከማታውቋቸው [ሀ]ቅዱሳን ሰዎች በስተቀር፣ ሁሉም [ለ]ኃጢአተኞች ስለሆኑ፣ ሁሉም ሰዎች ንስሀ ይገቡ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፱ ስለዚህ፣ እላችኋለሁ ከመጀመሪያ ጊዜ ጀምሮ የነበረውን ዘለአለማዊ [ሀ]ቃል ኪዳኔን ለእናንተ ልኬላችኋለሁ።

፵፱ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ።
፪ ሀ የሐዋ. ፫፥ ፳፩።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. እውነት፤ ወንጌል።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. መድኃኒት፤ ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
ለ ዮሐ. ፫፥ ፲፮–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥ ፳፬። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ስልጣን።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. የሰው ልጅ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
ሐ የሐዋ. ፯፥ ፶፭–፶፮፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፳–፳፫።
መ ፩ ቆሮ. ፲፭፥ ፳፭፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፻፮።
፯ ሀ ማቴ. ፳፬፥ ፴፮፤ ማር. ፲፫፥ ፴፪–፴፯፤ ራዕ. ፲፮፥ ፲፭፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥ ፲፩።
፰ ሀ ዕብ. ፲፫፥ ፪፤ ፫ ኔፊ ፳፰፥ ፳፭–፳፱።
ለ ገላ. ፫፥ ፳፪፤ ሞዛያ ፲፮፥ ፫–፭።
፱ ሀ ዘፍጥ. ፲፯፥ ፯፤ ት. እና ቃ. ፷፮፥ ፪። ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።

፲ እናም ቃል የገባሁትን ፈጽሜአለሁ፣ እና የምድር [ሀ]ህዝብ ለዚህ [ለ]ይሰግዳሉ፤ እናም፣ በራሳቸውም ካላደረጉት፣ በሀይል [ሐ]ዝቅ ይላሉ፣ አሁን ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደረጉትም በሀይል ይዋረዳሉና።

፲፩ ስለዚህ፣ በእነዚህ ህዝብ መካከል [ሀ]እንድትሄዱና፣ ስሙ ጴጥሮስ እንደነበረው እንደ ቀደመው ሐዋርያዬ፣ እንዲህም እንድትሏቸው ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ፥

፲፪ በመጀመሪያውና በመጨረሻው፣ በምድር ላይ በነበረው፣ እና ተመልሶም በሚመጣው፣ በጌታ ኢየሱስ ስም እመኑ፤

፲፫ በቅዱስ ትእዛዝ መሰረት፣ ለኃጢአቶች ስርየት፣ [ሀ]ንስሐ ግቡ እናም በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቁ፤

፲፬ ይህን የሚያደርጉም በቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች [ሀ]እጆችን በመጫን የመንፈስ ቅዱስ [ለ]ስጦታን ይቀበላሉ።

፲፭ እናም ዳግም፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ጋብቻን [ሀ]የሚከለክል በእግዚአብሔር የተሾመ አይደለም፣ [ለ]ጋብቻ ለሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነውና።

፲፮ ስለዚህ፣ ሰው አንዲት [ሀ]ሚስት እንድትኖረው ህግ ነው፣ እናም ሁለቱም አንድ [ለ]ሥጋ ይሆናሉ፣ እናም ይህም የሆነው [ሐ]ምድር የተፈጠረችበትን አላማ ታሟላ ዘንድ ነው፤

፲፯ እናም ምድር ከመፈጠሯ [ሀ]አስቀድሞ [ለ]እንደፍጥረቱ፣ ምድር በተመደበላት የሰው ቁጥርም ትሞላ ዘንድ ነው።

፲፰ እናም ሰውን [ሀ]ስጋ እንዳይበላ፣ ከስጋም [ለ]እንዲለይ የሚከለክል በእግዚአብሔር የተሾመ አይደለም፤

፲፱ ስለሆነም፣ የምድር [ሀ]አራዊት እና የሰማይ አዕዋፋት እና በምድር የሚበቅለውም፣ ለሰው ምግብና ልብስ ጥቅም፣ እናም በበቂም እንዲኖረው የተመደበ ነው።

፳ ነገር ግን አንድ ሰው ከሌላው በላይ [ሀ]እንዲኖረው አልተሰጠም፣ ስለዚህም [ለ]አለም በኃጢአት ወድቃለች።

፳፩ ሳያስፈልገው፣ ደምን [ሀ]ለሚያፈሰው ወይም ስጋን ለሚያባክነው ሰው፣ ወዮለት።

፳፪ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የሰው ልጅ [ሀ]የሚመጣው በሴት ወይም በምድር በሚጓዝ ሰው አምሳል አይደለም።

፳፫ ስለዚህ፣ [ሀ]አትታለሉ፣ ነገር ግን ጸንታችሁ ቆዩ፣ ሰማያት የሚንቀጠቀጡበትን፣ እና ምድርም እንደሰካራም የምትንቀጠቀጥበትን እና ወዲህና ወዲያ የምትናወጥበትን፣ እና [ለ]ሸለቆዎችም ከፍ ከፍ የሚሉበትን፣ እና [ሐ]ተራራዎችም ዝቅ የሚሉበትን፤ ስርጉጥጓጡም ሜዳ የሚሆንበትን ይህንን [መ]ጠብቁ—እና ይህ ሁሉ የሚሆነውም መላዕክቱ [ሠ]መለከቱን ሲነፉ ነው።

፳፬ ነገር ግን የጌታ ታላቅ ቀን ከመምጣቱ በፊት፣ [ሀ]ያዕቆብ በዱር ይበለፅጋል፣ እና ላማናውያንም እንደ ፅጌረዳ [ለ]ያብባሉ።

፲ ሀ ዘካ. ፪፥፲፩፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፰–፳፱፤ ፺፯፥፲፰–፳፩።
ለ ኢሳ. ፳፥፲፬።
ሐ ማቴ. ፳፫፥፲፪።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፲፫ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፥፲፱–፳።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
ለ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
፲፭ ሀ ፩ ጢሞ. ፬፥፩–፫።
ለ ዘፍጥ. ፪፥፲፰፣ ፳፬፤ ፩ ቆሮ. ፲፩፥፲፩። ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት።
፲፮ ሀ ያዕቆ. ፪፥፳፯–፴።
ለ ዘፍጥ. ፪፥፳፬፤ ማቴ. ፲፱፥፭–፮።
ሐ ቅ.መ.መ. ምድር—ለሰው የተፈጠረች ነች።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ለ ሙሴ ፫፥፬–፭። ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
፲፰ ሀ ዘፍጥ. ፱፥፫፤ ፩ ጢሞ. ፬፥፩–፫።
ለ ይህም ለመከልከል አዘዘ ማለት ነው።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፹፱፥፲–፲፫።
፳ ሀ የሐዋ. ፬፥፴፪፤ ት. እና ቃ. ፶፩፥፫፤ ፸፥፲፬፤ ፸፰፥፮።
ለ ቅ.መ.መ. አለማዊነት።
፳፩ ሀ ጆ.ስ.ት. ዘፍጥ. ፱፥፲–፲፭ (ተጨማሪ)።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፳፫ ሀ ማቴ. ፳፬፥፬–፭።
ለ ኢሳ. ፵፥፬፤ ት. እና ቃ. ፻፱፥፸፬።
ሐ ሚክ. ፩፥፫–፬።
መ ፪ ጴጥ. ፫፥፲፪፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፴፱።
ሠ ማቴ. ፳፬፥፳፱–፴፩።
፳፬ ሀ ፫ ኔፊ ፭፥፳፩–፳፮።
ለ ኢሳ. ፴፭፥፩፤ ፪ ኔፊ ፴፥፭–፮፤ ፫ ኔፊ ፳፩፥፳፪–፳፭፤ ት. እና ቃ. ፫፥፳፤ ፻፱፥፷፭።

፳፭ ፅዮንም [ሀ]በኮረብታዎች ላይ [ለ]ትበለፅጋለች እናም በተራራዎችም ላይ ሀሴትን ታደርጋለች፣ እናም በመረጥኩትም ስፍራ ላይ አብራ ትሰበሰባለች።

፳፮ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ እንዳዘዝኳችሁ ሂዱ፤ ለኃጢአታችሁ ሁሉ ንስሀ ግቡ፤ [ሀ]ለምኑ፣ ይሰጣችኋል፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል።

፳፯ እነሆ፣ ከፊታችሁ እሄዳለሁ እናም [ሀ]እከተላችኋለሁ፤ እና [ለ]በመካከላችሁ እሆናለሁ፣ እና እናንተም [ሐ]አታፍሩም።

፳፰ እነሆ፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ፣ [ሀ]በቶሎም እመጣለሁኝ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፶

በግንቦት ፱፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፣ አንዳንድ ሽማግሌዎች እንዴት የተለያዩ መናፍስት ራሳቸውን በአለም ላይ እንደሚገልጹ እንዳልገባቸው፣ እናም ስለዚህ ጉዳይ ባደረገው ልዩ ጥያቄ ምክንያትም ይህ ራዕይ እንደተሰጠ ገለጸ። መንፈሳዊ አጋጣሚዎች የሚባሉት በአባላቱ መካከል አዲስ አልነበሩም፣ አንዳንዶችም ራዕዮችንና መግለጦንች ተቀብለናል ይሉም ነበር።

፩–፭፣ ብዙ የሀሰት መናፍስት በምድር ውስጥ ይገኛሉ፤ ፮–፱፣ ለግብዞች እና ከቤተክርስቲያኗ ለሚቆረጡት ወዮላቸው፤ ፲–፲፬፣ ሽማግሌዎች ወንጌሉን በመንፈስ ይሰበኩ፤ ፲፭–፳፪፣ ሰባኪዎቹ እና ሰሚዎቹም በመንፈስ መታነጽ ያስፈልጋቸዋል፤ ፳፫–፳፭፣ የማያንጸውም ከእግዚአብሔርም የሚመጣ አይደለም፤ ፳፮–፳፰፣ ታማኞች የሁሉም ነገሮች ባለቤቶች ናቸው፤ ፳፱–፴፮፣ የንጹህ ሰዎች ጸሎቶችም መልስ ያገኛሉ፤ ፴፯–፵፮፣ ክርስቶስ መልካም እረኛ እና የእስራኤል አለት ነው።

፩ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ አድምጡ፣ እና ለሕያው አምላክም ድምፅ ጆሮአችሁን ስጡ፤ እናም በምድር ውስጥ ስላሉት መናፍስት፣ እና ቤተክርስቲያኗን እንደሚነካው እና እንደተስማማችሁት ስለ ጠየቃችሁኝ የሚሰጣችሁን የጥበብ ቃላት አድምጡ።

፪ እነሆ፣ እውነት እንዲህ እላችኋለሁ፣ አለምን የሚያታልሉ፣ በምድር ውስጥ የሚሄዱ፣ ብዙ [ሀ]የሀሰት መናፍስት የሆኑ መናፍስት አሉ።

፫ እናም [ሀ]ሰይጣን፣ እንዲጥላችሁም፣ ሊያታልላችሁ ፈልጓል።

፬ እነሆ፣ እኔ ጌታ እናንተን ተመልክቼአለሁ፣ እናም በስሜ [ሀ]በምትታወቀው ቤተክርስቲያን ውስጥም አፀያፊነቶችን ተመልክቻለሁ።

፭ ነገር ግን፣ በህይወትም ይሁን በሞት፣ ታማኝ የሆኑ እና [ሀ]የሚጸኑ የተባረኩ ናቸው፣ ዘለአለማዊ ህይወትን ይወርሳሉና።

፮ ነገር ግን [ሀ]ለሚያስቱ እና ለግብዞችም

፳፭ ሀ ዘፍጥ. ፵፱፥፳፮፤
፪ ኔፊ ፲፪፥፪–፫።
ለ ት. እና ቃ. ፴፭፥፳፬።
፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፫።
፳፯ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲፪።
ለ ፫ ኔፊ ፳፥፳፪።
ሐ ፩ ጴጥ. ፪፥፮፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፻፲፮።
፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፪።
፶ ፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፱።
ቅ.መ.መ. መንፈስ—ክፉ መንፈሶች።
፫ ሀ ሉቃ. ፳፪፥፴፩፤
፫ ኔፊ ፲፰፥፲፰።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. መፅናት።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል።

ወዮላቸው፣ ምክንያቱም፣ ጌታ እንዲህ ይላል፣ ወደ ፍርድ አመጣቸዋለሁና።

፯ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከእናንተ መካከል፣ አንዳንዶችን በማታለል [ሀ]ለጠላት [ለ]ሀይል የሰጡ [ሐ]ግብዞች አሉ፤ ነገር ግን እነሆ [መ]እነዚህም ደግመው ሊመለሱ ይችላሉ፤

፰ ግብዞቹ ግን፣ በዚህ ህይወትም ይሁን በሞት፣ እንደፈቃዴ ይታወቃሉ እናም ይቆረጣሉ፤ እናም ከቤተክርስቲያኔ [ሀ]ለተቆረጡ ለእነርሱ ወዮላቸው፣ በአለም ተሸንፈዋልና።

፱ ስለዚህ፣ በፊቴ እውነት እና ፅድቅ ያልሆነውን እንዳያደርግ እያንዳንዱ ሰው ይጠንቀቅ።

፲ እናም አሁን፣ በመንፈስ ወደ ቤተክርስቲያኑ ሽማግሌዎች፣ ኑ ይላል ጌታ፣ እና ይገባችሁ ዘንድ [ሀ]እንወቃቀስ፤

፲፩ ሰው እርስ በርሱ እንደሚወቃቀስም ፊት ለፊት እንወቃቀስ።

፲፪ አሁን፣ አንድ ሰው ሲወቃቀስ ሰውም ይረዳዋል፣ ምክንያቱም እንደ ሰው ይወቃቀሳልና፣ እንዲሁም እኔ ጌታ፣ [ሀ]ይገባችሁ ዘንድ ከእናንተ ጋር እወቃቀሳለሁ።

፲፫ ስለዚህም፣ እኔ ጌታ ይህን እጠይቃችኋለሁ—ስለምን ነበር [ሀ]የተሾማችሁት?

፲፬ [ሀ]በመንፈስ፣ እንዲሁም እውነትን ለማስተማር በተላከው [ለ]አፅናኝ፣ ወንጌሌን ትሰብኩ ዘንድ ነው።

፲፭ እና ከዚያም የማይገባችሁን [ሀ]መናፍስት ተቀብላችሁ፣ እናም ከእግዚአብሔር እንደሆኑም በማስመሰል እነዚህን ትቀበላላችሁ፤ እናም በዚህስ ትጸደቃላችሁን?

፲፮ እነሆ ይህን ጥያቄ ራሳችሁ ትመልሳላችሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ምህረት አደርግላችኋለሁ፤ ከዚህ በኋላ በእናንተ መካከል ደካማ የሆነ [ሀ]ብርቱም ይሆናል።

፲፯ እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ ተሹሞ እና፣ በእውነት መንፈስ በኩል፣ በአፅናኙ የእውነትን ቃል [ሀ]ለመስበክ እንዲሄድ የታዘዘ፣ [ለ]በእውነት መንፈስ ይሰብካልን ወይስ በሌላ ዘዴ?

፲፰ እናም በሌላ ዘዴ ከሆነ ከእግዚአብሔር አይደለም።

፲፱ እና ደግሞም፣ የእውነትንስ ቃል የተቀበለው፣ በእውነት መንፈስ ነው ወይስ በሌላ ዘዴ?

፳ በሌላ ዘዴ ከሆነ ከእግዚአብሔር አይደለም።

፳፩ ስለዚህ፣ ቃልን በእውነት መንፈስ የተቀበለው በእውነት መንፈስ ተሰብኮለት እንደተቀበለው፣ የማይገባችሁ እናም የማታውቁት ለምንድን ነው?

፳፪ በዚህም ምክንያት፣ የሚሰብከው እና የሚቀበለውም እርስ በርሳቸው ይግባባሉ፣ እና [ሀ]ይተናነጻሉ እና አብረውም [ለ]ይደሰታሉ።

፳፫ እና ያለማነጽ ያልሆነውም ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም፣ እና [ሀ]ከጭለማ ነው።

፳፬ ከእግዚአብሔር የሆነው [ሀ]ብርሀን ነው፤ እና ብርሀንን ተቀብሎ በእግዚአብሔር [ለ]የሚቀጥል፣ [ሐ]ተጨማሪ ብርሀንን ይቀበላል፤ እናም ብርሀኑም ፍጹም እስከሆነው ቀን ድረስም እየጨመረ ይበራል።

፯ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ለ ሞዛያ ፳፯፥፰–፱።
ሐ ማቴ. ፳፫፥፲፫–፲፭፤ አልማ ፴፬፥፳፰።
መ ይህም እነዚያ የታለሉት ሰዎች ማለት ነው።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፬፤ ፶፮፥፫፤ ፷፬፥፴፭።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፲ ሀ ኢሳ. ፩፥፲፰፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፲።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፳፬።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፭።
ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ—በመንፈስ ማስተማር።
ለ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፲፮ ሀ ኤተር ፲፪፥፳፫–፳፯።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ፤ የሚስዮን ስራ።
ለ ት. እና ቃ. ፮፥፲፭።
ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ እውነት።
፳፪ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፬፥፳፮።
ለ ዮሐ. ፬፥፴፮።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
፳፬ ሀ ፩ ዮሐ. ፩፥፭–፲፩፤ ሞሮኒ ፯፥፲፬–፲፱፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፵፭–፵፯፤ ፹፰፥፵፱።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ዮሐ. ፲፭፥፬–፭፣ ፲።
ሐ ፪ ኔፊ ፳፰፥፴።

፳፭ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እናም ይህን የምለውም [ሀ]እውነቱን ታውቁ ዘንድ፣ ከመካከላችሁም ጭለማን ታስወግዱ ዘንድ ነው፤

፳፮ ምንም እንኳን እርሱ ታናሽ እና የሁሉ [ሀ]አገልጋይ ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር የተሾመ እና የተላከ፣ እርሱ [ለ]ታላቅ ይሆን ዘንድ ተመርጧል።

፳፯ በመሆኑም፣ እርሱ የሁሉም ነገሮች [ሀ]ባለቤት ነው፤ በሰማይ እናም በምድር በልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ አብ ፈቃድ የተላኩ ነገሮች ሁሉ፣ ህይወት እና ብርሀን፣ መንፈስ እና [ለ]ሀይል፣ ለእርሱ ተገዢ ናቸውና።

፳፰ ነገር ግን ከሁሉም ኃጢአት [ሀ]የጸዳ እና [ለ]የነጻ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው የሁሉም ነገሮች ባለቤት ሊሆን አይችልም።

፳፱ እና ከሁሉም ኃጢአቶች ከጸዳችሁ እና ከነጻችሁ፤ የምትሹትን ሁሉ በኢየሱስ ስም [ሀ]ትጠይቃላችሁ እናም ይህም ይከናወናል።

፴ ነገር ግን ይህን እወቁ፣ የጠየቃችሁት ይሰጣችኋል፤ እናም [ሀ]የመሪነት ሀላፊነት ሲሰጣችሁም፣ መናፍስትም ይገዙላችኋል።

፴፩ በመሆኑም፣ እንዲህም ይሆናል፣ የማትረዱትን [ሀ]መንፈስ ስታዩ፣ እና መንፈሱንም ካልተቀበላችሁ፣ አብን በኢየሱስ ስም ጠይቁ፤ እና ያን መንፈስ እርሱ ካልሰጣችሁ፣ ከዚያም ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ታውቃላችሁ።

፴፪ እና ለእናንተም በዚያ መንፈስ ላይም [ሀ]ሀይል ይሰጣችኋል፤ እና ያ መንፈስ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነም በታላቅ ድምጽ ታሳውቁታላችሁ፣

፴፫ በመንፈሱም እንዳትሸነፉ፣ [ሀ]በስድብ ቃል ሳይሆን፣ ወይም በዚያም እንዳትያዙ፣ [ለ]በኩራት ወይም በደስታ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ታሳውቁታላችሁ።

፴፬ ከእግዚአብሔር የተቀበለውም፣ ከእግዚአብሔር እንደተቀበለው ይቁጠረው፤ እናም ለመቀበልም በእግዚአብሔር ብቁ ሆኖ ስለተቆጠረም ይደሰት።

፴፭ እናም በማድመጥ እናም የተቀበላችሁትን እነዚህን ነገሮች—እናም ከአብ [ሀ]መንግስቱን፣ እና ከእርሱ ያልተመደቡትን ነገሮች ለማሸነፍ [ለ]ሀይል ተሰጥቷችኋል—እናም ከዚህም በኋላ የምትቀበሏቸውን በማድረግ፣

፴፮ እናም እነሆ፣ በእውነትም እንዲህ እላችኋላሁ፣ በአገልጋዬ አንደበት የተሰጡትን እነዚህን ቃላቴን አሁን የምታደምጡ ሁሉ የተባረካችሁ ናችሁ፣ ለኃጢአቶቻችሁ [ሀ]ምህረት ተሰጥቷችኋልና።

፴፯ የተደሰትኩበት አገልጋዬ፣ ጆሴፍ ዌክፊልድ እና አገልጋዬ [ሀ]ፓርሊ ፒ ፕራት ከቤተክርስቲያናቱ መካከል ይሂዱ እናም [ለ]በምክር ቃላትም ያጠናክሯቸው፤

፴፰ እናም አገልጋዬ ጆን ኮርል፣ ወይም ለዚህ ሀላፊነት የተሾሙት አገልጋዮቼ ሁሉ፣ [ሀ]በወይን ስፍራ ወስጥ ያገልግሉ፤ እና ሀላፊነት የሰጠኋቸውን ነገሮች ያከናውኑ ዘንድ ማንም ሰው አያደናቅፋቸው—

፴፱ ስለዚህ፣ በዚህ ነገር አገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ ትክክል አይደለም፤ ይህም ቢሆን ንስሀ ይግባ እናም ይቅርታን ይቀበላል።

፵ እነሆ፣ እናንተ ህጻናት ናችሁ እና ሁሉ

፳፭ ሀ ዮሐ. ፰፥ ፴፪።
፳፮ ሀ ማር. ፲፥ ፵፪–፵፭።
ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
ለ ማቴ. ፳፫፥ ፲፩።
፳፯ ሀ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፭–፲፣
፶፫–፷፤ ፹፬፥ ፴፬–፵፩።
ለ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፳፰ ሀ ፫ ኔፊ ፲፱፥ ፳፰–፳፱፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥ ፸፬–፸፭።
ቅ.መ.መ. ቅድስና፤
ንጹህ፣ ንጹህነት።
ለ ፩ ዮሐ. ፩፥ ፯–፱።
፳፱ ሀ ሔለ. ፲፥ ፭፤
ት. እና ቃ. ፵፮፥ ፴።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
፴፩ ሀ ፩ ዮሐ. ፬፥ ፩።
ቅ.መ.መ. መንፈስ—
ክፉ መንፈሶች።
፴፪ ሀ ማቴ. ፲፥ ፩።
፴፫ ሀ ይሁዳ ፩፥ ፱።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፷፯፣ ፸፫።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
ለ ፩ ዮሐ. ፬፥ ፬፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥ ፳፣ ፵፯።
፴፮ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፵፪–፵፫።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፕራት፣
ፓርሊ ፓርከር።
ለ ት. እና ቃ. ፺፯፥ ፫–፭።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣
ኤድዋርድ።

ንም ነገሮች አሁን [ሀ]ትሸከሙ ዘንድ አትችሉም፤ [ለ]በጸጋ እና [ሐ]በእውነት እውቀትም [መ]ማደግ አለባችሁ።

፵፩ እናንተ [ሀ]አትፍሩ፣ [ለ]ህጻናት፣ የእኔ ናችሁና፣ እናም እኔ አለምን [ሐ]አሸንፌዋለሁ፣ እና እናንተም ከአባቴ ዘንድ [መ]የተሰጣችሁ ናችሁ፤

፵፪ አባቴ ከሰጠኝ ማንኛቸውም [ሀ]አይጠፋም።

፵፫ እናም አብ እና እኔ [ሀ]አንድ ነን። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ ነው፤ እና እኔን ከተቀበላችሁ፣ እናንተ በእኔ አላችሁ እና እኔም በእናንተ አለሁ።

፵፬ ስለዚህ፣ እኔ በመሀከላችሁ ነኝ፣ እና እኔም [ሀ]መልካሙ እረኛ፣ እና የእስራኤል [ለ]ድንጋይ ነኝ። በዚህ [ሐ]አለት ላይ የተመሰረተም [መ]አይወድቅም።

፵፭ እና ድምጼን የምትሰሙበትና እና [ሀ]የምታዩኝ፣ እና እኔ እንደሆንኩኝም የምታውቁበት ቀን ይመጣል።

፵፮ ስለዚህ፣ [ሀ]ትዘጋጁም ዘንድ [ለ]ጠብቁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፶፩

በግንቦት ፳፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በቶምሰን ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ ከምስራቅ አገሮች የተሰደዱ ቅዱሳን ኦሀዮ እየደረሱ ነበር፣ እናም የሚኖሩበትን ስፍራ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆነ። የዚህ ስራ መከናወን የኤጲስ ቆጶሱ ሀላፊነት ስለነበር፣ ኤጲስ ቆጶስ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ ስለ ጉዳዩ መመሪያ ፈለገ፣ እና ነቢዩም ጌታን ጠየቀ።

፩–፰፣ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ ሀላፊነትንና ንብረትን እንዲቆጣጠር ተሹሟል፤ ፱–፲፪፣ ቅዱሳን በቅንነት ይስሩ እና በእኩልነትም ይቀበላሉ፤ ፲፫–፲፭፣ የኤጲስ ቆጶስ ጎተራ ይኑራቸው እና ንብረቶችንም በጌታ ህግ አማካይነት ይቆጣጠሩ፤ ፲፮–፳፣ ኦሀዮ ጊዜያዊ የመሰብሰቢያ ስፍራ ትሆናለች።

፩ አድምጡኝ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፣ እና ለአገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እና ገራለሁ፣ እና መመሪያዎችን እሰጠዋለሁ፤ ምክንያቱም እነዚህን ህዝብ የሚያደራጅበትን መንገድ ይቀበል ዘንድ ያስፈልገዋልና።

፪ [ሀ]በህግጋቴ አማካይነትም መደራጀት አለባቸውና፤ ይህ ካልሆነ፣ እነርሱም ተለይተው ይጠፋሉ።

፫ ስለዚህ፣ የተደሰትኩባቸው፣ አገልጋዬ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እና እርሱ የመረጣቸውም፣ ለእነዚህ ህዝብ፣ እያንዳንዱም ሰው እንደየቤተሰቡ፣ እንደ ሁኔታው እና [ሀ]እንደ

፵ ሀ ፫ ኔፊ ፲፯፥ ፪–፫፤
ት. እና ቃ. ፸፰፥ ፲፯–፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ሐ ቅ.መ.መ. እውነት።
መ ፩ ቆሮ. ፫፥ ፪–፫፤
ት. እና ቃ. ፲፱፥ ፳፪–፳፫።
፵፩ ሀ ፩ ዮሐ. ፬፥ ፲፰።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
ሐ ዮሐ. ፲፮፥ ፴፫።
መ ዮሐ. ፲፥ ፳፯–፳፱፤ ፲፯፥ ፪፤
፫ ኔፊ ፲፭፥ ፳፬፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥ ፲፬፤
፹፬፥ ፷፫።
፵፪ ሀ ዮሐ. ፲፯፥ ፲፪፤
፫ ኔፊ ፳፯፥ ፴–፴፩።
፵፫ ሀ ዮሐ. ፲፯፥ ፳–፳፫፤
፫ ኔፊ ፲፩፥ ፴፭–፴፮።
ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
፵፬ ሀ ዮሐ. ፲፥ ፲፬–፲፭።
ቅ.መ.መ. መልካሙ እረኛ።
ለ ዘፍጥ. ፵፱፥ ፳፬፤
፩ ጴጥ. ፪፥ ፬–፰።
ቅ.መ.መ. የማዕዘን ድንጋይ።
ሐ ፩ ቆሮ. ፲፥ ፩–፬።
ቅ.መ.መ. አለት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ።
መ ሔለ. ፭፥ ፲፪።
፵፭ ሀ ት. እና ቃ. ፷፯፥ ፲–፲፫።
፵፮ ሀ አልማ ፴፬፥ ፴፪–፴፫።
ለ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፶፩ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣ ኤድዋርድ።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፴–፴፱፤ ፻፭፥ ፭።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
፫ ሀ የሐዋ. ፪፥ ፵፬–፵፭፤
፬ ኔፊ ፩፥ ፪–፫።

ሚያስፈልገው መጠን፣ ድርሻቸውን [ለ]በእኩል ይስጧቸው።

፬ እናም አገልጋዬ አኤድዋርድ ፓርትሪጅ ለሰው ድርሻውን በሚመድብበት ጊዜ፤ ይህንንም በቤተክርስቲያን ያለውን መብትና ውርስ ኃጢአትን እስካልሰራ እና በቤተክርስቲያንም ድምጽ ተጠያቂ እስካልሆነ ድረስ እንደቤተክርስቲያኗ ህግጋት እና [ሀ]ቃልኪዳኖች መሰረት በቤተክርስቲያኗም ይዞታ ስር እንዲሆን ድርሻውን የሚያረጋግጥለት ጽሁፍ ይስጠው።

፭ እናም ኃጢአት ከሰራ እና የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ግን፣ ለኤጲስ ቆጶሱ በቅድስና ለቤተክርስቲያኔ ድሆች እና ችግረኞች የሰጠውን ድርሻውን የመጠየቅ መብት አይኖረውም፤ ስለዚህ፣ ስጦታውን ቀጥሎ ለመያዝ አይችልም፣ ነገር ግን ለእርሱ በተሰጠው ድርሻ ላይ ግን የመጠየቅ መብት ሊኖረው ይችላል።

፮ እና በዚህም በምድሩ [ሀ]ህግጋት [ለ]በኩል ሁሉም ነገሮች ይረጋገጣሉ።

፯ እናም ለእነዚህ ህዝብ ተገቢ የሆኑት ነገሮችም ለእነዚህ ህዝብ ይሰጡ።

፰ እና ለእነዚህ ህዝብ የተረፈውም [ሀ]ገንዘብ—[ለ]ገንዘቡንም በመውሰድ፣ በህዝቦቹ ፍላጎታቸው መሰረት፣ ምግብ እና ልብሶችን የሚያስገኝ ወኪል ለእነዚህ ህዝብ ይመደብ።

፱ እንዳዘዝኳችሁ አንድ ትሆኑ ዘንድ፣ እያንዳንዱ ሰው [ሀ]በቅንነት ይስራ፣ እና በእነዚህ ህዝብም መካከል [ለ]እኩልም ይሁኑ፣ እና በእኩልም ይቀበሉ።

፲ ለእነዚህ ህዝብ ተገቢ የሆነውም ተወስዶ [ሀ]የሌላ ቤተክርስቲያን ለሆነው አይሰጥ።

፲፩ ስለዚህ፣ ሌላ ቤተክርስቲያን ከዚህች ቤተክርስቲያን ገንዘብ ከተቀበለ፣ በተስማሙበትም መጠን መልሰው ለቤተክርስቲያኗ ይክፈሉ።

፲፪ እና ይህም፣ በቤተክርስቲያኗ [ሀ]ድምፅ በተወከለው፣ በኤጲስ ቆጶሱ ወይም በወኪሉ በኩል የሚደረግ ይሁን።

፲፫ እና ደግሞም፣ ኤጲስ ቆጶሱ ለዚህች ቤተክርስቲያን [ሀ]የግምጃ ቤት ይመስርት፤ እናም ህዝቡ [ለ]ከሚፈልገው በላይ የሆነው፣ ሁሉም ነገሮችን፣ በገንዘብ እና በምግብ በኤጲስ ቆጶሱ እጆች በኩል ይጠበቁ።

፲፬ እናም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ስለሚሰራ፣ ለራሱ ፍላጎቶች፣ እናም ለቤተሰቦቹ ፍላጎቶች፣ የሚሆንን ይዞ ያስቀምጥ።

፲፭ እና ስለዚህም ራሳቸውን [ሀ]በህግጋቴ በኩል የሚያደራጁበት መብት ለእነዚህ ህዝብ ሰጥቻቸዋለሁ።

፲፮ እኔ ጌታ ሌላ እስከምሰጣቸው ድረስ፣ እና ከዚህም እንዲሄዱ እስከማዛቸው ድረስ፣ [ሀ]ይህን ምድር ለጥቂት ወቅት ቀድሼ እሰጣቸዋለሁ፤

፲፯ እናም ሰዓቱ እና ቀኑ አልተሰጣቸውም፣ ስለዚህ ይህን ምድር ለአመታት እንደሚኖሩበት አይነት ይስሩበት፣ እና ይህም ለእነርሱ የሚጠቅም ይሆንላቸዋል።

፲፰ እነሆ፣ ይህም በሌሎች ስፍራዎች፣ በሁሉም ቤተክርስቲያኖች ውስጥ፣ ለአገልጋዬ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ [ሀ]ምሳሌ ይሆናል።

፲፱ እና ታማኝ፣ ሐቀኛ፣ እና ብልህ [ሀ]መጋቢ ሆኖ የተገኘውም ወደ ጌታው

፫ ለ ት. እና ቃ. ፵፱፥፳።
፬ ሀ ይህም ክፍል ፳ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አንቀጾች እና ቃል ኪዳኖች ተብሎ ይጠራል ማለት ነው። ት. እና ቃ. ፴፫፥፲፬፤ ፵፪፥፲፫። ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፩–፳፪።
ለ ፩ ጴጥ. ፪፥፲፫፤ ት. እና ቃ. ፺፰፥፭–፯።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፻፬።
ለ ት. እና ቃ. ፻፬፥፲፭–፲፰።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣ ታማኝነት።
ለ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳፯። ቅ.መ.መ. አንድነት።
፲ ሀ ይህም የቤተክርስቲያኗ ሌላ ቅርንጫፍ እንጂ ሌላ ሀይማኖት ማለት አይደለም።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፶፭። ቅ.መ.መ. ጎተራ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፫–፴፬፣ ፶፭፤ ፹፪፥፲፯–፲፱።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፶፩፥፪።
፲፮ ሀ ይህም ከርትላንድ፣ ኦሀዮ አካባቢ ማለት ነው።
፲፰ ሀ ይህም ንድፍ ማለት ነው።
፲፱ ሀ ማቴ. ፳፬፥፵፭–፵፯። ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።

[ለ]ደስታ ይገባል፣ እና ዘለአለማዊ ህይወትንም ይወርሳል።

፳ በእውነትም፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ በማታውቁበት [ሀ]ሰአት [ለ]ቶሎ የምመጣው፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፶፪

በሰኔ ፯፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች የተሰጠ ራዕይ። በሰኔ ፫ ተጀምሮ በሰኔ ፯ የተዘጋ ጉባኤ ከርትላንድ ውስጥ ተካሂዶ ነበር። በዚህ ጉባኤ ውስጥም የመጀመሪያው ልዩ የሊቀ ካህን ሀላፊነት ሹመቶች ተደርገው ነበር፣ እናም የሀሰት እና የሚያታልሉ መናፍስትም ተገልጠው እና ተገስጸውም ነበር።

፩–፪፣ የሚቀጥለው ጉባኤ በሚዙሪ ውስጥ እንዲሆን ተወስኗል፤ ፫–፰፣ አንዳንድ ሽማግሌዎች አብረው እንዲጓዙም ተመድበዋል፤ ፱–፲፩፣ ሽማግሌዎችም ሐዋርያት እና ነቢያት የጻፉትን ያስተምሩ፤ ፲፪–፳፩፣ በመንፈስ የሚታነጹት የምስጋና እና የጥበብ ፍሬ ያመጣሉ፤ ፳፪–፵፬፣ ወደ ሚዙሪ ለጉባኤው እየተጓዙ እያሉ፣ ወንጌልን እየሰበኩ እንዲሄዱ የተለያዩ ሽማግሌዎች ተመድበዋል።

፩ እነሆ፣ ጌታ በእነዚህ በመጨረሻው ቀናት [ሀ]ለጠራቸው እና ለመረጣቸው ሽማግሌዎች በመንፈሱም ድምፅ፣ እንዲህ ይላል—

፪ እንዲህም አለ፤ እኔ ጌታ [ሀ]በቃል ኪዳን ወራሾች ለሆኑት፣ እና ለያዕቆብ [ለ]ቅሪት ለሆኑት ህዝቤ፣ [ሐ]በቀደስኩላቸው [መ]ምድር ላይ፣ በሚዙሪ ውስጥ የሚቀጥለው ጉባኤ እስከሚጠራ ድረስ ምን እንደምታደርጉ አስታውቃችኋለሁ።

፫ ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ቤታቸውን ትተው ለመሄድ ለመዘጋጀት በሚችሉበት፣ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ እና ስድኒ ሪግደን ወዲያው ይጓዙ፣ እና ወደ ሚዙሪ ምድርም ይጓዙ።

፬ እናም ለእኔ ታማኝ እስከሆኑም ድረስ፣ ምን እንደሚያደርጉ እንዲያውቁም ይደረግላቸዋል፤

፭ እናም ደግሞ፣ ታማኝ እስከሆኑም ድረስ፣ የውርሳችሁን [ሀ]ምድር እንዲያውቁት ይደረጋል።

፮ እና ታማኝ እስካልሆኑም ድረስ፣ በእኔ ፈቃድ፣ እና መልካም እንደሚመስለኝም ይገለላሉ።

፯ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ላይመን ዋይት እና አገልጋዬ ጆን ኮርል ፈጥነው ይጓዙ፤

፰ እና አገልጋዬ ጆን መርዶክ፣ እና አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ በድትሮይት በኩል ወደዚያ ይጓዙ።

፱ ከዚያም ስፍራ፣ [ሀ]ነቢያት እና ሐዋርያት ከጻፉት፣ እና በእምነት ጸሎት አማካይነት [ለ]አፅናኙ ካስተማራቸው ሌላ [ሐ]ምንም

፲፱ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፳ሀ ማቴ. ፳፬፥፵፬።
ለ ራዕ. ፳፪፥፯–፲፯።
፶፪ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፪ሀ አብር. ፪፥፯–፲፩።
ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ለ መዝ. ፻፴፫፥፬፤
፫ ኔፊ ፭፥፳፩–፳፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፰፥፶፯፤
፹፬፥፫–፬።
መ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፫።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፫።
፱ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፲፪፤
፶፪፥፴፯።
ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ ማስተማር፣ አስተማሪ— በመንፈስ ማስተማር፤ አፅናኝ።
ሐ ሞዛያ ፲፰፥፲፱–፳።

ሳይሉ፣ ቃሉን በሚያልፉበት ስፍራዎች እየሰበኩ ይጓዙ።

፲ [ሀ]ሁለት በሁለት ሆነውም ይጓዙ፣ እና በዚህም በሚያልፉበትም ስፍራዎች፣ [ለ]በውሀ በማጥመቅ እና በውሀውም አጠገብ [ሐ]እጃቸውን በመጫን፣ በእያንዳንዱ ስብሰባዎች ውስጥ ይስበኩ።

፲፩ ጌታም እንዲህ ይላል፣ [ሀ]በፅድቅም ስራዬን በአጭር እቆርጣለሁ፣ ድል ለመንሣት ፍርድን የማመጣበት ቀን ይመጣልና።

፲፪ አገልጋዬ ላይመን ዋይትም ይጠንቀቅ፣ ሰይጣን እንደ [ሀ]ገለባ ሊያበጥረው ይፈልጋልና።

፲፫ እናም እነሆ፣ [ሀ]ታማኝ የሆነው እርሱ በብዙ ነገሮች ላይ ገዢ ይሆናልና።

፲፬ እና ደግሞም፣ እንዳትታለሉም ለሁሉም ነገሮች ንድፍን እሰጣችኋለሁ፤ ሰይጣን በምድር ላይ አለና፣ እና አገሮችን እያሳታቸውም ይሄዳል—

፲፭ ስለዚህ የሚጸልየው፣ መንፈሱ [ሀ]የተዋረደውም፣ [ለ]ስርዓቴን ካከበረ፣ እርሱም በእኔ ዘንድ [ሐ]ተቀባይነትን ያገኛል።

፲፮ መንፈሱ ትሁት፣ ቋንቋውም ቅንና የሚያንፅ የሆነው፣ የሚናገረውም፣ ስርዓቶቼን ቢያከብር፣ እርሱ ከእግዚአብሔር ነው።

፲፯ እና ደግሞም፣ በሀይሌ የሚንቀጠቀጠውም እርሱ [ሀ]ጠንካራ እንዲሆን ይደረጋል፣ እና በምሰጣችሁ ራዕዮች እና እውነቶች በኩልም የምስጋና እና [ለ]የጥበብ ፍሬዎችን ያመጣል።

፲፰ እና ደግሞም የተሸነፈውም እና በዚህም ንድፍ አማካይነት፣ ፍሬ [ሀ]የማያመጣውም ከእኔ አይደለም።

፲፱ ስለዚህ፣ ከሰማይ በታች ሁሉ በዚህ ንድፍ አማካይነት መናፍስትን በሁሉም ጉዳዮች [ሀ]ታውቃላችሁ።

፳ ቀኖቹም ቀርበዋል፤ ሰዎችም እንደ እምነታቸው [ሀ]ይከናወንላቸዋል።

፳፩ እነሆ፣ ይህ ትእዛዝ ለመረጥኳቸው ሽማግሌዎች ሁሉ የተሰጠው ነው።

፳፪ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ [ሀ]ቶማስ ቢ ማርሽ እና አገልጋዬ እዝራ ቴይርም ቃሉን በየመንገዳቸው እየሰበኩ ወደ እዚያ ምድር ደግመውም ይጓዙ።

፳፫ እና ደግሞም፣ አገልጋዬ አይዛክ ሞርሊ እና አገልጋዬ እዝራ ቡዝ፣ ቃሉን በዚያም ምድር እግረ መንገዳቸውን እየሰበኩ፣ ደግመው ይጓዙ።

፳፬ እና ደግሞም፣ አገልጋዮቼ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እና ማርቲን ሀሪስ ከአገልጋዮቼ ስድኒ ሪግደን እና ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ ጋር ይጓዙ።

፳፭ አገልጋዮቼ ዴቪድ ዊትመር እና ሀርቪ ውትሎክም፣ ደግመውም እግረ መንገዳቸውን እየሰበኩ ወደ እዚያው ምድር ይጓዙ።

፳፮ እናም አገልጋዮቼ [ሀ]ፓርሊ ፒ ፕራት እና [ለ]ኦርሰን ፕራትም፣ እግረ መንገዳቸውን፣ እንዲሁም ወደ እዚያው ምድር እየሰበኩ ይጓዙ።

፳፯ እናም አገልጋዮቼ ሰለሞን ሀንኮክ እና ሰሚየን ካርተርም ወደ እዚያ ምድርም ደግመውም ይጓዙ፣ እናም እግረ መንገዳቸውን ይስበኩ።

፳፰ አገልጋዮቼ ኤድሰን ፉለር እና ጄከብ ስኮትም እንዲሁ ይጓዙ።

፳፱ አገልጋዮቼ ሊቫይ ደብሊው ሀንኮክ እና ዘበዲ ኮልትርንም እንዲሁ ይጓዙ።

፲ ሀ ማር. ፮፥፯፤
ት. እና ቃ. ፷፩፥፴፭።
ለ ዮሐ. ፩፥፳፮።
ሐ የሐዋ. ፰፥፲፬–፲፯።
፲፩ ሀ ሮሜ ፱፥፳፰።
፲፪ ሀ ሉቃ. ፳፪፥፴፩፤
፫ ኔፊ ፲፰፥፲፯–፲፰።
፲፫ ሀ ማቴ. ፳፭፥፳፫፤
ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፶፫።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ሐ ት. እና ቃ. ፺፯፥፰።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፷፮፥፰፤
፻፴፫፥፶፰።
ለ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፲፰ ሀ ማቴ. ፫፥፲።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፳ ሀ ማቴ. ፰፥፭–፲፫።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥፭።
ቅ.መ.መ. ማርሽ፣ ቶማስ ቢ።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣
ኤድዋርድ።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ፕራት፣
ፓርሊ ፓርከር።
ለ ቅ.መ.መ. ፕራት፣ ኦርሰን።

፴ አገልጋዮቼ ሬኖልድዝ ካሁን እና ሳሙኤል ኤች ስሚዝም እንዲሁ ይጓዙ።

፴፩ አገልጋዮቼ ዊለር ቦልድውን እና ውልያም ካርተርም እንዲሁ ይጓዙ።

፴፪ እናም አገልጋዮቼ [ሀ]ኑወል ናይት እና ሴላ ጄ ግርፍንም ይሾሙ፣ እናም እንዲሁ ይጓዙ።

፴፫ አዎን፣ እውነት እላለሁ፣ እነዚህ ሁሉ ወደ አንድ ስፍራ በተለያዩ መንገዶቻቸው ይጓዙ እናም አንድ በሌላው ሰው [ሀ]መሰረት ላይ አያንጽም፣ ወይም በሌላ ሰውም መንገድ አይጓዝም።

፴፬ ታማኝ የሆነው፣ እርሱ ይጠበቃል እና ብዙ [ሀ]ፍሬ በማፍራትም ይባረካል።

፴፭ እና ደግሞም፣ እንዲህ እላችኋለሁ፣ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ዌክፊልድና ሰለሞን ሀምፍሪ ወደ ምስራቅ አገሮች ይጓዙ፤

፴፮ ትንቢቶቹ እንዲሚሉ፣ [ሀ]ካዩት እና ከሰሙት እናም በእርግጥ [ለ]ከሚያምኑት፣ ከነቢያትና ከሐዋርያት በቀር ምንም ነገሮችን [ሐ]ሳያውጁ፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋርም ያገልግሉ።

፴፯ በኃጢአት ምክንያትም፣ ለሂምን በሰት የተሰጠውም [ሀ]ይወሰድበት፣ እናም ለሳይመንድስ ራይደር ይሰጥ።

፴፰ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ጃርድ ካርተር እንደ ካህን [ሀ]ይሾም፣ ጆርጅ ጄምስም እንዲሁ እንደ [ለ]ካህን ይሾም።

፴፱ የሚቀሩት ሽማግሌዎችም ቤተክርስቲያኖችን [ሀ]ይጠብቁ፣ እና በአካባቢያቸውም ቃሉን ያውጁ፤ እናም [ለ]የጣኦት አምላኮም እንዳይኖር እና ጥፋት እንዳይሰራም በገዛ እጆቻቸው ይስሩ።

፵ እናም በሁሉም ነገሮችም [ሀ]ድሀውን እና [ለ]ችግረኛውን፣ የታመመውን እና የተሰቃየውን አስታውሱ፣ ይህን የማያደርግም፣ እርሱ ደቀ መዝሙሬ አይደለምና።

፵፩ እና ደግሞም፣ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እና ስድኒ ሪግደን እና ኤድዋርድ ፓርትሪጅ ከቤተክርስቲያኗ [ሀ]ማስተዋወቂያ ይውሰዱ። እና አንድ ደግሞ ለአገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ይሰጠው።

፵፪ እና በዚህም፣ እንዲሁም እንዳልኩት፣ ታማኝ ከሆናችሁ፣ [ሀ]የውርሳችሁ ምድር በሆነው፣ እና አሁንም የጠላቶቻችሁ ምድር በሆነው፣ [ለ]በሚዙሪ ምድር ለመደሰት ራሳችሁን ትሰበሰባላችሁ።

፵፫ ነገር ግን፣ እነሆ፣ እኔ ጌታ ከተማውን በጊዜው አፈጥነዋለሁ፣ እና ታማኝ የሆነውንም [ሀ]በደስታ እና በሀሴት አነግሰዋለሁ።

፵፬ እነሆ፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፣ እናም በኋለኛው ቀን [ሀ]አነሳቸዋለሁ። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፶፫

በሰኔ ፰፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለአልጀርኖን ስድኒ ጊልበርት የተሰጠ ራዕይ። በስድኒ ጊልበርት ጥያቄ ምክንያት፣ ነቢዩ ስለወንድም ጊልበርት የቤተክርስቲያን ስራና ሀላፊነት ጌታን ጠየቀ።

፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥፮–፯።
፴፫ ሀ ሮሜ ፲፭፥፳።
፴፬ ሀ ዮሐ. ፲፭፥፲፮፤
ት. እና ቃ. ፲፰፥፲፭–፲፮።
፴፮ ሀ ዮሐ. ፫፥፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ሐ ሞዛያ ፲፰፥፲፱–፳፤
ት. እና ቃ. ፶፪፥፱።
፴፯ ሀ ማቴ. ፳፭፥፳፭–፴።
፴፰ ሀ ት. እና ቃ. ፸፱፥፩።
ለ ቅ.መ.መ. ካህን፣
የአሮናዊ ክህነት።
፴፱ ሀ አልማ ፮፥፩።
ለ ቅ.መ.መ. ጣኦት አምላኪ።
፵ ሀ ት. እና ቃ. ፻፬፥፲፭–፲፰።
ቅ.መ.መ. ደሀ።
ለ ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።
፵፩ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፷፬።
፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፰፥፱፤
፶፯፥፩–፫።
ለ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፵፬ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፯–፺፰።

፩–፫፣ የስድኒ ጊልበርት የቤተክርስቲያን ጥሪ እና ምርጫ እንደ ሽማግሌ እንዲሾም ነው፤ ፬–፯፣ እርሱም እንደ ኤጲስ ቆጶስ ወኪል እንዲያገለግልም ነው።

፩ እነሆ፣ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት፣ እንዲህ እልሀለሁ፣ ጸሎቶችህን ሰምቼአለሁ፤ እኔ ጌታ በኋለኛው ቀናት ባነሳኋት በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለህን ጥሪና [ሀ]ምርጫ እውቀት ይሰጥህ ዘንድ እኔ፣ ጌታ አምላክህን፣ ጠይቀሀል።

፪ እነሆ፣ ለአለም ኃጢአት [ሀ]የተሰቀልኩ እኔ ጌታ አለምን [ለ]እንድትተው ትእዛዝን እሰጥሀለሁ።

፫ በቃሌ በኩል፣ እምነትን እና ንስሀ መግባትን እና ለኃጢአቶች [ሀ]ስርየት እና [ለ]እጆችን በመጫን መንፈስ ቅዱስን መቀበልን ለመስበክ፣ የሽማግሌነት ሹመቴን በራስህ ላይ ተቀበል፤

፬ እናም ከዚህ በኋላ በሚሰጠው ትእዛዝ፣ ኤጲስ ቆጶሱ በሚመድብበት ስፍራም ለዚህች ቤተክርስቲያን [ሀ]ወኪል እንድትሆንም ነው።

፭ እና ደግሞም፣ በእውነት እልሀለሁ፣ ከአገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እና ከስድኒ ሪግደን ጋር ተጓዝ።

፮ እነሆ፣ እነዚህም የምትቀበላቸው የመጀመሪያ ስነ ስርዓቶች ናቸው፤ እና በወይን ስፍራዬ ውስጥ ባገለገልክ መጠን፣ ቅሪቶቹም በሚመጣው ጊዜ ይገለጣሉ።

፯ እና ደግሞም፣ እስከ ፍጻሜው [ሀ]የሚጸና እርሱ ብቻ እንደሚድን እንድትማርም እፈልጋለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፺፬

በሰኔ ፲፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለኑወል ናይት የተሰጠ ራዕይ። በቶምሰን ኦሀዮ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት የቤተክርስቲያኗ አባላት ስለ ንብረት መቀደስ ጉዳዮች አልተስማሙም ነበር። እራስን መውደድና ስግብግብነትም ይታዩ ነበር። ወደ ሼክርስ ሄዶበት ከነበረው ሚስዮን በኋላ (ክፍል ፵፱ መግቢያን ተመልከቱ)፣ ሊመን ኮፕሊም ትልቅ የእርሻ ስፍራውን ከኮልዝቪል ኒው ዮርክ ለሚመጡ ቅዱሳን በውርስ ለመባረክ የገባውን ቃል ሰብሮ ነበር። በዚህ ምክንያትም፣ (በቶምሰን ውስጥ የሚኖሩ አባላት መሪ) ኑወል ናይት እና ሌሎች ሽማግሌዎች ምን ማድረግ እንደሚችሉ ለመጠየቅ ነቢዩ ዘንድ መጥተው ነበር። ነቢዩም ጌታን ጠይቀ እናም በቶምሰን የሚኖሩትን አባላት ከሊመን ኮፕሊ እርሻ እንዲወጡ እና ወደ ምዙሪ እንዲጓዘ መመሪያ የሚሰጠውን ይህን ራዕይ ተቀበለ።

፩–፮፣ ምህረት ለማግኘት ቅዱሳን የወንጌሉን ቃል ኪዳን መጠበቅ አለባቸው፤ ፯–፲፣ በስቃይም ትዕግስተኛ መሆን አለባቸው።

፩ እነሆ፣ ጌታ፣ እንዲሁም [ሀ]አልፋና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፣ እንዲሁም ለአለም ኃጢአት [ለ]የተሰቀለው እንዲህ ይላል—

፪ እነሆ፣ በእውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣

፺፫ ፩ሀ ቅ.መ.መ. መመረጥ፤
መጠራት እና መመረጥ፤
ምርጦች።
፪ሀ ቅ.መ.መ. መሰቀል።
ለ ቅ.መ.መ. አለማዊነት፤
አለም።
፫ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ለ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥ ፮፣ ፰–፲፣ ፲፬–፲፭፤ ፹፬፥ ፪፻፫።
፯ሀ ቅ.መ.መ. መፅናት።
፺፬ ፩ሀ ራዕ. ፩፥ ፰፤
ት. እና ቃ. ፲፱፥ ፩።
ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
ለ ቅ.መ.መ. መሰቀል።

አገልጋዬ ኑወል ናይት፣ በሾምኩህ ስልጣን ውስጥ ጸንተህ ቁም።

፫ እና ወንድሞችህ ጠላቶቻቸውን ለማምለጥ ፈቃድ ካላቸው፣ ለኃጢአቶቻቸው ሁሉ ንስሀ ይግቡ፣ እና በፊቴም በእውነት [ሀ]ትሁት እና የተዋረዱ ይሁኑ።

፬ እናም ለእኔ የገቡት [ሀ]ቃል ኪዳን ስለተሰበረ፣ ይህም [ለ]ከንቱ ሆኗል እናም ተሽሮአልም።

፭ እናም በእርሱ ጠንቅ [ሀ]ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት፣ ወደ ጥልቅም ባሕር መስጠም ይሻለው ነበርና።

፮ ቃል ኪዳንን የሚያከብሩት እና ትእዛዝን የሚከተሉት ግን የተባረኩ ናቸው፣ እነርሱም [ሀ]ምህረትን ያገኛሉና።

፯ ስለዚህ፣ ጠላቶቻችሁ እንዳይመጡባችሁ አሁን ሂዱ፣ ከአገሩም ሽሹ፤ እናም ተጓዙ፣ እና መሪያችሁ እና ገንዘቦችን እንዲከፍልላችሁ የምትሹትን ምረጡ።

፰ እንደዚሁም ወደ ምዕራብ ክፍለ ሀገሮች፣ ወደ [ሀ]ሚዙሪ ምድር፣ ወደ ላማናውያን ድንበርም ተጓዙ።

፱ ጉዟችሁን ከጨረሳችሁ በኋላም፣ እነሆ እንዲህ እላችኋለሁ፣ ስፍራን እስካዘጋጅላችሁ ድረስ፣ እንደ ሰዎች [ሀ]የምትኖሩበትን ፈልጉ።

፲ እና ደግሞም፣ [ሀ]እስክመጣ ድረስ በስቃይም [ለ]ትዕግስተኛ ሁኑ፤ እናም፣ እነሆ፣ በቶሎም እመጣለሁ፣ እና ደመወዜ ከእኔ ጋር ነው፣ እናም እኔን ተግተው [ሐ]የሚሹኝም ለነፍሳቸው [መ]እረፍትን ያገኛሉ። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፶፭

በሰኔ ፲፬፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለውልያም ደብሊው ፈልፕስ የተሰጠ ራዕይ። አታሚው ውልያም ደብሊው ፈልፕስ እና ቤተሰቡ ከርትላንድ ውስጥ ገና ደርሰው ነበር፣ እና ነቢዩም ስለ እርሱ ጉዳይ ጌታ መረጃ እንዲሰጠው ፈልጎ ነበር።

፩–፫፣ ውልያም ደብሊው ፈልፕስ እንዲጠመቅ፣ እንደ ሽማግሌ እንዲሾም፣ እና ወንጌሉን እንዲሰብክ ተጠርቷል እናም ተመርጧል፤ ፬፣ በቤተክርስቲያኗ ትምህርት ቤት ውስጥ ላሉትም ልጆች መጻህፍትንም እንዲጽፍ ነው፤ ፭–፮፣ የስራው አካባቢ ወደ ሆነው፣ ወደ ሚዙሪም ይጓዝ።

፩ እነሆ፣ ጌታ፣ አዎን፣ እንዲሁም [ሀ]የአለም ሁሉ ጌታ፣ ለአንተ ለአገልጋዬ ውልያም እንዲህ ይላልህ፣ ተጠርተሀል እናም ተመርጠሀል፤ እና በውሀ [ለ]ከተጠመቅህ በኋላ፣ ሙሉ አይንህን ወደ እግዚአብሔር ክብር በማድረግ ይህንንም ካላደረግህ፣ ለኃጢአቶችህ ስርየትን ታገኛለህ እና [ሐ]እጅንም በመጫን መንፈስ ቅዱስን ትቀበላለህ፤

፪ እና ከዚያም በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ እጅ፣ በህያው እግዚአብሔር ልጅ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጠመቅ ንስሀን እና የኃጢአት [ሀ]ስርየትን ለመስበክ

፫ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴–፴፱። ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
ለ ት. እና ቃ. ፶፰፥፴፪–፴፫።
፭ሀ ማቴ. ፲፰፥፮–፯።
፮ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፰ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥፵፪።
፱ሀ ፩ ተሰ. ፬፥፲፩።
፲ሀ ራዕ. ፳፪፥፲፪። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ሐ ምሳ. ፰፥፲፯። ቅ.መ.መ. ጸሎት።
መ ማቴ. ፲፩፥፳፰–፴። ቅ.መ.መ. እረፍት።
፶፭ ፩ሀ ዘዳግ. ፲፥፲፬፤ ፩ ኔፊ ፲፩፥፮፤ ፪ ኔፊ ፳፱፥፯።
ለ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
ሐ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
፪ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።

በዚህ ቤተክርስቲያን ሽማግሌ እንድትሆን ትሾማለህ።

፫ እና በማንም ላይ እጆችህን ስትጭን፣ በፊቴ የተዋረዱ ከሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስን የመስጠት ሀይል ይኖርሀል።

፬ እና ዳግም፣ ለቤተክርስቲያኗ ትምህርት ቤቶች [ሀ]መጻህፍትን በማተም በመምረጥ እና በመጻፍ አገልጋዬን ኦሊቨር ካውድሪን በስራው እንድትረዳው፣ በዚህም እንደሚያስደስተኝ ህጻናት ልጆች በፊት ለፊቴ መመሪያን እንዲቀበሉ ታደርግ ዘንድ ትሾማለህ።

፭ እና ዳግም፣ በእውነት እልሀለሁ፣ ለዚህም ምክንያት፣ ይህን ስራ ለማከናወን በምትወርስበት ምድር በዚያ [ሀ]ጸንተህ ትቆይ ዘንድ ከአገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ እና ስድኒ ሪግደን ጋር ትጓዛለህ።

፮ እና ዳግም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ኮ ከእነርሱ ጋር ይጓዝ። እንዲሁም፣ እንደ ፈቃዴም፣ የሚቀረው ከዚህ በኋላ ይገለጻል። አሜን።

ክፍል ፶፮

በሰኔ ፲፭፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ይህም ራዕይ በሚኖርበት በፍሪድሪክ ጂ ዊልያምስ እርሻ ላይ ስላለው ሀላፊነት በተመለከተ ጆሴፍ ስሚዝ ለእርሱ የተቀበለለትን የቀድሞውን ራዕይ (በቁጥር ፰ "ትእዛዝ" ተብሎ የተጠቀሰው) ባለማክበሩ እዝራ ቴይርን ይገስጻል። የሚቀጥለው ራዕይ ደግሞም ከቶማስ ቢ ማርሽ ጋር ወደ ሚዙሪ እንዲጓዝ የተጠራበትን ይሰርዛል (ክፍል ፶፪፥፳፪ ተመልከቱ)።

፩–፪፣ ደህንነትን ለማግኘት ቅዱሳን መስቀሉን መሸከም እና ጌታን መከተል አለባቸው፤ ፫–፲፫፣ ጌታ ያዛል እናም ይሽራል፣ እና የማይታዘዙትም ይጣላሉ፤ ፲፬–፲፯፣ ድሀውን ለማይረዳው ባለጠጋም ወዮለት፣ እና ልባቸው ላልተሰበሩ ድሆችም ወዮላቸው፤ ፲፰–፳፣ በልባቸው ንጹሀን የሆኑ ድሆች ብፁዓን ናቸው፣ ምድርን ይወርሳሉና።

፩ በስሜ [ሀ]የምትታወቁ ህዝቤ ሆይ፣ አድምጡ ይላል ጌታ አምላካችሁ፤ እነሆ ቁጣዬ በአማጸኞች ላይ ነዷል፣ እናም በአህዛብ ላይ በሚመጣው [ለ]የጉብኝት እና የመዓት ቀን፣ ክንዴን እና ቁጣዬን ያውቃሉ።

፪ [ሀ]መስቀሉን አንስቶ [ለ]የማይከተለኝ፣ እና ትእዛዛቴን የማያከብረው፣ እርሱ አይድንም።

፫ እነሆ፣ እኔ ጌታ አዛለሁ፤ እና ትእዛዝን ሰጥቼ እና ትእዛዜም [ሀ]ከተሰበረ በኋላም የማይታዘዘውም በራሴ ጊዜ [ለ]ይቆረጣል።

፬ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ መልካምም እንደመሰለኝ አዝዛለሁ [ሀ]እሽራለሁም፤ እናም፣ ጌታ እንዲህ ይላል፣ ይህም ሁሉ [ለ]በሚያምጹት ራስ ላይ ይመለስላቸዋል።

፭ ስለዚህ፣ ለአገልጋዮቼ [ሀ]ቶማስ ቢ. ማርሽ እና እዝራ ቴይር የሰጠሁትን ትእዛዝ እሽራለሁ፣ እና ለአገልጋዬ ቶማስ ወደ ሚዙሪ አገር ፈጥኖ እንዲጓዝም አዲስ ትእዛዝን ሰጥቼዋለሁ፣ እና አገልጋዬ ሴላ ጄ ግርፍን አብሮት ይሄዳል።

፮ ምክንያቱም እነሆ፣ ቶምሰን ውስጥ

፬ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፰፤ ፻፱፥፯፣ ፲፬።
፭ሀ ዓሞ. ፱፥፲፭።
፶፮ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፵፩፥፩።
ለ ኢሳ. ፲፥፫–፬፤ ሞር. ፱፥፪፤ ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬፤ ፻፳፬፥፲።
፪ሀ ሉቃ. ፲፬፥፳፯።
ለ ፩ ጴጥ. ፪፥፳፩፤ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲–፲፫፤ ሞሮኒ ፯፥፲፩። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፲፬–፲፮፤ ፶፥፰።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፴፩–፴፫።
ለ ቅ.መ.መ. አመጽ።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ማርሽ፣ ቶማስ ቢ።

ባሉት ህዝቤ አንገተ ደንዳናነት እና በእነርሱ አመጽ ምክንያት ለአገልጋዮቼ ሴላጂ ግርፍን እና ኒውል ናይት የሰጠኋቸውን ትእዛዝ እሽራለሁ።

፯ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ኒውል ናይት ከእነርሱ ጋር ይቆይ፤ እና በፊቴ የሚጸጸቱ እና ወደ መረጥኩት ምድር በእርሱ ተመርተው የሚሄዱት ሁሉም ይሂዱ።

፰ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ እዝራ ቴይር [ሀ]ለኩራቱ እና ራሱን ለመውደዱ ንስሀ መግባት፣ እናም ስለሚኖርበት ስፍራ በፊት የሰጠሁትን ትእዛዝ ማክበር አለበት።

፱ እና ይህን ቢያደርግ፣ በምድሩም ላይ መከፋፈል ስለማይኖር፣ ወደ ሚዙሪ አገር እንዲሄድም ይመረጣል፤

፲ አለበለዚያም፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ የከፈለውን ገንዘብ ይቀበላል፣ እናም ከስፍራው ይሄዳ፣ ከቤተክርስቲያኔም [ሀ]ይቆረጣል፤

፲፩ እና ምንም እንኳን ሰማይ እና ምድር ቢያልፉም፣ እነዚህ ቃላት [ሀ]አያልፉም፣ ነገር ግን ሁሉም ይፈጸማሉ።

፲፪ እናም አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊም ገንዘቡን መክፈል ቢኖርበትም፣ እነሆ፣ እኔ ጌታ መልሼ በሚዙሪ አገር ውስጥ እከፍለዋለሁ፣ እና እርሱ የሚቀበላቸውም ባደረጉት መጠን ደግመው ዋጋቸውን ይቀበላሉ፤

፲፫ በውርስ መሬቶቻቸውም እንኳ ቢሆን ባደረጉት መጠን ይቀበላሉ።

፲፬ እነሆ፣ ጌታ ለህዝቤ እንዲህ ይላል— እናንተ ብዙ የምታደርጉት እና ንስሀ የምትገቡባቸው ነገሮች አሉአችሁ፤ እነሆ፣ ኃጢአቶቻችሁ ወደ እኔ መጥተዋል፣ እና ይቅርታም አልተሰጣቸውምና፣ ምክንያቱም በገዛ መንገዳችሁ [ሀ]ምክርን ስለምትሹ ነው።

፲፭ እናም ልባችሁም አልረኩም። እናም እውነትን አታከብሩም፣ ነገር ግን ፅድቅ ባልሆነው [ሀ]ትደሰታላችሁ።

፲፮ ንብረታችሁን [ሀ]ለድሆች [ለ]የማትሰጡ እናንት [ሐ]ባለጠጎች ወዮላችሁ፣ [መ]ሀብቶቻችሁም ነፍሳችሁንያዝላሉና፤ እና በጉብኝት እና በፍርድ እና በቁጣም ቀንም ለቅሶአችሁ ይህ ይሆናል፥ [ሠ]የአዝመራ ወቅት አለፈ፣ በጋም አለቀ፣ እና ነፍሴም አልዳነም!

፲፯ ልባችሁ ያልተሰበሩ፣ መንፈሶቻችሁም ያልተዋረዱ፣ እና ሆዳችሁ ያልሞላና፣ የሌሎች ሰዎች ንብረቶችን ከመያዝ እጆቻችሁን ያላቆማችሁ፣ አይኖቻችሁ [ሀ]በስግብግብነት የተሞላና፣ በእጆቻችሁ የማትሰሩ [ለ]ድሀ ሰዎችም ወዮላችሁ!

፲፰ ነገር ግን ልባቸው ንጹህ የሆኑ፣ ልቦቻቸው [ሀ]የተሰበሩ፣ እና መንፈሶቻቸው የተጸጸቱ [ለ]ድሆች ግን ብፁዓን ናቸው፣ ምክንያቱም ለደህንነታቸው የእግዚአብሔር [ሐ]መንግስት በሀይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ ይመለከታሉና፤ [መ]የምድርም ስብ ለእነርሱ ይሆናልና።

፲፱ እነሆ፣ ጌታ ይመጣል፣ እናም [ሀ]ሽልማቱም ከእርሱ ጋር ይሆናል፣ እና ለእያንዳንዱን ሰውም ዋጋውን ይሰጠዋል፣ እና ድሀውም ይደሰታልና፤

፳ ትውልዶቻቸውም ምድርን ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ድረስ [ሀ]ይወርሳሉ። እና አሁን የምነግራችሁን እፈፅማለሁ። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፲፩ ሀ ፪ ኔፊ ፱፥፲፯።
፲፬ ሀ ያዕቆ. ፬፥፲።
፲፭ ሀ አልማ ፵፩፥፲፤
፫ ኔፊ ፳፯፥፲፩።
፲፮ ሀ ምሳ. ፲፬፥፴፩፤
አልማ ፭፥፶፭–፶፮።
ቅ.መ.መ. ደሀ።
ለ ቅ.መ.መ. ምፅዋት፣
የምፅዋት ስጦታ።
ሐ ኤር. ፲፯፥፲፩፤
፪ ኔፊ ፱፥፴።
መ ያዕ. ፭፥፫።
ሠ ኤር. ፰፥፳፤
አልማ ፴፬፥፴፫–፴፭፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፪።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. መመኘት።
ለ ሞዛያ ፬፥፳፬–፳፯፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፵፪፤
፷፰፥፴–፴፪።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ለ ማቴ. ፭፥፫፤ ፰፤
ሉቃ. ፮፥፳፤ ፫ ኔፊ ፲፪፥፫።
ቅ.መ.መ. ደሀ።
ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
መ ቅ.መ.መ. ምድር።
፲፱ ሀ ራዕ. ፳፪፥፲፪፤
ት. እና ቃ. ፩፥፲።
፳ ሀ ማቴ. ፭፥፭፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፮–፶፰።

ክፍል ፶፯

በሀምሌ ፳፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በፅዮን፣ በጃክሰን የአገዛዝ ክፍል ሚዙሪ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። "የውርሳችሁን ምድር" ወደሚገልጽበት ምዙሪ እንዲሄዱ ጌታ ያዘዘውን በመከተል (ክፍል ፶፪)፣ ሽማግሌዎች ከኦሀዮ ወደ ሚዙሪ ምዕራባዊ ድንበር ተጉዘዋል። ጆሴፍ ስሚዝ ስለላማናውያን ጉዳይ በማሰብ፣ ነቢዩ እንዲህ አለ፥ "ምድረበዳው እንደ ጽጌረዳ የሚያብበው መቼ ነው? ፅዮን በክብሯ የምትገነባውስ መቼ ነው፣ እና በኋለኛው ቀናት ሁሉም አገሮች የሚመጡበት ቤተመቅደስህ የት ነው የሚቆመው?" ከዚህ በኋላም ይህን ራዕይ ተቀበለ።

፩–፫፣ ኢንዲፔንደንስ ሚዙሪ የፅዮን ከተማ እና የቤተመቅደስ ስፍራ ነው፤ ፬–፯፣ ቅዱሳንም መሬቶችን ይግዙ እና በዚያም አካባቢ ውርሶችን ይቀበላሉ፤ ፰–፲፮፣ ስድኒ ጊልበርት ግምጃ ቤትን ያቋቁም፣ ዊልያም ደብሊው ፈልፕስ አሳታሚ ይሁን፤ እና ኦሊቨር ካውድሪም የሚታተሙትን ፅሁፎች ያርም።

፩ ለቅዱሳኑ መሰብሰቢያ የመደብኩት እና [ሀ]በቀደስኩት በዚህ [ለ]በሚዙሪ [ሐ]ምድር ውስጥ በትእዛዜ አማካይነት [መ]የተሰበሰባችሁ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ አድምጡ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፪ ስለዚህ፣ ይህም የቃል ኪዳን ምድር፣ እና [ሀ]ለፅዮን ከተማ [ለ]ስፍራም ነው።

፫ እና ጌታ አምላካችሁ እንዲህ ይላል፣ ጥበብን የምትቀበሉ ከሆነ እነሆ ጥበብም። እነሆ፣ አሁን ኢንዲፔንደንስ ተብሎ የሚጠራው አማካዩ ስፍራ ነው፤ እናም [ሀ]የቤተመቅደሱ ስፍራ ከፍርድ ቤቱ ሳይርቅ፣ ወደ ምዕራብ የሚገኘው ነው።

፬ ስለዚህ፣ ይህ ምድር፣ እናም ከዚያ ወደ ምዕራብ ያሉትም መሬቶች፣ እንዲሁም [ሀ]በአይሁድና በአህዛብ መካከል እስከሚሄደው መስመር ያሉትን መሬቶች በቅዱሳኑ [ለ]መገዛታቸው ጥበብ ነው፤

፭ እና ደቀ መዛሙርቶቼ ምድርን [ሀ]ለመግዛት እስከቻሉም ድረስ፣ የሳር መስክ ድንበር ላይ ያሉትን መሬቶች እንዲሁ ጥበብ ነው። እነሆ፣ ይህን ለዘለአለም ውርስ [ለ]ማግኘታቸው ጥበብ ነው።

፮ እና አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርትም፣ በፅድቅ ለመደረግ እስከተከናወነ ድረስ እና ጥበብም እንደመራው መጠን፣ ገንዘብን ለመቀበል፣ ለቤተክርስቲያኗ [ሀ]ወኪል በመሆን፣ በአካባቢዎችም ሁሉ መሬቶችን ለመግዛት በሾምኩት ሀላፊነት ይቁም።

፯ እናም አገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅም በሰጠሁት ሀላፊነት ይቁም፣ እና በትእዛዜም አማካይነት ለቅዱሳኑ ውርሳቸውን [ለ]ያካፍል፤ እናም እንዲረዱት የመረጣቸውም ይህን ያድርጉ።

፰ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት እራሱን በዚህ ስፍራ ያቋቁም፣ እናም ያለማታለል እቃዎችን በመሸጥ ምድርን ለቅዱሳኑ እርዳታ ለመግዛት እና ደቀ መዛሙርትን በሚወር

፶፯ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፷፩፥ ፲፯።
ለ ት. እና ቃ. ፶፪፥ ፵፪።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፯–፰፤ ፵፭፥ ፷፬–፸፩።
መ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፳፰፥ ፱፤ ፵፪፥ ፱፣ ፷፪።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፶፯፤ ፺፯፥ ፲፭–፲፯።
፬ሀ በዚህም ይሁዳ ስለ ማለት ላማናውያን የሚጠቅስ፣ አህዛብ ስለ ነጭ ሰፋሪዎች የሚጠቅስ ነው።
ለ ት. እና ቃ. ፷፫፥ ፬።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፵፱፣ ፶፩፤ ፻፩፥ ፸–፸፬።
ለ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፵፬።
፮ሀ ት. እና ቃ. ፶፫።
፯ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፳፬። ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣ ኤድዋርድ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፩፥ ፱–፲፩፤ ፶፰፥ ፲፬–፲፰።

ሱበት ስፍራ ላይ እንዲቋቋሙ የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ነገሮች ለማግኘት የሚያስችሏቸውን ገንዘብ ለማግኘትም የግምጃ ቤትን ይመስርት።

፱ እናም በእርሱ እንደ ጸሀፊ ከተቀጠሩት ሰዎች ማናቸውም በኩል ለህዝቡ እቃዎች ለመላክ እንዲችል፣ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት ፈቃድ ያግኝ—እነሆ ይህ ጥበብ ነው፣ እና ማንም የሚያነበው ቢኖር ይረዳው፤

፲ እናም [ሀ]በጭለማ እና በሞት አካባቢ እና [ለ]ጥላ ውስጥ ላሉት ወንጌሌም እንዲሰበክ፣ እንደዚህም ቅዱሳኔን ያስተዳድራቸው።

፲፩ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ [ሀ]ውልያም ደብሊው ፊልፕስ በዚህ ስፍራ ላይ ይስፈር፣ እናም ለቤተ ክርስቲያኑም አንድ [ለ]አሳታሚ ሰው ይመስረት።

፲፪ እናም እነሆ፣ አለምም ፅሁፉን ከተቀበሉ—እነሆ ጥበብም እነሆ—ለቅዱሳኑ ጥቅም፣ ምንም የሚያገኘውን በፅድቅ ያግኝ።

፲፫ እናም አገልጋዬ [ሀ]ኦሊቨር ካውድሪ፣ በምመድብለት በማንኛውም ስፍራ፣ መንፈሱም በእርሱ በኩል ይህን ስለሚሰጥ፣ ሁሉም ነገሮች በፊቴ ትክክል እንዲሆኑ ፅሑፍ በመገልበጥ፣ በማስተካከል፣ እና በመምረጥ እንዳዘዝኩት እርሱን ይርዳው።

፲፬ እናም የተናገርኩባቸውም ሰዎች ሁሉ፣ በሚቻለው ፍጥነት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ነገሮችን እንደተናገርኳቸው ለማከናወን በፅዮን ምድር ውስጥ ይመስረቱ።

፲፭ እና አሁን ስለ መሰብሰቡ ጉዳይ—ኤጲስ ቆጶሱና ወኪሉ ወደዚህ ምድር እንዲመጡ ለታዘዙት ቤተሰቦች በሚቻልበት በኩል ወዲያውም ይዘጋጁ፣ እናም በሚወርሱበትም ስፍራ ይትከሉ።

፲፮ እናም ለሚቀሩትም ሽማግሌዎች እና አባላትም ሌሎች መረጃዎች ከዚህ በኋላ ይሰጣቸዋል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፶፰

በነሀሴ ፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በፅዮን ጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩና አብረውት የተጓዙት በጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ ውስጥ ከገቡ በኋላ በመጀመሪያው ሰንበት፣ የሀይማኖት ስብሰባ ነበር እና ሁለት አባላትም ተጠምቀው ነበር። በዚያ ሳምንትም፣ ከቶምሰን ቅርንጫፍ የመጡት የኮልዝቪል ቅዱሳን እና ሌሎችም በስፍራው ደረሱ (ክፍል ፶፬ን ተመልከቱ)። በዚህ አዲስ መሰብሰቢያ ስፍራ ውስጥ ጌታ ስለነሱ ምን ፈቃድ እንዳለው ለማወቅ ብዙዎቹ ጓጉተው ነበር።

፩–፭፣ በስቃይ የሚጸኑ በክብር ይነገሳሉ፤ ፮–፲፪፣ ቅዱሳኑ ለበጉ ጋብቻ እና ለጌታ እራት ይዘጋጁ፤ ፲፫–፲፰፣ ኤጲስ ቆጶሳት በእስራኤል ውስጥ ፈራጆች ናቸው፤ ፲፱–፳፫፣ ቅዱሳን የአገርን ህግጋት ያክብሩ፣ ፳፬–፳፱፣ ሰዎች ነጻ ምርጫቸውን መልካምን ለማድረግ ይጠቀሙበት፤ ፴–፴፫፣ ጌታ ያዛል ይሽራልም፣ ፴፬–፵፫፣ ንስሀ ለመግባት፣ ሰዎች ኃጢአቶቻቸውን መናዘዝና መተው አለባቸው፤ ፵፬–፶፰፣ ቅዱሳን ውርሳቸውን ገዝተው በሚዙሪ ይሰብሰቡ፤ ፶፱–፷፭፣ ወንጌሉ ለእያንዳንዱ ፍጥረት መሰበክ አለበት።

፲ ሀ ኢሳ. ፱፥፪፤ ማቴ. ፬፥፲፮። ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።

ለ መዝ. ፳፫፥፬።

፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ፊልፕስ፣ ውልያም ደብሊው።

ለ ት. እና ቃ. ፶፰፥፴፯፣ ፵–፵፩።

፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ካውደሪ፣ ኦልቨር።

፩ አድምጡ፣ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ እናም ቃሌንም ስሙ፣ እናም ስለራሳችሁ እና ስለላኳችሁ [ሀ]ስለዚህ አገር ያለኝን ፈቃድም ከእኔ ተማሩ።

፪ እውነት እላችኋለሁ፣ በህይወትም ይሁን [ሀ]በሞት ትእዛዜን [ለ]የሚጠብቅ የተባረከ ነው፤ እናም [ሐ]በመከራው [መ]ታማኝ የሆነው፣ እርሱ በመንግስተ ሰማይ ያለው ዋጋ ታላቅ ይሆናል።

፫ ከዚህ በኋላ ስለሚመጡት ነገሮች [ሀ]አምላካችሁ ያቀደውን፣ እናም ብዙ መከራን ተከትሎ የሚመጣውን [ለ]ክብር፣ በእዚህ ጊዜ በተፈጥሮ አይኖቻችሁ ልታዩ አትችሉም።

፬ ከብዙ [ሀ]መከራ በኋላ [ለ]በረከቶች ይመጣሉና። ስለዚህ በብዙ [ሐ]ክብር [መ]አክሊልም የምትጭኑበት ቀን ይመጣል፤ ሰአቱ አልደረሰም፣ ነገር ግን እየቀረበ ነው።

፭ በልባችሁ [ሀ]ልታሮሩት እና ቀጥሎ የሚመጣውን ትቀበሉ ዘንድ፣ ይህን አስቀድሜ የምነግራችሁን አስታውሱ።

፮ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለዚህ ምክንያት ነው የሰደድኳችሁ—ታዛዥ እንድትሆኑ፣ እና ወደፊት ስለሚመጡት ነገሮች [ሀ]ለመመስከር ልባችሁ [ለ]እንዲዘጋጁ፤

፯ ደግሞም የእግዚአብሔር [ሀ]ፅዮን ስለምትሰራበት ምድር መሰረቱን በመገንባት፣ እና ምስክርነቱንም በመስጠት ትከበሩ ዘንድ ነው፤

፰ እና ደግሞም የሶባ ግብዣ [ሀ]ለደሀው እንዲዘጋጅ፤ አዎን፣ የሶባ ግብዣ፣ [ለ]የሰነበተ ወይን እንዲዘጋጅ፣ ይህም አለም የነቢያት አንደበት እንደማይወድቁ እንዲያውቅ ነው፤

፱ አዎን፣ ሁሉም አገሮች የሚጋበዙበት በደንብ የተዘጋጀው የጌታ ቤት እራት የሆነው ይዘጋጅ ዘንድ ነው።

፲ መጀመሪያ፣ ባለጠጋውና የተማረው፣ ጥበበኛውና መሳፍንቱ፤

፲፩ እና ከዚያም በኋላ የሀይሌ ቀን ይመጣል፤ ከዚያም ደሀው፣ አንካሳው፣ እና አይነስውሩም፣ እና ደንቆሮውም ወደ በጉ [ሀ]ጋብቻ ይመጣሉ፣ እናም ለሚመጣው ታላቅ ቀን የተዘጋጀውን የጌታን [ለ]እራት ይበላሉ።

፲፪ እነሆ፣ እኔ ጌታ ይህን ተናግሬአለሁ።

፲፫ እና [ሀ]ምስክርም ከፅዮን፣ አዎን፣ ከእግዚአብሔር ቅርስ ከተማ አንደበት ይሄድ ዘንድ—

፲፬ አዎን፣ ለዚህ ምክንያት ነው ወደዚህ የሰደድኳችሁ፣ እና አገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅንም የመረጥኩት፣ እናም ተልዕኮውን በዚህ አገር ውስጥ የሰጠሁት።

፲፭ ነገር ግን ያለማመን እና ልበ ደንዳናነት ከሆኑት ኃጢአቶቹ ንስሀ ካልገባ፣ [ሀ]እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።

፲፮ እነሆ ይህ ተልዕኮው ለእርሱ ተሰጥቶታል፣ እናም ዳግመኛም አይሰጥም።

፲፯ በዚህ ተልዕኮ የሚቆመው፣ እንደቀደሙት ቀናት፣ በእስራኤል [ሀ]ፈራጅ እንዲሆን፣ የእግዚአብሔር ቅርስ መሬቶችን [ለ]ለልጆቹ እንዲያከፋፍል ተመድቧልና፤

፲፰ እናም የእርሱን ሕዝብ በእግዚአብሔር [ሀ]ነቢያት በኩል በተሰጡት የመንግስቱ ህግጋት አማካይነት በጻድቁ ምስክር፣ እናም በአማካሪዎቹ እርዳታም እንዲፈርድ ተመድቧል።

፶፰ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥ ፩–፰።
፪ሀ ፩ ጴጥ. ፬፥ ፮።
ለ ሞዛያ ፪፥ ፵፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
መ ፪ ተሰ. ፩፥ ፬።
፫ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ለ ቅ.መ.መ. ክብር።
፬ሀ መዝ. ፴፥ ፭፤ ት. እና ቃ. ፻፩፥ ፪–፯፤ ፻፫፥ ፲፩–፲፬፤ ፻፱፥ ፸፮።
ለ ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
ሐ ሮሜ ፰፥ ፲፯–፲፰፤ ት. እና ቃ. ፻፴፮፥ ፴፩።
መ ቅ.መ.መ. አክሊል፤ ከፍተኛነት።
፭ሀ ዘዳግ. ፲፩፥ ፲፰–፲፱።
፮ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
ለ ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፰።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ።
ለ ኢሳ. ፳፭፥ ፮።
፲፩ሀ ማቴ. ፳፪፥ ፩–፲፬፤ ራዕ. ፲፱፥ ፱፤ ት. እና ቃ. ፰፭፥ ፫።
ለ ሉቃ. ፲፬፥ ፲፮–፳፬።
፲፫ሀ ሚክ. ፬፥ ፪።
፲፬ሀ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣ ኤድዋርድ።
፲፭ሀ ፩ ቆሮ. ፲፥ ፲፪።
፲፯ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥ ፸፪–፸፬።
ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፲፰ሀ ቅ.መ.መ. ነቢይ።

፲፱ እውነት እላችኋለሁና፣ በዚህ አገር ህግጋቴ ይጠበቃል።

፳ ማንም ሰው መሪ ነኝ ብሎ አያስብ፤ ነገር ግን እንደ ፈቃዱ ምክር የሚፈርደውን፣ ወይም በሌላ ቃል፣ የሚመክር ወይም በፍርድ ወንበር የሚቀመጠው እግዚአብሔር እርሱ ይምራው።

፳፩ የአገርን ህግጋት ማንም ሰው አይጣስ፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን [ሀ]ህግጋትን የሚጠብቅ የአገርን ህግጋት መጣስ አያስፈልገውምና።

፳፪ ስለዚህ፣ ለመንገስ መብት ያለው እርሱ [ሀ]እስኪነግስ፣ እና ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስከሚያደርግ፣ ባሉት ባለስልጣናት ተገዙ።

፳፫ እነሆ፣ ከእጄ የተቀበላችኋቸው [ሀ]ህግጋት የቤተክርስቲያኗ ህግጋት ናቸው፣ እና በዚህም ብርሀን ያዙአቸው። እነሆ፣ ይህ ጥበብ ነው።

፳፬ እና አሁን ይህ አገር መኖሪያው ስለሆነው አገልጋዬ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እና አማካሪዎቹ አድርጎ ስለሾማቸውም፤ እናም [ሀ]ኀተራዬን እንዲጠብቅ ተሹሞ በዚህ አገር ስለሚኖረውም ስለእርሱ እናገራለሁ፤

፳፭ ስለዚህ፣ እርስ በራሳቸው እና ከእኔም ጋር እንደሚመክሩት፣ ቤተሰቦቻቸውን ወደዚህ አገር ያምጡ።

፳፮ እነሆ፣ በሁሉም ጉዳዮች ትእዛዝ መስጠቴ ተገቢ አይደለም፤ ምክንያቱም በሁሉም ነገር መገደድ ያለበት እርሱም [ሀ]ሰነፍ ነው እናም ብልህ አገልጋይ አይደለም፤ ስለዚህ ምንም ዋጋን አይቀበልም።

፳፯ እውነት እላችኋለሁ፣ ሰዎች መልካም ስራን [ሀ]በጉጉት ማከናወን፣ እናም ብዙ ነገሮችን በራሳቸው ነጻ ምርጫ ማድረግ፣ እናም ብዙ ጽድቅንም መስራት አለባቸው፤

፳፰ ሀይል በእነርሱ ውስጥ ነውና፣ በዚህም ራሳቸውን [ሀ]ይወክላሉ። እናም ሰዎች መልካም ስራን ከሰሩ ዋጋቸውን አያጡም።

፳፱ ነገር ግን እስኪታዘዝ ድረስ ምንም የማያደርግ፣ እና ትእዛዝን በሚጠራጠር ልብ የሚቀበል፣ እና በስንፍና የሚጠብቅ፣ እርሱ [ሀ]ይፈረድበታል።

፴ ሰውን [ሀ]የፈጠርኩ፣ እኔ ማን ነኝ ትእዛዛቴንስ የማያከብረውን ጥፋተኛ እንዳይሆን የማልይዘው እኔ እኔ ማን ነኝ? አል ጌታ፤

፴፩ [ሀ]ቃል ገብቼ እና ያልፈጸምሁ እኔ ማን ነኝ? ይላል ጌታ፤

፴፪ አዛለሁ እናም ሰዎች አያከብሩም፣ [ሀ]እሸራለሁ እና በረከቶችንም አይቀበሉም።

፴፫ ከዚያም በልባቸው እንዲህ ይላሉ፥ ይህ የጌታ ስራ አይደለም፣ ቃል ኪዳኖቹ አልተሟሉምና። ነገር ግን ለእነዚህ ወዮላቸው፣ ዋጋቸው ከላይ ሳይሆን [ሀ]ከስር አድፍጦ ይጠብቃቸዋልና።

፴፬ እናም አሁን ስለዚህ አገር ሌሎች ተጨማሪ መመሪያዎችን እሰጣችኋለሁ።

፴፭ ገንዘቡን ለቤተክርስቲያኗ ኤጲስ ቆጶስ [ሀ]በመስጠት አገልጋዬ ማርቲን ሀርስ ለቤተክርስቲያኗ ምሳሌ መሆኑ ይህ በእኔ ዘንድ ጥበብ ነው።

፴፮ ደግሞም፣ ውርስን ለመቀበል ወደ እዚህ አገር ለሚመጣ ሰው ሁሉ ይህ ህግ ነው፤ እና በገንዘቡም ህጉ እንደሚመራው ያደርግበታል።

፴፯ ለኀተራ፣ እናም [ሀ]ለማተሚያ ቤት፣ የሚሆን ቦታ በኢንዲፔንደንስም መሬቶች እንዲገዙ ይህም ደግሞ በእኔ ዘንድ ጥበብ ነው።

፴፰ መልካም እንደመሰለው ውርሱን እንዲቀበልም፣ ሌሎች መመሪያዎችም ለአገልጋዬ ማርቲን ሀርስ በመንፈስ ይሰጡታል፤

፳፩ሀ ሉቃ. ፳፥ ፳፪–፳፮፤
ት. እና ቃ. ፺፰፥ ፬–፲፤
እ.አ. ፩፥ ፲፪።
ቅ.መ.መ. መንግስት።

፳፪ሀ ቅ.መ.መ. መሲህ፤
አንድ ሺህ አመት፤
ኢየሱስ ክርስቶስ።

፳፫ሀ ቅ.መ.መ. ህግ።

፳፬ሀ ት. እና ቃ. ፶፩፥ ፲፫፤
፸፪፥ ፱–፲፭።

፳፮ሀ ማቴ. ፳፬፥ ፵፭–፶፩፤
ት. እና ቃ. ፻፯፥ ፺፱–፻።

፳፯ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች፤
ትጋት።

፳፰ሀ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።

፳፱ሀ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።

፴ሀ ኢሳ. ፵፭፥ ፱–፲፤
ሔለ. ፲፪፥ ፮።

፴፩ሀ ት. እና ቃ. ፩፥ ፴፯–፴፰፤
፹፪፥ ፲።

፴፪ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥ ፫–፬።

፴፫ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፵፭።

፴፭ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፴–፴፪።

፴፯ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥ ፲፩–፲፪።

፴፱ ለኃጢአቱም ንስሀ ይግባ፣ የአለምን [ሀ]ምስጋናን ይፈልጋልና።

፵ እናም አገልጋዬ [ሀ]ውልያም ደብሊው ፈልፕስም በተሾመበት ስልጣን ሀላፊነቱን ያከናውን፣ እናም ውርሱንም በዚህ አገር ይቀበል።

፵፩ እናም እርሱም ንስሀ ይገባ ዘንድ ያስፈልገዋል፣ ምክንያቱም ከሌሎች በላይ ስልጣን ለማግኘት ስለሚፈልግ፣ እናም በፊቴም በበቂ የዋህ ስላልሆነ፣ እኔ ጌታ አልተደሰትኩበትም።

፵፪ እነሆ፣ ለኃጢያቶቹ [ሀ]ንስሀ የሚገባም፣ [ለ]ይቅርታን ይቀበላል፣ እናም እኔ ጌታ ደግሜ [ሐ]አላስታውሳቸውም።

፵፫ በዚህም ሰው ለኃጢአቶቹ ንስሀ እንደገባ ታውቃላችሁ—እነሆ፣ [ሀ]ይናዘዛቸዋል እናም [ለ]ይተዋቸዋልም።

፵፬ እናም አሁን ስለተቀየሩት የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ይህን እላለሁ፣ በእምነት በሆነ ጸሎት ካልፈለጉ በቀር፣ እና ጌታ ካልመደበላቸው በስተቀር፣ ውርሳቸውን የሚቀበሉበት ጊዜ፣ ገና ብዙ አመታት፣ ይቀራሉ።

፵፭ እነሆ፣ ህዝብን ከአለም ዳርቻዎች ድረስ በአንድነት [ሀ]ይሰበስቧቸዋልና።

፵፮ ስለዚህ፣ ራሳችሁን በአንድነት አሰባስቡ፣ እና በዚህ አገር እንዲቀሩ ያልተጠሩትም በአካባቢው ባሉት ክፍለ ሀገሮች ወንጌሉን ይስበኩ፣ እና ከዚያም በኋላ ወደ የቤቶቻቸው ይመለሱ።

፵፯ በመንገዳቸውም ላይ ይስበኩ፣ እናም ስለእውነትም በሁሉም ቦታዎች [ሀ]ምስክርነት ይስጡ፣ እናም ባለጠጎችን፣ እናም ከፍ ያሉትንም ሆነ ዝቅ ያሉትን፣ እናም ደሆችንም ንስሀ እንዲገቡ ይጥሯቸው።

፵፰ የምድር ኗሪዎች ንስሀ በሚገቡበት መጠን፣ [ሀ]ቤተክርስቲያኖችን ይመስርቱ።

፵፱ በቤተክርስቲያኗ ድምፅም፣ በኦሀዮ ቤተክርስቲያን፣ [ሀ]በፅዮን ምድር ለመግዛት ገንዘብ የሚቀበል ወኪል ይመረጥ።

፶ እናም ለአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን የፅዮን አገርን አገላለፅ፣ እና በመንፈስ እንደሚገለፀለትም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መግለጫ [ሀ]ይፅፍ ዘንድ ትእዛዝን እሰጠዋለሁ፤

፶፩ እናም በኤጲስ ቆጶስ ወይም በወኪሉ እጅ የሚገቡት ገንዘቦች የሚሰበሰቡበት ማዘዣ፣ እርሱም መልካም እንደሚመስለው ወይም እንደሚመራበት ለእግዚአብሔር ልጆች ውርስ መሬት ይገዛ ዘንድ ለሁሉም ቤተክርስቲያኖች ደብዳቤ እና ማዘዣ ያቅርብ።

፶፪ እነሆ እውነት እላችኋለሁ፣ ደቀመዛሙርቶቹ እና የሰው ልጆች ልባቸውን እንዲከፍቱ፣ እንዲሁም ጊዜ እንደፈቀደ ክፍለ ሀገሩን ሁሉ ይገዛ ዘንድ የጌታ ፍላጎት ነው።

፶፫ እነሆ፣ ይህም ጥበብ ነው። ይህን ያድርጉ ያለበለዚያ ደም ካልፈሰሰ በቀር ምንም [ሀ]ወርስ አይቀበሉምና።

፶፬ ደግሞም፣ የሚገኝ መሬት እስካለ ድረስ፣ የተለያዩ ችሎታ ያላቸው ሰራተኞች ለእግዚአብሔር ቅዱሳን እንዲሰሩ ወደዚህ አገር ይላኩ።

፶፭ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በዕቅድ ይደረጉ፤ ጊዜ በጊዜም ኤጲስ ቆጶሱ ወይም የቤተክርስቲያኗ ወኪል በምድር ላይ የመስራትን መብት እንዲታወቅ ያድርጉ።

፶፮ የመሰብሰቢያው ስራም በጥድፊያ ወይም በመሯሯጥ አይሁን፤ ነገር ግን ይህም በቤተክርስቲያኗ ጉባኤ ላይ ሽማግሌዎች ከጊዜ ወደጊዜ እንደሚቀበሉት እውቀት መጠን የሚመከሩት ይሁን።

፶፯ አገልጋዬ ስድኒ ርግደን ይህን አገር እና

፴፱ ሀ ፪ ኔፊ ፳፮፥፳፱፤
ት. እና ቃ. ፻፳፩፥ ፴፬–፴፯።
፵ ሀ ቅ.መ.መ. ፈልፕስ፣
ውልያም ደብሊው።
፵፪ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ለ ኢሳ. ፩፥፲፰።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
ሐ ኢሳ. ፵፫፥፳፭።
፵፫ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፥፳፤ ፷፬፥፯።
ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
ለ ት. እና ቃ. ፹፪፥፯።
፵፭ ሀ ዘዳግ. ፴፫፥፲፯።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፵፯ ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፰።
፵፰ ሀ ይህም የቤተክርስቲያኗ
ቅርንጫፎች ማለት ነው።
፵፱ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፶ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፭–፶፮።
፶፫ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳፯–፴፩።

[ሀ]ቤተመቅደስ የሚሰራበትን ስፍራ ለጌታ ይቀድስ እናም ይመርቅ።

፶፰ የጉባኤ ስብሰባም ይጠራ፤ እናም ከዚያም በኋላ አገልጋዮቼ ስድኒ ርግደን እና ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ በመሬታቸው ላይ እንዲያከናውኑ የሰጠኋቸውን እናም ጉባኤዎቹ [ሀ]የመረጣቸውን ለማከናወን ይመለሱ፣ እናም ኦሊቨር ካውድሪም ከእነርሱ ጋር ይሂድ።

፶፱ የሚያውቀውን እና በእርግጥ የሚያምነውን በሚጓዝበት መንገድ [ሀ]ሳይሰብክ ማንም ሰው ከዚህ አገር አይመለስ።

፷ ለዛይባ ፒተርሰን የተሰጠው ይወሰድበት፤ እናም የቤተክርስቲያን አባልነቱንም መሆንም ይቀጥል፣ እናም ለኃጢአቶቹ በሚገባ [ሀ]እስከሚገሰጽ ድረስ በራሱ እጅ ከወንድሞች ጋር ይስራ፤ ኃጢአቶቹን ሁሉ አልተናዘዛቸውም፣ እናም ሊደብቃቸው ያስባልና።

፷፩ አንዳንዶቹ መመዘን ከሚቻለው በላይ የተባረኩት ወደዚህ አገር የሚመጡት የቀሩት የቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎችም በጉባኤ በዚህ አገር ውስጥ ይሰብሰቡ።

፷፪ አገልጋዬም ኤድዋርድ ፓርትሪጅም የእነርሱን ጉባኤ ይምራ።

፷፫ እናም በመንገዳቸውም ወንጌልን በመስበክ፣ ስለተገለጡላቸው ነገሮች ምስክር በመስጠት፣ ይመለሱ።

፷፬ በእውነት፣ ድምፅ ከዚህ ስፍራ ወደ አለም ሁሉ፣ እናም ወደ ምድር ዳርቻ ድረስ፣ ሊሄድ ይገባል—የሚያምኑትን በሚከተለው [ሀ]ምልክት፣ ወንጌሉ ለእያንዳንዱ ፍጥረት [ለ]መስበክ አለበት።

፷፭ እናም እነሆ የሰው ልጅ [ሀ]ይመጣል። አሜን።

ክፍል ፶፱

በነሀሴ ፯፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ፣ በፅዮን ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ከዚህ ራዕዩ በፊትም፣ ህዝቡ በዚያን ጊዜ ስለተሰበሰቡበት የፅዮን መሬት ነቢዩ በግልፅ ጻፈ። ምድሩም ጌታ እንዳዘዘው ተቀድሶ ነበር፣ እናም ወደፊት ቤተመቅደስ የሚሰራበት ስፍራም ተመርቆ ነበር። ይህ ራዕይ በተቀበለበት ቀን፣ የጆሴፍ ናይት ቀዳማዊ ባለቤት ፖሊ ናይት ሞተች፣ እርሷም በ ፅዮን የሞተች የመጀመሪያ የቤተክርስቲያኗ አባል ነበረች። የመጀመሪያ አባላት ይህን ራዕይ "ቅዱሳን ሰንበትን የሚጠብቁበት እና እንዴት እንደሚጾሙና እንደሚጸልዩ የሚያስተምር" ነው ብለው ይናገሩበት ነበር።

፩–፬፣ በፅዮን ውስጥ የሚገኙት ታማኝ ቅዱሳን ይባረካሉ፤ ፭–፰፣ ጌታን በማፍቀር እና በማገልገል ትእዛዛቱን ያክብሩ፤ ፱–፲፱፣ የጌታን ቀን ቅዱስ አድርጎ በመጠበቅ፣ ቅዱሳን በስጋ እና በመንፈስ ተባርከዋል፤ ፳–፳፬፣ ጻድቃኑም በዚህ አለም ሰላም እና በሚመጣው አለም ዘለአለማዊ ህይወት ቃል ተገብቶላቸዋል።

፩ እነሆ፣ ጌታም እንዲህ ይላል፣ እንዳዘዘኳቸው ሙሉ [ሀ]አይናቸውን ወደ ክብሬ አድርገው ወደዚህ አገር የመጡት የተባረኩ ናቸው።

፶፯ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፫፤
፹፬፥፫–፭፤
፴፩፤ ፺፯፥፲–፲፯።
፶፰ ሀ ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።
፶፱ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፷ ሀ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፷፬ ሀ ቅ.መ.መ. ምልክት።
ለ ቅ.መ.መ. መስበክ።
፷፭ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፶፱ ፩ ሀ ማቴ. ፮፥፳፪–፳፬፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፯።

፪ በህይወት ያሉት ምድርን [ሀ]ይወርሳሉ፣ እና [ለ]የሞቱትም ከሁሉም ድካሞቻቸው ያርፋሉ፣ እናም ስራዎቻቸው ይከተሏቸዋል፤ እናም ባዘጋጀሁላቸው በአባቴም [ሐ]ቤቶች ውስጥ [መ]አክሊልን ይቀበላሉ።

፫ አዎን፣ ወንጌሌን በማክበር በፅዮን ምድር ላይ እግሮቻቸውን ያሳረፉትም የተባረኩ ናቸው፤ ምክንያቱም፤ የምድር መልካም ነገሮች የእነርሱ ደመወዛቸው ይሆናልና፣ እና ምድርም [ሀ]በጥንካሬዋ መልካም ውጤት ታመጣለች።

፬ ከላይ በሚመጡም በረከቶችም፣ አዎን፣ እናም በፊቴ [ሀ]ታማኝ እና [ለ]ትጉሆች ለሆኑትም፣ ጥቂት ባልሆኑ ትእዛዛት፣ እናም በጊዜአቸውም [ሐ]ራዕይና አክሊልን ይቀበላሉ።

፭ ስለዚህ፣ እንዲህ በማለት ትእዛዛትን እሰጣቸዋለሁ፥ ጌታ አምላክህን በፍጹም [ሀ]ልብህ፣ በሙሉ ሀይልህ፣ አዕምሮህ፣ እና ጉልበትህ [ለ]ውደድ፤ እናም በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም [ሐ]አገልግለው።

፮ [ሀ]ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ። [ለ]አትስረቅ፤ ወይም [ሐ]አታመንዝር፣ ወይም [መ]አትግደል፣ ወይም እንደዚህ አይነት ነገሮችን አታድርግ።

፯ ጌታ አምላክህን በሁሉም ነገሮች [ሀ]አመስግን።

፰ የተሰበረ ልብን እና [ሀ]የተዋረደ መንፈስን [ለ]መስዋዕት አድርገህ ለጌታ አምላካህ [ሐ]በፅድቅ አቅርብ።

፱ ከአለም ነገሮች ራስህን ንጹህ እና [ሀ]ነውር የሌለበት ለማድረግ ወደ ጸሎት ቤት ሂድ፣ እናም [ለ]በቅዱስ ቀኔም ቅዱስ ስርዓቶችህን አቅርብ፤

፲ በእውነት ከስራህ እንድታርፍ እናም ለልዑልም አምልኮህን [ሀ]እንድትሰጥ ይህ ቀን ተሰጥቶሀልና፤

፲፩ ነገር ግን፣ በሁሉም ቀናት እና በሁሉም ጊዜያት ስእለትህም በፅድቅ ይቅረብ።

፲፪ በዚህ በጌታ ቀን ግን፣ በወንድሞችህ እና በጌታህ ፊት ኃጢአትህን [ሀ]በመናዘዝ፣ መስዋዕትህን እና ቅዱስ [ለ]ቁርባንህን ለልዑልህ ለማቅርብ አስታውስ።

፲፫ [ሀ]ጾምህ ፍጹም እንዲሆን፣ ወይም በሌላ ቃል [ለ]ደስታህ እንዲሞላ፣ ምግብህን በአንድ ልብ ከማዘጋጀት በቀር በዚህ ቀን ሌላ ምንም ነገር አታድርግ።

፲፬ በእውነት፣ ይህ ጾም እና ጸሎት፣ ወይም በሌላ ቃል፣ መደሰት እና መጸለይ ነው።

፲፭ እነዚህን ነገሮች [ሀ]በምስጋና፣ እና በፈቃደኛ ልብ እና ፊት፣ እናም ኃጢአትም ስለሆነ በብዙ [ለ]መሳሳቅ ሳይሆን [ሐ]በደስተኛ [መ]ልብና ፊት ካደረግህ—

፲፮ በእውነት እላለሁ፣ ይህን ነገር ካላደ

፪ ሀ ማቴ. ፭፥፭፤ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳፣ ፵፰–፵፱።
ለ ራዕ. ፲፬፥፲፫። ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት፤ ገነት።
ሐ ዮሐ. ፲፬፥፪፤ ት. እና ቃ. ፸፪፥፬፤ ፸፮፥፻፲፩፤ ፹፩፥፮፤ ፺፰፥፲፰።
መ ቅ.መ.መ. አክሊል፤ ከፍተኛነት።
፫ ሀ ዘፍጥ. ፬፥፲፪፤ ሙሴ ፭፥፴፯።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
ለ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፩፤ ፸፮፥፯፤ ፺፰፥፲፪፤ ፻፩፥፴፪–፴፬። ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ልብ።
ለ ዘዳግ. ፲፩፥፩፤ ማቴ. ፳፪፥፴፯፤ ሞሮኒ ፲፥፴፪፤ ት. እና ቃ. ፳፥፲፱። ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ሐ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ጓደኝነት።
ለ ቅ.መ.መ. መስረቅ።
ሐ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
መ ቅ.መ.መ. ግድያ።
፯ ሀ መዝ. ፺፪፥፩፤ አልማ ፴፯፥፴፯፤ ት. እና ቃ. ፵፮፥፴፪። ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ለ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ሐ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
፱ ሀ ያዕ. ፩፥፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. የሰንበት ቀን።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
ለ ይህም በጊዜ፣ በችሎታ ወይም በገንዘብም ቢሆን፣ እግዚአብሔርን እና ሰዎች በማገልገል ቁርባን ማቅረብ ማለት ነው። ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፱።
ሐ ዘፀአ. ፳፭፥፪፤ ት. እና ቃ. ፷፬፥፴፬።
መ ምሳ. ፲፯፥፳፪።

ረግህ፣ የምድር ሙላት፣ እንዲሁም የዱር አራዊቶች እና የሰማይ አዕዋፋት፣ እናም በዛፍ ላይ የሚወጡት እና በምድር የሚራመዱ ሁሉ የአንተ ይሆናሉ፤

፲፯ አዎን፣ ቅጠላ ቅጠሎች፣ እናም ለምግብ ይሁን ለልብስ፣ ወይም ለቤትም፣ ወይም ለጋጣ፣ ወይም የመዝናኛ ስፍራዎች፣ ወይም ለአትክልት ስፍራ፣ ወይም ለወይን ስፍራም፣ የሚሆኑትን ከምድር የሚመጡት መልካም ነገሮች ሁሉ የአንተ ይሆናሉ፤

፲፰ አዎን፣ በጊዜአቸው ሀበምድር ላይ የሚያድጉት ነገሮች የተፈጠሩት ለሰው ጥቅም፣ አይንን እና ልብን ለማስደሰት ነውና፤

፲፱ አዎን፣ ለምግብ እና ለልብስ፣ ለጣዕም እና ሽታ፣ ሰውነትን ለማጠንከር እና ነፍስንም ለማደስ የተፈጠረ ነው።

፳ እናም እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለሰው ስለሰጠ እግዚአብሔርን ያስደስተዋል፤ በብልጫ ወይም በግድ ሳይሆን፣ በጥበብ እንደዚህ እንዲጠቀሙባቸው ነውና የተፈጠሩት።

፳፩ በሁሉም ነገሮች ውስጥ የእርሱ እጅ እንዳለበት ሀካለመመስከር እና ትእዛዙን ካለማክበር በቀር፣ በምንም መንገድ ሰው እግዚአብሔርን ለአያስቀይመውም፣ ወይም በማንም ላይ ቁጣው አይቀጣጠልም።

፳፪ እነሆ፣ ይህም በህግ እና በነብያቱ መሰረት ነው፤ በዚህም ጉዳይ ደግማችሁ አትነትርኩኝ።

፳፫ ነገር ግን ሀየፅድቅን ስራ የሚሰራው ለደመወዙን፣ እንዲሁም በዚህ አለም ሐሰላም፣ እና በሚመጣው አለምም መዘለአለማዊ ህይወትን ይቀበላል።

፳፬ እኔ ጌታ ይህን ተናግሬአለሁ፣ እና መንፈስም ይመሰክራል። አሜን።

ክፍል ፷

በነሀሴ ፰፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በጃክሰን አውራጃ ሚዙሪ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ ወደ ጃክሰን አውራጃ የተጓዙ እና በመሬቱና በቤተመቅደስ መገንቢያ ቦታ መቀደስ የተሳተፉ ሽማግሌዎች ምን ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው ለማወቅ ፈልገው ነበር።

፩–፱፣ ሽማግሌዎች በኃጢአተኞቹ ጉባኤ መካከል ወንጌልን ይስበኩ፤ ፲–፲፬፣ ጊዜአቸውን አያጠፉም እናም ችሎታቸውንም አይደብቁም፤ ፲፭–፲፯፣ ወንጌሉን ባልተቀበሉት ላይ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ እግራቸውን ይጠቡ።

፩ እነሆ፣ ወደመጡበት አገር ፈጥነው ለሚመለሱት ለቤተክርስቲያኑ ሽማግሌዎች ጌታ እንዲህ ይላል፥ እነሆ፣ ወደዚህ ስፍራ መምጣታችሁ አስደስቶኛል፤

፪ ነገር ግን በአንዳንዶች አልተደሰትኩም፣ ሀአንደበቶቻቸውን አልከፈቱምና፣ ነገር ግን ሰውን ለበመፍራት የሰጠኋቸውን ችሎታ ሐደብቀዋል። ለእነዚህ አይነቶችም ወዮላቸው፣ ቁጣዬ በእነርሱ ላይ ነዳለችና።

፫ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ለእኔ ይበልጥ ታማኝ ካልሆኑ ይህም፣ እንዲሁም ያላቸውም፣ ሀይወሰድባቸዋል።

፬ እኔ ጌታ ከላይ በሰማያት፣ እናም በምድር ሀሰራዊት መካከልም እገዛለሁና፤ እናም

፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. ምድር።
፳፩ ሀ ኢዮብ ፩፥፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. መበደል።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
ለ ቅ.መ.መ. መባረክ፣
የተባረከ፣ በረከት።
ሐ ማቴ. ፲፩፥፳፰–፴።
ቅ.መ.መ. ሰላም።
መ ት. እና ቃ. ፲፬፥፯።
፷ ፪ ሀ ኤፌ. ፮፥፲፱–፳።
ለ ማቴ. ፳፭፥፲፬–፴።
ቅ.መ.መ. ፍርሀት—
ሰውን መፍራት።
ሐ ሉቃ. ፰፥፲፮፤ ፲፰።
፫ ሀ ማር. ፬፥፳፭፤
ት. እና ቃ. ፩፥፴፫።
፬ ሀ አልማ ፴፫፥፱።

[ለ]እንቁዎቼን በምሰበስብበት ጊዜ፣ ሁሉም ሰዎች የእግዚአብሔር ሀይልን የሚያውጀው ምን እንደሆነም ያውቃሉ።

፭ ነገር ግን፣ ወደ መጣችሁበት አገር ስለምትጓዙበትም እነግራችኋለሁ። ለእኔ ምንም ልዩነት ስለሌለው፣ እንደሚመስላችሁ መዘውር ይሰራ ወይም ይገዛ፣ እናም ሴንት ሉዊስ ወደሚባለው ከተማም ፈጥናችሁ ተጓዙ።

፮ ከዚያም ቦታ አገልጋዮቼ ስድኒ ሪግደን፣ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ እና ኦሊቨር ካውድሪ ም ወደ ስንሰናቲ ይጓዙ፤

፯ እናም በዚህ ስፍራም ድምጻቸውን አንስተው፣ ያለ ቍጣና አለ ጥርጥር፣ ቅዱስ እጆችን በማንሳት፣ በጎላ ድምፅ ቃላቴን ይግለጹ። [ሀ]ቅዱሳን አደርጋችሁ ዘንድ ይቻለኛልና፣ እናም ኃጢአቶቻችሁም [ለ]ተሰርየዋል።

፰ እና የሚቀሩትም፣ ከመጡባቸው ቤተክርስቲያኖች እስከሚመለሱ ድረስ፣ ሁለት በሁለት በመሆን፣ እናም በችኮላ ሳይሆን፣ ቃሉን በኃጢአተኞቹ ጉባኤ መካከል በመስበክ፣ ከሴንት ልዊስ ጎዞአቸውን ይጀምሩ።

፱ እናም ይህም ሁሉ ለቤተክርስቲያኖቹ ጥቅም ነው፤ ለዚህም ምክንያት ልኬአቸዋለሁና።

፲ እናም አገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ የሰጠሁትን ገንዘብ፣ እንዲመለሱ ለታዘዙት ለእኔ ሽማግሌዎች ክፊሉን ይስጥ፤

፲፩ እና የሚችለውም፣ በወኪሉ በኩልም ይህን ይመልስ፤ እናም ከማይችለውም፣ ከእርሱ ይህ አይጠበቅበትም።

፲፪ እናም አሁን ወደዚህ ምድር እየመጡ ስላሉትም ቅሪቶች እናገራለሁ።

፲፫ እነሆ፣ በኃጢአተኞቹ ጉባኤ መካከል ወንጌሌን እንዲሰብኩ ተልከው ነበር፤ ስለዚህ፣ እንዲህም ትእዛዝ እሰጣቸዋለሁ፥ ጊዜአችሁን [ሀ]አታጥፉ፣ [ለ]ችሎታችሁንም እንዳይታወቁ አትቅበሩ።

፲፬ እናም ወደ ፅዮን ምድር ከመጣችሁም እናም ቃሌን ካወጃችሁ በኋላ፣ በችኮላ፣ ወይም [ሀ]በቁጣ ወይም በጥላቻ ሳይሆን፣ በኃጢአተኞቹ ጉባኤ መካከል ወንጌሌን በማወጅ ፈጥናችሁ ተመለሱ።

፲፭ እናም እንዳታስቆጧቸው በፊት ለፊታቸው ሳይሆን በሚስጥር፣ በማይቀበሏችሁም ላይ ከእግራችሁ በታች ያለውን [ሀ]ትቢያ አራግፉ፤ ይህም በፍርድ ቀን ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ እግራችሁን እጠቡ።

፲፮ እነሆ፣ ይህም ለእናንተ በቂ እናም የእርሱ የላካችሁም ፈቃድ ነው።

፲፯ እናም በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ አንደበት በኩልም ስለስድኒ ሪግደን እና ኦሊቨር ካውድሪ ይገለጣል። የሚቀረውም ከዚህ በኋላ ይገለጣል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፷፩

በነሀሴ ፲፪፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በመክኢልዋኢን መታጠፊያ፣ በሚዙሪ ወንዝ ዳርቻ ላይ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ወደ ከርትላንድ በሚመለሱበት ጉዞ ነቢዩ እና አስር ሽማግሌዎች በሚዙሪ ወንዝ ላይ በታንኳዎች ተጉዘው ነበር። በጉዞአቸው ሶስተኛው ቀን ብዙ አደገኛ አጋጣሚዎች ነበሯቸው። ሽማ

፬ ለ ኢሳ. ፷፪፥፫፤
ዘካ. ፱፥፲፮፤
ሚል. ፫፥፲፯፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥፫።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ለ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣
ኤድዋርድ።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፵፪።
ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣
ስራ ፈቺ።
ለ ማቴ. ፳፭፥፳፬–፴፤
ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፰።
፲፬ ሀ ምሳ. ፲፬፥፳፱።
፲፭ ሀ ማቴ. ፲፥፲፬፤
ሉቃ. ፱፥፭፤
የሐዋ. ፲፫፥፶፩፤
ት. እና ቃ. ፳፬፥፲፭፤
፸፭፥፳፤ ፺፱፥፬።

ግሌ ዊልያም ደብሊው ፌልፕስ፣ በቀን ራዕይ፣ አጥፊው በውሀ ገጽ ላይ በሀይል ሲንሳፈፍ አየው።

፩–፲፪፣ ጌታ በውሀዎች ላይ ብዙ ጥፋቶችን አውጇል፤ ፲፫–፳፪፣ ውሀዎች በዮሐንስ ተረግመዋል፣ እናም አጥፊው በእነዚህ ገጾች ላይ ይንሳፈፋል፤ ፳፫–፳፱፣ አንዳንዶች ውሀዎችን ለማዘዝ ሀይል አላቸው፤ ፴–፴፭፣ ሽማግሌዎች ሁለት በሁለት ይጓዙ እናም ወንጌልን ይስበኩ፤ ፴፮–፴፱፣ ለሰው ልጅ መመለስም ይዘጋጁ።

፩ እነሆ፣ እናም ሁሉም [ሀ]ሀይል ያለውን፣ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም የሆነውን፣ እንዲሁም [ለ]አልፋና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያና የመጨረሻውን የእርሱን ድምፅ አድምጡ።

፪ እነሆ፣ እኔ ጌታ ኃጢአቶችን ስለምሰርይ፣ እና ኃጢአታቸውን በትሁት ልብ [ሀ]ለሚናዘዙት [ለ]በምህረት የተሞላሁ ስለሆንኩ፣ ኃጢአታችሁ [ሐ]የተሰረየላችሁ፣ በዚህ ስፍራ የተሰበሰባችሁ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ ጌታ እንዲህ ይላችኋል፤

፫ ነገር ግን እንዲህ እላችኋለሁ፣ በዳርቻዎቹ ያሉት ኗሪዎች እምነት በማጣት እየጠፉ እያሉ፣ እነዚህ ሁሉም ሽማግሌዎቼ በውሀ ላይ በፍጥነት መጓዝ አያስፈልጋቸውም።

፬ ይሁን እንጂ፣ ይህን የፈቀድኩት እናንት ምስክር እንድትሰጡ ነው፤ እነሆ፣ በውሀዎች ላይ፣ እና ከዚህ በኋላም ተጨማሪ ብዙ አደጋዎች አሉ፤

፭ እኔ ጌታ፣ በቁጣዬ በውሀዎች ላይ ብዙ ጥፋቶችን አውጇለሁ፤ አዎን፣ በተለይም በእነዚህ ውሀዎች ላይ።

፮ ይሁን እንጂ፣ ሁሉም ስጋ በእጄ ነው፣ እናም ከመካከላችሁ ታማኝ የሆነው በውሀዎች አይጠፋም።

፯ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት እና አገልጋዬ [ሀ]ውልያም ደብሊው ፌልፕስ ወደ ጥሪአቸው እና ተልዕኮአቸው በፍጥነት መሄዳቸው አስፈላጊ ነው።

፰ ይሁን እንጂ፣ አንድ እንድትሆኑ፣ [ሀ]በክፋትም እንዳትጠፉ፣ ለኃጢአታችሁ ሁሉ [ለ]ከመገሰጻችሁ በፊት እንድትሄዱ አልፈቅድም፤

፱ አሁን ግን፣ እንዲህ እላለሁ፣ መሄዳችሁ ፍቃዴ ነው። ስለዚህ፣ አገልጋዮቼ ስድኒ ጊልበርት እና ዊልያም ደብሊው ፌልፕስ በፊት አብረዋቸው የነበሩትን ይውሰዱ፣ እናም ተልዕኮአቸውን ለማሟላትም በፍጥነት ጉዞአቸውን ይጀምሩ፣ እናም በእምነትም ይቋቋማሉ፤

፲ እናም ታማኝ ከሆኑም ይጠበቃሉ፣ እና እኔ፣ ጌታም፣ ከእነርሱ ጋር ነኝ።

፲፩ እናም የሚቀሩት ለልብስ የሚያስፈልገውን ይውሰዱ።

፲፪ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርትም፣ እንደተስማማችሁበት፣ አስፈላጊ ያልሆኑትን ይውሰድ።

፲፫ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ስለእነዚህ ነገሮች በተመለከተ [ሀ]ትእዛዝን የምሰጣችሁ [ለ]ለጥቅማችሁ ነውና፤ እናም እኔ ጌታ፣ እንደ ቀደሙት ቀናት ከሰዎች ጋር እንዳደረግሁ አነጋግራችኋለሁ።

፲፬ እነሆ፣ እኔ ጌታ በመጀመሪያ [ሀ]ውሀዎችን ባረኩአቸው፤ ነገር ግን በመጨረሻዎቹም ቀናት፣ በአገልጋዬ ዮሐንስ አንደበትም ውሀዎችን [ለ]ረገምኩ።

፲፭ ስለዚህ፣ ማንኛውም ስጋ በውሀዎች ላይ ደህና የማይሆንበት ቀናት ይመጣሉ።

፲፮ እና በመጪዎቹ ቀናትም፣ ልቡ ቅን ከሆነው በስተቀር፣ ማንም ወደ ፅዮን ምድር በውሀዎች ላይ ለመጓዝ አይችልም ይባላል።

፷፩ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ሀይል።
ለ ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
፪ሀ ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ሞዛያ ፬፥፲–፲፩።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ፌልፕስ፣ ውልያም ደብሊው።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፲፫ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
ለ ት. እና ቃ. ፷፩፥፯።
፲፬ሀ ዘፍጥ. ፩፥፳።
ለ ራዕ. ፰፥፰–፲፩።

፲፯ እናም፣ እኔ ጌታ በመጀመሪያው ምድርን [ሀ]እንደረገምኩት፣ እንዲሁም በመጨረሻዎቹም ቀናት፣ በጊዜውም ለቅዱሳን ጥቅም፣ ከዚህም ስቡን እንዲካፈሉ ባርኬዋለሁ።

፲፰ እና አሁንም ለአንዱ የተናገርኩትን ለሁሉም እንደተናከርኩ፣ እምነታቸው ወድቆ እና እንዳይጠመዱ፣ ስለእነዚህ ውሀዎች ወንድሞቻችሁን እንድታስጠነቅቁ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ፤

፲፱ እኔ ጌታ አውጄአለሁ፣ እናም አጥፊውም በዚህ ፊት ይንሳፈፋል፣ እናም አዋጁን አልሽርም።

፳ ትላንትና፣ እኔ ጌታ፣ ተቆጥቼአችሁ ነበር፣ ነገር ግን ዛሬ ቁጣዬ ከእናንተ ተመልሷል።

፳፩ ስለዚህ፣ በፍጥነት እንዲጓዙ የነገርኳቸውም—ደግሞም እንዲህ እላችኋለሁ፣ ጉዞአቸውን በፍጥነት ይጀምሩ።

፳፪ እናም ከትንሽ ጊዜ በኋላ፣ ተልዕኮአቸውን እስካሟሉ ድረስ፣ በውሀም ይሁን በምድር መሄዳቸው በእኔ ዘንድ ለውጥ አያመጣም፤ ከዚህም በኋላ እንዲያውቁት እንደተደረገው እንደ ውሳኔአቸው ይሁን።

፳፫ እናም አሁን፣ አገልጋዮቼን ስድኒ ሪግደንን፣ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን፣ እና ኦሊቨር ካውድሪ ን በተመለከተም፣ ወደ ቤቶቻቸው ሲጓዙ፣ በመስኖ ላይ ካልሆነ በስተቀር፣ ደግመው በውሀዎች እንዳይመጡ፤ ወይም በሌላ አባባልም በመስኖ ካልሆነ በስተቀር በውሀዎች አይጓዙ።

፳፬ እነሆ፣ እኔ ጌታ ለቅዱሳኔ የመጓዣ መንገድን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እናም እነሆ፣ ይህም መንገዱ ነው—እንዲጓዙ እና ወደ ፅዮን ምድር እንዲሄዱ ትእዛዝ እስከተሰጣቸው ድረስ፣ ከመስኖው ከወጡ በኋላ፣ በምድር ይጓዛሉ፤

፳፭ እናም፣ በመንገዱም ድንኳኖቻቸውን [ሀ]በመትከል፣ እንደ እስራኤል ልጆችም ያደርጋሉ።

፳፮ እናም፣ እነሆ፣ ይህም ለወንድሞቻችሁ ሁሉ የምትሰጡት ትእዛዝ ነው።

፳፯ ይሁን እንጂ፣ ለአንዱ ውሀዎችን ለማዘዝ [ሀ]ሀይል ተሰጥቶታል፣ ለሌላውም በመንፈስ መንገዶቹን ሁሉ እንዲያውቅም ተሰጥቶታል፤

፳፰ ስለዚህ፣ ከዚህ በኋላ የሚሆነው በእኔ ስለሚወሰን፣ በምድርም ይሁን ወይም በውሀ ላይ፣ የህያው እግዚአብሔር መንፈስ እንደሚመራው ያድርግ።

፳፱ እናም ለእናንተም የቅዱሳኑ መንገድ፣ ወይም የጌታ ሰራዊት ቅዱሳን መጓዣ መንገድ ተሰጥቷችኋል።

፴ እና ደግሞም፣ በእውነት እላችኋላሁ፣ ስንሰናቲ እስኪደርሱ ድረስ፣ አገልጋዮቼ ስድኒ ሪግደን፣ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ እና ኦሊቨር ካውድሪ በኃጢአተኞቹ ጉባዔዎች መካከል አንደበቶቻቸውን አይክፈቱ፤

፴፩ እና በዚያም ስፍራ ወደ እግዚአብሔር፣ አዎን፣ በኃጢአታቸው ምክንያት ንዴቱ ወደተቀጣጠለው፣ በእነዚያ ሰዎች፣ ለጥፋትም [ሀ]በደረሱት ሰዎች ላይ፣ ድምጻቸውን ከፍ ያደርጋሉ።

፴፪ እና ከእዚያም ወደ ወንድሞቻቸው ጉባኤዎች ይጓዙ፣ እንዲሁም አሁን አግልግሎታቸው ከኃጢአተኞቹ ጉባኤ በላይ በእነርሱ መካከል በጣም የሚፈለግ ነውና።

፴፫ እናም አሁን፣ የሚቀሩትን በተመለከተ፣ ይጓዙ እናም፣ እንደሚሰጣቸውም፣ በኃጢአተኞቹ ጉባኤ መካከልም ቃልን [ሀ]ይስበኩ፤

፴፬ እናም ይህን እስካደረጉ ድረስ ልብሳቸውን [ሀ]ያጸዳሉ፣ እናም በፊቴም እንከን አይኖራቸውም።

፴፭ እናም አብረው፣ ወይም መልካም እንደሚመስላቸው፣ [ሀ]ሁለት በሁለት ሆነ

፲፯ ሀ ሙሴ ፭፥፴፫።
፳፭ ሀ ዘኁል. ፱፥፲፰።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይል፤ ክህነት።
፴፩ ሀ አልማ ፴፯፥፴፩፤ ሔለ. ፲፫፥፲፬፤ ት. እና ቃ. ፻፩፥፲፩።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. መመስከር፤ መስበክ።
፴፬ ሀ ፪ ኔፊ ፱፥፵፬፤ ያዕቆ. ፪፥፪፤ ሞዛያ ፪፥፳፰።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።

ውም ይጓዙ፣ የተደሰትኩባቸውን አገልጋዬ ሬኖርልድስ ካሁን እና አገልጋዬ ሳሙኤል ኤች ስሚዝ ብቻ ወደ ቤቶቻቸው እስከሚመለሱ ድረስ አይለያዩ፣ እና ይህም በእኔ የላቀ ጥበብ እቅድ ነው።

፴፮ እና አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እናም ለአንዱ የተናገርኩትን ለሁሉ እንደምናገር ነው፣ [ሀ]ህጻናት ሆይ፣ ተደሰቱ፤ [ለ]በመካከላችሁ ነኝ፣ እናም [ሐ]አልተውኳችሁምና፤

፴፯ እናም ራሳችሁን በፊቴ ዝቅ እስካደረጋችሁ ድረስ፣ [ሀ]የመንግስቱ በረከቶች የእናንተ ናቸው።

፴፰ የሰው ልጅ መምጣትን [ሀ]እየጠበቃችሁ፣ ታጠቁ፣ እናም የነቃችሁ ሁኑ፣ እናም በመጠንም ኑሩ፣ ባላሰባችሁበት ሰዓት ይመጣልና።

፴፱ [ሀ]ወደ ፈተናም እንዳትገቡ፣ የሚመጣበትን ቀን በህይወት ወይም በሞት መታገስ ትችሉ ዘንድ ዘወትር [ለ]ጸልዩ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፷፪

በነሀሴ ፲፫፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በቻርተን ሚዙሪ ውስጥ፣ በሚዙሪ ወንዝ ዳርቻ ላይ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ከኢንድፐንደንስ ወደ ከርትላንድ በጉዞ ላይ የነበሩት ነቢዩ እና ቡድኖቹ ወደ ፅዮን ምድር የሚጓዙትን ብዙ ሽማግሌዎች ተገናኙአቸው፣ እናም ከደስታ ሰላምታ በኋላ፣ ይህን ራዕይ ተቀበለ።

፩–፫፣ ምስክርነቶች በሰማይ ይመዘገባሉ፤ ፬–፱፣ ሽማግሌዎች ይጓዙ እናም በማመዛዘን እና በመንፈስ እንደተመሩ ይስበኩ።

፩ እነሆ፣ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ እናም አድምጡ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፣ እንዲሁም፣ የሰውን ድክመት እና [ሀ]የሚፈተኑትን እንዴት [ለ]እንደሚረዳቸው የሚያውቅው፣ [ሐ]አማላጃችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፪ እናም በእውነትም አይኖቼ ወደ ፅዮን ምድር ገና ባልተጓዙት ላይ ናቸው፤ ስለዚህ ተልዕኮአችሁ ገና አልተሟላም።

፫ ይሁን እንጂ፣ የተባረካሁ ናችሁ፣ የሰጣችሁት [ሀ]ምስክርነት መላእክት እንዲመለከቱት በሰማይ [ለ]ተመዝግበዋልና፣ እናም በእናንተም ተደስተዋል፣ እና [ሐ]ለኃጢአታችሁም ይቅርታን አግኝታችኋል።

፬ እና አሁንም ጉዞአችሁን ቀጥሉ። ራሳችሁንም [ሀ]በፅዮን ምድር ሰብስቡ፤ እናም ተሰብስቡ አብራችሁም ተደሰቱ እና ለልዑሉም ቅዱስ ቁርባንን አቅርቡ።

፭ እና ከዚያም፣ ለእኔ ምንም ልዩነት ስለለው፣ መልካም እንደሚመስላችሁ፣ አዎን፣ እንዲሁም ሁላችሁም በአንድነት፣ ወይም ሁለት በሁለት፣ ተመልሳችሁ ምስክርነታችሁን ስጡ፤ ታማኝም ሁኑ፣ እናም ለምድር ኗሪዎችም፣ ወይም፣ በኃጢአተኞቹ ጉባኤዎች መካከልም የምስራችን [ሀ]ስበኩ።

፮ እነሆ፣ እኔ ጌታ ያገናኘኋችሁ የተስፋ ቃል እንዲሟላ፣ በመካከላችሁ ያሉት

፴፮ ሀ ዮሐ. ፲፫፥፴፫።
ለ ማቴ. ፲፰፥፳።
ሐ ኢሳ. ፵፩፥፲፫–፲፯፤
፩ ኔፊ ፳፩፥፲፬–፲፭።
፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፶፥፵፭።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፷፪ ፩ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ዕብ. ፪፥፲፰፤
አልማ ፯፥፲፪።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፰፥፫–፬።
ቅ.መ.መ. አማላጅ።
፫ሀ ሉቃ. ፲፪፥፰–፱።
ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
ለ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፬፥፷፩።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፪።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።

ታማኞችም በሚዙሪ አገር ውስጥ እንዲጠበቁ እና እንዲደሰቱ ነው። እኔ ጌታ ለታማኞች የተሰፋ ቃል ሰጥቻለሁ እናም [ሀ]ለመዋሸት አልችልም።

፯ እኔ ጌታ ፈቃደኛ ነኝ፣ በመካከላችሁ ማንም በፈረሶች፣ ወይም፣ በበቅሎዎች፣ ወይም በሰረገሎች ለመጓዝ ቢፈልግ ካለው፣ ይህን ከጌታ እጅ ለሁሉም ነገሮች [ሀ]በምስጋና ልብ ቢቀበል፣ ይህን በረከት ይቀበላል።

፰ እነዚህ ነገሮችን በማመዛዘን እና መንፈስም እንደመራቸው በኩል ማድረጋቸው የእነርሱ ፈንታ ነው።

፱ እነሆ፣ [ሀ]መንግስቱ የእናንተ ነውና። እናም እነሆ፣ ዘወትር [ለ]ከታማኙ ጋር ነኝ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፷፫

በነሀሴ ፴፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩ፣ ስድኒ ሪግደን፣ እና ኦሊቨር ካውድሪ በነሀሴ ፳፯ ከሚዙሪ ጉዞአቸው ወደ ከርትላንድ ደርሰው ነበር። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ይህን ራዕይ እንዲህ በማለት ገልጿል፥ "ቤተክርስቲያኗ አዲስ በሆነችበት በእነዚህ ቀናት፣ ደህንነታችንን በሚመለከት ከጌታ ቃልን ለማግኘት ታላቅ ጉጉት ነበር፤ እናም አሁን የፅዮን ምድርን በሚመለከት የጊዜው አሳሳቢ ጉዳይ ስለነበር፣ ስለ ቅዱሳን መሰባሰብ እና መሬቶችን ስለመገዛት እና ስለ ሌሎች ጉዳዮች ከጌታ ተጨማሪ መረጃዎችን ጠየቅሁ።"

፩–፮፤ በኃጢአተኞች ላይ የቁጣ ቀን ይመጣል፤ ፯–፲፪፤ ምልክቶች በእምነት አማካይነት ይመጣሉ፤ ፲፫–፲፱፤ በልባቸው የሚያመነዝሩ እምነትን ይክዳሉ እናም ወደ እሳቱ ባሕር ይጣላሉ፤ ፳፤ የታመኑ በክብር በተለወጠችው ምድር ውርሳቸውን ይቀበላሉ፤ ፳፩፤ በክብር የመለወጥ ተራራ ላይ የነበረው ሙሉ ታሪክ ገና አልተገለጠም፤ ፳፪–፳፫፤ ታዛዡ የመንግስትን ሚስጥራት ይቀበላል፤ ፳፬–፴፩፤ የፅዮን ውርሶች ይገዙ፤ ፴፪–፴፭፤ ጌታ ጦርነቶችን አውጇል፣ እናም ኃጢአተኛ ኃጢአተኛውን ይገድላል፤ ፴፮–፵፰፤ ቅዱሳን ወደ ፅዮን ይሰባሰባሉ እናም ይህን ለመገንባትም ገንዘብ ይስጡ፤ ፵፱–፶፬፤ ለታማኞቹ በትንሳኤ፣ እና በአንድ ሺህ ዘመን ዳግም ምፅአት በረከቶች ተረጋግጠውላቸዋል፤ ፶፭–፶፰፤ ይህም የማስጠንቀቂያ ቀን ነው፤ ፶፱–፷፮፤ ያለስልጣን በሚጠቀሙት ዘንድ የጌታ ስም በከንቱ ይጠራል።

፩ አድምጡ፣ እናንት ህዝብ ሆይ፣ እናም ልባችሁን ክፈቱ እናም ከሩቅም ስሙ፤ እናም፣ ራሳችሁን የጌታ ህዝብ ብላችሁ የምትጠሩትም ስሙ፣ እናም እናንተን በሚመለከት የጌታን ቃል እና ፍላጎት አድምጡ።

፪ አዎን፣ እውነትም እላለሁ፣ በኃጢአተኛው እና [ሀ]በአመጸኛው ላይ የተቀጣጠለውንም የቁጣውን ቃል አድምጡ፤

፫ ለመውሰድ የሚፈልገውን [ሀ]ይወስዳል፣ እና ለማዳን የሚፈልገውንም በህይወት ያድናል፤

፬ እንደራሱ ፈቃድ እና ደስታም ይገነባል፤ እናም የፈለገውንም ያጠፋል፣ እናም

፮ሀ ኤተር ፫÷፲፪።
፯ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፱ሀ ት. እና ቃ. ፷፩÷፴፯።
ለ ማቴ. ፳፰÷፳።
፷፫ ፪ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።

ነፍስንም ወደ ገሀነም ይጥል ዘንድ ይቻለዋል።

፭ እነሆ፣ እኔ ጌታ ድምጼን አሰማለሁ፣ እና ይህም ይከበራል።

፮ ስለዚህ፣ በእውነት እላለሁ፣ ኃጢአተኛው ያድምጥ፣ እናም አመጸኛውም ይፍራ እናም ይንቀጥቀጥ፤ እናም የማያምኑትም ከንፈሮቻቸውን ይያዙ፣ እንደ [ሀ]አውሎ ነፋስ [ለ]የቁጣው ቀን ይመጣባቸዋልና፣ እናም ስጋ ለባሽ ሁሉ እኔ እግዚአብሔር እንደሆንኩኝም [ሐ]ያውቃሉ።

፯ እናም ምልክቶችን የሚሻ [ሀ]ምልክቶችን ያገኛል፣ ነገር ግን ለደህንነት አይሆንለትም።

፰ እውነት እላችኋለሁ፣ በመካከላችሁ ምልክቶችን የሚሹ አሉ፣ እናም እንደነዚህ አይነቶችም ከመጀመሪያ ጀምሮም ነበሩ።

፱ ነገር ግን፣ እነሆ፣ እምነት በምልክቶች አይመጣምና፣ ነገር ግን ምልክቶች የሚያምኑትን ይከተሏቸዋል።

፲ አዎን፣ ምልክቶች የሚመጡት [ሀ]በእምነት ነው፣ በሰዎች ፈቃድ ወይም ፍላጎት ሳይሆን፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

፲፩ አዎን፣ ምልክቶች ታላቅ ስራዎች ይሆኑ ዘንድ [ሀ]በእምነት ይመጣሉ፣ ምክንያቱም ያለ እምነት ማንም ሰው እግዚአብሔርን ሊያስደስት አይችልምና፤ እናም እግዚአብሔር የተቆጣበት በእርሱም አይደሰትም፤ ስለዚህ፣ ለእንደእነዚህ አይነቶች፣ [ለ]በቁጣ [ሐ]ከእርግማን በቀር፣ ምንም ምልክቶችን አያሳይም።

፲፪ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ፣ በመካከላችሁ ለእምነት ምልክቶችን እና ድንቆችን ለሰዎች ጥቅም እና ለክብሬ ሳይሆን ለፈቃዳቸው በሚሹ ላይ አልተደሰትኩም።

፲፫ ይሁን እንጂ፣ ትእዛዛትን ሰጥቻለሁ፣ እናም ብዙዎችም ከትእዛዛቴ ፈቀቅ ብለዋል እናም አልጠበቋቸውም።

፲፬ በመካከላችሁም [ሀ]ዘማዊ እና ዘማዊት ነበሩ፤ አንዳንዶቹም ከእናንተ ተለይተዋል፣ እናም ከዚህ በኋላ የሚገለጡት ሌሎቹም ከእናንተ ጋር ቀርተዋል።

፲፭ እንደዚህ አይነቶቹ ይጠንቀቁ እናም ፈጥነውም ንስሀ ይግቡ፣ አለበለዚያም ፍርድ እንደ አጥማጅ ይመጣባቸዋል፣ እናም ሞኝነታቸውም በግልፅ ይታያል፣ እናም በህዝብ አይኖች ውስጥ ስራዎቻቸውም ይከተሏቸዋል።

፲፮ እናም፣ አስቀድሜ እንደተናገርሁ፣ በእውነት እንዲህ እላችኋላሁ፣ ሴትን [ሀ]የተመለከተ እናም [ለ]የተመኛትም፣ ወይም ማናቸውም በልባቸው [ሐ]ቢያመነዝሩ፣ መንፈስም አይኖራቸውም፣ ነገር ግን እምነትን ይክዳሉ እናም ይፈራሉ።

፲፯ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ እንዳልኩት፣ [ሀ]የሚፈሩና የማያምኑ፣ እናም [ለ]የሐሰተኞችም ሁሉ፣ እናም ሀሰትን የሚወዱ እና [ሐ]የሚዋሹ፣ እና የሴሰኞችም፣ እና የአስማተኞችም፣ እና ጣዖትንም የሚያመልኩ፣ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል [መ]ባሕር ነው፤ ይኸውም [ሠ]ሁለተኛው ሞት ነው።

፲፰ በእውነት አላለሁ፣ እነርሱ [ሀ]በመጀመሪያው ትንሳኤ ስፍራ አይኖራቸውም።

፲፱ እናም አሁን እነሆ፣ እኔ ጌታ እንዲህ እላችኋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች በመካከላችሁ ስላሉ፣ [ሀ]ትጸድቁ ዘንድ አይቻላችሁም።

፮ ሀ ኤር. ፴፥፳፫።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፤ ፍትህ።
ሐ ኢሳ. ፵፱፥፳፮።
፯ ሀ ት. እና ቃ. ፵፮፥፱። ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲ ሀ ሞሮኒ ፯፥፴፯። ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፲፩ ሀ ዕብ. ፲፩፥፮።
ለ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፭።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፳፬–፳፭።
፲፮ ሀ ማቴ. ፭፥፳፯–፳፰፤ ት. እና ቃ. ፵፪፥፳፫–፳፮።
ለ ቅ.መ.መ. ምኞት።
ሐ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
፲፯ ሀ ራዕ. ፳፩፥፰።
ለ ቅ.መ.መ. ሐሰት።
ሐ ራዕ. ፳፪፥፲፭፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፫።
መ ራዕ. ፲፱፥፳፤ ፪ ኔፊ ፱፥፰–፲፱፡ ፳፮፤ ፳፰፥፳፫፤ ያዕቆ. ፮፥፲፤ አልማ ፲፪፥፲፮–፲፰፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፴፮። ቅ.መ.መ. ሲዖል።
ሠ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
፲፰ ሀ ራዕ. ፳፥፮።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ማፅደቅ፣ ከበደል ነጻ መሆን።

፳ ይሁን እንጂ፣ በእምነት [ሀ]የጸናው እና ፈቃዴንም የሚያደርገው፣ እርሱ ያሸንፋል፣ እናም በክብር የመለወጥ ቀን ሲመጣም [ለ]ውርሱን ይቀበላል

፳፩ እንዲሁም፣ ሙሉ ታሪኩን ገና ያልተቀበላችሁትን፣ ለሐዋሪያቴ [ሀ]በተራራው ላይ ባሳየሁት ስርዓት [ለ]ምድር [ሐ]በክብር ስትለወጥም፣ ውርሱን ይቀበላል።

፳፪ እናም አሁን፣ በእውነት እላችኋላሁ፣ እንደተናገርኳችሁ ፈቃዴን አሳውቃችኋለሁ፣ እነሆ እንድታውቁትም አደርጋለሁ፣ ይህም በትእዛዝ አይደለም ምክንያቱም ትእዛዛቴን የማያከብሩ ብዙዎች አሉና።

፳፫ ነገር ግን ትእዛዛቴን ለሚጠብቀው ለእርሱ የመንግስቴን [ሀ]ሚስጥራት እሰጠዋለሁ፣ እና በእርሱም ውስጥ ለዘለአለም ሕይወት [ለ]የሚፈልቅ [ሐ]የህያው ውኃ ምንጭ ይሆናል።

፳፬ እናም አሁን፣ እነሆ ይህም ጌታ አምላካችሁ ለቅዱሳኑ ያለው ፍላጎት ይህ ነው፣ ችኅፈር የሚያመጣው ግራ መጋባት እንዳይኖር፣ በፍጥነት ሳይሆን፣ በፅዮን ምድር ራሳቸውን ይሰብስቡ።

፳፭ እነሆ፣ [ሀ]የፅዮንን ምድር—እኔ ጌታ በእጆቼ ይዣታለሁ፤

፳፮ ይሁን እንጂ፣ እኔ ጌታም [ሀ]የቄሣርን ለቄሣር አስረክቤአለሁ።

፳፯ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ በአለም ትጠቀሙ ዘንድ፣ በአለምም የእኛ ነው የምትሉት እንዲኖራችሁ፣ እነርሱም በቁጣም እንዳይነሳሱባቸው፣ መሬቶች እንድትገዙ ፍቃዴ ነው።

፳፰ [ሀ]ሰይጣንም፣ ደምን እስከማፍሰስ ድረስም፣ እንዲያስቆጣቸው በልቦቻቸው ውስጥ ቁጣን ያነሳሳል።

፳፱ ስለዚህ፣ የፅዮን ምድርም በመግዛት ወይም በደም በስተቀር አይገኝም፣ አለበለዚያም ለእናንተ ምንም ውርስ የላችሁም።

፴ እና በመግዛትም ቢሆን፣ እነሆ የተባረካችሁ ናችሁ፤

፴፩ እናም በደምም ቢሆን፣ ደምን ለማፍሰስ ስለተከለከላችሁ፣ እነሆ፣ ጠላቶቻችሁ ያጠቋችኋል፣ እናም ከከተማ ወደ ከተማም፣ ከምኩራብ ወደ ምኩራብ ትቀጣላችሁ፣ እናም ውርስን ለመቀበል ጥቂቶች ብቻ ይቀራሉ።

፴፪ እኔ ጌታም በኃጢአተኞቹ ተቆጣሁ፤ መንፈሴንም ከምድር ኗሪዎች እከለክላለሁ።

፴፫ በቁጣዬም ማልሁ፣ እናም በምድርም ፊት ላይ [ሀ]ጦርነቶችን አወጅኩኝ፣ እናም ኃጢአተኛውም ኃጢአተኛውን ይገድላል፣ እናም ፍርሀትም በእያንዳንዱ ሰው ላይ ይመጣል፤

፴፬ እናም [ሀ]ቅዱሳንም ደግመው አያመልጡም፤ ይሁን እንጂ፣ እኔ ጌታ ከእነርሱ ጋር ነኝ፣ እና ከአባቴ ፊትም ከሰማይ [ለ]እወርዳለሁ እናም [ሐ]ኃጢአተኞቹንም በማይጠፉ [መ]እሳት አነዳቸዋለሁ።

፴፭ እናም እነሆ፣ ይህም ገና አይደለም፣ ነገር ግን በቅርቡ የሚሆን ነው።

፴፮ ስለዚህ፣ በምድር ላይ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እኔ ጌታ በማወጄ ምክንያት፣ የእኔ ቅዱሳን ራሳቸውን በፅዮን ምድር መሰብሰባቸው ፍቃዴ ነው፤

፴፯ እናም እያንዳንዱ ሰው [ሀ]ፅድቅን በእ

፳ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፴፭።
ለ ማቴ. ፭፥፭፤
ት. እና ቃ. ፶፱፥፪፤
፹፰፥፳፭–፳፮።
፳፩ ሀ ማቴ. ፲፯፥፩–፫።
ለ ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።
ሐ ቅ.መ.መ. አለም— የአለም መጨረሻ።
፳፫ ሀ አልማ ፲፪፥፱–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፩፤
፹፬፥፲፱፤ ፻፯፥፲፰–፲፱።
ለ ዮሐ. ፬፥፲፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ህያው ውሀ።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፳፮ ሀ ሉቃ. ፳፥፳፭፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፩–፳፫።
ቅ.መ.መ. መንግስት።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጦርነት።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ለ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ሐ ማቴ. ፫፥፲፪፤
፪ ኔፊ ፳፮፥፮፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፯፤
፷፬፥፳፬፤ ፻፩፥፳፫–፳፭፣ ፷፮።
ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
መ ቅ.መ.መ. እሳት።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።

ጆቹ እና ታማኝነትን በወገቡ ይውሰድ፣ እናም የማስጠንቀቂያ [ለ]ድምፅም ወደ ምድር ኗሪዎች ይሰማ፤ እናም በቃል እና ፈጥኖ በመሄድ በስደት በኃጢአተኞች ላይ [ሐ]ክፉ ነገሮች እንደሚመጡ ይገለጹ።

፴፰ ስለዚህ፣ በከርትላንድ ውስጥ በዚህ እርሻ የሚኖሩት ደቀ መዛሙርቴ የስጋዊ ጉዳያቸውን ያዘጋጁ።

፴፱ አገልጋዬ ታይተስ ቢሊንግስ፣ በሚመጣው ጸደይ፣ ትእዛዝ እስከምሰጣቸው ድረስ ከማይሄዱት ለራሴ ከምጠብቃቸው በስተቀር በዚህ ስፍራ ከሚኖሩት ጋር፣ ወደ ፅዮን ምድር ለመጓዝ መዘጋጀት እንዲችል፣ ሀላፊነት ያለበትን መሬትን ይሸጥ።

፵ እናም የሚቀረውም ገንዘብ ሁሉ፣ ብዙም ይሁን ጥቂት ግድ የለኝም፣ ወደ ፅዮን ምድር እንዲቀበሉ ለሾምኳቸው ይላክ።

፵፩ እነሆም እኔ ጌታ፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ወደ ፅዮን ምድር የሚሄዱትን፣ እና በዚህም የሚቀሩትን ደቀ መዛሙርቴን [ሀ]ለመለየት የሚያስችለውን ሀይል እሰጠዋለሁ።

፵፪ እናም አገልጋዬ ኒውል ኬ ውትኒ የግምጃ ቤቱን፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ የግምጃ ቤቱን በትንሽ ወቅት እንደያዘ ይቀጥል።

፵፫ ይሁን እንጂ፣ ለመስጠት የሚችለውን ገንዘብ ሁሉ ወደ ፅዮን ምድር እንዲላክ ይስጥ።

፵፬ እነሆ፣ እነዚህ ነገሮች በእጆቹ ውስጥ ናቸው፣ በጥበብም ያድርጋቸው።

፵፭ በእውነትም እላለሁ፣ ለሚቀሩትም ደቀ መዛሙርት ወኪል እንዲሆንም ይሾም፣ እናም ለዚህ ሀይልም ይሾም፤

፵፮ እናም አሁን፣ ከአገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ጋር፣ እነዚህን ነገሮች በማብራራት፣ ፈጥኖም ቤተክርስቲያኖችን ይጎብኝ። እነሆ፣ ገንዘብን እንደመራሁት ማግኘቱ ፍቃዴ ነው።

፵፯ [ሀ]ታማኝ የሆነው እና የሚጸናውም አለምን ያሸንፋል።

፵፰ ወደ ፅዮን ምድር ሀብትን የላከው በዚህ አለም [ሀ]ውርስን ይቀበላል፣ እናም ስራዎቹ ይከተሉታል፣ እናም በሚመጣው አለምም ዋጋው ይሰጠዋል።

፵፱ አዎን፣ እናም፣ ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ [ሀ]የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው፣ ጌታ ሲመጣም፣ እና አሮጌው ነገሮች [ለ]አልፈው፣ እናም ሁሉም ነገሮች አዲስ ሲሆኑም፣ ከሞት [ሐ]ይነሳሉ እናም ከዚህም በኋላ [መ]አይሞቱምና፣ እናም በቅዱስ ከተማውም ከጌታም ውርስን ይቀበላሉ።

፶ እናም ጌታ ሲመጣ የሚኖረው፣ እና ሀይማኖትን የጠበቀውም፣ እርሱ [ሀ]የተባረከ ነው፤ ይሁን እንጂ በሰው እድሜ [ለ]እንዲሞትም ተወስኖለታል።

፶፩ ስለዚህ፣ ልጆች እድሜአቸው እስኪገፉ ድረስም [ሀ]ያድጋሉ፤ ሽማግሌዎችም ይሞታሉ፤ ነገር ግን በምድርም ትቢያ ውስጥ አያንቀላፉም፣ ነገር ግን በቅጽበት ዓይንም [ለ]ይለወጣሉ።

፶፪ ስለዚህ፣ ለዚህም ምክንያት ነው ሀዋሪያት ለአለም ስለሙታን ትንሳኤ የሰበኩት።

፶፫ እነዚህ ነገሮች ወደፊት መመልከት ያለባችሁ ነገሮች ናቸው፤ እናም፣ እንደ ጌታ አነጋገር፣ እናም በሚመጣው ጊዜም፣ እንዲሁም በሰው ልጅ ምፅዓት ቀን፣ አሁንም [ሀ]ቀርቧልና።

፶፬ እናም እስከዚያም ሰአት ድረስ በብልህ

፴፯ ለ ት. እና ቃ. ፩፥፬።
ሐ ኢሳ. ፵፯፥፲፩።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፵፯ ሀ ሞዛያ ፪፥፵፩፤
ት. እና ቃ. ፮፥፲፫።
፵፰ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፲፰።
፵፱ ሀ ራዕ. ፲፬፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፵፬–፵፯።
ለ ፪ ቆሮ. ፭፥፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
መ ራዕ. ፳፩፥፬፤
አልማ ፲፩፥፵፭፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፯።
ቅ.መ.መ. የማይሞት፣
አለሚችነት።
፶ ሀ ቅ.መ.መ. መባረክ፣
የተባረከ፣ በረከት።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
፶፩ ሀ ኢሳ. ፷፭፥፳–፳፪፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፰፤
፻፩፥፳፱–፴፩።
ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፶፩–፶፪፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፪።
፶፫ ሀ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፭።

መካከል ሰነፎች [ሀ]ደናግል ይኖራሉ፤ እናም በዚያም ሰዓት ጻድቃን ከኃጢአተኞቹ ሁሉ የሚለዩበት ይመጣል፤ እናም በዚያም ቀን ኃጢአተኞቹን [ለ]ነቅለው እንዲያወጡ እና በማይጠፋው እሳት ውስጥ እንዲወረውሯቸው መላእክቴን እልካለሁ።

፶፭ እናም አሁን እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ ጌታ በአገልጋዬ [ሀ]ስድኒ ሪግደን አልተደሰትኩም፤ በልቡም ራሱን [ለ]ከፍ ከፍ ያደርጋል፣ እናም ምክርንም አልተቀበለምና፣ ነገር ግን መንፈስንም አሳዝኗል፤

፶፮ ስለዚህ የእርሱ [ሀ]ፅሑፍ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት የለውም፣ እናም ሌላም ይጻፍ፤ እናም ጌታ ይህን ካልተቀበለውም፣ እነሆ በሾምኩበት ሹመትም አይቆምም።

፶፯ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በየዋህነት ኃጢአተኞችን ንስሀ እንዲገቡ [ሀ]ለማስጠንቀቅ በልቦቻቸው ፍላጎት [ለ]ያላቸው፣ በዚህ ሀይልም ይሾሙ።

፶፰ ይህም፣ የብዙ ቃላት ቀን ሳይሆን፣ የማስጠንቀቂያ ቀን ነውና። እኔ ጌታም በመጨረሻዎቹ ቀናት ውስጥ አይዘበትብኝምና።

፶፱ እነሆ፣ እኔም ከበላይ ነኝ፣ እናም በበታችም ሀይሌ ይኖራል። ከሁሉም በላይ፣ እና በሁሉም የምሰራ፣ እናም በሁሉም የምኖር ነኝ፣ እናም ሁሉንም [ሀ]እመረምራለሁ፣ እናም ሁሉም ነገሮች ለእኔ ተገዢ የሚሆኑበትም ቀን ይመጣል።

፷ እነሆ፣ እኔ [ሀ]አልፋና ኦሜጋ፣ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ነኝ።

፷፩ ስለዚህ፣ ሁሉም ሰዎች እንዴት [ሀ]ስሜን በከንፈሮቻቸው እንደሚይዙ ይጠንቀቁ—

፷፪ ምክንያቱም እነሆ፣ እውነት እላለሁ፣ የጌታን ስም በከንቱ የሚጠቀሙ፣ እናም ያለስልጣን የሚጠሩ፣ በዚህ እርግማን ውስጥ ያሉ ብዙዎች አሉ።

፷፫ ስለዚህ፣ ቤተክርስቲያን ለኃጢአታቸው ንስሀ ይግቡ፣ እናም እኔ ጌታ የእኔ አደርጋቸዋለሁ፤ አለበለዚያም ይቆረጣሉ።

፷፬ ከላይ የሚመጣውእርሱ [ሀ]ቅዱስ እንደሆነ፣ እናም በጥንቃቄ እና በመንፈስም ቁጥጥር [ለ]መነገር እንዳለበትም አስታውሱ፤ እና በዚህም ውስጥ እርግማን የለም፣ እናም መንፈሱን የምትቀበሉት በጸሎት [ሐ]በኩል ነው፤ ስለዚህ፣ ይህ ባይሆን በእርግማን ይቀራሉ።

፷፭ [ሀ]በጸሎት በመንፈስ እንደተማሩት፣ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ስድኒ ሪግደን ቤትን ይፈልጉባቸው።

፷፮ እነዚህ [ሀ]ከሁሉም ይልቅ የዘለአለም [ለ]ክብርን፣ አለበለዚያም ታላቅን እርግማን፣ ይቀበሉ ዘንድ፣ እነዚህንም ነገሮች በትዕግስት ማሸነፍ ይቻል ዘንድ ነውና። አሜን።

ክፍል ፷፬

መስከረም ፲፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች የተሰጠ ራዕይ። በሚዙሪ ውስጥ እያለ ለሌላ ጊዜ ያስተላለፈውን የመፅሐፍ ቅዱስን ትርጉም ስራ ደግሞ ለመጀመር፣ ነቢዩ ወደ ሀይረም ኦሀዮ ለመሄድ እየተዘጋጀ ነበር። ወደ ፅዮን (ሚዙሪ) እንዲ

፶፬ ሀ ማቴ. ፳፭፥፩–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፮–፶፱።
ለ ሞዛያ ፲፮፥፪።
፶፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ለ ቅ.መ.መ. ኩራት።
፶፮ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፶።
፶፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥፲፬–፲፭።
ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣
ማስጠንቀቂያ፤
የሚሲዮን ስራ።
ለ ት. እና ቃ. ፬፥፫–፯።
፶፱ ሀ ፩ ቆሮ. ፪፥፲።
፷ ሀ ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
፷፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማራከስ።
፷፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
ለ ቅ.መ.መ. ማክበር።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፪፥፲፬።
፷፭ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፷፮ ሀ ፪ ቆሮ. ፬፥፲፯።
ለ ሮሜ ፰፥፲፰፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፬፤
፻፴፮፥፴፩።

ጓዙ የታዘዙት ወንድሞችም በጥቅምት ለመሄድ በቅንነት እየተዘጋጁ ነበር። በዚህ ስራ በበዛበት ጊዜ፣ ይህን ራዕይ ተቀብሎ ነበር።

፩–፲፩፣ በራሳቸው ታላቅ ኃጢአት እንዳይቀር፣ ቅዱሳን እርስ በራሳቸውም ይቅር እንዲባባሉ ታዘዋል፤ ፲፪–፳፪፣ ንስሀ የማይገቡት በቤተክርስቲያኗ ለፍርድ ይቅረቡ፤ ፳፫–፳፭፣ አስራትን የሚከፍል በጌታ መምጫ ጊዜ አይቃጠልም፤ ፳፮–፴፪፣ ቅዱሳን እዳን እንዲያስወግዱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፤ ፴፫–፴፮፣ አመጸኞች ከፅዮን ውስጥ ይቆረጣሉ፤ ፴፯–፵፣ ቤተክርስቲያኗ አገሮችን ትፈርዳለች፤ ፵፩–፵፫፣ ፅዮን ታብባለች።

፩ እነሆ፣ ጌታ አምላካችሁ እንዲህ ይላችኋል፣ አቤቱ እናንት የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ፣ አድምጡ እናም ስሙ፣ እናም እኔ እናንተን በተመለከተ ያለኝን ፈቃድ ተቀበሉ።

፪ እውነት እላችኋለሁ፣ አለምን [ሀ]እንድ ታሸንፉ እፈልጋለሁ፤ ስለዚህ፣ በእናንተ ላይ [ለ]ርህራሄ ይኖረኛል።

፫ በመካከላችሁ ኃጢአት የሰሩ አሉ፤ ነገር ግን በእውነት እላለሁ፣ አንድ ጊዜ፣ [ሀ]ለክብሬ ስል፣ እናም ለነፍሳት ደህንነት ስል፣ ለኃጢአታችሁ [ለ]ይቅርታን አድርጌአለሁ።

፬ ለእናንተም መሀሪ እሆናለሁ፣ መንግስትንም ሰጥቻችኋለሁና።

፭ [ሀ]ስርዓቶቼን እስካከበረ ድረስ፣ በህይወት እያለ፣ የመንግስቱ የሚስጥራት [ለ]ቁልፎችም ከአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ በመሰረትኩበት መንገድ፣ አይወሰድበትም።

፮ በከንቱ በእርሱ ላይ ምክንያት የሚፈልጉበት አሉ፤

፯ ይሁን እንጂ፣ እርሱም ኃጢአትን ሰርቷል፤ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ኃጢአታቸውን በፊቴ የሚናዘዙ፣ እና [ሀ]ይቅርታን የሚጠይቁ፣ [ለ]ለሞት ኃጢአትን ላልሰሩት፣ እኔ ጌታ [ሐ]ይቅርታ አደርግላቸዋለሁ።

፰ ደቀ መዛሙርቶቼ፣ በቀደሙት ቀናት፣ እርስ በርሳቸው [ሀ]ምክንያት ይፈልጉ ነበር እና በልቦቻቸውም ይቅርታን አያደርጉም ነበር፤ እናም በዚህ ክፉ ነገርም ተሰቃይተው እናም በምሬት [ለ]ተቀጥተው ነበር።

፱ ስለዚህ፣ እርስ በርሳችሁ [ሀ]ይቅርታን መስጠት አለባችሁ እላችኋለሁ፤ ወንድሙ ለተላለፈው [ለ]ይቅርታን የማይሰጠው በጌታ ፊት ይኮነናል፤ ምክንያቱም በእርሱ ታላቁ ኃጢአት ይኖራልና።

፲ እኔ ጌታ [ሀ]ይቅር የምለውን ይቅር እላለሁ፣ ነገር ግን እናንተ ለሁሉም ሰዎች [ለ]ይቅርታን ታደርጉ ዘንድ ይጠበቅባችኋል።

፲፩ እና በልባችሁም እንዲህ ማለት ይገባችኋል—በእኔ እና በአንተ መካከል እግዚአብሔር [ሀ]ይፍረድ፣ እናም [ለ]እንደስራህም ይከፍልሀልና።

፲፪ እናም ለኃጢአቶቹ ንስሀ ያልገባውም፣ እና ያልተናዘዘውንም፣ [ሀ]በቤተክርስቲያኗ ፊት አምጡት፣ እናም በቅዱሳን መጻህፍት ውስጥ በትእዛዝም ሆነ በራዕይ እንደሚላችሁም እንዲሁ አድርጉበት።

፲፫ እናም ይህንንም የምታደርጉት ለእግ

፷፬ ፪ሀ ፩ ዮሐ. ፭፥፬።
ለ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
፫ሀ ሙሴ ፩፥፴፱።
ለ ኢሳ. ፵፫፥፳፭።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ለ ት. እና ቃ. ፳፰፥፯፤ ፹፬፥፲፱።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፯ሀ ዘኁል. ፭፥፮–፯፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፳፤ ፶፰፥፵፫።
ቅ.መ.መ. መናዘዝ።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፵፩–፵፪።
ሐ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት፤ ይቅርታ ማድረግ።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፱ሀ ማር. ፲፩፥፳፭–፳፮፤ ት. እና ቃ. ፹፪፥፩።
ለ ማቴ. ፮፥፲፬–፲፭፤ ኤፌ. ፬፥፴፪።
፲ሀ ዘፀአ. ፴፫፥፲፱፤ አልማ ፴፱፥፮፤ ት. እና ቃ. ፶፮፥፲፬።
ለ ሞዛያ ፳፮፥፳፱–፴፩።
፲፩ሀ ፩ ሳሙ. ፳፬፥፲፪።
ለ ፪ ጢሞ. ፬፥፲፬።
፲፪ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፹–፺፫።

ዚአብሔር ክብር ነው፣ ይቅርታ ስላላደረጋችሁ፣ ወይም ርህራሄ ስለሌላችሁ ሳይሆን፣ ነገር ግን በህግ ፊት ይህንኑ ለማረጋገጥ፣ ህግን የሰጣችሁን እንዳታስቀይሙ ነው—

፲፬ እውነት እላለሁ፣ በእነዚህ ምክንያቶች እነዚህን ነገሮች አድርጉ።

፲፭ እነሆ፣ እኔ ጌታ አገልጋዬ በነበረው ኤዝራ ቡዝ፣ እና ደግሞም በአገልጋዬ አይዛክ ሞርሊ ተቆጥቻለሁ፣ ምክንያቱም ህግንም ይሁን ትእዛዝን አላከበሩምና።

፲፮ በልቦቻቸው ክፉትን ፈልገዋል፣ እናም እኔ ጌታ መንፈሴን ከእነርሱ አርቄአለሁ። ክፉት የሌለባቸውን ነገሮች እንደ ክፉ [ሀ]ኮንነዋልና፤ ይሁን እንጂ፣ አገልጋዬን አይዛክ ሞርሊን ይቅር ብዬዋለሁ።

፲፯ እና ደግሞም አገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ፣ እነሆ፣ ኃጢአትን ሰርቷል፣ እናም [ለ]ሰይጣንም ነፍሱን ሊያጠፉ ይሻል ነገር ግን፣ እነዚህን ነገሮች ሲያውቋቸው፣ እናም ለክፉታቸው ንስሀ ሲገቡ፣ ይቅርም ይሰጣቸዋል።

፲፰ እናም አሁን፣ እውነትም እላለሁ፣ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት፣ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ወደ ሀላፊነቱ፣ እና በፅዮን ምድር ወዳለው ወኪሉ፣ ይመለስ ዘንድ ፍቃዴ ነው፤

፲፱ እናም፣ እንዳይጠፉም፣ ያያቸውን እና የሰማቸውን ነገሮች ደቀ መዛሙርቴ እንዲያውቋቸው ያደርጋል። እናም በእዚህም ምክንያት እነዚህን ነገሮች ተናግሬአለሁና።

፳ እና እንዲህም እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ አይዛክ ሞርሊ ለመሸከም ከሚችለው በላይ [ሀ]እንዳይፈተን፣ እናም ሊጎዳችሁም የስህተት ምክር እንዳይሰጥም፣ የእርሻ ቦታው ይሸጥ ዘንድ አዘዝኩኝ።

፳፩ አገልጋዬ ፍሬድሪክ ጂ ዊልያምስ የእርሻ ቦታውን መሸጡ የእኔ ፈቃድ አይደለም፣ እኔ ጌታ፣ ኃጢአተኞችን በማልጥልበት አምስት አመት ጊዜያት፣ በዚህም የተወሰኑትን አድን ዘንድ፣ በከርትላንድ ምድር የምሽግ ስፍራን ለመጠበቅ እፈልጋለሁና።

፳፪ እናም ከዚያ ቀን በኋላ፣ እኔ ጌታ ወደ ፅዮን ምድር በተከፈተ ልብ የሚሄደውን ማንንም እንደ [ሀ]ጥፋተኛ አልቆጥርም፤ እኔ ጌታ የሰው ልጆችን [ለ]ልብ እሻለሁና።

፳፫ እነሆ፣ አሁን እስከ ሰው ልጅ [ሀ]ምፅዓት ድረስ ቀኑም [ለ]ዛሬ ተብሎ ይጠራል፣ እናም እውነትም [ሐ]የመስዋዕት ቀን ነው፣ እናም ህዝቤ አስራትን የሚከፍሉበትም ቀን ነው፤ [መ]አስራትን የሚከፍልም በእርሱ ምፅዓት ጊዜ [ሠ]አይቃጠልም።

፳፬ ከዛሬ በኋላ እንደ ምድጃ እሳት [ሀ]የሚነድ ቀን ይመጣልና—ይህም እንደ ጌታ አባባል ነው—እውነትም እላለሁ፣ [ለ]ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፤ እናም አቃጥላቸዋለሁ፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነኝና፤ እናም [ሐ]በባቢሎን ውስጥ የሚቀሩትንም አላድንም።

፳፭ ስለዚህ፣ ካመናችሁኝ፣ ዛሬ ተብሎ በሚጠራው ቀን ትሰራላችሁ።

፳፮ እናም አገልጋዬ [ሀ]ኒወል ኬ ውትኒ እና ስድኒ ጊልበርት በዚህ ያላቸውን ንብረት እና [ለ]ግምጃዎቻቸውን መሸጣቸው አስፈላጊ አይደለም፤ በዚህ ስፍራ ቤተክርስቲ

፲፮ ሀ ፪ ኔፊ ፲፭፥፳፤
ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፲፮።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣ ኤድዋርድ።
ለ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. በደል።
ለ ዘፀአ. ፴፭፥፭፤ ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፭፤ ፷፬፥፴፬።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ት. እና ቃ. ፵፭፥፮፤ ፷፬፥፳፬–፳፭።
ሐ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
መ ሚል. ፫፥፲–፲፩።
ቅ.መ.መ. አስራት፣ አስራት መክፈል።
ሠ ሚል. ፬፥፩፤ ፫ ኔፊ ፳፭፥፩፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፯።
፳፬ ሀ ኢሳ. ፷፮፥፲፭–፲፮።
ቅ.መ.መ. ምድር—ምድርን ማፅዳት፤ አለም—የአለም መጨረሻ።
ለ ሚል. ፫፥፲፭፤ ፪ ኔፊ ፲፪፥፲፪፤ ፳፫፥፲፩።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፥፲፮።
ቅ.መ.መ. ባቢሎን።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ዊትኒ፣ ኒውል ኬ።
ለ ት. እና ቃ. ፶፯፥፰።

ያን የሚቀሩት ወደ ፅዮን ምድር ከመሄዳቸው በፊት ይህም ጥበብ አይደለምና።

፳፯ እነሆ፣ በህግጋቴ ውስጥ በጠላታችሁ ዘንድ [ሀ]እዳ አትግቡ ይላል፣ ወይም የተከለከለ ነው፤

፳፰ ነገር ግን እነሆ፣ በሚያስደስተው ጊዜ ጌታ አይወስድም፣ እናም መልካም በመሰለውም ይከፍላል አልተባለም።

፳፱ ስለዚህ፣ እናንት ወኪል ስለሆናችሁ፣ በጌታ መልእክት ትጓዛላችሁ፤ እናም እንደ ጌታ ፈቃድ በኩል የምታደርጉት ነገር ሁሉ የጌታ ስራ ነውና።

፴ እናም በእነዚህም የመጨረሻ ቀናት ለቅዱሳኑ፣ በፅዮን ምድር [ሀ]ውርስን እንዲያገኙ ታደርጉ ዘንድ ተሹማችኋል።

፴፩ እናም እነሆ፣ [ሀ]ቃላቴ እርግጥ በመሆናቸውና [ለ]ስለማይወድቁ፣ እነርሱም እንደሚያገኟቸው እኔ ጌታ እገልፅላችኋለሁ።

፴፪ ነገር ግን ሁሉም ነገሮች በጊዜአቸው ይከናወኑ ዘንድ ግድ ነው።

፴፫ ስለዚህ፣ መልካም ሥራን ትሰሩ ዘንድ [ሀ]አትታክቱ፣ የታላቅ ስራን መሰረት እየገነባችሁ ነውና። እናም [ለ]ከትትንሽ ነገሮች ታላቅ ነገሮች ይወጣሉና።

፴፬ እነሆ፣ ጌታ [ሀ]ልብን እና መልካም ፈቃድ ያለውን አዕምሮ [ለ]ይሻል፤ እናም ፈቃድ ያለው እና [ሐ]ታዛዡ የሆነው እርሱ በእነዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናት የፅዮንን ምድርን በረከት ይበላሉ።

፴፭ እናም [ሀ]አመጸኞችም ከፅዮን ምድር [ለ]ይቆረጣሉ፣ እናም ተለይተው ይሄዳሉ፣ እናም ምድሩንም አይወርሱም።

፴፮ በእውነት እላለሁ፣ አመጸኞቹ [ሀ]ከኤፍሬም ወገን አይደሉም፣ ስለዚህም ይነቀላሉ።

፴፯ እነሆ፣ እኔ ጌታ በእነዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናት ቤተክርስቲያኔን በኮረብታ ላይ እንደተቀመጠ ዳኛ በአህዛብ ትፈርድ ዘንድ እንድትቀመጥ ሰርቻታለሁ።

፴፰ እንዲህም ይሆናል የፅዮን ኗሪዎች ፅዮንን በሚመለከቱ ነገሮችን ላይ [ሀ]በፍርድ ይቀመጣሉ።

፴፱ እናም ሐሰተኞች እና ግብዞች በእነርሱ ይፈተናሉ፣ እናም [ሀ]ሐዋርያት እና ነቢያት ያልሆኑትም ይታወቃሉ።

፵ እናም [ሀ]ዳኛ የሆነው [ለ]ኤጲስ ቆጶስ እና አማካሪዎቹም፣ [ሐ]በሀላፊነታቸው ታማኝ ካልሆኑ፣ ይኮነናሉ፣ እናም [መ]ሌሎችም በእነርሱ ስፍራ ይተከላሉ።

፵፩ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ [ሀ]ፅዮን ታብባለች፣ እናም የጌታም [ለ]ክብር በእርሷ ላይ ያርፋል፤

፵፪ እናም እርሷም ለህዝብ [ሀ]ምልክት ሆና ትቆማለች፣ እናም ከሰማይ በታች ካሉት ሀገሮች ውስጥም ወደ እርሷ ይመጣሉ።

፵፫ እናም በእርሷ ምክንያት የአለም ሀገሮች ሁሉ [ሀ]የሚንቀጠቀጡበት፣ እናም በአስፈሪዎቿም ምክንያት የሚደነግጡበት ቀን ይመጣል። ጌታም ይህን ተናግሯል። አሜን።

፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. እዳ።
፴ ሀ ት. እና ቃ. ፳፫፥፶፰።
፴፩ ሀ ማር. ፲፫፥፴፩፤
፪ ኔፊ ፴፩፥፲፭፤
ት. እና ቃ. ፩፥፴፯–፴፰።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፫።
፴፫ ሀ ገላ. ፮፥፱።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፫፥፲፮።
፴፬ ሀ ዘዳግ. ፴፪፥፵፮፤
ኢያ. ፳፪፥፭፤
ሞር. ፱፥፳፯።
ቅ.መ.መ. ልብ።
ለ ሚክ. ፮፥፰።
ሐ ኢሳ. ፩፥፲፱።
ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ት. እና ቃ. ፶፩፥፭፤
፶፥፰–፱፤ ፶፮፥፫።
ቅ.መ.መ. ውግዘት።
፴፮ ሀ ዘዳግ. ፴፫፥፲፮–፲፯።
፴፯ ሀ ኢሳ. ፪፥፫–፬፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፳፩።
፴፱ ሀ ራዕ. ፪፥፪።
ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
፵ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፲፯፤
፻፯፥፸፪–፸፬።
ለ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
ሐ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣
መጋቢነት።
መ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፱–፻።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፯፤
፹፬፥፬–፭፤ ፺፯፥፲፭–፳።
ቅ.መ.መ. ክብር።
፵፪ ሀ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፵፫ ሀ ኢሳ. ፷፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፺፯፥፲፰–፳።

ክፍል ፷፭

ጥቅምት ፴፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ስለጸሎት የተሰጠ ራዕይ።

፩–፪፣ የእግዚአብሔር የመንግስቱ ቁልፎች በምድር ለሰው ተሰጥተዋል፣ እናም ወንጌሉም አሸናፊ ይሆናል፤ ፫–፮፣ የአንድ ሺህ ዘመን መንግስተ ሰማያት ይመጣል እናም በምድርም በእግዚአብሔር መንግስት ጋር ተዋሀዳለች።

፩ አድምጡ፣ እናም ሀያል እና ጠንካራ የሆነው፣ አካሄዱም እስከ ምድር ዳርቻ የሆነውን፣ አዎን ድምጹም ለሰዎች የሆነውን፣ ከላይም እንደተላከ ድምጽ የሆነውን፣ እነሆ—የጌታን መንገድ [ሀ]አዘጋጁ፣ ጥርጊያውንም አቅኑ፤

፪ በምድርም ለሰው የእግዚአብሔር [ሀ]መንግስት [ለ]ቁልፎችም ተሰጥተዋል፣ እናም ከዚህም ወንጌሉ፣ እጅም ሳይነካው ከተራራው ተፈንቅሎ ምድርን [ሐ]እስከሚሞላ ድረስ እንደሚንከባለለውም [መ]ድንጋይ፣ ወደ ምድር ዳርቻምይገፋል።

፫ አዎን፣ ድምፅም ይጮህል—የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ የበጉን [ሀ]እራት አዘጋጁ፣ [ለ]ለሙሽራውም ተዘጋጁ።

፬ ወደ ጌታም ጸልዩ፣ ቅዱስ ስሙንም ጥሩ፣ በአህዛብም መካከል ድንቅ ስራዎቹን እንዲታወቁ አድርጉ።

፭ የዚህች ኗሪዎችም እንዲቀበሉት፣ መንግስቱም በምድር ላይ እንዲሄድ፣ ጌታን ጥሩ፣ እናም የሰው ልጅ [ሀ]የክብሩን ብርሀን [ለ]ለብሶ ከሰማይ በምድር ከተሰራችው የእግዚአብሔርን [ሐ]መንግስት ጋር ለመገኛኘት [መ]በሚገለጥበት ወደ ፊት ለሚመጡት ቀናትም ተዘጋጁ።

፮ ስለዚህ፣ [ሀ]መንግስተ ሰማያት እንድትመጣ፣ የእግዚአብሔር [ለ]መንግስት ወደ ፊት ይሂድ፣ አንተም፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ በሰማይም እንዳከበርህ እንዲሁ በምድርም ትከበር ዘንድ፣ ጠላቶችህም ይዋረዱ ዘንድ፤ ክብርም፣ ኃይልም፣ እና ግርማም [ሐ]የአንተ ናትና፣ ከዘለአለም እስከዘለዓለም። አሜን።

ክፍል ፷፮

ጥቅምት ፳፱፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሂራም ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ውልያም ኢ. መክለለን ለነበሩት አምስት ጥያቄዎች መልስ በነቢዩ በኩል በሚስጥር እንዲመልስለት ጌታን ጠይቆ ነበር፣ እነዚህም ለጆሴፍ ስሚዝ የታወቁ አልነበሩም። በመክለለን ጥያቄ፣ ነቢዩ ጌታን ጠየቀ እና ይህን ራዕይ ተቀበለ።

፷፭ ፩ ሀ ኢሳ. ፵፥፫፤
ማቴ. ፫፥፫፤
ዮሐ. ፩፥፳፫።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፺፥፩–፭።
ለ ማቴ. ፲፮፥፲፱፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፱።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ሐ መዝ. ፸፪፥፲፱።
ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት፤ ዳንኤል—ትንቢተ ዳንኤል።
መ ዳን. ፪፥፴፬–፵፭።
፫ ሀ ማቴ. ፳፪፥፩–፲፬፤
ራዕ. ፲፱፥፱፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. ሙሽራ።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ክብር።
ለ መዝ. ፺፫፥፩።
ሐ ዳን. ፪፥፵፬።
መ ማቴ. ፳፬፥፴።
፮ ሀ ራዕ. ፲፩፥፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ሐ ፩ ዜና ፳፱፥፲፩፤
ማቴ. ፮፥፲፫።

፩–፬፣ የወንጌሉ ሙሉነት ዘለአለማዊው ቃል ኪዳን ነው፤ ፭–፰፣ ሽማግሌዎች ይስበኩ፣ ይመስክሩ፣ እናም ከህዝብም ጋር ይወያዩ፤ ፱–፲፫፣ ታማኝ የወንጌል አገልግሎትም የዘለአለም ህይወትን ውርስ ያረጋግጣል።

፩ እነሆ፣ ጌታ ለአገልጋዬ ውልያም መክለለን እንዲህ ይላል—ከኃጢአቶችህ ዞር እስካልህ ድረስ፣ እና እውነቴን እስከተቀበልህ ድረስ የተባርክ ነህ፣ እንዲሁም በስሜ [ሀ]የሚያምኑት ሁሉ፣ ይላል ጌታ ቤዛህ፣ የአለም አዳኝ።

፪ እውነት እልሀለሁ፣ [ሀ]ዘለአለማዊ ቃል ኪዳኔን፣ እንዲሁም በነቢያት እና ሐዋርያት በቀደሙት ቀናት እንደተጻፈው፣ [ለ]ህይወት እንዲኖራቸው እና በመጨረሻዎቹም ቀናት የሚገለጡትን ክብሮች ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ፣ ወደሰው ልጆች የተላከውን የወንጌሌን ሙሉነት በመቀበልህ የተባረክህ ነህ።

፫ በእውነትም እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ውልያም ሆይ፣ አንተ፣ በሁሉም ባይሆን፣ ንጹህ ነህ፤ ስለዚህ በፊቴ ለማያስደስቱኝ ነገሮች ንስሀ ግባ፣ ጌታ እነዚህን [ሀ]ያሳይሀልና።

፬ እናም አሁን፣ በእውነትም፣ እኔ ጌታ ስለአንተ በመመልከት ያለኝን ፈቃዴን፣ ወይም አንተን በተመልከተ ፈቃዴን አሳይህ ዘንድ እሻለሁ።

፭ እነሆ፣ በእውነትም እልሀለሁ፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ፣ እና ከከተማ ወደ ከተማ፣ አዎን፣ ባልታወጁበት አካባቢዎች ውስጥ ሁሉ ወንጌሌን [ሀ]ታውጅ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፮ በዚህ ስፍራ ለብዙ ቀናት አትቆይ፤ ወደ ፅዮን አገርም ገና አትሂድ፣ ነገር ግን፣ ለመላክ የምትችለውን ላክ፤ አለበለዚያም፣ ስለ ንብረቶችህ አታስብ።

፯ ወደ ምስራቅ ባሉ ምድሮችም [ሀ]ተጓዝ፣ በእያንዳንዱም ስፍራዎች፣ ለእያንዳንዱም ሰው እናም በየምኩራቦቻቸው፣ ከህዝብ ጋር እየተወያየህ፣ [ለ]ምስክርነትህን ስጥ።

፰ አገልጋዬ ሳሙኤል ኤች ስሚዝም አብሮህ ይሂድ፣ እናም አትተወው፣ እናም አስተምረውም፤ እናም ታማኝ የሆነውም እርሱ በሁሉም ስፍራ [ሀ]ጠንካራ ይሆናል፤ እና እኔ ጌታም ከአንተ ጋር እሄዳለሁ።

፱ በታመሙትም ላይ [ሀ]እጆችህን ጫን፣ [ለ]ይድኑማል። እኔ ጌታ እስከምልክህ ድረስም አትመለስ። በስቃይህም ትእግስተኛ ሁን። [ሐ]ለምን፣ እናም ይሰጥሀል፤ አንኳኳ፣ ይከፈትልህማል።

፲ ብኩንነትን አትሻ። ከፅድቅ ያልሆኑውን ሁሉ ተው። የተፈተንህበትን [ሀ]አመንዝራትን አትፈጽም።

፲፩ እነዚህ ያዘዝኩህን [ሀ]ጠብቅ፣ እውነት እና ታማኝ ናቸውና፤ እናም ሀላፊነትህን ታጎላለህ፣ እናም የዘለአለም ደስታ [ለ]መዝሙሮች በራሳቸው ላይ ሆኖ ብዙ ህዝብን ወደ [ሐ]ፅዮን ትገፋለህ።

፲፪ እስከመጨረሻውም በእነዚህ ነገሮች [ሀ]ፅና፣ እናም በጸጋ እና በእውነት በተሞላው በአባቴም ቀኝ በኩልም የዘለአለም ህይወት [ለ]አክሊል ይኖርሀል።

፲፫ በእውነትም፣ እንዲህ ይላል ጌታ [ሀ]እግዚአብሔርህ፣ ቤዛህ፣ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ። አሜን።

፷፮ ፩ሀ ዮሐ. ፩፥፲፪።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፪ሀ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ለ ዮሐ. ፲፥፲፤ ፫ ኔፊ ፳፯፥፲፫።
፫ሀ ያዕቆ. ፬፥፯፤ ኤተር ፲፪፥፳፯።
፭ሀ ማር. ፲፮፥፲፭።
፯ሀ ት. እና ቃ. ፳፰፥፮።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፰ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥፲፯፤ ፻፴፫፥፶፰።
፱ሀ ቅ.መ.መ. ለታመሙት አገልግሎት መስጠት፤ እጅን መጫን።
ለ ማቴ. ፱፥፲፰።
ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።
ሐ ያዕ. ፩፥፭።
፲ሀ ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
፲፩ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፵፭።
ለ ኢሳ. ፴፭፥፲፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፸፩።
ቅ.መ.መ. መዘመር።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፩፥፮።
፲፪ሀ ፪ ጢሞ. ፫፥፲፬–፲፭፤ ፪ ኔፊ ፴፩፥፳።
ለ ኢሳ. ፷፪፥፫፤ ማቴ. ፳፭፥፳፩፤ ፩ ጴጥ. ፭፥፬።
፲፫ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።

ክፍል ፷፯

ህዳር መጀመሪያ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። የልዩ ጉባኤ ጊዜ ነበር፣ እናም በነቢዩ በኩል ከጌታ የመጡት ራዕዮች መታተም ተወያይቶ ውሳኔም ተደርሶበት ነበር (የክፍል ፩ ርዕስን ተመልከቱ)። ውልያም ደብሊው. ፌልፕስ የቤተክርስቲያኗን ማተሚያ በኢንድፔንደንስ፣ ምዙሪ መስርቶ ነበር። በጉባኤው ራዕዮችን በ Book of Commandments (መጽሐፈ ትእዛዛት) ለማተም እና ፲ ሺህ ቅጂዎች ለማተም ተወሰነ (ይህም ቀድሞ ባልታወቁ ችግሮች ምክንያት ወደ ፫ ሺህ ተቀንሶ ነበር)። ብዙ ወንድሞችም፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነትም እንደተገለጠላቸው፣ በዚያ ጊዜ ለመታተም የተሰበሰቡት ራዕዮች እውነት እንደሆኑ ምስክርነቶችን ሰጥተው ነበር። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደመዘገበው ክፍል ፩ ተብሎ የሚታወቀውን ራዕይ ከተቀበለ በኋላ፣ በራዕዮቹ ውስጥ የነበሩት ቃላት ጥቂት ንግግሮች ነበሩባቸው። ይህም ራዕይ ተከተለ።

፩–፫፥ ጌታ የሽማግሌዎችን ጸሎት ይሰማል እናም ይጠብቃቸዋል፤ ፬–፱፥ ከራዕዮቹ ጥቂቱን ክፍል እንዲያባዛለት ከጠቢባን አንዱን ጠየቀ፤ ፲–፲፬፥ ታማኝ ሽማግሌዎች በመንፈስ ህያው ይሆናሉ እናም የእግዚአብሔርንም ፊት ያያሉ።

፩ እናንት የቤተክርስቲያኔ [ሀ]ሽማግሌዎች፣ በአንድነት የተሰበሰባችሁ፣ ጸሎቶቻችሁን የሰማሁ፣ ልባችሁንም የማውቅ፣ እና ልመናችሁም በፊቴ የሆነው፣ እነሆ እናም አድምጡ።

፪ እነሆ እናም አስተውሉ፣ [ሀ]አይኖቼ በእናንተ ላይ ናቸው፣ እናም ሰማያት እና ምድርም በእጆቼ ውስጥ ናቸው፣ እናም የዘለአለም ሀብትንም እሰጥ ዘንድ የእኔ ናቸው።

፫ ለእናንተ የቀረቡላችሁን በረከቶች ትቀበሉ ዘንድ እንደሚገባችሁ ለእምነታችሁ ተግታችኋል፤ ነገር ግን እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ በልባችሁ [ሀ]ፍርሀት አለ፣ እናም በእውነት የማትቀበሉበት ምክንያቱ ይህ ነው።

፬ እናም አሁን እኔ ጌታ በፊት ለፊታችሁ የተቀመጡት ትእዛዛት እውነት እንደሆኑ [ሀ]ምስክርነትን እሰጣችኋለሁ።

፭ አይኖቻችሁ በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ ላይ ነበሩ፣ እናም [ሀ]ቋንቋውን ታውቃላችሁ፣ እናም ፍጹም አለመሆኑን ታውቃላችሁ፣ እናም በልባችሁም ከቋንቋው በላይ ለመግለፅ እውቀት እንዲኖራችሁ ፈልጋችሁም ነበር፤ ይህንም ታውቃላችሁ።

፮ አሁን፣ በመፅሐፈ ትእዛዛት ውስጥ፣ እንዲሁም ከመካከሉ ታናሽ የሆነውንም ፈልጉ፣ እናም በመካከላችሁ ከሁሉም በላይ [ሀ]ጠቢብ የሆነውንም ምረጡ፤

፯ ወይም፣ በመካከላችሁ እንደዚህ አንድነት ለመጻፍ የሚችል ማንም ቢኖር፣ ከዚያም እነዚህ እውነት እንደሆኑ አናውቅም በማለታችሁም መልካም አደረጋችሁ፤

፰ ነገር ግን፣ እንደዚህ አይነት አንድም መጻፍ ባትችሉ፣ እውነት እንደሆኑ [ሀ]ባለመመስከራችሁም ትኮነናላችሁ።

፱ በውስጣቸው [ሀ]ጽድቅ ያልሆነ እንደሌሉ ታውቃላችሁና፣ እናም ፅድቅ የሆነው ከላይ፣ [ለ]ከብርሀናት አባት ይመጣልና።

፲ እና ዳግም፣ እውነት እላችኋለሁ ይህ

፷፯ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
፪ሀ መዝ. ፴፬፥ ፲፭።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት፤ እውነት።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፩፥ ፳፬።
፮ሀ ፪ ኔፊ ፱፥ ፳፰–፳፱፤ ፵፪።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ምስክር።
፱ሀ ሞሮኒ ፯፥ ፲፭–፲፰።
ለ ያዕ. ፩፥ ፲፯፤ ት. እና ቃ. ፶፥ ፳፬፤ ፹፬፥ ፵፭፤ ፹፰፥ ፵፱።

እድላችሁ ነው፤ እናም [ሀ]ከቅናት እና [ለ]ፍርሀት ራሳችሁን ብታርቁ፤ እናም በፊቴም [ሐ]ትሁት ብትሆኑ፣ ወደ አገልግሎቱ እንደተሾማችሁ ቃል ኪዳንን እሰጣችኋለሁ፣ በብቃት ትሁት አይደላችሁምና፣ [መ]መጋረጃውም ይገፈፋል እናም [ሠ]አይታችሁኝም እኔ ማን እንደሆንኩም በሰውነት ወይም በስጋዊ አዕምሮ ሳይሆን፣ በመንፈስ ይህን ታውቃላችሁ።

፲፩ በእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳሳ ካልሆነ በስተቀር፣ ማንም ቢሆን በስጋ እግዚአብሔርን ያየው [ሀ]አንድስ እንኳ የለም።

፲፪ ማንም [ሀ]ተፈጥሮአዊ ሰው በእግዚአብሔር ፊት፣ በስጋዊ አዕምሮም፣ ይቆም ዘንድ አይችልም።

፲፫ አሁንም በእግዚአብሔር ፊት፣ ወይም የመላእክትን አገልግሎት፣ ትመለከቱ ዘንድ አትችሉም፤ ስለዚህ፣ [ሀ]ፍጹም እስክትሆኑም ድረስ [ለ]በትዕግስት ፅኑ።

፲፬ አዕምሮዎቻችሁም ወደ ነበሩበት አይመለሱ፤ እናም [ሀ]ብቁ ስትሆኑም፣ በጊዜዬ፣ በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እጆች በኩል የተሰጣችሁን ታያላችሁ እናም ታውቃላችሁም። አሜን።

ክፍል ፷፰

ህዳር ፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ ስለኦርሰን ሀይድ፣ ሉክ ኤስ ጆንሰን፣ ላይማን ኢ. ጆንሰን፣ እና ውልያም ኢ. መክለለን የጌታን ሀሳብ እንዲታወቅ በቀረበው ልመና መልስ አማካይነት በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ምንም እንኳን የዚህ ራዕይ ክፍል ለእነዚህ አራት ሽማግሌዎች የተሰጠ ቢሆንም፣ በውስጡ ያሉት አብዛኛዎቹ ለቤተክርስቲያኗ ሁሉ ተገቢ የሆኑ ናቸው። ይህ ራዕይ በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በትምህርት እና ቃል ኪዳን ቅጂ ውስጥ በታተመበት ጊዜ በጆሴፍ ስሚዝ አመራር ተስፋፍቶ ነበር።

፩–፭፣ ሽማግሌዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስተው የተናገሩት ቅዱሳን መጻህፍት ናቸው፤ ፮–፲፪፣ ሽማግሌዎች ይሰበኩ እናም ያጥምቁ፣ እናም በእውነት የሚያምኑትን ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ ፲፫–፳፬፣ ከአሮን ወንድ ልጆች መካከል በኩሩ በቀዳሚ አመራር ስር እንደ ኤጲስ ቆጶስ አመራር ያገለግላል (ይህም ማለት፣ እንደ ኤጲስ ቆጶስ የአመራር ቁልፎችን ይይዛል)፤ ፳፭–፳፰፣ ወላጆች ወንጌልን ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩ ታዝዘዋል፤ ፳፱–፴፭፣ ቅዱሳን ሰንበትን ያክብሩ፣ በትጋት ይስሩ፣ እናም ይጸልዩ።

፩ አገልጋዬ፣ ኦርሰን ሀይድ፣ በህያው እግዚአብሔር [ሀ]መንፈስ በኩል፣ ከህዝብ ወደ ህዝብ፣ ከምድር ወደ ምድር፣ በኃጢአተኞቹ ስብሰባዎች ውስጥ፣ በምኩራቦች ውስጥ፣ ምክንያቶችን በመስጠት እና ቅዱስ መጻህፍቶችን ሁሉ ለእነርሱ በማብራራት፣ ዘለአለማዊ ወንጌልን እንዲያውጅ በሹመት ተጠርቶ ነበር።

፲ ሀ ቅ.መ.መ. ቅንዓት፣ መቅናት።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርሀት።
ሐ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
መ ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ።
ሠ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፰፤ ፺፫፥፩፤ ፺፯፥፲፮።
፲፩ ሀ ጆ.ስ.ት. ዘፀአ. ፴፫፥፳፡ ፳፫ (ተጨማሪ)፤ ዮሐ. ፩፥፲፰፤ ፮፥፵፮፤ ጆ.ስ.ት. ፩ ዮሐ. ፬፥፲፪ (ተጨማሪ)፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፱–፳፪፤ ሙሴ ፩፥፲፩፡ ፲፬።
፲፪ ሀ ሞዛያ ፫፥፲፱። ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
፲፫ ሀ ማቴ. ፭፥፵፰፤ ፫ ኔፊ ፲፪፥፵፰።
ለ ሮሜ ፪፥፯። ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
፷፰ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።

፪ እናም፣ እነሆ፣ እና ተልዕኮአቸው እንዲሄዱ ለተወሰነላቸው፣ በክህነት ለተሾሙት ሁሉ ይህም ምሳሌ ነው—

፫ እናም ይህም በመንፈስ ቅዱስ በመነሳሳት [ሀ]ለሚናገሩትም ምሳሌ ነው።

፬ እናም [ሀ]በመንፈስ ቅዱስ ሲነሳሱ የሚናገሩት ማንኛውም ነገር ቅዱሳን መጻህፍት ይሆናሉ፣ የጌታ ፈቃድም ይሆናል፣ የጌታ አዕምሮም ይሆናል፣ የጌታ ቃል ይሆናል፣ የጌታ ድምጽ፣ እናም ለደህንነት የእግዚአብሔር [ለ]ሀይልም ይሆናል።

፭ እነሆ፣ አገልጋዮቼ ሆይ፣ ይህም ለእናንተ የተሰጠ የጌታ ቃል ኪዳን ነው።

፮ ስለዚህ፣ ተደሰቱ፣ እናም [ሀ]አትፍሩ፣ እኔ ጌታ ከእናንተ ጋር ነኝና፣ እናም ከጎናችሁ እቆማለሁና፣ እና ስለ እኔም፣ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የህያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንኩኝ፣ እስቀድሜም እንደነበርኩኝ፣ ህያውም እንደሆንኩኝ፣ እናም ዳግምም እንደምመጣ ትመሰክራላችሁ።

፯ ይህም ለአንተ አገልጋዬ [ሀ]ኦርሰን ሀይድ፣ እናም ለአገልጋዬ ሉክ ጆንሰንም፣ እናም ለአገልጋዬ ላይመን ጆንሰንም፣ እና ለአገልጋዬ ውልያም ኢ. መክለለንም፣ እናም ለቤተክርስቲያኔ ታማኝ ሽማግሌዎች ሁሉ የተሰጠ የጌታ ቃል ነው—

፰ ወደአለም ሁሉ [ሀ]ሂዱ፣ ለእያንዳንዱም [ለ]ፍጥረት፣ በሰጠኋችሁ [ሐ]ስልጣን እየሰራችሁ፣ በአብ፣ እና በወልድ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም [መ]እያጠመቃችኋቸው ወንጌልን [ሠ]ስበኩ።

፱ እናም [ሀ]የሚያምን እና የተጠመቀ [ለ]ይድናል፣ እናም ያላመነ ግን [ሐ]ይፈረድበታል።

፲ እናም የሚያምነውም፣ እንደተጻፈው ይባረካል [ሀ]ምልክቶችም ይከተሉታል።

፲፩ እናም ለእናንተም የዘመኑን [ሀ]ምልክቶች፣ እናም የሰው ልጅ መምጫ ምልክቶች፣ ታውቁ ዘንድ ይሰጣችኋል፤

፲፪ እናም አብም የሚመሰክርላቸው ሁሉ፣ ለእናንተም እነርሱን ለዘለአለም [ሀ]የምታትሙባቸውን ሀይል ይሰጣችኋል። አሜን።

፲፫ እናም አሁን፣ ከቃል ኪዳኖች እና ከትእዛዛት በተጨማሪ ሌሎች ነገሮችን የሚመለከቱት፣ እነዚህ ናቸው—

፲፬ ጌታ በፈቀደ ጊዜ፣ እንደ መጀመሪያው ለማገልገል፣ ከዚህ በኋላ ለቤተክርስቲያኗ የሚሾሙ ሌሎች [ሀ]ኤጲስ ቆጶሳት አሉ፤

፲፭ ስለዚህ እነዚህም ብቁ የሆኑ [ሀ]ሊቀ ካህናት መሆን ይገባቸዋል፣ እናም፣ [ለ]የአሮን እውነተኛ ተወላጆች ካለሆኑ በስተቀር፣ በመልከ ጼዴቅ ክህነት [ሐ]ቀዳሚ አመራር በኩልም ይሾማሉ።

፲፮ እናም እነርሱም [ሀ]የአሮን እውነተኛ ተወላጆች ሊሆኑ፣ ከአሮን ወንድ ልጆች በኩር ከሆኑ፣ ለኤጲስ ቆጶስ አመራርነት ህጋዊ መብት አላቸው፤

፲፯ በኩሩም በዚህ ክህነት የአመራር መብትን፣ እናም የዚህንም [ሀ]ቁልፎች ወይም ስልጣናት ይይዛልና።

፲፰ የአሮን [ሀ]እውነተኛ ተወላጅ እና በኩር ካልሆነ በስተቀር፣ ማንም ሰው ለዚህ ሀላፊ

፫ ሀ ፪ ጴጥ. ፩፥፳፩፤
ት. እና ቃ. ፲፰፥፴፪፤
፵፪፥፲፮፤ ፻፥፭።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤
ራዕይ።
ለ ሮሜ ፩፥፲፮።
፮ ሀ ኢሳ. ፵፩፥፲።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይድ፣ ኦርሰን።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፪፤ ፹፬፥፷፪።
ለ ማር. ፲፮፥፲፭።
ሐ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ሠ ቅ.መ.መ. መስበክ፤
የሚስዮን ስራ።
፱ ሀ ማር. ፲፮፥፲፮፤
ት. እና ቃ. ፳፥፳፭።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የጊዜዎች
ምልክቶች።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፰፤
፻፴፪፥፵፱።
ቅ.መ.መ. ማተም፣
ማስተሳሰር።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፷፪፥፩።
ለ ቅ.መ.መ. አሮን፣
የሙሴ ወንድም።
ሐ ቅ.መ.መ. ቀዳሚ አመራር።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፲፭–፲፯።
ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፲፰ ሀ ዘፀአ. ፵፥፲፪–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፰፤
፻፯፥፲፫–፲፮፤ ፸–፸፮።

ነት፣ የዚህን ክህነት ቁልፎች ለመያዝ ህጋዊ መብት አይኖረውም።

፲፱ ነገር ግን፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት [ሀ]ሊቀ ካህን በታናሾቹ ሀላፊነቶች ለማስተዳደር ስልጣን እንዳለው የአሮን እውነተኛ ተወላጅ እና በኩር በማይገኝበት ጊዜ፣ በመልከ ጼዴቅ ክህነት ቀዳሚ አመራር እጆች ስር ለዚህ ስልጣን ከተጠራ፣ እና ከተለየ እና ከተሾመ፣ [ለ]በኤጲስ ቆጶስ ሀላፊነት ለማስተዳደር ይችላል።

፳ እና፣ ደግሞም፣ የአሮን እውነተኛ ተወላጅም በዚህ ቀዳሚ አመራር መመረጥ፣ እና በብቃት መገኘት፣ እናም [ሀ]መቀባት፣ እናም በአመራሩ እጆች ስር [ለ]መሾም አለባቸው፣ አለበለዚያ በክህነት ስልጣናቸው ለማስተዳደር ህጋዊ ስልጣን አይኖራቸውም።

፳፩ ነገር ግን፣ ከአባት ወደ ልጅ በሚወረሰው ክህነት መብትን በሚመለከት በታወጀው መሰረትም፣ ተወላጅነታቸውን በሚያረጋግጡበት ጊዜ፣ ወይም ከላይ በተጠቀሱት አመራር እጆች ስር በጌታ ራዕይ ካገኙ፣ መቀባታቸውን ለማረጋገጥ ይችላሉ።

፳፪ እና ደግሞም፣ ለዚህ አገልግሎት የተለየ፣ ማንም ኤጲስ ቆጶስ ወይም ሊቀ ካህን፣ በቤተክርስቲያኗ [ሀ]ቀዳሚ አመራር ፊት ካልሆነ በስተቀር፣ በወንጀል መኮነን ወይም ለፍርድ ሊቀርብ አይገባም፤

፳፫ እናም ጥርጣሬ በሌለው ምስክር በአመራሩ ፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ፣ ይፈረድበታል፤

፳፬ እናም ንስሀ ቢገባ፣ በቤተክርስቲያኗ ቃል ኪዳኖች እና ትእዛዛት መሰረት [ሀ]ይቅርታን ያገኛል።

፳፭ እና ደግሞም፣ [ሀ]ወላጆች በፅዮን፣ ወይም በተደራጁት [ለ]ካስማዎቿ፣ ውስጥ ልጆች ኖሯቸው፣ [ሐ]ስምንት አመት ሲሆናቸው፣ ስለ ንስሀ፣ በህያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ እምነት፣ እናም ስለ ጥምቀት እና እጆችን በመጫን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ስለመቀበል ትምህርትን [መ]ባያስተማሯቸው፣ [ሠ]ኃጢአቱ በወላጆች ራስ ላይ ይሆናል።

፳፮ ይህም [ሀ]ለፅዮን፣ ወይም በማንኛውም በተደራጁት ካስማዎቿ፣ ኗሪዎች ህግም ነውና።

፳፯ እናም ልጆቻቸውም ለኃጢአቶቻቸው [ሀ]ስርየት [ለ]በስምንት አመታቸው [ሐ]ይጠመቁ፣ እናም የእጆችንም መጫን ይቀበሉ።

፳፰ እናም ልጆቻቸውን [ሀ]እንዲጸልዩም፣ እናም በጌታ ፊት በቅንነት እንዲራመዱም ያስተምሩ።

፳፱ እናም የፅዮን ኗሪዎችም [ሀ]የሰንበትን ቀን ያክብሩ፣ ይቀድሱትም።

፴ እናም የፅዮን ኗሪዎችም፣ እንዲያገለግሉ እስከተጠሩ ድረስ፣ በሙሉ ታማኝነት አገልግሎታቸውንም ያስታውሱ፤ ስራ ፈት የሆነ እርሱ በጌታ ፊት ይታሰባልና።

፴፩ አሁን፣ እኔ ጌታ፣ በፅዮን ኗሪዎች አልተደሰትኩም፣ [ሀ]ስራ ፈቶች በመካከላቸው አሉና፤ እናም ልጆቻቸውም [ለ]በኃጢአት ውስጥ እያደጉ ናቸውና፤ ለዘለአለማዊ ሀብትም በቅንነት [ሐ]አይሹም፣ ነገር ግን አይኖቻቸው በስግብግብነት ተሞልተዋል።

፴፪ እነዚህ ነገሮች መሆን አይገባቸውም፣ እናም ከመካከላቸው መወገድ አለባቸው፤

፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ለ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. መቀባት።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ቀዳሚ አመራር።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—
የወላጆች ሀላፊነቶች።
ለ ቅ.መ.መ. ካስማ።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፰፥ ፵፪፤
፳፥ ፸፩።
መ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ።
ሠ ያዕቆ. ፩፥ ፲፱፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፵፮–፵፰።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ለ ቅ.መ.መ. መልስ
መስጠት፣ ሂሳብ፣
ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፶፱፥ ፱–፲፪።
ቅ.መ.መ. የሰንበት ቀን።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣
ስራ ፈቺ።
ለ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
ሐ ት. እና ቃ. ፮፥ ፯።

ስለዚህ፣ አገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ እነዚህን አባባሎች ወደ ፅዮን ምድር ይውሰድ።

፴፫ እናም ትእዛዝም እሰጣቸዋለሁ—በትክክለኛው ጊዜ በጌታ ፊት [ሀ]ጸሎትን የማያከናውነው እርሱ፣ በህዝቤ ዳኛ ፊት [ለ]ይታሰብ።

፴፬ እነዚህ [ሀ]አባባሎች እውነተኛዎች እና የታመኑ ናቸው፤ ስለዚህ አትተላለፏቸው፣ ወይም [ለ]አታጉድሏቸውም።

፴፭ እነሆ፣ እኔ [ሀ]አልፋና ኦሜጋ ነኝ፣ እናም በቶሎ [ለ]እመጣለሁ። አሜን።

ክፍል ፵፱

ህዳር ፲፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በአጭር ጊዜ ለመታተም የታሰቡት የራዕይ ዝግጅቶች በህዳር ፩–፪ ልዩ ጉባኤ ላይ ጸድቀው ነበር። በህዳር ፫፣ በኋላም ተጨማሪ መግለጫ በመባል የታወቀው፣ በዚህ በክፍል ፻፴፫ ውስጥ ያለው ራዕይ ተጨምሮ ነበር። ኦሊቨር ካውድሪ የራዕዮች እና ትእዛዛት ዝግጅቶች ፅሁፎችን ወደ ኢንዲፔንደንስ ሚዙሪ ለመታተም እንዲወስድ ተመርጦ ነበር። የሚዙሪ ቤተክርስቲያንን ለመገንባት ተሰጥቶ የነበረውን ገንዘብም እንዲሁ መውሰድ ነበረበት። ይህም ራዕይ ጆን ዊትመር ከኦሊቨር ካውደሪ ጋር አብሮ እንዲሄድ መመሪያ ሰጥቷል እናም ዊትመር እንደ ቤተክርስቲያኗ የታሪክ ምሁር እና መዝጋቢ እንዲጓዝ እና ታሪካዊ ነገሮችን እንዲሰበስብ መመሪያ ሰጥቶ ነበር።

፩–፪፣ ጆን ዊትመር ኦሊቨር ካውድሪን ተከትሎ ወደ ሚዙሪ ይሂድ፤ ፫–፰፣ እርሱም ይስበክ፣ እና ታሪካዊ መረጃዎችን ይሰብስብ፣ እናም ይጻፍ።

፩ ለአገልጋዬ [ሀ]ኦሊቨር ካውድሪ ጥቅምም አድምጡኝ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ። እውነተኛ እና ታማኝ የሆነ ከእርሱ ጋር ካልሄደ በስተቀር፣ ወደ ፅዮን ምድር ይዞ የሚሄዳቸውን ትእዛዛት እና ገንዘቦች ለእርሱ በአደራ መስጠቱ በእኔ ዘንድ ጥበብ አይደለም።

፪ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ አገልጋዬ [ሀ]ጆን ዊትመር ከአገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ጋር ይሄዱ ዘንድ ፍቃዴ ነው፤

፫ እና ደግሞም ስለቤተክርስቲያኔ የሚመለከታቸውን እና የሚያውቃቸውን አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ መጻፉን እና [ሀ]ታሪክንም መሰብሰቡን ይቀጥል፤

፬ እና ደግሞም ከኦሊቨር ካውድሪ እና ከሌሎችም [ሀ]ምክርን እና እርዳታን ይቀበል።

፭ እና ደግሞም፣ በአለም ያሉት አገልጋዮቼም [ሀ]የመጋቢነታቸውን መግለጫዎች ወደ ምድረ ፅዮን ይላኩ፤

፮ ምድረ ፅዮንም የመቀበያ እና እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚደረጉባት ዋና ስፍራ ናትና።

፯ ይሁን እንጂ፣ በቀላል እውቀትን እንዲያገኝ፣ አገልጋዬ ጆን ዊትመር፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ፣ እናም ከቤተክርስቲያኗ ወደ ቤተክርስቲያኗ፣ ለብዙ ጊዜ ይጓዝ፣

፰ እየሰበከ እና እያብራራ፣ ለቤተክርስ

፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ፤ ዳኛ፣ ፍርድ።
፴፬ ሀ ራዕ. ፳፪፥፮።
ለ ት. እና ቃ. ፳፥፴፭፤ ፺፫፥፳፬–፳፭።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. አልፋ እና ኦሜጋ።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፲፪።
፵፱ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ካውደሪ፣ ኦልቨር።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ዊትመር፣ ጆን።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፵፯፥፩–፫፤ ፹፭፥፩።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፭ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።

ቲያኗ ጥቅም እና ʺበፅዮን ምድር ለሚያድጉት የሚቀጥሉት ትውልዶች እስከዘለአለም ይይዟቸው ዘንድ ከትውልድ ወደ ትውልድም ጥቅም እንዲሆንላቸው፣ ሁሉንም ነገሮች እያባዛ፣ እየመረጠ፣ እና እያገኘ ለብዙ ጊዜ ይጓዝ። አሜን።

ክፍል ፸

ህዳር ፲፪፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። የነቢዩ ታሪክ እንደሚገልጸው ከህዳር ፩ እስከ ፲፪ አራት ልዩ ጉባኤዎች ተካሂደዋል። በእነዚህም ስብሰባዎች ማብቂያ ላይ፣ በኋላም እንደ የ Book of Commandments (መፅሐፈ ትእዛዛት) እና ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች የታተሙት ራዕዮች ታላቅ አስፈላጊነት ታሰበበት። ይህም ራዕይ የተሰጠው ጉባኤው እነዚህን ራዕዮች "ለቤተክርስቲያኗ ከአለም ሁሉ ሀብቶች በላይ ታላቅ ዋጋ እንዳላቸው" በድምጽ ምርጫ ከተሰጠ በኋላ ነበር። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ ስለ ዚህ ራዕይ "የአዳኛችን መንግስት ሚስጥር ቁልፎች ለሰው በአደራ እንደተሰጡ በማሳየት፣ በእነዚህ የመጨረሻዎቹ ቀናት የቤተክርስቲያኗ መሰረት፣ እና ለአለምም ጥቅም" የሚሆን ነው ብሎታል።

፩–፭፣ ራዕዮችን እንዲያትሙ መጋቢዎች ተመርጠዋል፤ ፮–፲፫፣ በመንፈሳዊ ነገሮች የሚያገለግሉ ደሞዛቸው ይገባቸዋል፤ ፲፬–፲፰፣ ቅዱሳን በስጋዊ ነገሮች እኩል መሆን አለባቸው።

፩ እነሆ፣ እና አድምጡ፣ እናንት የፅዮን ኗሪዎች፣ እናም በሩቅ ያላችሁ የቤተክርስቲያኔ ህዝብ፣ እናም ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ ለአገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ፣ እና ደግሞም ለአገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ፣ እና ደግሞም ለአገልጋዬ ጆን ዊትመር፣ ለአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን፣ እና ደግሞም ለአገልጋዬ ውልያም ደብሊው ፌልፕስ በትእዛዝ መንገድ የምሰጣቸውን የጌታን ቃል ስሙ።

፪ ትእዛዝ እሰጣቸዋለሁና፤ ስለዚህ፣ አድምጡ እናም ስሙ፣ ጌታ እንዲህ ይላቸዋልና—

፫ እኔ ጌታ መርጫቸዋለሁ፣ እናም በሰጠኋቸው፣ እና ከዚህም በኋላ ለምሰጣቸው ራዕዮች እና ትእዛዛት ʺመጋቢዎች እንዲሆኑ ሾሚአቸዋለሁ፤

፬ እናም የዚህን የመጋቢነትን ዘገባ በፍርድ ቀን እፈልግባቸዋለሁ።

፭ ስለዚህ፣ እኔም መርጫቸዋለሁ፣ እናም እነዚህን የሚመለከቱትን ጥቅሞቻቸውን፣ አዎን ቅሬታዎችን ማስተዳደር፣ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ ይህም ሀላፊነታቸው ነው።

፮ ስለዚህ፣ እነዚህን ነገሮች ለቤተክርስቲያኗም ሆነ ለአለም እንዳይሰጡ ትእዛዝ እሰጣቸዋለሁ፤

፯ ይሁን እንጂ፣ ከመሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው እና መሻታቸው በላይ እስከተቀበሉ ድረስ፣ ወደ ʺጎተራዬ ያግቡ፤

፰ እናም፣ እንደ መንግስት ህግጋት ʺወራሾች እስከ ሆኑ ድረስ፣ ጥቅሙም ለፅዮን ኗሪዎች፣ እናም ለትውልዶቻቸው፣ የተቀደሰ ይሆናል።

፱ እነሆ፣ ጌታ ከእያንዳንዱ ሰው፣ እንዲሁም እኔ ጌታ እንደመደብኩት ወይም

፰ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።

፸ ፫ሀ ፩ ቆሮ. ፬፥፩፤ ት. እና ቃ. ፸፪፥፳።

፯ሀ ት. እና ቃ. ፸፪፥፱–፲።

፰ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳።

ከዚህ በኋላ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ምመድበው፣ [ሀ]በመጋቢነቱ የምጠብቅበት ይህ ነው።

፲ እናም እነሆ፣ በህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አባል የሆነ ከእነዚህ የህግ ግዴታዎች ነጻ የሆነ ማንም የለም፤

፲፩ አዎን፣ ኤጲስ ቆጶስ ወይም የጌታን ጎተራን የሚጠብቀው [ሀ]ወኪል፣ ወይም በስጋዊ ነገሮች ላይ መጋቢነት የተሰጠውም ቢሆን ከእነዚህ የህግ ግዴታዎች ነጻ አይደሉም።

፲፪ ለመንፈሳዊ ጉዳዮችንም ሊያስተዳድር የተመረጠውም፣ ለስጋዊ ጉዳዮች አስተዳደር መጋቢነት እንደተሰጣቸው ሁሉ፣ እርሱም [ሀ]ደሞዙ ይገባዋል፤

፲፫ አዎን፣ እንዲሁም በብዛትም፣ ይህ ብዛትም ለእነርሱ በመንፈስ መግለጥ በኩል ይጨመርላቸዋል።

፲፬ ይሁን እንጂ፣ በስጋዊ ነገሮች [ሀ]እኩል ሁኑ፣ እናም ይህንንም በመሰሰት አይደለም፣ አለበለዚያም፣ የመንፈስ መገለጥ ብዛቱ ይከለከላልና።

፲፭ በእዚህ እያሉ አገልጋዮቼ በረከቴ በላያቸው እንዲገለጥ እና [ሀ]በትጋታቸው ምላሽ እና ለደህንነታቸው እንዲሁም ለጥቅማቸው ይህን [ለ]ትእዛዝም እሰጣቸዋለሁ፤

፲፮ ለምግብ እና [ሀ]ለልብስ፣ ለውርስ፣ ለቤቶች እና መሬትም እኔ ጌታ ባስቀመጥኳቸው ስፍራ ሁሉ እና በምልካቸው በማንኛቸውም ስፍራ ይሆኑ ዘንድ ይህን ትእዛዝም እሰጣቸዋለሁ።

፲፯ [ሀ]በብዙ ነገሮች ታማኝ ነበሩና፣ እናም ኃጢአትንም ባለመስራት ድረስ በጎን ነገር አድርገዋልና።

፲፰ እነሆ፣ እኔ ጌታ [ሀ]መሐሪ ነኝ እናም እባርካቸዋለሁ፣ እናም ወደ እነዚህ ነገሮች ደስታም ይገባሉ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፸፩

ታህሳስ ፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህን ራዕይ እስከሚቀበል ድረስ ነቢዩ ከጸሀፊው ከስድኒ ሪግደን ጋር መፅሐፍ ቅዱስን መተርጎም ቀጥሎ ነበር፣ በጊዜውም ይህም በዚህ የተሰጣቸውን መመሪያዎች ያሟሉ ዘንድ ትርጉምን ለጥቂት ጊዜ አቁመው ነበር። ቤተክርስቲያኗን የካደው እዝራ ቡዝ በጻፋቸው ደብዳቤዎች ምክንያት በቤተክርስቲያኗ ላይ የነበረውን የጥላቻ ስሜት ለማቃለል ወንድሞች ለመስበክ ሊሄዱ ይገባል።

፩–፬፣ ጆሴፍ ስሚዝ እና ስድኒ ሪግደን ወንጌሉን እንዲያውጁ ተልከዋል፤ ፭–፲፩፣ የቅዱሳኑ ጠላቶችም ያፍራሉ።

፩ እነሆ፣ ለእናንተ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና [ሀ]ስድኒ ሪግደን ጌታ እንዲህ ይላል፣ በእውነትም አንደበታችሁን ከፍታችሁ፣ እንደተሰጣችሁ መንፈስ እና ሀይል፣ እንዲሁም በፈቃዴ ወንጌሌን [ለ]የምትሰብኩበት፣ የመንግስቱንም ነገሮች፣ [ሐ]ሚስጥራት ከቅዱስ መጻህፍቶች ውስጥ የምታብራሩበት አስፈላጊ እና

፱ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣
መጋቢነት።
፲፩ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፯።
፲፫ሀ ሉቃ. ፲፥፯።
፲፬ሀ ት. እና ቃ. ፵፱፥፳።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣
የቅድስና ህግ።
፲፭ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ዘዳግ. ፲፥፲፪–፲፫።
፲፮ሀ ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፮–፳።
፲፯ሀ ማቴ. ፳፭፥፳፩–፳፫።
፲፰ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፸፩ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፩፣ ፷፭።

በእኔም ጠቃሚ መስሎ የሚታይበት ጊዜ መጥቷል።

፪ እውነት እላችኋለሁ፣ በየአካባቢው ላሉት ለአለም እና ለቤተክርስቲያኗም፣ ለአንድ ወቅት፣ እንዲሁም እንድታውቁት እስከሚደረግ ድረስ አውጁ።

፫ በእውነት፣ ይህም የሰጠኋችሁ የወቅቱ ተልዕኮ ነው።

፬ ስለዚህ፣ በወይን ስፍራዬ አገልግሉ። የምድር ኗሪዎችንም ጥሯቸው፣ እናም መስክሩ፣ እናም ለሚመጡት ትእዛዛት እና ራዕዮችም መንገድን አዘጋጁ።

፭ አሁን፣ እነሆ ይህም ጥበብ ነው፤ የሚያነበውም [ሀ]ይረዳው እና ደግሞም [ለ]ይቀበለውም፤

፮ ለሚቀበለውም ለእርሱ [ሀ]በብዛት፣ እንዲሁም ሀይል ይሰጠዋልም።

፯ ስለዚህ፣ ጠላታችሁን [ሀ]አሳፍሩ፤ በግልጽ እናም በግል [ለ]እንዲያገኟችሁ ጥሯቸው፤ እናም ታማኝ ብትሆኑ እፍረታቸው ይገለጣል።

፰ ስለዚህ፣ ብርቱ ማስረጃቸውን በጌታ ላይ ያምጡ።

፱ በእውነትም፣ ጌታ እንዲህ ይላችኋል—በእናንተ ላይ እንዳትበለጽጉ የሚከላከል [ሀ]መሳሪያ አይከናወንም፤

፲ እናም ማንም ሰው በእናንተ ላይ ድምጹን ቢያነሳ እኔ በወሰንኩት ጊዜ ያፍራል።

፲፩ ስለዚህ፣ ትእዛዛቴን ጠብቁ፤ እውነተኛ እና ታማኝ ናቸውና። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፸፪

በታህሳስ ፬፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ብዙ ሽማግሌዎች እና አባላት ሀላፊነታቸውን ለመማር እና በቤተክርስቲያኗ ትምህርቶች ለመታነፅ ተሰብስበው ነበር። ይህ ክፍል በአንድ ቀን የተሰጡ ሶስት ራዕዮች የተቀናጁበት ነው። ከ፩ እስከ ፰ ያሉት ቁጥሮች ኒዌል ኬ ውትኒ እንደ ኤጲስ ቆጶስ የተጠራበትን ያሳውቃሉ። ከዚያም ተጠራ እና ተሾመ፣ ከዚያም፣ ስለ ኤጲስ ቆጶሱ ሀላፊነቶች ተጨማሪ ማስረጃዎች የሚሰጡበትን ከቁጥር ፱ እስከ ፳፫ ያለውንም ተቀብሎ ነበር። ከዚህም በኋላ፣ ከቁጥር ፳፬ እስከ ፳፮ ስለፅዮን መሰብሰብ መመሪያ ሰጥተው ነበር

፩–፰፣ ሽማግሌዎች የመጋቢነታቸውን መግለጫ ለኤጲስ ቆጶሱ ይስጡ፤ ፱–፲፭፣ ኤጲስ ቆጶሱ ግምጃ ቤትን ይጠብቃል፣ እናም ድሆችን እና ችግረኞችን የሚሹት ይንከባከባል፤ ፲፮–፳፮፣ ኤጲስ ቆጶሳት የሽማግሌዎችን ብቃነት ያረጋግጡ።

፩ አድምጡ፣ እናም [ሀ]መንግስት እና ሀይል የተሰጣችሁ አቤቱ እናንት የተሰባሰባችሁት የቤተክርስቲያኔ [ለ]ሊቀ ካህና ትየጌታን ድምፅ ስሙ።

፪ በእውነትም ጌታ እንዲህ ይላል፣ ለእናንተ፣ ወይም ከእናንት በዚህ የጌታ የወይን ስፍራ በሆነች ቤተክርስቲያን፣ [ሀ]ኤጲስ ቆጶስ ይመረጥ ፍቃዴ ነው።

፫ እናም በእውነት በዚህም ነገር ያደረጋችሁት ጥበብ ነው፣ ከእያንዳንዱ [ሀ]መጋቢ እጅ፣ በጊዜም ይሁን በዘለአለም፣ [ለ]የመ

፭ሀ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
ለ አልማ ፲፪፥፱–፲፩።
፮ሀ ማቴ. ፲፫፥፲፪።
፯ሀ ሙሴ ፯፥፲፫–፲፯።
ለ ት. እና ቃ. ፳፫፥፴፯፤ ፳፳፥፳–፱።
፱ሀ ኢሳ. ፶፬፥፲፯።
፸፪ ፩ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ት. እና ቃ. ፳፳፥፲፬–፲፱።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፫ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
ለ ሉቃ. ፲፱፥፲፩–፳፯።

ጋቢነቱን [ሐ]መግለጫ እንዲያቀርብ በጌታ ይጠበቅበታልና።

፬ በጊዜ ታማኝ እና [ሀ]ብልህ የሆነው ለእርሱ በአባቴ የተዘጋጁትን [ለ]መኖሪያዎች ለመውረስ ብቁ ሆኖ ይገኛል።

፭ እውነት እላችኋለሁ፣ በቤተክርስቲያኗ በዚህ [ሀ]የወይን ስፍራ ውስጥ ያሉ ሽማግሌዎች የመጋቢነታቸውን መግለጫ በዚህ የወይን ስፍራዬ በእኔ ለሚመረጠው ኤጲስ ቆጶሱ ይስጡ።

፮ እነዚህ ነገሮችም፣ በፅዮን ላለው ኤጲስ ቆጶሱ ተላልፈው እንዲሰጡ በመመዝገቢያው ውስጥ ይሁኑ።

፯ እናም [ሀ]የኤጲስ ቆጶሱ ሀላፊነት በተሰጡት ትእዛዛት እና በጉባኤ ድምጽ እንዲታወቅ ይደረጋል።

፰ እናም አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ ሀይል የሚመረጠው እና የሚሾመው ሰው አገልጋዬ [ሀ]ኒወል ኬ ውትኒ ነው። ይህም፣ የቤዛችሁ፣ የጌታ አምላካችሁ ፈቃድ ነው። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፱ ከተሰጠው ህግ በተጨማሪ፣ በዚህ የወይን ስፍራ ቤተክርስቲያን ውስጥ የተሾመውን የኤጲስ ቆጶሱን ሀላፊነት የሚያሳውቀው የጌታ ቃል፣ በእውነትም ይህ ነው—

፲ የጌታን [ሀ]ጎተራ መጠበቅ፤ በዚህ የወይን ስፍራ ቤተክርስቲያን ውስጥ ገንዘቦችን መቀበል ነው፤

፲፩ አስቀድሞ እንደታዘዘው የሽማግሌዎችን መግለጫ ለመቀበል፤ እናም የሚከፍሉት እስካላቸው ድረስ፣ ለሚቀበሉት የሚከፍሉትን እንደፍላጎታቸው [ሀ]ለማስተዳደር ነው፤

፲፪ ይህም ደግሞ ለቤተክርስቲያኗ ጥቅም፣ ለድሀው እና ለችግረኛው፣ ይቀደስ ዘንድ ነው።

፲፫ እናም ለመክፈል ችሎታ [ሀ]የሌለው ለእርሱ፣ መግለጫው ይወሰድ እናም፣ ጌታ በእጆቹ ከሚያስቀምጣቸው ገንዘቦች እዳውን ለሚከፍልለት፣ ለፅዮን ኤጲስ ቆጶስ ይሰጥ።

፲፬ እናም በመንፈሳዊ ነገሮች፣ ወንጌሉን እና የመንግስቱን ጉዳዮች ለቤተክርስቲያኗ እና ለአለም በማስተዳደር የሚያገለግለውም ታማኝ አገልጋይ፣ እዳውን ለፅዮን ኤጲስ ቆጶስ በዚህ ይከፍላል፤

፲፭ በመሆኑም ከቤተክርስቲያኑ ይወጣል፣ [ሀ]በህጉ መሰረት ወደ ፅዮን የሚመጣው እያንዳንዱ ሰው በፅዮን ኤጲስ ቆጶስ ፊት ሁሉንም ነገሮች ማቅረብ ይኖርበታልና።

፲፮ እናም አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ የወይን ስፍራ ያሉት እያንዳንዱ ሽማግሌዎች በዚህ የወይን ስፍራ ለሚገኘው ኤጲስ ቆጶስ የሀላፊነቱን መግለጫ መስጠት ይኖርበታል—

፲፯ ከዚህ የወይን ስፍራ ዳኛ ወይም ኤጲስ ቆጶስ በፅዮን ባለ ኤጲስ ቆጶስ የሚሰጥ [ሀ]የምስክር ወረቀት እያንዳንዱን ሰው ተቀባይ ያደርገዋል፣ እናም ለሁሉም ነገሮች መልስ ይሰጣል፣ እንደ ብልህ [ለ]መጋቢ እና ታማኝ አገልጋይም ያስቀጥረዋል፤

፲፰ አለበለዚያም በፅዮን ኤጲስ ቆጶስ ተቀባይነትን አያገኝም።

፲፱ እናም አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለዚህ የወይን ስፍራ ቤተክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ መግለጫ የሚሰጥ እያንዳንዱ ሽማግሌ፣ ለራሱ እና ለመግለጫው በሁሉም ነገሮች ማረጋገጫ ይሆንለት ዘንድ እንዲያቀርብ፣ ባገለገለባት ቤተክርስቲያን ወይም ለቤተክርስቲያናቱ ብቁ ስለመሆኑ ምስክር ይሰጥ።

፫ ሐ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፪፤ ፻፬፥፲፩–፲፫።
፬ ሀ ማቴ. ፳፬፥፵፭–፵፯።
ለ ት. እና ቃ. ፶፱፥፪።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፩፤ ፵፮፥፳፯፤ ፶፰፥፲፯–፲፰፤ ፻፯፥፷፯–፷፰።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ዊትኒ፣ ኒውል ኬ።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፸፥፯–፲፩፤ ፸፰፥፫።
ቅ.መ.መ. ጎተራ።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፭፥፳፬።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴–፴፩።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣ የቅድስና ህግ።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፷፬፤ ፹፬።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፪።

፳ እና ደግሞም፣ [ሀ]የተጻፉትን ነገሮችን በመመልከት ሀላፊነት የተሰጣቸው አገልጋዮቼም ከኤጲስ ቆጶስ ወይም ከኤጲስ ቆጶሳት በሁሉም ነገሮች እርዳታ የማግኘት መብት አላቸው—

፳፩ ያም [ሀ]ራዕዮችም እንዲታተሙ፣ እናም እስከ ምድር ዳርቻ እንዲሄዱ፤ ቤተክርስቲያኗን በሁሉም ነገሮች የሚረዱትን ገንዘቦች ያገኙ ዘንድ፤

፳፪ በሁሉም ነገሮች ራሳቸውን ተቀባይ እንዲያደርጉ፣ እናም እንደ ብልህ መጋቢም ይረጋገጥላቸው ዘንድ ነው።

፳፫ እናም አሁን፣ እነሆ፣ ይህም፣ በተመሰረተችበት በማንኛውም ምድር ውስጥ፣ ለቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፎች ሁሉ ምሳሌ ይሆናል። እናም አሁን፣ የምለውን አበቃለሁ። አሜን።

፳፬ ስለቤተክርስቲያኗ አባላት፣ ከመንግስት ህግጋት በተጨማሪም ጥቂት ቃላት—በመንፈስ ቅዱስ ወደ ፅዮን እንዲሄዱ [ሀ]የተመደቡት፣ እናም ወደ ፅዮን ለመጓዝ እድለኛም የሆኑት—

፳፭ ከቤተክርስቲያኗ ሶስት ሽማግሌዎች፣ ወይም ከኤጲስ ቆጶስ የምስክር ወረቀትን፣ ለኤጲስ ቆጶሱ ይውሰዱ፤

፳፮ አለበለዚያም ወደ ፅዮን ምድር የሚሄደውም እንደ ብልህ መጋቢ አይረጋገጥለትም። ይህም ደግሞ ምሳሌ ነው። አሜን።

ክፍል ፸፫

በጥር ፲፥ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፥ በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። ካለፈው ህዳር መጀመሪያ ጀምሮ፥ ነቢዩ እና ስድኒ ሪግደን በመስበክ ተጠምደው ነበር፥ እናም በዚህም የተነሳ በቤተክርስቲያኗ ላይ ተነስቶ የነበረውን ጥላቻ ለመቀነስ ብዙ ነገሮችን አከናውነው ነበር (የክፍል ፸፩ ርዕስን ተመልከቱ)

፩–፪፥ ሽማግሌዎች በመስበክ ይቀጥሉ፤ ፫–፮፥ ጆሴፍ ስሚዝ እና ስድኒ ሪግደን መፅሀፍ ቅዱስ እስኪገባደድ ድረስ መተርጎምን ይቀጥሉ።

፩ በእውነትም ጌታ እንዲህ ይላልና፣ እስከ ጉባኤ ድረስ ወንጌሌን በመስበክ፣ እናም በአካባቢው ዙሪያ የሚገኙትን ቤተክርስቲያኖችን በማበረታታት [ሀ]ይቀጥሉ ዘንድ ፍቃዴ ነው፤

፪ እና ከዚያም፣ እነሆ፣ በጉባኤው [ሀ]ድምፅ የተለያዩት ተልዕኮአቸው ምን እንደሆኑም ይገለፅላቸዋል።

፫ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዮቼ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ስድኒ ሪግደን፣ ጌታም እንዲህ ይላል፣ ዳግም [ሀ]መተርጎም [ለ]የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው፤

፬ እናም፣ በተቻለ መጠን፣ እስከ ጉባኤው ድረስም በአካባቢው ዙሪያ ውስጥ ስበኩ፤ እናም ከዚያም ይህም እስኪገባደድ ድረስ የትርጉምን ስራ መቀጠላችሁ አስፈላጊ ነው።

፳ ሀ ት. እና ቃ. ፸፥፫–፮።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
፸፫ ፩ ሀ ይህም በሚስዮን ላይ ያሉት ማለት ነው፤ ት. እና ቃ. ፵፯–፷፷ ተመልከቱ።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፷፫።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷–፷፩፤ ፸፮፥፲፭። ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
ለ ይህም ጆሴፍ እና ስድኒ ከዚህ በፊት መፅሐፍ ቅዱስን መተርጎም እንዲያቆሙና ወንጌልን እንዲሰብኩ ታዘው ነበር ማለት ነው። ት. እና ቃ. ፸፩፥፪።

፭ እናም ተጨማሪ እውቀቶች እስከሚሰጣቸው ድረስ፣ እንዲሁም እንደተጻፈው፣ ይህም ለሽማግሌዎች ምሳሌ ይሁን።

፮ አሁን ምንም ተጨማሪ በዚህ ጊዜ አልሰጣችሁም። ወገባችሁን [ሀ]ታጠቁ እናም በመጠን ኑሩ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፸፬

በ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ በዌይን አውራጃ፣ ኒው ዮርክ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ቤተክርስቲያኗ ከመደራጀቷ በፊትም፣ ነቢዮ ስለ ርዕሱ መልስ እንዲፈልግ ያደረጉ ስለትክክለኛው የጥምቀት መንገድ ጥያቄዎች ነበሩ። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፣ ይህ ራዕይ የህጻናት ጥምቀት ተቀባይነትን ለማሳየት ሁልጊዜም የሚጠቀሙበትን የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሰት፣ ፩ ቆሮንቶስ ፯፥፲፬ን የሚያብራራ ነው።

፩–፭፣ ጳውሎስ በጊዜው የነበረችውን ቤተክርስቲያን የሙሴን ህግጋትን እንዳታከብር መከረ፤ ፮–፯፣ ህጻናት ልጆች ቅዱስ ናቸው እናም በኃጢአት ክፍያውም የተቀደሱ ናቸው።

፩ [ሀ]ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና፥ ያላመነችም ሚስት በባልዋ ተቀድሳለች፤ አለዚያ ልጆቻችሁ ርኩሳን በሆኑ ነበር፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።

፪ አሁን፣ በሐዋርያት ዘመን የግርዘት ህግ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በማያምኑት አይሁዶች ዘንድ ይተገበር ነበር።

፫ እናም እንዲህ ሆነ በህዝብም መካከል የግርዘት ህግን የሚመለከት ታላቅ [ሀ]ክርክር ተነስቶ ነበር፣ ያላመነ ባል ልጆቹ [ለ]እንዲገረዙ እና ተፈጽሞ ለነበረውም ለሙሴ [ሐ]ህግ ተገዢ እንዲሆን ፍላጎት ነበረውና።

፬ እናም እንዲህም ሆነ፣ ልጆቹም በሙሴ ህግ ተገዢ ሆነው በማደጋቸው፣ የአባቶቻቸውን [ሀ]ባህሎች ተከተሉ እናም በክርስቶስ ወንጌል አላመኑም፣ በዚህም ያልተቀደሱ ሆኑ።

፭ ስለዚህ፣ በዚህም ምክንያት ነው ሐዋርያው ለቤተክርስቲያኗ ከጌታ ሳይሆን ከራሱ፣ በመካከላቸው የሙሴ [ሀ]ህግ ካልተሻረ በስተቀር የሚያምኑ ከማያምኑ ጋር [ለ]አንድነት የላቸውምበማለት የጻፈው፣

፮ ልጆቻቸው እንዳይገረዙ፤ እና ይህም በአይሁዶች መካከል ይተገበር ስለነበር፣ ህጻናት ልጆች አይጸደቁም የሚለው ባህልም እንዲቀር የትእዛዝን ፅሑፍ ሰጣቸው፤

፯ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ [ሀ]የኃጢአት ክፍያ አማካይነት [ለ]ስለተቀደሱ ህጻናት [ሐ]ልጆች [መ]የተቀደሱ ናቸው፤ እና ይህም የቅዱሳት መጻህፍት ትርጉም ነው።

ክፍል ፸፭

በጥር ፳፭፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ በአምኸርስት ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ

፮ሀ ፩ ጴጥ. ፩፥፲፫።
፸፬ ፩ሀ ፩ ቆሮ. ፯፥፲፬–፲፱።
፫ሀ የሐዋ. ፲፭፥፩–፴፭፤ ገላ. ፪፥፩–፭።
ለ ቅ.መ.መ. መግረዝ።
ሐ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ባህል።
፭ሀ ፪ ኔፊ ፳፭፥፳፬–፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—በሀይማኖቶች መካከል መጋባት።
፯ሀ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
ሐ ሞሮኒ ፰፥፰–፲፭፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥፵፮–፵፯፤ ፻፴፯፥፲።
መ ቅ.መ.መ. ደህንነት—የልጆች ደህንነት።

በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ክፍል በአንድ ቀን የተሰጡ ሁለት የተለያዩ ራዕዮችን (የመጀመሪያው ከቁጥር ፩ እስከ ፳፪ ውስጥ እና ሁለተኛው ከቁጥር ፳፫ እስከ ፴፮ ውስጥ ያሉትን) የያዘ ነው። ጊዜውም ጆሴፍ ስሚዝ እንደ ታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት ተደግፎ የተሾመበት ጉባኤ ነበር። መልእክታቸውን ሰዎች እንዲገባቸው በሚያደርጉበት ጊዜ ችግር ያጋጠማቸው አንዳንድ ሽማግሌዎች ወዲያውኑ ስለ ሀላፊነታቸው በዝርዝር ለመማር ፍላጎት አደረባቸው። እነዚህ ራዕዮች ተከትለው መጡ።

፩–፭፣ ወንጌልን የሚሰብኩ ታማኝ ሽማግሌዎች ዘለአለማዊ ህይወትን ያገኛሉ፤ ፮–፲፪፣ ሁሉንም ነገሮች የሚያስተምረውን አፅናኙን ለመቀበል ጸልዩ፣ ፲፫–፳፪፣ መልእክታቸውን በማይቀበሉት ላይ ሽማግሌዎች በፍርድ ይቀመጣሉ፤ ፳፫–፴፮፣ የሚስዮኖች ቤተሰቦች ከቤተክርስቲያኗ እርዳታን ይቀበሉ።

፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ፣ እንዲሁም [ሀ]አልፋና ኦሜጋ፣ ጌታችሁ እና አምላካችሁ፣ በመንፈስ [ለ]ድምፅም እናገራለሁ—

፪ እናንት ወንጌሌን ለመስበክ፣ እና [ሀ]የወይን ስፍራዬን [ለ]ለመግረዝ ስማችሁን የሰጣችሁ ሆይ፣ አድምጡ።

፫ እነሆ፣ እንዲህ እላችኋለሁ ሳትዘገዩ፣ ወይም [ሀ]ስራ ሳትፈቱ፣ በአቅማችሁ ሁሉ እየሰራችሁ ትሄዱ ዘንድ ፍቃዴ ነው—

፬ በሰጠኋችሁ ራዕዮች እና ትእዛዛት መሰረት [ሀ]እውነትን [ለ]በማወጅ ድምጻችሁን እንደ መለከት ድምጽ ከፍ አድርጉ።

፭ እናም ታማኝ ብትሆኑ ብዙ [ሀ]ነዶም በጀርባችሁ ትሸከማላችሁ፣ እናም [ለ]በክብር፣ እናም [ሐ]በግርማ፣ [መ]አለሚችነት፣ እናም [ሠ]በዘለአለም ሕይወት [ረ]አክሊልም ይጫንላችኋል።

፮ ስለዚህ፣ ለአገልጋዬ ዊልያም መክለለን በእውነትም እለዋለሁ፣ ወደ ምስራቅ አገሮች እንዲሄድ የሰጠሁትን ትእዛዝ [ሀ]ሽሬዋለሁ፤

፯ እናም አዲስ ተልዕኮ እና አዲስ ትእዛዝንም እሰጠዋለሁ፣ በዚህም እኔ ጌታ ለልቡ [ሀ]ስለማጉረምረሙም [ለ]እገስጸዋለሁ፤

፰ እናም ኃጢአትን ሰርቷል፤ ይሁን እንጂ፣ ይቅርታ ሰጥቼዋለሁ እና ዳግም እንዲህም እለዋለሁ፣ ወደ ደቡብ አገሮች ሂድ።

፱ እናም አገልጋዬ ሉክ ጆንሰን ከእርሱም ጋር ይሂድ፣ እናም ያዘዝኳቸውን ነገሮችንም ያውጁ—

፲ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉንም ነገሮች የሚያስተምራቸውን [ሀ]አፅናኙን በጌታ ስም በመጥራትም—

፲፩ እንዳይታክቱም ዘወትር [ሀ]ይጸልዩ፤ እና ይህን እስካደረጉ ድረስ፣ እስከመጨረሻም አብሬአቸው እሆናለሁ።

፲፪ እነሆ፣ ይህም እናንተን በተመልከተ የጌታ አምላካችሁ ፈቃድ ነው። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

፲፫ እናም ዳግም፣ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ አገልጋዬ [ሀ]ኦርሰን ሀይድ እና አገልጋዬ [ለ]ሳሙኤል ኤች ስሚዝ ወደ ምስራቅ አገሮች ጎዞአቸውን ይጀምሩ፣ እናም ያዘዝኳቸውን ነገሮች ያውጁ፤ እናም ታማኝም

፸፭ ፩ሀ ራዕ. ፩፥፰።
ቅ.መ.መ. አልፋ
እና ኦሜጋ።
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፪ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
ለ ያዕቆ. ፭፥፳፪።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣
ስራ ፈቺ።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፥፴፯።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፭ሀ መዝ. ፻፳፮፥፮፤
አልማ ፳፮፥፭።
ለ ቅ.መ.መ. ክብር።
ሐ ቅ.መ.መ. ክብር።
መ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣
አለሚችነት።
ሠ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም
ህይወት።
ረ ቅ.መ.መ. አክሊል።
፮ሀ ት. እና ቃ. ፶፮።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ሀሳቦች፤
ማጉረምረም።
ለ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፲ሀ ዮሐ. ፲፬፥፳፮።
ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፲፩ሀ ፪ ኔፊ ፴፪፥፱።
፲፫ሀ ቅ.መ.መ. ሀይድ፣ ኦርሰን።
ለ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ሳሙኤል ኤች።

ቢሆኑ፣ እስከ መጨረሻም [ሐ]አብሬአቸው እሆናለሁ።

፲፬ እና ደግሞም፣ በእውነት ለአገልጋዩ ላይመን ጀንሰን፣ እናም ለአገልጋዩ [ሀ]ኦርሰን ፕራት ይህን እላቸዋለሁ፣ እነርሱም ወደ ምስራቅ አገሮች ጉዞአቸውን ያቅኑ፣ እናም እነሆ፣ እስከ መጨረሻውም እኔ ከእነርሱ ጋር ነኝና።

፲፭ እና ደግሞም፣ ለአገልጋዩ አሳ ዶድስ፣ እና ለአገልጋዩ ካልቭስ ውልሰን እናገራለሁ፣ እነርሱም ወደ ምእራብ አገሮች ጉዞአቸውን ያቅኑ፣ እናም እንዳዘዝኳቸው ወንጌሌን ያውጁ።

፲፮ እናም ታማኝ የሆነውም ሁሉንም ነገሮች ያሸንፋል፣ እናም በመጨረሻም ቀን [ሀ]ከፍ ይደረጋል።

፲፯ እና ደግሞም፣ ለአገልጋዬ ሜጀር ኤን አሽሊ እና ለአገልጋዬ በር ሪግስ እላቸዋለሁ፣ ወደ ደቡብ አገሮችም ጉዞአቸውን ያቅኑ።

፲፰ አዎን፣ ሁሉም እንዳዘዝኳቸው፣ በየቤቱ፣ እና በየመንደሩ፣ እና በየከተማው ይጓዙ።

፲፱ እናም በሚገቡበትም ቤት ውስጥ፣ እና ከተቀበሏችሁም፣ በቤቱ ላይ በረከታችሁን ተዉ።

፳ እናም በምትገቡበትም ቤት ውስጥ፣ ባይቀበሏችሁም፣ በቶሎ ከቤቱ ውጡ፣ እናም ምስክር እንዲሆንባቸው ከእግራችሁ ትቢያን [ሀ]አራግፉ።

፳፩ እናም [ሀ]በደስታ እና በስኬታማነት ይሞላሉ፤ እናም ይህን እወቁ፣ [ለ]በፍርድም ቀን የእዚያ ቤት ፈራጆች ትሆናላችሁ እናም ትኮንናቸዋላችሁም፤

፳፪ እናም ከዚያ ቤት ይልቅ ለአረመኔው በፍርድ ቀን ይቀልለታል፤ ስለዚህ፣ ወገባችሁን [ሀ]ታጠቁ እናም ታማኝ ሁኑ፣ እናም ሁሉንም ነገሮች ታሸንፋላችሁ፣ እናም በመጨረሻም ቀን ከፍ ትደረጋላችሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፳፫ ደግሞም፣ ጌታ ለእናንተ እንዲህ ይላል፣ ስለእናንተ ያለውን ፈቃዱን ለማወቅ ስማችሁን የሰጣችሁ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች ሆይ—

፳፬ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ እነዚያን ቤተሰቦች መርዳት፣ እናም የተጠሩት እና ወደ አለም ወንጌልን ለመስበክ መሄድ ያለባቸውን ቤተሰቦች መርዳት፣ የቤተክርስቲያኗ ሀላፊነት ነው።

፳፭ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ ይህን ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፣ ወንድሞቻችሁ ልቦቻቸውን ለመክፈት ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ፣ ለቤተሰቦቻችሁ ስፍራዎችን ተቀበሉ።

፳፮ እናም ስፍራዎችን፣ እና የቤተክርስቲያናን እርዳታ ለቤተሰባቸው ለመቀበል የሚችሉት እንደነዚህ አይነቶች፣ ወደ አለም፣ ወደ ምስራቅም ወይም ምዕራብ፣ ወይም ሰሜን፣ ወይም ወደ ደቡብ፣ ከመሄድ እንዳይቀሩ።

፳፯ ይጠይቁ እናም ይቀበላሉ፣ ያንኳኩ እናም ይከፈትላቸዋል፣ እናም ከላይም፣ እንዲሁም [ሀ]ከአፅናኙ ዘንድ፣ የት መሄድ እንዳለባቸው ያውቃሉ።

፳፰ እና ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]ቤተሰቡን [ለ]የማስተዳደር ሀላፊነት ያለበት እያንዳንዱም ሰው፣ ያስተዳድር፣ እናም ዘውዱን በምንም አያጣውም፣ እናም በቤተክርስቲያናም ውስጥ ያገልግል።

፳፱ እያንዳንዱም ሰው በሁሉም ነገሮች [ሀ]ይትጋ። እናም [ለ]ስራ ፈት የሆነ፣ ንስሀ ካልገባ እና መንገዱን ካላሻሻለ፣ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ስፍራ አይኖረውም።

፲፫ ሐ ማቴ. ፳፰፥፲፱–፳።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ፕራት፣ ኦርሰን።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፭፥፴፭።
፳ ሀ ማቴ. ፲፥፲፬፤
ሉቃ. ፲፥፲፩–፲፪፤
ት. እና ቃ. ፳፬፥፲፭፤
፷፥፲፭።

፳፩ ሀ ማቴ. ፭፥፲፩–፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።
፳፪ ሀ ኤፌ. ፮፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፭–፲፰።
፳፯ ሀ ፪ ኔፊ ፴፪፥፬፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥፮።
ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።

፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ።
ለ ፩ ጢሞ. ፭፥፰፤
ት. እና ቃ. ፹፫፥፪።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣
ስራ ፈቺ።

፴ ስለዚህ፣ አገልጋዩ ስሚኦን ካርተር እና አገልጋዩ ኢመር ሀሪስ በአገልግሎት ይተባበሩ፤

፴፩ እና ደግሞም አገልጋዩ ኤዝራ ታየር እና አገልጋዩ [ሀ]ቶማስ ቢ. ማርሽም፤

፴፪ እና ደግሞም አገልጋዩ ሀይረም ስሚዝ እና አገልጋዩ ሬይኖልድ ካሁንም፤

፴፫ እና ደግሞም አገልጋዩ ዳንኤል ስታተን እና አገልጋዩ ሲሞር ብረንሰንም፤

፴፬ እና ደግሞም አገልጋዩ ሲልቨስተር ስሚዝ እና አገልጋዩ ጊድየን ካርተር

፴፭ እና ደግሞም አገልጋዩ ራግልስ ኤምስ እና አገልጋዩ ስቲቨን ባርነትም፤

፴፮ እና ደግሞም አገልጋዩ ማይካ ቢ. ዌልተን እና አገልጋዩ ኢድን ስሚዝም። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፸፮

በየካቲት ፲፮፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። ከዚህ ራዕይ ጽሑፉ አስቀድሞ፣ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፥ "ከአምኸርስት ጉባኤ እንደተመለስኩ፣ ቅዱሳን መጻህፍትን መተርጎምን ቀጠልኩ። ከተቀበልኳቸው ከተለያዩ ራዕዮች፣ የሰውን ልጅ ደህንነት የሚመለከቱ ብዙ አስፈላጊ ነጥቦች ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተወሰዱ፣ ወይም ከመከማቸቱ በፊት እንደጠፉ ግልፅ ነበር። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ በስጋ ባከናወነው በኩል ደመወዙን የሚሰጥ ከሆነ፣ ለቅዱሳን የዘለአለም ቤት እንዲሆን የተወሰነበት ሰማይ ከአንድ በላይ የሆኑ መንግስታትን እንደሚያጠቃልል ቀሪው እውነት በራሱ የሚያስረዳ ነው። በዚህም መሰረት፣ . . . የቅዱስ ዮሐንስን ወንጌል ስንተረጉም፣ እኔ እና ሽማግሌ ሪግደን የሚቀጥለውን ራዕይ ተመለከትን።" ራዕዩ በተሰጠበት ግዜ፣ ነቢዩ ዮሐንስ ፭፥ ፳፱ን እየተረጎመ ነበር።

፩–፬፣ ጌታ እግዚአብሔር ነው፤ ፭–፲፣ የመንግስት ሚስጥራት ለታማኞቹ ሁሉ ይገለጣሉ፤ ፲፩–፲፯፣ ሁሉም በጻድቃንም ሆነ በኃጢአተኛ ትንሳኤ ከሞት ይነሳሉ፤ ፲፰–፳፬፣ የብዙ አለማት ኗሪዎች በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ አማካይነት የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ናቸው፤ ፳፭–፳፱፣ የእግዚአብሔር መልአክ ተጣለ እናም ዲያብሎስም ሆነ፤ ፴–፵፱፣ የጥፋት ልጆችም በዘለአለም እርግማን ይሰቃያሉ፤ ሌሎች ሁሉም የተወሰነ የደህንነትን ደረጃ ያገኛሉ፤ ፶–፸፣ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ዘለአለማዊ ክብር ያላቸው ፍጡራን ክብር እና ደመወዝ ተገልጿል፤ ፸፩–፹፣ የተረስትሪያልን መንግስት የሚወርሱትም ተገልጸዋል፤ ፹፩–፻፲፫፣ በቲለስቲያል፣ ተረስትሪያል፣ እና በሰለስቲያል ክብሮች ውስጥ ያሉት ሁኔታቸው ተገልጿዋል፤ ፻፲፬–፻፲፱፣ ታማኝ የሆኑት የእግዚአብሔርን መንግስት ሚስጥራት በመንፈስ ቅዱስ ሀይል አማካይነት ማየት እና መረዳት ይችላሉ።

፩ [ሀ]አድምጡ፣ እናንተ ሰማያት ሆይ፣ ምድር ሆይ ጆሮሽን ስጪ፣ እናም ነዋሪዎችዋም ተደሰቱ፣ ጌታ [ለ]እግዚአብሔር ነውና፣ እናም ከእርሱም በቀር [ሐ]ማንም [መ]አዳኝ የለምና።

፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማርሽ፣ ቶማስ ቢ።

፸፮ ፩ ሀ ኢሳ. ፩፥ ፪።

ለ ኤር. ፲፥ ፲። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።

ሐ ኢሳ. ፵፫፥ ፲፩፤ ሆሴ. ፲፫፥ ፬።

መ ቅ.መ.መ. አዳኝ።

፪ ጥበቡ [ሀ]ታላቅ ነው፣ መንገዶቹም [ለ]ድንቅ ናቸው፣ እናም የአሰራሩንም መጠን ማንም ሊያገኘው አይቻለውም።

፫ [ሀ]አላማዎቹ አይወድቁም፣ እጁንም ይከለክል ዘንድ የሚቻለው ማንም የለም።

፬ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም [ሀ]አንድ ነው፣ እና አመታቱም ከቶ [ለ]አያልቁም።

፭ ጌታ እንዲህ ይላል—እኔ ጌታ [ሀ]ለሚፈሩኝ [ለ]መሀሪ እና ይቅር ባይ ነኝ፣ እና በፅድቅ እና በእውነት እስከ መጨረሻው [ሐ]የሚያገለግሉኝንም በማክበር እደሰታለሁ።

፮ ዋጋቸውም ታላቅ እና [ሀ]ክብራቸውም ዘለአለማዊ ይሆናል።

፯ እና ለእነርሱም ሁሉንም [ሀ]ሚስጥራት፣ አዎን፣ ከጥንት ጀምሮ የተሰወሩትን የመንግስቴን ሚስጥራት ሁሉ [ለ]እገልጽላቸዋለሁ፣ እና በሚመጡት ዘመናትም መንግስቴን የተመለከቱትን ነገሮች ሁሉ በጎ ፈቃዴን ያውቁ ዘንድ አደርጋቸዋለሁ።

፰ አዎን፣ የዘለአለምን ድንቆችንም ያውቃሉ፣ የሚመጡትን፣ እንዲሁም የብዙ ትውልዶች ነገሮችንም አሳያቸዋለሁ።

፱ እናም [ሀ]ጥበባቸውም ታላቅ ይሆናል፣ እናም [ለ]መረዳታቸውም እስከ ሰማያት የዘለቀ ይሆናል፤ እናም የጥበበኞችም ጥበብ ትጠፋለችና፣ እናም የአስተዋዮችም [ሐ]ማስተዋል ትሰወራለች።

፲ [ሀ]በመንፈሴም [ለ]አብራላቸዋለሁና፣ እናም የፈቃዴን ሚስጥራት—አዎን እንዲሁም [ሐ]ዓይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን፣ በሰውም ልብ ያልታሰቡትንም ነገሮች፣ [መ]በሀይሌ አሳውቃቸዋለሁ።

፲፩ እኛ፣ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ስድኒ ሪግደን፣ በጌታችን አንድ ሺ ስምንት መቶ ሰላሳ ሁለት አመት በየካቲት አስራ ስድስት ቀን [ሀ]በመንፈስ ሆነን—

፲፪ [ሀ]በመንፈስ ሀይልም፣ የእግዚአብሔርን ነገሮች ለማየት እና ለመረዳት፣ [ለ]አይኖቻችን ተከፈቱ እናም እውቀቶቻችንም ብሩህ ሆኑ—

፲፫ እንዲሁም አለም ከመፈጠሯ በፊት ከመጀመሪያ ጀምሮ የነበሩት ነገሮችም፣ በአብ እቅፍ ውስጥ በነበረው በአንድያ ልጁ በኩል፣ [ሀ]ከመጀመሪያው ጀምሮ፣ በአብ ተቀድሰው የነበሩትም፤

፲፬ ስለ እርሱም ምስክርን እንሰጣለን፤ እናም የምንመሰክረውም፣ ልጅ ስለሆነው፣ ያየነው እናም በሰማያዊ [ሀ]ራዕይ [ለ]ስላነጋገርነው ስለኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ወንጌል ነው።

፲፭ ጌታ የሰጠንን [ሀ]የትርጉም ስራ እየሰራን እያለ፣ እንደሚከተለው ወደ ተሰጠን ወደ ዮሐንስ መፅሐፍ በአምስተኛው ምዕራፍ ቁጥር ሀያ ዘጠኝ ላይ ደረስን—

፲፮ ስለ ሙታን ትንሳኤ፣ እነዚያ [ሀ]የሰው ልጅ ድምፅ [ለ]ስለ ሚሰሙት በመናገር፥

፲፯ [ሀ]መልካምም ያደረጉ [ለ]ጻድቃን

፪ ሀ ፪ ኔፊ ፪፥፳፬፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፩–፫።
ለ ራዕ. ፲፭፥፫።
፫ ሀ ፩ ነገሥ. ፰፥፶፮፤
ት. እና ቃ. ፩፥፴፰፤
፷፬፥፴፩።
፬ ሀ ዕብ. ፲፫፥፰፤
ት. እና ቃ. ፴፭፥፩፤
፴፰፥፩–፬፤ ፴፱፥፩–፫።
ለ መዝ. ፻፪፥፳፭–፳፯፤
ዕብ. ፩፥፲፪።
፭ ሀ ዘዳግ. ፮፥፲፫፤
ኢያ. ፬፥፳፫–፳፬።
ቅ.መ.መ. ማክበር፤
ፍርሀት።
ለ ዘፀአ. ፴፬፥፮፤
መዝ. ፻፫፥፰።
ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ት. እና ቃ. ፬፥፪።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል
ክብር።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ሚስጥሮች።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፷፩፤ ፹፱፥፬፤
፺፰፥፲፪፤ ፻፳፩፥፳፮–፴፫።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
ሐ ኢሳ. ፳፱፥፲፬፤
፪ ኔፊ ፱፥፳፰–፳፱።
፲ ሀ ሞሮኒ ፲፥፭።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት፤
ራዕይ።
ሐ ኢሳ. ፷፬፥፬፤
፩ ቆሮ. ፪፥፱፤
፫ ኔፊ ፲፯፥፲፭–፲፯፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፲፬–፻፲፮።
መ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፲፩ ሀ ራዕ. ፩፥፲።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መለወጥ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፲፥፩፤ ፻፴፯፥፩፤
፻፴፰፥፲፩፤ ፳፱።
፲፫ ሀ ሙሴ ፬፥፪።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፱፥፶፯።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ
ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. የሰው ልጅ።
ለ ዮሐ. ፭፥፳፰።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ለ የሐዋ. ፳፬፥፲፭።

[ሐ]ትንሣኤ፣ ክፉትንም ያደረጉ በኃጥአን ትንሣኤ ይነሳሉ።

፲፰ አሁን ይህም እንድንደነቅ አደረገን፣ ምክንያቱም በመንፈስ ለእኛ ተሰጥቶን ነበርና።

፲፱ እናም በእነዚህ ነገሮች ላይ [ሀ]እያሰላሰልን ሳለን፣ ጌታ የመረዳት አይኖቻችንን ነካ እናም ተከፈቱ፣ እናም የጌታ ክብርም በዙሪያችን በራ።

፳ እናም የወልድን [ሀ]ክብር፣ [ለ]በአብ [ሐ]ቀኝ በኩል ተመለከትን እናም እርሱን በሙላት ተቀበልን፤

፳፩ እናም ቅዱሳን [ሀ]መላእክት፣ እና በዙፋኑ ፊት [ለ]ተቀድሰው የነበሩትን፣ እግዚአብሔርን ሲያመልኩት እና እርሱንም ለዘለአለም [ሐ]የሚያመልከውን በጉን አየን።

፳፪ እናም አሁን፣ ስለ እርሱ ከተሰጡት ብዙ [ሀ]ምስክሮች በኋላ፣ ይህም በመጨረሻ ስለ እርሱ የምንሰጠው ምስክርነት፥ እርሱ [ለ]ህያው መሆኑን ነው!

፳፫ [ሀ]በእግዚአብሔር ቀኝ [ለ]አይተነዋልና፤ እናም እርሱ የአብ [ሐ]አንድያ ልጅ እንደሆነም ሲመሰክርም ድምፅ ሰምተናል—

፳፬ [ሀ]አለማትም [ለ]በእርሱ፣ እናም በእርሱም አማካይነት፣ እናም ከእርሱም ዘንድ ናቸው እናም ተፈጥረዋል፣ እናም ነዋሪዎችዋም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች [ሐ]ልጆች ናቸው።

፳፭ እናም ይህንም አየን፣ እንመሰክራለንም፣ በእግዚአብሔር ፊት ስልጣን የነበረው፣ አብ ይወደው የነበረው እና በአብም እቅፍ የነበረው በአንድያ ልጁ ያመጸው፣ የእግዚአብሔር [ሀ]መልአክ ከእግዚአብሔር እና ከወልድ ፊት ተጥሎ ነበር፣

፳፮ እና የጥፋት ልጅ ተብሎም ተጠራ፣ ሰማያትም ስለእርሱ አነቡ—እርሱም [ሀ]ሉሲፈር፣ የንጋት ልጅ ነበር።

፳፯ እናም የንጋት ልጅ የሆነው እርሱም [ሀ]የወደቀ ነው፣ ወድቋልም፣ ይህንንም ተመለከትን፣ እናም አስተዋልን!

፳፰ እናም በመንፈስ እያለን፣ ጌታ ራዕይን እንድንፅፍ አዘዘን፤ ሰይጣንን፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ [ሀ]ያመጸውን፣ እና የእግዚአብሔርንና የእርሱን ክርስቶስ መንግስት ለመውሰድ የሻውን የቀደመውን [ለ]እባብ [ሐ]ዲያብሎስ አይተነዋልና—

፳፱ እነሆ፣ ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ጋርም [ሀ]ተዋጋ፣ እናም በዙሪያቸውም ከበባቸው።

፴ እናም በራዕይም የተዋጋቸውን እና ያሸነፋቸውን ስቃይ ተመለከትን፣ እንደህም ሲል የጌታ ድምፅ ወደ እኛ መጣ፥

፴፩ ጌታም ሀይሌን ስለሚያውቁት ሁሉ፣ እናም በዚህም ተካፋይ ስለሆኑት፣ እናም በዲያብሎስም ሀይል አማካይነት ራሳቸውን [ሀ]እንዲሸነፉ እውነትንም እንዲክዱና ሀይሌም እንዲረክስ የፈቀዱትን በተመለከተ እንዲህ ይላል—

፴፪ ባይወለዱ ይሻላቸው ብዬ ያልኳቸው፣ [ሀ]የጥፋት [ለ]ልጆች እነርሱ ናቸው፤

፲፯ ሐ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ— እግዚአብሔር አብ።
ሐ የሐዋ. ፯፥፶፮።
፳፩ ሀ ማቴ. ፳፭፥፴፩፤ ት. እና ቃ. ፻፴፥፮–፯፤ ፻፴፮፥፴፯።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
ለ ት. እና ቃ. ፳፥፲፯።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ— እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ክርስቶስ ከሟችነት በኋላ መገለጡ።
ሐ ዮሐ. ፩፥፲፬። ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።
፳፬ ሀ ሙሴ ፩፥፴፩–፴፫፤ ፯፥፴። ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
ለ ዕብ. ፩፥፩–፫፤ ፫ ኔፊ ፱፥፲፭፤ ት. እና ቃ. ፲፬፥፱፤ ፺፫፥፰–፲።
ሐ የሐዋ. ፲፯፥፳፰፣ ፳፱፤ ዕብ. ፲፪፥፱። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፴፮–፴፱፤ ሙሴ ፬፥፩–፬። ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፳፮ ሀ ኢሳ. ፲፬፥፲፪–፲፯። ቅ.መ.መ. አጥቢያ ኮከብ።
፳፯ ሀ ሉቃ. ፲፥፲፰።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. የሰማይ ጦርነት።
ለ ራዕ. ፲፪፥፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፳፱ ሀ ራዕ. ፲፫፥፯፤ ፪ ኔፊ ፪፥፲፰፤ ፳፰፥፲፱–፳፫።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፴፪፤ ሙሴ ፭፥፳፬–፳፮።
ለ ቅ.መ.መ. የጥፋት ልጆች።

፴፫ ከዲያብሎስ እና ከመላእክቱ ጋር ለዘለአለም በእግዚአብሔር ቁጣ ለመሰቃየት የተረገሙ የቁጣ እቃዎች ናቸውና፤

፴፬ እነርሱን በተመለከተ በዚህም አለም ይሁን በሚመጣው አለም [ሀ]ይቅርታ የላቸውም ብያለሁ—

፴፭ ከተቀበሉት በኋላ መንፈስ ቅዱስን፣ እና የአብን አንድያ ልጅ [ሀ]ስለካዱት፣ እናም እርሱንም በራሳቸው [ለ]ስለሰቀሉት እና ስላዋረዱት ይቅርታ የላቸውም።

፴፮ እነዚህም፣ ከዲያብሎስ እና ከመላእክቱ ጋር ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ [ሀ]ባሕር የሚሄዱት ናቸው—

፴፯ እናም ሁለተኛው [ሀ]ሞትም ሀይልን የሚያገኝባቸውም እነርሱ ናቸው፤

፴፰ አዎን፣ በእውነትም፣ ከቁጣው ስቃይ በኋላ፣ በጌታ ዘመንም የማይድኑት እነርሱ [ሀ]ብቻ ናቸው።

፴፱ ሌሎቹም ሁሉ፣ በታረደው፣ አለማትም ከመሰራታቸው አስቀድሞ በአብ እቅፍ በነበረው [ሀ]በበጉ ታላቅ ድል እና ክብር የተነሳ፣ በሙታን [ለ]ትንሳኤ [ሐ]ይመጣሉ።

፵ እና ይህም የሰማያት ድምፅ ለእኛ የመሰከረልን ምስራች [ሀ]ወንጌል ነው—

፵፩ እርሱም፣ እንዲሁም ኢየሱስ፣ ለአለም [ሀ]ሊሰቀልና [ለ]የአለም ኃጢአቶችን [ሐ]ሊሸከም፣ እናም አለምንም [መ]ሊቀድስና፣ ከርኩሳትም [ሠ]ሊያጸዳ ወደ አለም እንደመጣ፣ የሰማያት ድምፅ የመሰከረልን ምስራች ይህ ነው፤

፵፪ በእርሱም አማካይነት አብ በእርሱ ሀይል ያደረጋቸውን እና በእርሱ የተሰሩት ሁሉ [ሀ]ይድኑ ዘንድ፤

፵፫ እርሱም አብን የሚያከብር፣ እናም አብም ከገለጠው በኋላ ወልድን ከሚክዱት የጥፋት ልጆች በስተቀር የእጆቹን ስራዎች ሁሉ የሚያድን ነው።

፵፬ ስለዚህ፣ ከእነርሱም በስተቀር ሁሉን ያድናል—እነርሱም መጨረሻ ወደሌለው፣ [ሀ]የዘለአለም [ለ]ቅጣት ወደሆነው፣ [ሐ]ከዲያብሎስ እና ከመላእክቱ ጋር ገዢ ለመሆን ስቃያቸው የሆነው [መ]ትላቸው ወደ ማይሞትበት እሳቱም ወደ ማይጠፋበት ወደ ዘለአለም ቅጣት ይሄዳሉ—

፵፭ እናም [ሀ]መጨረሻውን፣ ወይም ስፍራውን፣ ወይም ስቃያቸውን ማንም ሰው አያውቅም፤

፵፮ ይህም አልተገለጠም፣ ወይም የዚህ ተካፋዮች ከሆኑት በስተቀር፣ ይህም የተገለጠም አይደለም፣ ወይም ለሰውም አይገለጠም፤

፵፯ ይሁን እንጂ፣ እኔ ጌታ ይህን በራዕይ ለብዙዎች አሳይቻለሁ፣ ነገር ግን ወዲያውም ደግሜ ዘግቼዋለሁ።

፵፰ ስለዚህ፣ የዚህን መጨረሻ፣ ስፋት፣ ከፍታ፣ [ሀ]ጥልቀት፣ እና ስቃይ አልተረዱትም፣ ወይም በዚህ [ለ]ፍርድ [ሐ]ከተመደቡት በስተቀር ማንም ሰው አይረዳውም።

፵፱ እናም ድምፅም እንዲህ ሲል ሰማን፥ ይህን ራዕይ ጻፍ፣ የኃጢአተኞችም ስቃይ መጨረሻ ይህ ነውና።

፶ ደግሞም እንመሰክራለን—አይተን

፴፬ ሀ ማቴ. ፲፪፥፴፩–፴፪። ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።

፴፭ ሀ ፪ ጴጥ. ፪፥፳–፳፪፤ አልማ ፴፱፥፮። ቅ.መ.መ. ይቅርታ የሌለው ኃጢያት።

ለ ዕብ. ፮፥፬–፮፤ ፩ ኔፊ ፲፱፥፯፤ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፳፯።

፴፮ ሀ ራዕ. ፲፱፥፳፤ ፳፥፲፤ ፳፩፥፰፤ ፪ ኔፊ ፱፥፲፮፤ ፳፰፥፳፫፤ አልማ ፲፪፥፲፮–፲፰፤ ት. እና ቃ. ፷፫፥፲፯።

፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።

፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. የጥፋት ልጆች።

፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።

ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።

ሐ ይህም መቤዠት ማለት ነው፤ ቁጥር ፴፰ ተመልከቱ። ሁሉም ከሞት ይነሳሉ። አልማ ፲፩፥፵፩–፵፭ ተመልከቱ። ቅ.መ.መ. ህያው ማድረግ።

፵ ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፥፲፫–፳፪። ቅ.መ.መ. ወንጌል፤ የቤዛነት ዕቅድ።

፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. መሰቀል።

ለ ፩ ዮሐ. ፪፥፩–፪።

ሐ ኢሳ. ፶፫፥፬–፲፪፤ ዕብ. ፱፥፳፰።

መ ቅ.መ.መ. ቅድስና።

ሠ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።

፵፪ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።

፵፬ ሀ ት. እና ቃ. ፲፱፥፮–፲፪።

ለ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።

ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።

መ ኢሳ. ፷፮፥፳፬፤ ማር. ፱፥፵፫–፵፰።

፵፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፳፰–፳፱።

፵፰ ሀ ራዕ. ፳፥፩።

ለ አልማ ፵፪፥፳፪።

ሐ ይህም የፍርድ ውሳኔ መስጠት፣ መመደብ ማለት ነው።

ሰምተናልና፣ እናም ይህም መልካምን በማድረግ በጻድቃት [ሀ]ትንሣኤ የሚነሱትን በሚመለከት የክርስቶስ ወንጌል [ለ]ምስክርነት ይህ ነው—

፶፩ እነርሱም የኢየሱስን ምስክር የተቀበሉ፣ እናም በስሙም [ሀ]ያመኑ እና ቀብሩን በሚመስል [ለ]ድርጊት፣ በስሙ በውሀ ውስጥ [ሐ]በመቀበር [መ]የተጠመቁ ናቸው፣ እና ይህንም ያደረጉት እርሱ በሰጣቸው ትእዛዝ መሰረት ነው—

፶፪ ይህም ትእዛዛትን በማክበርም ከኃጢአታቸው ሁሉ [ሀ]እንዲታጠቡ እና [ለ]እንዲጸዱ፣ እናም ወደዚህ [ሐ]ሀይል [መ]በተሾመው እና በተሳሰረው [ሠ]እጆችንም በመጫን መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ነው፤

፶፫ እናም በእምነት ያሸነፉም፣ እናም መልካም ለሚያደርጉት እና ለእውነተኞች ሁሉ አብ በሚያፈሰው [ሀ]በቅዱሱ የተስፋ መንፈስ [ለ]ታትመዋል።

፶፬ እነርሱም [ሀ]የበኩር ልጅ ቤተክርስቲያን ናቸው።

፶፭ እነርሱም አብ [ሀ]ሁሉንም ነገሮች በእጆቻቸው የሰጣቸው ናቸው—

፶፮ እነርሱም የእርሱን ሙላት እና ክብር የተቀበሉ [ሀ]ካህናት እና ነገስታት ናቸው፤

፶፯ እናም ከአንድያ ልጅ [ሀ]ስርዓት እና [ለ]የሔኖክ ስርዓት ከነበረው እንደ መልከ ጼዴቅ ስርዓት የልዑልም [ሐ]ካህናት ናቸው።

፶፰ ስለዚህ፣ እንደተጻፈውም፣ እነርሱ [ሀ]አማልክቶች፣ እነሆ [ለ]የእግዚአብሔር [ሐ]ልጆች ናቸው፣

፶፱ ስለዚህ፣ ሁሉም ነገሮች የእነርሱ ናቸው፣ በህይወትም ይሁን በሞት፣ ወይም አሁን ያሉ ነገሮች ወይም ወደፊት የሚመጡት ነገሮች፣ [ሀ]ሁሉም የእነርሱ ናቸውም እነርሱ የክርስቶስ ናቸው፣ እናም ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

፷ እናም እነርሱም ሁሉንም ነገሮች [ሀ]ያሸንፋሉ።

፷፩ ስለዚህ፣ ማንም በሰው [ሀ]አይመካ፣ ነገር ግን ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች [ለ]በሚያደርገው በእግዚአብሔር [ሐ]ይመካ።

፷፪ እነዚህም በእግዚአብሔር እና በእርሱ ክርስቶስ [ሀ]ፊት ለዘለአለም [ለ]ይኖራሉ።

፷፫ በምድር በህዝቡ ላይ [ሀ]ሊነግስ በሰማይ ደመና [ለ]በሚመጣበት ጊዜ ይዞአቸው የሚመጣውም [ሐ]እነዚህ ናቸው።

፶ ሀ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፶፩ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፳፭–፳፯፣ ፴፯።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፫።
ሐ ሮሜ ፮፥፫–፭። ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ።
፶፪ ሀ ፪ ኔፊ ፱፥፳፫፤ ሞሮኒ ፰፥፳፭–፳፮።
ለ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
መ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ሠ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
፶፫ ሀ ኤፌ. ፩፥፲፫፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፫–፭። ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
ለ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
፶፬ ሀ ዕብ. ፲፪፥፳፫፤ ት. እና ቃ. ፺፫፥፳፩–፳፪። ቅ.መ.መ. በኩር።
፶፭ ሀ ፪ ጴጥ. ፩፥፫–፬፤ ት. እና ቃ. ፶፥፳፮–፳፰፤ ፹፬፥፴፭–፴፰።
፶፮ ሀ ዘፀአ. ፲፱፥፮፤ ራዕ. ፩፥፭–፮፤ ፳፥፮።
፶፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፩–፬።
ለ ዘፍጥ. ፲፬፥፳፭–፵። ቅ.መ.መ. ሔኖክ።
ሐ ቅ.መ.መ. ካህን፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፶፰ ሀ መዝ. ፹፪፥፩፣ ፮፤ ዮሐ. ፲፥፴፬–፴፮። ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፳፰። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ሐ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴት ልጆች።
፶፱ ሀ ሉቃ. ፲፪፥፵፪–፵፬፤ ፫ ኔፊ ፳፰፥፲፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፮–፴፰።
፷ ሀ ራዕ. ፫፥፭፤ ፳፩፥፯።
፷፩ ሀ ዮሐ. ፭፥፵፩–፵፬፤ ፩ ቆሮ. ፫፥፳፩–፳፫።
ለ ት. እና ቃ. ፵፱፥፮።
ሐ ፪ ኔፊ ፴፫፥፮፤ አልማ ፳፮፥፲፩–፲፮። ቅ.መ.መ. ክብር።
፷፪ ሀ ት. እና ቃ. ፲፬፥፯። ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
ለ መዝ. ፲፭፥፩–፫፤ ፳፬፥፫–፬፤ ፩ ኔፊ ፲፭፥፴፫–፴፬፤ ሙሴ ፮፥፶፯።
፷፫ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፪። ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት።
ለ ማቴ. ፳፬፥፴።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፮–፺፰። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

፷፬ እነዚህም [ሀ]በመጀመሪያው ትንሳኤ ስፍራም የሚኖራቸውም እነዚህ ናቸው።

፷፭ እነዚህም በጻድቃን [ሀ]ትንሳኤ የሚመጡት ናቸው።

፷፮ ወደ [ሀ]ፅዮን [ለ]ተራራ፣ እናም ከሁሉም በላይ ቅዱስ ወደሆነው ሰማያዊ ስፍራ፣ ወደ ህያው እግዚአብሔር ከተማ የሚመጡትም እነዚህ ናቸው።

፷፯ እነዚህም ወደ አእላፋት መላእክት፣ ወደ [ሀ]ሔኖክ እና ወደ [ለ]በኩራት ቤተክርስቲያንና ወደ ታላቁ ጉባኤ የመጡት ናቸው።

፷፰ እነዚህም እግዚአብሔር እና ክርስቶስ ሁሉንም [ሀ]በሚፈርዱበት በሰማይ ስሞቻቸው [ለ]የተጻፉላቸውም ናቸው።

፷፱ እነዚህ [ሀ]የአዲስ ኪዳን አማላጅ በሆነው፣ ይህን ፍጹም [ለ]የኃጢአት ክፍያን በመፈጸም የራሱን [ሐ]ደም በማፍሰስ ባከናወነው በኢየሱስ [መ]ፍጹም የሆኑት ጻድቃን [ሠ]ሰዎች ናቸው።

፸ እነዚህ ሰውነታቸው [ሀ]ሰለስቲያል የሆኑ ናቸው፣ [ለ]ክብራቸውም እንደ [ሐ]ጸሀይ፣ እንዲሁም ከሁሉም በላይ በሆነ የእግዚአብሔር ክብር፣ ክብሩም የጠፈር ጸሀይ አይነተኛ ሆኖ እንደተጻፈ የሆነው ነው።

፸፩ እና ደግሞም፣ [ሀ]የተረስትሪያልን አለም አየን፣ እና እነሆ እናም አስተውሉ፣ እነዚህም የተረስትሪያል የሆኑ፣ [ለ]ጨረቃ ከጠፈር ጸሀይ እንደሚለይ፣ ክብራቸው የአብን ሙላት ከተቀበለው የበኩር ቤተክርስቲያን የተለዩ ናቸው።

፸፪ እነሆ፣ እነዚህም [ሀ]ካለህግ የሞቱት ናቸው፤

፸፫ እና እነርሱ ደግሞም እንደ ሰዎች በሥጋ ይፈረድባቸው ዘንድ ወልድ የጎበኛቸው፣ እናም [ሀ]ወንጌሉንም [ለ]የሰበከላቸው [ሐ]በወኅኒ ውስጥ የነበሩ የሰዎች [መ]ነፍሳት ናቸው፤

፸፬ በስጋ የኢየሱስን [ሀ]ምስክር ያልተቀበሉ፣ ነገር ግን በኋላ የተቀበሉት ናቸው።

፸፭ እነዚህ በምድር የተከበሩ፣ በሰዎች ተንኮል ምክንያት የታወሩ ሰዎች ናቸው።

፸፮ እነርሱ ክብሩን ቢቀበሉም፣ ሙላቱን ግን የማይቀበሉ ናቸው።

፸፯ እነዚህ የወልድን መገኘት ቢቀበሉም፣ የአብን ሙላት የማይቀበሉ ናቸው።

፸፰ ስለዚህ፣ [ሀ]የተረስትሪያል ሰውነቶች እንጂ የሰለስቲያል ሰውነቶች አይደሉምና፣ እናም ጨረቃ ከጸሀይ ልዩ እንደሆነም ክብሩም እንዲሁ ልዩ ነው።

፸፱ እነዚህም በኢየሱስ ምስክርነት [ሀ]ደፋር ያልሆኑት ናቸው፤ ስለዚህ፣ የአምላካችንን መንግስት አክሊል አይቀበሉም።

፹ እናም አሁን ይህም በመንፈስ እያለን ጌታ እንድንፅፈው ያዘዘን ስለ ተረስትሪያል ያየነው ራዕይ መጨረሻ ነው።

፹፩ እና ደግሞም፣ እንዲሁም በጠፈር ውስጥ የኮኮብ ክብር ከጨረቃ ክብር ልዩ

፷፬ ሀ ራዕ. ፳፥፮።
፷፭ ሀ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፷፮ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ኢሳ. ፳፬፥፳፫፤ ዕብ. ፲፪፥፳፪–፳፬፤ ራዕ. ፲፬፥፩፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፪፤ ፻፴፫፥፶፮።
፷፯ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፱–፲፪።
ለ ዕብ. ፲፪፥፳፫፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶፫–፶፬። ቅ.መ.መ. በኩር።
፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
ለ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
፷፱ ሀ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
ሐ ቅ.መ.መ. ደም።
መ ሞሮኒ ፲፥፴፪–፴፫።
ሠ ት. እና ቃ. ፻፳፱፥፫፤ ፻፴፰፥፲፪።
፸ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፳፰–፳፱፤ ፻፴፩፥፩–፬፤ ፻፴፯፥፯–፲። ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
ለ ት. እና ቃ. ፻፴፯፥፩–፬።
ሐ ማቴ. ፲፫፥፵፫።
፸፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፴። ቅ.መ.መ. ተረስትሪያል ክብር።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፵–፵፩።
፸፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፯፥፯፣ ፱። ቅ.መ.መ. ህግ።
፸፫ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ፩ ጴጥ. ፫፥፲፱–፳፤ ፬፥፮፤ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥፳፰–፴፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፱፤ ፻፴፰፥፰። ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት፤ ሲዖል።
መ አልማ ፵፥፲፩–፲፬። ቅ.መ.መ. መንፈስ።
፸፬ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፸፰ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፵–፵፪።
፸፱ ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥፲፮።

እንደሆነ፣ አነስተኛ የሆነውን [ሀ]የቲለስቲያል ክብር ተመለከትን።

፹፪ እነዚህም የክርስቶስን ወንጌል ወይም የኢየሱስን [ሀ]ምስክርነት ያልተቀበሉት ናቸው።

፹፫ እነዚህም መንፈስ ቅዱስን ያልካዱት ናቸው።

፹፬ እነዚህም ወደ [ሀ]ሲኦል የተጣሉት ናቸው።

፹፭ እነዚህ [ሀ]እስከመጨረሻው ትንሳኤ ድረስ፣ ጌታ እንዲሁም ክርስቶስ፣ [ለ]በጉ፣ ስራውን እስከሚጨርስ ድረስ [ሐ]ከዲያብሎስ ነጻ የማይሆኑት ናቸው።

፹፮ እነዚህም ዘለአለማዊ በሆነው አለም ውስጥ የእርሱን ሙላት የማይቀበሉ፣ ነገር ግን በተረስትሪያል አገልግሎት አማካይነት የመንፈስ ቅዱስን ሙላት የሚቀበሉት ናቸው፤

፹፯ እናም ተረስትሪያልም በሰለስቲያል [ሀ]አገልግሎት አማካይነት ይቀበላሉ።

፹፰ እና ደግሞ የቲለስቲያልም እንዲያገለግሉአቸው በተመረጡት መላእክት ወይም ለእነርሱ አገልጋይ መናፍስት እንዲሆኑ በተመረጡ ይህን ይቀበላሉ፤ እነርሱም የደህንነት ወራሾች ይሆናሉና።

፹፱ እናም በሰማያዊ ራዕይ አዕምሮን ሁሉ የሚያልፈውን የቲለስቲያል ክብርን እንደዚህም ተመለከትን፤

፺ እና እግዚአብሔር ከገለጠለት በስተቀር ማንም አያውቀውም።

፺፩ እናም ከቲለስቲያል ክብር በሁሉም ነገሮች፣ እንዲሁም በክብር፣ በሀይል፣ እናም በስልጣን፣ እናም በአለቅነት የላቀውን የተረስትሪያል ክብርን እንዲህ ተመለከትን።

፺፪ እናም ከሁሉም ነገሮች በላይ የሆነውን፣ እግዚአብሔር፣ እንዲሁም አብ፣ በዙፋኑ ላይ ለዘለአለም የሚነግስበትን የሰለስቲያል ክብርን እንዲህ ተመለከትን፤

፺፫ በዙፋኑ ፊትም ሁሉም ነገሮች በትህትና [ሀ]በማወደስ ይሰግዳሉ፣ እናም ለእርሱም ለዘለአለም ክብርን ይሰጣሉ።

፺፬ በእርሱ [ሀ]ፊት የሚኖሩትም [ለ]የበኩር ቤተክርስቲያን ናቸው፤ እናም የእርሱን ሙላት እና [ሐ]ጸጋ በመቀበልም እንደሚታዩም ያያሉ፣ እናም [መ]እንደሚታወቁም ያውቃሉ፤

፺፭ እና በሀይልም፣ እና በስልጣን፣ እና በአለቅነትም [ሀ]እኩል ያደርጋቸዋል።

፺፮ እና [ሀ]የጸሀይ ክብር አንድ እንደሆነ የሰለስቲያል ክብርም አንድ ነው።

፺፯ እናም የጨረቃ ክብር አንድ እንደሆነም፣ የተረስትሪያል ክብር አንድ ነው።

፺፰ እናም የከዋክብት ክብር አንድ እንደሆን፣ እንዲሁ የቲለስቲያል ክብር አንድ ነው፤ አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ በክብር እንደሚለይም፣ በቲለስቲያል ክብር ውስጥ በክብር አንዱ ከሌላው የተለየ ነው፤

፺፱ እነዚህም [ሀ]የጳውሎስ፣ እናም የአጵሎስ፣ እናም የኬፋ ናቸው።

፻ እነዚህም የአንድ እና የሌላም—አንዳንዶች የክርስቶስ እና አንዳንዶች የዮሐንስ፣ እናም አንዳንዶቹም የሙሴ፣ እናም አንዳንድ የኤልያስ፣ እናም አንዳንዱ የኢሳይያስ፣ አንዳንዱ የኢሳይያስ፣ እናም አንዳንዱ የሔኖኮች ነን የሚሉ ናቸው፤

፻፩ ነገር ግን ወንጌሉን፣ ወይም የኢየሱስን ወይም የነቢያትን ምስክርነት፣ ወይም [ሀ]የዘለአለም ቃል ኪዳንን ያልተቀበሉ ናቸው።

፻፪ በመጨረሻም፣ እነዚህም ከቅዱሳኑ

፹፩ ሀ ቱ. እና ቃ. ፹፰፥ ፴፩።
ቅ.መ.መ. ቲለስቲያል ክብር።
፹፪ ሀ ቱ. እና ቃ. ፻፴፰፥ ፳፩።
፹፬ ሀ ፪ ኔፊ ፱፥ ፲፪፤
አልማ ፲፪፥ ፲፩።
ቅ.መ.መ. ሲዖል።
፹፭ ሀ አልማ ፲፩፥ ፵፩፤
ቱ. እና ቃ. ፵፫፥ ፲፰፤
፹፰፥ ፻–፻፩።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፹፯ ሀ ቱ. እና ቃ. ፻፴፰፥ ፴፯።
፺፫ ሀ ቅ.መ.መ. ማክበር።
፺፬ ሀ ቱ. እና ቃ. ፻፴፥ ፯።
ለ ቅ.መ.መ. በኩር።
ሐ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
መ ፩ ቆሮ. ፲፫፥ ፲፪።
፺፭ ሀ ቱ. እና ቃ. ፳፱፥ ፲፫፤
፸፰፥ ፭–፯፤ ፹፬፥ ፴፰፤
፹፰፥ ፻፯፤ ፻፴፪፥ ፳።
፺፮ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥ ፵–፵፩።
፺፱ ሀ ፩ ቆሮ. ፫፥ ፬–፯፤ ፳፪።
፻፩ ሀ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።

ጋር፣ ወደ በኩር [ሀ]ቤተክርስቲያን በደመና [ለ]እንዲነጠቁ የማይሰበሰቡት ናቸው።

፻፫ [ሀ]እነዚህም [ለ]ሀሰተኞች፣ እና አስማተኞች፣ እና ሴሰኞች፣ እና [ሐ]አመንዝሮች፣ እና ሀሰትንም የሚወዱ እና የሚያደርጉትም ናቸው።

፻፬ እነዚህ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን [ሀ]ቁጣ የሚቀበሉት ናቸው።

፻፭ እነዚህ፣ ዘለአለማዊ እሳት የቂም [ሀ]በቀልን የሚቀጡትም ናቸው።

፻፮ እነዚህ ወደ [ሀ]ሲኦል የሚጣሉት እናም፣ ክርስቶስ ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች [ለ]እስከሚያደርግበት፣ እና ስራውን [ሐ]ፍጹም እስከሚያደርግበት እስከ [መ]ዘመኑ ፍጻሜ፣ [ሠ]ሁሉን በሚገዛው እግዚአብሔር ብርቱ [ረ]ቁጣም የሚሰቃዩት ናቸው፤

፻፯ አሸንፌአለሁ እናም መጥመቂያው፣ እንዲሁም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን [ሀ]ወይን መጥመቂያን፣ ብቻዬን [ለ]ረግጫለሁ፣ በማለት መንግስትን ወደ አብ በፍጹም ንፅህና እንከሚያስረክብበት ድረስ የሚሰቃዩት እነርሱ ናቸው።

፻፰ ከዚያም እርሱም በስልጣኑ [ሀ]ዙፋኑ ለዘለአለም ይነግስ ዘንድ የክብር አክሊል ይጫንለታል።

፻፱ ነገር ግን እነሆ፣ እናም አስተዋሉ፣ የቲለስቲያል አለምን ክብር እና ነዋሪዎችን፣ በሰማይ ጠፈር እንዳሉት ከዋክብት አይነት፣ ወይም እንደ ባህር ዳር አሸዋዎች ለመቆጠር እንደማይቻሉም አየን።

፻፲ እናም የጌታ ድምፅ እንዲህ ሲል ሰማን፥ በዙፋኑ ላይ ለሚቀመጠው ከዘለአለም እስከ ዘለአለም እነዚህ ሁሉ በጉልበት ይንበረከካሉ፣ እናም እያንዳንዱ ምላስም [ሀ]ይናዘዝለታል፤

፻፲፩ እንደ ስራቸውም መጠን ይፈረድባቸዋል፣ እናም ለእያንዳንዱ ሰውም [ሀ]እንደ ስራው በተዘጋጀለት [ለ]መኖሪያ ግዛቱን ይቀበላል፤

፻፲፪ እና እነርሱም የልዑል አገልጋዮች ይሆናሉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እና ክርስቶስ [ሀ]በሚኖሩበት፣ ከዘለአለም እስከዘለአለም መምጣት አይችሉም።

፻፲፫ ይህም በመንፈስ ሳለን ያየነውና እንድንፅፈውም የታዘዝነው ራዕይ መጨረሻ ነው።

፻፲፬ ነገር ግን የጌታ ስራዎች፣ እናም በክብርና፣ በሀይል፣ እናም በአለቅነት ለማስተዋል ከሚቻለው በላይ እንደሆኑ ያሳየን የመንግስቱ [ሀ]ሚስጥራት [ለ]ታላቅና አስደናቂ ናቸው፤

፻፲፭ እነዚህንም በመንፈስ እያለንም እንዳንፅፋቸው አዝዞናል፣ እናም ሰው ይናገራቸው ዘንድ [ሀ]በህግ ያልተገቡ ናቸው።

፻፲፮ ሰው ያሳውቃቸው ዘንድ [ሀ]ችሎታ አይኖረውም፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት እና በፊቱም ራሳቸውን ለሚያጸዱት በሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ብቻ ሰው ሊያያቸው እና [ለ]ሊረዳቸው ይቻለዋልና፤

፻፲፯ ለእነዚህም ራሳቸው የሚያዩበትን እና የሚያውቁበትን ልዩ መብት ይሰጣቸዋል፤

፻፲፰ በስጋ እያሉም፣ በመንፈስ ሀይል እና

፻፪ [ሀ] ት. እና ቃ. ፸፰፥፳፩።
[ለ] ፩ ተሰ. ፬፥፲፮–፲፯፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፮–፺፰።
፻፫ [ሀ] ራዕ. ፳፩፥፰፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥፲፯–፲፰።
[ለ] ቅ.መ.መ. ሐሰት።
[ሐ] ቅ.መ.መ. ማመንዘር።
፻፬ [ሀ] ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፻፭ [ሀ] ይሁዳ ፩፥፯።
፻፮ [ሀ] ቅ.መ.መ. ሲዖል።
[ለ] ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፬–፳፰።
[ሐ] ዕብ. ፲፥፲፬።
[መ] ኤፌ. ፩፥፲።
[ሠ] ት. እና ቃ. ፹፯፥፮።
[ረ] ት. እና ቃ. ፲፱፥፫–፳።
፻፯ [ሀ] ዘፍጥ. ፵፱፥፲–፲፪፤
ኢሳ. ፳፫፥፩–፫።
[ለ] ራዕ. ፲፱፥፲፭፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፮፤
፻፴፫፥፵፮–፶፫።
፻፰ [ሀ] ት. እና ቃ. ፻፴፯፥፫።
፻፲ [ሀ] ፊልጵ. ፪፥፱–፲፩፤
ሞዛያ ፳፯፥፴፩።
፻፲፩ [ሀ] ራዕ. ፳፥፲፪–፲፫።
ቅ.መ.መ. ስራዎች።
[ለ] ዮሐ. ፲፬፥፪፤
ት. እና ቃ. ፶፱፥፪፤
፹፩፥፮።
፻፲፪ [ሀ] ት. እና ቃ. ፳፱፥፳፱፤
ራዕ. ፳፩፥፳፫–፳፯።
፻፲፬ [ሀ] ያዕቆ. ፬፥፰።
[ለ] ራዕ. ፲፭፥፫፤
ሞር. ፱፥፲፮–፲፰፤
ሙሴ ፩፥፫–፭።
፻፲፭ [ሀ] ፪ ቆሮ. ፲፪፥፬።
፻፲፮ [ሀ] ፫ ኔፊ ፲፯፥፲፭–፲፯፤
፲፱፥፴፪–፴፬።
[ለ] ፩ ቆሮ. ፪፥፲–፲፪።

በመገለጥ በኩል በክብር አለም ውስጥ የእርሱን መገኘት ያዩ ዘንድም ይሰጣቸዋል።

፻፲፱ እናም ለእግዚአብሔር እና ለበጉ ክብር እና ውዳሴ፣ እናም አለቅነትም ከዘለአለም እስከዘለአለም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፸፯

በመጋቢት ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) አካባቢ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፣ “ቅዱሳን መጻህፍትን ከመተርጎም ጋር በተገናኘ፣ ስለቅዱስ ዮሐንስ ራዕይ የሚቀጥለውን መግለጫ ተቀበልኩ”።

፩–፬፣ አራዊት መንፈስ አላቸው እናም በዘለአለማዊ ደስታ ይኖራሉ፤ ፭–፯፣ ይህች ምድር የ፯ ሺህ አመታት ጊዜያዊ ህይወት አላት፤ ፰–፲፣ የተለያዩ መላእክት ወንጌልን ደግመው መለሱ እና በምድርም አገለገሉ፤ ፲፩፣ የ፻፵፬ ሺህዎቹ መታተም ፲፪–፲፬፣ ክርስቶስ በሰባት ሺህ አመታት መጀመሪያ ውስጥ ይመጣል፤ ፲፭፣ ሁለት ነቢያት በአይሁድ ሀገሮች ይነሳሉ።

፩ ጥ. በራዕይ ምዕራፍ ፬፣ እና ቁጥር ፮ ውስጥ በዮሐንስ የተነገረው የብርጭቆ [ሀ]ባሕር ምንድን ነው?

መ. ይህም [ለ]ምድር በተቀደሰ፣ በማይጠፋ፣ እና [ሐ]ዘለአለማዊ ሁኔታዋ ነው።

፪ ጥ. በዚህ ተመሳሳይ አንቀፅ ውስጥ ስለተነገሩት አራቱ እንስሳት ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. እነዚህ ገላጩ ዮሐንስ፣ [ሀ]ሰማይን፣ የእግዚአብሔርን [ለ]ገነትን፣ የሰውን፣ እናም የእንስሣትን፣ እና በምድርም የሚንቀሳቀሱት፣ እና የሰማይ አዕዋፋት [ሐ]ደስታን፤ መንፈሳዊ ነገሩ ጊዜአዊ በሆነው ምስል መሆኑን፤ እናም ጊዜአዊ ነገሩም መንፈሳዊ በሆነው [መ]የተመሰለ መሆኑን፤ [ሠ]የእንስሳ እና እግዚአብሔር የፈጠራቸው ሌሎች ፍጡራንም ደግመው የሰው [ረ]መንፈስ በሰውየው ምስል እንደሆነ ለማሳየት የተጠቀመባቸው ምሳሌያዊ መግለጫዎች ናቸው።

፫ ጥ. አራቱ እንስሳት በልዩ እንስሣት የተወሰኑ ናቸው፣ ወይስ ክፍሎችን እና ስርዓቶችን የሚወክሉ ናቸው?

መ. ለዮሐንስ ህያዋን ፍጡራን በየክፍሎቻቸው በተወሰነ ምድባዊ ስርዓታቸው ወይም በፍጥረት [ሀ]ተፅዕኖ አካባቢያቸው ውስጥ ክብራቸውን በመወከል፣ በዘለአለማዊ [ለ]ደስታቸው ሲደሰቱ፣ የታዩት፣ በአራት ልዩ እንስሳት የተወሰኑ ናቸው።

፬ ጥ. እንስሣቱ በነበራቸው አይኖች እና ክንፎች ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. አይኖቻቸው ብርሀን እና [ሀ]እውቀትን እና በእውቀት የተሞሉ መሆናቸውን የሚወክሉ ናቸው፤ እናም ክንፎቻቸውም የመንቃነቅ፣ የመስራት፣ እናም ሌሎች [ለ]ሀይላትን የሚወክሉ ናቸው።

፭ ጥ. በዮሐንስ ስለተነገሩት ሀያ አራት [ሀ]ሽማግሌዎች ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. ዮሐንስ ያያቸው ሽማግሌዎች፣ በአገልግሎት ስራ [ለ]ታማኝ የነበሩ እና ሞተው የነበሩት ሽማግሌዎች እንደሆኑ፣ [ሐ]በሰባቱ

፸፯ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፥ ፮–፱።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥ ፲፯–፳፥ ፳፭–፳፮።
ሐ ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ፤ የሰለስቲያል ክብር።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ሰማይ።
ለ ቅ.መ.መ. ገነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ደስታ።
መ ቅ.መ.መ. ምሳሌዎች።
ሠ ሙሴ ፫፥ ፲፱።
ረ ኤተር ፫፥ ፲፭–፲፮፤ አብር. ፭፥ ፯–፰። ቅ.መ.መ. መንፈስ።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፺፫፥ ፴፤ ሙሴ ፫፥ ፱።
ለ ት. እና ቃ. ፺፫፥ ፴፫–፴፬።
፬ሀ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ለ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፭ሀ ራዕ. ፬፥ ፬፤ ፲።
ለ ራዕ. ፲፬፥ ፬–፭።
ሐ ራዕ. ፩፥ ፬።

አብያተክርስቲያናት አባል የሆኑ፣ እና በእግዚአብሔር ገነት በሰማይ እንደሚገኙ ሊገባን ያስፈልገናል።

፮ ጥ. ዮሐንስ ስላየው፣ ከጀርባው በሰባት [ሀ]ማኅተም የተዘጋ መጽሐፍ ምን እንዲገባን ያስፈልገናል?

መ. ይህም የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ [ለ]ሚስጥራት፣ እና ስራዎች፤ በሰባት ሺ አመታት ኑሮ፣ ወይም ጊዜአዊ ህይወት፣ ጊዜ የተደበቁትን የዚህን [ሐ]ምድር አስተዳደር በሚመለከት እንደያዘ ሊገባን ያስፈልጋል።

፯ ጥ. ስለታታተሙት ሰባት ማኅተሞች ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. የመጀመሪያው ማኅተም [ሀ]የመጀመሪያውን ሺህ አመታት ነገሮችን እንደያዘ፣ እናም ሁለተኛውም ደግሞ የሁለተኛውን ሺ አመታት፣ እናም እስከሰባተኛው እንዲሁ እንደሚቀጥል ሊገባን ያስፈልጋል።

፰ ጥ. በራዕይ ፯ኛ ምዕራፍ እና ፩ኛ ቁጥር ውስጥ ስለተነገሩት አራት መላዕክት ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. እነዚህ መላዕክት ከእግዚአብሔር እንደተላኩ፣ ለእነርሱም፣ ህይወትን ለማዳን እናም ለማጥፋት፣ በምድር አራት ክፍሎች ላይ ሀይል እንደተሰጣቸው፤ እነዚህም [ሀ]ዘለአለማዊውን ወንጌል ለእያንዳንዱ ሕዝብ፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ እና ወገን በአደራ የሚሰጡ መሆኑን፤ ሰማያትን ለመዝጋት፣ በህይወትም ለማተም፣ ወይም የጭለማ [ለ]አካባቢዎችንም ለመጣል ሀይል እንዳላቸው እንዲገባን ያስፈልጋል።

፱ ጥ. በራዕይ ፯ኛ ምዕራፍ እና ፪ኛ ቁጥር፣ ከምስራቅ ስለሚነሳው መልአክ ምን እንዲገባን ያስፈልገናል?

መ. ከምስራቅ የሚነሳው መልአክ [ሀ]በእስራኤል አስራ ሁለቱ ጎሳ ላይ የህያው እግዚአብሔር ማተሚያ የተሰጠው እንደሆነ እዲገባን ያስፈልጋል፤ ስለዚህ፣ ዘለአለማዊ ወንጌሉን ይዞ፣ የአምላካችንን ባሪያዎች [ለ]ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ፣ ብሎ ወደ አራቱ መላእክት ይጮሀል። እናም፣ ከተቀበላችሁትም፣ ይህም የእስራኤልን ነገዶች ለመሰብሰብ እና ሁሉንም ነገሮች [ሐ]ደግሞ ለመመለስ የሚመጣው [መ]ኤልያስ ነበር።

፲ ጥ. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች የሚከናወኑበት በምን ጊዜ ነው?

መ. የሚከናወኑት [ሀ]በስድስት ሺህ አመታት ውስጥ፣ ወይም በስድስተኛው ማኅተም በሚከፈትበት ነው።

፲፩ ጥ. ከእስራኤል ጎሳዎች ሁሉ መካከል፣ [ሀ]የአንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ መታተም—ከእያንዳንዱ ጎሳ አስራ ሁለት ሺ—ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. የታተሙት ዘለአለማዊውን ወንጌል እንዲያስተዳድሩ በእግዚአብሔር ቅዱሱ ስርዓት የተሾሙት [ለ]ሊቀ ካህናት እንደሆኑ እንዲገባን ያስፈልጋል፤ እነዚህም ወደ [ሐ]በኩር ቤተክርስቲያን የመምጣት ፈቃድ ያሏቸውን እንዲያመጡ በምድር አገሮች ላይ ሀይል በተሰጣቸው መላዕክት ከእያንዳንዱ ሕዝብ፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ እና ወገን መካከል የተሾሙት ናቸውና።

፲፪ ጥ. በራዕይ ምእራፍ ፰ ውስጥ ስለተጠቀሰው [ሀ]የመለከት መነፋት ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. እግዚአብሔር አለምን በስድስት ቀናት እንደሰራ፣ እና በሰባተኛው ቀን

፮ ሀ ራዕ. ፭፥፩።
 ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
 ሐ ቅ.መ.መ. ምድር።
፯ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፰–፻፲።
፰ ሀ ራዕ. ፲፬፥፮–፯።
 ለ ማቴ. ፰፥፲፩–፲፪፤ ፳፪፥፩–፲፬፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፸፩–፸፫።
፱ ሀ ራዕ. ፯፥፬–፰።
 ለ ሕዝ. ፱፥፬።
 ሐ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
 መ ቅ.መ.መ. ኢልያ።
፲ ሀ ራዕ. ፮፥፲፪–፲፯።
፲፩ ሀ ራዕ. ፲፬፥፫–፭።
 ለ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
 ሐ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶፩–፸። ቅ.መ.መ. በኩር።
፲፪ ሀ ራዕ. ፰፥፪።

ስራውን እንደጨረሰ፣ እናም [ለ]እንዲቀደስ እንዳደረገው፣ እናም ደግሞም በሰባተኛው ቀን ሰውን ከምድር [ሐ]አፈር እንዳበጀው፣ እንዲሁም፣ በሰባት ሺ አመታት መጀመሪያ ላይ ጌታ አምላክ ምድርን [መ]እንደሚቀድስ፣ እናም የሰውን ደህንነት እንደሚፈፅም፣ እናም ሁሉንም ነገሮች [ሠ]እንደሚፈርድ፣ እናም ሁሉንም ነገሮች፣ በሁሉም ነገሮች መጨረሻ፣ ሲያትም በሀይሉ ካልጨመራቸው በስተቀር፣ ሁሉንም ነገሮች [ረ]እንደሚያድን እንዲገባን ያስፈልጋል፤ እናም፣ በሰባተኛው ሺ አመታት መጀመሪያ፣ የሰባቱ መላዕክት መለከት ድምፅ የስራው መዘጋጃ እና መጨረሻ—ዳግሞ ከመምጣቱ በፊት መንገዱ የሚዘጋጅበት ነው።

፲፫ ጥ. በራዕይ ምዕራፍ ፱ ውስጥ የተጻፉት ነገሮች የሚከናወኑበት መቼ ነው?

መ. እነዚህ የሚከናወኑት ሰባተኛው ማኅተም ከተከፈተ፣ ከክርስቶስ መመለስ በፊት ነው።

፲፬ ጥ. በራዕይ ምዕራፍ ፲ ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ ዮሐንስ [ሀ]ስለበላት ታናሽ መጽሐፍ ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. ይህም የእስራኤልን ነገዶች [ለ]ለመሰብሰብ የተሰጠው ተልዕኮ፣ እናም ስርዓት እንደሆነ እንዲገባን ያስፈልጋል፤ እነሆ፣ እንደተጻፈው፣ ይህ መጥቶ ሁሉንም ነገሮች [ሐ]ዳግሞ መመለስ ያለበት ኤልያስ ነው።

፲፭ ጥ. በራዕይ ምዕራፍ አስራ አንድ ውስጥ ስለተጠቀሱት ሁለቱ [ሀ]ምስክሮች ምን ሊገባን ያስፈልገናል?

መ. እነዚህም [ለ]በመጨረሻው ቀናት፣ [ሐ]በዳግም መመለሱ ጊዜ፣ እና ከተሰበሰቡ እና የኢየሩሳሌም ከተማን በአባቶቻቸው [መ]ምድር ላይ ለሚሰሩ ለአይሁዶች እንዲተነቢዩ [ሠ]በአይሁድ ሀገሮች የሚነሱት ሁለት ነቢያት ናቸው።

ክፍል ፸፰

በመጋቢት ፩፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚያ ቀን ነቢዩ እና ሌሎች መሪዎች የቤተክርስቲያኗን ጉዳይ ለመወያየት ተሰብስበው ነበር። ይህም ራዕይ ነቢዩ፣ ስድኒ ሪግደን፣ እና ኒዌክ ኬ. ውትኒ ወደ ምዙሪ በመጓዝ እና ፅዮንን ለመመስረት እና ድሆችን ለመርዳት ገንዘብ የሚያስገኝ፣ የቤተክርስቲያኗን የንግድ እና የማተም ጥረቶችን የሚረዳ "ድርጅት" እንዲመሰርቱ መመሪያ የሚሰጥ ነበር። ይህም ድርጅት፣ የትብብር ድርጅት ተብሎ የሚታወቀው፣ የተመሰረተው በሚያዝያ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) እና የፈረሰው በ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) ነበር (ክፍል ፹፪ን ተመልከቱ)። ከፈረሰ በኋላ፣ በጆሴፍ ስሚዝ አመራር፣ "የድሀውን ህዝቤ የጎተራ ስራዎችን" የሚለው "የንግድ እና የማተሚያ ድርጅት" የሚለውን በራዕይ ውስጥ ቀይሯል፣ እናም "ስርዓት" የሚለው ቃል "ድርጅት" የሚለውን ቃል ተክቷል።

፲፪ ለ ዘፍጥ. ፪፥፩–፫፤
ዘፀአ. ፳፥፲፩፤ ፴፩፥፲፪–፲፯፤
ሞዛያ ፲፫፥፲፮–፲፱፤
ሙሴ ፫፥፩–፫፤
አብር. ፭፥፩–፫።
ሐ ዘፍጥ. ፪፥፯።
መ ት. እና ቃ. ፹፰፥፲፯–፳።
ሠ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
ረ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፲፬ ሀ ሕዝ. ፪፥፱–፲፤ ፫፥፩–፬፤ ራዕ. ፲፥፲።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
ሐ ማቴ. ፲፯፥፲፩።
፲፭ ሀ ራዕ. ፲፩፥፩–፲፬።
ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ሐ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
መ ዓሞ. ፱፥፲፬–፲፭።
ሠ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።

፩–፬፣ ቅዱሳን ጎተራ ማዘጋጀት እና መመስረት ይገባቸዋል፤ ፭–፲፪፣ ንብረቶቻቸውን በጥበብ መጠቀም ወደ ደህንነት ይመራል፤ ፲፫–፲፬፣ ቤተክርስቲያኗ ከምድራዊ ሀይላት ጥገኝነት ነጻ መሆን ይገባታል፤ ፲፭–፲፯፣ ሚካኤል (አዳም) በቅዱሱ (ክርስቶስ) አመራር ያገለግላል፤ ፲፯–፳፪፣ ታማኞች ብጹአን ናቸው፣ ሁሉንም ነገሮች ይወርሳሉና።

፩ ጌታ ለጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እንዲህ ሲል ተናገረው፥ ራሳችሁን የሰበሰባችሁት፣ በቤተክርስቲያኔ [ሀ]ታላቅ ክህነት የተሾማችሁት አድምጡኝ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፤

፪ እናም በፊቴ ባቀረባችሁት ነገር ደህንነት ለእናንተ ይሆንላችሁ ዘንድ፣ ከበላይ [ሀ]የሾማችሁን፣ በጆሮአችሁ የጥበብ ቃላትን የሚናገራችሁን የእርሱን [ለ]ምክር ስሙ፣ ይላል ጌታ አምላክ።

፫ በእውነትም እንዲህ እላችኋለሁ፣ ጊዜው መጥቷል፣ እና አሁንም ተቃርቧል፤ እናም እነሆ፣ እናም ተመልከቱ፣ በዚህ ስፍራ እና [ሀ]በፅዮን ምድርም፣ [ለ]የድህውን ህዝቤ [ሐ]የጎተራ ስራዎችን የሚቆጣጠር እና የሚመሰረት የህዝቤ [መ]ድርጅት መኖር አለበት—

፬ ይህም ለቤተክርስቲያኔ ቋሚ እና ዘለአለማዊ አመሰራረት እና ስርዓት፣ ራሳችሁ የተቀበላችሁትን ምክንያት ወደፊት ለመግፋት፣ ለሰው ደህንነት እና በሰማይ ላለው ለአባታችሁ ክብር፤

፭ ሰማያዊ ነገሮችን ለማግኘትም፣ እናንተም በሰማያዊ ነገሮች፣ አዎን፣ እናም በምድራዊ ነገሮችም [ሀ]በእኩል እንድትተሳሰሩ ዘንድ ነው።

፮ በምድራዊ ነገሮች እኩል ካልሆናችሁ ሰማያዊ ነገሮችን ለማግኘት እኩል አትሆኑም፤

፯ [ሀ]በሰለስቲያል አለም ውስጥ ስፍራን እንድሰጣችሁ ከፈለጋችሁ፣ ያዘዝኳችሁን እና የምጠብቅባችሁን ነገሮች [ለ]በማድረግ ራሳችሁን [ሐ]ማዘጋጀት አለባችሁና።

፰ እናም አሁን፣ ጌታ በእውነት እንዲህ ይላል፣ ሁሉም ነገሮች፣ በእናንተ በዚህ [ሀ]ስርዓት አብራችሁ በተጣመራችሁበት፣ ለእኔ [ለ]ክብር መደረጋቸው አስፈላጊ ነው፤

፱ ወይም፣ በሌላ ቃላትም፣ አገልጋዬ ኒወል ኬ ውትኒ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ እና አገልጋዬ ስድኒ ሪግደን በፅዮን ውስጥ ካሉት ቅዱሳን ጋር ይማከሩ፤

፲ አለበለዚያም፣ የተዘጋጁላቸውን ነገሮች ይሰወርባቸውም ዘንድ እና እንዳይገባቸው፣ [ሀ]ሰይጣን ልቦቻቸውን ከእውነቱ ሊያርቀው ይሻልና።

፲፩ ስለዚህ፣ በስምምነት ወይም ሊሰበር በማይችል በዘለአለማዊ [ሀ]ቃል ኪዳን ራሳችሁን እንድታዘጋጁ እና እንድታደራጁ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፲፪ እናም ይህን የሚሰብረውም ሹመቱን እና የቤተክርስቲያን ደረጃውን ያጣል፣ እና እስከቤዛ ቀንም በሰይጣን [ሀ]እንዲን ገላታ ይሰጣል።

፲፫ እነሆ፣ ይህም እናንተን የማዘጋጅበት ዝግጅት፣ እናም የተሰጣችሁን ትእዛዝ ለማከናወን ትችሉ ዘንድ የምሰጣችሁ መሰረት እና ምሳሌ ነው፤

፲፬ [ሀ]መከራም የሚመጣባችሁ ቢሆን እንኳ፣ በእኔ አሳብ ቤተክርስቲያኗ ከሰለ

፸፰ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. የመልከጼዴቅ ክህነት።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ለ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥ ፩–፪።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፴–፴፩።
ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።
ሐ ት. እና ቃ. ፸፪፥ ፱–፲፤ ፹፫፥ ፭–፯።
መ ት. እና ቃ. ፹፪፥ ፲፩–፲፪፣ ፲፭–፳፩።
፭ ሀ ት. እና ቃ. ፵፱፥ ፳።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፤ የቅድስና ህግ።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
ለ ት. እና ቃ. ፹፪፥ ፲።
ሐ ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፰፤ ፻፴፪፥ ፫።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፺፪፥ ፩።
ለ ሙሴ ፩፥ ፴፱።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
፲፪ ሀ ፩ ቆሮ. ፭፥ ፭፤ ት. እና ቃ. ፹፪፥ ፳፩፤ ፻፬፥ ፰–፲።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፪–፬።

ስቲያል አለም በታች ካሉት ሌሎች ፍጥረቶች ሁሉ በላይ ነጻ ሆና ትቆም ዘንድ፤

፲፭ ለተዘጋጀላችሁ [ሀ]አክሊል ትመጡ፣ እና በብዙ መንግስታት ላይ [ለ]ገዢዎች ትሆኑ ዘንድ የማዘጋጅበት ዝግጅት፣ የምሰጣችሁ መሰረት እና ምሳሌ ነው፣ [ሐ]አዳም-ኦንዳይ-አማንን የመሰረተው ጌታ አምላክ፣ የፅዮን ቅዱስ፤

፲፮ [ሀ]ሚካኤልን እንደ ልኡል የሾመው፣ እናም እግሮቹን ያጸና፣ እናም በከፍታም ላይ ያስቀመጠው፣ እናም የደህንነትን ቁልፎች፣ የቀናት መጀመሪያ እና የህይወት መጨረሻ በሌለው፣ በቅዱሱ ምክር እና አመራር አማካይነት የደህንነትን ቁልፎች የሰጠው ጌታ አምላክም እንዲህ ይላል።

፲፯ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እናንት ትንሽ ልጆች ናችሁ፣ እናም አብ በእጆቹ ምን አይነት ታላቅ በረከቶች እንዳለው እና ለእናንተም እንዳዘጋጀ ገና አልገባችሁም፤

፲፰ እናም ሁሉንም ነገሮች አሁን [ሀ]መሸከም አትችሉም፤ ይህም ቢሆን፣ ተደሰቱ፣ እንደሚገባችሁ [ለ]እመራችኋለሁና። መንግስት የእናንተ ናት እናም በእዚያም ያሉ በረከቶች የእናንተ ናቸው፣ እናም [ሐ]የዘለአለም ባለጠግነትም የእናንተ ናቸውና።

፲፱ እናም ሁሉንም ነገሮች [ሀ]በምስጋና የሚቀበል እርሱ የከበረ ይሆናል፤ እናም የምድር ነገሮችም፣ እንዲሁም [ለ]በመቶ እጥፍ፣ አዎን በብዙ፣ ለእርሱ ይጨመሩለታልና።

፳ ስለዚህ፣ ያዘዝኳችሁን ነገሮች እንዲሁ አድርጉ፣ ይላል ቤዛችሁ፣ እንዲሁም እናንተን [ሀ]ከመውሰዱ አስቀድሞ ሁሉንም ነገሮች የሚያዘጋጀው [ለ]የአህመን ልጅ፤

፳፩ የበኩር [ሀ]ቤተክርስቲያን ናችሁና፣ እናም በደመናው ወደላይ [ለ]ይወስዳችኋል፣ እናም ለእያንዳንዱም የድርሻውን ይሰጠዋልና።

፳፪ እናም ታማኝ እና [ሀ]ብልህ የሆነ [ለ]መጋቢው [ሐ]ሁሉንም ነገሮች ይወርሳል። አሜን።

ክፍል ፸፱

በመጋቢት ፲፪፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ።

፩–፬፣ ጄርድ ካርተር በአፅናኙ ወንጌልን እንዲሰብክ ተጠርቷል።

፩ በእውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ጄሪድ ካርተር ዳግም ወደ ምስራቅ አገሮች፣ ከስፍራ ወደ ስፍራ፣ እናም ከከተማ ወደ ከተማ፣ [ሀ]በተሾመበት ሹመት ሀይል ውስጥ ታላቅ ደስታ የምስራች፣ እንዲሁም ዘለአለማዊ ወንጌልን፣ እየሰበከ እንዲሄድ ፍቃዴ ነው።

፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አክሊል፤ ከፍተኛነት።
ለ ራዕ. ፭፥፲፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶፮–፷፤ ፻፴፪፥፲፱።
ሐ ቅ.መ.መ. አዳም-ኦንዳይ-አማን።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፩፤ ፻፯፥፶፬–፶፭። ቅ.መ.መ. አዳም።
፲፰ ሀ ዮሐ. ፲፮፥፲፪፤ ፫ ኔፊ ፲፯፥፪–፫፤ ት. እና ቃ. ፶፥፵።
ለ ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፲።
ሐ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፲፱ ሀ ሞዛያ ፪፥፳–፳፩። ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
ለ ማቴ. ፲፱፥፳፱።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፺፭፥፲፯።
ለ ፩ ተሰ. ፬፥፲፯።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶፫–፶፬።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፯–፺፰።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፸፪፥፫–፬።
ለ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፰።
፸፱ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥፴፰። ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።

፪ እናም እውነትን እና የሚሄድበትን መንገድ የሚያስተምረውን ᵘአፅናኙንም እልክለታለሁ፤

፫ እናም የታመነ ቢሆን፣ ደግሞም በነዶም አነግሰዋለሁ።

፬ ስለዚህ፣ ልብህ ይደሰት፣ አገልጋዬ ጄርድ ካርተር፣ እናም ᵘአትፍራ፣ ይላል ጌታህ፣ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ። አሜን።

ክፍል ፹

በመጋቢት ፯፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ለስቲቨን ቢዩረት የተሰጠ ራዕይ።

፩–፭፣ ስቲቨን ባርነት እና ኢድን ስሚዝ በሚመርጡበት ስፍራ እንዲሰብኩ ተጠርተዋል።

፩ በእውነት ጌታ ለአንተ አገልጋዬ ስቲቨን ባርነት እንዲህ ይላል፥ ሂድ፣ ወደ አለም ሂድ እናም በድምፅህ አካባቢ ለሚመጣው ፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ᵘስበክ።

፪ እናም የጉዞ ጓደኛ ከፈለግህ፣ አገልጋዬን ኢድን ስሚዝን እሰጥሀለሁ።

፫ ስለዚህ፣ ሂዱ እናም ወንገሌን ስበኩ፣ ወደ ሰሜን ይሁን ወደ ደቡብ፣ ወደምስራቅ ይሁን ወደምእራብ ግድ የለም፣ አትሳሳቱምና።

፬ ስለዚህ፣ የሰማችሁትን ነገሮች አውጁ፣ እናም በእውነት እመኑ፣ እናም እውነት እንደሆነ ᵘእወቁ።

፭ እነሆ፣ ይህ ᵘየጠራችሁ፣ የቤዛችሁ፣ እንዲሁም የእርሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ነው። አሜን።

ክፍል ፹፩

በመጋቢት ፲፭፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ፍሬድሪክ ጂ ዊልያምስ ሊቀ ካህን እና ለታላቅ ክህነት አመራር አማካሪ እንዲሆን ተጠርቷል። ይህ ራዕይ በመጋቢት ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ሲመጣ፣ ጄሲ ጋውዝ በአመራሩ ውስጥ ለጆሴፍ ስሚዝ አማካሪነት እንደተጠራ የታሪክ መዝገቡ ያሳይ ነበር። ነገር ግን፣ በተመደበበት በትክክል ስላልሰራ፣ ጥሪው ከዚያም ወደ ፍሬድሪክ ጂ ዊልያምስ ተለውጦ ነበር። ይህ ራዕይ [በመጋቢት ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) የተጻፈው] ቀዳሚ አመራርን በስርዓት የማደራጀት፣ በዚህም ሀላፊነት የአማካሪ ሹመቶችን የመጥራት፣ እና የሹመቱም ክብር የሚገለጥበት የመጀመሪያው እርምጃ እንደነበር ሊታሰብበት ይገባል። ወንድም ጋውዝ ለጊዜያዊነት አገለገለ ነገር ግን በታህሳስ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ከቤተክርስቲያኗ ተወገዘ። ወንድም ዊልያምስ በዚህ ሹመት በመጋቢት ፲፰፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) ተሹሞ ነበር።

፪ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፳፮።
ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፭–፮።

፹ ፩ሀ ማር. ፲፮፥፲፭።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣

በእግዚአብሔር መጠራት፣
የተጠራበት።

፩–፪፣ የመንግስት ቁልፎች በቀዳሚ አመራር ዘወትር ይያዛሉ፤ ፫–፯፣ ፍሬድሪክ ጂ ዊልያምስ በአገልግሎቱ ታማኝ ነው፣ ዘለአለማዊ ህይወትም ይኖረዋል።

፩ እውነት፣ እውነት እልሀለሁ ለአገልጋዬ ፍሬድሪክ ጂ ዊልያምስ፥ የሚናገረው ድምፅ፣ የጌታ አምላክህን ቃል ስማ፣ እናም የተጠራህበትን፣ እንዲሁም የቤተክርስቲያኔ [ሀ]ሊቀ ካህን እናም ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ አማካሪነት ጥሪን አድምጥ፤

፪ ለእርሱም፣ ዘወትር ለታላቅ ክህነት [ሀ]አመራር የሚሆነውን፣ የመንግስቱን [ለ]ቁልፎች ሰጥቻለሁ፥

፫ ስለዚህ፣ በእውነት እቀበለዋለሁ እናም እባርከዋለሁ፣ እናም በምክር፣ በሰጠሁህ ሀላፊነት፣ ሁልጊዜ ድምፅህን አውጥተህ እናም በልብህ፣ በአለም ፊት እና በስውር በመጸለይ፣ ደግሞም ወንጌልን በምድር ኗሪዎች ምድር፣ እናም በወንድሞችህ መካከል በማወጅ ለማገልገል ታማኝ እስከሆንክ ድረስ፣ አንተም ትባረካለህ።

፬ እነዚህን ነገሮች በማድረግ ከሁሉም በላይ የሆነ መልካም ነገሮችን ለሰዎች ታደርጋለህ፣ እናም ጌታህ የሆነውን የእርሱን [ሀ]ክብር ከፍ ታደርጋለህ።

፭ ስለዚህ፣ የታመንህ ሁን፤ በመደብኩህ ሀላፊነት ቁም፤ ደካማውን [ሀ]ደግፍ፣ የዛሉትን እጆች አቅና፣ እናም [ለ]የሰለሉትን ጉልበቶች [ሐ]አጠንክር።

፮ እናም እስከመጨረሻው ታማኝ ብትሆን [ሀ]የህያውነት አክሊልን፣ እና በአባቴ ዘንድ [ለ]ቤት ባዘጋጀሁት ቤት ውስጥ [ሐ]ዘለአለማዊ ህይወት ይኖርሀል።

፯ እነሆ፣ እናም እነዚህ የአልፋ እና ኦሜጋ፣ እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቃላት ናቸው። አሜን።

ክፍል ፹፪

በሚያዝያ ፳፮፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.)፣ በኢንድፐንደንስ፣ በጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ጊዜው በቤተክርስቲያኗ ሊቀ ካህናት እና ሽማግሌዎች የምክር ስብሰባ ላይ ነበር። በምክር ስብሰባው ላይ፣ ከዚህ በፊት በጥር ፳፭፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በአምኸርስት ኦሀዮ ውስጥ በሊቀ ካህናት፣ በሽማግሌዎች፣ እና በአባላት ጉባኤ ላይ ለዚህ ሀላፊነት የተሾመው ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እንደ ታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት ተደግፎ ነበር (የክፍል ፸፭ ርዕስን ተመልከቱ)። ይህ ራዕይ ከዚህ በፊት (ክፍል ፸፰) የቤተክርስቲያኗን ንግድ እና የማተም ጥረቶችን የሚቆጣጠር የትብብር ድርጅት ተብሎ ይታወቅ የነበረውን ድርጅት (በኋላም፣ በጆሴፍ ስሚዝ አመራር፣ “ስርዓት” የሚለው ቃል “ድርጅት” የሚለውን ተካ) እንዲመሰረት ተደጋጋሚ መመሪያ ሰጠ።

፩–፬፣ ብዙ ለተሰጠው፣ ከእርሱ ብዙ ይጠበቃል፤ ፭–፯፣ ጭለማ በአለም ላይ ነግሷል፤ ፰–፲፫፣ እሱ ያለውን ስናደርግ ጌታ በቃሊ ይታሰራል፤ ፲፬–፲፯፣ ፅዮን በውበት እና በቅድስና መጨመር አለባት፤ ፲፰–፳፬፣ እያንዳንዱ ሰው ለባልንጀራው መልካም ሊሻ ይገባዋል።

፹፩ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፰–፱፣ ፳፪።
ቅ.መ.መ. ቀዳሚ አመራር።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፬ሀ ሙሴ ፩፥፴፱።
፭ሀ ሞዛያ ፬፥፲፭–፲፮።
ለ ኢሳ. ፴፭፥፫።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፰፥፯።
፮ሀ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሚችነት።
ለ ዮሐ. ፲፬፥፪–፫፤ ት. እና ቃ. ፶፱፥፪፤ ፻፮፥፰።
ሐ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት፤ የዘለዓለም ህይወት።

፩ አገልጋዮቼ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እርስ በርስ መተላለፋችሁን [ሀ]ይቅር ብትባባሉ፣ እኔ ጌታ እንዲሁ ይቅር እላችኋለሁ።

፪ ይህም ቢሆን፣ በመካከላችሁ ታላቅ ኃጢአት የሰሩ አሉ፤ አዎን፣ [ሀ]ሁላችሁም ኃጢአት ሰርታችኋል፤ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተጠንቀቁ፣ እናም ከኃጢአት ተቆጠቡ፣ አለበለዚያ የበለጠ ፍርድ በራሳችሁ ላይ ይወድቅባችኋል።

፫ [ሀ]ብዙ ለተሰጠው ከእርሱ ብዙ [ለ]ይጠበቅበታልና፤ እናም በታላቅ [ሐ]ብርሀን ላይ [መ]ኃጢአት የሚሰራ የባሰውን ፍርድ ይቀበላል።

፬ [ሀ]ለራዕዮች ስሜን ትጠራላችሁ፣ እናም እኔ እሰጣችኋለሁ፤ እናም የምሰጣችሁን፣ የምለውን ባትጠብቁ፣ ህግ ተላላፊዎች ትሆናላችሁ፤ እናም [ለ]ፍትህና ፍርድ በህጌ ላይ የተመደቡ ቅጣት ናቸው።

፭ ስለዚህ፣ ለአንዱ የምናገረው ለሁሉም የተናገርሁት ነው፥ ነቅታችሁ [ሀ]ጠብቁ፣ [ለ]ጠላትም ተፅዕኖውን እያስፋፋ ነው፣ እናም [ሐ]ጭለማም ነግሷል፤

፮ እናም የእግዚአብሔር ቁጣ በምድር ኗሪዎች ላይ ተቀጣጥሏል፣ እናም ማንም መልካምን አያደርግም፣ ሁሉም መንገዳቸውን [ሀ]ስተዋል።

፯ እናም አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ ጌታ እናንተን በምንም [ሀ]ኃጢአት ሀላፊ አላደርጋችሁም፤ መንገዳችሁን ሂዱ ዳግመኛም ኃጢአትን አትስሩ፤ ነገር ግን ኃጢአት ለሚሰራው ነፍስ [ለ]የቀድሞው ኃጢአት ይመለስበታል፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፰ እና ደግሜም፣ እላችኋለሁ፣ ለእናንተ ያለኝ ፈቃዴን ትረዱ ዘንድ [ሀ]አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤

፱ ወይም፣ በሌላ አባባል፣ ለደህንነታችሁ ይሆንላችሁ ዘንድ፣ በፊቴ ምን [ሀ]ማድረግ እንዳለባችሁ መመሪያ እሰጣችኋለሁ።

፲ እኔ ጌታ የምለውን ስታደርጉ በቃሌ [ሀ]እታሰራለሁ፤ ነገር ግን የምለውን ባታደርጉ፣ የተስፋ ቃል የላችሁም።

፲፩ ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ፍርድ ወዲያውኑ ሊመጣ ካልሆነ በቀር፣ በተለያዩ ሀላፊነታችሁ አገልጋዮቼ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እና ኒወል ኬ ውትኒ፣ ኤ ስድኒ ጊልበርት እና ስድኒ ሪግደን፣ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ እና ጆን ዊትመር እና ኦሊቨር ካውድሪ፣ እና ደብሊው ደብሊው ፌልፐስ እና ማርቲን ሀሪስ በመተላለፍ ሊሰበር በማይቻል [ሀ]ስምምነት እና ቃል ኪዳን ይስማሙ—

፲፪ የድሆችን ጉዳዮች፣ በፅዮን ምድር እና በከርትላንድ ምድር ውስጥ ከኤጲስ ቆጶስ አመራር ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ለማስተዳደር በቃል ኪዳን ይስማሙ፤

፲፫ የከርትላንድን ምድር በራሴ ጊዜ ለልዑል እግዚአብሔር ቅዱሳን ጥቅም፣ እና ለፅዮን [ሀ]ካስማ፣ ቀድሼዋለሁና።

፲፬ [ሀ]ፅዮን በውበት፣ እና በቅድስና፣ ልትልቅ ይገባል፤ ድንበሮችዋም ሊሰፉ፣ ካስማዎቿም ሊጠናከሩ፣ አዎን፣ እውነት

፹፪ ፩ ሀ ማቴ. ፮፥ ፲፬–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፷፬፥ ፱–፲፩።
፪ ሀ ሮሜ ፫፥ ፳፫።
፫ ሀ ሉቃ. ፲፪፥ ፵፰፤
ያዕ. ፬፥ ፲፯።
ቅ.መ.መ. መልስ
መስጠት፣ ሂሳብ፣
ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ለ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣
መጋቢነት።
ሐ ዮሐ. ፲፭፥ ፳፪–፳፬።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
መ ቅ.መ.መ. ኃጢያት፤
ክህደት።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
ለ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
፮ ሀ ሮሜ ፫፥ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፩፥ ፲፮።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥ ፴፪–፴፫፤
፶፰፥ ፵፫።
፰ ሀ ዮሐ. ፲፫፥ ፴፬።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፫፥ ፰።
፲ ሀ ኢያ. ፳፫፥ ፲፬፤
፩ ነገሥ. ፰፥ ፳፫፤
ት. እና ቃ. ፩፥ ፴፰፤
፻፴፥ ፳–፳፩።
ቅ.መ.መ. መባረክ፣
የተባረከ፣ በረከት፤
ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣
መታዘዝ።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥ ፫–፯፣
፲፩–፲፭።
፲፫ ሀ ኢሳ. ፴፫፥ ፳፤ ፶፬፥ ፪።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።

እላችኋለሁ፣ ፅዮን ልትነሳ እና [ለ]የውበት ልብሷን ልትለብስ ይገባል።

፲፭ ስለዚህ፣ በዚህ ቃል ኪዳን ራሳችሁን እንድታስተሳስሩ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፣ እናም ይህም በጌታ ህግጋት መሰረት መደረግ አለበት።

፲፮ እነሆ፣ ይህም በእኔ ዘንድ መልካም የሚሆንላችሁ ጥበብም ነው።

፲፯ እናም እናንተም [ሀ]እኩል ትሆኑ ዘንድ ይገባል፣ ወይም በሌላ አባባል፣ የሀላፊነታችሁን ጉዳዮች የማስተዳደር ጥቅም፣ እያንዳንዱ ሰው፣ ፍላጎቱ ትክክለኛ እስከሆነ ድረስ፣ በፍላጎቱ እና በሚያስፈልገው፣ በንብረቶች ላይ እኩል መብት ይኖረዋል—

፲፰ እናም ይህ ሁሉ ለህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ጥቅም፣ እያንዳንዱ ሰው [ሀ]ችሎታውን ያሻሽል ዘንድ፣ እያንዳንዱም ሰው ሌሎች ችሎታዎችን ያገኝ ዘንድ፣ አዎን፣ ከአንድ መቶ እጥፍ፣ የቤተክርስቲያኗ ሁሉ የጋራ ንብረት እንዲሆን ወደ ጌታ [ለ]ጎተራ ያገባ ዘንድ—

፲፱ እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን ፍላጎት እንዲሻ፣ እናም ለሁሉም ነገሮች ሙሉ [ሀ]አይኑን ወደ እግዚአብሔር ክብር ያደርግ ዘንድ ነው።

፳ ይህ ስርዓት፣ ኃጢአት ካልሰራችሁ በስተቀር፣ እንደ ዘለአለም [ሀ]ስርዓት ለእናንተ፣ እና ለእናንተ ተተኪዎቻችሁ መድቤአለሁ።

፳፩ እናም በዚህ ቃል ኪዳን ላይ ኃጢአት የሚፈፅም ነፍስ፣ እና ልቡን በዚህ ላይ የሚያደነድን፣ በቤተክርስቲያኔ ህግጋት መሰረት ይደረግባቸዋል፣ እናም እስከቤዛ ቀን በሰይጣን [ሀ]እንዲጎሰሙ ይሰጣሉ።

፳፪ እና አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እና ይህ ጥበብ ነው፣ በዓመፃ ገንዘብ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ፣ እናም እነዚህም አያጠፏችሁም።

፳፫ ፍርድን ለእኔ ብቻ ተዉት፣ የእኔ ነውና እናም [ሀ]እከፍለዋለሁ። ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን፣ በረከቶቼ ከእናንተ ዘንድ ይኑሩ።

፳፬ ከፅናታችሁ ካልወደቃችሁ፣ [ሀ]መንግስትም የእናንተ ናትና፣ እናም ለዘለአለምም ትሆናለች። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፹፫

በሚያዝያ ፴፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በእንድፐንደንስ ሚዙሪ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህን ራዕይ የተቀበለው ነቢዩ ከወንድሞች ጋር ለመምከር እንደተቀመጠ ነው።

፩–፬፣ ሴቶች እና ልጆች በባሎቻቸው እና በአባቶቻቸው የመደገፍ መብት አላቸው፤ ፭–፮፣ ባልቴቶች እና የሙት ልጆች በቤተክርስቲያኗ ላይ የመደገፍ መብት አላቸው።

፩ በእውነትም፣ ስለሴቶች እና ስለልጆች፣ ባሎቻቸውን እና አባቶቻቸውን [ሀ]ስላጡት የቤተክርስቲያኗ አባላት፣ ቤተክርስቲያኗ ካላት ህግጋት በተጨማሪ ጌታ እንዲህ ይላል፥

፲፬ ለ ኢሳ. ፶፪፥፩፤
ት. እና ቃ. ፻፲፫፥፯–፰።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፶፩፥፫።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣
የቅድስና ህግ።
፲፰ ሀ ማቴ. ፳፭፥፲፬–፴፤
ት. እና ቃ. ፷፥፲፫።
ቅ.መ.መ. ስጦታ፤
የመንፈስ ስጦታዎች።
ለ ት. እና ቃ. ፵፮፥፰–፴፫፣
፶፰፤ ፻፲፱፥፩–፫።
ቅ.መ.መ. ጎተራ።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፷፯።
ቅ.መ.መ. አይን፣ አይኖች።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፬፥፰–፲።
፳፫ ሀ ሮሜ ፲፪፥፲፱፤
ሞር. ፫፥፲፭።
፳፬ ሀ ሉቃ. ፲፪፥፴፪፤
ት. እና ቃ. ፳፬፥፫–፰።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
፹፫ ፩ ሀ ያዕ. ፩፥፳፯።

፪ ሴቶች፣ ባሎቻቸው እስከሚወሰዱ ድረስ፣ በባሎቻቸው የመደገፍ [ሀ]መብት አላቸው፤ እናም የሚተላለፉ ሆነው እስካልተገኙ ድረስ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ህብረት ይኖራቸዋል።

፫ እናም ታማኝ ካልሆኑም በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ህብረት አይኖራቸውም፣ ነገር ግን በምድር ህግ መሰረት በውርሳቸው ላይ ለመቆየት ይችላሉ።

፬ ለእድሜ እስኪደርሱ ድረስ ሁሉም [ሀ]ልጆች በወላጆቻቸው ላይ የመደገፍ መብት አላቸው።

፭ እናም ከዚያም በኋላ፣ ወላጆቻቸው ለውርስ የሚሰጧቸው ከሌላቸው፣ በቤተክርስቲያኗ ላይ፣ ወይም በሌላ አባባል በጌታ [ሀ]ጎተራ ላይ መብት አላቸው።

፮ እናም ጎተራውም በቤተክርስቲያኗ ቅድስና ይጠበቃል፤ እናም [ሀ]ባልቴቶች እና የሙት ልጆችም፣ እናም [ለ]ድሆች፣ ይረዳሉ። አሜን።

ክፍል ፹፬

በመስከረም ፳፪ እና ፳፫፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በመስከረም ወር ውስጥ፣ ሽማግሌዎች ከምስራቅ ስቴቶች ተልዕኮአቸው መመለስ እናም የአገልግሎታቸውን ሀተታ ማቅረብ ጀምረው ነበር። በዚህ የደስታ ዘመን ውስጥ አብረው እያሉ ነው ይህ መልእክት የመጣው። ነቢዩ ይህንንም የክህነት ራዕይ በማለት ሰይሞታል።

፩–፭፣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም እና ቤተመቅደሱ በሚዙሪ ውስጥ ይገነባሉ፤ ፮–፲፯፣ የክህነት ዘር ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ተሰጥቷል፤ ፲፰–፳፭፣ ታላቁ ክህነት የእግዚአብሔርን እውቀት ቁልፍ ይዟል፤ ፳፮–፴፪፣ አነስተኛው ክህነት የመላእክትን አገልግሎት እና የማዘጋጀውን ወንጌል ቁልፍ ይዟል፤ ፴፫–፵፬፣ ሰዎች ዘለአለማዊ ህይወትን የሚያገኙት በክህነት ስልጣን መሀላ እና ቃል ኪዳን በኩል ነው፤ ፵፭–፶፫፣ የክርስቶስ መንፈስ ለሰዎች ያበራላቸዋል፣ እናም አለም በኃጢአት ተይዟል፤ ፶፬–፷፩፣ ቅዱሳን ስለተቀበሉት ነገሮች መመስከር አለባቸው፤ ፷፪–፸፮፣ እነርሱም ወንጌሉን ይስበኩ፣ ምልክቶችም ይከተላሉ፤ ፸፯–፺፩፣ ሽማግሌዎች ካለ ኮረጆም ወይም ከረጢት ይሂዱ፣ እናም ጌታ ለፍላጎታቸው ይንከባከባቸዋል፤ ፺፪–፺፯፣ ወንጌልን የሚቃወሙ ወረርሽኝ እና እርግማን ይጠብቃቸዋል፤ ፺፰–፻፪፣ ስለ ፅዮን መዳን የሚዘመረው አዲስ መዝሙር ተሰጥቷል፤ ፻፫–፻፲፣ እያንዳንዱም ሰው በሀላፊነቱ ይቁም እናም በጥሪውም ያገልግል፤ ፻፲፩–፻፳፣ የጌታ አገልጋዮች የመጨረሻ ቀናት የጥፋት ርኩሰትን ያውጁ።

፩ ለአገልጋዩ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ እና ለስድስት ሽማግሌዎች፣ በልባቸው አንድ ሲሆኑ እና ድምጻቸውን ወደላይ [ሀ]ከፍ ሲያደርጉ የተሰጠ የኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ።

፪ አዎን፣ [ሀ]በነብያቱ አንደበት እንደተናገረው፣ ለህዝቦቹ [ለ]ዳግም መመለስ፣ እናም

፪ ሀ ፩ ጢሞ. ፭፥፰።
፬ ሀ ሞዛያ ፬፥፲፬።
፭ ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፫።
ቅ.መ.መ. ጎተራ።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ባል የሞተባት።
ለ ሞዛያ ፬፥፲፮–፳፮፤
ሔለ. ፬፥፲፩–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፴–፴፱።
ቅ.መ.መ. ደሀ።
፹፬ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፪ ሀ የሐዋ. ፫፥፲፱–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።

[ሐ]አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ በምትሆነው፣ [መ]በፅዮን ተራራ በመቆም [ሠ]ለቅዱሳኑ መሰብሰቢያ እንድትሆን በመጨረሻዎቹ ቀናት የተመሰረተችውን ቤተክርስቲያን በተመለከተ ጌታ የተናገረው ቃል።

፫ ያም ከተማ፣ በጌታ ጣት በሚዞሪ ስቴት ምዕራፍ ድንበር ውስጥ በተመደበው፣ እና በጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ጌታ በተደሰተባቸው እጅ በተመረቀው፣ [ሀ]በቤተመቅደስ ቅንጣት ምድር ተጀምሮ ይገነባል።

፬ እውነት ይህ የጌታ ቃል ነው፣ [ሀ]የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ከተማ በሚሰበሰቡት ቅዱሳን፣ በዚህ ስፍራ፣ እንዲሁም [ለ]በቤተመቅደስ ስፍራ ተጀምራ ትገነባለች፣ ይህም ቤተመቅደስ በዚህ ትውልድ ይሰራል።

፭ በእውነትም ለጌታ ቤት እስከሚገነባ ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍምና፣ እናም ደመናም ያርፍበታል፣ ደመናውም ቤቱን የሚሞላው የጌታ [ሀ]ክብር ይሆናል።

፮ እናም የሙሴ ልጆች፣ በአማቱ [ሀ]በዮቶር [ለ]እጆች በኩል በተቀበለው ቅዱስ ክህነት፤

፯ እናም ዮቶር በካሌብ እጅ ይህን ተቀበለ፤

፰ እና ካሌብም ይህን ከኢሊዮ እጅ ተቀበለ፤

፱ ኢሊዮ ይህን ከጆርሚ እጅ ተቀበለ፤

፲ እናም ጆርሚም ይህን ከጋድ እጅ ተቀበለ፤

፲፩ እና ጋድም ከኢሳይያስ እጅ፤

፲፪ እናም ኢሳይያስም ይህን ከእግዚአብሔር እጅ ተቀበለ።

፲፫ ኢሳይያስም በአብርሐም ቀናት ኖረ፣ እናም በእርሱም ተባርኮ ነበር—

፲፬ ይህም [ሀ]አብርሐም ክህነትን፣ እስከ [ለ]ኖሀ ድረስ ከነበሩት ከአባቶቹ ዘሮች በተቀበለው [ሐ]ከመልከ ጼዴቅ ተቀበለ፤

፲፭ እናም ከኖህ እስከ [ሀ]ሄኖክ፣ በአባቶቻቸው ዘር በኩል ተቀበሉ፤

፲፮ እናም ከሄኖክም በወንድሙ [ሀ]ሸመቃ ምክንያት ወደተገደለው፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛት ምክንያት የመጀመሪያው ሰው በነበረው በአባቱ [ለ]አዳም እጅ ክህነትን [ሐ]ወደ ተቀበለው [መ]አቤል—

፲፯ ይህም [ሀ]ክህነት በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን በሁሉም ትውልዶች የሚቀጥል፣ እና ለቀናቱ መጀመሪያ ወይም ለአመታቱ መጨረሻ አመታት የሌለው ነው።

፲፰ እናም ጌታ [ሀ]ክህነትን [ለ]በአሮን እና በዘሮቹ ላይ፣ በሁሉም ትውልዶች ውስጥ፣ አረጋገጠ፣ ይህም ክህነት ደግሞም ይቀጥላል እናም በቅዱሱ የእግዚአብሔር ስርዓት በኩል የሆነው ክህነት ለዘለአለምም [ሐ]ይቀጥላል።

፲፱ እናም ይህም ታላቅ ክህነት ወንጌሉን ያስተዳድራል እናም የመንግስቱን [ሀ]ሚስጥር ቁልፎች፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን [ለ]እውቀት ቁልፎችን፣ ይዟል።

፳ ስለዚህ፣ በዚህም [ሀ]ስርዓት ውስጥ፣ የአምላክ አይነት ሀይል ይታያል።

፪ሐ ኤተር ፲፫፥፪–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፰–፱፤
፵፭፥፷፮–፷፯፤
እ.አ. ፩፥፲።
ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
መ ኢሳ. ፪፥፪–፭፤
ዕብ. ፲፪፥፳፪፤
ራዕ. ፲፬፥፩፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፷፮፤
፹፬፥፴፪፤ ፻፴፫፥፲፰፣ ፶፮።
ሠ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፫።
፬ሀ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
ለ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፯፤
፷፬፥፵፩–፵፫፤
፺፯፥፲፭–፳፤ ፻፱፥፲፪፣ ፴፯።
፮ሀ ቅ.መ.መ. ዮቶር።
ለ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
፲፬ሀ ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ለ ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ።
ሐ ቅ.መ.መ. መልከ ጼዴቅ።
፲፭ሀ ቅ.መ.መ. ሔኖክ።
፲፮ሀ ሙሴ ፭፥፳፱–፴፪።
ለ ቅ.መ.መ. አዳም።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፯፥፵–፶፯።
መ ቅ.መ.መ. አቤል።
፲፯ሀ አልማ ፲፫፥፩–፲፱፤
አብር. ፪፥፱፣ ፲፩።
ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፲፰ሀ ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. አሮን፣ የሙሴ ወንድም።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፫።
፲፱ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳፫፤
፻፯፥፲፰–፲፱።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ለ አብር. ፩፥፪።
፳ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።

፳፩ ካለዚህም ስርዓት፣ እናም ካለክህነት [ሀ]ስልጣን፣ የአምላክነት ሀይል ለሰዎች በስጋ አይታይም።

፳፪ ካለዚህ ማንም [ሀ]ሰው የእግዚአብሔርን ፊት፣ እንዲሁም አብን፣ ለመመልከት እና ለመኖር አይችልም።

፳፫ አሁን [ሀ]ሙሴ በምድረበዳ ይህን ለእስራኤል ልጆች በግልፅ አስተማረ፣ እናም የእግዚአብሔርን ፊት [ለ]ይመለከቱ ዘንድ እንዲችሉም ህዝቦቹን [ሐ]ለመቀደስ በትህትና ፈለገ፤

፳፬ ነገር ግን፣ ልቦቻቸውን [ሀ]አደነደኑ እናም በእርሱም ፊት ለመፅናት አልቻሉም፤ ስለዚህ፣ ጌታ [ለ]በቁጣው፣ ንዴቱ በእነርሱ ላይ ስለተቀጣጠለ፣ በምድረበዳ ሳሉ ሁሉ ክብሩ ወደሆነው እረፍቱ [ሐ]አይገቡም ብሎ መሀላ ገባ።

፳፭ ስለዚህ፣ [ሀ]ሙሴን፣ እናም ደግሞም ቅዱስ [ለ]ክህነትን ከመካከላቸው ወሰደ፤

፳፮ እናም የመላእክትን [ሀ]አገልግሎት [ለ]ቁልፍን እና የመዘጋጃ ወንጌሉን የያዘው፣ አነስተኛው [ሐ]ክህነትም ቀጠለ።

፳፯ ይህም ወንጌል፣ ጌታ በቁጣው በአሮን ቤት በእስራኤል ልጆች መካከል ከእናቱ ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ [ሀ]እስከተሞላው፣ እግዚአብሔር እስካነሳው [ለ]ዮሐንስ ድረስ እንዲቀጥል ያደረገው [ሐ]የንስሀ እና [መ]የጥምቀት፣ እና [ሠ]የኃጢአት ስርየት፣ እና [ረ]የስጋዊ ትእዛዛት [ሰ]ህግ ወንጌል ነው።

፳፰ በልጅነቱም ሳለ ነበር የተጠመቀው፣ እናም በስምንት ቀን እድሜውም፣ የአይሁድን መንግስት ለመጣል፣ እና በእጆቹ [ሀ]ሁሉም ሀይል ለተሰጠው ጌታ መምጫ ያዘጋጀው እና በህዝቦቹም ፊት የጌታን መንገድ [ለ]ያቀና ዘንድ ወደዚህ ሀይል በእግዚአብሔር መልአክ ተሹሞ ነበር።

፳፱ እና ደግሞም፣ የሽማግሌ እና የኤጲስ ቆጶስ ሀላፊነትም ከታላቁ ክህነት ጋር አስፈላጊ ሆኖ [ሀ]የተያያዘ ነው።

፴ እና ደግሞም፣ የመምህር እና የዲያቆን ሀላፊነትም፣ በአሮን እና በልጆቹ ላይ ከተረጋገጠው፣ ከአነስተኛው ክህነት ጋር አስፈላጊ ሆነው የተያያዙ ናቸው።

፴፩ ስለዚህ፣ የሙሴን ልጆች በተመለከተ እንዳልኩትም—የሙሴ ልጆች እና ደግሞም የአሮን ልጆች ተቀባይ የሆነውን የሚቃጠል [ሀ]መሥዋዕትንና ሌላ መሥዋዕትን በጌታ ቤት ውስጥ፣ በዚህ ትውልድ ለጌታ በተቀደሰው [ለ]ስፍራ እንደመደብኩት በሚገነባው ቤት፣ ያቀርባሉ—

፴፪ እናም የሙሴ እና የአሮን ወንድ ልጆችም፣ እነርሱም እናንተ ናችሁ፣ [ሀ]በፅዮን ተራራ ላይ በጌታ ቤት ውስጥ በጌታ [ለ]ክብር ይሞላሉ፤ እና ደግሞም የጠራኋቸውና [ሐ]ቤተክርስቲያኔን እንዲገነቡ የላኳቸውም የእነርሱ ልጆች ናቸው።

፴፫ እነዚህን የተናገርኩባቸውን ሁለት [ሀ]ክህነቶች በማግኘት እና ጥሪያቸውን ለማ

፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ስልጣን፤
ክህነት።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፩።
፳፫ ሀ ዘፀአ. ፲፱፥፫–፲፩፤ ፴፫፥፲፩።
ለ ዘፀአ. ፳፬፥፱–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፩።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፳፬ ሀ ዘፀአ. ፳፥፲፰–፳፩፤ ፴፪፥፰፤
ዘዳግ. ፱፥፳፫፤
፩ ኔፊ ፲፯፥፴–፴፩፤ ፵፪።
ለ መዝ. ፺፭፥፰፤
ዕብ. ፫፥፰–፲፩፤
ያዕቆ. ፩፥፯–፰፤
አልማ ፲፪፥፴፮።
ሐ ጆ.ስ.ት. ዘፀአ. ፴፬፥፩–፪
(ተጨማሪ)፤
ዘኁል. ፲፬፥፳፫፤
ዕብ. ፬፥፩–፲፩።
፳፭ ሀ ዘዳግ. ፴፬፥፩–፭።
ለ ቅ.መ.መ. የመልከ
ጼዴቅ ክህነት።
፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፳።
ለ ት. እና ቃ. ፲፫።
ሐ ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
፳፯ ሀ ሉቃ. ፩፥፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. መጥምቁ ዮሐንስ።
ሐ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ሠ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ረ ዕብ. ፯፥፲፩–፲፮።
ሰ ቅ.መ.መ. የሙሴ ህግ።
፳፰ ሀ ማቴ. ፳፰፥፲፰፤
ዮሐ. ፲፯፥፪፤
፩ ጴጥ. ፫፥፳፪፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፲፮–፲፯።
ለ ኢሳ. ፵፥፫፤
ማቴ. ፫፥፩–፫፤
ዮሐ. ፩፥፳፫።
፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፭።
፴፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፳፬።
ለ ት. እና ቃ. ፶፯፥፫።
፴፪ ሀ ዕብ. ፲፪፥፳፪፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፷፮፤
፹፬፥፪፤ ፻፴፫፥፶፮።
ለ ቅ.መ.መ. ክብር።
ሐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ክህነት።

ጉላት [ለ]ታማኝ የሆኑት፣ ሰውነታቸውን በማደስ በመንፈስ [ሐ]ይቀደሳሉና።

፴፬ እነርሱም የሙሴ እና የአሮን ወንድ ልጆች፣ እናም [ሀ]የአብርሐም [ለ]ዘር፣ እና ቤተክርስቲያንና መንግስት፣ እናም በእግዚአብሔር [ሐ]የተመረጡ ይሆናሉ።

፴፭ እና ደግሞም ይህን ክህነት የሚቀበሉትም ሁሉ እኔን ይቀበሉኛል፣ ይላል ጌታ፤

፴፮ አገልጋዮቼን የሚቀበል እኔን [ሀ]ይቀበለኛልና፤

፴፯ እናም እኔን የሚቀበለኝም አባቴን [ሀ]ይቀበላል፤

፴፰ እናም አባቴን የሚቀበልም የአባቴን መንግስት ይቀበላል፤ ስለዚህ አባቴ ያለው [ሀ]ሁሉ ለእርሱም ይሰጠዋል።

፴፱ እናም ይህም በክህነት ባለ [ሀ]መሀላ እና ቃል ኪዳን መሰረት ነው።

፵ ስለዚህ፣ ይህን ክህነት የሚቀበሉም፣ ሊሰበር የማይችለውን፣ ወይም ሊጠፋ የማይቻለውን፣ ይህን መሀላ እና ቃል ኪዳን ከአባቴ ዘንድ ይቀበላሉ።

፵፩ ነገር ግን ከተቀበለው በኋላ ይህን ቃል ኪዳን [ሀ]የሚሰብረው፣ እና ከዚህም ሁሉ የሚዞርም፣ በዚህ አለምም ሆነ በሚመጣው አለም ለኃጢአቱ ምህረት [ለ]አያገኝም።

፵፪ እናም እናንተ ወደተቀበላችሁት፣ በዚህ ቀን ለምትገኙትም ከሰማያት በራሴ ድምፅ ወዳረጋገጥሁላችሁ ክህነት ለማይመጡም ወዮላቸው፤ እናም የሰማይ ሰራዊትን እና [ሀ]መላእክቴን እናንተን በሚመለከት ሀላፊነት ሰጥቻቸዋለሁ።

፵፫ እና አሁንም ራሳችሁን በተመለከተ እንድትጠነቀቁም፣ ለዘለአለም ህይወት ቃላትም በትጋት [ሀ]ታደምጡ ዘንድ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፵፬ ከእግዚአብሔር አንደበት ከሚመጣው እያንዳንዱ ቃልም [ሀ]ትኖራላችሁና።

፵፭ የጌታ [ሀ]ቃል እውነት ነውና፣ እናም [ለ]እውነት የሆነውም ብርሀን ነው፣ እናም ብርሀን የሆነውም መንፈስ፣ እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ነው።

፵፮ እናም መንፈስም ወደአለም ለሚመጣው [ሀ]ለእያንዳንዱ ሰው [ለ]ብርሀን ይሰጣል፤ እናም መንፈስም በአለም ውስጥ ያለውን የመንፈስን ድምፅ ለሚያደምጥ ሰው ሁሉ ያበራለታል።

፵፯ እናም የመንፈስን ድምፅ የሚያደምጠው እያንዳንዱም ሰው ወደ እግዚአብሔር፣ እንዲሁም ወደአብ፣ ይመጣል።

፵፰ እናም አብም ያደሰውን እና በእናንተ ያረጋገጠውን [ሀ]ቃል ኪዳን [ለ]ያስተምረዋል፣ ይህንንም ያረጋገጠው ለእናንተ ጥቅም ነው፣ እናም ለእናንተ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለአለም ሁሉ ጥቅም ነው።

፵፱ እና [ሀ]አለምም ሁሉ በኃጢአት ተይዟል፣ እናም [ለ]በጭለማ እና በኃጢአት ባርነት ስር ያቃስታል።

፶ እናም በዚህም [ሀ]በኃጢአት [ለ]ባርነት

፴፫ ለ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፴፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥ ፴–፴፪።
ቅ.መ.መ. የአብርሐም
ቃል ኪዳን።
ለ ገላ. ፫፥ ፳፱፤
አብር. ፪፥ ፱–፲፩።
ቅ.መ.መ. አብርሐም—
የአብርሐም ዘር።
ሐ ቅ.መ.መ. ምርጦች።
፴፮ ሀ ማቴ. ፲፥ ፵–፵፪፤
ሉቃ. ፲፥ ፲፮፤
ት. እና ቃ. ፻፲፪፥ ፳።
፴፯ ሀ ዮሐ. ፲፫፥ ፳።
፴፰ ሀ ሉቃ. ፲፪፥ ፵፫–፵፬፤
ሮሜ ፰፥ ፴፪፤
ራዕ. ፳፩፥ ፯፤
፫ ኔፊ ፳፰፥ ፲፤
ት. እና ቃ. ፻፴፪፥ ፲፰–፳።
ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት መሀላ
እና ቃል ኪዳን።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. ክህደት።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፴፩–
፴፰፤ ፻፴፪፥ ፳፯።
፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፹፰።
፵፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፭፥ ፳፫–፳፭፤
ት. እና ቃ. ፩፥ ፲፬።
፵፬ ሀ ዘዳግ. ፰፥ ፫፤
ማቴ. ፬፥ ፬፤
ት. እና ቃ. ፺፰፥ ፲፩።
፵፭ ሀ መዝ. ፴፫፥ ፬።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ቃል።
ለ ቅ.መ.መ. እውነት።
፵፮ ሀ ዮሐ. ፩፥ ፱፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥ ፪።
ለ ቅ.መ.መ. ህሊና፤
ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፵፰ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን፤
አዲስ እና የዘለአለም
ቃል ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣
መነሳሳት።
፵፱ ሀ ፩ ዮሐ. ፭፥ ፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
፶ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
ለ ገላ. ፬፥ ፱።

ስር እንደሆኑም ታውቃላችሁ፣ ምክንያቱም ወደእኔ አይመጡምና።

፶፩ ወደእኔ የማይመጣው በኃጢአት ባርነት ስር ነውና።

፶፪ እናም ድምጼን የማይቀበልም [ሀ]ከድምጼ ጋር የተዋወቀ አይደለም፣ እናም ከእኔ አይደለም።

፶፫ እናም በዚህም ጻድቃንን ከኃጥአን ትለያላችሁ፣ እናም አሁንም [ሀ]አለም ሁሉ [ለ]በኃጢአት እና ጭለማ ስር [ሐ]እንደሚያቃስቱ ታውቃላችሁ።

፶፬ እናም ባለፉት ጊዜያት አዕምሮአችሁ [ሀ]ባለማመን ምክንያት ጨልሞባችሁ ነበር፣ እናም የተቀበላችሁትን እንደተራ ተቀበላችሁታልና—

፶፭ [ሀ]ከንቱነት እና ያለማመን መላዋን ቤተክርስቲያን በፍርድ ላይ አድርገዋል።

፶፮ እናም ይህም ፍርድ በፅዮን ልጆች፣ እንዲሁም በሁሉም ላይ ያርፋል።

፶፯ እና እነርሱም ንስሀ እስኪገቡ እና አዲሱን [ሀ]ቃል ኪዳን፣ እንዲሁም [ለ]መፅሐፈ ሞርሞንን እና የሰጠኋቸውን [ሐ]የወደፊት ትእዛዛትን፣ በመናገር ብቻ ሳይሆን በጻፍኳቸው መሰረት [መ]በማድረግ እስከሚያስታውሱ ድረስ ከዚህ ፍርድ በታች ይቆያሉ—

፶፰ ይህንንም የሚያስታውሱት ለአባታቸው መንግስትም የሚገባ ፍሬ ያመጡ ዘንድ ነው፤ አለበለዚያም መቅሰፍት እና ፍርድ በፅዮን ልጆች ላይ ይወርድባቸዋል።

፶፱ የመንግስት ልጆች ቅዱስ ምድሬን ይበክላሉን? በእውነት፣ እላችኋለሁ፣ አይበክሉም።

፷ በእውነትም፣ ድምጼ የሆናችሁ እናንተ፣ [ሀ]ቃላቴን አሁን ለምትሰሙ ይህን እላችኋለሁ፣ እነዚህን ነገሮች እስከተቀበላችሁ ድረስ የተባረካችሁ ናችሁ፤

፷፩ በአእምሮአችሁ [ሀ]በእርጋታ እና በጸሎት መንፈስ፣ በመሆን የሰማችሁትንም እነዚያን ነገሮች ለአለም ትመሰክሩ ዘንድ—በዚህ ትእዛዝ ኃጢአታችሁን [ለ]ይቅር እላለሁና።

፷፪ ስለዚህ፣ ወደ አለም ሁሉ [ሀ]ሂዱ፤ እናም ልትሄዱ በማትችሉበትም ቦታ፣ ከእናንተ ምስክራችሁ ወደ አለም ሁሉ ወደ እያንዳንዱ ፍጥረት እንዲሄድ፣ ላኩ።

፷፫ እናም [ሀ]ለሐዋሪያቴ እንዳልኳቸውም፣ ለእናንተም እላለሁ፣ ለእናንተም ይህን ሐዋሪያቴ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ሊቀ ካህናት ናችሁ፤ እናንተም አባቴ [ለ]የሰጠኝ ናችሁ፤ [ሐ]ጓደኛዎቼም ናችሁ፤

፷፬ ስለዚህ፣ ለሐዋሪያቴም እንዳልኳቸው ለእናንተም ደግሜ እላለሁ፣ በቃላቶቻችሁ [ሀ]የሚያምኑት እናም ኃጢአታቸው [ለ]ይሰረይ ዘንድ በውሀ የሚጠመቁ እያንዳንዱ [ሐ]ነፍሳትም [መ]መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ።

፷፭ እናም ያመኑትንም እነዚህ [ሀ]ምልክቶች ይከተሉአቸዋል—

፷፮ በስሜም ብዙ ድንቅ [ሀ]ስራዎች ይሰራሉ፤

፷፯ [ሀ]በስሜም አጋንንትን ያወጣሉ፤

፷፰ በስሜም የታመሙትን [ሀ]ይፈውሳሉ፤

፷፱ በስሜም የእውሩን አይኖች ያበራሉ፣ እናም የደንቆሮዎችን ጆሮዎች ይከፍታሉ፤

፸ እናም የዲዳውም ምላስ ይናገራል፤

፶፪ ሀ ዮሐ. ፲፥ ፳፯።
፶፫ ሀ ቅ.መ.መ. አለም።
ለ ቅ.መ.መ. አለማዊነት።
ሐ ሮሜ ፰፥ ፳፪፤ ሙሴ ፯፥ ፵፰።
፶፬ ሀ ቅ.መ.መ. አለማመን።
፶፭ ሀ ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።
፶፯ ሀ ኤር. ፴፩፥ ፴፩–፴፬።
ለ ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፫፥ ፵–፵፩።
መ ያዕ. ፩፥ ፳፪–፳፭፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፲፫–፲፭።
፷ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥ ፴፬–፴፮።
፷፩ ሀ ት. እና ቃ. ፵፫፥ ፴፬፤
፹፰፥ ፻፳፩፤ ፻፥ ፯።
ለ ዳን. ፱፥ ፱።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፷፪ ሀ ማር. ፲፮፥ ፲፭፤
ት. እና ቃ. ፩፥ ፪–፭።
ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፷፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
ለ ፫ ኔፊ ፲፭፥ ፳፬፤
ት. እና ቃ. ፶፥ ፵፩–፵፪።
ሐ ዮሐ. ፲፭፥ ፲፫–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥ ፵፭።
፷፬ ሀ ማር. ፲፮፥ ፲፭–፲፮።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ሐ ቅ.መ.መ. ነፍስ።
መ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
፷፭ ሀ ማር. ፲፮፥ ፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. ምልክት።
፷፮ ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
፷፯ ሀ ማቴ. ፲፯፥ ፲፬–፳፩።
፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. መፈወስ፣ ፈውሶች።

፸፩ እናም ማንም ሰው [ሀ]መርዝ ቢሰጣቸውም አይጎዳቸውም፤

፸፪ እናም የእባብ መርዝም ሊጎዳቸው በእነርሱ ላይ ሀይል አይኖረውም።

፸፫ ነገር ግን፣ በእነዚህ በሚሆኑነገሮች በራሳቸው [ሀ]እንዳይታበዩ፣ ወይም በአለም ፊትም እንዳይናገሩ ትእዛዝ እሰጣቸዋለሁ፣ እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ጥቅም እና ደህንነት ተሰጥተዋልና።

፸፬ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በቃላቶቻችሁ የማያምኑት፣ እናም መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ በስሜ በውሀ ውስጥ ለኃጢአታቸው ስርየት [ሀ]ያልተጠመቁት፣ [ለ]ይፈረድባቸዋል፣ እናም እኔ እና አባቴ ወዳለንበት ወደአባቴ መንግስትም አይመጡም።

፸፭ እናም ለእናንተ የተሰጠው ይህ ራዕይ እና ትእዛዝ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ በአለም ሁሉ ላይ የሚሰራ ነው፣ እናም ወንጌሉም ላልተቀበሉት ሁሉም ነው።

፸፮ ነገር ግን፣ መንግስት ለተሰጣቸው ሁሉ በእውነት እላለሁ—ለቀደመው ክፉ ስራቸው ንስሀ ይገቡ ዘንድ፣ ለክፉና ለማያምን ልቦቻቸውም፣ እናም በላኳችሁ ጊዜ ያመጹት በፅዮን ያሉት ወንድሞቻችሁም ይነቀፋ ዘንድ ይህም ከእናንተ ለእነርሱ መሰበክ ይገባል።

፸፯ እና ባልንጀሮቼ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ባልንጀሮቼ ብዬ እጠራችኋለሁና፣ ደግሜም እላችኋለሁ፣ ከእነርሱ ጋር በነበርኩበት ጊዜ ወንጌልን ለመስበክ በሀይሌ በሚጓዙበት ቀናት እንደነበሩት ባልንጀሮቼ ትሆኑ ዘንድ ይህን ትእዛዝ ለእናንተ መስጠቴ አስፈላጊ ነው፤

፸፰ ሁለት እጀ ጠባብም ይሁን [ሀ]ኮረጆም ወይም ከረጢት እንዲኖራቸው አልፈቀድኩላቸውምና።

፸፱ እነሆ፣ አለምን ትፈትኑ ዘንድ ልኬአችኋለሁ፣ እና ለሠራተኛም [ሀ]ደመወዙ ይገባዋል።

፹ እናም ማንም የሚሄድና ይህን የመንግስትን [ሀ]ወንጌል [ለ]የሚሰብክ፣ እናም በሁሉም ነገሮች በእምነቱ ጸንቶ የቆመ ሰው፣ በአዕምሮ ወይም በሰውነት፣ በእግርና እጆቹ፣ ወይም መገጣጠሚያዎቹ አይደክሙም ወይም አይዝሉም፤ እናም የራሱም [ሐ]ጠጉር ሳይታወቅ ምድር ላይ አይወድቅም። እናም አይራቡም ወይም አይጠሙም።

፹፩ ስለዚህ፣ ለነገ ምን እንደምትበሉ፣ ምን እንደምትጠጡ፣ ወይም ምን እንደምትለብሱ [ሀ]አትጨነቁ።

፹፪ የሜዳ አበቦች እንዴት እንደሚያድጉ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም፣ አይፈትሉም፤ እናም የዓለም መንግሥታት እንኳ በክብራቸው ሁሉ ከእነዚህ እንደ አንዱ አልለበሱም።

፹፫ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ [ሀ]አባታችሁ [ለ]ያውቃልና።

፹፬ ስለዚህ፣ ነገ ለራሱ [ሀ]ይጨነቅ።

፹፭ እንዴት ወይስ [ሀ]ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ ነገር ግን ዘወትር የህይወትን ቃል በአዕምሮዎቻችሁ ውስጥ [ለ]አከማቹ፣ እና ይህም በዚያች ሰዓት ለእያንዳንዱ ሰው ተመዝኖ የሚሰጠው [ሐ]ይሰጣችኋል።

፹፮ ስለዚህ፣ ይህ ትእዛዝ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ለአገልግሎት በእግዚአብሔር ለተጠሩት [ሀ]ታማኝ ለሆኑት ሁሉ ስለ

፸፩ ሀ ማር. ፲፮፥፲፰፤
የሐዋ. ፳፰፥፫–፱፤
ት. እና ቃ. ፳፬፥፲፫፤
፻፳፬፥፺፰–፻።
፸፫ ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፳፬።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
፸፬ ሀ ፪ ኔፊ ፱፥፳፫፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፶–፶፪።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ—አስፈላጊ።
ለ ዮሐ. ፫፥፲፰።
፸፰ ሀ ማቴ. ፲፥፱–፲፤
ት. እና ቃ. ፳፬፥፲፰።
፸፱ ሀ ት. እና ቃ. ፴፩፥፭።
፹ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
ሐ ሉቃ. ፳፩፥፲፰።
፹፩ ሀ ማቴ. ፮፥፳፭–፳፰።
፹፪ ሀ ቅ.መ.መ. የሰማይ አባት።
ለ ማቴ. ፮፥፰።
፹፬ ሀ ማቴ. ፮፥፴፬።
፹፭ ሀ ማቴ. ፲፥፲፱–፳፤
ሉቃ. ፲፪፥፲፩–፲፪፤
ት. እና ቃ. ፻፥፮።
ለ ፪ ኔፊ ፴፪፥፫፤
አልማ ፲፯፥፪–፫፤
ት. እና ቃ. ፮፥፳፤
፲፩፥፳፩–፳፮።
ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
ሐ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ—በመንፈስ
ማስተማር።
፹፮ ሀ ማቴ. ፳፬፥፵፭–፵፮፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፮–
፳፱፤ ፻፯፥፺፱–፻።

ሆነ፣ የመንግስትን ወንጌል ለማወጅ የሚሄድ ማንም ሰው ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ኮረጆም ወይም ከረጢት አይውሰድ።

፹፯ እነሆ፣ ጻድቅ ላልሆነው ስራዎቻቸው ዓለምን እንድትወቅሱ፣ እና ስለሚመጣው ፍርድም ታስተምሯቸው ዘንድ [ሀ]ልኬአችኋለሁ።

፹፰ እናም [ሀ]የሚቀበሏችሁም ቢሆን፣ እኔም በዚያም እገኛለሁ፣ በፊታችሁም እሄዳለሁና። በቀኛችሁ እና በግራችሁ እሆናለሁ፣ እናም መንፈሴም በልባችሁ ውስጥ ይገኛል፣ እናም ይደግፏቹም ዘንድ [ለ]መላእክቴ በዙሪያችሁ ይሆናሉ።

፹፱ ማንም የሚቀበላችሁ እኔን ይቀበለኛል፤ እናም እርሱም ይመግባችኋል፣ እናም ያለብሳችኋል፣ እናም ገንዘብም ይሰጣችኋል።

፺ እናም የሚመግባችሁ፣ ወይም የምሚያለብሳችሁ፣ ወይም ገንዘብንም የሚሰጣችሁ፣ በምንም ዋጋው [ሀ]አይጠፋበትም።

፺፩ እናም እነዚህን ነገሮች የማያደርገው እርሱ ደቀ መዛሙርቴ አይደለም፤ በዚህም [ሀ]ደቀመዛሙርቴን ታውቋቸዋላችሁ።

፺፪ ለማይቀበላችሁም፣ ከእርሱ ተለይታችሁ ውጡ፣ እናም በሙቀትም ይሁን በቅዝቀዛ እግሮቻችሁን በውሀ፣ እንዲሁም በንጹ ውሀ [ሀ]አጽዱ፣ እናም ምስክርንም ለሰማይ አባታችሁ አቅርቡ፣ እናም ወደእርሱም ደግማችሁ አትመለሱ።

፺፫ እናም በምትገቡበትም መንደር ወይም ከተማ፣ ይህንኑ አድርጉ።

፺፬ ይህም ቢሆን፣ ተግታችሁ ፈልጉ እናም አትታክቱ፤ እናም እናንተን ወይም ቃላቶቻችሁን፣ ወይም እኔን በመመልከት ያላችሁን ምስክር ለማይቀበል ለዚያ ቤት ወይም መንደር ወይም ከተማ ወዮለት።

፺፭ እናንተን ወይም ቃላቶቻችሁን፣ ወይም እኔን በመመልከት ያላችሁን ምስክር ለማይቀበል ለእዚም ቤት ወይም መንደር ወይም ከተማ ደግሜ ወዮለት እላለሁ።

፺፮ እኔ፣ [ሀ]ሁሉን የሚገዛው፣ [ለ]ጥፋተኝነታቸውን [ሐ]ለመቅጣት እጆቼን በአህዛብ ላይ አሳርፌአለሁ።

፺፯ እናም መቅሰፍቶችም ይሆናሉ፣ እናም ስራዬን እስከምጨርስ ድረስም አይወሰዱም፣ ይህም በፅድቅ [ሀ]በአጭር ይቆረጣል—

፺፰ የሚቀሩት፣ እንዲሁም ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ፣ ሁሉ እስከሚያውቁኝ ድረስ፣ እናም በጌታ እውቀትም ይሞላሉ፣ እናም [ሀ]ዓይን ለዓይን ይተያያሉ፣ እናም ድምፃቸውንም ያነሣሉ፥ እናም በአንድነትም ይህን አዲስ መዝሙር እንዲህ በማለት [ለ]ይዘምራሉ፥

፺፱ ጌታ ፅዮንን ዳግም መልሷል፤
ጌታ ሕዝቡ፣ [ሀ]እስራኤልን፣ [ለ]አድኗል፣
[ሐ]በጸጋ በሆነ [መ]ምርጫ፣
እናም በአባቶቻቸው [ሠ]ቃል ኪዳን፣
ይህም በእምነት የተከናወነ ነበር።

፻ ጌታ ህዝቡን ተቤዠ
እናም ሰይጣንም [ሀ]ታስሯል እና የጊዜ ቀመር
አይኖርም።
ጌታ ሁሉንም ነገሮች [ለ]በአንድ ጠቅልሏል።
ጌታ [ሐ]ፅዮንን ከላይ መልሶ አምጥቷል።
ጌታ ፅዮንንም ከታችም መልሶ [መ]አምጥቷል።

፹፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፹፰ ሀ ማቴ. ፲፥፵፤ ዮሐ. ፲፫፥፳።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፵፪።
ቅ.መ.መ. መላእክት።
፺ ሀ ማቴ. ፲፥፵፪፤
ማር. ፱፥፵፩።
፺፩ ሀ ዮሐ. ፲፫፥፴፭።
፺፪ ሀ ማቴ. ፲፥፲፬፤
ሉቃ. ፱፥፭፤
ት. እና ቃ. ፳፬፥፲፭።
፺፮ ሀ ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚገዛ።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ክፉ፣ ክፋት።
፺፯ ሀ ማቴ. ፳፬፥፳፪።
፺፰ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፰።
ለ መዝ. ፺፮፥፩፤ ራዕ. ፲፭፥፫፤
ት. እና ቃ. ፳፭፥፲፪፤
፻፴፫፥፶፮።
ቅ.መ.መ. መዘመር።
፺፱ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል።
ለ ራዕ. ፭፥፱፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፳፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
መ ቅ.መ.መ. መመረጥ።
ሠ ቅ.መ.መ. የአብርሐም
ቃል ኪዳን።
፻ ሀ ራዕ. ፳፥፪–፫፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፩፤
፵፭፥፶፭፤ ፹፰፥፻፲።
ለ ኤፌ. ፩፥፲፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፫።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፭፥፲፩–፲፬፤
ሙሴ ፯፥፷፪–፷፬።
ቅ.መ.መ. ፅዮን።
መ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፱፤
፷፫፥፵፰።

፻፩ [ሀ]ምድርም አምጣለች እና ጥንካሬዋንም አምጥታለች፤
እውነትም በሆዷ ውስጥ የተመሰረተ ነው፤
እና ሰማያትም በእርሷ ላይ ፈገግ ይላሉ፤
እናም እርሷም የአምላኳን [ለ]ክብር ልብስ ለብሳለች፤
እርሱም በሕዝቦቹ መካከል ቆሟልና።

፻፪ ክብር፣ እና ሀይል፣ እና ብርታት፣
ለአምላካችን ይሁን፤ እርሱም [ሀ]በምህረት፣
በፍትህ፣ በጸጋ፣ እና [ለ]በሰላም የተሞላ ነውና፣
ከዘለአለም እስከዘለአለም፣ አሜን።

፻፫ እና ደግሞም፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ዘለአለማዊ ወንጌሌን ለማወጅ የሚሄደው እያንዳንዱ ሰው፣ ቤተሰብ ያላቸው ቢሆን፣ እናም የገንዘብ ስጦታን ቢቀበሉ፣ ይህን ጌታ እንደሚመራቸው ለእነርሱ እንዲልኩ ወይም ለእነርሱ ጥቅም ያውሉት ዘንድ አስፈላጊ ነው፣ ይህም መልካም ነውና።

፻፬ እናም [ሀ]ገንዘብ የሚቀበሉት ቤተሰብ የሌላቸውም፣ ለራዕዮች መገለጥ እና መታተም እናም ለፅዮን መመስረት የተቀደሰ ይሆን ዘንድ፣ ወደ በፅዮን ወይም በኦሀዮ ላለ ኤጲስ ቆጶስ ይላኩት።

፻፭ እናም ማንም ሰው ኮት ወይም ሙሉ ልብስን ቢሰጣችሁ፣ አሮጌውን ወስዳችሁ [ሀ]ለደሀው ስጡ፣ እናም በደስታም ሂዱ።

፻፮ እናም በመካከላችሁ አንዱ ሰው በመንፈሱ ጠንካራ ቢሆን፣ [ሀ]በቅንነት እንዲታነጽ፣ ደግሞም ጠንካራ ይሆን ዘንድ፣ ከእርሱ ጋር ደካማ የሆነውን [ለ]ይውሰድ።

፻፯ ስለዚህ፣ ከእናንተ ጋር [ሀ]በአነስተኛው ክህነት የተሾሙትን ውሰዱ፣ እናም ቀጠሮም ያድርጉ፣ እናም መንገድንም እንዲያዘጋጁላችሁ፣ እናም እናንተ ራሳችሁ ልታከናውኑት የማትችሉትን ቀጠሮ ያሟሉላችሁ ዘንድ በፊታችሁ ስደዷቸው።

፻፰ እነሆ፣ ይህም በቀደሙት ጊዜያት ሐዋሪያቴ ቤተክርስቲያኔን የገነቡበት መንገድ ነው።

፻፱ ስለዚህ፣ እያንዳንዱ ሰው በተሾመበት ይቁም፣ እናም በጥሪውም ያገልግል፤ እናም ራስ ለእግር እግር አስፈላጊ አይደለም አይበለው፤ ምክንያቱም ያለእግር ሰውነት ሊቆም ይቻለዋል?

፻፲ ደግሞም፣ ሁሉም አብረው ይታነጹ ዘንድ፣ አሰራሩም በፍጹም ሆኖ ይቀጥል ዘንድ፣ አካል እያንዳንዱ [ሀ]ብልቶች ያስፈልጉታልና።

፻፲፩ እናም እነሆ፣ [ሀ]ሊቀ ካህናት፣ እና ደግሞም ሽማግሌዎች፣ እና ደግሞም አነስተኛዎቹ [ለ]ካህናት ይጓዙ ዘንድ ይገባል፤ ነገር ግን [ሐ]ዲያቆናት እና [መ]መምህራን ቤተክርስቲያኗን [ሠ]እንዲጠብቁ፣ በቤተክርስቲያኗ የማይጓዙ አገልጋዮች በመሆን እንዲወከሉ ይገባቸዋል።

፻፲፪ እናም ኤጲስ ቆጶሱ፣ ኒወል ኬውትኒ፣ ደግሞም በአካባቢው እና በቤተክርስቲያናቱ መካከልም፣ የደሆችን ፍላጎት በመጠበቅ ሀብታሞችን እና ትእቢተኞችን [ሀ]ዝቅ በማድረግ [ለ]ለመርዳት መጓዝ ይገባዋል።

፻፲፫ ሀላፊነትን እንዲወስድ እና በሚመራው መንገድ ስጋዊ ሀላፊነትን እንዲያከናውን [ሀ]ወኪልንም መጥራት ይገባዋል።

፻፲፬ ይህም ቢሆን፣ ኤጲስ ቆጶሱ ወደ ኒውዮርክ ከተማ፣ ደግሞም ወደ አልበኒ ከተማ፣ እናም ደግሞም ወደ ቦስተን ከተማ ይሂድ፣ እናም የእነዚህ ከተማ ሰዎችንም በወንጌሉ ድምጾች፣ በጎላ ድምፅ፣ እነዚህን ነገሮች

፻፩ ሀ ቅ.መ.መ. ምድር።
ለ ቅ.መ.መ. ክብር።
፻፪ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ለ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፻፬ ሀ ት. እና ቃ. ፶፩፥ ፰–፱፣ ፲፪–፲፫።
፻፭ ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ—በአለማዊ እቃዎች ደሀነት።
፻፮ ሀ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ለ ቅ.መ.መ. ጓደኝነት።
፻፯ ሀ ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
፻፲ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፪፥ ፲፪–፳፫።
፻፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ለ ቅ.መ.መ. ካህን፣ የአሮናዊ ክህነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያቆን።
መ ቅ.መ.መ. መምህር፣ የአሮናዊ ክህነት።
ሠ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፻፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፮፥ ፲፮።
ለ ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።
፻፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፺፥ ፳፪።

ቢቃወሙ ስለሚጠብቃቸው [ሀ]ውድመት እና የከፋ ጥፋት ያስጠንቅቅ።

፻፲፭ እነዚህን ነገሮች ቢቃወሙ የፍርዳቸው ሰአት ደርሶአልና፣ እናም ቤታቸውም [ሀ]በውድመት ይቀርላቸዋል።

፻፲፮ በእኔ [ሀ]ይመን እናም እርሱም [ለ]አያፍርም፤ እናም የራሱም [ሐ]ጠጉር ሳይታወቅ ምድር ላይ አይወድቅም።

፻፲፯ እናም እውነት እላችኋለሁ፣ የቀራችሁት አገልጋዮቼ፣ ጉዳያችሁ እንደሚፈቅድላችሁ፣ በተለያዩት ጥሪዎቻችሁ፣ ወደ ታላቅ እና ታዋቂ ከተማዎች እና መንደሮች፣ በፅድቅ አለምን ጻድቅ ላልሆኑ እና እግዚአብሔርን ለማያመልኩ ስራዎቻቸውን እየወቀሳችሁ፣ በግልፅ እና በሚገባ ሁኔታ የመጨረሻ ቀናት የጥፋት ርኩሰትን በመግለፅ ሂዱ።

፻፲፰ በእናንተም መንግስቶቻቸውን [ሀ]እደመስሳቸዋለሁ፤ ምድርን [ለ]ማናውጥ ብቻ ሳይሆን፣ ኮከባዊውን ሰማያትንም አናውጣለሁ ይላል ሁሉን የሚገዛው አምላክ።

፻፲፱ እኔ ጌታ የሰማይን ሀይላት ለመጠቀም እጆቼን እዘረጋለሁና፤ አሁን ልታዩት አትችሉም፣ ነገር ግን ከትንሽ ጊዜ በኋላ ታዩታላችሁ፣ እናም እኔ እንደሆንኩኝ፣ እናም በህዝቤ መካከል [ሀ]ለመንገስ [ለ]እንደምመጣም ታውቃላችሁ።

፻፳ እኔ [ሀ]አልፋና ኦሜጋ፣ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው፣ ነኝ። አሜን።

ክፍል ፹፭

በህዳር ፳፯፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ክፍል በእንድፐንደንስ ሚዙሪ ውስጥ ለሚኖረው ዊልያም ደብሊው. ፌልፕስ ነቢዩ ከጻፈው ደብዳቤ ውስጥ የተውጣጣ ምንባብ ነው። ይህም የተሰጠው ወደፅዮን ቢሄዱም፣ ንብረቶቻቸውን እንዲቀድሱ የሚያዘውን ትዝዛዝ ያልተከተሉና በዚህም ምክንያት በተመሰረተው በቤተክርስቲያኗ ህግጋት መረሰት ውርሳቸውን ያልተቀበሉት ቅዱሳንን ጥያቄ ለመመለስ ነበር።

፩–፭፣ በፅዮን ውስጥ ውርሶች የሚገኙት በቅድስና በኩል ነው፤ ፮–፲፪፣ ኃያል እና ብርቱ የሆነው ብቻ ለቅዱሳኑ ውርስን በፅዮን ውስጥ ይሰጣል።

፩ እርሱ የመደበው የጌታ ሂሳብ ሰራተኛ ሀላፊነትም፣ ታሪክን ለመጠበቅ፣ እና በፅዮን የሚደረጉትን ሁሉንም ነገሮች፣ እና ንብረቶቻቸውን [ሀ]የቀደሱትን ሁሉ፣ እና ከኤጲስ ቆጶሱ ውርስን በህግ የሚቀበሉትን የአጠቃላይ የቤተክርስቲያኗን [ለ]መዝገብ ለመጠበቅ ነው።

፪ ደግሞም አኗኗራቸውን፣ እምነታቸውን፣ እና ስራቸውን፤ እና ደግሞም ውርሶቻቸውን ከተቀበሉ በኋላ የሚያምጹትን ከሀዲዎችን መዝገብ ለመጠበቅ ነው።

፫ ህዝቦቹን [ሀ]አስራት በማስከፈል፣ እነር

፻፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬።
፻፲፭ ሀ ሉቃ. ፲፫፥፴፭።
፻፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. መታመን።
ለ መዝ. ፳፪፥፭፤
፩ ጴጥ. ፪፥፮።
ሐ ማቴ. ፲፥፳፱–፴፩።
፻፲፰ ሀ ዳን. ፪፥፵፬–፵፭።
ለ ኢዩ. ፪፥፲፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፰፤
፵፭፥፵፫፣ ፵፰፤
፹፰፥፹፯፣ ፺።
ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣
የኋለኛው ቀናት፤
የጊዜዎች ምልክቶች።
፻፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፲፪፣ ፴፭–፴፮፤
፳፱፥፱–፲፩፤ ፵፭፥፶፱።
ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፻፳ ሀ ቅ.መ.መ. አልፋ
እና ኦሜጋ።
፹፭ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴–፴፭።
ለ ት. እና ቃ. ፳፩፥፩፤
፵፯፥፩፤ ፷፱፥፫–፰።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. መቀደስ፣
የቅድስና ህግ።

ሱን [ለ]ለበቀል እና ለመቃጠል ቀን ለማዘጋጀት፣ በሰጣቸው ህጉ ተስማሚ በሆነው፣ ውርሶቻቸውን [ሐ]በቅድስና የማይቀበሉት ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር ስማቸው መመዝገቡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ እና ትእዛዝ ጋር የሚቃረን ነው።

፬ የትውልድ ሐረጋቸውም አይጠበቅ፣ ወይም በቤተክርስቲያኗ መዝገብ ወይም ታሪክ ውስጥ የሚገኝ አይሁን።

፭ ስሞቻቸውም ወይም የአባቶቻቸው ስሞች፣ ወይም የልጆቻቸው ስሞች በእግዚአብሔር ህግጋት [ሀ]መፅሐፍ ውስጥ ተፅፈው አይገኙም፣ ይላል የሰራዊት ጌታ።

፮ አዎን፣ በሁሉም ነገሮች በለሆሳስ የሚናገር እና [ሀ]ሰንጥቆ የሚገባው፣ እናም ይህን ሲገልፅም አጥንቶቼን የሚያንቀጠቅጥ፣ [ለ]አነስተኛ ለስላሳ ድምፅም እንዲህ ይላል፥

፯ እናም እንዲህ ይሆናል፣ እኔ ጌታ አምላክ የሀይልን በትር በእጁ የያዘ፣ ብርሀንን እንደልብስ የለበሰ፣ አንደበቱም ቃላትን፣ እንዲሁም ዘለአለማዊ ቃላትን፣ የሚናገር፣ ኃያል እና ብርቱ እልካለሁ፤ አንጀቱም፣ የእግዚአብሔርን ቤት ለማስተካከል፣ እና ስማቸው እና የአባቶቻቸው እና የልጆቻቸውም ስም በእግዚአብሔር ህግ መፅሐፍ ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙትን ቅዱሳን ውርሶቻቸውን በእጣ ለማደራጀት የእውነት ምንጭ ይሆንላቸዋል፤

፰ በእግዚአብሔር ተጠርቶ የተመደበው፣ እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን [ሀ]ታቦት የያዘ ሰው፣ በመብረቅ እንደተመታ ዛፍ፣ በፍላጻ ሞት ይወድቃል።

፱ እናም [ሀ]በመታሰቢያ መጽሐፍ ውስጥ ተፅፈው የማይገኙት ሁሉ በዚያ ቀን ምንም ውርስ አያገኙም፣ ነገር ግን ለሁለትም ይሰነጥቃቸዋል፣ ውርሶቻቸውም ከማያምኑት ጋር ያደርግባቸዋል፣ በዚያም [ለ]ዋይታና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

፲ የምላቸው እነዚህ ነገሮች ከእኔ አይደሉም፤ ስለዚህ፣ ጌታ እንደተናገረው እንዲሁ ደግሞ ይፈጽመዋል።

፲፩ እናም፣ በህግ [ሀ]መፅሐፍ ውስጥ ስሞቻቸው ተፅፎ የማይገኙት ወይም [ለ]በአመጻ የሚገኙት፣ ወይም ከቤተክርስቲያኗ [ሐ]የተቆረጡት የታላቅ ክህነት ክፍል የነበሩት፣ እና የአነስተኛው ክህነት፣ ወይም አባላት፣ በዚያ ቀን በልዑል እግዚአብሔር ቅዱሳን መካከል ውርሳቸውን አያገኙም፤

፲፪ ስለዚህ፣ በዕዝራ በምዕራፍ ሁለት በስልሳ አንደኛ እና ሁለተኛ አንቀጾች ውስጥ እንደሚገኘው፣ ለእነርሱም ለካህናት ልጆች እንደተደረገው ይደረግባቸዋል።

ክፍል ፹፮

በታህሳስ ፮፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩ ይህን ራዕይ የተቀበለው የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ያልታተመ ጽሁፍን ሲገመግም እና ሲያርም ነበር።

፩–፯፣ ጌታ ስለስንዴ እና እንክርድ ምሳሌ ትርጉም ሰጠ፤ ፰–፲፩፣ በስጋ መሰረት ህጋዊ ወራሾች ለሆኑት የሚመጣውን የክህነት በረከቶች ገለፀ።

፫ ለ ሚል. ፫፥፲–፲፩፣ ፲፯፤
ት. እና ቃ. ፺፯፥፳፭–፳፮።
ሐ ቅ.መ.መ. አስራት፣
አስራት መክፈል።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. የሕይወት
መፅሐፍ።
፮ ሀ ዕብ. ፬፥ ፲፪።
ለ ፩ ነገሥ. ፲፱፥ ፲፩–፲፪፤
ሔለ. ፭፥ ፴–፴፩፤
፫ ኔፊ ፲፩፥ ፫–፯።
፰ ሀ ፪ ሳሙ. ፮፥ ፮–፯፤
፩ ዜና ፲፫፥ ፱–፲።
ቅ.መ.መ. የኪዳን ታቦት።
፱ ሀ ፫ ኔፊ ፳፬፥ ፲፮፤
ሙሴ ፮፥ ፭–፮።
ቅ.መ.መ. የመታሰቢያ
መፅሐፍ።
ለ ት. እና ቃ. ፲፱፥ ፭።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የሕይወት
መፅሐፍ።
ለ ቅ.መ.መ. ክህደት።
ሐ ቅ.መ.መ. ውግዘት።

፩ ስለስንዴ እና እንክርድ [ሀ]ምሳሌ በሚመለከት በእውነት ለእናንተ አገልጋዮቼ ጌታ እንዲህ ይላል፥

፪ እነሆ፣ በእውነት እላለሁ፣ እርሻው አለም ሲሆን፣ እናም ሐዋርያትም ዘሩን የዘሩት ነበሩ፤

፫ እናም ካንቀላፉ በኋላ የቤተክርስቲያኗ አሳዳጅ፣ ከሀዲ፣ ጋለሞታ፣ እንዲሁም አህዛብን የእርሷን ጽዋ እንዲጠጡ የምታደርገው [ሀ]ባቢሎን፣ በልቧም ጠላት፣ እንዲሁም ሰይጣን፣ ለመንገስ የተቀመጠው—እነሆ እርሱም እንክርዳዶችን ይዘራል፤ ስለዚህ፣ እንክርዳዶቹም ስንዴውን ያንቃሉ፣ እናም [ለ]ቤተክርስቲያኗ ወደበረሀ እንድትበር ያደርጋታል።

፬ ነገር ግን፣ እነሆ፣ [ሀ]በመጨረሻ ቀናት፣ እንዲሁም ጌታ ቃልን በሚያመጣበት ጊዜ፣ እና ስለትቱም እያቆጠቆጠ ነው እናም ገና እየለመለመም ነው—

፭ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሄደው እርሻውን [ሀ]ለማጨድ ተዘጋጅተው የሚጠባበቁ [ለ]መላእክት ወደ ጌታ በቀን እና በማታ ይለምናሉ፤

፮ ነገር ግን ጌታ እንዲህ ይላቸዋል፣ ስለቱ ገና እየለመለመ እያለ እንክርዳዶችን አትንቀሉ (በእውነት እምነታችሁ ደካማነውና)፣ አለበለዚያም ስንዴውንም ደግማችሁ ታጠፉታላችሁና።

፯ ስለዚህ፣ መከሩ ሁሉ እስከሚያብብ ድረስ ስንዴዎቹ እና እንክርዳዶቹ አብረው ይደጉ፤ ከዚያም መጀመሪያ ስንዴዎቹን ከእንክርዳዶቹ መካከል ሰብስቡ፣ እናም ስንዴዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ፣ እነሆ እናም አስተውሉ፣ በነዶው ታስረዋል፣ እናም እርሻውም ለመቃጠል ይቀራል።

፰ ስለዚህ፣ በአባቶቻችሁ ዘር [ሀ]ክህነት ለሚቀጥሉላችሁ ጌታ እንዲህ ይላችኋል—

፱ እናንተ፣ በስጋ መሰረት ህጋዊ [ሀ]ወራሾች ናችሁና፣ እናም በእግዚአብሔር ውስጥ ከክርስቶስ ጋር ከአለም [ለ]ተሰውራችኋል—

፲ ስለዚህ ህይወታችሁ እና ክህነቱ ይቀራሉ፣ እናም በእናንተም እና በዘራችሁም አለም ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ቅዱሳን ነቢያት አንደበት የተነገሩት ሁሉም ነገሮች [ሀ]በዳግም እስከሚመለሱ ድረስም መቅረት ያስፈልጋቸዋናል።

፲፩ ስለዚህ፣ በመልካምነት፣ ለአህዛብ [ሀ]ብርሀን ሆናችሁ፣ እና በዚህ ክህነት በኩልም የህዝቤ [ለ]እስራኤል አዳኝ በመሆን ከቀጠላችሁ የተባረካችሁ ናችሁ። ጌታ ይህን ብሎታል። አሜን።

ክፍል ፹፯

በታህሳስ ፳፭፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል በከርትላንድ ኦሀዮ ወይም በአካባቢው የተሰጠ የጦርነት ራዕይ እና ትንቢት። በዚህ ጊዜ በዮናይትድ ስቴትስ ውስጥ ስለ ባርነት እና ሳውዝ ኬሮላይና የመንግስት ቀረጥ ስለመሰረዟ ክርክር በብዛት ይገኝ ነበር። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፣ "በሀገሮች መካከል ያለው ችግር ቤተክርስቲያኗ ከዱር የመውጣት ጉዞዋን ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ከነበረው በላይ" ለነቢዩ "በግልፅ ይታይ" ነበር።

፹፮ ፩ ሀ ማቴ. ፲፫፥ ፯–፵፫፤ ት. እና ቃ. ፻፩፥ ፷፭–፷፯።
፫ ሀ ራዕ. ፲፯፥ ፩–፱። ቅ.መ.መ. ባቢሎን።
ለ ራዕ. ፲፪፥ ፯፣ ፲፬።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. መከር።
ለ ት. እና ቃ. ፴፰፥ ፲፪።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፫፥ ፰። ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፱ ሀ አብር. ፪፥ ፱–፲፩። ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ለ ኢሳ. ፵፱፥ ፪–፫።
፲ ሀ የሐዋ. ፫፥ ፲፱–፳፩። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፲፩ ሀ ኢሳ. ፵፱፥ ፮።
ለ ት. እና ቃ. ፻፱፥ ፶፱–፷፯።

፩–፬፡ በሰሜን እና በደቡብ ስቴቶች መካከል ጦርነት ተተነበየ፤ ፭–፰፡ ታላቅ መቅሰፍት በምድር ነዋሪዎች ላይ ይደርሳል።

፩ እውነትም፣ ጌታ፣ [ሀ]በደቡብ ኬሮላይና ማመፅ በሚጀምረው፣ የብዙ ነፍሳት ሞት እና ስቃይ ውጤት ስለሆነው፣ በአጭር ጊዜ ስለሚመጣው ጦርነት እንዲህ ይላል፤

፪ እናም፣ ከዚህ ስፍራ አንስቶ፣ በሁሉም ህዝብ ላይ [ሀ]ጦርነት የሚፈስበት ጊዜ ይመጣል።

፫ እነሆ፣ የደቡብ ስቴቶቹ ከሰሜን ስቴቶቹ ጋር ይከፋፈላሉ፣ እናም የደቡብ ስቴቶች ሌሎች ሀገሮችን፣ እንዲሁም እንግሊዝ ተብለው የሚጠሩትንም ይጠራሉ፣ እናም እነርሱም፣ ከሌሎች አገሮች ራሳቸውን ለመጠበቅ፣ ሌሎች አገሮችን ይጠራሉ፤ እና ከዚያም [ሀ]ጦርነት በሁሉም ሕዝቦች ላይ ይፈሳል።

፬ እናም እንዲህ ይሆናል፣ ከብዙ ቀናት በኋላ፣ ለጦርነት የተዘጋጁት እና የሰለጠኑት [ሀ]ባሪያዎች በጌታቸው ላይ ይነሳሉ።

፭ እናም እንዲህ ይሆናል በምድሩ የሚቀሩትም ራሳቸውን ያዘጋጃሉ፣ እናም በጣም ይቆጣሉ፣ እናም አህዛብን በታላቅ ስቃይ ያሰቃዩአቸዋል።

፮ በመሆኑም፣ በጎራዴ እና ደም በማፍሰስ የምድር ነዋሪዎች [ሀ]ያዝናሉ፤ እናም፣ የክፉ ጥፋት ሕዝብን ሁሉ በፍጹም እንዲጠፉ እስከሚያደርጋቸው ድረስ፣ [ለ]በረሀብ፣ እና ወረርሽኝ፣ እና በምድር መንቀጥቀጥ፣ እና በሰማይ ነጎድጓድ፣ እና በአስፈሪ እና በግልፅ መብረቅም [ሐ]የምድር ነዋሪዎች ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔርን እጅ ንዴት፣ እና ቁጣ፣ እና [መ]ግሰጻ እንዲሰማቸው ይደረጋሉ።

፯ በጠላቶቻቸው ላይ እንዲበቀሉ የቅዱሳን እና የቅዱሳን [ሀ]ደም ወደሚጮኹበት ወደ [ለ]ፀባኦት ጌታ ጆሮዎች መምጣትን ያቆማሉ።

፰ ስለዚህ፣ የጌታ ቀን እስከሚመጣ ድረስ፣ በተቀደሱ ስፍራዎች [ሀ]ቁሙ፣ እናም አትነቃነቁ፤ እነሆ፣ [ለ]በቶሎ ይመጣልና፣ ይላል ጌታ። አሜን።

ክፍል ፹፰

በታህሳስ ፳፯ እና ፳፰፣ ፲፰፻፴፪፣ እና በጥር ፫፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህም በነቢዩ "'የወይራ ቅጠል'. . .ከገነት ዛፍ የተቀጠፈች፣ ለእኛ የተሰጠ የጌታ የሰላም መልእክት" ተብሎ ተጠቁሞ ነበር። ይህም ራዕይ የተሰጠው ሊቀ ካህናት በጉባኤ "አንድ በአንድ እና በድምጽ ጌታ ለእኛ ስለፅዮን መገንባት ፍላጎቱን እንዲገልጽልን" ከጸለዩ በኋላ ነበር።

፩–፭፡ ታማኝ ቅዱሳን የዘለአለም ህይወት ተስፋ የሆነውን ያንን አፅናኝ ተቀበሉ፤ ፮–፲፫፡ ሁሉም ነገሮች በክርስቶስ ብርሀን ቁጥጥር ስር ያሉ እና የሚገዙ ናቸው፤ ፲፬–፲፮፡ ትንሳኤ የሚመጣው በቤዛነት በኩል ነው፤ ፲፯–፴፩፡ ለሰለስቲያል፣ ለተረስት

፹፯ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፥፲፪–፲፫።
፪ ሀ ኢዩ. ፫፥፱–፲፮፤
ማቴ. ፳፬፥፮–፯፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፮፤
፷፫፤ ፷፫፥፴፫።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፰–፷፱።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፬፥፲፪።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፬–፳፩፤
፹፰፥፹፱።
ለ ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፳፱።
ሐ ቅ.መ.መ. አለም—
የአለም መጨረሻ።
መ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፯ ሀ ኤተር ፰፥፳፪–፳፬።
ለ ያዕ. ፭፥፬፤
ት. እና ቃ. ፺፰፥፪፤ ፺፭፥፯።
፰ ሀ ማቴ. ፳፬፥፲፭፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፴፪፤
፻፩፥፳፩–፳፪።
ለ ራዕ. ፫፥፲፩።

ሪያል፣ ወይም፣ ለቲለስቲያል ህግ ታዛዥ መሆን ሰዎችን ለእነዚህ መንግስታት እና ክብሮች ያዘጋጃል፤ ፴፪–፴፭፣ በኃጢአት የሚኖሩትም በመርከስ ይቀራሉ፣ ፴፮–፵፩፣ ሁሉም መንግስታት በህግ የሚገዙ ናቸው፤ ፵፪–፵፭፣ እግዚአብሔር ለሁሉም ነገሮች ህግ ሰጥቷል፤ ፵፮–፶፣ ሰው እግዚአብሔርንም እንኳ ይረዳዋል፤ ፶፩–፷፩፣ አገልጋዮቹን ወደ መስክ ልኮ እናም በየተራ ስለሚጎበኛቸው ሰው ምሳሌ፤ ፷፪–፸፫፣ ወደጌታ ቅረቡ፣ እናም ፊቱንም ታያላችሁ፤ ፸፬–፹፣ ራሳችሁን ቀድሱ እናም የመንግስትን ትምህርት እርስ በርስ ተማማሩ፤ ፹፩–፹፭፣ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው እያንዳንዱ ሰው ጎረቤቱን ሊያስጠነቅቅ ይገባዋል፤ ፹፮–፺፬፣ ምልክቶች፣ የፍጥረታት መናወጥ፣ እና መላዕክት የጌታን መምጫ መንገድ ያዘጋጃሉ፤ ፺፭–፻፪፣ መላዕክታዊ መለከቶች ሙታንን በየተራቸው እንዲነሱ ይጠሯቸዋል፤ ፻፫–፻፲፮፣ መላእክታዊ መለከቶች የወንጌሉን በዳግም መመለስ፣ የባቢሎንን መውደቅ፣ እና የታላቁን የእግዚአብሔር ጦርነት ያውጃሉ፤ ፻፲፯–፻፳፮፣ ትምህርትን ፈልጉ፣ የእግዚአብሔርን ቤት (ቤተመቅደስን) መስርቱ፣ እናም የልግስና ማሰሪያንም ልበሱ፤ ፻፳፯–፻፵፩፣ የነቢያት ትምህርት ቤት ስርዓት፣ እግሮችን የማጠብ ስርዓት በመጨመር፣ ተመድቧል።

፩ በእውነት፣ እናንተን በመመልከት ያለውን ፈቃዱን ለመቀበል ለተሰበሰባችሁት ጌታ እንዲህ ይላል፥

፪ እነሆ፣ ይህ ጌታን የሚያስደስት ነው፣ እናም መላእክትም በእናንተ [ሀ]ተደስተዋል፤ የጸሎታችሁ [ለ]ምፅዋትም [ሐ]በፀባኦት ጌታ ጆሮዎች ውስጥ መጥተዋል፣ እናም በተቀደሱት ስሞች፣ እንዲሁም የሰለስቲያል አለም በሆኑት፣ [መ]መፅሀፍ ውስጥ ተመዝግበዋል።

፫ ስለዚህ፣ ለእናንተ፣ እንዲሁም ወደ እናንት ባልንጀሮቼ፣ በልባችሁ ውስጥ እንዲኖር፣ ሌላ [ሀ]አፅናኝ፣ እንዲሁም [ለ]ቅዱስ የተስፋ መንፈስን እልክላችኋለሁ፤ ያም አፅናኝ፣ በዮሐንስ ምስክር ውስጥ እንደ ተመዘገበው፣ ለደቀመዛሙርቴ ቃል የገባሁላቸው ነው።

፬ ይህም አፅናኝ [ሀ]ለዘለአለም ህይወት፣ እንዲሁም የሰለስቲያል መንግስት [ለ]ክብርን፣ እንደምሰጣችሁ የገባሁላችሁ ቃል ኪዳን ነው፤

፭ ይህም [ሀ]የበኩሩ ቤተክርስቲያን፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሆነ፣ እንዲሁም ከሁሉም በላይ ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር ነው—

፮ [ሀ]እርሱም በሁሉም ነገሮች ውስጥና በሁሉም ነገሮች በኩል በመሆን የእውነት [ለ]ብርሀን ይሆን ዘንድ፣ በዚህም ሁሉን ነገሮች [ሐ]እንዲረዳ ዘንድ፣ ወደላይ ያረገው፣ ደግሞም ከሁሉም ነገሮች በታች [መ]የወረደው ነው።

፯ ይህም እውነት ያበራል። ይህም [ሀ]የክርስቶስ ብርሀን ነው። እርሱም በጸሀይ ውስጥ፣ እናም የጸሀይ ብርሀን፣ እናም ያም [ለ]የተሰራበት ሀይል ነው።

፰ እርሱም በጨረቃ ውስጥ፣ እናም የጨረቃ ብርሀን፣ እና ያም የተሰራበት ሀይል ነው፤

፹፰ ፪ ሀ ሉቃ. ፲፭፥፲።
ለ የሐዋ. ፲፥፩–፬።
ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ያዕ. ፭፥፬፤
ት. እና ቃ. ፺፭፥፯።
መ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
፫ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፲፮።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶፫።
ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፲፬፥፯።
ለ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. በኩር።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ።
ለ ት. እና ቃ. ፺፫፥፪፤ ፰–፴፱።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን፤
እውነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
መ ት. እና ቃ. ፻፳፪፥፰።
ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፯ ሀ ሞሮኒ ፯፥፲፭–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፵፭።
ለ ዘፍጥ. ፩፥፲፮።
ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።

፱ የከዋክብትም ብርሀን፣ እናም እነዚህም የተሰሩበት ሀይል፤

፲ እናም ምድርንም፣ እናም ይህም ሀይል፣ እንዲሁም [ሀ]የቆማችሁበት ምድር ነው።

፲፩ እናም ብርሀን የሚሰጣችሁም፣ የሚበራው ብርሀንም፣ በእርሱ አይኖቻችሁን የሚያበራው በኩል ነው፣ ያ ብርሀንም [ሀ]የምትረዱበትን የሚያነሳሳው ነው፤

፲፪ ያም ከእግዚአብሔር ፊት ጠፈርን [ሀ]ለመሙላት የሚሄድ [ለ]ብርሀን ነው—

፲፫ [ሀ]በሁሉም ነገሮች ውስጥ ነው፣ ለሁሉም ነገሮች [ለ]ህይወት ይሰጣል፣ ሁሉም ነገሮች የሚገዙበት [ሐ]ህግ፣ እንዲሁም፣ በዘለአለም እቅፍ ውስጥ ያለው፣ በሁሉም ነገሮች መካከል ውስጥ ያለው፣ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠው የእግዚአብሔር ሀይል የሆነው ብርሀን ነው።

፲፬ አሁን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለእናንተ በተደረገላችሁ [ሀ]ቤዛነት በኩል የሙታን ትንሳኤ ይመጣል።

፲፭ እናም [ሀ]መንፈስና [ለ]አካል የሰው [ሐ]ነፍስ ናቸው።

፲፮ እናም የሙታን [ሀ]ትንሳኤ የነፍስ ቤዛነት ነው።

፲፯ እናም የነፍስ ቤዛነትም ሁሉንም ነገሮች ህይወት በሚሰጠው፣ በልቡ [ሀ]ድሀውና [ለ]የዋሁ [ሐ]ምድርን ይወርሳሉ ተብሎ በታወጀበት በእርሱ በኩል ነው።

፲፰ ስለዚህ፣ [ሀ]ለሰለስቲያል ክብር ያዘጋጅ ዘንድ፣ ጽድቅ ካልሆነው ሁሉ መንጻት አለበት፤

፲፱ የተፈጠረበትን አላማ ካሟላ በኋላ፣ [ሀ]በክብር፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር አብም ፊት፣ ይነግሳል፤

፳ የሰለስቲያል መንግስት የሆኑት አካላት ለዘለአለም [ሀ]የራሳቸው ያደርጉት ዘንድ ነው፤ ለዚህም [ለ]ምክንያት ተሰርቷል እና ተፈጥሯል፣ እናም ለዚህም ምክንያት [ሐ]ተቀድሷል።

፳፩ እናም በምሰጣችሁ ህግ፣ እንዲሁም በክርስቶስ ህግ፣ በኩል የማይቀደሱት፣ ሌላ መንግስትን፣ እንዲሁም የተረስትሪያል መንግስትን ወይም የቲለስቲያል መንግስትን፣ መውረስ አለባቸው።

፳፪ በሰለስቲያል መንግስት [ሀ]ህግ መፅናት የማይችለው በሰለስቲያል ክብር መፅናት አይችልምና።

፳፫ እና በተረስትሪያል መንግስት ህግ መፅናት የማይችለውም [ሀ]በተረስትሪያል ክብር መፅናት አይችልም።

፳፬ እና በቲለስቲያል መንግስት ህግ መፅናት የማይችለውም [ሀ]በቲለስቲያል ክብር መፅናት አይችልም፤ ስለዚህ ለመንግስት ክብር ብቁ አይደለም። ስለዚህ የክብር መንግስት ባልሆነ መንግስት ውስጥ መፅናት አለበት።

፳፭ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]ምድር በሰለስቲያል መንግስት ህግ ትጸናለች፣ የፍጥረቷን አላማ ታሟላለችና፣ እናም ህግጋትን አትተላለፍምና—

፳፮ ስለዚህ፣ [ሀ]ትቀደሳለች፤ አዎን፣ ምንም እንኳን [ለ]የምትሞትም ቢሆን፣ ዳግም

፲ ሀ ሙሴ ፪፥፭።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፲፪ ሀ ኤር. ፳፫፥፳፬።
ለ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
፲፫ ሀ ቆላ. ፩፥፲፮–፲፯።
ለ ዘዳግ. ፴፥፳፤ ት. እና ቃ. ፲፥፸።
ሐ ኢዮብ ፴፰፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፴፮–፴፰። ቅ.መ.መ. ህግ።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ፤ የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣ የኃጢያት ክፍያ።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ፤ ሰው፣ ሰዎች—ሰው፣ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ።
ለ ቅ.መ.መ. ሰውነት።
ሐ ዘፍጥ. ፪፥፯። ቅ.መ.መ. ነፍስ።
፲፮ ሀ አልማ ፲፩፥፵፪። ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ።
ለ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፥፯–፱።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳።
ለ ሙሴ ፩፥፴፱። ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
ሐ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፭።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ተረስትሪያል ክብር።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቲለስቲያል ክብር።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ምድር።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።
ለ ቅ.መ.መ. አለም—የአለም መጨረሻ።

ህይወት ይሰጣታል፣ እናም ህይወት በተሰጠባት ሀይልም ትጸናለች፣ እናም [ሐ]ጻድቃንም [መ]ይወርሷታል።

፳፯ ምንም እንኳን ቢሞቱም፣ ዳግም እንደ [ሀ]መንፈሳዊ ሰውነት [ለ]ይነሳሉ።

፳፰ ሰለስቲያል መንፈስ የሆኑትም ፍጥረታዊ ሰውነት የሆነውን አንድ አይነት ሰውነት ይቀበላሉ፤ እንዲሁም ሰውነታችሁን ትቀበላላችሁ፣ እናም [ሀ]ክብራችሁም ሰውነታችሁ [ለ]ህይወት የተሰጠበት ያ ክብር ይሆናል።

፳፱ [ሀ]በሰለስቲያል ክብር ህይወት ከፊሉ የተሰጣችሁም፣ እንዲሁም ደግሞ ሙሉነትን፣ ትቀበላላችሁ።

፴ እናም [ሀ]በተረስትሪያል ክብር ክፍል ህይወት የተሰጣቸውም አንድ አይነት፣ እንዲሁም ሙሉነትን፣ ይቀበላሉ።

፴፩ እናም [ሀ]በቲለስቲያል ክብር ክፍል ህይወት የተሰጣቸውም አንድ አይነት፣ እንዲሁም ሙሉነትን፣ ይቀበላሉ።

፴፪ እናም የቀሩ ሰዎችም [ሀ]ህይወት ይሰጣቸዋል፤ ይህም ቢሆን፣ ሊያገኟቸው የሚችሉትን ለመቀበል [ለ]ፈቃደኛ ስላልነበሩ፣ ለመቀበል ፈቃደኛ በሆኑት ለመደሰት ወደስፍራቸው ዳግም ይመለሳሉ።

፴፫ ለሰው ስጦታ ቢሰጠው እና ስጦታውን ባይቀበለው ምን ይጠቅመዋል? እነሆ፣ በተሰጠው አይደሰትም፣ ወይም በስጦታ ሰጪውም አይደሰትም።

፴፬ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በህግ የሚመራው በህግ ይጠበቃል እና በዚህ ፍጹም ይሆናልም [ሀ]ይቀደሳልም።

፴፭ [ሀ]ህግን የሚሰብርና በህግ የማይጸናው፣ በራሱ ህግ ለመሆን የሚፈልገው፣ እና በኃጢአት ለመፅናት ፈቃደኛ የሆነው፣ እና ሁሉ በኃጢአት የሚጸናው ግን በህግ ወይም [ለ]በምህረት፣ [ሐ]በፍትህ፣ ወይም በፍርድ ሊቀደስ አይችልም። ስለዚህ፣ [መ]ረክሰው መቅረት አለባቸው።

፴፮ ሁሉም መንግስታት የተሰጣቸው ህግ አላቸው፤

፴፯ እናም ብዙ [ሀ]መንግስታት አሉ፤ መንግስት የሌለበት ምንም ስፍራ የለም፤ እና፣ ታላቁ ወይም ታናሹ መንግስት፣ ስፍራ የሌለው ምንም መንግስት የለም።

፴፰ እናም ለእያንዳንዱም መንግስት [ሀ]ህግ ተሰጥቷል፤ እና ለእያንዳንዱም ህግ ልዩ ገደብና አካሄድ አላቸው።

፴፱ በእነዚህ [ሀ]አካሄዶች [ለ]የማይጸኑትም ከጥፋት ነጻ አይሉም።

፵ [ሀ]የመረዳት ችሎታ ከመረዳት ችሎታ ጋር ይጣበቃል፤ [ለ]ጥበብም ጥበብን ይቀበላል፤ [ሐ]እውነት እውነትን ያቅፋል፣ [መ]በጎነት በጎነትን ያፈቅራል፤ [ሠ]ብርሀን ከብርሀን ጋር ይጣበቃል፤ ምህረት በምህረት ላይ [ረ]ርህራሄ አላት እና የራሷንም ታደርገዋለች፤ ፍትህ መንገዱን ይቀጥላል እናም የራሱንም ይወስዳል፤ ፍርድም በዙፋን ላይ በሚቀመጠውና ሁሉንም ነገሮች በሚመራውና በሚያከናውነው ፊት ይሄዳል።

፳፮ሐ ፪ ጴጥ. ፫፥፲፩–፲፬።
ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
መ ማቴ. ፭፥፭፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፶፰፤
፶፱፥፪፤ ፷፫፥፵፱።
፳፯ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፵፬።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፳፰ሀ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
ለ ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፪፤
፷፫፥፶፩፤ ፻፩፥፴፩።
፳፱ሀ ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—
የሰው እንደ እግዚአብሔር
አይነት ለመሆን ያለው
ችሎታ፤
የሰለስቲያል ክብር።
፴ሀ ቅ.መ.መ. ተረስትሪያል
ክብር።
፴፩ሀ ቅ.መ.መ. ቲለስቲያል ክብር።
፴፪ሀ አልማ ፲፩፥፵፩–፵፭።
ለ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
፴፬ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፴፭ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
ሐ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
መ ራዕ. ፳፪፥፲፩፤
፩ ኔፊ ፲፭፥፴፫–፴፭፤
፪ ኔፊ ፱፥፲፮፤
አልማ ፯፥፳፩።
፴፯ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፲፭።
፴፰ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፲፫።
፴፱ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፥፳–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ማፅደቅ፣
ከበደል ነጻ መሆን።
፵ሀ ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣
እውቀተኛዎች።
ለ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ሐ ቅ.መ.መ. እውነት።
መ ቅ.መ.መ. በጎነት።
ሠ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
ረ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።

፵፩ ሁሉንም ነገሮች [ሀ]ይረዳል፣ እና ሁሉም ነገሮች በፊቱ ናቸው፣ እና ሁሉም ነገሮች በዙሪያው ናቸው፤ እና በሁሉም ነገሮች ላይ፣ በሁሉም ነገሮች ውስጥ ነው፣ እና በሁሉም ነገሮች ከዳር እስከ ዳር ነው፤ እና ሁሉም ነገሮች በእርሱ፣ እና በእርሱ በኩል፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር፣ ለዘለአለም ናቸው።

፵፪ እና ዳግም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለሁሉም ነገሮች [ሀ]በጊዜአቸው እና በወቅታቸው የሚሄዱበት ህግ ሰጥቷል፤

፵፫ እናም መንገዶቻቸውም፣ እንዲሁም ምድርን እና ፕላኔቶችን የሚያካትቱት የሰማያት እና የምድር መንገዶች፣ የተወሰኑ ናቸው።

፵፬ እናም በጊዜአቸው እና በወቅታቸውም፣ በደቂቃዎቻቸው፣ በሰአቶቻቸው፣ በቀናቶቻቸው፣ በሳምንቶቻቸው፣ በወራቶቻቸው፣ በአመቶቻቸው እርስ በራስ [ሀ]ብርሀን ይሰጣሉ—እነዚህም ሁሉ ለእግዚአብሔር [ለ]አንድ አመት ናቸው፣ ነገር ግን ለሰው አይደሉም።

፵፭ ምድር በክንፎቿ ትሽከረከራለች፣ እናም [ሀ]ጸሀይ ብርሀኑን በቀን ይሰጣል፣ እና ጨረቃም ብርሀኗን በማታ ትሰጣለች፣ እና ከዋክብትም፣ በእግዚአብሔር [ለ]ሀይል መካከል በክብር በክንፎቻቸው ሲሽከረከሩ፣ ብርሀናቸውን ይሰጣሉ።

፵፮ እንዲገባችሁ፣ እነዚህን መንግስታት ከምን ጋር ላመሳስል?

፵፯ እነሆ፣ እነዚህ ሁሉ መንግስታት ናቸው፣ እናም ማንኛውን ወይም ከእነዚህ ታናሾችን ያየ ማንም ሰው እግዚአብሔር በሞገሱ እና በክብሩ ሲሄድ [ሀ]አይቶታል።

፵፰ እላችኋለሁ፣ እርሱ አይቶታል፤ ይህም ቢሆን፣ [ሀ]የራሱ ወደ ሆኑት የመጣውንም አልተቀበሉትም።

፵፱ [ሀ]ብርሀንም በጭለማ ያበራል፣ እና በጨለማም ያሉት አይረዱትም፤ ይህም ቢሆን፣ በእርሱ ውስጥ እና በእርሱ ህይወት ተሰጥቷችሁ እግዚአብሔርን [ለ]የምትረዱበት ቀን ይመጣል።

፶ ከዚያም እንዳያችሁኝ፣ እንደሆንኩኝ፣ እና በውስጣችሁ ያለሁት የእውነት ብርሀን እንደሆንኩኝ፣ እና እናንተም በእኔ ውስጥ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ፤ አለበለዚያም ውጤታማ አትሆኑም።

፶፩ እነሆ፣ እነዚህን መንግስታት እርሻ ባለው ሰው አመሳስላቸዋለሁ፣ እናም አገልጋዮቹ እርሻውን ይቆፍሩ ዘንድ ወደ እርሻው ላካቸው።

፶፪ እና ለመጀመሪያው እንዲህ ይላል፥ ሂድ እና በእርሻው ስራ፣ እና በመጀመሪያው ሰዓት ወደአንተ እመጣለሁ፣ እና የፊቴ ደስታን ታያለህ።

፶፫ እና ለሁለተኛውም እንዲህ ይላል፥ አንተ ደግመህ ወደ እርሻው ሂድ፣ እና በሁለተኛው ሰዓት በፊቴ ደስታ እጎበኝሀለሁ።

፶፬ እና ደግሞም ለሶስተኛውም አለ፥ እጎበኝሀለሁ።

፶፭ እና ለአራተኛውም፣ እና ቀጥሎም ለአስራ ሁለቱ።

፶፮ በመጀመሪያው ሰዓት የእርሻው ጌታ ወደ መጀመሪያው ሄደ፣ እና በዚያ ሰዓት ሁሉ ከእርሱ ጋር ቆየ፣ እና እርሱም በጌታው ፊት ብርሀን ተደሰተ።

፶፯ እና ከዚያም ሁለተኛውን፣ እና ሶስተኛውን፣ እና አራተኛውን፣ እና እስከ አስራ ሁለተኛው ድረስ ደግሞ ለመጎብኘት ከመጀመሪያው ተለይቶ ሄደ።

፵፩ ሀ ፩ ዮሐ. ፫፥፳፤
፩ ኔፊ ፱፥፮፤
፪ ኔፊ ፱፥፳፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፩–፫።
ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
፵፪ ሀ ዳን. ፪፥፳–፳፪፤
አብር. ፫፥፬–፲፱።
፵፬ ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
ለ መዝ. ፺፥፬፤
፪ ጴጥ. ፫፥፰።
፵፭ ሀ ዘፍጥ. ፩፥፲፮፤
አብር. ፬፥፲፮።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፯–፲፫።
፵፯ ሀ አልማ ፴፥፵፬፤
ሙሴ ፩፥፳፯–፳፰፤ ፮፥፷፫፤
አብር. ፫፥፳፩።
፵፰ ሀ ዮሐ. ፩፥፲፩፤
፫ ኔፊ ፱፥፲፮፤
ት. እና ቃ. ፴፱፥፩–፬።
፵፱ ሀ ት. እና ቃ. ፮፥፳፩፤
፶፥፳፫–፳፬፤ ፹፬፥፵፭–፵፯።
ለ ዮሐ. ፲፯፥፫፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፩፣ ፳፰።

፶፰ እንደዚሁ ሁሉም፣ እያንዳንዱ በሰዓቱ፣ እና በጊዜው፣ እና በወቅቱ፣ የጌታቸውን ፊት ብርሀን ተቀበሉ—

፶፱ ከመጀመሪያው ጀምሮ፣ እና [ሀ]እስከ መጨረሻው በመቀጠል፣ እና ከመጨረሻው እስከመጀመሪያው፣ እና ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው እንዲህ ተቀበሉ፤

፷ ጌታው በእርሱ እና እርሱም በጌታው፣ ይከብር ዘንድ፣ ሁሉም ይከብሩ ዘንድ፣ እያንዳንዱም ሰው ሰዓቱ እስኪያልቅ ድረስ፣ እንዲሁም ጌታው እንዳዘዘው እንዲሁ ተቀበለ።

፷፩ ስለዚህ፣ በዚህ ምሳሌ እነዚህን መንግስታት፣ እና [ሀ]የሚኖሩባቸውን፣ እንዲሁም በሰአቱ፣ እና በጊዜው፣ እና በወቅቱ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ባወጀው ያሉትን እያንዳንዱ መንግስት እመስላለሁ።

፷፪ እና ዳግም፣ [ሀ]ባልንጀሮቼ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በቅርብ እያለሁ [ለ]እንድትጠሩኝ ዘንድ፣ ከምሰጣችሁ ከዚህ ትእዛዝ ጋር፣ እነዚህን አባባሎች በልባችሁ [ሐ]እንድታሰላስሏቸው እተውላችኋለሁ—

፷፫ ወደ እኔ [ሀ]ቅረቡ እና እኔም ወደ እናንተ እቀርባለሁ፤ ተግታችሁም [ለ]ፈልጉኝ እናም [ሐ]ታገኙኛላችሁ፤ ለምኑ፣ እናም ይሰጣችኋል፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል።

፷፬ ለእናንተ [ሀ]አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ነገር በስሜ አብን [ለ]ብትለምኑ፣ ይሰጣችኋል።

፷፭ እናም ለእናንተ [ሀ]አስፈላጊ ያልሆነውን ብትጠይቁ፣ ወደ [ለ]ኩነኔም ይቀየርባችኋል።

፷፮ እነሆ፣ የምትሰሙት በምድረበዳ እንደሚጮኽ ሰው [ሀ]ድምፅ ነው—በምድረበዳ፣ ምክንያቱም ልታዩት አትችሉምና—ድምጼ፣ ምክንያቱም ድምጼ [ለ]መንፈስ ነውና፤ መንፈሴም እውነት ነው፤ [ሐ]እውነትም ይጸናልና መጨረሻም የለውም፤ እና በእናንተ ቢሆንም ይበዛል።

፷፯ እና ወደ [ሀ]ክብሬ ዐይኖቻችሁ [ለ]ቢያተኩሩ፣ ሰውነታችሁ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፣ እና በእናንተም ምንም ጭለማ አይኖርም፤ እና ብሩህ የሆነ ሰውነትም ሁሉንም ነገሮች [ሐ]ይረዳል።

፷፰ ስለዚህ፣ [ሀ]አዕምሮዎቻችሁ ለእግዚአብሔር የቀኑ እንዲሆኑ ራሳችሁን [ለ]ቀድሱ፣ እናም እርሱን [ሐ]የምታዩበት ቀን ይመጣል፤ ፊቱን ለእናንተ ይገልጣልና፣ እና ይህም በራሱ ጊዜና፣ በራሱ መንገድ፣ እናም እንደ ፈቃዱ ይሆናል።

፷፱ የሰጠኋችሁን ታላቅ እና የመጨረሻ ቃል ኪዳን አስታውሱ፤ [ሀ]ከንቱ ሀሳቦቻችሁንና ከልክ በላይ የሆኑ [ለ]ሳቆችን ከእናንተ አስወግዱ።

፸ ቆዩ፣ በዚህም ስፍራ ቆዩ፣ እና የክብር ስብሰባን፣ እንዲሁም በእዚህ በመጨረሻው መንግስት የመጀመሪያ አገልጋዮች የሆኑትን፣ ጥሩ።

፸፩ እናም ያስጠነቀቋቸውም በጉዞአቸው ጌታን ይጥሩ፣ እና ለጥቂት ወቅትም የተ

፶፱ ሀ ማቴ. ፳፥፩–፲፮።

፷፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፮፥፳፬።

፷፪ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፷፫፤ ፺፫፥፵፭።
ለ ኢሳ. ፶፭፥፮፤ ያዕ. ፩፥፭፤ ት. እና ቃ. ፵፮፥፯።
ሐ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።

፷፫ ሀ ዘካ. ፩፥፫፤ ያዕ. ፬፥፰፤ ራዕ. ፫፥፳።
ለ ፩ ዜና ፳፰፥፱፤ ኤተር ፲፪፥፵፩፤ ት. እና ቃ. ፻፩፥፴፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፬፥፯፤ ፵፱፥፳፮።

፷፬ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥፲፰፤ ፵፮፥፳፰–፴።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።

፷፭ ሀ ያዕ. ፬፥፫።
ለ ት. እና ቃ. ፷፫፥፯–፲፩።

፷፮ ሀ ኢሳ. ፵፥፫፤ ፩ ኔፊ ፲፯፥፲፫፤ አልማ ፭፥፴፯–፴፰፤ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፳።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ሐ ቅ.መ.መ. እውነት።

፷፯ ሀ ዮሐ. ፯፥፲፰።
ለ ማቴ. ፮፥፳፪፤ ሉቃ. ፲፩፥፴፬–፴፮፤ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፱።
ሐ ምሳ. ፳፫፥፯፤ ት. እና ቃ. ፺፫፥፳፰።
ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።

፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. አዕምሮ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ት. እና ቃ. ፷፯፥፲–፲፫፤ ፺፫፥፩፤ ፺፯፥፲፭–፲፯።

፷፱ ሀ ማቴ. ፲፪፥፴፮፤ ሞዛያ ፬፥፳፱–፴፤ አልማ ፲፪፥፲፬።
ለ ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፭፤ ፹፰፥፻፳፩።

ቀበሉትን [ሀ]ማስጠንቀቂያ በልቦቻቸው ያሰላስሉ።

፸፪ እነሆ፣ እናም አስተውሉ፣ መንጋዎቻችሁን እንከባከባለሁ፣ እና ሽማግሌዎችን አስነሳለሁ እና ወደ እነርሱም እልካለሁ።

፸፫ እነሆ፣ ስራዬን በራሱ ጊዜ አፈጥናለሁ።

፸፬ እናም የዚህ የመጨረሻ መንግስት የመጀመሪያ [ሀ]አገልጋዮች ለሆናችሁ፣ አብራችሁ እንድትሰበሰቡ፣ እና ራሳችሁን እንድታደራጁ፣ እና ራሳችሁን እንድታዘጋጁ፣ እና ራሳችሁን [ለ]ትቀድሱ ዘንድ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ አዎን፣ [ሐ]አነጻችሁም ዘንድ ልባችሁን አንጹ፣ እጆቻችሁን እና እግሮቻችሁንም በፊቴ [መ]የጸዱ ይሁኑ፤

፸፭ ከዚህ ክፉ ትውልድ ደም ንጹህ መሆናችሁን ወደ [ሀ]አባታችሁ፣ አምላካችሁና፣ አምላኬ፣ እመሰክር ዘንድ፤ እንደ ፈቃዴም የገባሁላችሁ ቃል ኪዳን፣ ይህን ታላቅ እና የመጨረሻ ቃል ኪዳን፣ ላሟላ እችል ዘንድ ነው።

፸፮ ደግሞም፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ [ሀ]በጸሎት እና [ለ]በጾም ትበረቱም ዘንድ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፸፯ እናም የመንግስቱን [ሀ]ትምህርት እርስ በርስ [ለ]ትማማሩም ዘንድ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፸፰ በትጋት አስተምሩ እናም፣ [ሀ]ጸጋዬ ከእናንተ ጋር ይሆናል፣ ይህም በፅንሰ ሀሳብ፣ በመሰረታዊ መርሆች፣ በትምህርት፣ በወንጌሉ ህግ፣ ከእግዚአብሔር መንግስት ጋር ግኑኝነት ባላቸው ሁሉም ነገሮች፣ ለእውቀታችሁ አስፈላጊ የሆኑትን ፈጽማችሁ [ለ]እንድትማሩ ዘንድ፤

፸፱ [ሀ]በሰማይና ምድር፣ እናም ከምድር በታች፣ ስላሉትም ነገሮች፤ ስለነበሩት ነገሮች፣ ስለአሉ ነገሮች፣ እና በቅርብም ስለሚሆኑት ነገሮች፤ በቤት ስላሉም ነገሮች፣ በሌሎች ሀገሮች ስላሉትም ነገሮች፤ ስለህዝብ [ለ]ጦርነቶች እና አወዛጋቢ ጉዳዮች፣ እና በምድር ላይ ስላሉት ፍርዶች፤ እና የሀገራት እና የመንግስታትም እውቀቶች በፍጹም እንድትማሩ ዘንድ፣ ጸጋዬ ከእናንተ ጋር ይሆናል—

፹ በተጠራችሁበት ጥሪ፣ እና በልዩ ሀላፊነት በሰጠኋችሁ ተልዕኮ፣ ጥሪዎቻችሁን እንድታጎሉ በምልካችሁ ጊዜ በሁሉም ነገሮች ትዘጋጁ ዘንድ ጸጋዬ ከእናንተ ጋር ይሆናል።

፹፩ እነሆ፣ የላኳችሁ [ሀ]እንድትመሰክሩ እና ሰዎችን [ለ]እንድታስጠነቅቁ ነው፣ እናም የተጠነቀቀው ሰው ባልንጀራውን ማስጠንቀቁ አስፈላጊ ነው።

፹፪ ስለዚህ፣ ምክንያትም አይኖራቸውም፣ እና ኃጢአቶቻቸውም በራሳቸው ላይ ናቸው።

፹፫ ከጊዜው [ሀ]ቀድሞ [ለ]የሚፈልገኝም ያገኘኛል፣ እና አይተውም።

፹፬ ስለዚህ ለመጨረሻ ጊዜ [ሀ]በአህዛብ መካከል በመሄድ በአገልግሎታችሁ ፍጹማን ትሆኑ ዘንድ፤ የጌታም አንደበት የጠራቸውን ሁሉ ለማምጣት፤ ህግን [ለ]ለማሰር እና ምስክርንም ለማተም እና ከሚመጣውም የፍርድ ሰአት ቅዱሳንን ታዘጋጁ ዘንድ ቆዩ እናም ተግታችሁም ስሩ።

፸፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ።
፸፬ ሀ ማቴ. ፳፥፩፤ ፲፮።
ለ ዘሌዋ. ፳፥፯–፰፤ ፫ ኔፊ ፲፱፥፳፰–፳፱፤ ት. እና ቃ. ፶፥፳፰–፳፱፤ ፻፴፫፥፷፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ንጹህ እና ርኩስ።
መ ኤተር ፲፪፥፴፯።
፸፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—ሰው፣ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ፤ እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ፤ የሰማይ አባት።
፸፮ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
፸፯ ሀ ቅ.መ.መ. የክርስቶስ ትምህርት።
ለ ቅ.መ.መ. ማስተማር፣ አስተማሪ።
፸፰ ሀ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፰፤ ፺፥፲፭፤ ፺፫፥፶፫።
፸፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሰማይ።
ለ ቅ.መ.መ. ጦርነት።
፹፩ ሀ ቅ.መ.መ. መመስከር።
ለ ት. እና ቃ. ፴፰፥፵፩። ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ።
፹፫ ሀ አልማ ፴፯፥፴፭።
ለ ዘዳግ. ፬፥፳፱–፴፩፤ ኤር. ፳፱፥፲፪–፲፬፤ ት. እና ቃ. ፶፬፥፲።
፹፬ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፵፩።
ለ ኢሳ. ፰፥፲፮–፲፯።

፹፭ ነፍሳቸውም በዚህም ሆነ በሚመጣው አለም ክፉዎችን የሚጠብቀውን፣ [ሀ]የርኩሰጥ ጥፋት የሆነውን፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ያመልጥ ዘንድ ቅዱሳንን ታዘጋጁ ዘንድ ቆዩ እናም ተግታችሁም ስሩ። እውነት እላችኋለሁ የጌታ አንደበት [ለ]እስኪጠራቸው ድረስ የመጀመሪያ ያልሆኑት ሽማግሌዎች በወይኑ ስፍራ መስራታቸውን ይቀጥሉ፤ ሰአታቸው ገና አልደረሰምና፤ ልብሶቻቸውም ከዚህ ትውልድ ደም [ሐ]የነጹ አይደሉም።

፹፮ [ሀ]ነጻ ሆናችሁ በተፈጠራችሁበትም [ለ]አርነት ጸንታችሁ ቁሙ፤ [ሐ]በኃጢአትም ራሳችሁን [መ]አትጥመዱ፣ ነገር ግን፣ ጌታ እስከሚመጣ ድረስ፣ እጆቻችሁን [ሠ]እንዲጸዱ አድርጉ።

፹፯ ለብዙ ቀናት ሳይቆይ እና [ሀ]ምድርም እንደሰካራም ሰው [ለ]ትፍገመገማለች እና ወዲህና ወዲያ ትናወጣለች፣ እና [ሐ]ጸሀይም ፊቷን ትሰውራለች፣ ብርሀኗንም ትከለክላለች፤ እና ጨረቃም [መ]በደም ትርሳለች፤ እና [ሠ]ከዋክብትም እጅግ ይቆጣሉ፣ እናም የበለስ ፍሬ ከበለስ እንደሚወድቅም ራሳቸውን ይጥላሉ።

፹፰ እና ከምስክርነታችሁ በኋላ በህዝብ ላይ ንዴት እና ቁጣ ይመጣል።

፹፱ ከምስክርነታችሁ በኋላ፣ በመካከሏ ሁከት የሚያመጣ የምድር [ሀ]መናወጥ ምስክርነት ይመጣል፣ እና ሰዎችም ወደ ምድር ይወድቃሉ እናም ለመነሳትም ይሳናቸዋል።

፺ እና ደግሞም የነጎድጓድ፣ እና የመብረቅ [ሀ]ድምፅ፣ እና የማእበል ድምፅ፣ እና ከገደባቸው በላይ ራሳቸውን በሚወረውሩ የባህር ማዕበል ድምፅ ምስክርነት ይመጣል።

፺፩ እና ሁሉም ነገሮች [ሀ]በሁከት ውስጥ ይሆናሉ፣ እና በእርግጥም፣ የሰዎች ልብ በፍርሀት ይደክማል፤ ፍርሀት በሁሉም ሰዎች ላይ ይመጣልና።

፺፪ እናም፣ ተዘጋጁ፣ ተዘጋጁ፣ በምድር የምትኖሩ ሆይ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ መጥቷልና። እነሆ፣ እና አስተውሉ፣ [ሀ]ሙሽራው መጥቷል፤ ከእርሱ ጋር ለመገናኘትም ውጡ በማለት፣ በከፍተኛ ድምፅ በመጮህ፣ የእግዚአብሔርን መለከት በመንፋት፣ [ለ]መላዕክትም በሰማይ መካከል ይበራሉ።

፺፫ እና ወዲያውም በሰማይ [ሀ]ታላቅ ምልክት ይታያል፣ እናም ሁሉም ሰዎች አብረው ያዩታል።

፺፬ እና ሌላም መልአክ መለከቱን እንዲህ በማለት ይነፋል፥ ህዝብን ሁሉ [ሀ]የዝሙቷን ቁጣ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ ያደረገችው፣ የእግዚአብሔን ቅዱሳን የምታሳድድ፣ ደማቸውን የምታፈስ—በብዙ ውሀዎች እና በባህር ደሴቶች ላይ የተቀመጠችው—ያቺ [ለ]ታላቅ [ሐ]ቤተክርስቲያን፣ የርኩሰት [መ]እናት፣ እነሆ፣ የምድር [ሠ]እንክርዳድ እርሷ ነች፤ አንድ ላይ ታስራለች፤ እስሯም ተጠናክሯል፣ እና ማንም ሰው ሊፈታው አይችልም፤ ስለዚህ፣ [ረ]ለመንደድ ተዘጋ

፹፭ ሀ ማቴ. ፳፬፥፲፭።
ለ ት. እና ቃ. ፲፩፥፲፭።
ሐ ፩ ኔፊ ፲፪፥፲–፲፩፤
ያዕቆ. ፩፥፲፱፤ ፪፥፪፤
ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፴፫።
ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፹፮ ሀ ሞዛያ ፭፥፰።
ቅ.መ.መ. መብት።
ለ ዮሐ. ፰፥፴፮።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ፤
ነጻ፣ ነጻነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
መ ገላ. ፭፥፩።
ሠ ኢዮብ ፲፯፥፱፤ መዝ. ፳፬፥፬፤
አልማ ፭፥፲፱።
፹፯ ሀ ኢሳ. ፲፫፥፬–፲፫።
ለ ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፰።
ሐ ኢዩ. ፪፥፲፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፵፪፤
፻፴፫፥፵፱።
መ ራዕ. ፮፥፲፪።
ሠ ኢዩ. ፫፥፲፭።
፹፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፫፥፳፭።
፺ ሀ ራዕ. ፰፥፭፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፯–፳፭።
፺፩ ሀ ት. እና ቃ. ፵፭፥፳፮።
፺፪ ሀ ማቴ. ፳፭፥፩–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፴፫፥፲፯፤
፻፴፫፥፲፣ ፲፱።
ለ ራዕ. ፰፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፲፯።
፺፫ ሀ ማቴ. ፳፬፥፴፤
ሉቃ. ፳፩፥፳፭–፳፯።
ቅ.መ.መ. የጊዜዎች
ምልክቶች።
፺፬ ሀ ራዕ. ፲፬፥፰።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፬–፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ—
የዲያብሎስ ቤተክርስቲያን።
መ ራዕ. ፲፯፥፭።
ሠ ማቴ. ፲፫፥፴፰።
ረ ት. እና ቃ. ፷፬፥፳፫–፳፬፤
፻፩፥፷፭–፷፮።
ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።

ጅታለች። እና መለከቱም ረጅም እና ጉልህ ይሆናል፣ እና ሁሉም ህዝብ ይሰሙታል።

፺፭ እና በሰማይም ለግማሽ ሰአት ያህል [ሀ]ጸጥታ ይሆናል፤ እና ወዲያውም፣ መጽሐፍ [ለ]ጥቅልል ከተጠቀለለ በኋላ እንደሚዘረጋ፣ የሰማይ መጋረጃዎች ይዘረጋሉ፣ እናም የጌታ [ሐ]ፊትም ይገለጣል፤

፺፮ እና በህይወት በምድር ላይ ያሉት ቅዱሳን በቅፅበት ይለወጣሉ እና እርሱን ያገኙት ዘንድም [ሀ]ይነጠቃሉ።

፺፯ እና በየመቃብራቸው ያንቀላፉትም [ሀ]ይነሳሉ፣ መቃብሮቻቸውም ይከፈታሉና፤ እና እነርሱ ደግመውም በሰማይ አምድ መካከል እርሱን ለመቀበል ይነጠቃሉ—

፺፰ መጀመሪያ ከእርሱ ጋር የሚወርዱት፣ እና በምድርና በመቃብራቸው ያሉት፣ እርሱን ለመቀበል የተነጠቁት፣ እነርሱም የክርስቶስ፣ [ሀ]የመጀመሪያ ፍሬዎች፣ ናቸው፤ እና ይህም ሁሉ የሚሆነው የእግዚአብሔር መልአክ መለከት ድምፅ ሲሰማ ነው።

፺፱ ከዚህ በኋላም ሌላ መልአክ፣ ሁለተኛው መለከት፣ ያሰማል፤ ከዚያም፣ ወንጌልን ለመቀበልና እንደሰዎች በሥጋ [ሀ]ይፈረድባቸው ዘንድ፣ [ለ]በወህኒ ለእነርሱ የተዘጋጀውን ድርሻቸውን የተቀበሉት፣ በመምጫው ጊዜ የክርስቶስ የሆኑት ቤዛነትም ይመጣል።

፻ ደግሞም፣ ሶስተኛው መለከት የሆነው ሌላ መለከት ይነፋል፤ ከዚያም የሚፈረድባቸውና [ሀ]በኩነኔ የሚገኙት ሰዎች [ለ]ነፍሳት ይመጣሉ፤

፻፩ እነዚህም የቀሩት [ሀ]ሙታን ናቸው፤ እና ይህ [ለ]ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፣ ያም እስከምድር ፍጻሜም ድረስ፣ በሕይወት አይኖሩም።

፻፪ እና አራተኛው መለከት የሆነው ሌላ መለከትም እንዲህ በማለት ይነፋል፥ እስከታላቅ እና መጨረሻው ዘመን፣ እንዲሁም እስከፍጻሜው፣ ድረስ ከሚቀሩት መካከል [ሀ]ቆሸሸው የሚቀሩ አሉ።

፻፫ እና አምስተኛው መለከት የሆነው፣ [ሀ]ዘለአለማዊውን ወንጌል በሰማይ መካከል በመብረር ለሀገር ለነገድ ለቋንቋ ለህዝብ የሚሰብከው አምስተኛው መልአክ፣ ሌላውን መለከት ይነፋል፤

፻፬ ይህም፣ ለህዝብ ሁሉ በማለት፣ የመለከቱ ድምፅ ይሆናል፣ በሰማይና በምድር፣ እና ከምድር በታች ላሉት—[ሀ]ሁሉም ጆሮዎች ይሰሙታልና፣ እና የመለከቱንም ድምፅ እንዲህ ሲል ሲሰሙም፣ ጉልበት ሁሉ [ለ]ይንበረከካል ምላስም ሁሉ ይናዘዛል፥ እግዚአብሔርን [ሐ]ፍሩ፣ እና በዙፋኑ ላይ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ለሚቀመጠው ክብሩን ስጡ፤ የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና።

፻፭ እና ደግሞም፣ ስድስተኛው መልአክ የሆነው ሌላ መልአክም መለከቱን እንዲህ በማለት ይነፋል፥ ህዝብን ሁሉ የዝሙቷን ቁጣ ወይን ጠጅ እንዲጠጡ ያደረገችው [ሀ]ወድቃለች፤ ወድቃለች፣ ወድቃለች!

፻፮ እና ዳግም፣ ሰባተኛው መልአክ የሆነው ሌላ መልአክ መለከቱን እንዲህ በማለት ይነፋል፥ ተፈፅሟል፤ ተፈፅሟል! የእግዚአብሔር [ሀ]በግ [ለ]አሸንፎታል እናም መጥመቂያውን፣ እንዲሁም ሁሉን የሚገዛ የእግዚ

፺፭ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፪።
ለ ራዕ. ፰፥፲፩።
ሐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፺፮ ሀ ፩ ተሰ. ፬፥፲፮–፲፯።
፺፯ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፫፤ ፵፭፥፵፭–፵፮፤ ፻፴፫፥፶፮።
ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፺፰ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፫።
፺፱ ሀ ፩ ጴጥ. ፬፥፮።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፫፤ ፻፴፰፥፰።
ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
፻ ሀ ቅ.መ.መ. መኮነን፣ ኩነኔ።
ለ ራዕ. ፳፥፲፪–፲፫፤ አልማ ፲፩፥፵፩፤ ት. እና ቃ. ፵፫፥፲፰፤ ፸፮፥፹፭።
፻፩ ሀ ራዕ. ፳፥፭።
ለ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፻፪ ሀ ቅ.መ.መ. እድፍ፣ እድፍነት።
፻፫ ሀ ራዕ. ፲፬፥፮–፯።
ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
፻፬ ሀ ራዕ. ፭፥፲፫።
ለ ኢሳ. ፵፭፥፳፫፤ ፊልጵ. ፪፥፱–፲፩።
ሐ ቅ.መ.መ. ማክበር፤ ፍርሀት—እግዚአብሔርን መፍራት።
፻፭ ሀ ራዕ. ፲፬፥፰፤ ት. እና ቃ. ፩፥፲፮።
፻፮ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
ለ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፭።

አብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያን፣ ብቻውን [ሐ]ረግጦታል።

፻፯ ከዚያም መላእክቱ የሀይሉን የክብር አክሊል ይደፋሉ፣ እና [ሀ]ቅዱሳንም [ለ]በክብሩ ይሞላሉ፣ እና [ሐ]ውርሳቸውን ይቀበላሉ እና ከእርሱም ጋር [መ]እኩል ይደረጋሉ።

፻፰ ከዚያም የመጀመሪያው መልአክ መለከቱን ዳግም በሚኖሩት ጆሮዎች ላይ ያሰማል፣ እና የሰዎችን የሚስጥር ስራዎችና [ሀ]በመጀመሪያው ሺህ አመታት የእግዚአብሔርን ታላቅ ስራዎች [ለ]ይገልጣል።

፻፱ ከዚያም ሁለተኛው መልአክ መለከቱን ይነፋል፣ እና የሰዎችን የሚስጥር ስራዎች፣ እና የልባቸውን ሀሳብና ስሜታቸውን፣ እና በሁለተኛው ሺህ አመታት የእግዚአብሔርን ታላቅ ስራዎች ይገልጣል—

፻፲ እናም ሰባተኛው መልአክ መለከቱን እስከሚነፋ ድረስ ይቀጥላል፤ እና በምድር ላይ እና በባህር ላይ ይቆማል፣ እና [ሀ]ዘመንም እንደሚፈጸም በዙፋኑ ላይ በሚቀመጠው ስም ይምላል፤ እና የቀደመውንም እባብ፣ ዲያብሎስ የሚባለው፣ [ለ]ሰይጣንም ይያዛል፣ እና [ሐ]ለአንድ ሺህ ለሚሆን ዘመንም አይፈታም።

፻፲፩ ከዚያም ሰራዊቱን ለመሰብሰብ ይችል ዘንድ ለትንሽ ዘመን [ሀ]ይለቀቃል።

፻፲፪ እና ሰባተኛው መልአክ [ሀ]ሚካኤል፣ እንዲሁም የመላእክት አለቃው፣ ሰራዊቱን፣ እንዲሁም የሰማይ ሰራዊትን፣ ይሰበስባል።

፻፲፫ እና ዲያብሎስም ሰራዊቱን ይሰበስባል፤ እንዲሁም የሲኦል ሰራዊትን፣ እና ከሚካኤልና ከሰራዊቱ ጋር ለመዋጋት ይመጣል።

፻፲፬ ከዚያም የታላቁ እግዚአብሔር [ሀ]ጦርነት ይመጣል፤ እና በቅዱሳን ላይ ከዚህ በኋላ ሀይል እንዳይኖራቸው፣ ዲያብሎስና ሰራዊቱ ወደራሳቸው ስፍራም ይጣላሉ።

፻፲፭ ሚካኤል ጦርነታቸውን ይዋጋላቸዋልና፣ እና በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን፣ እንዲሁም የበጉን፣ ዙፋን [ሀ]የሚፈልገውን ያሸንፋል።

፻፲፮ ይህም የእግዚአብሔርና [ሀ]የተቀደሱት ክብር ነው፤ እና ከዚህም በኋላ [ለ]ሞትን አይቀምሱም።

፻፲፯ ስለዚህ፣ [ሀ]ባልንጀሮቼ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እንዳዘዝኳችሁ የክብር ስብሰባችሁን ጥሩ።

፻፲፰ እና ሁሉም እምነት ስለሌላቸው፣ ተግታችሁ ፈልጉ እና እርስ በርሳችሁም [ሀ]የጥበብ ቃላትን [ለ]ተማማሩ፤ አዎን፣ ከተመረጡት [ሐ]መጽሀፍትም የጥበብን ቃላት ፈልጉ፤ እውቀትን፣ እንዲሁም በጥናትና ደግሞም በእምነት፣ እሹ።

፻፲፱ ራሳችሁን አደራጁ፤ አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ አዘጋጁ፤ [ሀ]ቤትን፣ እንዲሁም የጸሎትን ቤት፣ የጾምን ቤት፣ የእምነትን ቤት፣ የእውቀትን ቤት፣ የክብርን ቤት፣ የስርዓትን ቤት፣ የእግዚአብሔርን ቤት መስርቱ፤

፻፮ሐ ኢሳ. ፷፫፥፫–፬፤
ራዕ. ፲፱፥፲፭፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፯፤
፻፴፫፥፶።
፻፯ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ለ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
ሐ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
መ ት. እና ቃ. ፸፮፥፺፭።
፻፰ሀ ት. እና ቃ. ፸፯፥፮–፯።
ለ አልማ ፴፯፥፳፭፤
ት. እና ቃ. ፩፥፫።
፻፲ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፻።
ለ ራዕ. ፳፥፩–፫፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፳፮፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥፳፰።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሐ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፻፲፩ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፳፪፤
፵፫፥፴–፴፩።
፻፲፪ሀ ቅ.መ.መ. ሚካኤል።
፻፲፬ሀ ራዕ. ፲፮፥፲፬።
፻፲፭ሀ ኢሳ. ፲፬፥፲፪–፲፯፤
ሙሴ ፬፥፩–፬።
፻፲፮ሀ ቅ.መ.መ. ቅድስና፤
ከፍተኛነት።
ለ ራዕ. ፳፩፥፬፤
አልማ ፲፩፥፵፭፤ ፲፪፥፲፰፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥፵፱።
ቅ.መ.መ. የማይሞት፣
አለሚችነት።
፻፲፯ሀ ት. እና ቃ. ፻፱፥፯።
፻፲፰ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፯–፹።
ቅ.መ.መ. ማስተማር፣
አስተማሪ።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፭፥፬፤
፻፱፥፯፣ ፲፬።
፻፲፱ሀ ት. እና ቃ. ፺፭፥፫፤
፺፯፥፲–፲፯፤ ፻፱፥፪–፱፤
፻፲፭፥፰።
ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።

፻፳ በእዚህም መግባታችሁ በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፤ መውጣታችሁም በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፤ ሰላምታችሁም፣ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጆቻችሁን በማንሳት፣ በጌታ ስም ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ቤት መስርቱ።

፻፳፩ ስለዚህ፣ ጥቅም የሌለውን ንግግራችሁን ሁሉ፣ [ሀ]ሳቆችን ሁሉ፣ [ለ]ከፍተኛ ፍላጎታችሁን ሁሉ፣ [ሐ]ኩራታችሁን እና ተራ አስተሳሰባችሁን ሁሉ፣ እና ክፉ ድርጊታችሁን ሁሉ [መ]አቁሙ።

፻፳፪ ከመካከላችሁም መምህር መድቡ፣ እና ሁሉም ታናጋሪ እንዲሆኑ አታድርጉ፤ ነገር ግን፣ ሁሉም ሲናገሩ ሁሉም ይታነጹ ዘንድ፣ እና እያንዳንዱም ሰው እኩል ባለመብት ይሆን ዘንድ፣ አንድ በአንድ በተራ እንዲናገር አድርጉ እና ሁሉም የሚነገረውን እንዲሰሙ አድርጉ።

፻፳፫ እርስ በርሳችሁ [ሀ]መዋደዳችሁን አረጋግጡ፤ [ለ]ትምክህተኞች አትሁኑ፤ በወንጌሉ አስፈላጊ እንደሆነም እርስ በርስ መካፈልን ተማሩ።

፻፳፬ [ሀ]ስራ ፈት መሆንን አቁሙ፤ እርኩስ መሆንንም አቁሙ፤ እርስ በራስ [ለ]ስህተት መፈለግን አቁሙ፤ አስፈላጊ ከሆነው በላይ መተኛትንም አቁሙ፤ እንዳትደክሙ፣ ወደመኝታችሁ በጊዜ ሂዱ፤ ሰውነቶቻችሁ እና አዕምሮዎቻችሁ ይነቃቁ ዘንድም በማለዳ ተነሱ።

፻፳፭ እና ከሁሉም በላይ፣ የፍጹምነትና [ሀ]የሰላም ማሰሪያ የሆነውን [ለ]ልግስና፣ እንደ ካባ፣ ልበሱት።

፻፳፮ [ሀ]እስከምመጣም ድረስ ሳትታክቱ ዘንድ፣ ዘወትር [ለ]ጸልዩ። እነሆ እናም አስተውሉ፣ በቶሎ እመጣለሁ፣ እናም እናንተንም ወደራሴ እወስዳችኋለሁ። አሜን።

፻፳፯ ደግሞም፣ ለነብያቱ [ሀ]ትምህርት ቤት አመራር፣ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን [ለ]ሹማምንቶች ሁሉ፣ ወይም በሌላ ቃል፣ ከሊቀ ካህናት ጀምሮ እስከ ዲያቆን ድረስ በቤተክርስቲያኑ እንዲያገለግሉ ለተጠሩት ተዘጋጅቶ፣ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ እንዲማሩበት የተመሰረተውን ቤት ስርዓት በሚመለከት—

፻፳፰ እናም ይህም የትምህርት ቤቱ አመራር ቤት ስርዓት ይሆናል፥ ፕሬዘደንት ወይም መምህር እንዲሆን የተሾመው በሚዘጋጅለት ቤት ውስጥ በስፍራው ቆሞ ይገኝ።

፻፳፱ ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በኅላ ንግግር ሳይሆን፣ በቤቱ ውስጥ ያሉት ተሰብሳቢዎች ቃላቶቹን በጥንቃቄና በግልፅ በሚሰሙበት ስፍራ መጀመሪያ ይሁን።

፻፴ እና ወደ እግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሲመጣም፣ በቤቱ ውስጥ የመጀመሪያ መሆን ይገባዋልና—እነሆ፣ ይህም ድንቅ ነው፣ ምሳሌም ይሆን ዘንድ—

፻፴፩ የዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ምልክት ወይም ማስታወሻም ይሆን ዘንድ፣ በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት በመንበርከክ እራሱን [ሀ]ያቅርብ።

፻፴፪ እናም ከእርሱ በኋላ ማንም ሲገባ፣ መምህሩ ይነሳ፣ እና ወደሰማይ በተዘረጉ እጆች፣ አዎን፣ እንዲሁም በቀጥታ፣ ወንድሙን ወይም ወንድሞችን በእነዚህ ቃላት ሰላም ይበላቸው፥

፻፴፫ እናንት ወንድም ወይም ወንድሞችናችሁ? በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ በምልክት ወይም በዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ማስታወሻ ሰላም እላችኋለሁ፣ በዚህም ቃል ኪዳን፣ በማይለወጥ፣ በማይነቃነቅ፣ እና በማይቀየር ቁርጥ ውሳኔ፣ በእግዚአብሔር

፻፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፭፤ ፹፰፥፷፱።
ለ ቅ.መ.መ. ስጋዊ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩራት።
መ ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፬፤ ፻፥፯።
፻፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ፍቅር።
ለ ቅ.መ.መ. መመኘት።
፻፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።
ለ ት. እና ቃ. ፷፬፥፰–፲።
ቅ.መ.መ. ክፉ መናገር።
፻፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ለ ቅ.መ.መ. ልግስና።
፻፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
፻፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
ለ ቅ.መ.መ. ሀላፊነት፣ ሀላፊ።
፻፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማምለክ።

ጸጋ በፍቅር እስር ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛት ሁሉ ያለእንከን፣ በምስጋና መስጠት፣ ከዘለአለም እስከዘለአለም ጓደኛች ሁና [ሀ]ወንድማችሁ ለመሆን ወደ [ለ]ማህበርተኛነት እቀበላችኋለሁ። አሜን።

፻፴፬ እናም ለዚህ ሰላምታ ብቁ ሆኖ የማይገኘውም ከመካከላችሁ ምንም ስፍራ አይኑረው፤ ቤቴ በእርሱ [ሀ]እንዲረከስ አትፈቅዱምና።

፻፴፭ እና የሚገባውና በፊቴ ታማኝ የሚሆነው፣ እና ወንድም የሆነው፣ ወይም ወንድሞችም ከሆኑ፣ ወደሰማይ በተዘረጉ እጆች፣ በአንድ አይነት ጸሎት እና ቃል ኪዳን፣ ወይም በአንድ አይነት ምልክት አሜን በማለት ለፕሬዘደንት ወይም ለመምህሩ ሰላምታ ይሰጣሉ።

፻፴፮ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ፣ በነቢያትም ትምህርት ቤት ውስጥ፣ እርስ በርስ ሰላምታ የምትሰጣጡበት ምሳሌ ነው።

፻፴፯ እናም መሸሸጊያ፣ ለምትታነጹበት የመንፈስ ቅዱስ [ሀ]ድንኳን ይሆን ዘንድ፣ በጌታ ቤት፣ እንዲሁም በነቢያት ትምህርት ቤት ውስጥ፣ መንፈስ በሚናገረው በምታደርጉት ሁሉ ጸሎት እና ምስጋና በመስጠት እንድታደርጉ ተጠርታችኋል።

፻፴፰ እና ከዚህ ትውልድ [ሀ]ደም ንጹህ ያልሆነን በመካከላችሁ ማንንም ወደ እዚህ ትምህርት ቤት አትቀበሉ።

፻፴፱ እና እርሱም እግርን [ሀ]ማጠብ በሆነ ስርዓት ተቀበሉት፣ ለዚህም ምክንያት ነበር የእግር ማጠብ ስነስርዓት የተመሰረተው።

፻፵ ደግሞም፣ የእግር ማጠብ ስርዓት የሚከናወነው በፕሬዘደንቱ፣ ወይም በቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች አመራር ነው።

፻፵፩ ይህም የሚጀምረው በጸሎት ነው፤ እና ዳቦው እና ወይኑ [ሀ]ከተሰጠ በኋላ፣ እኔን በሚመለከት በዮሐንስ ምስክር ምዕራፍ አስራ ሶስት ውስጥ በምስክርነት በሰጠው [ለ]ምሳሌ ራሱን ያልብስ። አሜን።

ክፍል ፹፱

በየካቲት ፳፯፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በስብሰባዎቻቸው ጊዜ የቀድሞዎቹ ቅዱሳን ትምባሆ በመጠቀማቸው ምክንያት፣ ነቢዩ ስለጉዳዩ ያሰላስል ዘንድ ተመርቶ ነበር፤ በዚህም ምክንያት፣ ስለጉዳዩ ጌታን ጠየቀ። የጥበብ ቃል ተብሎ የሚታወቀው ይህም ራዕይ የዚህ ውጤት ነበር።

፩–፱፣ የወይን ጠጅ፣ የሚያሰክሩ መጠጦች፣ ትምባሆ፣ እና ትኩስ መጠጦችን መጠቀም ተከልክለዋል፤ ፲–፲፯፣ የመድሀኒት ቅጠላቅጠል፣ ፍራፍሬዎች፣ ስጋ፣ እና እህል ለሰዎች እና ለእንስሳት ጥቅም የተመደቡ ናቸው፤ ፲፰–፳፩፣ ለወንጌሉ ህግ፣ የጥበብ ቃልን በተጨማሪ፣ ታዛዥ መሆን ስጋዊ እና መንፈሳዊ በረከቶችን ያመጣል።

፩ [ሀ]የጥበብ ቃል፣ በከርትላንድ ውስጥ ለተሰበሰቡት ለሊቀ ካህናት ቡድን፣ እና ለቤተክርስቲያኗ፣ እና ደግሞም ለፅዮን ቅዱሳን ጥቅም—

፻፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. እህት፤
ወንድሞች፣ ወንድም።
ለ ቅ.መ.መ. ጓደኝነት።
፻፴፬ ሀ ት. እና ቃ. ፺፯፥፲፭–፲፯፤ ፻፲፥፯–፰።
፻፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፶፥፳፩–፳፬።
፻፴፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፬–፸፭፣ ፹፬–፹፭።
፻፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ማጠብ፣
የታጠበ፣ የሚታጠቡ።
፻፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ ቁርባን።
ለ ዮሐ. ፲፫፥፬–፲፯።
፹፱ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. የጥበብ ቃል።

፪ በትእዛዝ ወይም በማስገደድ ሳይሆን፣ ነገር ግን በራዕይ እና በጥበብ ቃል፣ በመጨረሻዎቹ ቀናት ለቅዱሳን ሁሉ በጊዜያዊ ደህንነት ውስጥ የእግዚአብሔርን ስርዓት እና [ሀ]ፈቃድ በማሳየት እንደ ሰላምታ የሚላክ፤

፫ [ሀ]ከተስፋ ጋር የሆነ መሰረታዊ መርህ፣ ለደካማው እና ቅዱሳን ለሆኑት ወይም ቅዱሳን ተብለው ለተጠሩት ደካማ [ለ]ቅዱሳን ሁሉ ችሎታ ይሆን ዘንድ የተሰጠ የጥበብ ቃል ነው።

፬ እነሆ፣ ጌታ ለእናንተ እንዲህ ይላችኋል፥ በመጨረሻዎቹ ቀናት ውስጥ [ሀ]በሚያድሙ ሰዎች ልብ ውስጥ ባሉት እና በሚኖሩት [ለ]ተንኮል እና አላማዎች ምክንያት፣ በራዕይ ይህን የጥበብ ቃል ለእናንተ በመስጠት አስጠንቅቄአችኋለሁ፣ እናም ጥንቱንም አስቀድሜ [ሐ]አስጠንነቅቄአችኋለሁ

፭ በመካከላችሁ ማንም ሰው [ሀ]ወይን ወይም የሚያሰክር መጠጥ የሚጠጣ ቢሆን፣ በፊቱ ቅዱስ ቁርባናችሁን ታቀርቡ ዘንድ በተሰባሰባችሁበት ጊዜ ብቻ ካልሆነ በስተቀር፣ እነሆ ይህ መልካም አይደለም፣ በአባታችሁም ፊት ተቀባይነት አይኖረውም።

፮ እናም፣ እነሆ፣ ይህም የወይን ጠጅ፣ አዎን፣ ከወይን ፍሬ በራሳችሁ የተሰራ ንጹህ [ሀ]ወይን ይሁን።

፯ ደግሞም፣ [ሀ]የሚያሰክር መጠጥ፣ ሰውነትን ለማጠብ እንጂ፣ ለሆድ አይደለም።

፰ እና ዳግም፣ ትምባሆ [ሀ]ለሰውነት፣ ወይም ለሆድ አይደለም፣ እና ለሰውም መልካም አይደለም፣ ነገር ግን በማመዛዘን እና በጥበብ ቢጠቀሟቸው፣ ለብልዝነት እና ለታመሙ ከብቶች የመድሀኒት ቅጠላት ናቸው።

፱ ደግሞም፣ ትኩስ መጠጦችም ለሰውነት እና ለሆድ አይደሉም።

፲ እናም ደግሞ እውነት እላችኋለሁ፤ ሁሉንም መልካም የሆኑትን [ሀ]ቅጠላ ቅጠል እግዚአብሔር ለሰውነት፤ ለፍጥረት እና ለሰው ጥቅም ይሆኑ ዘንድ መድቧቸዋልና—

፲፩ እያንዳንዶቹን ቅጠላ ቅጠል ሁሉ በወቅታቸው፤ ፍራፍሬዎችም ሁሉ በወቅታቸው መድቧቸዋል፤ እነዚህን ሁሉ በብልሃት እና [ሀ]በምስጋና ይጠቀሟቸው ዘንድ ነው።

፲፪ አዎን፣ [ሀ]የእንስሳትና የሰማይ አዕዋፋትንም [ለ]ስጋ፣ እኔ ጌታ ለሰው በምስጋና ጥቅም መድቤአቸዋለሁ፤ ነገር ግን እነዚህን [ሐ]እያሰለሱ ይጠቀሟቸው፤

፲፫ እና በክረምት ወይም በብርድ ወይም በረሀብ ጊዜያት ብቻ እንጂ፣ ይህን የማይጠቀሙበት ቢሆን የሚያስደስተኝ ነው።

፲፬ እና [ሀ]እህልም ለሰው እና ለእንስሳት ጥቅም፣ ለህይወት ሀይል፣ የተመደበ ነው፣ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለምድር አራዊትና ለሰማይ አዕዋፋት፣ እና በምድር ላይ የሚሮጡት እና ለሚርመሰመሱት ለዱር እንስሳት ነው፤

፲፭ እና እነዚህንም በድርቅ እና በከፍተኛ የረሀብ ጊዜያት ይሆኑ ዘንድ ብቻ ለሰው ጥቅም እግዚአብሔር እነዚህንም ሰራ።

፲፮ የወይን ፍሬም፤ በምድር ውስጥ ወይም ከምድር በላይ ፍሬ የሚያመጣውም እንደሆነው፣ ሁሉም እህል ለሰው ምግብ ጥሩ ነው—

፲፯ ይህም ቢሆን፣ ስንዴ ለሰው፣ በቆሎ ለበሬ፣ እና አጃ ለፈረስ፣ እና አጃ ለአዕ

፪ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፴፬።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ትእዛዛት።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፹፱፥ ፲፰–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
፬ሀ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
ለ ቅ.መ.መ. ሽንገላ (ውሸት)፣ መዋሸት፣ ማታለል።
ሐ ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣ ማስጠንቀቂያ።
፭ሀ ዘሌዋ. ፲፥ ፱–፲፩፤
ኢሳ. ፭፥ ፲፩–፲፪፤
፩ ቆሮ. ፮፥ ፲።
፮ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥ ፩–፬።
፯ሀ ምሳ. ፳፥ ፩፤ ፳፫፥ ፳፱–፴፭።
፰ሀ ፩ ቆሮ. ፫፥ ፲፮–፲፯።
ቅ.መ.መ. ሰውነት።
፲ሀ ይህም አትክልቶች ማለት ነው። ዘፍጥ. ፩፥ ፳፱፤
ት. እና ቃ. ፶፱፥ ፲፯–፳።
፲፩ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፲፪ሀ ፩ ጢሞ. ፬፥ ፫–፬፤
ት. እና ቃ. ፵፱፥ ፲፰–፳፩።
ለ ዘፍጥ. ፱፥ ፫፤
ዘሌዋ. ፲፩፥ ፩–፰።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፱፥ ፳።
፲፬ሀ ዳን. ፩፥ ፮–፳።

ዋፋት እና ለአሳማ፣ እና ለምድር አራዊት ሁሉ፣ እና ገብስ፣ እንደ ሌላ እህልም፣ ለጠቃሚ እንስሳቶች ሁሉ፣ እና ለለስላሳ መጠጥ።

፲፰ እና ትእዛዛትን በማክበር፣ እነዚህን ነገሮች የሚጠብቁ እና ለማድረግ የሚያስታውሱ ቅዱሳን ሁሉ፣ ለስጋቸው [ሀ]ፈውስ እና ለአጥንታቸው መጠገን ይቀበላሉ፤

፲፱ እናም [ሀ]ጥበብ እና ታላቅ [ለ]የእውቀት ሀብቶች፣ እንዲሁም የተሰወሩ ሀብቶችንም ያገኛሉ፤

፳ እናም [ሀ]ይሮጣሉ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ አይደክሙም።

፳፩ እና እኔ ጌታ፣ አጥፊው መልአክ የእስራኤል ልጆችን እንዳለፋቸው፣ እነርሱን [ሀ]ያልፋቸው ዘንድ እና እንዳይገድላቸውም ዘንድ፣ [ለ]የተስፋ ቃል እሰጣቸዋለሁ። አሜን።

ክፍል ፺

በመጋቢት ፰፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የቀዳሚ አመራርን ለመመስረት የቀጠለ እርምጃ ነው (የክፍል ፹፩ ርዕስን ተመልከቱ)፤ በዚህም ምክንያት፣ የተጠቀሱት አማካሪዎች በመጋቢት ፲፰፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) ተሾሙ።

፩–፭፥ የመንግስት ቁልፎች ለጆሴፍ ስሚዝ እና በእርሱም በኩል ለቤተክርስቲያኗ ተሰጥተዋል፤ ፮–፯፥ ስድኒ ሪግደን እና ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ በቀዳሚ አመራር ያገልግሉ፤ ፰–፲፩፥ ወንጌሉ ለእስራኤል ህዝብ፣ ለአህዛብ፣ እና ለአይሁድ፣ እያንዳንዱም ሰው በሚሰማው ቋንቋ ይሰበክለት፤ ፲፪–፲፰፥ ጆሴፍና አማካሪዎቹ ቤተክርስቲያኗን በስርዓት ያደራጁ፤ ፲፱–፴፯፥ የተለያዩ ግለሰቦች በቅንነት እንዲሄዱ እና በመንግስቱ እንዲያገለግሉ በጌታ ተመክረዋል።

፩ ጌታ እንዲህ ይላል፣ ልጄ ሆይ እውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣ በልመናህ መሰረት፣ ኃጢአቶችህ [ሀ]ተሰርየውልሀል፣ የአንተ እና የወንድሞችህ ጸሎቶች ወደ ጆሮዎቼ መጥተዋልና።

፪ ስለዚህ፣ የተሰጠህን የመንግስት [ሀ]ቁልፎች ለመያዝ ከዚህ ጀምሮ ተባርከሀል፤ ይህም [ለ]መንግስት ለመጨረሻ ጊዜ እየመጣ ያለው ነው።

፫ እውነት እልሀለሁ፣ በዚህ አለምም ሆነ በሚመጣው አለም ሳለህ፣ የመንግስት ቁልፎች ከአንተ በምንም መንገድ አይወሰድብህም፤

፬ ይህም ቢሆን፣ አዎን፣ በአንተ በኩል [ሀ]የእግዚአብሔር ቃላት ለሌላ፣ እንዲሁም ለቤተክርስቲያኗ፣ ይሰጣሉ።

፭ እና የእግዚአብሔርን ቃላት የሚቀበሉ ሁሉ፣ እንደ ቀላል ነገር እንዳይቆጥሯቸው፣ እና በዚህም ፍርድ እንዳይመጣባቸው፣ እና ማእበሉ ሲወርድ፣ እና ነፋሱም ሲነፍስ፣ እና [ሀ]ዝናብም ሲጥል፣ እና ቤታቸውንም ሲገፋው እንዳይደናቀፉ እና እንዳይወድቁ፣ እንዴት እንደሚይዟቸው [ለ]ይጠንቀቁ።

፲፰ ሀ ምሳ. ፫፥፰።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት፤ እውቀት።
፳ ሀ ኢሳ. ፵፥፴፩።
፳፩ ሀ ዘፀአ. ፲፪፥፳፫፣ ፳፱።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፹።

፺ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፰፥፪።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
፬ ሀ የሐዋ. ፯፥፴፰፤
ሮሜ ፫፥፪፤
ዕብ. ፭፥፲፪፤
ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፴፱፣ ፻፳፮።
ቅ.መ.መ. ትንቢት፣ መተንበይ።
፭ ሀ ማቴ. ፯፥፳፮–፳፯።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥፲፬።

፮ ደግሞም፣ ለወንድሞችህ ስድኒ ሪግደንና ፍሬደሪክ ጂ ዊሊያም እውነት እላቸዋለሁ፣ ኃጢአቶቻቸውም ደግሞ ተሰርየዋል፣ እና የዚህን የመጨረሻ መንግስት ቁልፎችን መያዝን በተመለከተ ከአንተ ጋር እንደ እኩል ይቆጠራሉ፣

፯ ደግሞም እንዲደራጅ ያዘዝኩትን የነብያት [ሀ]ትምህርት ቤት ማስተዳደሪያ ቁልፎችን መያዝን በተመለከተ ከአንተ ጋር እንደ እኩል ይቆጠራሉ፤

፰ በዚህም፣ የሚያምኑት ሁሉ፣ ለፅዮን፣ እና ለእስራኤል ህዝብ፣ እና ለአህዛብ ደህንነት በአገለግሎታቸው ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ፤

፱ በአገልግሎትህ ቃልን ይቀበሉ ዘንድ፣ እና በአገልግሎታቸውም ቃል፣ እስከ ምድር ዳርቻ ይሄድ ዘንድ፤ [ሀ]መጀመሪያ ወደ [ለ]አህዛብ፣ እና ከዚያም እነሆ አስተውሉ፣ ወደ አይሁድም ይዞራሉ።

፲ ከዚያም ህዝብን፣ የአህዛብን አገሮች፣ [ሀ]የጆሴፍን ቤት፣ የደህንነታቸውን ወንጌል ለማሳመን የጌታ እጅ በሀይል [ለ]የሚገለጥበት ቀን ይመጣል።

፲፩ በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፣ የወንጌል ሙላትን ለዚህ [ሀ]ሀይል [ለ]በተሾሙት በኩል፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ በሚፈስባቸው [ሐ]በአፅናኙ አገልግሎት፣ እያንዳንዱ ሰው በገዛ ልሳን እና በራሱ ቋንቋ [መ]ይሰማል።

፲፪ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]በአገልግሎቱ እና በአመራሩ እንድትቀጥሉ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፲፫ እና የነቢያትን ትርጉም ስትጨርሱ፣ ከዚህ በኋላ የቤተክርስቲያኗን እና [ሀ]የትምህርት ቤቱን ጉዳዮች [ለ]ትመራላችሁ፤

፲፬ እና ከጊዜ ወደ ጊዜም፣ በአፅናኙ እንደሚገለጸው፣ ተነግረው የማይታወቁ የመንግስትን [ሀ]ሚስጥራት [ለ]በራዕይ ተቀበሉ፤

፲፭ እና ቤተክርስቲያኖችንም በስርዓት አደራጁ፣ እና [ሀ]አጥኑና [ለ]ተማሩ፣ እና ሁሉንም መልካም መጻህፍት፣ [ሐ]ቋንቋዎች፣ ልሳኖች፣ እና ህዝብን እወቁ።

፲፮ እና ይህም፣ ኮሚቴውን መምራት፣ እና የዚህን ቤተክርስቲያን እና መንግስት ጉዳዮች በስርዓት ማደራጀት፣ በህይወታችሁ ሁሉ ጉዳያችሁ እና ተልዕኮአችሁ ይሆናል።

፲፯ [ሀ]አትፈሩ፣ ወይም አትዋረዱ፤ ነገር ግን በትዕቢታችሁ እና [ለ]በኩራታችሁም ተገሰጹ፣ በነፍሶቻችሁ ወጥመድ ያመጣልና።

፲፰ ቤቶቻችሁንም በስርዓት አስተካክሉ፤ [ሀ]ስራ ፈትነትን እና [ለ]ጽዱ አለመሆንን ከእናንተ አርቁ።

፲፱ አሁን፣ እውነት እልሀለሁ፣ ወድያውኑ ሲቻል፣ ለአማካሪህ እና ለጸሀፊህ፣ እንዲሁም ለፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ ቤተሰብ ስፍራ ይሰጥ።

፳ እና አዛውንቱ አገልጋዬ፣ [ሀ]ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊም፣ አሁን በሚኖርበት ስፍራ ከቤተሰቡ ጋር ይቀጥል፤ እና የጌታ አንደበት እስከሚወስንበትም ድረስ አይሸጥ።

፳፩ እና አማካሪዬ፣ እንዲሁም [ሀ]ስድኒ

፯ ሀ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
፱ ሀ ማቴ. ፲፱፥፴፤ ኤተር ፲፫፥፲–፲፪።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፵፪፤ ት. እና ቃ. ፻፯፥፴፫፤ ፻፴፫፥፰።
፲ ሀ ዘፍጥ. ፵፱፥፳፪–፳፮፤ ፩ ኔፊ ፲፭፥፲፫–፲፬።
ለ ት. እና ቃ. ፵፫፥፳፫–፳፯፤ ፹፰፥፹፬፤ ፹፯–፺፪።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት፤ ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ሐ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
መ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
ለ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፩–፺፪።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፯–፹፤ ፻፲፰፤ ፺፫፥፶፫።
ለ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፱–፻፤ ፻፴፥፲፰–፲፱።
ሐ ቅ.መ.መ. ቋንቋ።
፲፯ ሀ ሮሜ ፩፥፲፮፤ ፪ ኔፊ ፮፥፲፫።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፳፩። ቅ.መ.መ. ኩራት።
፲፰ ሀ ት. እና ቃ. ፺፫፥፵፫–፵፱። ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፵፪።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።

ሪግደን፣ የጌታ አንደበት እስከሚወስንበት ድረስ አሁን በሚኖርበት ይቆይ።

፹፪ እና ኤጲስ ቆጶሱ በቅንነት [ሀ]ወኪልን ለማግኘት ይፈልግ፣ እና ይህም ሰው [ለ]ሀብት ያከማቸ፣ የእግዚአብሔር ሰው፣ እና ጠንካራ እምነት ያለው ይሁን—

፹፫ በዚህም እያንዳንዱን እዳ ለመክፈል ችሎታ ይኖረው ዘንድ፤ የጌታ ጎተራ በሰዎቹ አይኖች ፊት መጥፎ ስም አይኖረው ዘንድ ወኪሉ ሀብት ያከማቸ የእግዚአብሔር ሰው፣ እና ጠንካራ እምነት ያለው ይሁን።

፹፬ [ሀ]ተግታችሁ ፈልጉ፣ ዘወትር [ለ]ጸልዩ፣ እናም እመኑ፣ እና በቅንነት ከተራመዳችሁ እና እርስ በራስ ቃል ኪዳን የገባችሁበትን [ሐ]ቃል ኪዳን ካስታወሳችሁ፣ [መ]ሁሉም ነገሮች ለእናንተ በጎነት አብረው ይሰራሉ።

፹፭ [ሀ]ቤተሰቦቻችሁ አነስተኛ ይሁኑ፤ በተለይም የቤተሰባችሁ አባል ያልሆኑትን በሚመለከት፤ በተለይም የአዛውንቱ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ ቤተሰብም፤

፹፮ ስራዎቹ እንዲከናወኑ፣ ለእናንተ የተሰጧችሁ ነገሮች ከእናንተ እንዳይወሰዱ እና ብቁ ላልሆኑት እንዳይሰጥ ዘንድ—

፹፯ እና በዚህም ያዘዝኳችሁን ነገሮች ለማከናወን እንዳትደናቀፉ ቤተሰቦቻችሁ አነስተኛ ይሁኑ።

፹፰ ደግሜ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ባሪያዬ ቪየና ዣክ ወጪዋን እንድትችል፣ እና ወደ ፅዮን ምድር ለመሄድ ገንዘብ ይሰጣት ዘንድ ፍቃዴ ነው፤

፹፱ እና የሚቀረው ገንዘብም ለእኔ ይቀደስ፣ እና በጊዜዬም ዋጋዋን ታገኛለች።

፺ እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ ፅዮን ምድር እንድትሄድ፣ እና ከኤጲስ ቆጶስ እጅ ውርሷን እንድትቀበል ፍቃዴ ነው፤

፺፩ ታማኝ እስከሆነች ድረስ በሰላም እንድትሰፍር፣ እና ከዚህ በኋላ በቀኖቿ ስራ ፈት እንዳትሆን ፍቃዴ ነው።

፺፪ እነሆም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህን ትእዛዝ ጻፉ፣ እና በፅዮን ውስጥ ያሉ ወንድሞቻችሁን፣ በፍቅር ሰላምታ፣ በጊዜዬ በፅዮን [ሀ]እንድትመሩ እንደተጠራችሁ ንገሯቸው።

፺፫ ስለዚህ፣ በዚህ ጉዳይ እኔን ማድከማቸውን ያቁሙ።

፺፬ እነሆ፣ እላችኋለሁ በፅዮን ያሉት ወንድሞቻችሁ ንስሀ ይግቡ፣ እና መላእክት በእነርሱ ይደሰቱ።

፺፭ ይህም ቢሆን፣ በብዙ ነገሮች አልተደሰትኩም፤ እና በአገልጋዬ [ሀ]ዊሊያም ኢ. መክሌይን፣ ወይም በአገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት አልተደሰትኩም፤ እና ኤጲስ ቆጶሱና ሌሎች ንስሀ የሚገቡበት ብዙ ነገሮች አላቸው።

፺፮ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ እኔ ጌታ [ሀ]ከፅዮን ጋር እጣላለሁ፣ እና ጠንካራዋን ለምኛለሁ፣ እና እስክትሸነፍ እና በፊቴ [ለ]ንጹህ እስክትሆን ድረስ [ሐ]እገስጻለሁ።

፺፯ ከስፍራዋ ልትነቃነቅ አትችልምና። እኔ ጌታ ተናግሬዋለሁ። አሜን።

ክፍል ፺፩

በመጋቢት ፱፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ነቢዩ በዚህ ጊዜ ብሉይ ኪዳንን በመተርጎም ላይ ነበር። አፖ

፹፪ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፻፲፪–፻፲፫።
ለ ያዕቆ. ፪፥፲፯–፲፱።
፹፬ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
መ ዕዝ. ፰፥፳፪፤ ሮሜ ፰፥፳፰፤ ት. እና ቃ. ፻፥፲፭፤ ፻፳፪፥፯–፰።
፹፭ ሀ ይህም ጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ ይንከባከባቸው የነበሩ ደሆች ማለት ነው።
፺፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፩–፺፪።
፺፭ ሀ ት. እና ቃ. ፷፮፥፩፤ ፸፭፥፮–፱።
፺፮ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ሐ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፤ ተግሳጽ።

ክርፋ በሚባለው የጥንት ፅሁፎች ክፍል ላይ ሲደርስ፣ ጌታን ጠየቀ እና ይህን መመሪያ ተቀበለ።

፩–፫፣ አፖክርፋው በትክክል የተተረጎመ ነው ነገር ግን በውስጡ በሰዎች እጆች እውነት ያልሆኑ ብዙ ተጨማሪዎች ነገሮችን ይይዛል፤ ፬–፮፣ ይህም መንፈስ የበራላቸውን ይጠቅማል።

፩ በእውነት፣ ጌታ [ሀ]አፖክርፋን በሚመለከት እንዲህ ይላል—በውስጡ እውነት የሆኑ አያሌ ነገሮችን ይዟል፣ እና አብዛኛውም በትክክል የተተረጎመ ነው፤

፪ በውስጡ፣ በሰዎች እጆች የተጨመሩ፣ እውነት ያልሆኑ ብዙ ነገሮችም አሉ።

፫ እውነት እላችኋለሁ፣ አፖክርፋው መተርጎሙ አስፈላጊ አይደለም።

፬ ስለዚህ፣ የሚያነበው፣ [ሀ]ይረዳው፣ መንፈስ እውነትን ይገልጣልና፤

፭ እና [ሀ]መንፈስ ያበራለት እርሱም ከዚህ ጥቅም ያገኛል፤

፮ እና በመንፈስ የማይቀበለውም፣ አይጠቀምበትም። ስለዚህ መተርጎሙ አስፈላጊ አይደለም። አሜን።

ክፍል ፺፪

በመጋቢት ፲፭፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ራዕዩ በቅርብ ለጆሴፍ ስሚዝ እንደ አማካሪ ለተመደበው ለፍረድሪክ ጂ ዊልያምስ በትብብር ድርጅት ውስጥ ስላለው ሀላፊነት መመሪያ የሚሰጥ ነው (ክፍሎች ፸፰ እና ፹፪ ርዕሶችን ተመልከቱ)።

፩–፪፣ ጌታ በትብብር ስርዓት ውስጥ አባል ስለመሆን ትእዛዝ ሰጥቷል።

፩ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ ከዚህ አስቀድሞ በተሰጠው ትእዛዝ አማካይነት ለተደራጀው [ሀ]የትብብር ስርዓት ስለአገልጋዩ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ፣ በስርዓቱ እንድትቀበሉት ዘንድ፣ ራዕይ እና ትእዛዝ ሰጥቻችኋለሁ። ለአንዱ የምለው ለሁሉም እንዲሁ እላለሁ።

፪ ደግሞም፣ ለአገልጋዩ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ እላለሁ፣ የዚህ ስርዓት ተሳታፊ አባል ሁን፤ እና የበፊቱን ትእዛዛት በማክበር ታማኝ እስከሆንክ ድረስ ለዘለአለም ትባረካለህ። አሜን።

ክፍል ፺፫

በግንቦት ፮፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ።

፩–፭፣ ታማኝ የሆኑ ሁሉ ጌታን ያያሉ፤ ፮–፲፰፣ የእግዚአብሔር ልጅ የአብን ክብር በሙላት እስከሚቀበል ድረስ ከጸጋ ወደ ጸጋ እንደሄደ ዮሐንስ መሰከረ፤ ፲፱–፳፣

፺፩ ፩ሀ ቅ.መ.መ. አፖክርፋ።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፭ሀ ቅ.መ.መ. መነሳሻ፣ መነሳሳት፤ መንፈስ ቅዱስ።
፺፪ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፩፣ ፲፭–፳፩። ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።

ታማኝ ሰዎች፣ ከጸጋ ወደ ጸጋ በመሄድ ሙሉነቱን ደግመው መቀበል ይችላሉ፤ ፳፩–፳፪፣ በክርስቶስ በኩል የተወለዱትም የበኩር ቤተክርስቲያን ናቸው፤ ፳፫–፳፰፣ ክርስቶስ የእውነትን ሁሉ ሙላት ተቀበለ፣ እና ሰውም በታዛዥነት ይህንኑ ሊያደርግ ይችላል፤ ፳፱–፴፪፣ ሰው በመጀመሪያም ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፤ ፴፫–፴፭፣ ንጥረ-ነገሮች ዘለአለማዊ ናቸው፣ እና ሰው የደስታን ሙላት በትንሳኤ ሊቀበል ይችላል፤ ፴፮–፴፯፣ የእግዚአብሔር ክብር የመረዳት ችሎታ ነው፤ ፴፰–፵፣ በክርስቶስ ቤዛነት ምክንያት ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ንጹሀን ናቸው፤ ፵፩–፶፫፣ መሪ ወንድሞች ቤተሰቦቻቸውን በስርዓት እንዲያደራጁ ታዘዙ።

፩ በእውነት፣ ጌታ እንዲህ ይላል፥ [ሀ]ኃጢአቶቹን የሚተውና ወደ እኔ የሚመጣ፣ እና ስሜን [ለ]የሚጠራ፣ እና ድምጼን [ሐ]የሚያከብር፣ እና ትእዛዛቴን የሚያከብር እያንዳንዱ ነፍስ ሁሉ [መ]ፊቴን [ሠ]የሚያይበት እና እኔ እንደሆንኩም የሚያውቅበት ጊዜ ይመጣል፤

፪ እና እኔ ወደ አለም ለሚመጣ ለእያንዳንዱ ሰው ሁሉ የማበራ የእውነት [ሀ]ብርሀን ነኝ፤

፫ እኔ በአብ [ሀ]እንዳለሁ አብም በእኔ ነው እናም አብና እኔም አንድ ነን—

፬ ሙላቱን [ሀ]ስለሰጠኝ አብ ነኝ፣ እና በአለም ውስጥ ስለነበርኩና [ለ]ስጋንም ድንኳኔ ስላደረግሁ፣ እና በሰውም ልጆች መካከል ስለኖርኩ ወልድ ነኝ።

፭ በአለም ውስጥ ነበርኩ እና አባቴንም ተቀበልኩኝ፣ እና [ሀ]ስራዎቹም በግልፅ የታዩ ነበሩ።

፮ እና [ሀ]ዮሐንስ አየና [ለ]ስለክብሬ ሙላት መሰከረ፣ እና [ሐ]የዮሐንስ ሙሉ ምስክር ከዚህ በኋላ ይገለጣል።

፯ እናም እንዲህ በማለትም መሰከረ፥ ክብሩን፣ አለም ከመሆኗ በፊት [ሀ]ከመጀመሪያ ጀምሮ እንደነበረ አየሁ፤

፰ ስለዚህ፣ በመጀመሪያው [ሀ]ቃል ነበር፣ እርሱም ቃል፣ እንዲሁም የደህንነት መላእክተኛ ነበርና—

፱ የአለም [ሀ]ብርሀን እና [ለ]አዳኝ፤ አለም በእርሱ ሆኗልና፣ እና በእርሱም ውስጥ የሰዎች ህይወት እና የሰዎች ብርሀን ነበር፣ ወደ አለምም የመጣ የእውነት መንፈስ እርሱ ነውና።

፲ አለማት በእርሱ [ሀ]ሆነዋልና፤ ሰዎችም በእርሱ ተፈጥረዋል፤ ሁሉም ነገሮች በእርሱ፣ በእርሱም አማካይነት፣ እና ከእርሱ ሆነዋል።

፲፩ እና እኔ ዮሐንስ ክብሩን፣ በጸጋ እና በእውነት፣ እንዲሁም በመጣው እና በስጋም በኖረው፣ እና በመካከላችን በኖረው፣ በእውነት መንፈስ ተሞልቶ፣ እንደ አብ አንድያ ልጅ ክብሩን እንዳየሁ እመሰክራለሁ።

፺፫ ፩ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት፤
ብቁ፣ ብቁነት።
ለ ኢዩ. ፪፥፴፪።
ሐ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
መ ጆ.ስ.ት. ፩ ዮሐ. ፬፥፲፪
(ተጨማሪ)።
ሠ ዘፀአ. ፴፫፥፲፩፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፯–፰፤
፷፯፥፲–፲፪፤ ፹፰፥፷፰፤
፻፩፥፳፫፤ ፻፴፥፫።
ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፪ሀ ዮሐ. ፩፥፬–፱፤
ት. እና ቃ. ፲፬፥፱፤
፹፬፥፵፭–፵፯፤ ፹፰፥፮–፯።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፫ሀ ዮሐ. ፲፥፳፭–፴፰፤
፲፯፥፳–፳፫፤
ት. እና ቃ. ፶፥፵፫–፵፭።
፬ሀ ሞዛያ ፲፭፥፩–፯።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—ስልጣን።
ለ ሉቃ. ፩፥፳፮–፴፭፤
፪፥፬–፲፬፤
፫ ኔፊ ፩፥፲፪–፲፬፤
ኤተር ፫፥፲፬–፲፮።
፭ሀ ዮሐ. ፭፥፴፮፤ ፲፥፳፭፤
፲፬፥፲–፲፪።
፮ሀ ዮሐ. ፩፥፴፬።
ለ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር።
ሐ ዮሐ. ፳፥፴–፴፩።
፯ሀ ዮሐ. ፩፥፩–፫፣ ፲፬፤ ፲፯፥፭፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፴፱።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ፤
ያህዌህ።
፱ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
፲ሀ ዕብ. ፩፥፩–፫፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፳፬፤
ሙሴ ፩፥፴፩–፴፫።

፲፪ እና እኔ ዮሐንስ በመጀመሪያ [ሀ]ሙላትን እንዳልተቀበለ፣ ነገር ግን [ለ]በጸጋ ላይ ጸጋን እንደተቀበለ አየሁ፤

፲፫ እና ሙላትን በመጀመሪያ አልተቀበለም፣ ነገር ግን ሙላትን እስከሚቀበል ድረስ [ሀ]ከጸጋ ወደ ጸጋ ቀጠለ፤

፲፬ እና ሙላትን በመጀመሪያ ስላልተቀበለ፣ በዚህም [ሀ]የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ተጠርቷል።

፲፭ እና እኔ [ሀ]ዮሐንስ እመሰክራለሁ እና አስተውሉ፣ ሰማያት ተከፈቱ [ለ]መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ላይም [ሐ]በርግብ አምሳል ወረደ፣ እናም አረፈበት፣ እና ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ [መ]የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።

፲፮ እና እኔ ዮሐንስ እርሱ የአብን ክብር በሙላት እንደተቀበለ እመሰክራለሁ፤

፲፯ እና [ሀ]ሀይልን [ለ]ሁሉ፣ በሰማይ እና በምድር ላይ ተቀበለ፣ እና [ሐ]የአብ ክብርም ከእርሱ ጋር ነበር፣ በእርሱ ውስጥም ይኖራልና።

፲፰ እና እንዲህም ይሆናል፣ እናንተ ታማኝ ብትሆኑ የዮሐንስን ምስክር በሙላት ትቀበላላችሁና።

፲፱ እነዚህን አባባል የምሰጣችሁ እንድትረዱ እና እንዴት እንደምታመልኩ እንድታውቁ፣ እና ምን [ሀ]እንደምታመልኩ እንድታውቁ፣ በስሜ ወደ አብ እንድትመጡ፣ እና በጊዜም ሙላትን ትቀበሉ ዘንድ ነው።

፳ [ሀ]ትእዛዛቴን የምታከብሩ ከሆናችሁም [ለ]ሙላቱን ትቀበላላችሁና፣ እና እኔ በአብ እንደሆንኩ እናንተ በእኔ [ሐ]ትከብራላችሁ፤ ስለዚህ፣ እላችኋለሁ፣ [መ]በጸጋ ላይ ጸጋን ትቀበላላችሁ።

፳፩ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ [ሀ]በመጀመሪያም ከአብ ዘንድ ነበርኩኝ፣ እና [ለ]በኩርም ነኝ፤

፳፪ እና በእኔ የተወለዱትም የዚህ [ሀ]ክብር [ለ]ተካፋዮች ናቸው፣ እና የበኩር ቤተክርስቲያንም ናቸው።

፳፫ አስቀድማችሁ [ሀ]ከአብ ጋር የነበራችሁ እናንተ መንፈስ፣ እንዲሁም የእውነት መንፈስ ነበራችሁ፤

፳፬ እና ነገሮች እንዳሉ፣ እንደነበሩ፣ እናም ወደፊት እንደሚሆኑ [ሀ]የሚታወቅበት [ለ]እውነት ነው።

፳፭ እና ማንኛውም ከዚህ [ሀ]በላይ ወይም በታች የሆነው ከክፉው መንፈስ ነው፣ እርሱም ከመጀመሪያ [ለ]ሀሰተኛ የነበረው ነው።

፳፮ [ሀ]የእውነት መንፈስም እግዚአብሔር ነው። እኔ የእውነት መንፈስ ነኝ፣ እና ዮሐንስ ስለእኔ እንዲህ በማለት መስክሯል፥ የእውነትን ሙላት፣ አዎን፣ እንዲሁም ሁሉንም እውነቶች ተቀበለ።

፳፯ እና ትእዛዛቱን ካላከበረ በስተቀር ማንም ሰው [ሀ]ሙላትን አይቀበልም።

፳፰ ትእዛዛቱን [ሀ]የሚያከብርም፣ በእውነት

፲፪ ሀ ፊልጵ. ፪፥፮–፲፩።
ለ ዮሐ. ፩፥፲፮–፲፯።
፲፫ ሀ ሉቃ. ፪፥፶፪።
፲፬ ሀ ሉቃ. ፩፥፴፩–፴፭፤ ት. እና ቃ. ፯፥፳፩። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።
፲፭ ሀ ዮሐ. ፩፥፳፱–፴፬።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ሐ ቅ.መ.መ. የርግብ መልእክት።
መ ማቴ. ፫፥፲፮–፲፯።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ—ስልጣን።
ለ ማቴ. ፳፰፥፲፰፤ ዮሐ. ፲፯፥፪፤ ፩ ጴጥ. ፫፥፳፪።
ሐ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ— እግዚአብሔር አብ።
፲፱ ሀ ዮሐ. ፬፥፳፩–፳፬፤ ፲፯፥፫፤ የሐዋ. ፲፯፥፳፪–፳፭። ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፶፥፳፰።
ለ ዮሐ. ፩፥፲፮፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፮–፴፱።
ሐ ዮሐ. ፲፯፥፬–፭፣ ፳፪። ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
መ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
፳፩ ሀ ዮሐ. ፩፥፩–፪፤ ፩ ጴጥ. ፩፥፲፱–፳፤ ሙሴ ፬፥፪።
ለ ቅ.መ.መ. በኩር።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
ለ ፩ ጴጥ. ፭፥፩፤ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፶፯።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—ሰው፣ የሰማይ አባት የመንፈስ ልጅ።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ለ ቅ.መ.መ. እውነት።
፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፴፭።
ለ ዮሐ. ፰፥፵፬፤ ፪ ኔፊ ፪፥፲፰፤ ሙሴ ፬፥፬።
፳፮ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፮።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፍጹም።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።

እና ሁሉንም ነገሮች [ለ]በማወቅ እስከሚከበር ድረስ፣ እውነት እና [ሐ]ብርሀንን ይቀበላል።

፳፱ ሰው ደግሞ [ሀ]በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር። [ለ]የመረዳት ችሎታ፣ ወይም የእውነት ብርሀን፣ የተፈጠረ ወይም የተሰራ አይደለም፣ በእርግጥም ሊሆን አይችልም።

፴ ሁሉም እውነት እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ተፅዕኖ አካባቢያቸው፣ በራሳቸው [ሀ]የሚሰሩ፣ እንደየራሳቸው የመረዳት ችሎታ፣ ራሳቸውን የቻሉ ናቸው፤ አለበለዚያም ምንም አይኖርም።

፴፩ እነሆ፣ ይህ የሰው [ሀ]ነጻ ምርጫ ነው፣ እና ይህ የሰው ኩነኔ ነው፤ ከመጀመሪያ የነበረው [ለ]በግልጽ ስለታየላቸው፣ እና ብርሀንንም አልተቀበሉትምና።

፴፪ እና መንፈሱ [ሀ]ብርሀንን የማይቀበል በእርሱ በፍርድ ላይ ነው።

፴፫ ሰው [ሀ]መንፈስ ነውና። [ለ]ንጥረ-ነገሮች ዘለአለማዊ ናቸው፣ እና መንፈስ እና ንጥረ-ነገር ሳይለያዩ የተያያዙ፣ የደስታን ሙላትን የሚቀበሉ ናቸው።

፴፬ እና [ሀ]ሲለያዩም፣ ሰው [ለ]የደስታን ሙላት አይቀበልም።

፴፭ [ሀ]ንጥረ-ነገሮች የእግዚአብሔር ድንኳን ናቸው፤ አዎን፣ ሰውም የእግዚአብሔር ድንኳን፣ እንዲሁም [ለ]ቤተመቅደሳት፣ ነው፤ እና ቤተመቅደሱ የረከሰ ቢሆን፣ እግዚአብሔር ያንን ቤተመቅደስ ያፈርሰዋል።

፴፮ የእግዚአብሔር [ሀ]ክብር [ለ]የመረዳት ችሎታ ነው፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ [ሐ]ብርሀንና እውነት ነው።

፴፯ ብርሀን እና እውነት [ሀ]ክፉውን ይተዋል።

፴፰ እያንዳንዱ የሰው መንፈስ በመጀመሪያ [ሀ]የዋህ ነበር፤ እና እግዚአብሔር ሰውን [ለ]ከውድቀቱ [ሐ]ሲያድን፣ ሰዎችም ዳግም በህጻንነት በእግዚአብሔር ፊት [መ]የዋህ ሆኑ።

፴፱ ክፉውም መጣ እና፣ ባለመታዘዝና በአባቶቻቸው [ሀ]ባህል ምክንያት፣ ብርሀንን እና እውነትን ከሰዎች ልጆች [ለ]ነጠቀ።

፵ ነገር ግን [ሀ]ልጆቻችሁን በብርሀን እና በእውነት እንድታሳድጓቸው ዘንድ አዛችኋለሁ።

፵፩ ነገር ግን አገልጋዬ ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ እውነት እልሀለሁ፣ በዚህ ኩነኔ ቀጥለሀል፤

፵፪ በትእዛዛትም በኩል ልጆችህን ብርሀን እና እውነት [ሀ]አላስተማርክም፤ እና ክፉውም በአንተ ላይ ሀይል አለው፣ እና ይህም የስቃይህ ምክንያት ነው።

፳፰ ለ ዮሐ. ፲፯፥፫፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፵፱፤ ፷፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፥፳፬፤
፹፬፥፵፭።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፳፱ ሀ አብር. ፫፥፲፰።
ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች፤
ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣
እውቀተኛዎች።
፴ ሀ ፪ ኔፊ ፪፥፲፫–፳፯።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ለ ዘዳግ. ፴፥፲፭–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥፸፰–፸፱።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ
ብርሀን፤
እውነት።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፸፯፥፪፤
አብር. ፭፥፯–፰።
ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—
ሰው፣ የሰማይ አባት
የመንፈስ ልጅ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፴፩፥፯–፰፤
፻፴፰፥፲፯።
ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፴፬ ሀ ፪ ኔፊ ፱፥፰–፲።
ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴፭ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፥፳፪።
ለ ፩ ቆሮ. ፫፥፲፮–፲፯።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስ ክብር፤
ክብር።
ለ ት. እና ቃ. ፻፴፥፲፰–፲፱፤
አብር. ፫፥፲፱።
ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣
እውቀተኛዎች።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፮–፲፫።
፴፯ ሀ ሙሴ ፩፥፲፪–፲፮።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. የዋህ፣ የዋህነት።
ለ ቅ.መ.መ. የአዳም እና
የሔዋን ውድቀት።
ሐ ሞዛያ ፳፯፥፳፬–፳፮፤
ሙሴ ፮፥፶፬፤
እ.አ. ፩፥፫።
ቅ.መ.መ. ቤዛ፣
ማዳን፣ ቤዛነት።
መ ሞሮኒ ፰፥፰፣ ፲፪፣ ፳፪፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥፵፮–፵፯።
ቅ.መ.መ. ደህንነት—
የልጆች ደህንነት።
፴፱ ሀ ሕዝ. ፳፥፲፰–፲፱፤
አልማ ፫፥፰።
ቅ.መ.መ. ባህል።
ለ ማቴ. ፲፫፥፲፰–፲፱፤
፪ ቆሮ. ፬፥፫–፬፤
አልማ ፲፪፥፱–፲፩።
፵ ሀ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—
የወላጆች ሀላፊነቶች።
፵፪ ሀ ፩ ሳሙ. ፫፥፲፩–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፷፰፥፳፭–፴፩።

፵፫ አሁንም ትእዛዝ እሰጥሀለሁ—የምትድን ቢሆን ቤትህን [ሀ]በስርዓት አደራጅ፣ በቤትህ ውስጥ አያሌ ትክክል ያልሆኑ ነገሮች አሉና።

፵፬ ለአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን በእውነት እለዋለሁ፣ በአንዳንድ ነገሮች ልጆቹን በሚመለከት ትእዛዝን አላከበረም፤ ስለ ዚህ፣ አስቀድሞ ቤቱን በስርዓት ያደራጅ።

፵፭ በእውነት፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ይህን እላለሁ፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ ባልንጀሮቼ ብዬ እጠራችኋለሁ፣ እናንተ [ሀ]ባልንጀሮቼ ናችሁና፣ እና ከእኔም ጋር ውርስ ይኖራችኋል—

፵፮ [ሀ]አግልጋዮቼ ብዬ የምጠራችሁ በአለም ምክንያት ነው፣ እና እናንተም ለእነርሱ በእኔ ምክንያት አገልጋዮቻቸው ናችሁ—

፵፯ አሁንም፣ በእውነት ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እላለሁ—ትእዛዛትን አላከበርክም፣ እና በጌታ ፊትም [ሀ]ተገስጸህ መቆም ያስፈልግሀል፤

፵፰ [ሀ]ቤተሰብህ ንስሀ መግባትና አንዳንድ ነገሮችን መተው አለባቸው፣ እና የምትላቸውንም በቅንነት ማድመጥ ያስፈልጋቸዋል፣ ወይም ከስፍራቸው ይወጣሉ።

፵፱ ለአንዱ የምለው ለሁሉም እላለሁ፤ ዘወትር [ሀ]ጸልዩ አለበለዚያም ክፉው በውስጣችሁ ሀይል ይኖረዋል፣ እና ከስፍራችሁ ያስወጣችኋል።

፶ የቤተክርስቲያኔ ኤጲስ ቆጶስ፣ አገልጋዬ ኒውል ኬ ዊትኒም፣ ሊገሰፅ፣ እና ቤተሰቡን በስርዓት ሊያደራጅ፣ እና በቤትም በተጨማሪ ቅን እና አሳቢ እንዲሆኑ፣ እና ዘወትርም እንዲጸልዩ ሊያደርግ ያስፈልገዋል፣ ወይም [ሀ]ከስፍራቸው ይወጣሉ።

፶፩ ባልንጀሮቼ፣ አሁን እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ስድኒ ሪግደን በጉዞው ይሂድ፣ እና ይፍጠን፣ እና ደግሞም በምሰጠው የንግግር ችሎታ የጌታን [ሀ]የተወደደች አመትን፣ እና የደህንነትን ወንጌልን ያውጅ፤ እና በአንድ አላማ በምታደርጉት የእምነት ጸሎት እደግፈዋለሁ።

፶፪ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ፣ እና ፍሬድሪክ ጂ ዊሊያምስም ይፍጠኑ፣ እና እንድ እምነት ጸሎታቸውም ይሰጣቸዋል፤ እና እኔ የምላችሁን እስከጠበቃችሁ ድረስ በዚህ አለምም፣ ሆነ በሚመጣው አለም አትሸነፉም።

፶፫ እና፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ቅዱስ መጻሕፍቴን [ሀ]ለመተርጎም እንድትፈጥኑ፣ እና የታሪክ፣ እና የሀገሮች፣ እና የመንግስታት፣ የእግዚአብሔር እና የሰው ህግጋት [ለ]እውቀትን [ሐ]እንድታገኙ ፍቃዴ ነው፣ ይህም ሁሉ ለፅዮን ደህንነት ነው። አሜን።

ክፍል ፺፬

በነሀሴ ፪፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ሀይረም ስሚዝ፣ ሬኖልድስ ከሁን፣ እና ጄርድ ካርተር ለቤተክርስቲያን መገንባት በኮሚቴነት ተመድበዋል።

፩–፱፣ ጌታ ለቀዳሚ አመራር ስራ ስለሚገነባው ቤት የሚመለከት ትእዛዝ ሰጠ፤ ፲–፲፪፣ የማተሚያ ቤት ይገንባ፤ ፲፫–፲፯፣ ልዩ ውርሶች ተመድበዋል።

፵፫ሀ ፩ ጢሞ. ፫፥፬–፭።
፵፬ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፫፤ ፹፰፥፴፱።
፵፭ሀ ዘሌዋ. ፳፭፥፶፭፤ ፩ ኔፊ ፳፩፥፫–፰። ቅ.መ.መ. አገልግሎት።
፵፯ሀ ት. እና ቃ. ፺፭፥፩–፪። ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፵፰ሀ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ— የልጆች ሀላፊነቶች።
፵፱ሀ ፫ ኔፊ ፲፰፥፲፭–፳፩።
፶ሀ ት. እና ቃ. ፳፬፥፵።
፶፩ሀ ሉቃ. ፬፥፲፱።
፶፫ሀ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
ለ ቅ.መ.መ. እውቀት።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፰–፹፣ ፻፲፰።

፩ ደግሞም፣ [ሀ]ባልንጀሮቼ እውነት እላችኋለሁ፣ በዚህ በከርትላንድ ምድር ውስጥ፣ በቤቴ በመጀመር፣ የፅዮን [ለ]ካስማ ከተማን ጅማሬ መሰረት ለመጣል እና ለማዘጋጀት ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፪ እነሆም፣ በሰጠኋችሁ [ሀ]ምሳሌ መሰረት መደረግ አለበት።

፫ እና በደቡብ ያለው የመጀመሪያው ከፊል መሬት ለእኔ፣ ራዕዮችን ለሚቀበሉ በት ለአመራር ስራ፣ ለአመራር ቤት መሰሪያ ይቀደስ፤ እናም ይህም ቤተክርስቲያኗን እና መንግስቱን በሚመለከቱ ሁሉም ነገሮች [ሀ]ለአመራር አገልግሎት ስራ ነው።

፬ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህም፣ በውስጠኛው አደባባይ፣ አስራ ሰባት ሜትር በሀያ ሜትር ስፋት እና ርዝመቱ ይሁን።

፭ እና፣ ከዚህ በኋላ በሚሰጣችሁ ንድፍ መሰረት፣ የታች አደባባይና የላይ አደባባይ ይኑረው።

፮ እና፣ በክህነት ስልጣን ስርዓት መሰረት፣ ከዚህ በኋላ በሚሰጣችሁ ንድፍ መሰረት፣ ይህ ከመሰረቱ ጀምሮ ለጌታ ይቀደስ።

፯ እና ይህም ለአመራር ስራ ለጌታ ሁሉ ይቀደስ።

፰ እና ማንኛውም [ሀ]እርኩስ ነገር ወደውስጥ እንዲገባ አትፍቀዱ፤ እና [ለ]ክብሬም በዚያ ይሆናል፣ እና በዚያም እገኛለሁ።

፱ ማንኛውም [ሀ]እርኩስ ነገር ቢገባበት ግን፣ ክብሬ በዚያ አይሆንም፤ እና ወደዚህም አልገባም።

፲ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሁለተኛው ከፊሉ መሬት ለእኔ ቤት መሰሪያ፣ ለቅዱስ መጻሕፍቴ [ሀ]መታተምና [ለ]መተርጎም ስራ፣ እና ለማዛችሁ ማንኛቸውም ነገሮች ሁሉ፣ ለእኔ ይቀደስ።

፲፩ እና ይህም፣ በውስጥ አደባባዩ፣ አስራ ሰባት ሜትር በሀያ ሜትር ስፋት እና ርዝመት ይሁን፤ እና የበታች እና የላይ አደባባይ ይኑረው።

፲፪ እና ይህም ቤት ከመሰረቱ ጀምሮ፣ ለህትመት ስራ፣ በሚሰጣችሁ ንድፍ መሰረት በሁሉም ነገሮች ቅዱስ እና ያልረከሰ እንዲሆን ማንኛቸውም በማዛችሁ ሁሉም ነገሮች ሁሉ ለጌታ ይቀደስ።

፲፫ እና በሶስተኛው ከፊል መሬት ላይ አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ውርሱን ይቀበል።

፲፬ እና በሰሜን ላይ ባለው በመጀመሪያው እና በሁለተኛው ከፊል ስፍራ ላይ አገልጋዬ ሬኖልድስ ከሁን እና ጀርድ ካርተር ውርሶቻቸውን ይቀበሉ—

፲፭ የመደብኩላቸውን ስራ ያከናውኑ ዘንድ፣ እኔ ጌታ በሰጠኋችሁ ትእዛዝ መሰረት የቤቶቹ የግንባታ ኮሚቴ ይሁኑ።

፲፮ እነዚህ ሁለት ቤቶች እነርሱን በሚመለከት ትእዛዝ እስክሰጣችሁ ድረስ እንዳይገነቡ።

፲፯ አሁንም በዚህ ጊዜ ምንም ተጨማሪ ነገርን አልሰጣችሁም። አሜን።

ክፍል ፺፭

በሰኔ ፩፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የማምለኪያ እና የመማሪያ ቤት፣ በልዩም የጌታ ቤት፣ እንዲሰሩ ቀጣይ መለኮታዊ መመሪያ የተሰጠበት ነው (ክፍል ፹፰፥፻፲፱–፻፴፮ን ተመልከቱ)።

፺፬ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፺፫፥፵፭።
ለ ቅ.መ.መ. ካስማ።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፶፪፥፲፬–፲፭።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፱፣ ፳፪።
፰ሀ ሉቃ. ፲፱፥፵፭–፵፮፤
ት. እና ቃ. ፻፱፥፲፮–፳።
ለ ፩ ነገሥ. ፰፥፲–፲፩።
ቅ.መ.መ. ክብር።
፱ሀ ት. እና ቃ. ፺፯፥፲፭–፲፯።
፲ሀ ት. እና ቃ. ፻፬፥፶፰–፶፱።
ለ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።

፩–፮፣ ቅዱሳን የጌታን ቤት ለመስራት ባሳዩት ድክመት ይገሰጻሉ፤ ፯–፲፣ ጌታ ቤቱን በመጠቀም ህዝቡን ከላይ ሀይልን ሊያለብሳቸው ይፈልጋል፤ ፲፩–፲፯፣ ቤቱም የማምለኪያ ቦታ እና ለሐዋርያት ትምህርት ቤት እንዲሆን ይቀደስ።

፩ በእውነት ለምወዳችሁ ለእናንተ ጌታ እንዲህ ይላል፣ እና የምወዳቸውንም ኃጢአታቸውን [ሀ]ለመሰረይ [ለ]እገስጻቸዋለሁ፣ በቅጣትም [ሐ]ከፈተና በሁሉም ነገሮች [መ]የሚድኑበትን መንገድ አዘጋጃለሁና፣ እና ወድጃችኋለሁም—

፪ ስለዚህ፣ በፊቴ መቀጣት እና መገሰፅ ያስፈልጋችኋል፤

፫ [ሀ]ቤቴን ስለመገንባት የሰጠኋችሁን፣ ታላቅ ትእዛዝ በሁሉም ነገሮች ስላላሰባችሁበት፣ አስከፊ የሆነን ኃጢአት በእኔ ላይ ሰርታችኋልና፤

፬ [ሀ]እንግዳ የሆነን ስራዬን አከናውን ዘንድ፣ በሁሉም ስጋ ለባሽ ላይ መንፈሴን [ለ]አፈስ ዘንድ፣ ሐዋሪያቴን ለመጨረሻ ጊዜ የወይኑ ስፍራዬን [ሐ]እንዲመለምሉ ለማዘጋጀት ያዘጋጀሁት ንድፍ ታላቅ ትእዛዝ በሁሉም ነገሮች አላሰባችሁበትም፤

፭ ነገር ግን እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በመካከላችሁ የጠራኋቸው የተሾሙ ብዙ አሉ ነገር ግን [ሀ]የተመረጡት ጥቂቶች ናቸው።

፮ ያልተመረጡትም በጣም አሳዛኝ ኃጢአት ሰርተዋል፣ በዚያም በቀትርም ጊዜ [ሀ]በጨለማ ይሄዳሉ።

፯ እና ለዚህም ምክንያት [ሀ]ጾማችሁ እና ልቅሶአችሁ፣ ወደ [ለ]ፀባኦት ጌታ፣ ይህም ሲተረጎም የመጀመሪያው ቀን [ሐ]ፈጣሪ፣ የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ወደሆነው፣ ወደ እርሱ ጆሮዎች ይመጡ ዘንድ [መ]የክብር ስብሰባችሁን እንድትጠሩ ትእዛዝን ሰጠኋችሁ።

፰ አዎን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ቤትን ትገነቡ ዘንድ ትእዛዝ ሰጠኋችሁ፣ በዚህ ቤትም የመረጥኳቸውን ከላይ [ሀ]መንፈሳዊ ስጦታ ልሰጣችሁ አቅጃለሁ፤

፱ ይህም አብ ለእናንተ የሚገባው [ሀ]ቃል ኪዳን ነውና፤ ስለዚህ እንደ ኢየሩሳሌም ሐዋሪያቴ፣ እንድትቆዩ አዛችኋለሁ።

፲ ይህም ቢሆን፣ አገልጋዮቼ በጣም አሳዛኝ ኃጢአትን ሰርተዋል፤ እና በነቢያት [ሀ]ትምህርት ቤትም [ለ]አለመስማማት ተነስቷል፤ ይህም ለእኔ በጣም አሳዛኝ ነው ይላል ጌታ፤ ስለዚህ እንዲገሰጹ ላኳቸው።

፲፩ እውነት እላችኋለሁ፣ ቤትን እንድ ትገነቡ ፍቃዴ ነው። ትእዛዛቴን ብታከብሩ ይህን ለመገንባት ሀይል ይኖራችኋል።

፲፪ ትእዛዛቴን [ሀ]ካላከበራችሁ፣ የአብ [ለ]ፍቅር ከእናንተ ጋር አይቀጥልም፣ ስለዚህ በጭለማ ትሄዳላችሁ።

፲፫ አሁን ይህ ጥበብ፣ እና የጌታ አዕምሮ

፺፭ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
ለ ዘዳግ. ፲፩፥፩–፰፤ ምሳ. ፲፫፥፲፰፤ ዕብ. ፲፪፥፭–፲፩፤ ሔለ. ፲፭፥፫፤ ት. እና ቃ. ፻፩፥፬–፭፤ ፻፭፥፮። ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
ሐ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
መ ፩ ቆሮ. ፲፥፲፫።
፫ ሀ ሐጌ. ፩፥፯–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፱። ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
፬ ሀ ኢሳ. ፳፰፥፳፩፤ ት. እና ቃ. ፻፩፥፺፭።
ለ ምሳ. ፩፥፳፫፤ ኢዩ. ፪፥፳፰፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፴፰። ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ፤ የመንፈስ ስጦታዎች።
ሐ ያዕቆ. ፭፥፷፩–፸፭፤ ት. እና ቃ. ፳፬፥፲፱፤ ፴፫፥፫–፬። ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
፭ ሀ ማቴ. ፳፥፲፮፤ ት. እና ቃ. ፻፭፥፴፭–፴፯፤ ፻፳፩፥፴፬–፵። ቅ.መ.መ. መመረጥ።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ጾም፣ መጾም።
ለ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ሐ ቅ.መ.መ. መፍጠር፣ ፍጥረት።
መ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፣ ፸፬–፹፪፣ ፻፲፯–፻፳።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፪፤ ፴፱፥፲፭፤ ፶፫፥፲፮፤ ፻፲፥፱–፲። ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ።
፱ ሀ ሉቃ. ፳፬፥፵፱።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።
ለ ቅ.መ.መ. ጸብ።
፲፪ ሀ ዮሐ. ፲፭፥፲።
ለ ፩ ዮሐ. ፪፥፲፣ ፲፭።

ነው—በአለም በሚሰሩበት ሳይሆንም፣ ቤት ይሰራ፤ በአለም አይነት ኑሮ እንድትኖሩ አልሰጠኋችሁምና፤

፲፬ ስለዚህ፣ ለዚህ ሀይል ለምትመድቡት እና ለምትሾሙት ለሶስታችሁ በማሳያችሁ ስርዓት ይሰራ።

፲፭ እና በዚህ ውስጠኛ አደባባይም፣ መጠኑ አስራ ሰባት ሜትር ስፋት ይሁን፣ እና ርዝመቱም ሀያ ሜትር ይሁን።

፲፮ እና የውስጠኛው አደባባይ የታች ክፍል ለቅዱስ ቁርባን ለማቅረብ፣ እና ለስብከታችሁ፣ እና ለጾማችሁ፣ እና ለጸሎታችሁ፣ እና ከሁሉም በላይ የሆነውን ፍላጎታችሁን [ሀ]ለምታቀርቡበት ለእኔ ይቀደስ፣ ይላል ጌታ።

፲፯ እና የውስጠኛው አደባባይ ከፍተኛው ክፍልም ለሐዋሪያቴ ትምህርት ቤት ለእኔ ይቀደስ፣ አለ [ሀ]አህመን ልጅ፤ ወይም በሌላ ቃላት አልፈስ፤ ወይም በሌላ ቃላት፣ ኦሜገስ፤ እንዲሁም [ለ]ጌታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ። አሜን።

ክፍል ፺፮

በሰኔ ፬፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የፅዮን ከተማ ወይም ካስማ ስርዓትን በማሳየት፣ በከርትላንድ ላሉት ቅዱሳን እንደምሳሌ የተሰጠ ራዕይ። ምክንያቱ የሊቀ ካህናት ጉባኤ ነበር፣ እና የሚታሰብበት ዋናው ርዕስ ቢኖር በከርትላንድ አጠገብ ቤተክርስቲያኗ ያላትን የፍሬንች እርሻ ስፍራ የሚባለውን ምድር ስለመሸጥ ነበር። ጉባኤው ማን የእርሻ ስፍራውን በሀላፊነት እንደሚወስድ መስማማት ስላልቻሉ፣ ሁሉም ጉዳዩን በመመልከት ጌታን ለመጠየቅ ተስማሙ።

፩፣ የከርትላንድ የፅዮን ካስማ ብርቱ ትሁን፤ ፪–፭፣ ኤጲስ ቆጶስ ውርሱን ለቅዱሳኑ ያካፍል፤ ፮–፱፣ ጆን ጆንሰን በትብብር ስርዓት አባል ይሁን።

፩ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ይህንን ጉዳይ እንዴት ለመስራት የምታውቁበት ይህም ጥበብ ይህ ነው፣ ለፅዮን ብርታት የመሰረትኳት ይህች [ሀ]ካስማ ጠንካራ ትሆን ዘንድ ለእኔ አስፈላጊ ነውና።

፪ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ኒወል ኬ ውትኒ ቅዱስ ቤቴን ለመገንባት ያለምኩበትን፣ የጠቀሳችሁትን ስፍራ በሀላፊነት ይውሰድ።

፫ ደግሞም፣ በጥበብ መሰረትም፣ ውርስ ለሚፈልጉት ጥቅም ይሆን ዘንድ፣ በመካከላችሁ በምክር እንደሚወሰነው፣ በክፍልፋይ መሬቶች ይከፋፈል።

፬ ስለዚህ፣ ይህን ጉዳይ እና፣ ቃሌን ለሰዎች ልጆች ለማምጣት አላማ፣ [ሀ]ስርዓቴን ለመጥቀም አስፈላጊ የሆነውን ክፍል ታሚሉ ዘንድ አስታውሱ።

፭ እነሆም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የሰዎች ልጆች ልብ ለእናንተ ጥቅም በቁጥጥር ስር ለማዋል አላማ፣ ቃሌ ወደ ሰዎች ልጆች ይሄዱ ዘንድ ይህ ለእኔ በጣም አስፈላጊ ነው። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፮ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህም ጥበብ እና በእኔ አስፈላጊ ነው፣ መስዋዕቱን የተቀበልኩለት፣ እና ጸሎቱን የሰማሁለት፣ ከዚህ ጀምሮ ትእዛዛቴን እስካከበረ ድረስ

፲፮ሀ ት. እና ቃ. ፶፱፥፱–፲፬።
፲፯ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፳።
ለ ቅ.መ.መ. ጌታ።

፺፮ ፩ሀ ኢሳ. ፴፫፥፳፤ ፶፬፥፪።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፫–፬።
ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።

የዘለአለም ህይወት ቃል ኪዳን የምሰጠው አገልጋዬ ጆን ጆንሰን—

፯ እርሱም [ሀ]የዮሴፍ ትውልድ ዘር እና ለአባቶቹ የተሰጡትን የቃል ኪዳን በረከቶች ተካፋይ ነውና—

፰ እውነት እላችኋለሁ፣ ቃሌን ለሰዎች ልጆች ለማምጣት ይረዳ ዘንድ እርሱ የስርዓቱ አባል መሆኑ በእኔ ዘንድ አስፈላጊ ነው።

፱ ስለዚህ ለዚህ በረከት ሹሙት፣ እና በዚያም ይኖርበት ዘንድ በእናንተ መካከል ከተጠቀሰው ቤት ላይ ያሉትን እዳዎች ለመውሰድ በቅንነት ይፈልግ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፺፯

በነሀሴ ፪፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዩ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ፣ ነቢዩ ጌታን ለመረጃ በጠየቀበት መልስ፣ የፅዮን፣ የጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ ቅዱሳን ጉዳዮችን የሚያመራምር ነበር። በዚህ ጊዜ በሚዙሪ የነበሩት የቤተክርስቲያኗ አባላት በጥልቅ እየተሰቃዩ ነበር እና በሐምሌ ፳፫፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) ከጃክሰን የግዛት ክፍል ወጥተው እንዲሄዱ ስምምነትን እንዲፈርሙ ተገድደው ነበር።

፩–፪፣ ብዙዎቹ የፅዮን (ጃክሰን የግዛት ክፍል፣ ሚዙሪ) ቅዱሳን በእምነታቸው ተባርከዋል፤ ፫–፭፣ ፓርሊ ፒ ፕራት በፅዮን ትምህርት ቤት እንዲያገለግል ታዝዟል፤ ፮–፱፣ ቃል ኪዳናቸውን የሚያከብሩትን ጌታ ይቀበላቸዋል፤ ፲–፲፯፣ ልበ ንጹ የሆኑት እግዚአብሔርን የሚያዩበት ቤት በፅዮን ይሰራ፤ ፲፰–፳፩፣ ፅዮን ልበ ንጹህ ነች፤ ፳፪–፳፰፣ ታማኝ ከሆነች ፅዮን የጌታን ቅጣት ታመልጣለች።

፩ ባልንጀሮቼ እውነት እላችኋለሁ፣ በእውነት ትሁት ሆነው እና በቅንነት ጥበብን ለመማርና እውነትን ለማግኘት ስለሚጥሩት ብዙዎች፣ [ሀ]በፅዮን ምድር ስላሉት ወንድሞቻችሁ ያለኝን ፈቃድ አሳያችሁ ዘንድ በድምጼ፣ እንዲሁም በመንፈሴ ድምፅ እናገራችኋለሁ።

፪ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እንደ ነዚህ አይነቶች የተባረኩ ናቸው፣ ያገኙታልና፤ ፍርድንም ሳመጣባቸው ፅድቅ አደርግ ዘንድ፣ እኔ ጌታ [ሀ]ለቅን እና ለምፈልገው ሁሉ ምህረትን አሳያለሁና።

፫ እነሆ፣ በፅዮን ስላለው [ሀ]ትምህርት ቤት እላችኋለሁ፣ እኔ ጌታ በፅዮን ትምህርት ቤት በመኖሩ፣ ደግሞም በአገልጋዬ [ለ]ፓርሊ ፒ ፕራትም ተደስቻለሁ፣ እርሱም በእኔ ይኖራልና።

፬ በእኔ በመኖር የሚቀጥል ቢሆን ሌላ ትእዛዛትን እስከምሰጠው ድረስ በፅዮን ምድር ትምህርት ቤት ውስጥ በመሪነት ይቀጥላል።

፭ እናም ለትምህርት ቤቱ፣ እና ለፅዮን ውስጥ ቤተክርስቲያን መታነጽ ቅዱሳን መጻህፍትን ሁሉ እና ሚስጥራትን ለማብራራት በሚበዙ በረከቶች እባርከዋለሁ።

፮ እና ለሚቀሩት ትምህርት ቤትም፣ እኔ ጌታ፣ ምህረትን ለማሳየት ፈቃደኛ ነኝ፤ ይህም ቢሆን፣ [ሀ]መገሰፅ የሚያስፈልጋቸው ሌሎችም አሉ፣ እና ስራዎቻቸውም እንዲታወቁ ይደረጋል።

፯ሀ ቅ.መ.መ. ዮሴፍ፣ የያዕቆብ ልጅ።

፺፯ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።

፪ሀ ማቴ. ፭፥፭፤ ሞዛያ ፫፥፲፱።

፫ሀ ቅ.መ.መ. የነቢያት ትምህርት ቤት።

ለ ቅ.መ.መ. ፕራት፣ ፓርሊ ፓርከር።

፮ሀ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።

፯ [ሀ]ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ እና መልካም [ለ]ፍሬ የማይሰጥ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል እና ወደ እሳትም ይጣላል። እኔ ጌታ ተናግሬዋለሁ።

፰ እውነት እላችኋለሁ፣ በመካከላቸው [ሀ]ልቦቻቸው [ለ]ታማኝ እንደሆኑ፣ እና እንደተሰበሩ፣ እና መንፈሶቻቸው እንደተዋረዱ የሚያውቁ፣ እና ቃል ኪዳኖቻቸውን [ሐ]በመስዋዕት—አዎን፣ እኔ ጌታ በማዝዘው እያንዳንዱ መስዋእት—ለመከተል [መ]ፈቃደኛ የሆኑት ሁሉ፣ እኔ [ሠ]እቀበላቸዋለሁ።

፱ እኔ ጌታ በመልካም ምድር ውስጥ፣ በንጹህ ወንዝ አጠገብ እንደተተከለ፣ ውድ ፍሬዎች እንደሚሰጥ፣ በጣም ፍሬአማ እንደሆነ ዛፍ እንዲፈሩ አደርጋለሁ።

፲ እውነት እላችኋለሁ፣ በፅዮን ምድር ውስጥ በሰጠኋችሁ [ሀ]ንድፍ መሰረት [ለ]ቤት ይሰራልኝ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፲፩ አዎን፣ በቶሎም በህዝቤ አስራት ይሰራ።

፲፪ እነሆ፣ ለፅዮን ደህንነት [ሀ]ቤት ለእኔ ይሰራ ዘንድ፣ ከእጆቻቸው እኔ ጌታ የምጠብቅባቸው [ለ]አስራትና መስዋዕት ይህ ነው—

፲፫ ለቅዱሳን ሁሉ [ሀ]ምስጋናን የማቅረቢያ ቦታ፣ እና በአገልግሎቱ ስራ በተለያዩት ጥሪአቸው እና ሀላፊነታቸው የተጠሩት ሁሉ የሚማሩበት ቦታ፤

፲፬ በአገልግሎታቸው፣ በአስተያየታቸው፣ በመሰረታዊ መርህ፣ እና በትምህርታቸው፣ እና በላያችሁ የተሰጣችሁ የመንግስቱ [ሀ]ቁልፍ፣ በምድር ላይ ያለው የእግዚአብሔር [ለ]መንግስትን በሚመለከት ሁሉ፣ በዚህ ሁሉ ፍጹም [ሐ]መረዳት ይኖራቸው ዘንድ ነው።

፲፭ እና በጌታ ስም ቤትን ለእኔ እስከሰሩልኝ ድረስ፣ እና እንዳይረከስ፣ ማንኛውንም [ሀ]እርኩስ ነገር እንዲገባበት እስካልፈቀዱ ድረስ፣ [ለ]ክብሬ ያርፍበታል፤

፲፮ አዎን፣ እና በዚያም [ሀ]እገኛለሁ፣ እመጣበታለሁና፣ እና የሚገባበት [ለ]ንጹህ ልብ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያያል።

፲፯ ነገር ግን የረከሰ ቢሆን አልመጣበትም፣ እና ክብሬም አይገኝበትም፤ ቅዱስ ወዳልሆነ ቤተመቅደስ አልመጣምና።

፲፰ እሁንም እነሆ፣ ፅዮን እነዚህን ነገሮች ካደረገች [ሀ]ትበለፅጋለች፣ እና ታድጋለችም እናም በጣም የከበረች፣ በጣም ታላቅ፣ እና በጣም አስፈሪም ትሆናለች።

፲፱ እና የምድር [ሀ]ህዝብም ያከብሯታል፣ እና እንዲህም ይላሉ፥ በእርግጥም [ለ]ፅዮን የእግዚአብሔር ከተማ ነች፣ እና በእርግጥም ፅዮን ልትወድቅ አትችልም፣ ወይም ከስፍራዋ አትወጣም፣ እግዚአብሔር በዚያ ነውና፣ እና የጌታም እጅ በዚያ ነው፤

፳ እና በጉልበቱ ሀይል መድሀኒቷና ታላቅ [ሀ]ማማዋ እንደሚሆን መሀላ ገብቷል።

፳፩ ስለዚህ፣ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ [ሀ]ፅዮን ትደሰት፣ ይህች ፅዮን ነውና—ልበ ንጹህ፤ ስለዚህ፣ ኃጥአን ሁሉ ሲያዝኑ ፅዮን ትደሰት።

፯ ሀ ማቴ. ፫፥፲።
ለ ሉቃ. ፮፥፵፫–፵፭፤ አልማ ፭፥፴፮፤ ፶፪፤ ፫ ኔፊ ፲፬፥፲፭–፳።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. የተሰበረ ልብ።
ለ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣ ታማኝነት።
ሐ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
መ ት. እና ቃ. ፷፬፥፴፬።
ሠ ት. እና ቃ. ፶፪፥፲፭፤ ፻፴፪፥፶።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፭፥፲፬–፲፮።
ለ ት. እና ቃ. ፶፯፥፫፤ ፹፰፥፻፲፱፤ ፻፳፬፥፶፩።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
ለ ቅ.መ.መ. አስራት፣ አስራት መክፈል።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፤ ምስጋና መስጠት።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ሐ ቅ.መ.መ. ማስተዋል።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፺፬፥፱፤ ፻፱፥፳–፳፩።
ለ ሐጌ. ፪፥፯፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፭።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፥፩–፲።
ለ ማቴ. ፭፥፰፤ ት. እና ቃ. ፷፯፥፲–፲፫፤ ፹፰፥፷፰። ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፲፰ ሀ ት. እና ቃ. ፮፥፴፩፤ ፱፥፲፭።
፲፱ ሀ ኢሳ. ፷፥፲፬፤ ዘካ. ፪፥፲–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፮–፸፤ ፵፱፥፲።
ለ ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።
፳ ሀ ፪ ሳሙ. ፳፪፥፫።
፳፩ ሀ ሙሴ ፯፥፲፰። ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት፤ ፅዮን።

፳፪ እነሆም፣ እና አስተውሉ፣ በኃጢአተኞቹ ላይ [ሀ]በቀል እንደ አውሎ ንፋስ ፈጥኖ መጥቷል፤ እና ማንስ ያመልጠዋል?

፳፫ የጌታ [ሀ]መከራም ቀንና ሌሊት ያልፋል፤ ወሬውንም መላውን ህዝብ ያስደነግጣል፤ አዎን፣ ጌታ እስከሚመጣም አይቆምም፤

፳፬ የጌታ ቁጣ በርኩሰታቸውና በክፉ ስራዎቻቸው ሁሉ ላይ ተቀጣጥሏልና።

፳፭ ይህም ቢሆን፣ ፅዮን ያዘዝኳትን ማንኛውም ነገሮች ሁሉ የምትከተል ከሆነችም [ሀ]ታመልጣለች።

፳፮ ነገር ግን፣ ያዘዝኳትን ማንኛውም ነገሮች ሁሉ ባትከተል ግን፣ በሁሉም ስራዎቿ መሰረት በታላቅ ስቃይ፣ [ሀ]ቸነፈር፣ መቅሰፍት፣ በጎራዴ፣ [ለ]በበቀል፣ [ሐ]በምትበላም እሳት [መ]እጎበኛታለሁ።

፳፯ ይህም ቢሆን፣ እኔ ጌታ መስዋዕቴን እንደተቀበልኩ በጆሮዋ ይህ አንድ ጊዜ ይነበብላት፤ እና ኃጢአት ከዚህ በኋላ የማትሰራ ቢሆን ከእነዚህ ነገሮች [ሀ]ማንኛቸውም አይደርሱባትም።

፳፰ እና በበረከቶች [ሀ]እባርካታለሁ፣ እና በእርሷና በትውልዶቿ ላይ ለዘለአለም የሚሆኑ በረከቶች አበዛላታለሁ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ። አሜን።

ክፍል ፺፰

በነሀሴ ፮፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የመጣው በሚዙሪ ቅዱሳን በመሰደዳቸው ምክንያት ነበር። ተጨማሪ የቤተክርስቲያኗ አባላት በምዙሪ መስፈራቸው፣ በቅዱሳን ቁጥሮች፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ተፅዕኖአቸው፣ እና በባህልና በሀይማኖት ልዩነቶች ምክንያት ፍርሀት የነበራቸውን አንዳንድ ሌሎች ሰፋሪዎችን ረብሾ ነበር። በሀምሌ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.)፣ አመጸኛ ህዝብ የቤተክርስቲያኗን ንብረት አፈረሱ፣ ሁለት የቤተክርስቲያኗ አባላትን ሬንጅ ቀብተው በላባ ሸፈኑ፣ እናም ቅዱሳን ከጃክሰን አውራጃ ወጥተው እንዲሄዱ በግድ ጠየቁ። ምንም እንኳ በሚዙሪ የነበሩት ችግሮች ዜና ለነቢዩ በከርትላንድ ውስጥ (በዘጠኝ መቶ ማይል ርቀት) እንደደረሰው ምንም ጥርጣሬ ባይኖርም፣ የጉዳዩ አሳሳቢነት በዚህ ቀን ሊታወቀው የሚችለው በራዕይ ብቻ ነበር።

፩–፫፣ የቅዱሳኑ ስቃይ ለጥቅማቸው ይሆናል፤ ፬–፰፣ ቅዱሳን ለሀገሩ ህገ መንግስት ተባባሪዎች ይሁኑ፤ ፱–፲፣ ታማኝ፣ ብልህ፣ እና መልካም ሰዎች በህዝባዊ መንግስት መደገፍ ይገባቸዋል፤ ፲፩–፲፭፣ በጌታ ምክንያት ህይወታቸውን የሚያጡ ዘለአለማዊ ህይወት ይኖራቸዋል፤ ፲፮–፲፰፣ ጦርነትን አስወግዱ እና ሰላምን አውጁ፤ ፲፱–፳፪፣ የከርትላንድ ቅዱሳን ተገሰጹ እናም ንስሀ እንዲገቡ ታዘዙ፤ ፳፫–፴፪፣ ጌታ በህዝቦቹ ላይ የተጣለባቸውን ስቃይ እና መከራን የሚያስተዳድሩ ህጎቹን ጌታ ገለጠ፤ ፴፫–፴፰፣ ጦርነት ተቀባይነት የሚያገኘው ጌታ ሲያዝዘው ነው፤ ፴፱–፵፰፣ ቅዱሳን፣ ንስሀ ቢገቡ የጌታን በቀል ለማምለጥ ለሚችሉ ጠላቶቻቸውን ይቅርታን ይስጡ።

፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. በቀል።
፳፫ ሀ ኢሳ. ፳፰፥ ፲፬–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥ ፴፩።
፳፭ ሀ ፪ ኔፊ ፯፥ ፲፫–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፳፫፥ ፴፬፤
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥ ፳።
፳፮ ሀ ሉቃ. ፳፩፥ ፲–፲፫።
ለ ሚል. ፬፥ ፩–፫፤
፫ ኔፊ ፳፩፥ ፳–፳፩።
ሐ ኢዩ. ፩፥ ፲፭–፳።
መ ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፺፬–፺፱።
፳፯ ሀ ሕዝ. ፲፰፥ ፳፯።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።

፩ ባልንጀሮቼ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]አትፍሩ፣ ልባችሁ ይፅኑ፤ አዎን፣ ዘወትር ተደሰቱ፣ እና በሁሉም ነገሮች [ለ]ምስጋናን ስጡ፤

፪ ጌታን በትዕግስት [ሀ]ጠብቁ፣ ጸሎቶቻችሁ ወደፀባኦት ጌታ ጆሮዎች ገብተዋል፣ እናም በዚህ ህትመት እና ምስክር ተመዝግበዋልና—እነዚህም እንዲፈጸሙ ጌታ መሀላ ገብቷል እና አውጇል።

፫ ስለዚህ፣ እንዲሟሉም በማይለወጥ ቃል ኪዳን፣ ይህን የተስፋ ቃል ይሰጣችኋል፤ እና [ሀ]የተሰቃያችሁባቸው ነገሮች ሁሉ ለጥቅማችሁ፣ እና ለክብሬ፣ አብረው ይሰራሉ፣ ይላል ጌታ።

፬ አሁንም፣ ስለምድሩ ህግጋት በእውነትም እላችኋለሁ፣ ህዝቤ የማዝዛቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች ሁሉ እንዲያደርጉ ፍቃዴ ነው።

፭ እና መብቶችን እና ልዩ መብቶችን በመጠበቅ የነጻነትን መሰረታዊ መርህ የሚደግፈው፣ [ሀ]ህገ መንግስት የሆነው የምድሩ [ለ]ህግ ለሰው ዘር ሁሉ ነው፣ እና በፊቴም ተገቢ ነው።

፮ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ እናንተና የቤተክርስቲያኔ ወንድሞቻችሁ ለዚያ ለህገሩ ህገ መንግስት ተባባሪዎች መሆናችሁን ተገቢ አደርጋችኋለሁ፤

፯ የሰው ህግን በሚመለከትም፣ ከዚህ በላይ ወይም በታች የሆነው ከክፉ የሚመጣ ነው።

፰ እኔ ጌታ አምላክ ነጻ አደረኳችሁ፤ ስለዚህ በእርግጥም [ሀ]ነጻ ናችሁ፤ እና ህጉም ነጻ አድርጎአችኋል።

፱ ይህም ቢሆን፣ [ሀ]ክፉው ሲያስተዳድር ህዝቡ ያዝናል።

፲ ስለዚህ፣ [ሀ]ታማኝ ሰዎች እና ብልህ ሰዎች በቅንነት ይፈለጉ፣ እና መልካምና ብልህ ሰዎች ለመደገፍ ፈልጉ፤ አለበለዚያም ከዚህ በታች የሆኑት ማንኛውም ከክፉ የመጣ ነው።

፲፩ እና ከእግዚአብሔር አንደበት ከሚመጣው በእያንዳንዱ [ሀ]ቃል እንድትኖሩ ዘንድ፣ ክፉን ሁሉ እንድትተዉና በጥሩ ነገሮች ላይ እንድትጸኑ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፲፪ ታማኝ ለሆነው በሥርዓት ላይ ሥርዓት፣ በትእዛዝም ላይ ትእዛዝ [ሀ]እሰጠዋለሁና፤ እና በዚህም [ለ]እሞክራችኋለሁ እናም እፈትናችኋለሁም።

፲፫ እና ለእኔ ጉዳይ፣ ለስሜ ህይወቱን [ሀ]የሚሰጥም ዳግም ያገኘዋል፣ እንዲሁም ዘለአለማዊ ህይወትን።

፲፬ ስለዚህ፣ ጠላቶቻችሁን [ሀ]አትፍሩ፣ በቃል ኪዳኔ፣ [ለ]እስከሞትም ድረስ፣ እንደምትጸኑ፣ ብቁም ሆናችሁ እንድትገኙ፣ በሁሉም ነገሮች [ሐ]እፈትናችሁ ዘንድ በልቤ አውጇዋለሁና፣ ይላል ጌታ።

፲፭ በቃል ኪዳኔ ካልጸናችሁ ለእኔ ብቁ አይደላችሁም።

፲፮ ስለዚህ፣ [ሀ]ጦርነትን [ለ]አስወግዱና [ሐ]ሰላምንም አውጁ፣ እና የልጆችን ልብ ወደ አባቶች፣ እና የአባቶችንም ልብ ወደ ልጆች [መ]ለመቀየር በቅንነት ፈልጉ፤

፺፰ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፮።
ለ ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፪ሀ መዝ. ፳፯፥፲፬፤
ኢሳ. ፵፥፲፰–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፻፵፫፥፶፭።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፪፥፯።
ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፸፯–፹፤
፻፱፥፶፬።
ቅ.መ.መ. ህገ መንግስት፤ መብት።
ለ ፩ ጴጥ. ፪፥፲፫–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፩፤
፻፴፬፥፭።
፰ሀ ዮሐ. ፰፥፴፪፤ ፪ ቆሮ. ፫፥፲፯።
ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ፤ ነጻ፣ ነጻነት።
፱ሀ ምሳ. ፳፱፥፪።
፲ሀ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣ ታማኝነት።
፲፩ሀ ዘዳግ. ፰፥፫፤ ማቴ. ፬፥፬፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፵፫–፵፬።
፲፪ሀ ኢሳ. ፳፰፥፲፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፰፩።
ለ አብር. ፫፥፳፭–፳፮።
፲፫ሀ ሉቃ. ፱፥፳፬፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥፴፭–፴፰፤
፻፫፥፳፯–፳፰።
ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፲፬ሀ ነሀ. ፬፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፻፳፪፥፱።
ለ ራዕ. ፪፥፲፤
ት. እና ቃ. ፻፴፮፥፴፩፣ ፴፱።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፶፭።
፲፮ሀ ቅ.መ.መ. ጦርነት።
ለ አልማ ፵፰፥፲፬።
ቅ.መ.መ. ሰላም የሚሰራ።
ሐ ቅ.መ.መ. ሰላም።
መ ሚል. ፬፥፭–፮፤
ት. እና ቃ. ፪፥፩–፪።

፲፯ ደግሞም፣ [ሀ]የአይሁዶችን ልብ ወደ ነቢያት፣ እና የነቢያትንም ወደ አይሁዶች፤ አለበለዚያም እመጣና አለምን ሁሉ በእርግማን እመታታለሁ፣ እና በፊቴ ስጋ ለባሽ ሁሉ ይቃጠላል።

፲፰ ልባችሁ አይታወኩ፤ በአባቴ ቤት [ሀ]ብዙ መኖሪያዎች አሉ፤ እና ስፍራን አዘጋጅቼላችኋለሁና፤ እናም አባቴ እና እኔ ባለንበት እናንተም ደግሞ ትሆናላችሁ።

፲፱ እነሆ፣ እኔ ጌታ በከርትላንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉት ብዙዎች አልተደሰትኩም፤

፳ ኃጢአታቸውን፣ እና ክፉ መንገዶቻቸውን፣ የልባቸውን ኩራት፣ እና መጎምጀታችን፣ እና ርኵሰታቸውን አይተውም፣ እና የሰጠኋቸውን የጥበብ እና የዘለአለም ቃላትን አይከተሉም።

፳፩ እውነት እላችኋለሁ፣ ንስሀ ባይገቡ እና ያልኳቸውን ማንኛቸውንም ነገሮች ባታደርጉ፣ እኔ ጌታ [ሀ]እገስጻቸዋለሁ እና የፈቀድኩትን ሁሉ አደርጋለሁ።

፳፪ ደግሜም እላችኋልሁ፣ ያዘዝኳችሁን ማንኛቸውንም ነገሮች [ሀ]ብታደርጉ፣ እኔ ጌታ ቁጣን እና ንዴትን ከእናንተ አርቃለሁ፣ እና የሲዖል [ለ]ደጆችም አያሸንፏችሁም።

፳፫ አሁን፣ ስለቤተሰቦቻችሁ በሚመለከት እናገራችኋለሁ—ሰዎች እናንተን ወይም ቤተሰቦቻችሁን አንዴ [ሀ]ቢመቷችሁ፣ እና በትዕግስት ብትጸኑ እና እነርሱንም ባትሰድቡ ወይም በቀልንም ባታደርጉ፣ ዋጋን ታገኛላችሁ፤

፳፬ ነገር ግን በትዕግስት ባትጸኑ፣ በእናንተ ላይ [ሀ]እንደተመዘነ ትክክለኛ ሚዛን ሆኖ ይቆጠራል።

፳፭ ደግሞም፣ ጠላታችሁ ለሁለተኛ ቢመታችሁ፣ እና ጠላታችሁን ባትሰድቡ፣ እና በትዕግስት ብትጸኑ፣ ዋጋችሁ አንድ መቶ እጥፍ ይሆናል።

፳፮ ደግሞም፣ ለሶስተኛ ጊዜ ቢመታችሁ፣ እና [ሀ]በትዕግስትም ብትጸኑ፣ ዋጋችሁ በአራት እጥፍ ያድጋል፤

፳፯ እና እነዚህ ሶስት ምስክሮችም ንስሀ ባይገባ በጠላታችሁ ላይ ይቆማሉ፣ እናም አይወገዱም።

፳፰ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ያ ጠላት ወደ ፍርድ በፊቴ ባለመምጣቱ ከበቀሌ ካመለጠ፣ ዳግም ወደ እናንት ወይም ወደ ቤተሰባችሁ፣ እንዲሁም እስከ ሶስት እና አራት ትውልዶች ልጅ ልጆቻችሁ እንዳይመጣባችሁ በስሜ [ሀ]አስጠንቅቁት።

፳፱ ከዚያም፣ በእናንተ ወይም በልጆቻችሁ፣ ወይም እስከ ሶስትና አራት ትውልዶች በልጅ ልጆቻችሁ ከመጣባችሁ፣ ጠላታችሁን በእጆቻችሁ አሳልፌ እሰጣችኋለሁ።

፴ ከዚያም ካልቀጣችሁት፣ እናንት ደግሞም ልጆቻችሁ እና እስከ ሶስት እና አራት ትውልዶች የልጅ ልጆቻሁም ለፅድቃችሁ ዋጋን ታገኛላችሁ።

፴፩ ይህም ቢሆን፣ ጠላታችሁ በእጆቻችሁ ውስጥ ነው፤ እና በስራው በኩል ዋጋ ከሰጣችሁት ተገቢን ነገር አደረጋችሁ፤ ህይወታችሁን የሚሻ ቢሆን፣ እና ህይወታችሁ በእርሱ አደጋ ላይ ከሆነ፣ ጠላታችሁ በእጆቻችሁ ውስጥ ነው እና ተገቢንም ነገር አደረጋችሁ።

፴፪ እነሆ፣ ይህም ለአገልጋዬ ኔፊ፣ እና [ሀ]ለአባቶቻችሁ፣ ለዮሴፍ፣ እና ያዕቆብ፣ እና ለይስሀቅ፣ እና ለአብርሐም፣ እና ለቀደሙት ነብያቴ እና ሐዋሪያቴ የሰጠሁት ህግ ነው።

፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
፲፰ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፪፤
ት. እና ቃ. ፶፱፥፪፤
፸፮፥፻፲፩፤ ፹፩፥፮።
፳፩ ሀ ሞዛያ ፳፫፥፳፩፤
ሔለ. ፲፪፥፫።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ማቴ. ፲፮፥፲፯–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፴፫፥፲፪–፲፫።
፳፫ ሀ ሉቃ. ፮፥፳፱፤
አልማ ፵፫፥፵፮–፵፯።
ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።
፳፬ ሀ ማቴ. ፯፥፩–፪።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ማስጠንቀቅ፣
ማስጠንቀቂያ።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲።

፴፫ ደግሞም፣ ከየትኞቹም ሀገሮች፣ ነገዶች፣ ቋንቋዎችና ህዝብ ጋር እኔ ጌታ ካላዘዝኳቸው በስተቀር እንዳይዋጉ ለጥንቶቹ የሰጠሁት [ሀ]ህግ ነው።

፴፬ እና የትኛውም ሀገር፣ ነገድ፣ ወይም ህዝብ በእነርሱ ላይ ጦርነት ቢያውጅ፣ እነርሱ አስቀድመው ለዚያ ህዝብ፣ ሀገር፣ ወይም ቋንቋ [ሀ]የሰላም አርማን ያንሱ፤

፴፭ እና ህዝቦቹ ለሰላም ያቀረቡትን፣ ወይም ሁለተኛውን ወይም ሶስተኛውን፣ ባይቀበሉ፣ እነዚህን ምስክሮች በጌታ ፊት ያምጡ፤

፴፮ ከዚያም እኔ ጌታ ትእዛዝን እሰጣቸዋለሁ፣ እና ከእነዚያ ሀገሮች፣ ቋንቋዎችና ህዝብ ጋር ጦርነትን ቢያደርጉ ድርጊታቸውን ተገቢ ብዬ እቀበለዋለሁ።

፴፯ እና እኔ ጌታ ጦርነታቸውን፣ እና እስከ ሶስት እና አራት ትውልድ፣ የልጆቻቸውን ጦርነት፣ እና የልጅ ልጆቻቸውን ጦርነት፣ በጠላቶቻቸውም ላይ በቀልን እስኪያገኙ ድረስ [ሀ]እዋጋላቸዋለሁ።

፴፰ እነሆ፣ ይህም በፊቴ ተገቢ ይሆን ዘንድ ለሁሉም ህዝብ ምሳሌ ነው፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፴፱ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠላታችሁ ወደ እናንተ ከመጣ በኋላ ንስሀ ቢገባ እና ለምህረት ወደ እናንተ እየለመነ ቢመጣ፣ ይቅርታ አድርጉለት፣ እና በጠላታችሁም ላይ እንደምስክር አትያዙበት—

፵ እናም እስከ ሁለተኛና ሶስተኛ ድረስም ይቀጥል፤ እና ጠላታችሁ በእናንተ ላይ የተላለፈውን ንስሀ እስከገባለት ድረስ፣ እናንተ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት [ሀ]ይቅር በሉት።

፵፩ እና በመጀመሪያው ከተላለፉችሁ እና ንስሀ ካልገባ፣ ይህም ቢሆን ይቅርታ ስጡት።

፵፪ እና ለሁለተኛ ጊዜ ከተላለፉችሁ፣ እና ንስሀን ባይገባ፣ ይህም ቢሆን ይቅርታን ስጡት።

፵፫ እና ለሶስተኛ ጊዜ ቢተላለፉችሁ፣ እና ንስሀን ባይገባ፣ ደግሞም ይቅርታን ስጡት።

፵፬ ነገር ግን ለአራተኛ ጊዜ ቢተላለፉችሁ ይቅርታ አትስጡት፣ ነገር ግን እነዚህን ምስክሮች በጌታ ፊት አምጡ፤ እና ንስሀ እስከሚገባ ድረስ እና በእናንተ ላይ በተላለፈው ነገሮች ሁሉ በአራት እጥፍ ዋጋ እስከሚሰጣችሁ ድረስ አይደመሰሱም።

፵፭ ይህን ቢያደርግ፣ በሙሉ ልባችሁ ይቅርታን ትሰጡታላችሁ፤ እና ይህን ባያደርግ፣ እኔ ጌታ በጠላታችሁ ላይ በአንድ መቶ እጥፍ [ሀ]እበቀላለሁ፤

፵፮ እናም በሚጠሉኝ በልጆቹ ላይ፣ እና በልጅ ልጆቹ ላይ ሁሉ፣ እስከ [ሀ]ሶስትና አራት ትውልድ እበቀላለሁ።

፵፯ ነገር ግን፣ ልጆቹ ወይም የልጅ ልጆች ንስሀ ቢገቡ፣ እና በሙሉ ልባቸው እና በሙሉ ሀይላቸው፣ አዕምሮዋቸው፣ እናም ጉልበታቸው ወደ ጌታ [ሀ]ቢመለሱ፣ እና ለተላለፉት መተላለፊያዎች፣ ወይም አባቶቻቸው፣ ወይም የአባቶቻቸው አባቶች ለተላለፉበት ሁሉ በአራት እጥፍ ደግመው ቢመለሱ፣ ከዚያም የእናንተም ቁጣ ይመለስ፤

፵፰ እና [ሀ]በቀልም አይመጣባቸውም፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፣ እና መተላለፉቸውም በጌታ ፊት እንደ ምስክር በእነርሱ ላይ አይመጡባቸውም። አሜን።

ክፍል ፺፱

በነሀሴ ፳፱፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል

፴፫ ሀ ዘዳግ. ፳፥፲፤
አልማ ፵፰፥፲፬–፲፮።
፴፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፴፰–፵፩።
፴፯ ሀ ኢያ. ፳፫፥፲፤
ኢሳ. ፵፱፥፳፭።
፵ ሀ ማቴ. ፲፰፥፳፩–፳፪፤
ት. እና ቃ. ፷፬፥፱–፲፩።
ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፵፭ ሀ ሞር. ፰፥፳።
፵፮ ሀ ዘዳግ. ፭፥፱–፲።
፵፯ ሀ ሞዛያ ፯፥፴፫፤ ሞር. ፱፥፮።
፵፰ ሀ ሕዝ. ፲፰፥፲፱–፳፫።

ለጆን መርዶክ የተሰጠ ራዕይ። ባለቤቱ ጁሊያ ክላፕ በሚያዝያ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) ከሞተች በኋላ፣ እናት የሌላቸው ልጆቹ ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር እየኖሩ ሳሉ፣ ከአንድ አመት በላይ፣ ጆን መርዶክ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።

፩–፰፣ ጆን መርዶክ ወንጌልን እንዲሰብክ ተጠራ፣ እና እርሱን የሚቀበሉትም ጌታን ይቀበላሉ እና ምህረትንም ያገኛሉ።

፩ እነሆ፣ ለአገልጋዬ ጆን መርዶክ ጌታ እንዲህ ይላል—ወደ ምስራቅ ሀገሮች ከቤት ወደ ቤት፣ ከመንደር ወደ መንደር፣ እና ከከተማ ወደ ከተማ ዘለአለማዊ ወንጌሌን በዚያ ለሚኖሩት፣ [ሀ]በስደት እና በክፋት መካከል እያወጅህ እንድትሄድ ተጠርተሀል።

፪ እና [ሀ]የሚቀበልህም ይቀበለኛል፤ እና በእኔ ቅዱስ መንፈስ [ለ]መገለጥ ቃሌን ለማወጅ ሀይል ይኖርሀል።

፫ እናማንም [ሀ]እንደ ትንሽ ልጅ የሚቀበልህም፣ [ለ]መንግስቴን ይቀበላል፤ እነርሱም ብፁዓን ናቸው፥ [ሐ]ምህረት ያገኛሉና።

፬ እና ማንም አንተን [ሀ]የሚቃወም ከአባቴ እና ከቤቱ ይወገዳል፤ እና በእግረ መንገድህ በእነርሱም ላይ ምስክር ይሆን ዘንድ በተሰወሩ ስፍራዎች [ለ]እግሮችህን ታጸዳለህ።

፭ እነሆ እና አስተውል፣ በመጽሐፍም ጥራዝ እንደ ተጻፈው፣ በእኔ ላይ ከፅድቅ በመራቅ ክፉ ሥራቸው ሁሉ እወቀሳቸው ዘንድ፣ [ሀ]ለፍርድ በቶሎ [ለ]እመጣለሁ።

፮ አሁንም፣ እውነት እልሀለሁ፣ ልጆችህን እስክታስተዳድር እና በመልካም ወደ ፅዮን ኤጲስ ቆጶስ እስኪላኩ ድረስ እንድትሄድ ፍቃዴ አይደለም።

፯ እና ከጥቂት አመታት በኋላ፣ በእኔ የምትሻ ከሆነ፣ ውርስህን ለመቀበል ወደ መልካሚቱ ምድር መሄድ ትችላለህ፤

፰ አለበለዚያ እስከምትወሰድ [ሀ]ድረስ ወንጌሌን በማወጅ ትቀጥላለህ። አሜን።

ክፍል ፻

በጥቅምት ፲፪፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በፔሪስበርግ ኒው ዮርክ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና ለስድኒ ሪግደን የተሰጠ ራዕይ። ሁለቱ ወንድሞች፣ ለብዙ ቀናት ከቤተሰቦቻቸው ተለያይተው ስለነበር፣ ስለእነርሱ አስበው ነበር።

፩–፬፣ ጆሴፍ እና ስድኒ ለነፍሳት ደህንነት ወንጌሉን ይሰበኩ፤ ፭–፰፣ የሚናገሩትም በዚያች ሰዓት ይሰጣቸዋል፤ ፱–፲፪፣ ስድኒ ቃል ተቀባይ ይሁን እና ጆሴፍ ገላጭ እና በምስክርም ሀያል ይሁን፤ ፲፫–፲፯፣ ጌታ ንጹህ ህዝብ ያነሳል፣ እና የሚታዘዙም ይድናሉ።

፩ በእውነት ባልንጀሮቼ [ሀ]ስድኒ እና [ለ]ጆሴፍ፣ ጌታ ለእናንተ እንዲህ ይላል፣ ቤተሰቦቻችሁ ደህና ናቸው፤ በእጆቼም ውስጥ ናቸው፣ እና መልካም እንደሚመስለኝም አደርግባቸዋለሁ በእኔ ሁሉም ሀይል አለና።

፪ ስለዚህ፣ ተከተሉኝ፣ እና የምሰጣችሁንም ምክር አድምጡ።

፺፱ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
፪ሀ ማቴ. ፲፥፵።
ለ ፩ ቆሮ. ፪፥፬–፭።
፫ሀ ማቴ. ፲፰፥፩–፯።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ሐ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፬ሀ ዮሐ. ፲፪፥፵፬–፶።
ለ ት. እና ቃ. ፸፭፥፲፱–፳፪።
፭ሀ ይሁዳ ፩፥፲፬–፲፭።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፲፩–፲፬።
፰ሀ ማቴ. ፲፱፥፳፱።
፻ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ለ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ።

፫ እነሆ፣ እናም አስተውሉ፣ በዚህ ስፍራ፣ በዚህ ክፍለ ሀገር አካባቢ ብዙ ህዝብ አሉኝ፤ እና ውጤታማ በር በዚህ አካባቢ፣ በዚህ በምስራቅ ምድር ውስጥ ይከፈታል።

፬ ስለዚህ፣ እኔ ጌታ ወደዚህ ስፍራ ትመጡ ዘንድ ፈቀድኩኝ፤ ለነፍሳትም [ሀ]ደህንነት ይህም በእኔ ዘንድ አስፈላጊ ነበርና።

፭ ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ወደ እነዚህ ህዝብ ድምጾቻችሁን ከፍ አድርጉ፤ በልባችሁ የምጨምረውን ሀሳብ [ሀ]ተናገሩ፣ እና በሰዎችም ፊት አታፍሩም፤

፮ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት፣ አዎን፣ በዚያች ጊዜም፣ ምን እንደምትናገሩ [ሀ]ይሰጣችኋልና።

፯ ነገር ግን የምታውጁትን ማንኛውንም ነገር በስሜ፣ በሁሉም ነገሮች በተረጋጋ ልብ፣ [ሀ]በትሁት መንፈስ [ለ]ታውጁ ዘንድ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።

፰ እና ይህን የተስፋ ቃል እሰጣችኋለሁ፣ ይህን ስታደርጉ ለምትሉት ማንኛቸውም ነገሮች ሁሉ ምስክር ይሰጣችሁ ዘንድ [ሀ]መንፈስ ቅዱስ ይላካል።

፱ እና አንተ አገልጋዬ ስድኒ ለዚህ ህዝብ [ሀ]ቃል ተቀባይ እንድትሆን ፍቃዴ ነው፤ አዎን፣ በእውነትም በዚህ ሀላፊነት፣ እንዲሁም እንደ አገልጋዬ ጆሴፍ ቃል ተቀባይ እንድትሆኑ፣ እሾምሀለሁ።

፲ እና ለእርሱም [ሀ]በምስክር ሀያል እንዲሆን ሀይል እሰጠዋለሁ።

፲፩ እና ቅዱሳን መጻህፍትን ሁሉ ለመዘርዘር [ሀ]ሀያል እንድትሆንም ዘንድ፣ ለእርሱም ቃል ተቀባይ እንድትሆን ዘንድ ሀይልን እሰጥሀለሁ፣ እና በምድር ላይ ስላለችው መንግስቴ ነገሮች በሚመለከት የሁሉም ነገሮች እርግጠኛነትን ታውቅ ዘንድ እርሱም ለአንተ [ለ]ገላጭ ይሆናል።

፲፪ ስለዚህ፣ በጉዞአችሁ ቀጥሉ እና ልባችሁ ይደሰቱ፤ እነሆ፣ እና አስተውሉ፣ እኔ እስከመጨረሻም ከእናንተ ጋር ነኝና።

፲፫ አሁንም [ሀ]ፅዮንን በተመለከት ቃልን እሰጣችኋለሁ። ምንም እንኳን ለጥቂት ዘመን ብትገሰፅም፣ ፅዮን [ለ]ትድናለች።

፲፬ ወንድሞቻችሁ፣ አገልጋዮቼ [ሀ]ኦርሰን ሀይድ እና ጆን ጉልድ፣ በእጆቼ ውስጥ ናቸው፤ እና ትእዛዛቴን እስከጠበቁ ድረስ ይድናሉ።

፲፭ ስለዚህ፣ ልባችሁ ይፅናኑ፤ በቅንነት ለሚራመዱት፣ እና ለቤተክርስቲያኗ ቅድስና እና ጥቅም [ሀ]ሁሉም ነገሮች አብረው ይሰራሉና።

፲፮ ለራሴም በፅድቅ የሚያገለግሉኝ [ሀ]ንጹህ ህዝብ አስነሳለሁና፤

፲፯ እና የጌታን ስም [ሀ]የሚጠሩት፣ እና ትእዛዛቱን የሚጠብቁ ሁሉ ይድናሉ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፩

በታህሳስ ፲፮ እና ፲፯፣ ፲፰፻፴፫ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ በሚዙሪ የተሰበሰቡት ቅዱሳን በታላቅ ስደት ላይ ነበሩ። ለአመፅ የተነሱ ህዝብ እነርሱን በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ ካሉት ቤቶ

፬ ሀ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፭ ሀ ሐሌ. ፭፥፲፰፤
ት. እና ቃ. ፳፰፥፫–፬።
፮ ሀ ማቴ. ፲፥፲፱–፳፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፹፭።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ገር፤ ገርነት።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፷፩።
፰ ሀ ፪ ኔፊ ፴፫፥፩–፬።
፱ ሀ ዘፀአ. ፬፥፲፬–፲፮፤
፪ ኔፊ ፫፥፲፯–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፫–፻፬።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. መመስከር።
፲፩ ሀ አልማ ፲፯፥፪–፫።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፳፭።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፺፱፤
፻፭፥፱–፲፣ ፴፩፣ ፴፯።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይድ፣ ኦርሰን።
፲፭ ሀ ሮሜ ፰፥፳፰፤
ት. እና ቃ. ፺፥፳፬፤ ፻፭፥፵።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፲፯ ሀ ኢዩ. ፪፥፴፪፤
አልማ ፴፰፥፬–፭።

ቻቸው አሣደዋቸዋል እና አንዳንድ ቅዱሳን ራሳቸውን በቫን ቢዩረን፣ ላፈየት፣ እና ሬይ የግዛት ክፍሎች ውስጥ ለማሰባሰብ ሞከሩ፣ ነገር ግን ስደቱ ተከተላቸው። በዚያ ጊዜ የቅዱሳኑ ዋና ክፍል በክሌይ የግዛት ክፍል ሚዙሪ ውስጥ ነበር። በቤተክርስቲያኗ ግለሰቦች ላይም ብዙ የሞት ማስፈራሪያዎች ነበሩ። የጃክሰን የግዛት ክፍል ቅዱሳን የቤት እቃዎቻቸውን፣ ልብሶቻቸውን፣ ከብቶቻቸውን፣ እና ሌሎች የግል ንብረቶቻቸውን አጥተው ነበር፤ እና ብዙዎቹም እህሎቻቸውም ተደምስሠውባቸው ነበር።

፩–፰፣ ቅዱሳን የተገሰጹት እና የተሰቃዩት በመተላለፋቸው ምክንያት ነው፤ ፱–፲፭፣ የጌታ ቁጣ በህዝብ ላይ ያርፋል፣ ነገር ግን ህዝቦቹ ይሰበሰባሉ እና ይፅናናሉ፤ ፲፮–፳፩፣ ፅዮን እና ስቴኳ ይመሰረታሉ፤ ፳፪–፴፩፣ በአንድ ሺህ አመት ጊዜ ህይወት ምን እንደሚመስል ተገልጿል፤ ፴፪–፵፪፣ በዚያም ጊዜ ቅዱሳን ይባረካሉ እናም ዋጋን ይቀበላሉ፤ ፵፫–፷፪፣ የልኡል ሰው እና የወይራ ዛፍ ምሳሌ የፅዮንን ችግር እና የመጨረሻም ደህንነትን ያመለክታል፤ ፷፫–፸፭፣ ቅዱሳኑ አብረው መሰብሰባቸውን ይቀጥሉ፤ ፸፮–፹፣ ጌታ የዩናትድ ስቴትን ህገ መንግስት መስርቷል፤ ፹፩–፻፩፣ ቅዱሳንን፣ እንደ ሴቷ እና እንዳልጸደቀው ዳኛ ምሳሌ መሰረት፣ ቅዱሳንን ለስቃያቸው ክፍያ በቅንነት ይጠይቁ።

፩ ስለተቸገሩት፣ [ሀ]ስለተሰደዱ፣ እና ከውርስ መሬታቸው [ለ]ተወርውረው ስለወጡት ወንድሞቻችሁ እውነት እላችኋለሁ—

፪ እኔ ጌታ [ሀ]የተሰቃዩበት ስቃይ [ለ]በመተላለፋቸው ምክንያት እንዲመጣባቸው ፈቅጃለሁ፤

፫ ግን [ሀ]የእኔ አደርጋቸዋለሁ፣ እና መጥቼ ጌጤን በምሰራበት በዚያን ቀን የእኔ ይሆናሉ።

፬ ስለዚህ አንድያ ልጁን ለመስዋት እንዲያቀርብ እንደታዘዘው [ሀ]አብርሐም [ለ]መገሰፅና መፈተን አለባቸው።

፭ በግሰጻው የማይጸኑት፣ ግን [ሀ]የሚከዱኝ፣ ሁሉ [ለ]ሊቀደሱ አይችሉም።

፮ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ክርክር፣ እና [ሀ]ጸብ፣ እና [ለ]ቅናት፣ እና ጠብ፣ እና [ሐ]የመቋመጥ እና የመመኘት ፈቃድ በመካከላቸው ነበር፤ ስለዚህ በእነዚህ ነገሮች ውርሶቻቸውን በክለዋል።

፯ የጌታ አምላካቸውን ድምፅ [ሀ]ለማድመጥ ይዘገዩ ነበር፤ ስለዚህ፣ ጌታ አምላካቸው ጸሎታቸውን ያደምጥ ዘንድ፣ በችግር ቀናቸውም ይልስላቸው ዘንድ ዘግይቷል።

፰ በሰላም ቀናቸው ምክሬን ትንሽ ዋጋ እንዳለው ተመለከቱት፤ ነገር ግን፣ [ሀ]በችግራቸው ቀን፣ ሲያስፈልጋቸው [ለ]ይፈልጉኛል።

፱ እውነት እላችኋለሁ፣ ኃጢአቶቻቸው ቢያስቆጡም፣ ለእነርሱ አንጀቴ [ሀ]በርህራሄ ተሞልቷል። ሙሉ ሁሉ [ለ]አላስወግዳቸውም፤ እና [ሐ]በቁጣም ቀን በምህረት አስታውሳቸዋለሁ።

፻፩ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፫፥፩–፪፣ ፲፩፤ ፻፱፥፵፯።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፺፰፥፫–፬።
ለ ሞዛያ ፯፥፳፱–፴፤ ት. እና ቃ. ፻፫፥፬፤ ፻፭፥፪–፲።
፫ሀ ኢሳ. ፷፪፥፫፤ ሚል. ፫፥፲፯፤ ት. እና ቃ. ፷፥፬።
፬ሀ ዘፍጥ. ፳፪፥፩–፲፬፤ ያዕቆ. ፬፥፭። ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ለ ት. እና ቃ. ፻፭፥፩–፪፤ ፻፴፮፥፴፩። ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፭ሀ ማቴ. ፲፥፴፪–፴፫፤ ሮሜ ፩፥፲፮፤ ፪ ኔፊ ፴፩፥፲፬።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፮ሀ ቅ.መ.መ. ጸብ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅናት።
ሐ ቅ.መ.መ. ምኞት።
፯ሀ ኢሳ. ፶፱፥፪፤ ሞዛያ ፲፩፥፳፪–፳፭፤ ፳፩፥፲፭፤ አልማ ፭፥፴፰።
፰ሀ ሔለ. ፲፪፥፫።
ለ የሐዋ. ፲፯፥፳፯፤ አልማ ፴፪፥፭–፲፮።
፱ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት፤ ርህራሄ።
ለ ኤር. ፴፥፲፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፺፰፥፳፩–፳፪።

፲ መሀላ ገብቻለሁ፣ እና የቁጣዬ [ሀ]ጎራዴ ለህዝቤ እንደሚወድቅ ከዚህ በፊት በሰጠኋችሁ ትእዛዝም መሰረት አዋጁ ወጥቷል፣ እና እንዳልኩትም፣ ይሆናል።

፲፩ ቁጣዬ በሁሉም ህዝብ ላይ ያለሚዛን በቅርብም ይፈሳል፤ እና ይህን የማደርገውም የጥፋታቸው ጽዋ [ሀ]ሲሞላ ነው።

፲፪ እና በዚያ ቀን [ሀ]በመመልከቻ ማማ ላይ የሚገኙት ሁሉ፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ የእኔ የሆኑት እስራኤል ሁሉ ይድናሉ።

፲፫ እና የተበተኑት ሁሉ [ሀ]ይሰበሰባሉ።

፲፬ እና [ሀ]የሚያዝኑትም ሁሉ መፅናናትን ያገኛሉ።

፲፭ እና ለስሜ [ሀ]ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡም ሁሉ አክሊል ይጫንላቸዋል።

፲፮ ስለዚህ፣ ፅዮንን በሚመለከት ልባችሁ ይፅናኑ፤ ሁሉም ስጋዎች [ሀ]በእጆቼ ውስጥ ናቸውና፤ ዕረፉ እና እኔም አምላክ እንደሆንሁ [ለ]እወቁ፤

፲፯ ልጆቿ ቢበተኑም፣ [ሀ]ፅዮን ከስፍራዋ አትወጣም።

፲፰ የሚቀሩት እና ንጹህ ልብ ያላቸው፣ ይመለሳሉ እና እነርሱና ልጆቻቸው በዘለአለማዊ ደስታ [ሀ]መዝሙሮች፣ በፅዮን የፈረሱትን [ለ]ለመገንባት [ሐ]ወደውርሳቸው ይመጣሉ—

፲፱ እና እነዚህ ነገሮች ሁሉ ነቢያት ይፈጽሙ ዘንድ ነው።

፳ እነሆም፣ ከመደብኩት [ሀ]ስፍራ በስተቀር የተመደበ ምንም ሌላ ስፍራ የለም፤ ወይም፣ ለቅዱሳን መሰብሰቢያ ስራ፣ ከመደብኩት ስፍራ ሌላ የሚመደብ ምንም ስፍራ የለም—

፳፩ ለእነርሱ በቂ ክፍል የማይገኝበት ቀን እስኪመጣም ድረስ፤ ከዚያም እኔ የምመድብላቸው ሌሎች ስፍራዎች አሉኝ፣ እና ለፅዮን ይጋርዱ እና ብርታቷም ይሆኑ ዘንድ፣ እነዚህም [ሀ]ካስማ ተብለው ይጠራሉ።

፳፪ እነሆ፣ ስሜን የሚጠሩ፣ እና በዘለአለማዊ ወንጌሌ መሰረት የሚያመልኩኝ ሁሉ [ሀ]እንዲሰበሰቡና በተቀደሱ ስፍራዎች [ለ]እንዲቆሙ ፍቃዴ ነው፤

፳፫ እና ለሚመጣው ራዕይም ተዘጋጁ፣ በድንኳኔ ውስጥ፣ ምድርን የሚደብቀው፣ ቤተመቅደሴን የሚሸፍነው [ሀ]መጋረጃ ይወልቃል፣ እና ስጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት [ለ]ያዩኛል።

፳፬ እና [ሀ]የሚበሰብሱ እያንዳንዱ ነገሮች፣ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች፣ ወይም የሜዳ እንስሳት፣ ወይም የሰማይ አዕዋፋት፣ ወይም የባሕር ዓሦች ሁሉ [ለ]ይነድዳሉ፤

፳፭ ደግሞም አለቶችም በትልቅ ትኩሳት [ሀ]ይቀልጣሉ፤ እና እውቀቴና [ለ]ክብሬ በምድር ሁሉ እንዲኖሩ፣ ሁሉም ነገሮች [ሐ]አዲስ ይሆናሉ።

፳፮ እና በዚያም ቀን የሰዎች [ሀ]ጥላቻ፣ የእ

፲ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬።
፲፩ ሀ ሔለ. ፲፫፥፲፬፤
ኤተር ፪፥፱–፲፩።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፲፫ ሀ ዘዳግ. ፴፥፫–፮፤
፩ ኔፊ ፲፥፲፬።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፲፬ ሀ ማቴ. ፭፥፬።
፲፭ ሀ ማቴ. ፲፥፴፱።
ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣
ሰማዕትነት።
፲፮ ሀ ሙሴ ፮፥፴፪።
ለ ዘፀአ. ፲፬፥፲፫–፲፬፤
መዝ. ፵፮፥፲።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፲፰ ሀ ኢሳ. ፴፭፥፲፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፸፩።
ቅ.መ.መ. መዘመር።
ለ ዓሞ. ፱፥፲፫–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፪–
፭፤ ፻፫፥፲፩።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፫፥፲፩–፲፬።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፬።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፫–፲፬፤
፻፲፭፥፮፣ ፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
ለ ማቴ. ፳፬፥፲፭፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፴፪፤
፻፲፭፥፮።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ።
ለ ኢሳ. ፵፥፭፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፰፤ ፺፫፥፩።
ቅ.መ.መ. የኢየሱስ
ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፳፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፳፬።
ለ ሶፎ. ፩፥፪–፫፤
ሚል. ፬፥፩፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፺፬፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፯።
፳፭ ሀ ዓሞ. ፱፥፭፤
፪ ጴጥ. ፫፥፲–፲፬።
ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።
ለ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ሐ ራዕ. ፳፩፥፭።
፳፮ ሀ ኢሳ. ፲፩፥፮–፱።
ቅ.መ.መ. ጠላትነት።

ንስሳትም ጥላቻ፣ አዎን፣ የሁሉም ስጋ ለባስ ጥላቻ ከፊቴ [ለ]ይቋረጣል።

፳፰ እና በዚያም ቀን ማንም ሰው ያሻውን ቢጠይቅ፣ ይሰጠዋል።

፳፰ እና በዚያም ቀን [ሀ]ሰይጣንም ሰውን ለመፈተን ሀይል አይኖረውም።

፳፱ እና [ሀ]ሀዘንም አይኖርም ምክንያቱም ሞት የለምና።

፴ በዚያም ቀን [ሀ]ህጻን አርጅቶ ካልሆነ በቀር አይሞትም፤ እና ህይወቱም እንደ ዛፍ ህይወት ይሆናል፤

፴፩ እና ሲሞትም አያንቀላፋም፣ ያም በምድር ውስጥ አይቆይም፣ ነገር ግን በቅጽበት ዓይን [ሀ]ይለወጣል፣ እና [ለ]ይነጠቃል፣ እና ማረፊያውም የከበረ ይሆናል።

፴፪ አዎን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ጌታ በሚመጣበት በዚያ [ሀ]ቀን፣ ሁሉንም ነገሮች [ለ]ይገልጣል—

፴፫ ያለፉትን ነገሮች፣ እና ማንም ሰው የማያውቃቸውን [ሀ]የተደበቁ ነገሮችን፣ የምድር ነገሮችን፣ የተሰራበትን፣ እና አላማቸውን እና እቅዳቸውንም ይገልጣል—

፴፬ በጣም ውድ ስለሆኑ ነገሮች፣ ከበላይ ስላሉ ነገሮች፣ እና ከበታች ስላሉ ነገሮች፣ በምድር ውስጥ፣ እና በምድር ላይ፣ እና በሰማይ ውስጥ ስላሉ ነገሮችም ይገልጣል።

፴፭ እና ስለስሜ [ሀ]በመሰደድ የተሰቃዩት ሁሉ፣ እና በእምነት የሚፅናኑት፣ ምንም እንኳን ህይወታቸውን [ለ]ስለእኔ እንዲሰጡ ቢጠሩም በዚህ ክብር ሁሉ ተካፋዮች ይሆናሉ።

፴፮ ስለዚህ፣ [ሀ]እስከሞትም አትፍሩ፤ በዚህ አለም ደስታችሁ ሙሉ አይደለምና፣ ነገር ግን በእኔ [ለ]ደስታችሁ ሙላት አለው።

፴፯ ስለዚህ፣ ስለሰውነት አታስቡ፣ ወይም ስለሰውነት ህይወት፤ ነገር ግን [ሀ]ለነፍስ፣ እና ስለ ነፍስ ህይወትም አስቡ።

፴፰ እና [ሀ]በትዕግስት ነፍሶቻችሁን ታገኙ ዘንድ፣ የጌታን ፊት ዘወትር [ለ]እሹ፣ እና ዘለአለማዊ ህይወትም ይኖራችኋል።

፴፱ ሰዎች [ሀ]ወደ ዘለአለማዊ ወንጌሉ ሲጠሩ፣ እና በዘለአለማዊነትም ቃል ኪዳንን ሲገቡ፣ እንደምድር [ለ]ጨው እና የሰዎች ጣዕም ሆነው ይቆጠራሉ።

፵ የሰዎች ጣዕም እንዲሆኑም ይጠራሉ፤ ስለዚህ፣ ያ የምድር ጨው ጣዕሙን ካጣ፣ እነሆ፣ ጨውም ከዚያን ጊዜ በኋላ ከንቱ ይሆናል፣ ነገር ግን ይጣላል፣ እናም በሰዎች እግርም ይረገጣል።

፵፩ እነሆ፣ ስለፅዮን ልጆች፣ እንዲሁም ሁሉም ሳይሆን ብዙዎቹን፣ የሚመለከት ጥበብ ይህም ነው፤ ተላላፊዎች ሆነው ተገኝተዋል፣ ስለዚህ [ሀ]መገሰፅም ያስፈልጋቸዋል—

፵፪ ራሱን [ሀ]ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፣ ራሱንም [ለ]የሚያዋርድ ከፍ ይላል።

፵፫ አሁንም፣ ስለፅዮን ቤዛነት በሚመለከት ፈቃዴን ታውቁ ዘንድ፣ ምሳሌ አሳያችኋለሁ።

፵፬ አንድ [ሀ]መኮንን በጣም ምርጥ የሆነ ምድር ነበረው፤ እና ለአገልጋዮቹም እንዲህ ይላል፥ ወደ [ለ]ወይን ስፍራዬ፣ እንዲሁም ወደዚህ በጣም ወደ ተመረጠ ምድር

፳፯ ለ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፳፰ ሀ ራዕ. ፳፥፪–፫፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፳፮፤
ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲።
፳፱ ሀ ራዕ. ፳፩፥፬።
፴ ሀ ኢሳ. ፷፭፥፳–፳፪፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥፶፩።
፴፩ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፶፪፤
ት. እና ቃ. ፵፫፥፴፪።
ለ ፩ ተሰ. ፬፥፲፮–፲፯።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፩።
ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፳፰–፳፫።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር ሚስጥሮች።
፴፭ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳።
ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ለ ት. እና ቃ. ፺፰፥፲፫።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ስጋዊ ሞት።
ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ነፍስ።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ትዕግስት።
ለ ፪ ዜና ፯፥፲፬፤
ት. እና ቃ. ፺፫፥፩።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ለ ማቴ. ፭፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፻፫፥፲።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፵፪ ሀ አብድ. ፩፥፫–፬፤
ሉቃ. ፲፬፥፲፩፤
ሔለ. ፬፥፲፪–፲፫።
ለ ሉቃ. ፲፰፥፲፬።
ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፵፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፫፥፳፩–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።

ሂዱ፣ እና አስራ ሁለት የወይራ ዛፎችንም ትከሉ፤

፵፭ እና ጠላት ለማጥፋትና የወይን ስፍራዬን ፍሬ ለራሳቸው ለመውሰድ ሲመጡ፣ የወይራ ዛፎቼን እንዳይሰበሩ ዘንድ፣ በማማው ላይ [ሀ]ጠባቂዎች ይሆኑላችሁ ዘንድ፣ በአካባቢያቸውም ጠባቂዎችን አኑሩ፣ እና በዙሪያውም የሚገኘውን ምድር በሚመለከት ማማን ስሩ።

፵፮ አሁን፣ የመኮንኑ አገልጋዮች ጌታቸው እንዳዘዛቸው ሄደው አደረጉ፣ እና የወይራ ዛፎችን ተከሉ፣ እና በዙሪያም ቅጥርን ሰሩ፣ እና ጠባቂም አስቀመጡ፣ እና ማማ መስራትም ጀመሩ።

፵፯ እና የዚህን መሰረት እየገነቡ እያሉ፣ እርስ በራሳቸው እንዲህ መባባል ጀመሩ፥ ለጌታዬ ይህ ማማ ምን ይሰራለታል አለው?

፵፰ እና ለብዙም ጊዜ እርስ በራሳቸው እንዲህ በመባባል ተማከሩ፥ የሰላም ጊዜ እንደሆነ እያየ፣ ጌታዬ ከዚህ ማማ ምን ጉዳይ አለው?

፵፱ ገንዘቡ ለለዋጮች አደራ ቢሰጥ አይሻልምን? ለእነዚህ ነገሮች ምንም የሚያስፈልጉ አይደሉምና።

፶ እና እርስ በራሳቸው ባለመስማማት እያሉ በጣም ሀኬተኛ ሆኑ፣ እና የጌታቸውንም ትእዛዝ አላደመጡምና።

፶፩ እና ጠላትም በምሽት መጣ፣ እና [ሀ]ቅጥሩንም ሰበረ፤ እና የመኮንኑ አገልጋዮችም ተነሱ እና ፈሩ፣ እና ሸሹ፤ እና ጠላትም ስራቸውን አፈረሰው፣ እና የወይራ ዛፎችንም ሰበረ።

፶፪ አሁን፣ እነሆ፣ መኮንኑ፣ የወይኑ ስፍራ ጌታ፣ አገልጋዮቹን ጠራ፣ እናም አላቸው፣ ለምን! የዚህ ታላቅ ጥፋት ምክንያት ምንድን ነው?

፶፫ እና የወይን ስፍራውን ከተከላችሁ፣ እና አጥርንም በዙሪያው ካጠራችሁ፣ እና በግምቡ ላይ ጠባቂን ካስቀመጣችሁ በኋላ ማማን ስሩ፣ እና በማማውም ጠባቂን አስቀምጡ፣ እና የወይን ስፍራዬንም ጠብቁ፣ እና ጠላትም እንዳይመጣባችሁ አታንቀላፉ ብዬ እንዳዘዝኳችሁ አታደርጉም ነበርን?

፶፬ እነሆም፣ በማማው ላይ የነበረው ጠባቂ በሩቅ እያለ ጠላትን ገና በሩቅ ሳለ ያየው ነበር፤ ከዚያም ትዘጋጁ እና ጠላትንም አጥሩን ከመስበር ልታቆሙት፣ እና ከደምሳሹ እጆችም የወይን ስፍራዬን ልታድኑ በቻላችሁ ነበር።

፶፭ እና የወይን ስፍራው ጌታ ከአገልጋዮቹ ለአንዱ አለ፥ ሂድ እና የሚቀሩትን አገልጋዮቼን ሰብስብ፣ እና የቤቴ ብርታት የሆኑትን ጀግኖቼን፣ ወጣት ወንዶቼን፣ እና ከአገልጋዮቼ መካከልም ጎልማሳዎች የሆኑትን የቤቴን ብርቱዎች [ሀ]ሁሉ ውሰድ፣ እንዲቀሩ የመደብኳቸውን ብቻ አስቀር፤

፶፮ እና በቀጥታም ወደወይን ስፍራ መሬቴም ሂድ፣ እና የወይን ስፍራዬን አድን፤ የእኔ ነውና፤ በገንዘብም ገዝቼዋለሁና።

፶፯ ስለዚህ፣ ወደ መሬቴ በቀጥታ ሂድ፣ የጠላቶቼን ግንብ ስበር፤ ማማቸውንም ጣል፣ እና ጠባቂያቸውንም በትን።

፶፰ እና አንተን ለመቃወም እስከተሰበሰቡ ድረስ፣ በአጭር ጊዜ ከሚቀረው ቤቴ ጋር መጥቼና መሬቴን እንድወስደው ዘንድ፣ በጠላቶቼ ላይ [ሀ]ፍረድልኝ።

፶፱ እና አገልጋዩም ለጌታው አለ፥ እነዚህ ነገሮች መቼ ይሆናሉ?

፷ እና ለአገልጋዩም አለ፥ በቀጥታ ሂድ፣ እና እንደፈቀድኩትም ያዘዝኩህን ማንኛቸውን ነገሮች ሁሉ አድርግ፤

፷፩ እና ይህም—በቤቴ መካከል ታማኝና ብልህ [ሀ]መጋቢ፣ በመንግስቴም ውስጥ [ለ]ገዢ በሆንከው በአንተ ላይ ማህተሜ እና በረከቴ ይሆናል።

፵፭ ሀ ሕዝ. ፴፫፥፪፣ ፯፤
፫ ኔፊ ፲፮፥፲፰።
ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፶፩ ሀ ኢሳ. ፭፥፩–፯።
፶፭ ሀ ት. እና ቃ. ፻፫፥
፳፪፣ ፳፱–፴፤
፻፭፥፲፮፣ ፳፱–፴።
፶፰ ሀ ት. እና ቃ. ፺፯፥፳፪–፳፬፤
፻፭፥፲፭።
፷፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፳፪።
ለ ማቴ. ፳፭፥፳–፳፫።

፷፪ እና አገልጋዩም በቀጥታ ሄደ፣ እና ጌታው ያዘዘውን ማንኛቸውን ነገሮች ሁሉ አደረገ፤ እና ከብዙ ቀናትም [ሀ]በኋላ ሁሉም ነገሮች ተፈጸሙ።

፷፫ ዳግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በትክክል እና በተገቢ መንገድ ወደ ደህንነታቸው ለመመራት ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ፣ ስለቤተክርስቲያናት ሁሉ የሚመለከት ጥበቤን አሳያችኋለሁ—

፷፬ የቅዱሳኖቼ መሰብሰቢያ ስራ ይቀጥል ዘንድ፣ በስሜም [ሀ]በቅዱስ ቦታዎች እንገነባቸው ዘንድ፤ [ለ]የመከር ጊዜ መጥቷል፣ እና ቃሌም [ሐ]መፈጸም አለበት።

፷፭ ስለዚህ፣ ወደአባቴ መንግስት እንደ ስራው ደመወዝን ልሰጠው ስመጣ፣ በስንዴዎች እና [ሀ]እንክርዳዶች ምሳሌ መሰረት፣ ስንዴዎች በጎተራው እንዲሰበሰቡ እና የዘለአለም ህይወት ያገኙ ዘንድ፣ እና [ለ]በሰለስቲያል ክብር አክሊል እንዲሰጣቸው፣ ህዝቤን መሰብሰብ አለብኝ፤

፷፮ በማይጠፋ እሳት [ሀ]ይቃጠሉ ዘንድ፣ እንክርዳዶችም አንድ ላይ ይታሰራሉ፣ እና ማሰሪአቸውም ጠንካራ ይሆናል።

፷፯ ስለዚህ፣ በመደብኩት ስፍራ አብረው ለመሰብሰብ ይቀጥሉ ዘንድ፣ ለሁሉም ቤተክርስቲያኖች ትእዛዝን እሰጣለሁ።

፷፰ ይህም ቢሆን፣ በፊቱ ትእዛዝ እንዳልኳችሁ፣ [ሀ]መሰብሰቢያችሁ በችኮላ ወይም በሽሽት አይሁን፤ ነገር ግን በፊታችሁ ሁሉም ነገሮች ይዘጋጁ።

፷፱ እና ሁሉም ነገሮች በፊታችሁ ይዘጋጁ ዘንድ፣ ስለእነዚህ ነገሮች የሰጠኋችሁን ትእዛዝ አክብሩ—

፸ እንዲህ ያለውን ወይም የሚያስተምረውን፣ ለቅዱሳኔ መሰብሰብ መጀመሪያ እንዲሆን፣ የፅዮን ምድር እንዲሆን በመደብኩት ምድር አካባቢ በገንዘብ [ሀ]ለመግዛት የሚቻለውን መሬቶችን ሁሉ በገንዘብ ለመግዛት ያለውን ወይም የሚያስተምረውን፤

፸፩ በጃክሰን የግዛት ክፍል፣ እና በዙሪያው በሚገኙት የግዛት ክፍሎች፣ ሊገዛ የሚቻለውን መሬት ሁሉ፣ እና የሚቀረውን በእጄ ተዉት።

፸፪ አሁን እውነት እላችኋለሁ፣ ሁሉም ቤተክርስቲያናት ገንዘባቸውን ሁሉ አብረው ይሰብስቡ፤ [ሀ]በችኮላ ሳይሆን፣ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በጊዜአቸው ይደረጉ፤ እና በፊታቸሁ ሁሉንም ነገሮች እንዲዘጋጁ አድርጉ።

፸፫ እና የተከበሩ ሰዎች፣ እንዲሁም ብልህ ሰዎች፣ ይመደቡ፣ እና እነዚህን መሬቶች እንዲገዙ ላኳቸው።

፸፬ እና በምስራቅ አገሮች ያሉ ቤተክርስቲያናትም፣ ከተመሰረቱ በኋላ፣ ይህን ምክር ካደመጡ መሬቶችን መግዛትና መሰብሰብ ይችላሉ፤ እና በዚህም መንገድ ፅዮንን ይመስርቱ።

፸፭ አሁንም፣ በስሜ የሚጠሩት ቤተክርስቲያናት ድምጼን ለማድመጥ [ሀ]ፈቃደኞች ቢሆኑ፣ ፅዮንን ለማዳን እና፣ ደግሞም እንዳይጣሉ የፈረሱትን ስፍራዎቿን ለመመስረት በብቁ፣ እንዲሁም በሚትረፈረፍ፣ ተከማችቷል።

፸፮ ደግሞም እላችኋለሁ፣ በጠላቶቻቸው የተበተኑትም እንደገዢ በተመደቡት እጆች እና በእናንተ ላይ ስልጣን ባላቸው ሰዎች በኩል ለስቃያቸው ክፍያ፣ እና ለቤዛነት በቅንነት እንዲጠይቁ ፍቃዴ ነው—

፸፯ የፅድቅ እና ቅዱስ በሆኑ መሰረታዊ መርሆች፣ እንዲመሰረት እና ለሁሉም ስጋ ለባሽ [ሀ]መብት እና ጥበቃ እንዲደገፍ በፈቀድኩት በህዝብ ህግጋት እና [ለ]ህገ መንግስት መሰረት፤

፸፰ ሁሉም ሰው ስለወደፊቱ፣ በሰጠሁት

፷፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፴፯።
፷፬ ሀ ት. እና ቃ. ፹፯፥፰።
ለ ት. እና ቃ. ፴፫፥፫፣ ፯።
ቅ.መ.መ. መከር።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፥፴፰።
፷፭ ሀ ማቴ. ፲፫፥፮–፵፫፤
ት. እና ቃ. ፹፮፥፩–፯።
ለ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፷፮ ሀ ናሆ ፩፥፭፤ ማቴ. ፫፥፲፪፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፪፤
፷፫፥፴፫–፴፬።
፷፰ ሀ ት. እና ቃ. ፺፰፥፺፮።
፸ ሀ ት. እና ቃ. ፷፫፥፳፯–፳፱።
፸፪ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲–፲፪።
፸፭ ሀ አልማ ፭፥፴፯–፴፱።
፸፯ ሀ ቅ.መ.መ. መብት።
ለ ቅ.መ.መ. መንግስት።

ስነምግባር [ሀ]ምርጫ መሰረት፣ በትምህርትና በመሰረታዊ መርሆችም ይሰራ ዘንድ፣ እያንዳንዱም ሰው ለራሱ ኃጢአቶች [ለ]በፍርድ ቀን [ሐ]ይጠየቅበት ዘንድ ለቤዛነት በቅንነት እንዲጠይቁ ፍቃዴ ነው።

፸፱ ስለዚህ፣ ማንም ሰው ለሌላ በባሪያነት መተሳሰሩ ትክክል አይደለም።

፹ እና ለዚህ አላማ የዚህን [ሀ]ህገ መንግስት፣ ለዚህ አላማ ባነሳኋቸው የጥበብ ሰዎች እጅ አማካይነት፣ መሰርቼአለሁ እና ምድሩንም ደም [ለ]በማፍሰስ አድኜዋለሁ።

፹፩ አሁን፣ የፅዮን ልጆችን ከምን ጋር አመሳስላቸዋለሁ? ሰዎች ሳይታክቱ ዘወትር [ሀ]መጸለይ አለባቸውና፣ እንዲህ ከሚለው የሴቷ እና ፍትህዊ ያልሆነ ዳኛ [ለ]ምሳሌ ጋር አመሳስላቸዋለሁ—

፹፪ በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበር።

፹፫ በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፣ ወደ እርሱም እየመጣች ከጠላቴ ፍረድልኝ ትለው ነበር።

፹፬ ለአያሌ ቀንም ይህን ያደርግ ዘንድ አልወደደም፣ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ፥ ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፣ ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ዘወትር እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ።

፹፭ የፅዮንንም ልጆች በዚህም እመስላቸዋለሁ።

፹፮ በዳኛው እግር ላይም በቅንነት ይማጸኑ፤

፹፯ እና ካልሰማቸውም፣ በአስተዳዳሪው እግር ላይም በቅንነት ይማጸኑ፤

፹፰ አስተዳዳሪውም የማያደምጣቸው ከሆነ፣ በፕሬዘደንት እግር ላይም በቅንነት ይማጸኑ፤

፹፱ ፕሬዘደንቱም የማያደምጣቸው ከሆነ፣ ከዚያም ጌታ ይነሳል እና [ሀ]ከተሰወረበትም ስፍራ ይመጣል፣ እና በንዴቱም ህዝብን ያስጨንቃቸዋል፤

፺ በመዓቱም፣ እና በሀይለኛ ቁጣው፣ በጊዜው ክፉዎችን፣ ታማኝ ያልሆኑትን፣ እና ጻድቅ ያልሆኑትን [ሀ]መጋቢዎች ያገልላል፣ እና እድላቸውንም ከግብዞችና [ለ]ከማያምኑት ጋር ያደርግባቸዋል፤

፺፩ እንዲሁም በዚያ [ሀ]ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት በሆነበት፣ ወደ ድቅድቅ ጨለማ።

፺፪ ስለዚህ ጆሮዎቻቸው ለልቅሶዎቻችሁ ይከፈቱ ዘንድ፣ እኔ ለእነርሱ [ሀ]መሀሪ እሆን ዘንድ፣ እነዚህም ነገሮች እንዳይመጣባቸው ጸልዩ።

፺፫ ሁሉም ሰዎች [ሀ]ያለምክንያት ይቀሩ ዘንድ፣ ያልኳችሁ ሁሉ መፈጸም አለባቸው፤

፺፬ ብልህ ሰዎች እና መሪዎች [ሀ]ያላሰቧቸውን ነገሮች ይሰሙ እና ያውቁ ዘንድ መሆን አለባቸው፤

፺፭ ስራዬን ለማምጣት፣ እና ስራዬን፣ ማለት [ሀ]እንግዳ ስራዬን፣ እቀጥል ዘንድ፣ ሰዎችም በጽድቅ እና ኃጢአት መካከል [ለ]ለመለየት ይችሉ ዘንድ ነው፣ ይላል ጌታ።

፺፮ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ስድኒ ጊልበርት ለህዝቤ የመደብኩትን [ሀ]የኀተራ ስፍራዬን ወደ ጠላቶቼ እጆች ውስጥ መሸጡ ትእዛዜን እና ፈቃዴን የሚቃረን ነው።

፸፰ ሀ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ለ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣ የመጨረሻው።
ሐ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
፹ ሀ ፪ ኔፊ ፩፥፯–፱፤ ት. እና ቃ. ፺፰፥፭–፯። ቅ.መ.መ. ህገ መንግስት።
ለ ፩ ኔፊ ፲፫፥፲፫–፲፱።
፹፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ለ ሉቃ. ፲፰፥፩–፰።
፹፱ ሀ ኢሳ. ፵፭፥፲፭፤ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፩፣ ፬፤ ፻፳፫፥፮።
፺ ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።
ለ ራዕ. ፳፩፥፰። ቅ.መ.መ. አለማመን።
፺፩ ሀ ማቴ. ፳፭፥፴፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፭፤ ፳፱፥፲፭–፲፯፤ ፻፳፬፥፰።
፺፪ ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፺፫ ሀ ሮሜ ፩፥፲፰–፳፩።
፺፬ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲፭፤ ፫ ኔፊ ፳፥፵፭፤ ፳፩፥፰።
፺፭ ሀ ኢሳ. ፳፰፥፳፩፤ ት. እና ቃ. ፺፭፥፬።
ለ ሚል. ፫፥፲፰። ቅ.መ.መ. የመለየት ስጦታ።
፺፮ ሀ ቅ.መ.መ. ኅተራ።

፺፯ በጠላቶቼ፣ ራሳቸውንም በስሜ [ሀ]በሚጠሩት ፈቃድ፣ እኔ የመደብኩት ይራከስ ዘንድ አትፍቀዱ።

፺፰ ይህም በእኔና በህዝቤ ላይ የተደረገው ከፍተኛ እና አሳዛኝ ኃጢአት ነውና፣ በዚህም ምክንያት በአህዛብ ላይ በቅርብ የሚወድቁትን እነዚያን ነገሮች አውጃለሁ።

፺፱ ስለዚህ፣ ምንም እንኳን እንዲኖሩባቸው ባይፈቀድላቸውም፣ ህዝቤ ለእነርሱ የመደብኩላቸውን እንደገና እንዲይዙ፣ እና በመብትም እንዲይዙ ፍቃዴ ነው።

፻ ይህም ቢሆን፣ በዚያ አይኖሩም አላልኩም፤ ለመንግስቴ ብቁ የሆኑ ፍሬዎችና ስራዎች እስካመጡ ድረስ በእነዚያም ላይ ይኖራሉ።

፻፩ ይገነባሉ፣ እና ሌላም [ሀ]አይወርሰውም፤ የወይን ስፍራንም ይተክላሉ፣ እና የእነዚህን ፍሬዎቻቸውንም ይበላሉ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፪

በየካቲት ፲፯፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) የቤተክርስቲያኗ የመጀመሪያ ከፍተኛ ሸንጎ ሲመሰረት የተያዘ ቃለጉባኤ። የመጀመሪያዎቹ ቃለጉባኤዎች በሽማግሌዎች ኦሊቨር ካውድሪ እና ኦርሰን ሀይድ የተጻፉ ነበሩ። ነቢዩ ቃለጉባኤዎችን በሚቀጥለው ቀን አስተካከለ፣ እናም የተስተካከሉት ቃለጉባኤዎች በሚቀጥለው ቀን በከፍተኛ ሸንጎዎች "እንደ ቤተክርስቲያኗ መልክ እና ህገ መንግስት" በሙሉ ስምምነት ተቀባይነትን አገኙ። ይህ ክፍል በትምህርት እና ቃል ኪዳን ህትመት ሲዘጋጅ፣ ስለአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን የሆኑት ከ፴ እስከ ፴፪ ቁጥሮች በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በጆሴፍ ስሚዝ አመራር ተጨመሩ።

፩–፰፣ ከፍተኛ ሸንጎ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሚነሱ አስቸጋሪ ጉዳዮች መፍትሄ ለማግኘት ተመድቧል፤ ፱–፲፰፣ ለሚቀርቡ ጉዳዮች ስነስርዓቶችም ተሰጥተዋል፤ ፲፱–፳፫፣ የሸንጎው ፕሬዘደንት የሚገባ ውሳኔን ይሰጣል፤ ፳፬–፴፬፣ የይግባኝ ስነስርዓትም ተሰጥቷል።

፩ በዚህ ቀን ሀያ አራት የአጠቃላይ ሸንጎ ሊቀ ካህናት በጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ቤት ውስጥ በራዕይ ተሰበሰቡ፣ እና አስራ ሑለት ሊቀ ካህናት እና፣ ጉዳዩ እንደሚያስፈልገው አንድ ወይም ሶስት ፕሬዘደንት ያለውን የክርስቶስ ቤተክርስቲያንን [ሀ]ከፍተኛ ሸንጎ ማደራጀት ጀመሩ።

፪ ከፍተኛ ሸንጎውም፣ ቤተክርስቲያኗ ወይም [ሀ]የኤጲስ ቆጶስ ሸንጎ በጉዳዩ የነበሩትን ሁሉ በማርካት መፍትሄ ለማግኘት የማይቻሉትን፣ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ሊነሱ በሚችሉ አስፈላጊ ችግሮች ላይ መፍትሄ ለማግኘት በራዕይ ተመድቧል።

፫ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ ስድኒ ሪግደንና ፍረድሪክ ጂ ዊሊያምስ በሸንጎው ድምፅ እንደ ፕሬዘደንቶች ተረጋግጠው ነበር፤ እና ሊቀ ካህናት ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ፣ ጆሴፍ ኮ፣ ጆን ዊትመር፣ ማርቲን ሀሪስ፣ ጆን ኤስ ካርተር፣ ጀርድ ካርተር፣ ኦሊቨር ካውድሪ፣ ሳሙኤል ኤች ስሚዝ፣ ኦርሰን ሀይድ፣ ስይልቨስተር ስሚዝ፣ እና ሉክ ጆንሰን ለቤተክርስቲያኗ ቋሚ ሸንጎ በመሆን፣ በሸንጎው በአንድ ድምፅ ተመርጠው ነበር።

፬ ከዚያም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሸንጎዎች የተመደቡበትን እንደሚቀበሉ፣ እና

፺፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፫፥፬፤
፻፲፪፥፳፭–፳፮፤ ፻፳፭፥፪።

፻፩ ሀ ኢሳ. ፷፭፥፳፩–፳፪።
ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።

፻፪ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ከፍተኛ ሸንጎ።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፸፪–፸፬።

በሰማይ ህግ መሰረት በዚያም ሀላፊነት እንደሚሰሩ ተጠይቀው ነበር፣ ለዚህም የተመደቡበትን እንደሚቀበሉ፣ እና ሀላፊነታቸውን በተሰጣቸው በእግዚአብሔር ጸጋ መሰረት እንደሚፈፅሙም መልስ ሰጡ።

፭ ከላይ የተጠቀሱትን ሸንጎዎች ለመመደብ በቤተክርስቲያኗ ስም እና ለቤተክርስቲያኗ ድምጻቸውን የሰጡት ሸንጎዎች ቁጥር እንደሚከተለው ነበሩ፥ አርባ ዘጠኝ ሊቀ ካህናት፣ አስራ ሰባት ሽማግሌዎች፣ አራት ካህናት፣ እና አስራ ሶስት አባላት።

፮ ድምፅ ሰጡ፥ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሸንጎዎች፣ ወይም በእነርሱ ወኪል የተመደቡት ምትኮች ሰባቱ ካልተገኙ በስተቀር ከፍተኛ ሸንጎው ለመስራት ሀይል ሊኖረው አይችልም።

፯ እነዚህ ሰባቱም ብቁ እና ሸንጎዎቹ በማይኖሩበት ጊዜ በእነርሱ ምትክ ለመስራት ችሎታ አላቸው ብለው የሚያስቡአቸውን ሌሎች ሊቀ ካህናትን ለመመደብ ሀይል አላቸው።

፰ ድምፅ ሰጡ፥ ከላይ የተጠቀሱት ማንኛቸውም ሸንጎዎች በሞት፣ በመተላለፍ ምክንያት ከሀላፊነት ቢወገዱ፣ ወይም ከቤተክርስቲያኗ መንግስት አካባቢ በመውጣት በመወገድ ምክንያት ክፍተት ቢኖር፣ በፕሬዘደንቱ ወይም ፕሬዘደንቶቹ ጥቆማ፣ እና ለዚህ አላማ በቤተክርስቲያኗ ስም ለመስራት በተሰበሰቡት በሊቀ ካህናቱ ከፍተኛ ሸንጎ ድምፅ ቅበላ ይህም ስፍራ ይሞላል።

፱ የሸንጎው ፕሬዘደንት የሆነው የቤተክርስቲያኗ ፕሬዘደንት የሚመደበው [ሀ]በራዕይ ነው፣ እና በቤተክርስቲያኗም ድምፅ አስተዳደሪነቱ እውቅና [ለ]ይሰጠው።

፲ እና ይህም በሀላፊነቱ ክብር ምክንያት በቤተክርስቲያኗ ሸንጎ ይሰየማል፤ እና እርሱ በመተደበበት አይነት በተመደቡት ሁለት ሌሎች ፕሬዘደንቶች ይረዳ ዘንድም መብቱ ነው።

፲፩ እንዲረዱት የተመደቡት አንዱ ወይም ሁለቱ የማይኖሩ ቢሆን፣ ካለረዳቶቹ ሸንጎን ለመምራት ሀይል አለው፤ እና እርሱም ባይኖር፣ ሌሎቹ፣ ከሁለቱ አንዱ ወይም ሁለቱም ፕሬዘደንቶች በእርሱ ስፍራ ለመምራት ይችላሉ።

፲፪ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሸንጎ በትክክለኛው አሰራር በየጊዜው በሚደራጅበት ጊዜ፣ አስራ ሁለቱ ሸንጎዎች ምርጫን በእጣ የመወሰን ሀላፊነት አላቸው፣ በዚህም፣ ከቁጥር አንድ ጀምሮ ተከታትሎ እስከ አስራ ሁለት ድረስ፣ ከአስራ ሁለቱ የትኛው አስቀድሞ እንደሚናገር ይወሰናሉ።

፲፫ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለመስራት ሸንጎው ሲሰበሰብ፣ አስራ ሁለቱ ሸንጎዎች ጉዳዩ አዳጋች መሆን አለመሆን ያስቡበት፤ ይህ ካልሆነ፣ ከላይ በተጻፈው ምሳሌ መሰረት ሁለት የሸንጎው አባላት ብቻ ይነጋገሩበታል።

፲፬ ነገር ግን አስቸጋሪ እንደሚሆን የሚታሰብበት ከሆነ፣ አራት ይመደባሉ፤ ከዚያም በላይ አስቸጋሪ ከሆነም፣ ስድስት፤ ነገር ግን በማንኛውም ጉዳይ ከስድስት በላይ እንዲናገሩ አይመደቡም።

፲፭ በሁሉም ጉዳዮች፣ ስድብ ወይም ግፍን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተከሳሹ በሸንጎው ግማሽ አባላት የመዳኘት መብት አለው።

፲፮ እና በሸንጎው ፊት ለመናገር የተመደቡት አማካሪዎች፣ ማስረጃው ከተመረመረ በኋላ፣ በእውነት ግልጽ ጉዳዩን በሸንጎው ፊት ያቅርቡ፤ እና እያንዳንዱም ሰው በእኩልነት እና [ሀ]በፍትህዊነት መሰረት ይናገር።

፲፯ ሙሉ ቁጥሮችን የያዙ፣ ማለትም ፪፣ ፬፣ ፮፣ ፰፣ ፲፣ እና ፲፪ን የመረጡት አማካሪዎች ለተከሰሰው ሰው የሚቆሙለት፣ እና ስደብ ወይም ግፍን አስቀድሞ የሚከላከሉ ግለሰቦች ናቸው።

፲፰ በሁሉም ጉዳዮች፣ መረጃዎቹ ከተሰሙ እና በጉዳዩ እንዲናገሩ የተመረጡት

፱ [ሀ] ቅ.መ.መ. ራዕይ።
[ለ] ቅ.መ.መ. የቤተክርስቲያን መሪዎችን መደገፍ።
፲፯ [ሀ] ቅ.መ.መ. ፍትህ።

አማካሪዎች ንግግራቸውን ከፈጸሙ በኋላ፣ የተከሰሰው እና ከሳሹ በሸንጎው ፊት ለራሳቸው ለመናገር መብት አላቸው።

፲፱ መረጃዎቹ ከተሰሙ በኋላ፣ አማካሪዎቹ፣ ከሳሹ፣ እና ተከሳሹ ከተናገሩ በኋላ፣ ፕሬዘደንቱ በጉዳዩ ባለው መረጃ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፣ እና አስራ ሁለቱን አማካሪዎችንም ይህን በምርጫቸው እንዲቀበሉ ይጠራቸዋል።

፳ ነገር ግን፣ መረጃውን እና ያለገለልተኛነት አቤቱታውን ከሰሙ በኋላ፣ የሚቀሩት ያልተናገሩት አማካሪዎች ወይም ማንኛቸውም በፕሬዘደንቱ ውሳኔ ስህተት ቢያገኙ፣ ይህንንም ይግለጹ፣ እና ጉዳዩም እንደገና ይቀርባል።

፳፩ እና በጥንቃቄ እንደገና ከሰሙት በኋላ፣ ተጨማሪ ብርሀን በጉዳዩ ላይ ከታየ፣ በዚህም መሰረት ውሳኔው ይቀየር።

፳፪ ምንም ተጨማሪ ብርሀን ባልተሰጠበት ጉዳይ ግን፣ የሸንጎ አብላጫው እንደነበረ የመወሰን ሀይል ስላለው፣ የመጀመሪያው ውሳኔ አይለወጥም።

፳፫ [ሀ]ትምህርትን ወይም መሰረታዊ መርህን በሚመለከት የችግር ጉዳይ፣ ለሸንጎውን አዕምሮዎች ጉዳዩን ግልፅ ለማድረግ ብቁ ፅህፈት ባይኖር፣ ፕሬዘደንቱ መጠየቅ እና የጌታን አስተሳሰብ [ለ]በራዕይ ለማግኘት ይችላል።

፳፬ ሊቀ ካህናት፣ በውጪ እያሉ፣ ከዚህ በፊት እንደ ተመደበው፣ ሰዎቹ ወይም እያንዳንዳቸው ሲጠይቁ ለችግሮች መፍትሄ ለማግኘት ሸንጎን ለማደራጀት እና ለመጥራት ሀይል አላቸው።

፳፭ እና የተጠቀሰውም የሊቀ ካህናት ሸንጎ ከቁጥራቸው አንዱን በዚህ አይነት ሸንጎ ላይ ለጊዜው እንዲመራ ለመመደብ ሀይል አላቸው።

፳፮ ወዲያውም የሸንጎ ሂደታቸውን፣ ከውሳኔአቸው ጋር ሙሉ ምስክርን አያይዘው፣ ለቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር ከፍተኛ ሸንጎ መቀመጫ የመላክ ሀላፊነትም ለተጠቀሱት ሸንጎዎችም ነው።

፳፯ ሰዎቹ ወይም እያንዳንዳቸው በተጠቀሱት ሸንጎ ውሳኔ የማይደሰቱ ቢሆን፣ ለቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር ከፍተኛ ሸንጎ መቀመጫ ይገባኝ ለማቅረብ እና የምስክር ቃል ዳግም ሊያሰሙ ይችላሉ፣ ይህም ጉዳይ ከዚህ ቀደም በተጻፈው መሰረት ምንም ውሳኔ እንዳልተሰጠ በሚመስል አይነት ይደረግ።

፳፰ ይህ በውጪ ያሉት የሊቀ ካህናት ሸንጎ የሚጠሩት በጣም [ሀ]አስቸጋሪ ለሆኑት የቤተክርስቲያን ጉዳዮች ነው፤ እና ምንም ተራ ወይም ልዩ ያልሆኑ ጉዳዮች እንደዚህ አይነት ሸንጎን ለመጥራት ብቁ አይደሉም።

፳፱ በውጪ የሚጓዙት እና የሚገኙት ሊቀ ካህናት እንደዚህ አይነት ሸንጎ ለመጥራት ወይም ላለመጥራት አስፈላጊ እንደሆነም ለመወሰን ሀይል አላቸው።

፴ በከፍተኛ ሸንጎ ወይም [ሀ]በሚጓዙ ሊቀ ካህናት እና የሚጓዙ የአስራ ሁለቱን [ለ]ሐዋሪያት በያዘ ከፍተኛ ሸንጎ መካከል በውሳኔዎቻቸው ልዩነት አለ።

፴፩ ከመጀመሪያው ውሳኔ ይገባኝ ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን ከኋለኛው ውሳኔ ይግባኝ አይኖርም።

፴፪ የኋለኛው መጠራት የሚቻለው በቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ባለስልጣናት ብቻ፣ ይህም በመተላለፍ ጉዳይ ጊዜ ነው።

፴፫ ውሳኔ፥ የቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር መቀመጫ ፕሬዘደንት ወይም ፕሬዘደንቶች ለይገባኝ ለመቅረብ የሚችል፣ እንደዚህ አይነት ማንኛውም ጉዳይ፣ ይገባኙን እና ከእርሱ ጋር ያለውን መረጃና ምስክር ከመረመሩ በኋላ፣ ዳግም እንዲሰማ መብት እንደሚገባው ለመወሰን ሀይል አላቸው።

፴፬ አስራ ሁለቱ አማካሪዎች ከዚያም አስቀድሞ ማን እንደሚናገር ለመወሰን፣ እጣ ወይም መምረጫ ወረቀት ጣሉ፣ እና የሚቀጥለውም ውጤቱ ነበር፥ ፩፣ ኦሊቨር

፳፫ሀ ዘኁል. ፱፥ ፰።
ለ ቅ.መ.መ. ራዕይ።

፳፰ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥ ፸፰።
፴ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥ ፳፫–፳፬፤

፴፭–፴፰።
ለ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።

ካውድሪ፤ ፬፣ ጆሴፍ ኮ፤ ፫፣ ሳሙኤል ኤች ስሚዝ፤ ፩፣ ሉክ ጆንሰን፤ ፮፣ ጆን ኤስ ካርተር፤ ፯፣ ስይልቨስተር ስሚዝ፤ ፱፣ ጆን ጆንሰን፤ ፰፣ ኦርሰን ሀይድ፤ ፲፣ ጄርድ ካርተር፤ ፲፣ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ፤ ፲፩፣ ጆን ስሚዝ፤ ፲፪፣ ማርቲን ሀሪስ።ከጸሎት በኋላ ጉባኤው ተበተነ።

ኦሊቨር ካውድሪ፣
ኦርሰን ሀይድ፣
ጸሀፊዎች

ክፍል ፻፫

በየካቲት ፳፬፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ ፓርሊ ፒ ፕራት እና ላይመን ዋይት ስለእርዳታ እና በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ ወደሚገኘው መሬታቸው ቅዱሳንን ስለመመለስ ከነቢዩ ጋር ለመመካከር ከሚዙሪ ወደ ከርትላንድ ከደረሱ በኋላ የተቀበሉት ነበር።

፩–፬፣ ለምን ጌታ የጃክሰን የግዛት ክፍል ቅዱሳን እንዲሰደዱ እንደፈቀደ፤ ፭–፲፣ ትእዛዛትን ከጠበቁ ቅዱሳን ያሸንፋሉ፤ ፲፩–፳፣ የፅዮን ቤዛነት በሀይል ይመጣል፣ ጌታም በህዝቦቹ ፊት ይሄዳል፤ ፳፩–፳፰፣ ቅዱሳን በፅዮን ይሰብሰቡ፣ እና ህይወታቸውን የሚያጡትም ደግመው ያገኙታል፤ ፳፱–፵፣ የተለያዩ ወንድሞች የፅዮንን ሰፈር እንዲያደራጁና ወደ ፅዮን እንዲሄዱ ተጠሩ፤ ታማኝ ከሆኑም ውጤታማ እንደሚሆኑ የተስፋ ቃል ተሰጥቷቸዋል።

፩ ባልንጀሮቼ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እነሆ፣ በፅዮን ምድር የተበተኑትን ወንድሞቻችሁን ደህንነት እና [ሀ]ቤዛነት በሚመለከት ያላችሁን ሀላፊነት እንዴት [ለ]እንድትፈፅሙ ታውቁ ዘንድ ራዕይና ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤

፪ ቁጣዬን በጊዜዬ ያለልክ በማወርድባቸው በጠላቶቼ እጆች [ሀ]እየተሰደዱ እና እየተመቱት ስላሉት።

፫ የጥፋታቸውንም መስፈሪያ [ሀ]ይሞሉ ዘንድ፣ ጽዋቸውም ሙሉ ይሆን ዘንድ፣ እስከአሁን ፈቅጄላቸዋለሁና፤

፬ እና በስሜ ራሳቸውን የሚጠሩትም ለጥቂት ዘመን በከፍተኛ እና አሳዛኝ ተግሳፅ [ሀ]ይገሰጹ ዘንድ፣ ምክንያቱም አብረውም የሰጠኋቸውን አስተሳሰብና ትእዛዛት [ለ]አላዳመጡምና።

፭ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ ጌታ አምላካቸው የምሰጣቸውን [ሀ]ምክር ከዚህ ሰአት ጀምረው የሚያደምጡ ቢሆን፣ ህዝቤ ሊቀበሉ የሚችሉትን አዋጅ አውጃለሁ።

፮ እነሆ፣ ስላወጅኩት፣ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ጠላቶቼን ማሸነፍ ይጀምራሉ።

፯ እና እኔ ጌታ የምናገራቸውን ቃላት ለመከተል [ሀ]ቢያደምጡ፣ የአለም [ለ]መንግስታት ከእግሮቼ በታች እስከሚገዙ እና ምድርንም ለዘለአለም [ሐ]የራሳቸው እንዲያደርጓት [መ]ለቅዱሳን [ሠ]እስከምትሰጥ ድረስ ማሸነፍን አያቆሙም።

፰ ነገር ግን ትእዛዛቴን [ሀ]እስካላከበሩ እና ቃላቴንም እስካልተከተሉ ድረስ፣ የአለም መንግስታት ያሸንፏቸዋል።

፻፫ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፵፫–፷፪።
ለ ት. እና ቃ. ፵፫፥፰።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፩፤
፻፱፥፵፯።
፫ሀ አልማ ፲፬፥፲–፲፩፤ ፷፥፲፫።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፺፭፥፩።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣
ተግሳጽ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፩፥፪፤
፻፭፥፪–፮።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፯ሀ ት. እና ቃ. ፴፭፥፳፬።
ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ለ ዳን. ፪፥፵፬።
ሐ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳።
መ ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።
ሠ ዳን. ፯፥፳፯።
፰ሀ ሞዛያ ፩፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፹፪፥፲።

፱ ለአለም [ሀ]ብርሀንና ለሰዎች አዳኝ ይሆኑ ዘንድ ተመርጠው ነበርና፤

፲ እና የሰዎች አዳኞች እስካልሆናችሁ ድረስ፣ ጣዕሙን እንዳጣ [ሀ]ጨው ትሆናላችሁ፣ እና ከዚያን ጊዜ በኋላ ከንቱ ትሆናላችሁ፣ ደግሞም ትጣላላችሁ፣ እናም በሰዎችም እግር ትረገጣላችሁ።

፲፩ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ የተበተኑት ወንድሞቻችሁ ወደ ውርስ [ሀ]መሬታቸው እንዲመለሱ፣ እና የፈረሱትን የፅዮን ስፍራዎችንም እንዲገነቡ አውጃለሁ።

፲፪ [ሀ]ከብዙ ስቃይ በኋላ፣ አስቀድሜ እንዳዘዝኳችሁ፣ በረከት ይመጣል።

፲፫ እነሆ፣ ይህም ከስቃያችሁ እና ከወንድሞቻችሁ ስቃይ በኋላ በተስፋ ቃል የሰጠኋችሁ በረከት ነው—ቤዛነታችሁ፣ እና የወንድሞቻችሁ ቤዛነት፣ እንዲሁም የፅዮን ምድር እንደገና እንዳትሸነፍ እንድትመሰረት ዳግም መመለሷ።

፲፬ ይህም ቢሆን፣ ውርሶቻቸውን ካረከሱ ይሸነፋሉ፤ ውርሶቻቸውን የሚያረክሱ ቢሆን አላድናቸውምና።

፲፭ እነሆ እላችኋለሁ፣ የፅዮን ቤዛነት በሀይል ይመጣ ዘንድ ይገባል፤

፲፮ ስለዚህ፣ [ሀ]ሙሴ የእስራኤልን ልጆች እንደመራው፣ የሚመራቸው ሰው ለህዝቤ አስነሳለሁ።

፲፯ እናንተ የእስራኤል ልጆች፣ [ሀ]የአብርሐም ዘር ናችሁና፣ እና በሀይሌና በተዘረጋው ክንዴ ከባርነታችሁ ተመርታችሁ መውጣት ያስፈልጋችኋልና።

፲፰ እና አባቶቻችሁ በመጀመሪያ እንደተመሩት፣ የፅዮን ቤዛነትም እንዲሁ ይሆናል።

፲፱ ስለዚህ፣ ልባችሁ አይታወክ፣ ለአባቶቻችሁ እንዳልኳቸው ለእናንተም እላችኋለሁና፥ በፊታችሁ [ሀ]መልአኬን እልካለሁ፣ ነገር ግን [ለ]እኔ በመካከላችሁ አልገለጥም።

፳ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፊታችሁ [ሀ]መላዕክቴን እልካለሁ፣ እና በመካከላችሁም እገኛለሁ፣ እና በጊዜም መልካሙን ምድር [ለ]የራሳችሁ ታደርጋላችሁ።

፳፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በሰጠኋችሁ ምሳሌ ውስጥ [ሀ]የወይን ስፍራው ጌታ የሆነው አገልጋይ የተናገረውን የሚመስለው [ለ]ሰው አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ነው።

፳፪ ስለዚህ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ለቤቴ [ሀ]ጥንካሬ፣ ለወጣቶቼና ለጎልማሳዎቼ እንዲህ ይበል—በፅዮን ምድር፣ ለእኔ በተቀደሰው ገንዘብ በገዛሁት ምድር ላይ በአንድነት ተሰብሰቡ።

፳፫ እና ቤተክርስቲያኖቹ ሁሉ ብልህ ሰዎቻቸውን ከገንዘቦቻቸው ጋር ይላኩ፣ እና እንዳዘዝኳቸውም መሬቶችን [ሀ]ግዙ።

፳፬ እና የፅዮን ምድር እንዲሆን ከቀደስኩት [ሀ]ምድር፣ ከመልካሙ መሬቴ፣ እንዲሁም በእነርሱ ላይ በፊቴ ካመጣችሁት ከእነዚህ ምስክሮች በኋላ ከመሬታችሁ ሊያሰድዳችሁ ጠላቶቼ ከመጡባችሁ፣ እርገሟቸው፤

፳፭ እና ማንኛውም የምትረግሟቸውን፣ እረግማቸዋለሁ፣ እና ጠላቶቼንም ትበቀላላችሁ።

፳፮ እና በጠላቶቼ፣ በሚጠሉኝ ሶስተኛ እና አራተኛ ትውልድ ላይ [ሀ]ስትፈርዱም ከእናንተ ጋር እገኛለሁ።

፳፯ ለእኔ ህይወቱን ለመስጠት ማንም

፱ ሀ ፩ ኔፊ ፳፩፥ ፮።
፲ ሀ ማቴ. ፭፥ ፲፫–፲፮፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥ ፴፱–፵።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥ ፲፰።
፲፪ ሀ ራዕ. ፯፥ ፲፫–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፬፤
፻፲፪፥ ፲፫።
፲፮ ሀ ዘፀአ. ፫፥ ፪–፲፤
ት. እና ቃ. ፻፯፥ ፺፩–፺፪።
ቅ.መ.መ. ሙሴ።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. አብርሐም—
የአብርሐም ዘር፤
የአብርሐም ቃል ኪዳን።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፲፰–፳፬።
፳ ሀ ዘፀአ. ፲፬፥ ፲፱–፳።
ለ ት. እና ቃ. ፻፥ ፲፫።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን
አትክልት ስፍራ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፩፥ ፶፭–፶፰።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፭፥ ፲፫–፲፬፤
፻፭፥ ፲፯፤ ፳፱–፴።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፴፭–፴፮፤
፶፯፥ ፭–፯፤ ፶፰፥ ፵፱–፶፩፤
፻፩፥ ፸፰–፸፬።
፳፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፯–፰፤
፵፭፥ ፷፬–፷፮፤ ፶፯፥ ፩–፪።
፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፺፯፥ ፳፪።

ሰው አይፍራ፤ ማንም ለእኔ ህይወቱን [ሀ]አሳልፎ የሚሰጥ ዳግም ያገኝዋልና።

፳፱ እና ለእኔ ህይወቱን ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነውም ደቀመዝሙሬ አይደለም።

፳፱ አገልጋዬ [ሀ]ስድኒ ሪግደን፣ ቤተክርስቲያኖችን ስለፅዮን ዳግም መመለስ እና ቤዛነት የሰጠኋቸውን ትእዛዛት እንዲጠብቁ ለማዘጋጀት፣ ለምስራቅ ሀገሮች ተሰብሳቢዎች ድምጹን ከፍ ማድረጉ ፍቃዴ ነው።

፴ አገልጋዬ [ሀ]ፓርሊ ፒ ፕራትና አገልጋዬ ላይመን ዋይት፣ ወደፅዮን ምድር የሚሄዱ ሰዎችን በአስሮች ወይም በሀያዎች ወይም በሀምሳዎች ወይም በመቶዎች እስኪያደራጁ ድረስ፣ ለቤቴ [ለ]ጥንካሬ አምስት መቶዎችን እስኪያገኙ ድረስ፣ ወደወንድሞቻቸው መሬት እንዳይመለሱ ፍቃዴ ነው።

፴፩ እነሆ ይህም ፍቃዴ ነው፤ ጠይቁ፣ ይሰጣችኋል፤ ነገር ግን ሰዎች ፈቃዴዬን ሁልጊዜም [ሀ]አያደርጉም።

፴፪ ስለዚህ፣ አምስት መቶ የማታገኙ ቢሆን፣ ምናልባት ሶስት መቶ ታገኙ ዘንድ በቅንነት ፈልጉ።

፴፫ እና ሶስት መቶ ለማግኘት ባትችሉም፣ ምናልባት አንድ መቶ ታገኙ ዘንድ በቅንነት ፈልጉ።

፴፬ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ ወደፅዮን ምድር አብሮአችሁ እንዲሄዱ ከቤቴ ጥንካሬ መቶ እስከታገኙ ድረስ ወደፅዮን ምድር እንዳትሄዱ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፴፭ ስለዚህ፣ እንዳልኳችሁ ጠይቁ፣ ይሰጣችኋል፤ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ምናልባት ከእናንተ ጋር እንዲሄድ፣ እና በህዝቤ መካከል እንዲመራ፣ እና [ሀ]በተቀደሰው ምድርም መንግስቴን ያደራጅ፣ እና የፅዮን ልጆችን በተሰጡት እና ወደፊት በሚሰጣችሁ ህግጋት እና ትእዛዛት መሰረት ይመሠርት ዘንድ በቅንነት ጸልዩ።

፴፮ ድልና ክብር ሁሉ የሚመጣላችሁ [ሀ]በቅንነታችሁ፣ በታማኝነታችሁ፣ እና [ለ]በእምነት ጸሎታችሁ ነው።

፴፯ አገልጋዬ ፓርሊ ፒ ፕራት ከአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ጋር ይጓዝ።

፴፰ አገልጋዬ ላይመን ዋይት ከአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን ጋር ይጓዝ።

፴፱ አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ከአገልጋዬ ፍሬድሪክ ጂ ዊሊያምስ ጋር ይጓዝ።

፵ አገልጋዬ ኦርሰን ሀይድ ከአገልጋዬ ኦርሰን ፕራት ጋር፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ በሚመክራቸው በማንኛውም፣ የሰጠኋቸውን የእነዚህን ትእዛዛት ፍጻሜ ያገኙ፣ ይጓዙ፣ እና የሚቀረውንም በእጆቼ ይተዉት። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፬

በሚያዝያ ፳፫፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ፣ ኦሀዮ ወይም አካባቢ ስለትብብር ድርጅት በሚመለከት ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ (የክፍል ፸፰ እና ፹፪ ርዕሶችን ተመልከቱ)። ጊዜውም ምናልባት የትብብር ድርጅት አባላት በምክር ስብሰባ ቤተክርስቲያኗ ወዲያው ስለሚያስፈልጋት ለመወያየት በተሰበሰቡበት ጊዜ እንደነበር ይገመታል። ከዚህ በፊት በሚያዝያ ፲ በነበረው የድርጅቱ ስብሰባ ድርጅቱ እንዲፈርስ ተወስኖ ነበር። ይህ ራዕይ በምትኩ ይህ ድርጅት እንደገና እንዲደራጅ መመሪያ ሰጠ፤ የዚህ ንብረቶችም ለድርጅቱ አባላት በመጋቢ

፳፰ ሀ ማቴ. ፲፥፴፱፤
ሉቃ. ፱፥፳፬፤
ት. እና ቃ. ፺፰፥፲፫–፲፭፤
፻፳፬፥፶፬።

፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።

፴ ሀ ቅ.መ.መ. ፕራት፣ ፓርሊ ፓርከር።
ለ ት. እና ቃ. ፻፩፥፶፭።

፴፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲።

፴፭ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፩።

፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ት. እና ቃ. ፻፬፥፸፱–፹፪።

ነት ተከፋፍሎ ነበር። በጆሴፍ ስሚዝ አመራር ስር፣ “የትብብር ድርጅት” የሚባለው ሀረግ በኋላም በራዕዩ ውስጥ በ“የትብብር ስርዓት” ተተክቶ ነበር።

፩–፲፣ የትብብር ስርዓቱን የሚተላለፉት ቅዱሳን ይረገማሉ፤ ፲፩–፲፮፣ ጌታ ለቅዱሳኑን በራሱ መንገድ ያስተዳድራል፤ ፲፯–፲፰፣ የወንጌል ህግ ድሆን ስለመንከባከብ ይወስናል፤ ፲፱–፵፮፣ ለተለያዩ ወንድሞች መጋቢነቶች እና በረከቶች ተመድበዋል፤ ፵፯–፶፫፣ በከርትላንድ ውስጥ ያለው የትብብር ስርዓት እና በፅዮን ያለው ስርዓት ተለያይተው ይስሩ፤ ፶፬–፷፮፣ የጌታ ቅዱስ ሀብት ቅዱሳን መጻህፍትን ለማተም የተቋቋመ ነው፤ ፷፯–፸፯፣ የትብብር ስርዓትአጠቃላይ ሀብት በጋራ ስምምነት መሰረት ይስራ፤ ፸፰–፹፮፣ በትብብር ስርዓት ውስጥ ያሉት እዳዎቻቸውን ሁሉ ይክፈሉ፣ እና ጌታ ከገንዘብ እጦት ያድናቸዋል።

፩ ባልንጀሮቼ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]የትብብር ስርዓት እና ለቤተክርስቲያኔ ጥቅምና እስከምመጣም ድረስ ለሰዎች ደህንነት እንዲሁም ዘለአለማዊ ስርዓትም ይሆን ዘንድ፣ እንዲደራጅ እና እንዲመሰረት ያዘዝኩት ንብረቶችን ስለሚመለከት ስርዓት ምክርና ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ—

፪ ያዘዝኳቸው ታማኝ ቢሆኑ በሚበዙ በረከቶች እንዲሁም በማይለወጥ እና በማይቀየር ቃል ኪዳን ይባረካሉ፤

፫ ታማኝ እስካልሆኑ ድረስ ግን ለመረገም ይቀርባሉ።

፬ ስለዚህ፣ አንዳንድ አገልጋዮቼ ትእዛዜን እስካልጠበቁ ድረስ፣ [ሀ]በመጎምጀት እና በሀሰት ቃላት ቃል ኪዳንን ከሰበሩ ግን፣ በከፍተኛ እና አሳዛኝ እርግማን እረግማቸዋለሁ።

፭ እኔ ጌታ በልቤ አውጇዋለሁና፣ ማንም ሰው በስርዓቱ አባል ሆኖ እየተላለፈ ቢገኝ፣ ወይም በሌላ ቃላት፣ የተሳሰራችሁበትን ቃል ኪዳን ብትሰብሩ፣ በዚህ ህይወት የረገማል፣ እና በምፈልገውም ከእግር ስር ይረገጣል።

፮ እኔ ጌታ በእነዚህ ነገሮች [ሀ]አልዘበትምና—

፯ እና ይህም ሁሉ በመካከላችሁ ያሉት ንጹሕ ትክክለኛ ካልሆኑት ጋር እንዳይኮነኑ ዘንድ ነው፤ እና በመካከላችሁ ያሉት ጥፋተኞችም እንዳያመልጡ፤ ምክንያቱም እኔ ጌታ በቀኝ እጄ በኩል ለእናንተ የክብር [ሀ]አክሊል ቃል ኪዳን ገብቼአለሁና።

፰ ስለዚህ፣ እንደተላላፊ እስከተገኛችሁ ድረስ፣ ቁጣዬን በህይወታችሁ አታመልጡም።

፱ በመተላለፍ [ሀ]እስከተቆረጣችሁ ድረስ፣ እስከቤዛም ቀን ድረስ [ለ]የሰይጣንን [ሐ]መንገላታቶችን አያመልጡም።

፲ አሁንም ከመካከላችሁ ስርዓቱን ማንም ሰው ተላላፊ ሆኖ እና ለክፋቱ ንስሀ የማይገባ ሆኖ ቢገኝ፣ ለሰይጣን መንገላታት አልፋችሁ እንድትሰጡ ዘንድ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ሀይልን እሰጣችኋለሁ፤ እና በእናንተም ላይ ክፋትን [ሀ]ያደርግ ዘንድ ሀይል አይኖረውም።

፲፩ ይህም በእኔ ዘንድ ጥበብ ነው፤ ስለዚህ፣ ራሳችሁን እንድታደራጁ እና ለእያንዳንዱም ሰው [ሀ]መጋቢነቱን እንድትመድቡ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤

፲፪ እያንዳንዱም ሰው ለተመደበበት መጋቢነት መልስ ይሰጠኝ ዘንድ ይሁን።

፲፫ እኔ ጌታ እያንዳንዱ ሰው ለፍጥረቶቼ ለሰራሁት እና ላዘጋጀሁት የምድር በረከ

፻፬ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፫–፲፭።
ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።
፬ሀ ቅ.መ.መ. መመኘት።
፮ሀ ገላ. ፮፥፯–፱።
፯ሀ ኢሳ. ፳፰፥፭፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፶፮።
ቅ.መ.መ. ክብር።
፱ሀ ቅ.መ.መ. ውግዘት።
ለ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፪፥፳፩።
፲ሀ ት. እና ቃ. ፻፱፥፳፭–፳፯።
፲፩ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፪።
ቅ.መ.መ. መጋቢ፣ መጋቢነት።

ቶች [ሀ]በመጋቢነት [ለ]ተጠያቂ ይሆንም ዘንድ ፍቃዴ ነውና።

፲፬ እኔ ጌታ የእውነት [ሀ]የእጄን ስራ ሰማያትን ዘረጋሁ፤ እና ምድርንም [ለ]መሰረትሁ፤ እና በዚህ ያሉት ነገሮች ሁሉ የእኔ ናቸው።

፲፭ እና ቅዱሳኔን ማስተዳደር አላማዬ ነው፣ ሁሉም ነገሮች የእኔ ናቸውና።

፲፮ ነገር ግን፣ ይህም በእኔ [ሀ]መንገድ መደረግ አለበት፤ እና እነሆ እኔ ጌታ ቅዱሳኔን ለማስተዳደር፣ [ለ]ድሀዎቹን ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ በዚያም ሀብታሞችንም ለማውረድ ይህን መንገድ አውጃለሁ።

፲፯ [ሀ]ምድር ሙሉ ናት፣ እና በቂና የሚተርፍም አለና፤ አዎን፣ ሁሉንም ነገሮች አዘጋጅቻለሁ፣ እና ለሰዎች ልጆችም ለራሳቸው [ለ]ወኪል ይሆን ዘንድ ሰጥቻቸዋለሁ።

፲፰ ስለዚህ፣ ማንም ሰው እኔ ከሰራሁት [ሀ]የበዛውን ቢወስድ፣ እና በወንጌሌ [ለ]ህግ መሰረት [ሐ]ለድሀውና ለችግረኛው ድርሻውን ባያካፍል፣ በስቃይ ውስጥ አይኑን [መ]በገሀነም ከክፉዎች ጋር ከፍ ያደርጋል።

፲፱ አሁንም [ሀ]ስለስርዓቱ ንብረቶች እውነት እላችኋለሁ—

፳ አገልጋዬ ስድኒ ሪግደን አሁን የሚኖርበት ስፍራና የቆዳ ፋብሪካ መሬት ለመጋቢነቱ፣ እና እኔ እንደ ፈቃዴ፣ እርሱን በማዝበት ጊዜ በወይን ስፍራ ሲያገለግል ይደገፍበት ዘንድ ይመደብለት።

፳፩ እና ሁሉም ነገር በከርትላንድ ምድር ውስጥ በሚኖረው በስርዓቱ ሸንጎ፣ እና በጋራ ስምምነት ወይም በስርዓቱ ድምፅ መሰረት ይደረግ።

፳፪ እና ይህን መጋቢነት እና በረከት እኔ ጌታ በአገልጋዬ ስድኒ ሪግደን ላይ ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጣው ዘሩ በረከት ይሆን ዘንድ እሰጠዋለሁ።

፳፫ እና በፊቴ ትሁት እስከሆነ ድረስ በረከቶችንም አበዛለታለሁ።

፳፬ ደግሞም፣ አገልጋዬ ጆን ጆንሰን በቀድሞው ውርሱ አማካይነት በቅያሬ ያገኘውን መሬት ለመጋቢነቱ አገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ፣ ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ላለው ዘሩ፣ ይመድብለት፤

፳፭ ታማኝ እስከሆነ ድረስ፣ በረከቶችንም ለእርሱ እና ከእርሱም በኋላ ላለው ዘሩ አበዛለታለሁ።

፳፮ እና አገልጋዬ ማርቲን ሀሪስ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እንደመራው መሰረት፣ ገንዘቡን ቃላቴን ለማወጅ ያውለው።

፳፯ ደግሞም፣ አገልጋዬ ፍሬድሪክ ጂ ዊሊያምስ አሁን የሚኖርበት አካባቢ ስፍራ ይሰጠው።

፳፰ እና አገልጋዬ ኦሊቨር ካውድሪ ለእትመት ቢሮ ይሆነው ዘንድ፣ ቁጥር አንድ የሆነ የመሬት፣ ከቤቱ አጠገብ ባለው መሬት፣ ደግሞም አባቱ በሚኖርበት ስፍራ መሬት ይሰጠው።

፳፱ እና አገልጋዮቼ ፍሬድሪክ ጂ ዊሊያምስ እና ኦሊቨር ካውድሪ የእትመት ቢሮ ከሁሉም ነገሮቹ ጋር ይሰጣቸው።

፴ እና ይህም ለእነርሱ የሚመደብላቸው መጋቢነት ይሆናል።

፴፩ እና ታማኝም እስከሆኑ ድረስ፣ እነሆ እባርካቸዋለሁ፣ እና በረከቶቻቸውንም አባዛላቸዋለሁ።

፴፪ ይህም ለእነርሱ እና ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡ ዘሮቻቸው የመደብኩላቸው መጋቢነት መጀመሪያ ነው።

፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፸፪፥፫–፭፤ ፲፮–፳፪።
ለ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፤ ሂሳብ፤ ተጠያቂነት፤ ሀላፊነት።
፲፬ ሀ መዝ. ፲፱፥፩፤ ፳፬፥፩።
ለ ኢሳ. ፵፪፥፭፤ ፵፭፥፲፪። ቅ.መ.መ. መፍጠር፤ ፍጥረት።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፭። ቅ.መ.መ. በጎ ድርገት።
ለ ፩ ሳሙ. ፪፥፯–፰፤ ሉቃ. ፩፥፶፩–፶፫፤ ት. እና ቃ. ፹፰፥፲፯።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፮–፳። ቅ.መ.መ. ምድር።
ለ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
፲፰ ሀ ሉቃ. ፫፥፲፩፤ ያዕ. ፪፥፲፭–፲፮።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴።
ሐ ምሳ. ፲፬፥፳፩፤ ሞዛያ ፬፥፳፮፤ ት. እና ቃ. ፶፪፥፵።
መ ሉቃ. ፲፮፥፳–፴፩።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. የትብብር ስርዓት።

፴፫ እና፣ ታማኝ እስከሆኑ ድረስ፣ ለእነርሱ እና ከእነርሱ በኋላ ለዘሮቻቸው በረከቶችን፣ እንዲሁም ብዙ በረከቶችን፣ አበዛላቸዋለሁ።

፴፬ ደግሞም፣ አገልጋዩ ጆን ጆንሰን በውርሱ ያሉትን ቤቶቼን [ሀ]ለመገንባት ከተመደበው ምድር እና ለአገልጋዩ ኦሊቨር ካውድሪ ከተመደበው በስተቀር ሁሉም የሚኖርበት ቤትና ውርስ ይሰጠው።

፴፭ እና ታማኝ እስከሆነ ድረስ፣ በረከቶችን አበዛለታለሁ።

፴፮ እና በመንፈስ [ሀ]ድምፅ እንዲያውቅ እስከተደረገለት ድረስ፣ እና በስርዓቱ ምክር መሰረት፣ እና በስርዓቱ ድምፅ የቅዱሳኔን ከተማ ለመገንባት የተቀመጡትን መሬቶች ይሸጥም ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፴፯ ይህም ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ ለበረከት የመደብኩት የመጋቢነት መጀመሪያ ነው።

፴፰ እና ታማኝ እስከሆነም ድረስ የበረከቶች ብዛት አበዛለታለሁ።

፴፱ ደግሞም፣ ለአገልጋዩ [ሀ]ኒውል ኬ ዊትኒ አሁን የሚኖርበት ቤት እና መሬት፣ እና ግብይት ከሚገኝበት መሬት እና ህንጻ፣ እና ከግብይቱ ስፍራ በስተደቡብ ያለው መሬት፣ እና ደግሞም ፖታሽ የሚሰራበት ምድር ይመደብለት።

፵ እና ይህን ሁሉ ለአገልጋዩ ኒውል ኬ ዊትኒ ለመጋቢነት የመደብኩት ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ በረከት፣ በከርትላንድ ምድር ውስጥ ለስቴኬ ለመሰረትኩት ግብይት ይሆን ዘንድ ነው።

፵፩ አዎን፣ በእውነት ይህም፣ እንዲሁም የግብይይቱ ስፍራ ሁሉ፣ ለአገልጋዩ ኤን ኬ ዊትኒ፣ ለእርሱና [ሀ]ለወኪሉ እና ከእርሱም በኋላ ለዘሩ የመደብኩት መጋቢነት ነው።

፵፪ እና የሰጠሁት ትእዛዛቴን ለመጠበቅ ታማኝ እስከሆነ ድረስ፣ ለእነርሱ እና ከእነርሱ በኋላ ለዘሮቹ በረከቶችን፣ እንዲሁም የተትረፈረፉ በረከቶችን፣ አበዛላቸዋለሁ።

፵፫ ደግሞም፣ አገልጋዩ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ለሁለት መቶ ሜትር ርዝመት እና ስልሳ ሜትር ስፋት ያለው ለቤቴ መገንቢያ ይሆን ዘንድ የተቀመጠው መሬት፣ ደግሞም አባቱ አሁን በሚኖርበት ውርስ ይመደብለት።

፵፬ ይህም ለእርሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ፣ ለእርሱ እና ለአባቱ በረከት፣ የመደብኩለት መጋቢነት መጀመሪያ ነው።

፵፭ እነሆ፣ [ሀ]አባቱ ይረዳበት ዘንድ ወርስን አስቀምጫለሁና፤ ስለዚህ እንደአገልጋዩ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ቤት አባልም ይቆጠራል።

፵፮ እና በአገልጋዩ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ታማኝ እስከሆነ ድረስ በቤቱ በረከቶችን፣ እንዲሁም የተትረፈረፉ በረከቶችን አበዛለታለሁ።

፵፯ አሁንም ስለፅዮን በሚመለከት ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፣ እንደትብብር ስርዓት በፅዮን ካሉት ወንድሞቻችሁ ጋር፣ ከዚህ ጉዳይ በስተቀር፣ ከዚህ በኋላ እንዳትተሳሰሩ—

፵፰ ከተደራጃችሁ በኋላ፣ በከርትላንድ ከተማ ውስጥ የፅዮን [ሀ]ካስማ የትብብር ስርዓት ተብላችሁ ትጠራላችሁ። እና ወንድሞቻችሁም፣ ከተደራጁ በኋላ፣ የፅዮን ከተማ የትብብር ስርዓት ተብለው ይጠራሉ።

፵፱ እና በራሳቸውም ስሞች፣ እና በራሳቸው ስምም ይደራጁ፤ እና የራሳቸውንም ጉዳይ በራሳቸው ስም፣ እና በራሳቸው ስሞችም፣ ያድርጉ፤

፶ እና የራሳችሁንም ስራ በስማችሁ፣ እና በስሞቻችሁም አድርጉ።

፶፩ እና ይህ እንዲደረግ የማዝዘው እነርሱ [ሀ]በመሰደዳቸው እና ወደፊት ለሚመጣው ደህንነታችሁ፣ እና ለእነርሱም ደህንነት ነው።

፴፬ ሀ ት. እና ቃ. ፺፬፥፫፣ ፲።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ዊትኒ፣ ኒውል ኬ።
፵፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፻፲፪–፻፲፫።
፵፭ ሀ ት. እና ቃ. ፺፥፳።
ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ጆሴፍ ቀዳማዊ።
፵፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፫፤ ፺፬፥፩፤
፻፱፥፶፱።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
፶፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፱፥፵፯።

፶፪ በመተላለፍ፣ [ሀ]በመጎምጀት እና በሀሰት [ለ]ቃል በኩል ቃል ኪዳን ስለተሰበረ—

፶፫ ስለዚህ፣ ከወንድሞቻችሁ ጋር የነበራችሁ የትብብር ስርዓት ፈርሷል፣ እና እንዳልኩት በዚህ መንገድ፣ ይህ ስርዓት፣ ሁኔታችሁ በሚፈቅደው እና በሸንጎው ቀጥተኛ ድምፅ፣ ከዚህ ሰዓት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምትተሳሰሩት በሸንጎ በሚስማሙበት ብድር ብቻ ነው።

፶፬ ደግሞም፣ የመደብኩላችሁን መጋቢነት በተመለከተ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ።

፶፭ እነሆ፣ እነዚህ ንብረቶች ሁሉ የእኔ ናቸው፣ አለበለዚያም እምነታችሁ በከንቱ ነው፣ እና እናንተም ግብዞች ናችሁ፣ እና ለእኔ የገባችሁትም ቃል ኪዳን ተሰብሯል፤

፶፮ እና ንብረቶቹ የእኔ ከሆኑ፣ እናንተም የእኔ [ሀ]መጋቢዎች ናችሁ፤ አለበለዚያ መጋቢዎች አይደላችሁም።

፶፯ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በቤቴ ላይ መጋቢ፣ እንዲሁም በእርግጥም መጋቢዎች ትሆኑ ትሆኑ መድቤአችኋለሁ።

፶፰ እና ለዚህ አላማ ራሳችሁን እንድታደራጁ፣ እንዲሁም የቅዱስ መጻህፍቶቼን፣ የሰጧችሁን፣ ከዚህ በኋላም ከጊዜ ወደ ጊዜ የምሰጣችሁን ራዕዮች፣ እና [ሀ]የቃላቴን ሙላት እንድታትሙ አዝዤአችኋለሁ—

፶፱ ቤተክርስቲያኔን እና መንግስቴን በምድር ላይ ለመገንባት ባለኝ አላማ፣ እና ቅርብ ለሆነው፣ ህዝቤንም አብሬ ከእነርሱ ጋር [ሀ]ለምኖርበት [ለ]ጊዜ አዘጋጃቸውም ዘንድ ነበር።

፷ እና ለራሳችሁም የግምጃ ቤት አዘጋጁ፣ እና በስሜም ቀድሱት።

፷፩ እና ከመካከላችሁ አንዱ የግምጃ ቤቱን እንዲጠብቅ መድቡ፣ እና ለዚህ በረከትም ይሾማል።

፷፪ እና በግምጃ ቤቱም ላይ ማህተም ይኖራል፣ እና ሁሉም ቅዱስ ነገሮች ወደ ግምጃ ቤት ይወሰዳሉ፤ እና ከመካከላችሁ ማንም ይህን፣ ወይም ማንኛውንም ክፍል፣ የራሴ ነው ብለው አይጠሩትም፣ ይህም በአንድ ስምምነት ለሁላችሁም ይሆናልና።

፷፫ ደግሞም ይህን ከዚህ ሰዓት ጀምሮ እሰጣችኋለሁ፤ እና ይህም እንዲደረግ አድርጉ፣ ሂዱ እና እንዳልኩት እነዚህን የተቀደሱ ነገሮችን ለማሳተም ለዚህም አላማ፣ ከቅዱሱ ነገሮች በስተቀር፣ የተመደበላችሁን መጋቢነት ተጠቀሙበት።

፷፬ እና የቅዱስ ነገሮች [ሀ]ትርፍም በግምጃ ቤት ውስጥ ይቀመጥ፣ እና ማህተሙም በዚህ ላይ ይሁን፤ እና በስርዓት ድምፅ ወይም በትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር፣ በማንም ሰው ይህን ነገር አይጠቀምበት ወይም ከግምጃ ቤቱ አያውጡት፣ ወይም የታተመበትም አይፈታ።

፷፭ እንደዚሁም የቅዱስ ነገሮችን ትርፍ፣ ለተቀደሰ እና ቅዱስ አላማ፣ በግምጃ ቤት ትጠብቃላችሁ።

፷፮ እና ይህም የጌታ የተቀደሰ ግምጃ ቤት ይባላል፤ እና ለጌታ ቅዱስ እና የተቀደሰ ይሆን ዘንድ ማህተምም ይታተማል።

፷፯ ደግሞም፣ ሌላ ግምጃ ቤት ይዘጋጅ፣ እና የንብረት ሀላፊ የግምጃ ቤትን እንዲጠብቅ ይመደብ፣ እና በዚህም ላይ ማህተም ይደረግ፤

፷፰ እና የመደብኩላችሁን ንብረቶች፣ በቤቶች፣ ወይም በመሬቶች፣ ወይም፣ ለቅዱስ እና ለተቀደሰ አላማ ከምጠብቃቸው ከቅዱስ እና ከተቀደሱ ፅህፈቶች በስተቀር በሁሉም ነገሮች በማሻሻል በመጋቢነታችሁ የተቀበላችሁት ገንዘብ በመቶዎች፣ ወይም በሀምሳዎች፣ ወይም በሀያዎች፣ ወይም በአስሮች፣ ወይም በአምስቶች ሁሉ ወደ ግምጃ ቤቱ ገንዘቡ ወዲያው እንደተቀበላችሁ አስገቡት።

፶፪ ሀ ቅ.መ.መ. መመኘት።
ለ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
፶፮ ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፤ መጋቢነት።
፶፰ ሀ ቅ.መ.መ. የጆሴፍ ስሚዝ ትርጉም (ጆ.ስ.ት.)።
፶፱ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥ ፴፭–፴፮፤ ፸፯፥ ፲–፲፩።
ለ ቅ.መ.መ. አንድ ሺህ አመት።
፷፬ ሀ ይህም ትርፎች ወይም በእጅ የገቡት ገንዘቦች ማለት ነው።

፷፱ ወይም በሌላ አባባል፣ ማንኛውም ሰው አምስት ብር ቢያገኝ ወደ ግምጃ ቤት ያስገባው፤ ወይም አስር፣ ወይም ሀያ፣ ወይም ሀምሳ፣ ወይም መቶ ቢያገኝ እንዲሁ ያድርግ፤

፸ እና በመካከላችሁ ማንም ሰው የእኔ ነው የሚለው አይኑር፤ ይህ ወይም ማንኛውም ክፍል፣ የእርሱ ተብሎ አይጠራምና።

፸፩ እና በስርዓት ድምፅ እና በጋራ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛውንም ክፍል አይጠቀሙበት ወይም ምንም ነገር ከግምጃ ቤቱ አይውጣ።

፸፪ እና ይህም የስርዓት ድምፅ እና የጋራ ስምምነት ይሆናል—ከመካከላችሁ ማንም ሰው ለንብረት ሀላፊው እንዲህ ቢል፥ በመጋቢነቴ እንደረዳኝ ይህ ያስፈልገኛል—

፸፫ አምስት ብር፣ ወይም አስር ብር፣ ወይም ሀይ፣ ወይም ሀምሳ፣ ወይም መቶ ቢሆን፣ የንብረት ሀለፊው በመጋቢነቱ እንዲረዳው የሚያስፈልገውን ይሰጠዋል—

፸፬ ይህም በስርዓቱ ሸንጎ ፊት ታማኝ እንዳልሆነ እና ″ብልህ መጋቢ እንዳልሆነ በግልፅ እስከሚታይ ድረስ የሚያስፈልገው ይሰጠዋል።

፸፭ ነገር ግን ሁሉ አባል ከሆነ፣ እና በመጋቢነቱ ታማኝ እና ብልህ ቢሆን፣ ይህም ለንብረት ሀላፊው ምልክት ስለሚሆንለት ንብረት ሀላፊው አይከልክለው።

፸፮ ነገር ግን በመተላለፍ ምክንያት፣ የንብረት ሀላፊው ለሸንጎው እና ለስርዓቱ ድምፅ መላሽ ይሆናል።

፸፯ እና የንብረት ሀላፊው ታማኝ እና ብልህ መጋቢ ሆኖ በማይገኝበት ጉዳይ፣ ለሸንጎው እና ለስርዓቱ ድምፅ መላሽ ይሆናል፣ እና ከስፍራውም ይወጣል፣ እና በእርሱም ምትክ ″ሌላ ይመደባል።

፸፰ ደግሞም፣ እዳዎቻችሁን በሚመለከት እውነት እላችኋለሁ—እነሆ ″እዳዎቻችሁን ሁሉ ′እንድትከፍሉ ፍቃዴ ነው።

፸፱ እና በፊቴም ″ትሁት እንድትሆኑ፣ እና ይህን በረከት ′በቅንነት እና በየዋህነትና በእምነት ጸሎታችሁ እንድታገኙ ፍቃዴ ነው።

፹ እና ቅን እና ትሁት እስከሆናችሁ እና የእምነት ″ጸሎትን እስከተጠቀማችሁበት ድረስ፣ እነሆ የማድናችሁበት መንገድ እስከምልክላችሁ ድረስ፣ የአበዳሪዎቻችሁን ሰዎች ልብ አራራለሁ።

፹፩ ስለዚህ፣ ወደ ኒው ዮርክ ወዲያው ጻፉ እና ″በመንፈሴ እንደተሰጣችሁም መሰረት ጻፉ፤ እና በእናንት ላይ ስቃይ ለማምጣት በአዕምሮአቸው ላይ ያለውን ይወሰድ ዘንድ የአበዳሮዎቻችሁን ልብ አራራለሁ።

፹፪ እና ″ትሁት እና ታማኝ ብትሆኑ እና ስሜን የምትጠሩ እስከሆናችሁ ድረስ፣ እነሆ፣ ′ድልን እሰጣችኋለሁ።

፹፫ ለዚህም አንዴ ከባርነታችሁ ትወጡ ዘንድ፣ የተስፋ ቃልም እሰጣችኋለሁ።

፹፬ ገንዘብ በመቶዎች፣ ወይም በሺዎች፣ እንዲሁም ራሳችሁን ከእስር ለማውጣት መበደር እስከምትችሉት ድረስ ለማግኘት እድል እስካገኛችሁ ድረስ፣ ይህ መብታችሁ ነው።

፹፭ እና በእጆቻችሁ የሰጠኋችሁን ንብረቶችም፣ ለዚህ አንድ ጊዜ ስማችሁን በጋራ ስምምነት ወይም በሌላ በመስጠት፣ ወይም መልካም በሚመስላችሁ፣ በእዳ አስይዙ።

፹፮ ይህን ልዩ መብት ለአንድ ጊዜ እሰጣችኋለሁ፤ እነሆም፣ በፊታችሁ የዘረጋሁትን ነገሮች፣ በትእዛዛቴ መሰረት ለማድረግ ብትቀጥሉ፣ ሁሉም ነገሮች የእኔ ናቸው፣ እና እናንተም የእኔ መጋቢዎች ናችሁ፣ እና መምህር ቤቱ እንዲሰበር አይፈቅድምና። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፸፬ ሀ ሉቃ. ፲፮፥፩–፲፪።
፸፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፱–፻።
፸፰ ሀ ቅ.መ.መ. እዳ።
ለ ት. እና ቃ. ፷፬፥፳፯።
፸፱ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ቅ.መ.መ. ትጋት።
፹ ሀ ያዕ. ፭፥፲፭።
፹፩ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፹፪ ሀ ሉቃ. ፲፬፥፲፩፤
ት. እና ቃ. ፷፯፥፲።
ለ ት. እና ቃ. ፻፫፥፴፮።

ክፍል ፻፭

በሰኔ ፳፪፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) በሚዙሪ ፊሺንግ ወንዝ ላይ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በነቢዩ አመራር ስር፣ ከኦሀዮ እና ሌሎች አካባቢዎች የመጡ ቅዱሳን በኋላ የፅዮን ሰፈር ተብሎ በሚታወቀው ጉዞ ወደ ምዙሪ ተሰልፈው ሄዱ። አላማቸውም ከምዙሪ በግድ የወጡትን ቅዱሳን አጅበው በጃክሰን የግዛት ክፍል ወደነበሩበት መሬታቸው ለመመለስ ነበር። ቅዱሳንን ያሳደዱ የምዙሪ ሰዎች የፅዮን ሰፈር ጸያፍ እርምጃ ይወስዱብናል ብለው ፈርተው ነበር እናም በክሌይ የግዛት ክፍል፣ ምዙሪ ውስጥ የሚኖሩትን ቅዱሳን አስቀድመው አጥቅተው ነበር። የምዙሪ ገዢ ቅዱሳንን ለመርዳት የገባውን ቃል መልሶ ሲወስድ፣ ጆሴፍ ይህን ራዕይ ተቀበለ።

፩–፭፣ ፅዮን የምትገነባው የሰለስቲያል ህግን ጠባቂ በመሆን ነው፤ ፮–፲፫፣ የፅዮን ቤዛነት ለጥቂት ጊዜ ተላልፏል፣ ፲፬–፲፱፣ ጌታ የፅዮንን ጦርነት ይዋጋል፤ ፳–፳፮፣ ቅዱሳን ብልሆች ይሁኑ እና ሲሰበሰቡም በታላቅ ስራዎች ኩራት አይሰማቸው፤ ፳፯–፴፣ በጃክሰን እና በአጠገቡ የግዛት ክፍሎች መሬቶች ይገዙ፤ ፴፩–፴፬፣ ሽማግሌዎች በከርትላንድ ውስጥ በጌታ ቤት ውስጥ መንፈሳዊ ስጦታ ይቀበሉ፤ ፴፭–፴፯፣ የተጠሩት እና የተመረጡት ቅዱሳን ይቀደሳሉ፤ ፴፰–፵፩፣ ቅዱሳን ለአለም የሰላም አርማን ያንሱ።

፩ የተሰቃዩ ህዝቤን [ሀ]ቤዛነት በሚመለከት ፈቃዴን ትማሩ ዘንድ ራሳችሁን ለሰበሰባችሁት እውነት እላለሁ—

፪ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ስለግለሰብ ሳይሆን ስለቤተክርስቲያኗ ስናገር፣ በህዝቤ [ሀ]መተላለፍ ባይሆን ኖሮ፣ አሁንም ይድኑ ነበር።

፫ ነገር ግን እነሆ፣ በእጆቻቸው ለምጠብቃቸው ነገሮች ታዛዥ ለመሆን አልተማሩም፣ ነገር ግን በክፋት የተሞሉ ናቸው፣ እና እቃዎቻቸውን በቅዱሳን እንደሚገባው ለድሆችና በመካከላቸው ለሚሰቃዩት [ሀ]አያካፈሉም፤

፬ እና በሰለስቲያል መንግስት ህግ መሰረት አስፈላጊ በሆነው [ሀ]ህብረትም አይተባበሩም፤

፭ እና [ሀ]ፅዮን ካለሰለስቲያል መንግስት [ለ]ህግ መሰረታዊ መርሆች ካልሆነ [ሐ]በስተቀር ልትገነባ አይቻላትም፤ አለበለዚያም ወደ ራሴ ልቀበላት አልችልም።

፮ እና ህዝቤ [ሀ]ታዛዥነት እስኪማሩ ድረስ፣ አስፈላጊም ቢሆን በሚሰቃዩባቸው ነገሮች [ለ]መገሰፅ ያስፈልጋቸዋል።

፯ የምናገረው ህዝቤን እንዲመሩ ስለተመደቡት የቤተክርስቲያኔ [ሀ]የመጀመሪያ ሽማግሌዎች አይደለም፣ ሁሉም በፍርድ ላይ አይደሉምና፤

፰ ነገር ግን በሌላ ስፍራ ስላሉት ቤተክርስቲያኔ በሚመለከት እናገራለሁ—እንዲህ የሚሉ ብዙ አሉ፥ አምላካቸው የት አለ? እነሆ፣ በችግር ጊዜ ያድናቸዋል፣ አለበለዚያም ወደፅዮን አንሄድም፣ እና ገንዘባችንንም እናስቀራለን።

፱ ስለዚህ፣ በህዝቤ [ሀ]መተላለፍ ምክንያት ሽማግሌዎቼ የፅዮን ቤዛነት ለትንሽ ዘመን ይጠብቁ ዘንድ ፍቃዴ ነው—

፻፭ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፻፥፲፫።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፻፬፥፩–፭፣ ፶፪።
፫ሀ የሐዋ. ፭፥፩–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥፴።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣
የቅድስና ህግ።

፬ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፫–፯።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፴፬።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፬፥፲፭–፲፰።
፮ሀ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣
ታዛዥ፣ መታዘዝ።

ለ ት. እና ቃ. ፺፭፥፩–፪።
ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፯ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፪–፫።
፱ሀ ት. እና ቃ. ፻፫፥፬።

፲ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ፣ እና ህዝቤ በፍጹም እንዲማሩ፣ እና አጋጣሚም እንዲያገኙ፣ እና [ሀ]ህላፊነታቸውንና ከእጆቻቸው የምፈልገውን ነገሮች በሚመለከት በፍጹም ይማሩ ዘንድ ነው።

፲፩ እና [ሀ]ሽማግሌዎቼ ከላይ የኃይል [ለ]መንፈሳዊ ስጦታ እስኪሰጣቸው ድረስ ይህም ሆኖ አይሆንም።

፲፪ እነሆ፣ ታማኝ ቢሆኑ እና በፊቴም በትህትና እስከቀጠሉ ድረስ፣ ታላቅ መንፈሳዊ ስጦታ እና በረከት በእነርሱ ላይ [ሀ]ለማፍሰስ አዘጋጅቻለሁ።

፲፫ ስለዚህ ለፅዮን ቤዛነት ሽማግሌዎቼ ለጥቂት ዘመን ይጠብቁ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፲፬ እነሆ፣ የፅዮንን ጦርነት እንዲዋጉ በእጆቻቸው አልፈልግባቸውምና፤ ከዚህ በፊት ትእዛዝ እንደሰጠሁት፣ ይህንንም አሟላለሁና—ጦርነታችሁን [ሀ]እዋጋላችኋለሁ።

፲፭ እነሆ፣ [ሀ]አጥፊው ጠላቶቼን እንዲያጠፉ እና እንዲያባክን ልኬዋለሁ፤ እና ከብዙ አመታት በኋላ ውርሴን እንዲበክሉ፣ እና ለቅዱሳኔ መሰብሰብ [ለ]በቀደስኩባቸው ምድሮች ላይ ስሜን [ሐ]እንዲሰድቡ አይተዉም።

፲፮ እነሆ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ ለቤቴ [ሀ]ጥንካሬ፣ እንዲሁም ጀግኖቼን፣ ወጣት ወንዶቼን፣ እና ጎልማሳዎቼን ለህዝቤ ቤዛነት እንዲሰበሰቡ፣ እና የጠላቶቼን ማማዎች እንዲጥሉ፣ እና [ለ]ጠባቂዎቻቸውንም እንዲበትኑ እንዲነግራቸው አዘዝኩት፤

፲፯ ነገር ግን የቤቴ ጥንካሬ ቃላቴን አላደመጡም።

፲፰ ነገር ግን ቃላቴን ያደመጡ እስካሉ ድረስ፣ በታማኝነት ቢቀጥሉ በረከት እና [ሀ]የመንፈስ ስጦታ አዘጋጅቼላቸዋለሁ።

፲፱ ጸሎታቸውን ሰምቻለሁ፣ እና ስለታቸውን እቀበላለሁ፤ እና [ሀ]እምነታቸውም ተፈትኖ እስከዚህ ድረስ ይመጡም ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፳ አሁንም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ትእዛዝንም እሰጣችኋለሁ፣ ወደዚህ እስከመጣችሁ ድረስ በአካባቢው ለመቆየት የሚችሉ ይቆዮ፤

፳፩ መቆየት የማይችሉት፣ በምስራቅ ቤተሰብ ያላቸውም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ዳግማዊ፣ እስከመደባቸው ድረስ ለትንሽ ዘመን ይቆዩ፤

፳፪ ስለዚህ ጉዳይ እመክረዋለሁ፣ እና ለእነርሱ የሚመደቡላቸው ማናቸውም ነገሮች ሁሉ ይሟላሉ።

፳፫ እና በዚህ አካባቢ የሚኖሩት ህዝቤ ሁሉ ታማኝ እና ጸሎተኛ እና በፊቴ ትሁት ይሁኑ፣ እና የገለጥኩላቸውን ነገሮችንም እንዲገልጹ በእኔ ዘንድ ጥበብ እስኪሆን ድረስ አይግለጿቸው።

፳፬ ስለፍርድም አትናገሩ፣ ስለእምነት ወይም ስለታላቅ ስራም [ሀ]ኩራት አይሰማችሁ፣ ነገር ግን በምትችሉት መጠን በአንድ አካባቢ፣ ለሰዎች ስሜት እያሰባችሁ በጥንቃቄ ተሰብሰቡ።

፳፭ እነሆም፣ [ሀ]በሰላም እና በደህንነት ታርፉ ዘንድ፣ ለህዝቦቹም፥ ፍርድ እና ጽድቅን በህጉ መሰረት ፈፅሙ፣ እና በደላችንን መልሱልን እያላችሁ፣ በአይኖቻቸው ውስጥም ውለታ እና ጸጋ እሰጣችኋለሁ።

፳፮ እነሆ፣ ባልንጀሮቼ አሁን እላችኋለሁ፣ በዚህም መንገድ፣ የእስራኤል [ሀ]ሰራዊት እጅግ ታላቅ እስኪሆን ድረስ፣ በህዝቡ አይኖች ፊት ሞገስን ታገኛላችሁ።

፲ ሀ ቅ.መ.መ. ሁለንተና።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
ለ ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፪፤ ፺፭፥፰።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲።
፲፬ ሀ ኢያ. ፲፥፲፪–፲፬፤
ኢሳ. ፵፱፥፳፭፤
ት. እና ቃ. ፺፰፥፴፯።
፲፭ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥፫–፬፤
፻፫፥፴፭።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፳፬–፳፮።
ቅ.መ.መ. መስደብ።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፶፭፤
፻፫፥፳፪፤ ፴።
ለ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።
፲፰ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፥፯–፲።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
፳፬ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፸፫።
ቅ.መ.መ. ኩራት።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፳፮ ሀ ኢዩ. ፪፥፲፩።

፳፯ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና የመደብኳቸው ሽማግሌዎቼ የቤቴን ብርታት ለመሰብሰብ ጊዜን እስከሚያገኙ ድረስ [ሀ]በፈርኦን ልብ እንዳደረግሁት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ የህዝቡን ልብ አራራለሁ፣

፳፰ እና [ሀ]ብልህ ሰዎችንም፣ በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ እና በአካባቢው በሚገኙት የግዛት ክፍሎች ውስጥ [ለ]ሊገዙ የሚችሉትን መሬቶችን ሁሉ ስለመግዛት የሰጠሁትን ትእዛዝ ይፈጸሙ ዘንድ ነው።

፳፱ እነዚህ መሬቶች እንዲገዙ ፍቃዴ ነው፤ እና ከተገዙም በኋላ ቅዱሳኔ በሰጠኋችሁ የቅድስና [ሀ]ህግጋት መሰረት ይወስዷቸውም ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፴ እና እነዚህ መሬቶች ከተገዙ በኋላ፣ የእስራኤል [ሀ]ሰራዊት በገንዘባቸው የገዙትን መሬቶቻቸውን መልሰው በመውሰዳቸው፣ እና በእነዚያም የሚገኙትን የጠላቶቼን ማማዎች በመጣላቸው፣ እና ጠባቂዎቻቸውን በመበተናቸው፣ እና የሚጠሉኝ ጠላቶቼን እስከ ሶስተኛ እና አራተኛ ትውልዶች [ለ]ስለተበቀሉልኝ ከበደል ነጻ አደርጋቸዋለሁ።

፴፩ ነገር ግን በቅድሚያ ሰራዊቴ ታላቅ ይሁን፣ እና እንደጸሀይም የጠራ፣ እንደ [ሀ]ጨረቃ የተዋበ፣ እና ዓርማዎቿ ለሁሉም ህዝብ የሚያስፈራ ይሆንም ዘንድ በፊቴም [ለ]ይቀደስ፤

፴፪ የዚህ አለም መንግስትም የፅዮን መንግስት በእርግጥም የአምላካችን እና የእርሱ ክርስቶስ [ሀ]መንግስት እንደሆነም ለማወቅ ይገደዱ ዘንድ፤ ስለዚህ፣ ለህግጋቷ [ለ]ተገዢ እንሁን።

፴፫ እውነት እላችኋለሁ፣ በከርትላንድ ምድር ውስጥ ለስሜ እንዲገነባ ባዘዝኩት በቤቴ ውስጥ የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች [ሀ]የመንፈስ ስጦታቸውን ይቀበሉ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፴፬ እና ከቤዛነቷ በኋላ ስለፅዮን እና [ሀ]ስለ ህጓ የሰጠሁት ትእዛዛት ይሟሉ እናም ይፈጸሙ።

፴፭ [ሀ]የጥሪ ቀን ነበር፣ ነገር ግን ለመምረጫ ቀን ጊዜው መጥቷል፤ እና [ለ]ብቁ የሆኑ እነርሱ ይመረጡ።

፴፮ እና [ሀ]የተመረጡትም በመንፈስ ድምፅ ለአገልጋዬ ይገለጣሉ፤ እና እነርሱም [ለ]ይቀደሳሉ፤

፴፯ እና የተቀበሉትን [ሀ]ምክር እስከተከተሉ ድረስ፣ ከብዙ ቀናት በኋላ ፅዮንን የሚመለከቱ ነገሮችን ሁሉ ያከናውኑ ዘንድ ሀይል ይኖራቸዋል።

፴፰ ደግሞም እላችኋለሁ፣ ለመቷችሁ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ሰዎች፣ የሰላም ሀሳብ አቅርቡ፤

፴፱ እና [ሀ]የሰላም [ለ]አርማ አንሱ፣ እና ለምድር ዳርቻዎችም ሰላምን አውጁ፤

፵ እና በውስጣችሁ ባለው በመንፈስ ድምፅ መሰረት ለመቷችሁም የሰላም ሀሳብ አቅርቡላቸው፣ እና [ሀ]ሁሉም ነገሮች ለጥቅማችሁ አብረው ይሰራሉ።

፵፩ ስለዚህ፣ ታማኝ ሁኑ፤ እነሆ፣ እናም አስተውሉ፣ እስከመጨረሻውም [ሀ]እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ። እንዲሁም ይሁን። አሜን።

፳፯ ሀ ዘፍጥ. ፵፯፥፩–፲፪።
፳፰ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፸፫።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፭–፴፮።
፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴።
ቅ.መ.መ. መቀደስ፣
የቅድስና ህግ፤
የትብብር ስርዓት።
፴ ሀ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፫–፲፬፤
፻፩፥፶፭፤ ፻፫፥፳፪፣ ፳፮።
ለ ት. እና ቃ. ፺፯፥፳፪።
፴፩ ሀ መኃ. ፮፥፲፤
ት. እና ቃ. ፭፥፲፬፤ ፻፱፥፸፫።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፴፪ ሀ ራዕ. ፲፩፥፲፭።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
መንግስት ወይም
መንግስተ ሰማያት።
ለ ቅ.መ.መ. መንግስት።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፺፭፥፰–፱።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ።
፴፬ ሀ ይህም ት. እና ቃ. ፵፪
“ህግ” ተብሎ ይታወቃል
ማለት ነው።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. ጥሪ፣
በእግዚአብሔር መጠራት፣
የተጠራበት።
ለ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።
፴፮ ሀ ት. እና ቃ. ፺፭፥፭።
ቅ.መ.መ. መምረጥ፣
መረጠ፣ የተመረጠ (ግስ)።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሰላም።
ለ ቅ.መ.መ. ምልክት።
፵ ሀ ሮሜ ፰፥፳፰፤
ት. እና ቃ. ፺፥፳፬፤ ፻፥፲፭።
፵፩ ሀ ማቴ. ፳፰፥፲፱–፳።

ክፍል ፻፮

በህዳር ፳፭፣ ፲፰፻፴፬ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህ ለኦሊቨር ካውድሪ ታላቅ ወንድም ለሆነው ለዋረን ካውድሪ የተሰጠ ራዕይ ነው።

፩–፫፣ ዋረን ኤ ካውድሪ በሚኖርበት አካባቢ ቀዳሚ መሪ እንዲሆን ተጠርቷል፤ ፬–፭፣ ዳግም ምፅዓት የብርሀን ልጆችን እንደ ሌባ አይደርስባቸውም፤ ፮–፰፣ የቤተክርስቲያኗ ታማኝ አገልጋይነት ታላቅ በረከቶች ይከተሉታል።

፩ አገልጋዬ ዋረን ኤ ካውድሪ [ሀ]በፍሪደም እና በአካባቢዋ ምድር ውስጥ በቤተክርስቲያኔ እንደ ሊቀ ካህናት አመራር እንዲመደብ እና እንዲሾም ፍቃዴ ነው።

፪ ዘለዓለማዊ ወንጌሌንም ይስበክ፣ እና በራሱ ስፍራ ብቻ ሳይሆን፣ በአጠገቡ በሚገኙት የግዛት ክፍሎችም ድምጹን ከፍ ያድርግና ህዝብን ያስጠንቅቅ፤

፫ እና [ሀ]መንግስተ ሰማያትንና ፅድቁንም በትህትና [ለ]በመፈለግ፣ በምሰጠው በዚህ ከፍተኛ እና ቅዱስ ጥሪም ጊዜውን ሁሉ መስዋዕት ያድርግ፣ እና አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ይጨመሩለታል፤ [ሐ]ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና።

፬ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የጌታ [ሀ]መምጣት [ለ]ቀርቦአል፣ እና [ሐ]ሌባ በሌሊት እንደሚመጣም በአለም ላይ ይደርስል—

፭ ስለዚህ፣ [ሀ]የብርሀን ልጆች ትሆኑ ዘንድም ወገባችሁን አጥብቁ፣ እና ያም ቀን በሌሊት እንደ ሌባ [ለ]አይደርስባችሁም።

፮ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ዋረን ለመንግስቴ በትር ሲሰግድና እራሱን ከተንኮለኞች ሰዎች ሲለይ በሰማይ ደስታ ነበር።

፯ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ዋረን የተባረከ ነው፣ ምህረት እሰጠዋለሁና፤ እና ልቡ [ሀ]ግብዝነት ቢኖርበትም፣ በፊቴ ትሁት እስከሆነ ድረስ ከፍ አደርገዋለሁ።

፰ የሚቆምበትም [ሀ]ጸጋ እና ማረጋገጫም እሰጠዋለሁ፤ ታማኝ ምስክርና ለቤተክርስቲያኗም ብርሀን ሆኖ ቢቀጥል በአባቴ [ለ]ቤት አክሊል አዘጋጅቼለታለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፯

በሚያዝያ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) አካባቢ፣ በከርትላንድ ኦሀዮ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል ስለክህነት የተሰጠ ራዕይ። ይህ ራዕይ የተመዘገበው በ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ቢሆንም፣ ከቁጥር ፷ እስከ ፻ አብዛኛዎቹ በህዳር ፲፩፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጡ ራዕዮችን የሚያጠቃልሉ ነበሩ። ይህ ክፍል የአስራ ሁለት ቡድንን በየካቲት እና በመጋቢት ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ከተደራጀበት ጋር የተገ

፻፮ ፩ሀ ይህም የሪዶም ከተማ፣ ኒውዮርክ እና አካባቢዋ ማለት ነው።
፫ሀ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ማቴ. ፮፥ ፴፫።
ሐ ማቴ. ፲፥ ፲፤ ት. እና ቃ. ፴፩፥ ፭።
፬ሀ ያዕ. ፭፥ ፰።
ለ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
ሐ ፩ ተሰ. ፭፥ ፪።
፭ሀ ቅ.መ.መ. ብርሀን፣ የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ራዕ. ፲፮፥ ፲፭።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ከንቱ፣ ከንቱነት።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
ለ ዮሐ. ፲፬፥ ፪፤ ኤተር ፲፪፥ ፴፪–፴፬፤ ት. እና ቃ. ፶፱፥ ፪፤ ፸፮፥ ፻፲፩፤ ፹፩፥ ፮፤ ፺፰፥ ፲፰።

ናኝ ነው። ነቢዩ ምናልባት በቡድናቸው የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን በግን ቦት ፫፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) ለመሄድ በሚዘጋጁበት ጊዜ በነበሩት ፊት ይህን ሳያ ቀርበው አልቀረም።

፩–፮፣ ሁለት ክህነቶች አሉ፥ መልከ ጼዴቅ እና አሮናዊ፤ ፯–፲፪፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነትን የያዙት በቤተክርስቲያኗ የሀላፊነት ስፍራዎች ሁሉ ለማስተዳደር ሀይል ይኖራቸዋል፤ ፲፫–፲፯፣ ኤጲስ ቆጶስ ውጪውን ሥርዓት የሚያስተዳድረውን አሮናዊ ክህነትን ያስተዳድራል፤ ፲፰–፳፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የመንፈሳዊ በረከቶችን ሁሉ ቁልፎች ይዟል፤ የአሮናዊ ክህነት የመላዕክትን አገልግሎት ቁልፎችን ይዟል፤ ፳፩–፴፰፣ በአንድነት እና በፅድቅ ውሳኔዎቻቸው የሚደረጉባቸው ቀዳሚ አመራር፣ አስራ ሁለቱ፣ እና ሰባዎች የአመራር ቡድኖችን ይመሰርታሉ፤ ፴፱–፶፪፣ የአባቶች አለቃ ስርዓትም ከአዳም እስከ ኖህ ጀምሮ ተመስርቷል፤ ፶፫–፶፯፣ የጥንት ቅዱሳን በአዳም-ኦንዳይ-አማን ተሰበሰቡ፣ እና ጌታ በእነርሱም ታየ፤ ፶፰–፷፯፣ አስራ ሁለቱ የቤተክርስቲያኗ ሀላፊዎች በስርዓት ያቀናጁ፤ ፷፰–፸፮፣ ኤጲስ ቆጶሳት እንደ እስራኤል ቋሚ ዳኛ ያገለግላሉ፤ ፸፯–፹፬፣ ቀዳሚ አመራርና አስራ ሁለቱ እንደ ቤተክርስቲያኗ ከፍተኛ ዳኝነት ስርዓቱን ይመሰርታሉ፤ ፹፭–፻፣ የክህነት ፕሬዘደንቶች የየሀላፊነት ቡድኖቻቸውን ያስተዳድራሉ።

፩ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ፣ የሌዊ ክህነትን ጨምሮ፣ በስም [ሀ]መልከ ጼዴቅና፣ [ለ]አሮናዊ የሚባሉ ሁለት ክህነቶች አሉ።

፪ የመጀመሪያው [ሀ]የመልከ ጼዴቅ ክህነት ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት መልከ ጼዴቅ ታላቅ ሊቀ ካህን ስለነበር ነው።

፫ ከእርሱ ቀን በፊት እንደ እግዚአብሔር ልጅ [ሀ]ስርዓት ቅዱስ ክህነት ተብሎ የሚጠራ ነበር።

፬ ነገር ግን ለኃያል ጌታ ስም ክብር ወይም [ሀ]አምልኮ፣ ስሙን እጅግ በጣም በመደጋገም መጠቀምን ለማስወገድ፣ የጥንት ጊዜ ቤተክርስቲያኗ የነበሩት እነርሱ፣ ያን ክህነት የመልከ ጼዴቅ ክህነት በማለት ወይም በመልከ ጼዴቅ ስም ጠሩት።

፭ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ያሉ ሌሎቹ ስልጣናት ወይም ሀላፊነቶች ሁሉ ከዚህ ክህነት ጋር [ሀ]የተያያዙ ናቸው።

፮ ነገር ግን ሁለት ክፍሎች ወይም ዋና ክፍሎች አሉ—አንዱ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ስልጣን፣ እና ሌላው አሮናዊ ወይም [ሀ]ሌዊ ክህነት ነው።

፯ [ሀ]የሽማግሌ ሀላፊነት ከመልከ ጼዴቅ ክህነት በታች የሚሆን ነው።

፰ የመልከ ጼዴቅ ክህነት የፕሬዘደንትነት አመራርን ይይዛል፣ እና በመንፈሳዊ ነገሮች ለማስተዳደር፣ በአለም ዘመኖች ሁሉ በቤተክርስቲያኗ ሀላፊነቶች ላይ ሁሉ ሀይል እና [ሀ]ስልጣን አለው።

፱ እንደ መልከ ጼዴቅ ስርዓት ሁሉ፣ የታላቅ ክህነት [ሀ]አመራር በቤተክርስቲያኗ ውስጥ በሚገኙት ሀላፊነቶች ሁሉ የማስተዳደር መብት አለው።

፲ [ሀ]ሊቀ ካህናት እንደ መልከ ጼዴቅ ስርዓት፣ በቀዳሚ አመራር መመሪያ በመንፈሳዊ ነገሮች በማስተዳደር ሀላፊነታቸው፣ እና ደግሞም በሽማግሌ አመራር፣ በካህን አመራር (የሌዊው ስርዓት)፣ በመምህርነት፣ በዲያቆንነት፣ እና በአባል ሀላፊነቶች ለማስተዳደር [ለ]መብት አላቸው።

፻፯ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
፪ ሀ ጆ.ስ.ት. ዘፍጥ. ፲፬፥ ፳፭–፵ (ተጨማሪ)፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፲፬። ቅ.መ.መ. መልከ ጼዴቅ።
፫ ሀ አልማ ፲፫፥ ፫–፲፱፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፶፯።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ማክበር።
፭ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፳፱፤ ፻፯፥ ፲፬።
፮ ሀ ዘዳግ. ፲፥ ፰–፱።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፹፩፥ ፪፤ ፻፯፥ ፳፪፤ ፷፭–፷፯፤ ፺፩–፺፪።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥ ፴፬–፴፯።

፲፩ ሊቀ ካህን በማይኖርበት ጊዜ ሽማግሌ በእርሱ ምትክ ማስተዳደር ይችላል።

፲፪ ሊቀ ካህን እና ሽማግሌ፣ ከቤተክርስቲያኗ ቃል ኪዳናት እና ትእዛዛት በመስማማት፣ በመንፈሳዊ ነገሮች ያስተዳድሩ፤ እና ከፍተኛ ባለስልጣናት በማይኖሩበት ጊዜ፣ በእነዚህ የቤተክርስቲያኗ ሀላፊነቶች ሁሉ የማስተዳደር ሀላፊነት አላቸው።

፲፫ ሁለተኛው ክህነት [ሀ]አሮናዊ ክህነት ተብሎ ይጠራል፣ ምክንያቱም [ለ]በአሮን እና በዘሩ፣ በትውልዶቻቸው ሁሉ፣ የተሰጣቸው ነበርና።

፲፬ አነስተኛው ክህነት ተብሎ የሚጠራበት ምክንያትም ከታላቁ፣ ወይም ከመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ ጋር [ሀ]የተያያዘ ስለሆነ እና ለውጪአዊ ስርዓቶችን ለማስተዳደር ሀይል ስላለው ነው።

፲፭ [ሀ]የኤጲስ ቆጶስ አመራርም የዚህ ክህነት ስልጣን አመራር ነው፣ እና የዚህንም ቁልፎች ወይም ስልጣን ይዟል።

፲፮ የአሮን [ሀ]እውነተኛ ተወላጅ ካልሆነ በስተቀር፣ ማንም ሰው ለዚህ ሀላፊነት፣ ወይም የዚህን ክህነት ቁልፎች ለመያዝ፣ ህጋዊ መብት የለውም

፲፯ ነገር ግን እንደ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ሊቀ ካህን በአነስተኛ ሀላፊነቶች ሁሉ ለማስተዳደር ስልጣን ስላለው፣ የአሮን እውነተኛ ተወላጅ በማይገኝበት ጊዜ፣ በመልከ ጼዴቅ ክህነት [ሀ]አመራር በኩል ለዚህ ሀይል ከተጠራና ከተለየ እና [ለ]ከተሾመ በኋላ በኤጲስ ቆጶስ ሀለፊነት ለማስተዳደር ይችላል።

፲፰ የከፍተኛው፣ ወይም የመልከ ጼዴቅ ክህነት፣ ሀይል እና ስልጣን በቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ በረከቶች ላይ ሁሉ [ሀ]ቁልፎችን መያዝ ነው።

፲፱ በተጨማሪም፣ የመንግስተ ሰማያትን [ሀ]ሚስጥራት ለመቀበል ልዩ መብት እንዲኖረው፣ ሰማያት ለእነርሱ እንዲከፈቱላቸው፣ ከበኩሩ ቤተክርስቲያንና [ለ]ከአጠቃላይ ተሰብሳቢዎች ጋር እንዲገናኝ፣ እና ከእግዚአብሔር አብ እና ከአዲስ ኪዳን [ሐ]አማላጅ ከሆነው ከኢየሱስ ጋር መገናኘትን እና በእነርሱም መገኘት ለመደሰት ነው።

፳ የአነስተኛው ክህነት፣ ወይም የአሮናዊ ክህነት፣ ሀይል እና ስልጣን፣ ከቃል ኪዳናት እና ትእዛዛት ጋር በመስማማት፣ የመላእክትን አገልግሎት [ሀ]ቁልፎች ለመያዝ እና የውጪአዊ [ለ]ስርዓቶች የሆኑትን የወንጌሉን ፊደል እና ለኃጢአት [ሐ]ስርየት የንስሐ [መ]ጥምቀትን ለማስተዳደር ነው።

፳፩ ስለአስፈላጊነታቸውም ፕሬዘደንቶች፣ ወይም ከተለያዩ ከእነዚህ ሁለት ክህነቶች ውስጥ በተላያዩ ሀላፊነቶች ከተሾሙት መካከል የሚመጡ ወይም የሚሾሙ መሪዎች አሉ።

፳፪ [ሀ]ከመልከ ጼዴቅ ክህነትም፣ ሶስቱ ሊቀ ካህን [ለ]መሪዎች በቡድኑ ተመርጠው፣ ለሀለፊነቱ ተመድበውና ተሹመው፣ እና በቤተክርስቲያኗ እምነት፣ ታማኝነት፣ እና ጸሎት [ሐ]ተደግፈው የቤተክርስቲያኗን አመራር ቡድን ይመሰርታሉ።

፳፫ ተጓዥ [ሀ]አስራ ሁለቱ አማካሪዎች አስራ ሁለቱ [ለ]ሐዋርያት፣ ወይም ለአለም ሁሉ የክርስቶስ ስም ልዩ ምስክሮች፣ ተብለው ተጠርተዋል—በዚህም በጥሪአቸው

፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. አሮናዊ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. አሮን፣
የሙሴ ወንድም።
፲፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፶፪፤ ፻፯፥፭።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፲፬–
፳፩፤ ፻፯፥፷፰–፸፮።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፲፱ ሀ አልማ ፲፪፥፱–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፷፫፥፳፫፤
፹፬፥፲፱–፳፪።
ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር
ሚስጥሮች።
ለ ዕብ. ፲፪፥፳፪–፳፬።
ሐ ቅ.መ.መ. አማላጅ።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፲፫፤
፹፬፥፳፮–፳፯።
ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ሐ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. የመልከ
ጼዴቅ ክህነት።
ለ ት. እና ቃ. ፺፥፫፣ ፮፤
፻፯፥፱፣ ፷፭–፷፯፣
፸፰–፹፬፣ ፺፩–፺፪።
ሐ ቅ.መ.መ. የቤተክርስቲያን
መሪዎችን መደገፍ።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፴፫–፴፭።
ለ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።

ሀላፊነታቸው ከቤተክርስቲያኗ ሌሎች ሀላፊዎች ጋር ይለያያሉ።

፳፬ እና ከዚህ በፊት ከተጠቀሱት ሶስት ፕሬዘደንቶች ጋረ እኩል ስልጣን እና ሀይል ያለው ቡድንም ይሰራሉ።

፳፭ [ሀ]ሰባዎቹ ወንጌልን እንዲሰብኩ፣ እና ለአህዛብና በአለም ሁሉ ልዩ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋል—በዚህም በጥሪአቸው ሀላፊነታቸው ከቤተክርስቲያኗ ሌሎች ሀላፊዎች ጋር ይለያያሉ።

፳፮ እና ከተጠቀሱት አስራ ሁለቱ ልዩ ምስክሮች ወይም ሐዋርያት ጋር እኩል ስልጣን እና ሀይል ያለው ቡድንም ይሰራሉ።

፳፯ በማንኛቸውም በእነዚህ ቡድኖች የሚያደርጉ እያንዳንዱ ውሳኔዎች በአንድ ድምፅ መሆን አለባቸው፤ ይህም ማለት፣ እርስ በራስ ውሳኔዎቻቸው አንድ ሀይል ወይም ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ የእያንዳንዱ ቡድን እያንዳንዱ አባል በውሳኔው መስማማት አለባቸው—

፳፰ ሁኔታዎች በተቃራኒ እንዲሆን በማያስችሉበት ጊዜም አብላጫዎቹ ቡድንን መስራት ይችላሉ—

፳፱ ጉዳዩ ይህ ካልሆነ በስተቀር፣ ውሳኔዎቻቸው በመልከ ጼዴቅ ስርዓት ተሹመው የነበር እና ጻድቅና ቅዱስ ሰዎች እንደነበሩት የጥንት ሶስት ፕሬዘደንቶች ውሳኔዎች እንደነበራቸው አንድ አይነት በረከቶች መብት አይኖራቸውም።

፴ የእነዚህ ቡድኖች፣ ወይም የማንኛቸውም፣ ውሳኔዎችም ሁሉ [ሀ]ፅድቅ፣ በቅድስና፣ እና ልብን በማዋረድ፣ በየዋህነትና በትዕግስት፣ እና በእምነት፣ እና [ለ]በበጎነት፣ እና በእውቀት፣ ራስን በመግዛት፣ በመፅናት፣ እግዚአብሔርን በመምሰል፣ በወንድማማች መዋደድ እና በፍቅር ይድረሱ፤

፴፩ ምክንያቱም የተስፋ ቃሉ እነዚህ ነገሮች በእነርሱ አብዝተው የሚገኙ ቢሆን በጌታ እውቀት [ሀ]ፍሬ የሌላቸው አይሆኑም የሚል ነውና።

፴፪ እና እነዚህ ቡድኖች ማንኛውንም ውሳኔ ያለፅድቅ ባለመሆን የሰሩበት ጉዳይ ካለ፣ ይህም የቤተክርስቲያኗ መንፈሳዊ ባለስልጣናት በሆኑት በተለያዩ ቡድኖች አጠቃላይ ተሰብሳቢዎች ፊት ይቅረብ፤ አለበለዚያ ለውሳኔአቸው ምንም ይግባኝ አይኖርም።

፴፫ አስራ ሁለቱ፣ በሰማይ ከተመሰረተው ጋር በመስማማት፣ መጀመሪያ ወደ [ሀ]አህዛብ እና ሁለተኛም የአይሁዶች ቤተክርስቲያኗን ለመገንባት እና የእርሷን ጉዳዮች በሀገሮች ውስጥ ሁሉ ለመቆጣጠር፣ በቤተክርስቲያኗ አመራር መሪነት በጌታ ስም በማስተዳደር የሚጓዙ ከፍተኛ ሸንጎዎች ናቸው።

፴፬ ሰባዎች፣ [ሀ]በአስራ ሁለቱ ወይም በሚጓዙት ከፍተኛ ሸንጎ አመራር በኩል፣ መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ሁለተኛም ወደ አይሁዶች፣ ቤተክርስቲያኗን በመገንባት እና የእርሷን ጉዳዮች በሀገሮች ውስጥ ሁሉ በመቆጣጠር በጌታ ስም ይስሩ—

፴፭ አስራ ሁለቱ፣ መጀመሪያ ወደ አህዛብ እና ሁለተኛም ወደ አይሁዶች፣ በመላክ፣ ቁልፎችን በመያዝ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በማወጅ በሮችን ለመክፈት ተልከዋል።

፴፮ በፅዮን ካስማዎች የአካባቢው [ሀ]ከፍተኛ ሸንጎዎች በቤተክርስቲያኗ ጉዳይ ላይ፣ በውሳኔዎቻቸው ሁሉ ከአመራር ቡድን ወይም ከተጓዥ ከፍተኛ ሸንጎ ጋር እኩል ስልጣን ያላቸው ቡድኖች ያቋቁሙ።

፴፯ በፅዮን ውስጥ ያሉት ከፍተኛ ሸንጎ በፅዮን ካስማ ውስጥ ካሉት የአስራ ሁለቱ ቡድኖች ጋር በውሳኔዎቻቸው ሁሉ፣ በቤ

፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ሰባ።

፴ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፴፮።
ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።

ለ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፵፩።
ቅ.መ.መ. በጎነት።

፴፩ ሀ ፪ ጴጥ. ፩፥፭–፰።

፴፫ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፥፵፪፤
፫ ኔፊ ፲፮፥፬–፲፫፤
ት. እና ቃ. ፺፥፰–፱።

፴፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፪፥፳፩።

፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ከፍተኛ ሸንጎ።

ተክርስቲያኗ ጉዳዮች እኩል ስልጣን ያለው ቡድን ያቋቁማሉ።

፴፫ ለመስበክ እና ወንጌሉን ለማስተዳደር እርዳታ ሲያስፈልጋቸው፣ በማንም ሌሎች ምትክ፣ [ሀ]ሰባዎችን መጥራት የሚጓዙት ከፍተኛ ሸንጎ ሀላፊነት ነው።

፴፱ በትልቁ የቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፎች ውስጥ ሁሉ፣ በራዕይ እንደሚመደቡላቸው፣ [ሀ]ወንጌል ሰባኪዎችን መሾም የአስራ ሁለቱ ሀላፊነት ነው—

፵ የዚህ ክህነት ስርዓት የሚረጋገጠው ከአባት ወደ ወንድ ልጅ በሚተላለፍ፣ እና ቃል ኪዳን ለተገባላቸው ለእውነተኛ ተወላጆች ምርጥ ዘርም የሚገባ ነበር።

፵፩ ይህ ስርዓት [ሀ]በአዳም ዘመን የተቋቋመ፣ እና እንደዚህም [ለ]በዝርያ የተላለፈም ነበር።

፵፪ በስልሳ ዘጠኝ አመቱ በአዳም ወደ ተሾመውና (ከአዳም) ከመሞቱ ሶስት አመት በፊት ወደተባረከው፣ እና ትውልዶቹ በጌታ ምርጥ እንዲሆኑና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንዲጠበቁ በአባቱ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ወደ ተቀበለው ወደ [ሀ]ሴት ከአዳም ሄደ፤

፵፫ እርሱ (ሴት) [ሀ]ፍጹም ሰው ስለነበር፣ እና [ለ]በአምሳያነቱም እንደ አባቱ መልክ ስለነበር፣ በዚህም ምክንያት በሁሉም ነገሮች አባቱን ይመስል ነበር፣ እና ከእርሱም የሚለየው በእድሜ ብቻ ነበር።

፵፬ ኢኖስም በአንድ መቶ ሰላሳ አራት አመት እና አራት ወር እድሜው በአዳም እጅ ተሾመ።

፵፭ እግዚአብሔር ቃይናን በአርባ አመቱ በዱር ውስጥ ጠራው፤ በሸዶላማቅ ስፍራ በመጓዝም ከአዳም ጋር ተገናኘ። ሹመቱን ሲቀበል እድሜው ሰማንያ ሰባት ነበር።

፵፮ መለልኤል ደግሞም በባረከው በአዳም እጅ ሲሾም እድሜው አራት መቶ ዘጣና ስድስት አመትና ሰባት ቀን ነበር።

፵፯ ያሬድም ደግሞ በባረከው በአዳም እጅ ሲሾም እድሜው ሁለት መቶ አመት ነበር።

፵፰ [ሀ]ሔኖሕ በአዳም እጅ ሲሾም ሀያ አምስት አመቱ ነበር፤ እና በስልሳ አምስት አመቱም አዳም ባረከው።

፵፱ እና ጌታን አየ፣ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣ እና ሁልጊዜ በጌታ ፊት ነበር፤ እና ለሶስት መቶ ስልሳ አምስት አመታት [ሀ]አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣ [ለ]በሚቀየርበት ጊዜ እድሜው አራት መቶ ሰላሳ ነበር።

፶ [ሀ]ማቱሳላ በአዳም እጅ ሲሾም አንድ መቶ አመቱ ነበር።

፶፩ ላሜህ በሴት እጅ ሲሾም እድሜው ሰላሳ ሁለት ነበር።

፶፪ [ሀ]ኖህ በማቱሳላ እጅ ሲሾም አስር አመቱ ነበር።

፶፫ ከአዳም ሞት ሶስት አመት በፊት፣ [ሀ]ሊቀ ካህናት የነበሩትን ሴትን፣ ኢኖስን፣ ቃይናን፣ መለልኤልን፣ ያሬድን፣ ሄኖህን፣ እና ማቱሳላን ጻድቅ ከነበሩ ትውልዶቻቸው ጋር ወደ [ለ]አዳም-ኦንዳይ-አማን ሸለቆ ጠራቸው፣ እና በዚያም በረከቱን ሰጣቸው።

፶፬ እና ጌታን አዩት፣ እና ተነስተውም [ሀ]አዳምን ባረኩ፣ እና [ለ]ሚካኤል፣ ልኡል፣ የመላእክት አለቃ ብለው ጠሩት።

፶፭ እና ጌታ አዳምን አፅናናው፣ እንዲህም አለው፥ መሪ አድርጌሀለሁ፤ የአህዛብ

፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሰባ።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል ሰባኪ፤
የአባቶች አለቃ፣
ፓትሪያርክ።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. አዳም።
ለ ዘፍጥ. ፭፤
ት. እና ቃ. ፹፬፥፮–፲፮፤
ሙሴ ፮፥፲–፳፭።
፵፪ ሀ ቅ.መ.መ. ሴት።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. ፍጹም።
ለ ዘፍጥ. ፭፥፫።
፵፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሔኖክ።
፵፱ ሀ ዘፍጥ. ፭፥፳፬፤
ዕብ. ፲፩፥፭፤
ሙሴ ፯፥፴፱።
ለ ቅ.መ.መ. የተቀየሩ ሰዎች።
፶ ሀ ቅ.መ.መ. ማቱሳላ።
፶፪ ሀ ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ።
፶፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ለ ት. እና ቃ. ፸፰፥፲፭፤ ፻፲፯።
ቅ.መ.መ. አዳም-ኦንዳይ-አማን።
፶፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፳፩።
ቅ.መ.መ. አዳም።
ለ ቅ.መ.መ. ሚካኤል።

ሙላትም ከአንተ ይመጣሉ፣ እና በእነርሱም ላይ ለዘለአለም [ሀ]ልዑል ነህ።

፶፮ እና አዳም በተሰበሰቡት መካከል ቆመ፤ እና ምንም እንኳን በእድሜው ያጎነበሰ ቢሆንም፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፣ እስከመጨረሻ ትውልዱ ድረስ ለዘሩ ምን እንደሚደርስባቸው [ሀ]ተነበየ።

፶፯ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሔኖህ መፅሐፎች ውስጥ ተፅፈው ነበር፣ እና በጊዜአቸውም ይመሰከሩባቸዋል።

፶፰ የቤተክርስቲያኗን ሌሎች ሀላፊዎች [ሀ]መሾም እና ማደራጀትም [ለ]የአስራ ሁለቱ ሀላፊነት ነው፣ እንዲህም በሚል ራዕይ በመስማማት፥

፶፱ በፅዮን ምድር ውስጥ ለክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ የቤተክርስቲያኗን ጉዳይ በሚመለከት ከቤተክርስቲያኗ [ሀ]ህግጋት ተጨማሪ—

፷ እውነት እላችኋለሁ ይላል የሰራዊት ጌታ፣ የሽማግሌ ሀላፊነት ያላቸውን የሚመራ የሽማግሌዎች [ሀ]አመራር ያስፈልጋል፤

፷፩ እና ደግሞም [ሀ]የካህን ሀላፊነት ያላቸውን የሚመራ ካህን ያስፈልጋል፤

፷፪ እና ደግሞም፣ በዚህም አይነት፣ የመምህራን ሀላፊነት ያላቸውን [ሀ]የሚመራ መምህር፣ ደግሞም ዲያቆናት—

፷፫ ስለዚህ፣ ከዲያቆን እስከ መምህር፣ እና ከመምህር እስከ ካህን፣ እና ከካህን እስከ ሽማግሌ፣ በቤተክርስቲያኗ ቃል ኪዳኖች እና ትእዛዛት መሰረት በተለያዩ ሀላፊነቶች እንዲመደቡ ያስፈልጋል።

፷፬ ከዚያም ከሁሉም በላይ የሆነው፣ የታላቅ ክህነት ይመጣል።

፷፭ ስለዚህ፣ ከታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት አንዱ የክህነት ባለስልጣናትን ለመምራት መመደብ አለበት፣ እና እርሱም የቤተክርስቲያኗ የታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት ተብሎ ይጠራል፤

፷፮ ወይም፣ በሌላ ቃላትም፣ በቤተክርስቲያኗ ታላቅ ክህነት በበላይነት [ሀ]የሚመራ ሊቀ ካህን ይጠራል።

፷፯ ከዚህም እጆችን [ሀ]በመጫን በቤተክርስቲያኗ ላይ ስርዓቶች እና በረከቶች የሚከናወኑበት ይመጣሉ።

፷፰ ስለዚህ፣ የኤጲስ ቆጶስ ሀለፊነት ከዚህ ጋር እኩል አይደለም፤ [ሀ]የኤጲስ ቆጶስ ሀለፊነት የስጋዊ ነገሮችን ለማስተዳደር ነውና፤

፷፱ ይህም ቢሆን፣ የአሮን [ሀ]እውነተኛ ተወላጅ ካልሆነ በስተቀር፣ ኤጲስ ቆጶስ [ለ]ከታላቅ ክህነት መመረጥ አለበት፤

፸ የአሮን እውነተኛ ተወላጅ ካልሆነ በስተቀር የዚህን ክህነት ቁልፍ ለመያዝ አይችልምና።

፸፩ ይህም ቢሆን፣ ሊቀ ካህን፣ ወይም እንደ መልከ ጼዴቅ አይነት ስርዓት፣ በእውነት መንፈስ እያወቃቸው፣ በስጋዊ ነገሮች ለማስተዳደር መለያየት ይቻላል፤

፸፪ ዳግሞም ከቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች መካከል በመረጣቸው ወይም በሚመርጣቸው አማካሪዎቹ እርዳታ፣ የእስራኤል [ሀ]ዳኛ እንዲሆን፣ የቤተክርስቲያኗን ጉዳይ እንዲያከናውን፣ በሚተላለፉት ላይ በፊቱ በሚቀርበው ምስክር በህግጋት መሰረት ለፍርድ ይቀመጣል።

፸፫ ይህም የአሮን እውነተኛ ተወላጅ ባይሆንም እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት ወደ ታላቅ ክህነት የተሾመው ኤጲስ ቆጶስ ሀላፊነት ነው።

፸፬ የፅዮን ድንበር አድጋ እና ሌላ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ዳኛ በፅዮን ወይም በሌላ ቦታ ውስጥ እንዲኖር አስፈላጊ እስኪሆን ድረስ፣ እንደዚህም ዳኛ እንዲሁም በፅዮን ነዋሪዎች

፶፭ ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፲፮።
፶፮ ሀ ሙሴ ፭፥፲።
፶፰ ሀ ቅ.መ.መ. መሾም፣ ሹመት።
ለ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
፶፱ ሀ ት. እና ቃ. ፵፫፥፪–፱።
፷ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፹፱–፺።
፷፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፹፯።
፷፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፹፭–፹፮።
፷፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፱፣ ፺፩–፺፪።
ቅ.መ.መ. ፕሬዘደንት።
፷፯ ሀ ቅ.መ.መ. እጅን መጫን።
፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፷፱ ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፲፭–፳፩፤
፹፬፥፳፱፤ ፻፯፥፲፫–፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፸፪ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፲፯–፲፰።

ወይም በፅዮን ካስማዎች ወይም ለአገልግሎት በሚመደብበት በማንኛውም በቤተክርስቲያኗ ቅርንጫፍ ውስጥ መካከል ዋና ዳኛ ይሆናል።

፸፭ እና ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳት እስከተመደቡም ድረስ በዚህ ሀላፊነት ውስጥ ይሰራሉ።

፸፮ ነገር ግን የአሮን እውነተኛ ተወላጅ ለዚህ ክህነት አመራር፣ ለዚህ አገልግሎት [ሀ]ቁልፎች፣ እንደ መልከ ጼዴቅ ክህነት ስርዓት የታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት ለፍርድ ከሚመጣበት ጊዜ በስተቀር ያለአማካሪዎች በራሱ ሀሳብ በኤጲስ ቆጶስ ሀላፊነት ለመስራት፣ በእስራኤል ውስጥም በፍርድ ለመቀመጥ ህጋዊ መብት አለው።

፸፯ እና የእነዚህ ሸንጎዎች ውሳኔም እንዲህ ከሚለው ትእዛዝ ጋርም የሚስማማ ይሆናል፥

፸፰ ዳግሞም እውነት እላችኋለሁ፣ ለቤተክርስቲያኗ በጣም አስፈላጊ ጉዳዮች፣ እና ለቤተክርስቲያኗ በጣም [ሀ]አስቸጋሪ የህግ ጉዳዮች በኤጲስ ቆጶስ ወይም በዳኛ ውሳኔ በቂ ሆኖ ካልተገኘ፣ ወደ ቤተክርስቲያኗ ሸንጎ፣ በታላቅ ክህነት [ለ]አመራር ፊት ይተላለፋል እና ይወሰዳልም።

፸፱ እና የታላቅ ክህነት ሸንጎ አመራር ሌሎች ሊቀ ካህናትን፣ እንዲሁም አስራ ሁለትን፣ እንደ አማካሪዎች እንዲረዱ ለመጥራት ሀይል አለው፣ እና እንደዚህም የታላቅ ክህነት ሸንጎ አመራር እና አማካሪዎቹ በምስክሮቹ ላይ በቤተክርስቲያኗ ህግጋት መሰረት ውሳኔ ላይ ለመድረስ ሀይል አላቸው።

፹ እና ከዚህ ውሳኔ በኋላ በጌታ ፊት ይህ ደግሞም አይታሰብም፤ ይህም የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ሸንጎ ነውና፣ እና በመንፈሳዊ ጉዳዮች ውዝግብ ላይም የመጨረሻ ውሳኔን ይሰጣሉና።

፹፩ በቤተክርስቲያኗ አባል ሆኖ ከቤተክርስቲያኗ ሸንጎ ውጪ የሆነ ማንም የለም።

፹፪ እና የታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት እስከተላለፈ ድረስ፣ በታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት አስራ ሁለት አማካሪዎች በሚረዱት በቤተክርስቲያኗ ዋና ሸንጎ ፊት ይቀርባል፤

፹፫ እና በእርሱ ላይ የሚደረጉት ውሳኔዎች እርሱን በሚመለከት ላለው ውዝግብ መጨረሻ ይሆናል።

፹፬ እንደዚህም፣ በእውነት እና በፅድቅ መሰረት ሁሉም ነገሮች በስርዓትና በክብር በፊቱ ይደረጉ ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር [ሀ]ፍትህና ህግጋት ውጪ የሚሆን ማንም የለም።

፹፭ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]የዲያቆንነት ስልጣን ፕሬዘደንት ሀላፊነት አስራ ሁለት ዲያቆናትን ለመምራት፣ ከእነርሱም ጋር በሸንጎ ለመቀመጥ፣ እና፣ በተሰጡት ቃል ኪዳኖች መሰረት እርስ በራስ በመተናነጸት ሀላፊነታቸውን [ለ]ለማስተማር ነው።

፹፮ ደግሞም [ሀ]የመምህርነት ስልጣን ፕሬዘደንት ሀላፊነት ሀያ አራት መምህራንን ለመምራት፣ ከእነርሱም ጋር በሸንጎ ለመቀመጥ፣ በቃል ኪዳኖች እንደተሰጠው የስልጣናቸውን ሀላፊነት ለማስተማር ነው።

፹፯ ደግሞም የአሮናዊ ክህነት ፕሬዘደንት ሀላፊነት አርባ ስምንት [ሀ]ካህናትን ለመምራት፣ እና ከእነርሱም ጋር በሸንጎ ለመቀመጥ፣ በቃል ኪዳኖች እንደተሰጠም የስልጣናቸውን ሀላፊነቶች ለማስተማር ነው—

፹፰ ይህም ፕሬዘደንት [ሀ]ኤጲስ ቆጶሱ ይሁን፤ ከዚህ ክህነት ሀላፊነቶች አንዱ ይህ ነውና።

፹፱ ዳግም፣ የሽማግሌዎች ስልጣን ፕሬዘደንት ሀላፊነት ዘጠና ስድስት [ሀ]ሽማግሌዎችን ለመምራት፣ እና ከእነርሱም ጋር በሸ

፸፮ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፸፰ሀ ት. እና ቃ. ፻፪፥፲፫፣ ፳፫።
ለ ት. እና ቃ. ፷፰፥፳፪።
፹፬ሀ ቅ.መ.መ. ፍትህ።
፹፭ሀ ቅ.መ.መ. ዲያቆን።
ለ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳፫፤ ፹፰፥፸፯–፸፱፣ ፻፲፰።
፹፮ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፶፫–፷።
ቅ.መ.መ. መምህር፣ የአሮናዊ ክህነት።
፹፯ሀ ቅ.መ.መ. ካህን፣ የአሮናዊ ክህነት።
፹፰ሀ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፹፱ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።

ንጎ ለመቀመጥ፣ እና በቃል ኪዳናት መሰረት ለማስተማር ነው።

፺ ይህ አመራር ከሰባው ልዩ የሆነ ነው፣ እና በአለም ሁሉ [ሀ]ለማይጓዙት የታቀደ ነው።

፺፩ ደግሞም፣ የታላቅ ክህነት ፕሬዘደንት ሀላፊነት ቤተክርስቲያኗን ሁሉ [ሀ]ለመምራት፣ እና እንደ [ለ]ሙሴ አይነት ለመሆን ነው—

፺፪ እነሆ፣ አዎን፣ የቤተክርስቲያኗ የበላይ ለሚሆን የሚሰጡትን የእግዚአብሔርን [ሀ]ስጦታዎች ሁሉ የያዘ [ለ]ባለራዕይ፣ [ሐ]ገላጭ፣ ተርጓሚ፣ እና [መ]ነቢይ ይሆን ዘንድ ይህም ጥበብ ነው።

፺፫ እና ከሰባዎቹ መካከል ተመርጠው በሰባት ፕሬዘደንቶች ይመሩ ዘንድ፣ ይህም [ሀ]ስለሰባዎች ስርዓት በተሰጠው ራዕይ መሰረት ነው፤

፺፬ እና ከእነዚህ ፕሬዘደንቶች መካከል ሰባተኛው ፕሬዘደንት ስድስቱን የሚመራ ይሁን፤

፺፭ እና እነዚህ ሰባት ፕሬዘደንቶችም አባል ከሆኑባቸው ከመጀመሪያዎቹ ሰባዎች ተጨማሪ ሌሎች ሰባዎችን ይምረጡ፣ እና እነርሱንም የሚመሩ ይሁኑ፤

፺፮ እና ደግሞ በአስፈላጊው የወይን ስፍራ አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ሌሎች ሰባዎችም፣ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት ይመረጡ።

፺፯ እና እነዚህ ሰባዎች፣ መጀመሪያ ለአህዛብ እና ደግሞም ለአይሁዶች፣ [ሀ]ተጓዥ አገልጋዮች ናቸው።

፺፰ በአስራ ሁለቱ ወይም በሰባዎች አባል ያልሆኑት፣ የቤተክርስቲያኗ ሌሎች ሀላፊዎች ግን፣ ምንም እንኳን እንደዚህ አይነት ከፍተኛ ሀላፊነትና ስልጣናት በቤተክርስቲያኗ ቢኖራቸውም፣ በህዝብ ሁሉ መካከል ለመጓዝ ሀላፊነት የላቸውም፣ ነገር ግን ጉዳዮቻቸው እንደሚፈቅድላቸው ይጓዙ።

፺፱ ስለዚህ፣ አሁን እያንዳንዱም ሰው [ሀ]ተግባሩን፣ በተመደበበት ሀላፊነትም [ለ]በሙሉ ትጋት መስራትን ይማር።

፻ [ሀ]ሰነፍ የሆነው እርሱ ለመቆም ብቁ ሆኖ አይቆጠርም፣ እና ሀላፊነቱን የማይማር እና እራሱን ተቀባይ አድርጎ የማያሳይ ለመቆም [ለ]ብቁ ሆኖ አይቆጠርም። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፰

በታህሳስ ፳፮፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.)፣ በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህን ክፍል የተሰጠው ከዚህ በፊት እንደ ሰባ የተሾመውና ሀላፊነቱን እንዲያውቅ ራዕይ ለመጠየቅ ወደ ነቢዩ የመጣው ላይመን ሸርመን በጠየቀበት አይነት ነበር።

፩–፫፣ ላይመን ሸርመን ኃጢአቱ ተሰርዮለታል፤ ፬–፭፣ ከቤተክርስቲያኗ መሪ ሽማግሌዎች ጋር አብሮ ይቆጠር፤ ፮–፰፣ ወንጌሉን እንዲሰብክና ወንድሞቹን እንዲያጠናክር ተጠርቷል።

፺ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፴፯።

፺፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፱፤ ፷፭–፷፯።

ለ ት. እና ቃ. ፳፰፥፪፤ ፻፫፥፲፮–፳፩።

፺፪ ሀ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ስጦታዎች።

ለ ሞዛያ ፰፥፲፫–፲፰። ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።

ሐ ቅ.መ.መ. ራዕይ።

መ ት. እና ቃ. ፳፩፥፩። ቅ.መ.መ. ነቢይ።

፺፫ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፴፰። ቅ.መ.መ. ሰባ።

፺፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፴፰–፻፴፱።

፺፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሁለንተና።

ለ ቅ.መ.መ. ትጋት።

፻ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥፳፮–፳፱። ቅ.መ.መ. ስራ ሰልቺ፣ ስራ ፈቺ።

ለ ቅ.መ.መ. ብቁ፣ ብቁነት።

፩ አገልጋዬ ላይመን ጌታ ለአንተ እንዲህ ይሏል፥ በዚህ ማለዳ ከመደብኩት ምክር ትቀበል ዘንድ ወደዚህ በመምጣትህ ምክንያት ኃጢአትህ ተሰርዮልሀል።

፪ ስለዚህ፣ ስለመንፈሳዊ አቋምህ በሚመለከት ነፍስህ ″ትረፍ እና ድምጼን መቋቋምህንም አቁም።

፫ እና ተነሳ እና የገባሀውንና የምትገባውን ቃል ኪዳንህን ታከብር ዘንድ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በተጨማሪ ተጠንቀቅ፣ እና በጣም ታላቅ በሆኑ በረከቶችም ትባረካለህ።

፬ አገልጋዮቼ ″በክብር ስብሰባ እንዲሰበሰቡ እስኪጠሩ ድረስ በትእግስት ጠብቅ፣ ከዚያም ከመጀመሪያ ሽማግሌዎቼ ጋር ትታወሳለህ፣ እና ከመረጥኳቸው ከሚቀሩት ሽማግሌዎቼ ጋር መብትን በሹመት ትቀበላለህ።

፭ እነሆ፣ በታማኝነት ከቀጠልክ ይህም ለአንተ የአብ ″ቃል ኪዳን ነው።

፮ እና ከዚያም ጊዜ በኋላ በምልክህ በማንኛውም ስፍራ ወንጌሌን ″ለመስበክ መብት ይኖርህ ዘንድ በዚያም ቀን ይህ ይሟላልሀል።

፯ ስለዚህ፣ በንግግርህ ሁሉ፣ በጸሎቶችህ ሁሉ፣ በምታበረታታው ሁሉ፣ እና በምታደርገው ሁሉ ወንድሞችህን ″አጠናክር።

፰ እነሆም እና አስተውል፣ ልባርክህ እና ″ላድንህ ለዘለአለም ከአንተ ጋር ነኝ። አሜን።

ክፍል ፻፱

በመጋቢት ፳፯፣ ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.) በከርትላን ኦሀዮ ቤተመቅደስ ቅደሳ የቀረበ ጸሎት። በነቢዩ ፅሁፍ መሰረት፣ ይህ ጸሎት የተሰጠው በራዕይ ነበር።

፩–፭፣ የከርትላንድ ኦሀዮ ቤተመቅደስ የተገነባው የሰው ልጅ የሚጎበኘው ስፍራ እንዲሆን ነው፤ ፮–፳፩፣ የጸሎት፣ የጾም፣ የእምነት፣ የመማሪያ፣ የክብር፣ እና የስርዓት ቤት፣ እና የእግዚአብሔር ቤት ይሁን፤ ፳፪–፴፫፣ የጌታን ህዝብ የሚቃወሙ ንስሀ ያልገቡት ዝም ይበሉ፤ ፴፬–፵፪፣ ቅዱሳን በሀይል ጻድቃንን ወደ ፅዮን ለመሰብሰብ ይሂዱ፤ ፵፫–፶፫፣ በመጨረሻው ቀን በክፉዎች ላይ ከሚፈሰው መጥፎ ነገሮች ቅዱሳን ይዳኑ፤ ፶፬–፶፰፣ ሀገሮች፣ ህዝብና ቤተክርስቲያናት ለወንጌሉ ይዘጋጁ፤ ፶፱–፷፯፣ አይሁዶች፣ ላማናውያን፣ እና እስራኤል ሁሉ ይዳኑ፤ ፷፰–፹፣ ቅዱሳን በክብር የክብርን አክሊል ይጫኑ እና ዘለአለማዊ ደህንነትንም ያግኙ።

፩ ″ቃል ኪዳንን የሚጠብቁትንና በልቦቻቸው ሙላት በቅንነት በፊትህ የሚሄዱት አገልጋዮችህን ምህረት የምታሳየው የእስራኤል ጌታ አምላክ ሆይ፣ ለስምህ ˆምስጋና ይሁን—

፪ በዚህ ስፍራ (ከርትላንድ) ውስጥ በስምህ ቤት ″እንዲገነቡ አገልጋዮችህን ያዘዝህ ሆይ።

፫ አሁንም ጌታ ሆይ፣ አገልጋዮችህ ባዘዝኸው መሰረትም እንዳደረጉ ትመለከታለህ።

፬ አሁንም ቅዱስ አባት ሆይ፣ በስሙ ብቻ

፻፰ ፪ሀ ቅ.መ.መ. እረፍት።
፬ሀ ት. እና ቃ. ፻፱፥፮–፲።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲።
፮ሀ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፯ሀ ሉቃ. ፳፪፥፴፩–፴፪።
፰ሀ ፪ ኔፊ ፱፥፲፱።
፻፱ ፩ሀ ዳን. ፱፥፬።
ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
ለ አልማ ፴፯፥፴፯፤
ት. እና ቃ. ፵፮፥፴፪።
ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣ ምስጋናን፣ ምስጋና መስጠት።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፱።

ደህንነት ለሰው ልጆች በሚሰጠው በእቅፍ ባለው ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቅሀለን፣ ጌታ ሆይ እንድንገነባው ያዘዝከውን ይህን [ሀ]ቤት፣ የእኛ የአገልጋዮችህ እጆች [ለ]ስራን ትቀበል ዘንድ እንጠይቅሀለን።

፭ ይህን ስራ በታላቅ ስቃይ ዘመን እንደሰራነው ታውቃለህ፤ እና ለስምህ [ሀ]ቤት ለመስራት፣ የሰው ልጅ ለህዝቦቹ እራሱን የሚያሳይበት ስፍራ ይኖረው ዘንድ፣ ከድህነታችን እቃዎቻችንን ሰጥተናል።

፮ እና ባልንጀሮች ብለህ ጠርተኸን እንዲህ በማለት በሰጠኸን [ሀ]ራዕይ እንዳልከው፣ እንዳዘዝኳችሁ የክብር ስብሰባን ጥሩ፤

፯ እና ሁላችሁም እንደ እምነታችሁ፣ ተግታችሁ ፈልጉ እና እርስ በርስም የጥበብን ቃላት ተማማሩ፤ አዎን፣ ከምርጥ መፅሐፎች ውስጥ የጥበብ ቃላትን ፈልጉ፣ ትምህርትንም ፈልጉ፣ እንዲሁም በጥናትና ደግሞም በእምነት ይሁን፤

፰ ራሳችሁን አደራጁ፤ ለእያንዳንዱ አስፈላጊ ነገሮችም ተዘጋጁ፣ እና ቤት፣ እንዲሁም የጸሎት ቤት፣ የጾም ቤት፣ የእምነት ቤት፣ የመማሪያ ቤት፣ የክብር ቤት፣ የስርዓት ቤት፣ የእግዚአብሔርን ቤት መስርቱ፤

፱ መግባታችሁ በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፣ መውጣታችሁም በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፣ ወደ ልኡል እጆቻችሁን ከፍ በማድረግ ሰላምታዎቻችሁም በጌታ ስም እንዲሆን—

፲ አሁንም፣ ቅዱስ አባት፣ የክብር ስብሰባችንን ስንጠራ፣ በክብርህ እና በአንተ መለኮታዊ መስማማት ይደረግ ዘንድ፣ እኛን ህዝብህን በጸጋህ እንድትረዳን እንጠይቅሀለን፤

፲፩ እና በዚህም ለእኛ ለህዝብህ በተሰጠን ራእዮች የገባህልን [ሀ]ቃል ኪዳኖች የሚሟሉበትንም ለማግኘት በፊትህ በብቃት እንድንገኝም፤

፲፪ ቅዱስ እንዲሆን እንዲቀደስና ለስዕለትም ይገባ ዘንድ፣ ቅዱስ ፊትህ በዚህ ቤት ውስጥ ሁልጊዜም ይገኝ ዘንድ፣ [ሀ]ክብርህ በህዝብህ ላይ እና ለአንተ በምንቀድሰው በዚህ በቤትህ ላይም ያርፍ ዘንድ፤

፲፫ እና በጌታ ቤት መግቢያ በር ላይ የሚገቡት ህዝብ ሁሉ ሀይልህ እንዲሰማቸው፣ እና እንደቀደስከውም፣ ይህም ቤትህ፣ የቅድስናህ ስፍራ እንደሆነም በማወቅ ይሰማቸው ዘንድ።

፲፬ እና ቅዱስ አባት ሆይ በዚህ ቤት የሚያመልኩት ሁሉ የጥበብን ቃላት ከምርጥ መፅሀፍት ውስጥ ይማሩ ዘንድ፣ እና ትምህርትንም ይሹ ዘንድ፣ እንዲሁም አንተ እንዳልከው በጥናት፣ እና ደግሞም በእምነት፣ ይሆን ዘንድ ፍቀድልን፤

፲፭ እና በአንተም እንዲያድጉ፣ እና የመንፈስ ቅዱስን ሙላት እንዲቀበሉ፣ እና በህግጋትህ መሰረት እንዲመሰረቱ፣ እና አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ ለመቀበል ይዘጋጁም ዘንድ፤

፲፮ እና ይህም ቤት የጸሎት ቤት፣ የጾም ቤት፣ የእምነት ቤት፣ የክብር እና የእግዚአብሔር ቤት፣ እንዲሁም የአንተ ቤት ይሆን ዘንድ፤

፲፯ የህዝብህን ወደዚህ ቤት መግባታቸውም በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፤

፲፰ ከዚህ ቤት መውጣቸው በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፤

፲፱ እና ሰላምታቸውም ሁሉ፣ ወደ ልዑል ከፍ በተዘረጉ በቅዱስ እጆች በጌታ ስም ይሆን ዘንድ፤

፳ እና ምንም ምንም [ሀ]እርኩስ ነገር ወደ ቤትህ ውስጥ እንዲገባ ተፈቅዶለት እንዳያቆሽሸው ዘንድ፤

፳፩ እና ማናቸውም ህዝብህ ሲተላለፉም፣ ወዲያው ንስሀ እንዲገቡና ወደ አንተ እንዲመለሱ፣ እና በፊትህም ሞገስን እንዲያገኙ፣

፬ሀ ፩ ነገሥ. ፱፥፫።
ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።
ለ ፪ ኔፊ ፭፥፲፮።

፭ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፳፯–፳፰።

፮ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፯–፻፳።

፲፩ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፪፤
፻፭፥፲፩–፲፪፣ ፲፰፣ ፴፫።

፲፪ሀ ቅ.መ.መ. ክብር።

፳ሀ ት. እና ቃ. ፺፬፥፰–፱፤
፺፯፥፲፭–፲፯።

እና በቤትህ [ሀ]ለሚያከብሩህ ሁሉ እንዲፈስ ለመደብካቸው በረከቶች ደግመው እንዲመለሱም ዘንድ እንጠይቅሀለን።

፳፪ እና ቅዱስ አባት ሆይ፣ አገልጋዮችህ ከዚህ ቤት በሀይልህ ይታጠቁ ዘንድ፣ እና ስምህም በእነርሱ ላይ እንዲሆን፣ እና ክብርህም በዙሪያቸው፣ እና [ሀ]መላእክትህም ይጠብቋቸው ዘንድ እንጠይቅሀለን፤

፳፫ እና ከዚህም ስፍራ፣ በእውነት፣ በጣም ታላቅ እና የክብር ዜና ወደ ምድር [ሀ]ዳርቻዎች እንዲወሰድ፣ ይህም ያንተ ስራ እንደሆነ ያውቁ ዘንድ፣ እና ስለመጨረሻዎቹ ቀናት በነቢያትህ አንደበት የተናገርካቸው እንዲሟሉ እጅህን ትዘረጋም ዘንድ እንጠይቅሀለን።

፳፬ ቅዱስ አባት ሆይ፣ የሚያመልኩህን እና በቤትህ ለሁሉም ትውልዶች እና ለዘለአለም የተከበረ ስም እና ቋሚነት የያዙ ህዝብን እንድትመሰርት እንጠይቅሀለን፤

፳፭ በእነርሱም ላይ [ሀ]የሚሰራ ምንም መሳሪያ እንዳይከናወን፣ [ለ]ጉድጓድ የሚቆፍረውም በዚያው ውስጥ ይወድቅ ዘንድ፤

፳፮ በዚህ ቤት ውስጥ [ሀ]ስምህን በሰጠሀቸው ህዝብህ ላይ ምንም የክፋት ሴራ እንዳይነሳና [ለ]እንዳይሰለጥን፤

፳፯ እና በዚህ ህዝብ ላይ ማንም ህዝብ ቢነሳባቸው፣ ቁጣህ በእነርሱ ላይ ይቀጣጠል ዘንድ፤

፳፰ እና ይህን ህዝብ ቢመቱም አንተ እንድትመታቸው፣ ከጠላቶቻቸው እጆች ይድኑም ዘንድ፣ በጦርነት ቀን እንዳደረከው ለህዝብህ እንድትዋጋ እንጠይቅሀለን።

፳፱ ቅዱስ አባት ሆይ፣ በአለም ሁሉ በአገልጋይህ ወይም አገልጋዮችህ ላይ የሀሰት ዘገባ የሚያባዙትን ሁሉ፣ ዘለአለማዊው ወንጌልም በጆሮዎቻቸው ውስጥ ሲታወጅ ንስሀ ባይገቡ፣ ታሳፍራቸው፣ እና ታስደንቃቸው፣ እና ውርደትንና ግራ መጋባትንም ታመጣባቸው ዘንድ እንጠይቅሀለን፤

፴ እና ስራዎቻቸውም ሁሉ ከንቱ ይሆኑ ዘንድ፣ ከቁጣህም የተነሳ በሚመጣባቸው በበረዶና በቁጣህ ፍርድ [ሀ]ይጠረጉ ዘንድ፣ በህዝብህም ላይ የተነሳው [ለ]ሀሰት እና ስም ማጥፋት ማብቂያ ይኖረው ዘንድም እንጠይቅሀለን።

፴፩ ጌታ ሆይ፣ ለእነዚህ ነገሮች የተሰቃዩት አገልጋዮችህ ስለአንተም ስም በመመስከር በፊትህ ንጹህን እንደሆኑ ታውቃለህና።

፴፪ ስለዚህ ከዚህ [ሀ]ቀንበር ለሙሉና ፍጹም ደህንነት እንለምንሀለን፤

፴፫ ጌታ ሆይ፣ ስበረው፣ በዚህ ትውልድ መካከል እንድንነሳ እና ስራህንም እንሰራ ዘንድ፣ ከአገልጋዮችህ አንገት በሀይልህ ስበረው።

፴፬ ያህዌህ ሆይ፣ ምህረትህ በህዝብህ ላይ ምህረት ትሁን፣ እና ሁሉም ሰዎች [ሀ]ኃጢአትን ስለሚሰሩም፣ የህዝብህን መተላለፍ ይቅር በል፣ እና ለዘለአለምም ይደምሰስ።

፴፭ የአገልጋዮችህ [ሀ]ቅባትም ከላይ በሆነው ሀይልህም ይታተምባቸው።

፴፮ በበአለ ሀምሳ ቀን በነበሩት ላይ እንደደረሰም፣ በእነርሱም ላይ ይሁን፤ [ሀ]የልሳኖች፣ እንዲሁም በእሳት [ለ]የተከፋፈሉ ልሳኖች፣ እነርሱም የመተርጎም ስጦታ በህዝብህ ላይ ይፍሰስ።

፴፯ እና ቤትህም በድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ [ሀ]በክብርህ ይሞላ።

፴፰ ሲወጡና ቃልህን ሲያውጁ [ሀ]ህግን ለማተም እንዲችሉ፣ በቁጣህ [ለ]በምድር

፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማክበር።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።
፳፫ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥፪።
፳፭ ሀ ኢሳ. ፶፬፥፲፯።
ለ ምሳ. ፳፮፥፳፯፤
፩ ኔፊ ፲፬፥፫፤ ፳፪፥፲፬።
፳፮ ሀ ፩ ነገሥ. ፰፥፳፱።
ለ ት. እና ቃ. ፺፰፥፳፪።
፴ ሀ ኢሳ. ፳፰፥፲፯፤
ሞዛያ ፲፪፥፮፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፮።
ለ ፫ ኔፊ ፳፩፥፲፱–፳፩።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ቀንበር።
፴፬ ሀ ሮሜ ፫፥፳፫፤ ፭፥፲፪።
ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. መቀባት።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. የልሳኖች ስጦታ።
ለ የሐዋ. ፪፥፩–፫።
፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፭፤ ፻፱፥፲፪።
ቅ.መ.መ. ክብር።
፴፰ ሀ ኢሳ. ፰፥፲፮፤
ት. እና ቃ. ፩፥፰።
ለ ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።

ፏሪዎች ላይ በመተላለፋቸው ምክንያት በምታመጣቸው ፍርዶች ሁሉ የቅዱሳን ህን ልብ ያዘጋጁ ዘንድ፣ ህዝብህም በመከራ ቀን እንዳይደክሙ የቃል ኪዳንህ [ሐ]ምስክርነት በአገልጋዮችህ ላይ ይረፍ።

፴፱ እና አገልጋዮችህ በሚገቡበት በማንኛውም ከተማ፣ እና በዚያም ከተማ ምስክርነታቸውን ህዝብ ቢቀበሉት፣ በፅድቅ ከዚያ ከተማ ተሰብስበው ይወጡ ዘንድ፣ ወደ [ሀ]ፅዮንም ወይም አንተ ወደ ወሰንክላቸው ስፍራዎች በዘለአለማዊ ደስታ መዝሙር ወደ ስቴኳ ይመጡ ዘንድ፣ ሰላምና መድሀኒትህ በዚያ ከተማ ላይ ይሁን፤

፵ እና ይህም እስኪከናወን ድረስ፣ በዚያ ከተማ ላይ ፍርድህ አይውደቅበት።

፵፩ አገልጋዮችህ የሚገቡበት በማንኛውም ከተማ፣ እና በዚያም ከተማ የአገልጋዮችህን ምስክርንት ህዝብም ባይቀበሉት፣ ከዚህ ጠማማ ትውልድ ወደፊት ራሳቸውን እንዲያድኑ አገልጋዮችህ ቢያስጠነቀቋቸው፣ በነቢያትህ አንደበት በተናገርከው መሰረት በዚያ ከተማ ላይ ይሁን።

፵፪ ነገር ግን ያህዌህ ሆይ፣ አገልጋዮችህን ከእጆቻቸው ታድናቸውና ከደማቸው ታነጸቸው ዘንድ እንለምንሀለን።

፵፫ ጌታ ሆይ፣ በሰዎች ጥፋት አንደሰትም፤ [ሀ]ነፍሶቻቸውም በፊትህ የከበሩናቸው።

፵፬ ነገር ግን ቃልህ መፈጸም አለበት። [ሀ]በጸጋ እየተረዱ አገልጋዮችህ እንዲህ እንዲሉ እርዳቸው፥ ጌታ ሆይ፣ የአንተ ፈቃድ እንጂ የእኛ አይሁን።

፵፭ ቁጣህን ያለልክ እንድታወርድ—[ሀ]በመጨረሻዎቹ ቀናት፣ ስለክፉዎች በሚመለከት በነቢያትህ አንደበት ብዙ አስፈሪ ነገሮች ተናግረሀልና፤

፵፮ ስለዚህ፣ ጌታ ሆይ፣ ህዝብህን ከክፉዎች አሰቃቂ አደጋ አድናቸው፤ በመቃጠል ቀን ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ዘንድ፣ አገልጋዮችህ ህግን እንዲያትሙና ምስክርነትንም እንዲያስሩ አስችላቸው።

፵፯ ቅዱስ አባት፣ በሚዙሪ በጃክሰን የግዛት ክፍል ውስጥ፣ ከውርስ መሬቶቻቸው የተባረሩትን አስታውስ፣ እና ጌታ ሆይ፣ ይህን በእነርሱ ላይ የተደረገውን የስቃይ ቀንበር ስበረው።

፵፰ ጌታ ሆይ፣ በክፉ ሰዎች በጣም ተበድለዋል እናም ተሰቃይተዋል፤ እና እነርሱ በተሸከሙት አስቸጋሪ ሸከም ምክንያት ልባችን በሀዘን [ሀ]ተሞልቷል።

፵፱ ጌታ ሆይ፣ ይህን ስቃይ እንዲሸከሙ፣ እና የየዋሆቻቸውም ለቅሶ ወደ ጆሮዎችህ እንዲመጡ፣ እና [ሀ]ደማቸውም በፊትህ ምስክር በመሆን እንዲመጣ የምትፈቅደው፣ እና ለእነርሱም ምስክርነትህን የማታሳየውስ [ለ]እስከመቼ ነው?

፶ ጌታ ሆይ፣ ጥፋታቸውን ያቆሙ ዘንድ፣ ንስሀ መግባት የሚቻላቸውም ቢሆን ለኃጢአታቸው ንስሀ ይገቡ ዘንድ፣ ህዝብህን በሚያሳድዱ ክፉ አመጸኛ ቡድኖች ላይ [ሀ]ምህረትህን አኑር፤

፶፩ ነገር ግን ይህን የማያደርጉ ቢሆን፣ ጌታ ሆይ፣ ክንድህን ግለጥ እና ለህዝብህም በፅዮን የመደብከውን [ሀ]አድን።

፶፪ እና ይህም ባይሆን፣ የህዝብህ ተግባራቸው እንዳይወድቅ፣ ከሰማይ በታች ሥርና ቅርንጫፍም ይባክን ዘንድ ንዴትህ ይቀጣጠል፣ እና ቁጣህም ይውረድባቸው፤

፶፫ ነገር ግን ንስሀ እስከገቡ ድረስ ግን፣ አንተ መሐሪና ይቅር ባይ ነህ፣ እና በአንተ የተቀቡትን ፊታቸውን ስትመለከት ቁጣህን ትመልሳለህ።

፶፬ ጌታ ሆይ፣ ምህረትህ በምድር ህዝብ ሁሉ ላይ ትሁን፤ በምድራችን መሪዎች ላይም ምህረት ትኑር፤ በአባቶቻችን በክብር እና በድንቅ የሚጠበቁት እነዚያ መሰ

፴፰ሐ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
፴፱ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲።
፵፫ሀ ቅ.መ.መ. ነፍስ።
፵፬ሀ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
፵፭ሀ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።
፵፰ሀ ቅ.መ.መ. ርህራሄ።
፵፱ሀ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
ለ መዝ. ፲፫፥፩–፪።
፶ሀ ቅ.መ.መ. መሀሪ፣ ምህረት።
፶፩ሀ ት. እና ቃ. ፻፥፲፫፤ ፻፭፥፪።

ረታዊ መርሆች፣ እንዲሁም የምድራችን [ሀ]ህገ መንግስት ለዘለአለም ይቋቋም።

፶፭ ንጉሶችን፣ ልኡሎችን፣ ባላባቶችን፣ እና የምድርን ታላቆች፣ እና ሁሉንም ህዝብ፣ እና ቤተክርስቲያናትን፣ ድሆችን ሁሉ፣ እርዳታ የሚሹትን፣ እና በምድር የሚሰቃዩትን አስታውስ፤

፶፮ ያህዌህ ሆይ፣ አገልጋዮችህ ስለስምህ ለመመስከር ከቤትህ የሚወጡትን ልባቸው ያሰላስል ዘንድ፣ ጥላቻቸውም [ሀ]በእውነት ፊት ይከሰም ዘንድ፣ እና ህዝብህም በሁሉም አስተያየት ሞገስን ያገኙ ዘንድ፤

፶፯ እኛ አገልጋዮችህ [ሀ]ድምፅህን እንደሰማን እና አንተ እንደላከንም የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያውቁ ዘንድ፤

፶፰ ከእነዚህም መካከል፣ አንተ እንዳዘዝካቸው፣ አገልጋዮችህ የያዕቆብ ልጆች ጻድቃንን በስምህ ቅዱስ ከተማን ለመገንባት ይሰበስቡም ዘንድ አስታውስ።

፶፱ የህዝብህ [ሀ]መሰባሰብ በታላቅ ሀይል ይቀጥል ዘንድ፣ ስራህም በፅድቅ [ለ]በአጭር ይከናወን ዘንድ፣ አንተ ከመደብከው ከዚህ በላይ ሌላ [ሐ]ካስማ በፅዮን እንድትመሰርት እንጠይቅሀለን።

፷ ጌታ ሆይ፣ እንደ [ሀ]አህዛብ በተለየ ነው አንተ የሰጠኸንን ራዕዮች እና ትእዛዛት በመመልከት አሁን በፊትህ እነዚህን ቃላት ተናግረናል።

፷፩ ነገር ግን በጨፈገገ እና በጭለማ ቀን በተራራው ላይ ለተበተኑት ለያዕቆብ ልጆች ታላቅ ፍቅር እንዳለህ ታውቃለህ።

፷፪ ስለዚህ፣ ምህረት በያዕቆብ ልጆች ላይ ትሆን ዘንድ፣ ከዚህ ሰአት ጀምሮ [ሀ]ኢየሩሳሌምን ቤዛነት ትጀምር ዘንድ እንጠይቅሀለን፤

፷፫ እና የባርነትም ቀንበር [ሀ]ከዳዊት ቤት መሰበር እንዲጀምር፤

፷፬ እና [ሀ]የይሁዳ ልጆችም ለአባታቸው አብርሐም በሰጠኸው [ለ]ምድር መመለስ እንዲጀምሩ እንጠይቅሀለን።

፷፭ እና በመተላለፋቸው ተረግመው እና ተመትተው የነበሩት የያዕቆብ [ሀ]ቅሪቶችም ከዱር እና ከአውሬነት ሁኔታቸው ወደ ዘለአለማዊ ወንጌል ሙላት [ለ]እንዲቀየሩም አድርግ፤

፷፮ የደም ማፍሰስ መሳሪያዎቻቸውንም እንዲያስቀምጡ እና አመጻቸውንም ያቆሙ ዘንድ አድርግ።

፷፯ እና ወደ ምድር ዳርቻም የተበተኑት [ሀ]የእስራኤል ቅሪቶችም ወደ እውነት እውቀት ይምጡ፣ በመሲህም ይመኑ፣ እና ከመበደልም ይዳኑ፣ እና በፊትህም ይደሰቱ።

፷፰ ጌታ ሆይ፣ አገልጋይህን ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊን፣ እና ስቃዮቹን እና በደሎቹን ሁሉ—[ሀ]ከያህዌህ ጋር እንዴት [ለ]ቃል ኪዳን እንደገባ፣ እና የያዕቆብ አምላክ ሆይ፣ ለአንተ መሀላ እንደገባ—እና የሰጠኸውን ትእዛዛት፣ እና ፈቃድህን ለማከናወን በቅንነት እንደሚጥር አስታውስ።

፷፱ ጌታ ሆይ፣ በባለቤቱ እና በልጆቹ ላይ፣ በፊትህ ዘለአለማዊ ክብር ይኖራቸው ዘንድ እና በሚታደገው እጅህ እንድታድናቸው ዘንድ ምህረትን አድርግ።

፸ ጥላቻቸው ይሰበር እና በጎርፍ ይጠረግ ዘንድ፣ ከእስራኤል ጋር እንዲለወጡና እንዲድኑ፣ እና አንተም አምላክ እንደሆንክ

፶፬ ሀ ፩ ጴጥ. ፪፥፲፫–፲፭፤
ት. እና ቃ. ፺፰፥፭–፯፤
፻፩፥፸፯፤ ፹።
ቅ.መ.መ. ህገ መንግስት።
፶፮ ሀ ቅ.መ.መ. እውነት።
፶፯ ሀ ት. እና ቃ. ፳፥፲፮፤
፸፮፥፳፪–፳፬።
፶፱ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
ለ ማቴ. ፳፬፥፳፪።
ሐ ኢሳ. ፶፬፥፪።
፷ ሀ ፩ ኔፊ ፲፫፥፩–፵፪፤
፲፭፥፲፫–፲፰።
፷፪ ሀ ፫ ኔፊ ፳፥፳፱።
ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም።
፷፫ ሀ ቅ.መ.መ. ዳዊት።
፷፬ ሀ ዘካ. ፲፪፥፯–፱፤
ሚል. ፫፥፬፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፲፫፤ ፴፭።
ቅ.መ.መ. ይሁዳ፣
የያዕቆብ ልጅ።
ለ ዘፍጥ. ፲፯፥፩–፰።
ቅ.መ.መ. የቃል
ኪዳን ምድር።
፷፭ ሀ ፪ ኔፊ ፴፥፫፤
አልማ ፵፮፥፳፫–፳፬፤
፫ ኔፊ ፳፥፲፭–፳፩፤
ት. እና ቃ. ፲፱፥፳፯።
ለ ፪ ኔፊ ፴፥፮፤
፫ ኔፊ ፳፩፥፳–፳፪።
ቅ.መ.መ. መቀየር፣
የተቀየረ።
፷፯ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፷፰ ሀ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ለ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።

ያውቁ ዘንድ [ሀ]በዘመዶቻቸው ላይም ምህረት አድርግ።

፸፩ ጌታ ሆይ፣ ፕሬዘደንቶችን፣ እንዲሁም የቤተክርስቲያንን ፕሬዘደንቶች፣ ቀኝ እጅህ ከቤተሰቦቻቸው ሁሉና ከዘመዶቻቸው ጋር ዘለአለማዊ ክብር ትሰጣቸው ዘንድ፣ ስሞቻቸውም ቀጣይ እንዲሆኑና ከትውልድ ወደ ትውልድ ለዘለአለምም ይታወሱ ዘንድ አስታውስ።

፸፪ ጌታ ሆይ፣ ቤተክርስቲያንህን ሁሉ፣ ከየቤተሰባቸው ጋር፣ እና ከዘመዶቻቸው ጋር፣ ከታመሙት እና ከሚሰቃዩት ሁሉ ጋር፣ ከምድር ድሀ እና ትሁታን ጋር አስታውስ፤ በእጆችህ የመሰረትከው [ሀ]መንግስትህ ታላቅ ተራራ እንዲሆንና ምድርንም ሁሉ ይሞላ ዘንድ አስታውስ፤

፸፫ ቤተክርስቲያንህ ከምድረበዳው ጭለማ ወጥታ እንደ [ሀ]ጨረቃ የጠራች እንድትሆን፣ እንደጸሀይም ያማረች እንድትሆን፣ እና ሰንደቅ ዓርማም እንደያዘ ሰራዊት የምታስፈራ ትሆን ዘንድ፤

፸፬ እና ሰማይን በምትገልጥበት፣ እና በፊትህም ተራሮች [ሀ]እንዲመጡ እና [ለ]ሸለቆዎችም ከፍ እንዲሉ፣ ሸካራውም መንገድ የቀና እንዲሆን በምታደርግበት ቀን እንደ ሙሽራ እንድትለብስ፤ ክብርህም ምድርን ሁሉ ይሞላ ዘንድ፤

፸፭ ለሙታን መለከቱ ሲነፋ፣ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና [ሀ]እንነጠቅ ዘንድ፣ እንዲሁም ሁልጊዜም ከጌታ ጋር እንሆን ዘንድ፤

፸፮ ልብሶቻችን ንጹህ ይሆኑ ዘንድ፣ በእጆቻችንም የዘንባባንም ዝንጣፊዎች ይዘን፣ እና የፅድቅ [ሀ]ልብስ እንድንለብስ፣ እናም በራሳችንም የክብርን [ለ]አክሊል ተጎናጽፈን፣ እና [ሐ]ለስቃዮቻችንም የዘለአለም [መ]ደስታ እናጭድ ዘንድ አስታውሰን።

፸፯ ጌታ ኤልሻዳይ ሆይ፣ በእነዚህ ያቀረብናቸውን ልመናችንን ውስጥ ስማን፣ እና [ሀ]በግርማ፣ በክብር፣ በሀይል፣ በስልጣን፣ በእውነት፣ በመፍትሄ፣ በፍርድ፣ በምህረት፣ እና በዘለአለም ሙላት፣ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም በዙፋንህ ላይ ከምትቀመጥበት ከቅዱስ መኖሪያህ ሰማይም መልስ ስጠን።

፸፰ ጌታ ሆይ፣ አቤቱ አድምጠን፣ አቤቱ አድምጠን፣ አቤቱ አድምጠን! እና እነዚህ የምናቀርባቸውን ልመናዎቻችንን መልስ፣ እና በስምህ የገነባነውን፣ የእጆችህ ስራ የሆንነውን፣ የዚህንም ቤት ለአንተ መቀደስ ተቀበል፤

፸፱ ደግሞም ያንተን ስም ለመያዝ፣ ይህችንም ቤተክርስቲያን ተቀበል። እና ከዙፋንህ ዙሪያ ከሚገኙት ከደማቅ፣ አንጸባራቂ [ሀ]ሱራፌሎች ጋር በአድናቆት ምስጋና፣ ለአምላክ እና [ለ]ለበጉ ሆሳዕና በመዘመር ድምጻችንን እናሰማ ዘንድ በመንፈስህ ሀይልም እርዳን!

፹ እነዚህ የተቀቡትም በደህንነት [ሀ]እንዲለብሱ፣ እና ቅዱሳንህም በደስታ እንዲጮሁ ፍቀድ። አሜን፣ እናም አሜን።

ክፍል ፻፲

በሚያዝያ ፫፣ ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ቤተመቅደስ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ

፸ ሀ ይህም ቅርብ ዘመዶች ማለት ነው።
፸፪ ሀ ዳን. ፪፥፴፬–፴፭፤ ት. እና ቃ. ፷፭፥፪።
፸፫ ሀ መኃ. ፮፥፲፤ ት. እና ቃ. ፭፥፲፬፤ ፻፭፥፴፩።
፸፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፳፩–፳፪፤ ፵፱።
ለ ኢሳ. ፵፥፬፤ ሉቃ. ፫፥፭፤ ት. እና ቃ. ፵፱፥፳፫።
፸፭ ሀ ፩ ተሰ. ፬፥፲፯።
፸፮ ሀ ራዕ. ፯፥፲፫–፲፭፤ ፪ ኔፊ ፱፥፲፬።
ለ ቅ.መ.መ. አክሊል፤ ከፍተኛነት።
ሐ ዕብ. ፲፪፥፩–፲፩፤ ት. እና ቃ. ፶፰፥፬።
መ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፸፯ ሀ ቅ.መ.መ. ክብር።
፸፱ ሀ ኢሳ. ፮፥፩–፪።
ለ ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
፹ ሀ መዝ. ፻፴፪፥፲፮።

ስሚዝና ለኦሊቨር ካውድሪ የተገለጡ ራዕዮች። ጊዜውም በሰንበት የስብሰባ ቀን ነበር። የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፥ “በዚህ ቀን እና ረፋድ፣ የጌታን እራት በቅዱስ ጠረጴዛው ላይ ለማስተዳደር ልዩ መብት ከነበራቸው ከአስራ ሁለቱ በመቀበል ለቤተክርስቲያን ለማደል ሌሎቹን ፕሬዘደንቶች ረዳሁ። ይህን አገልግሎት ለወንድሞቼ ካከናወንኩ በኋላ፣ ወደ መስበኪያው ተመለስኩኝ፣ መጋረጃውን በመዝጋት እና ከኦሊቨር ካውድሪ ጋር በአክብሮት እና ጸጥተኛ ጸሎት አጎነበስኩኝ። ከጸሎት ከተነሳሁም በኋላ፣ የሚቀጥለው ራዕይ ለሁለታችን ተከፈተልን”።

፩–፲፣ ጌታ ያህዌህ በክብር መጣ እና የከርትላንድ ቤተመቅደስን እንደ ቤቱ ተቀበለ፤ ፲፩–፲፪፣ ሙሴ እና ኤልያስ እያንዳንዳቸው ተገለጡ እና ቁልፎቻቸውን እና የዘመን ፍጻሜዎቻቸውንም ሰጡ፤ ፲፫–፲፮፣ በሚልክያስ ቃል እንደተገባውም ኤልያስ ተመለሰ እና የዘመን ፍጻሜውን ቁልፎች ሰጠ።

፩ [ሀ]መጋረጃው ከአዕምሮዎቻችን ተወገደ፣ እና የመረጃ [ለ]አይኖቻችንም ተከፈቱ።

፪ ጌታን በመስበኪያው መደገፊያ ላይም በፊት ለፊታችን አየነው፤ እና ከእግሮቹም በታች የቡናማ ቢጫ ቀለም አይነት የነበረ ንጹህ ወርቅ የተነጠፈበት የሚመስል ስራ ነበር።

፫ [ሀ]ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ፤ የራሱ ጠጉርም እንደ ንጹህ በረዶም ነጭ ነበሩ፤ [ለ]ፊቱም ከብርቱ የጸሀይ ብርሀን በላይ የሚያበራ ነበር፤ [ሐ]ድምፁም እንዲህ የሚል እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ፣ እንዲሁም [መ]የያህዌህ ድምፅ ነበር፥

፬ እኔ [ሀ]ፊተኛውና ኋለኛው ነኝ፤ እኔ [ለ]ህያውም ነኝ፣ የተገደልኩትም እኔ ነኝ፤ እኔም በአብ ዘንድ [ሐ]አማላጃችሁ ነኝ።

፭ እነሆ፣ ኃጢአታችሁ [ሀ]ተሰርየዋል፤ በፊቴም ንጹህ ናችሁ፤ ስለዚህም፣ ራሳችሁን አቅኑ እናም ተደሰቱ።

፮ የወንድሞቻችሁ ልብም ይደሰት፣ እና በሀይላቸው ይህን [ሀ]ቤት በስሜ የሰሩት የህዝቤም ልብ ሁሉ ይደሰት።

፯ እነሆ፣ ይህን [ሀ]ቤት [ለ]ተቀብዬዋለሁ፣ እና ስሜም በዚህ ይሆናል፤ እና በምህረትም ራሴን ለህዝቤ አሳያለሁና።

፰ አዎን፣ ህዝቤ ትእዛዛቴን ቢጠብቁ፣ እና ይህን [ሀ]ቅዱስ ቤት [ለ]ባያጎድፍ፣ ለአገልጋዮቼ [ሐ]እገልጣለሁ፣ እና በራሴም ድምፅ አናገራቸዋለሁ።

፱ አዎን፣ በሚፈሱት [ሀ]በረከቶች እና አገልጋዮቼ በዚህ ቤት ውስጥ በተቀበሉት [ለ]መንፈሳዊ ስጦታዎች ምክንያት የሺዎች እና የአስር ሺዎች ልብ በእጅጉ ይደሰታሉ።

፲ እና የዚህ ቤት ዝናም በውጪ አገሮች ይስፋፋል፤ እና ይህም በህዝቤ ራሶች ላይ [ሀ]የሚፈሰው የበረከት መጀመሪያም ነው። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፲፩ ይህ [ሀ]ራዕይ ከተፈጸመ በኋላ፣ ሰማያት ዳግም ተከፈቱልን፤ እና [ለ]ሙሴ በፊታችን መጣ፣ እና ከምድር አራት ማዕዘናትን

፻፲ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ዐይነ-እርግብ።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፲፪፣ ፲፱፤
፻፴፮፥፴፪፤ ፻፴፰፥፲፩።
፫ ሀ ራዕ. ፩፥፲፬።
ለ ራዕ. ፩፥፲፮፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፲፯።
ሐ ሕዝ. ፵፫፥፪፤
ራዕ. ፩፥፲፭፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፳፩–፳፪።
መ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. በኩር።
ለ ዘዳግ. ፭፥፳፬።
ሐ ቅ.መ.መ. አማላጅ።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፱፥፬–፭።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።
ለ ፪ ዜና ፯፥፲፮።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
ለ ት. እና ቃ. ፺፯፥፲፭–፲፯።
ሐ ት. እና ቃ. ፶፥፴፭።
፱ ሀ ዘፍጥ. ፲፪፥፩–፫፤
ት. እና ቃ. ፴፱፥፲፭፤
አብር. ፪፥፰–፲፩።
ለ ት. እና ቃ. ፺፭፥፰።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ስጦታ።
፲ ሀ ት. እና ቃ. ፻፭፥፲፪።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ማቴ. ፲፯፥፫።

የእስራኤልን [ሐ]መሰብሰቢያ እና [መ]ከሰሜን ምድር የአስሩን ነገዶች መምሪያ [ሠ]ቁልፎችን ሰጠን።

፲፪ ከዚህ በኋላ፣ [ሀ]ኤልያ መጣ፣ እና በእኛና በዘራችን ከእኛም በኋላ የሚመጡ ትውልዶች ሁሉ ይባረካሉ በማለት የአብርሐም [ለ]ወንጌል [ሐ]የዘመን ፍጻሜን ሰጠን።

፲፫ ይህ ራዕይ ከተፈጸመ በኋላ፣ ሌላ ታላቅ እና የክብር ራዕይ ተከፈተልን፤ ሞትን ሳይቀምስ ወደሰማይ [ሀ]የተወሰደው ነቢዩ [ለ]ኤልያስ በፊት ለፊታችን ቆመ፣ እናም አለ፥

፲፬ እነሆ፣ በሚልክያስ አንደበት በመመስከር ተነግሮ የነበረው ጊዜ በሙላት መጥቷል—ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ እርሱ [ኤልያስ] እንደሚላክ—

፲፭ ይህም፣ ምድር በእርግማን እንዳትመታ፣ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች [ሀ]ለመመለስ እንዳለበት ተነግሮ የነበረው ጊዜ በሙላት መጥቷል።

፲፮ ስለዚህ፣ የዚህ የዘመን ፍጻሜ ቁልፎች በእጆቻችሁ ተሰጥተዋል፤ እና ይህም ታላቁና የሚያስፈራው የጌታ [ሀ]ቀን ቅርብ እንደሆነ፣ እንዲሁም በበር ላይ እንዳለም፣ ታውቃላችሁ።

ክፍል ፻፲፩

በነሀሴ ፮፣ ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.) በሴለም ማሳቹሰት ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ በአገልግሎት ስራዎቻቸው ምክንያት የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ብዙ እዳ ነበረባቸው። በሴለም ውስጥ ብዙ ገንዘቦች እንደሚገኙላቸው በመስማት፣ ነቢዩ፣ ስድኒ ሪግደን፣ ሀይረም ስሚዝ፣ እና ኦሊቨር ካውድሪ ወንጌልን ከመስበክ ጋር የተባለውን ለመመርመር ከከርትላንድ ኦሀዮ ወደ እዚያ ተጓዙ። ወንድሞች የቤተክርስቲያኗን ብዙ ጉዳዮች አከናወኑ እና ጥቂትም ሰበኩ። ምንም ገንዘብ እንደማይገኝ ግልፅ እየሆነ ሲመጣም፣ ወደ ከርትላንድ ተመለሱ። በስረ መሰረታቸው በግልፅ የሚታዩት ብዙዎቹ ጉዳዮች በዚህ ራዕይ ቃላት ውስጥ ተገንዝበዋል።

፩–፭፣ ጌታ የአገልጋዮቹን ስጋዊ ፍላጎቶች ይጠብቃል፤ ፮–፲፩፣ ፅዮንን በምህረት ይንከባከባታል እና ለአገልጋዮቹም መልካነትም ሁሉንም ነገሮች ያዘጋጃል።

፩ ስህተተኞች ብትሆኑም፣ እኔ ጌታ አምላካችሁ በዚህ ጉዞ በመምጣታችሁ ያልተደሰትኩባችሁ አይደለሁም።

፪ በዚህ ከተማ ለእናንተ፣ ለፅዮን ጥቅም፣ ብዙ ሀብቶች አሉኝ፣ እና በዚህ ከተማም በእናንተ መሳሪያነት ለፅዮን ጥቅም በጊዜዬ ሰብስቤ የማወጣቸው ብዙ ህዝብም አሉ።

፫ ስለዚህ፣ እንደምትመሩት፣ እና እንደሚሰጣችሁ፣ ከዚህ ከተማ ሰዎች ጋር ባልንጀሮች መሆናችሁ በእኔ ዘንድ አስፈላጊ ነው።

፬ እና በጊዜውም፣ በዚህ ከተማ ላይ ሀይል ይኖራችሁ ዘንድ፣ በዚህም የሚስጥር ክፍላችሁን እንዳያገኙባችሁ ዘንድ ይህን ከተማ

፲፩ሐ ያዕቆ. ፮፥፪፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥፯። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
መ ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፳፮–፴፪። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የጠፉት የእስራኤል አስር ነሳዎች።
ሠ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፲፪ሀ ገላ. ፫፥፮–፳፱። ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢልያ።
፲፫ሀ ቅ.መ.መ. የተቀየሩ ሰዎች።
ለ ቅ.መ.መ. ኤልያስ።
፲፭ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፰–፴፱። ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት፤ የትውልድ ሐረግ።
፲፮ሀ ቅ.መ.መ. የመጨረሻ ቀናት፣ የኋለኛው ቀናት።

በእጆቻችሁ አሳልፌ የምሰጥበት ጊዜ ይመጣል፤ እና ስለወርቅ እና ስለብር በሚመለከትም ሀብትም የእናንተ ይሆናል።

፭ [ሀ]ስለእዳዎቻችሁ አታስቡ፣ እንድትከፍሏቸውም ሀይልን እሰጣችኋለሁና።

፮ ስለፅዮንም አታስቡ፣ እርሷንም በምህረት እንከባከባታለሁና።

፯ በዚህ ስፍራ እና በአካባቢዋ ክፍለ ሀገሮች ቆዩ፤

፰ እና እናንተ በብዛት እንድትቆዩበት ፍቃዴ በሚሆንበት ስፍራም በውስጣችሁ የሚፈልቀው መንፈሴ [ሀ]ሰላምና ሀይል ምልክት ይሰጣችኋል።

፱ ይህንም ስፍራ በኪራይ አግኙት። ስለዚህ ከተማ የጥንት ነዋሪዎችና መስራቾችን በቅንነት ጠይቁ፤

፲ በዚህ ከተማ ውስጥ ከአንድ በላይ ሀብቶች አሉአችሁና።

፲፩ ስለዚህ፣ ያለኃጢአት እንደ እባብ [ሀ]ብልህ ሁኑ፤ እና እናንተ ልትቀበሉ በምትችሉት ፍጥነትም፣ ሁሉንም ነገሮች ለእናንተ [ለ]መልካምነት አዝዛለሁ። አሜን።

ክፍል ፻፲፪

በህምሌ ፳፫፣ ፲፰፻፴፯ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ ስለአስራ ሁለቱ የጥቦው ሐዋሪያት በሚመለከት ለቶማስ ቢ ማርሽ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህን ራዕይ የተቀበለው ሽማግሌዎች ሂበር ሲ ኪምባል እና ኦርሰን ሀይድ በእንግሊዝ ሀገር ወንጌሉን ለመጀመሪያ ጊዜ በሰበኩበት ቀን ነው። ቶማስ ቢ ማርሽ በዚህ ጊዜ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዘደንት ነበር።

፩–፲፣ አስራ ሁለቱ ወንጌሉን ይላኩ እና ለሁሉም ሀገሮች እና ህዝብም የማስጠንቀቂያን ድምፅ ያንሱ፤ ፲፩–፲፭፣ መስቀላቸውን ይሸከሙ፣ ኢየሱስንም ይከተሉ፣ እና በጎቹንም ይመግቡ፤ ፲፮–፳፣ የቀዳሚ አመራርን የሚቀበሉ ጌታን ይቀበላሉ፤ ፳፩–፳፱፣ ጭለማ ምድርን ሸፈነ፣ እና የሚያምኑ እና የሚጠመቁ ብቻ ይድናሉ፤ ፴–፴፬፣ ቀዳሚ አመራር እና አስራ ሁለቱ የዘመን ፍጻሜ ሙላትን ቁልፎች ይዘዋል።

፩ ለአገልጋዬ ቶምስ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፥ ጸሎትህን ሰምቻለሁ፤ እና በስሜ እንዲመሰክሩ እና በሁሉም ሀገር፣ ነገድ፣ ቋንቋና ህዝብ መካከል ወደ ውጪ [ሀ]እንዲላኩ በተመረጡት፣ እና በአገልጋዮቼ መሳሪያነት በተሾሙት በእነዚያ ወንድሞችህ ወኪል ያቀረብከው ምፅዋትህ እንደ [ለ]ማስታወሻ ወደ እኔ ዘንድ መጥቷል።

፪ እውነት እልሀለሁ፣ እኔ ጌታ በልብህ ውስጥ እና ከአንተም ጋር ያልተደሰትኩባቸው አንዳንድ ጥቂት ነገሮች አሉኝ።

፫ ይህም ቢሆን፣ ራስህን [ሀ]እስካዋረድህ ድረስ ከፍ ትደረጋለህ፤ ስለዚህ ኃጢአቶችህ ሁሉ ተሰርየዋል።

፬ ልብህ በፊቴ [ሀ]ሀሴትን ያድርግ፤ እና [ለ]ለአህዛብ ብቻ ሳይሆን ደግሞም [ሐ]ለአይሁዶች ስለስሜ ትመሰክራለህ፤ እና ቃሌን ወደ ምድር ዳርቻዎች ትልካለህ።

፭ [ሀ]አትጣላ፣ ስለዚህ ጠዋት በየማለዳው፣ በየቀኑ [ለ]የማስጠንቀቂያህ ድምፅህ ይሂድ፤

፻፲፩ ፭ ሀ ት. እና ቃ. ፷፬፥፳፯–፳፱።
፰ ሀ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፮።
ቅ.መ.መ. ሰላም።
፲፩ ሀ ማቴ. ፲፥፲፮።
ለ ሮሜ ፰፥፳፰፤
ት. እና ቃ. ፺፥፳፬፤
፻፥፲፭።
፻፲፪ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፲፰፥፳፰።
ለ የሐዋ. ፲፥፬።
፫ ሀ ማቴ. ፳፫፥፲፪፤
ሉቃ. ፲፬፥፲፩።
፬ ሀ ማቴ. ፱፥፪፤
ዮሐ. ፲፮፥፴፫።
ለ ት. እና ቃ. ፲፰፥፮፤ ፺፥፰–፱።
ሐ ት. እና ቃ. ፲፱፥፳፯።
፭ ሀ ይሁዳ ፩፥፫።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፬–፭።

እና ሲመሽም፣ በንግግርህ ምክንያት የምድር ነዋሪዎች ያንቀላፉም ዘንድ አትፍቀድ።

፮ በፅዮን ውስጥም መኖሪያህ ይታወቅ፣ እና መኖሪያህንም [ሀ]አትቀይር፤ በሰዎች ልጆች መካከል ስሜን ታሳውቅ ዘንድ፣ እኔ ጌታ ታከናውነው ዘንድለአንተ ታላቅ ስራ አለኝና።

፯ ስለዚህ ለስራውም ወገብህን [ሀ]አጥብቅ። እግሮችህም ይጫሙ፣ አንተ የተመረጥህ ነህና፣ እና መንገድህም በተራራዎች መካከል እና ከብዙ ህዝብ መካከል ነውና።

፰ እና በቃልህም ከፍ ያሉት [ሀ]የዋረዱ ይሆናሉ፣ እና በቃልህም የተዋረዱት ከፍ ይላሉ።

፱ ድምፅህም ለሚተላለፈው ግሳጼ ይሆናል፤ እና በግሳጼህም ስምን የሚያጠፉ ምላስም ጠማማነቱን ያቁም።

፲ [ሀ]ትሁት ሁን፤ እና ጌታ አምላክህ እጅህን ይዞ ይመራሀል፣ እና ለጸሎቶችህም መልስ ይሰጥሀል።

፲፩ ልብህን አውቃለሁ፣ እና ስለወንድሞችህም ጸሎትህን ሰምቻለሁ። ለእነርሱ ከሌሎች በላይ [ሀ]በፍቅርህ አድሎን አታድርግ፣ ነገር ግን ለእነርሱ ያለህ ፍቅርህ እንደራስህ ይሁን፤ እናም ፍቅርህም ለሁሉም ሰዎችና ስሜን ለሚወዱ ሁሉ ይብዛ።

፲፪ ለአስራ ሑለቱ ወንድሞችህም ጸልይ። ስለስሜም ብለህ በብርቱ ገስጻቸው፣ እና ለኃጢአቶቻቸው ሁሉ ይገሰጹ፣ እና [ሀ]ስለስሜም በፊቴ ታማኝ ሁን።

፲፫ [ሀ]ከፈተናዎቻቸው እና ከብዙም [ለ]ስቃይ በኋላ፣ እነሆ፣ እኔ ጌታ እፈልጋቸዋለሁ፣ እና ልባቸውን ባያጠጥሩ፣ እና አንገታቸውን በእኔ ላይ ባያደነደኑ፣ [ሐ]ይለወጣሉ፣ እኔም እፈውሳቸዋለሁ።

፲፬ አሁን፣ እልሀለሁ፣ እና ለአንተ የምለውን፣ ለአስራ ሁለቱ ሁሉ እላለሁ፥ ተነሳ እና ወገብህን አጥብቅ፣ [ሀ]መስቀልህንም ተሸከም፣ ተከተለኝ፣ እና በጎቼንም [ለ]መግብ።

፲፭ ራሳችሁን ከፍ አታድርጉ፤ በአገልጋዬ ጆሴፍ ላይ [ሀ]አታምጽ፤ በእውነት እልሀለሁ፣ ከእርሱ ጋር ነኝ፣ እና እጄም በእርሱ ላይ ይሆናልና፤ እና እኔ ለእርሱ፣ እና ዳግሞም ለእናንተም፣ የሰጠኋቸው [ለ]ቁልፎችም እስከምመጣ ድረስ ከእርሱ አይወሰዱም።

፲፮ እውነት እልሀለሁ አገልጋዬ ቶማስ፣ በሀገሮች ሁሉ መካከል በውጪ ስላሉት አስራ ሁለቱን በሚመለከት፣ የመንግስቴን ቁልፎች እንድትይዝ የመረጥኩህ ሰው ነህ—

፲፯ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ እና አገልጋዬ [ሀ]ስድኒ፣ እና አገልጋዬ [ለ]ሀይረም ሊመጡበት በማይችሉበት ስፍራ ሁሉ የመንግስትን በር እንድትከፍት ዘንድ፤

፲፰ በእነርሱም ላይ ለጥቂት ዘመን የቤተ ክርስቲያናትን ሸክሞች ሁሉ በእነርሱ ላይ አሳርፌአለሁና።

፲፱ ስለዚህ፣ የትም ቢልኩህ፣ ሂድ፣ እና እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እና ስሜን በምታውጅበት በማንኛውም ስፍራ ቃሌን ይቀበሉ ዘንድ [ሀ]ውጤታማ በርም ይከፈት ልሀል።

፳ ማንም ቃሌን [ሀ]የሚቀበል እኔን ይቀበላል፣ እና እኔን የሚቀበል ማንም፣ የላኳቸውን፣ ስለስሜም ለአንተ አማካሪዎች ያደረ

፮ ሀ መዝ. ፻፳፭፥፩።
፯ ሀ ኤፌ. ፮፥፲፫–፲፯።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
፲ ሀ ምሳ. ፲፰፥፲፪።
፲፩ ሀ ማቴ. ፭፥፵፫–፵፰።
ቅ.መ.መ. ልግስና፤
ፍቅር።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ
ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም
በራሳችን ላይ መውሰድ።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መፈተን፣ ፈተና።
ለ ዮሐ. ፲፮፥፴፫፤
ራዕ. ፯፥፲፫–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፶፰፥፫–፬።
ሐ ፫ ኔፊ ፲፰፥፴፪።
ቅ.መ.መ. መቀየር፣
የተቀየረ።
፲፬ ሀ ማቴ. ፲፮፥፳፬፤
ጆ.ስ.ት. ማቴ. ፲፮፥፳፭–፳፮
(ተጨማሪ)፤
ሉቃ. ፱፥፳፫።
ለ ዮሐ. ፳፩፥፲፭–፲፯።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. አመጽ።
ለ ት. እና ቃ. ፳፰፥፯።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ለ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሀይረም።
፲፱ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፮፥፱፤
ት. እና ቃ. ፻፲፰፥፫።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፭–፴፰።

ኳቸውን እነዚያን የቀዳሚ አመራርን ይቀበላል።

፳፩ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በስሜ፣ በወንድሞቻችሁ [ሀ]በአስራ ሁለቱ ድምፅ፣ በእናንተ ተገቢ ትእዛዝና [ለ]ስልጣን፣ የምትልኳቸው ሁሉ፣ በምትልኳቸው በየትኛውም ሀገር የመንግስቴን በር የመክፈት ሀይል ይኖራቸዋል—

፳፪ ይህን የሚሆነው በፊቴ ራሳቸውን ትሁት እስካደረጉ፣ እና በቃሌም እስከ ኖሩ፣ እና የመንፈሴንም ድምፅ [ሀ]እስካደመጡ ድረስ ነው።

፳፫ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]ጭለማ ምድርን፣ እና ታላቅ ጭለማም የህዝብን አዕምሮ ሸፍኗል፣ እና ስጋ ለባሽ ሁሉ በፊቴ [ለ]በስብሰዋል።

፳፬ እነሆ፣ [ሀ]በቀል፣ የቁጣ ቀን፣ የንዳድ ቀን፣ የጥፋት ቀን፣ [ለ]የለቅሶ ቀን፣ የሀዘን ቀን በምድር ነዋሪዎች ላይ በፍጥነት መጥቷል፤ እና እንደ አውሎ ንፋስም በምድር ፊት ሁሉ ይመጣል፣ ይላል ጌታ።

፳፭ እና በቤቴም ላይ [ሀ]ይጀምራል፣ እና ከቤቴም ይሄዳል፣ ይላል ጌታ፣

፳፮ መጀመሪያ ስሜን እናውቃለን [ሀ]በሚሉ [ለ]በማያውቁኝም፣ እና በቤቴም መካከል እኔን [ሐ]ስለሰደቡኝ ስለእነዚያ በመካከላችሁ ስላሉት፣ ይላል ጌታ።

፳፯ ስለዚህ፣ በዚህ ስፍራ ስላለው የቤተ ክርስቲያኔ ጉዳዮች እንዳታስቡበት ይሁን፣ ይላል ጌታ።

፳፰ ነገር ግን በፊቴ ልባችሁን [ሀ]አንጹ፤ ከዚያም ወደ አለም ሁሉ [ለ]ሂዱ፣ እና ላል ተቀበሉት ለእያንዳንዱ ፍጥረትም ወንጌሌን ስበኩ፤

፳፱ እና [ሀ]ያመነ እና [ለ]የተጠመቀም ይድናል፣ እና ያላመነ፣ እና ያልተጠመቀ [ሐ]ይፈረድበታል።

፴ ለእናንተ [ሀ]ለአስራ ሁለቱና ለአማካሪዎቻችሁ እና መሪዎቻችሁ እንዲሆኑም ለተመደቡት ለእነዚያ [ለ]ለቀዳሚ አመራር የዚህ ክህነት ሀይል የሙሉ [ሐ]ዘመን ፍጻሜ ለሆነው ለመጨረሻዎቹ ቀናት እና ለመጨረሻ ጊዜም ተሰጥቷል፣

፴፩ ሀይልን የምትይዙት፣ ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ በማንኛውም ዘመን ከተቀበሉት ሁሉ ጋር በተገናኘ ነው፤

፴፪ እውነት እላችኋለሁ፣ የተቀበላችሁት የዘመን [ሀ]ቁልፎች ከአባቶች [ለ]የመጡ እና በመጨረሻም ወደ እናንት ከሰማይ የተላኩ ናቸውና።

፴፫ እውነት እላችኋለሁ፣ ጥሪአችሁ እንዴት ታላቅ እንደሆነ ተመልከቱ። የዚህ ትውልድ ደም ከእጆቻችሁ [ሀ]እንዳይጠየቁ፣ ልባችሁንና ልብሶቻችሁን [ለ]አንጹ።

፴፬ እስከምመጣም ድረስ ታማኝ ሁኑ፣ ቶሎ [ሀ]እመጣለሁና፤ እና ለእያንዳንዱም ሰው እንደ [ለ]ስራው እንዲከፈለው ደመወዙም ከእኔ ዘንድ ነው። እኔ አልፋ እና ኦሜጋ ነኝ። አሜን።

፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፴፬–፴፭።
ለ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. ማዳመጥ፤
ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣
መታዘዝ።
፳፫ ሀ ኢሳ. ፷፥፪፤
ሚክ. ፫፥፮፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፩።
ቅ.መ.መ. ክህደት—
የመጀመሪያ የክርስትያን
ቤተክርስትያን ክህደት።
ለ ት. እና ቃ. ፲፥፳–፳፫።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. በቀል።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፳።
፳፭ ሀ ፩ ጴጥ. ፬፥፲፯–፲፰።
፳፮ ሀ ማቴ. ፯፥፳፩–፳፫፤
ት. እና ቃ. ፵፩፥፩፤ ፶፮፥፩።
ለ ሉቃ. ፮፥፵፮፤
ሞዛያ ፳፮፥፳፬–፳፯፤
፫ ኔፊ ፲፬፥፳፩–፳፫።
ሐ ቅ.መ.መ. መስደብ።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ለ ማር. ፲፮፥፲፭–፲፮።
፳፱ ሀ ሞር. ፱፥፳፪–፳፫፤
ት. እና ቃ. ፳፥፳፭–፳፮።
ለ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፴ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
ለ ቅ.መ.መ. ቀዳሚ አመራር።
ሐ ኤፌ. ፩፥፲፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፫፤
፻፳፬፥፵–፵፪።
ቅ.መ.መ. ዘመን።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፥፲፩–፲፮።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ አብር. ፩፥፪–፫።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፹፪፥፫።
ለ ያዕቆ. ፩፥፲፱።
፴፬ ሀ ራዕ. ፳፪፥፯፣ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፵፱፥፳፰፤ ፶፬፥፲።
ለ ቅ.መ.መ. ስራዎች።

ክፍል ፻፲፫

በመጋቢት ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.)፣ በፋር ዌስት፣ ምዙሪ ወይም አካባቢ ስለ ኢሳይያስ ፅሁፎች አንዳንድ መልሶች በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠበት።

፩–፮፣ የእሴይ ግንድ፣ ከዚያም የሚመጣው በትር፣ እና የእሴይ ስርም ምን እንደሆኑ ተገልጸዋል፤ ፯–፲፣ በፅዮን የተበተኑት ቅሪቶች ለክህነት ስልጣን መብት አላቸው እና ወደ ጌታ እንዲመለሱም ተጠርተዋል።

፩ በኢሳይያስ ፲፩ኛ ምእራፍ በ፩ኛ፣ ፪ኛ፣ ፫ኛ፣ ፬ኛ፣ እና ፭ኛ አንቀጾች ውስጥ የተነገረለት [ሀ]የእሴይ ግንድ ማን ነው?

፪ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፥ ይህም ክርስቶስ ነው።

፫ በኢሳይያስ ፲፩ኛ ምእራፍ በአንደኛው አንቀፅ ውስጥ ከእሴይ ግንድ እንደሚመጣ የተነገረለት በትር ምንድን ነው?

፬ እነሆ፣ ጌታ እንዲህ ይላል፥ ይህም በከፊል የእሴይ ተወላጅ እና [ሀ]የኤፍሬም ወይም የዮሴፍ ቤት አባል የሆነው፣ በእርሱም ላይ ብዙ [ለ]ሀይል ያረፈበት የክርስቶስ እጆች አገልጋይ የሆነው ነው።

፭ በኢሳይያስ ፲፩ኛ ምእራፍ ፲ኛ አንቀፅ ውስጥ የተነገረለት የእሴይ ስር ምንድን ነው?

፮ እነሆ፣ ጌታ እንዲህ ይላል፣ ይህም [ሀ]ለምልክት እና በመጨረሻዎቹ ቀናትም ህዝቤን [ለ]ለመሰብሰብ፣ ክህነትና የመንግስት [ሐ]ቁልፎች በመብት የእርሱ የሆነው የእሴይ፣ እንዲሁም የዮሴፍ ዘር ነው።

፯ የኢላየስ ሂግቢ ጥያቄዎች፥ በኢሳይያስ ፶፪ኛ ምእራፍ ፩ኛ አንቀጽ ውስጥ ፅዮን ሆይ፣ ኃይልሽን ልበሺ የሚለው ትእዛዝ ምን ማለቱ ነው—እና ኢሳይያስስ የሚያመለክተው የትኞቹን ህዝቦች ነው?

፰ የሚጠቁመውም እግዚአብሔር በመጨረሻዎቹ ቀናት ስለሚጠራቸው፣ [ሀ]ፅዮንን ዳግም ለማምጣትና እስራኤልን ለማዳን ክህነት መያዝ ስላለባቸው ስለእነርሱ ነው፤ እና [ለ]ኃይሏን መልበሷም ፅዮን በዘር [ሐ]መብት ያላትን የክህነት ባለስልጣንነትን መልበሷ ሲሆን፤ ደግሞም ወደአጣችው ሀይል መመለሷ ነው።

፱ ፅዮን ከአንገት እስራት ስለመፈታቷ ምን እንረዳላን፤ ፪ኛው አንቀፅ?

፲ መረዳት ያለብን የቀሩት [ሀ]ተባእቶች ከወደቁበት ወደ ጌታ [ለ]እንዲመለሱ በጥብቅ እንዲበረታቱ ነው፤ ይህንም ካደረጉ፣ የጌታ ቃል ኪዳንም እንደሚናገራቸው፣ ወይም ራዕይን እንደሚሰጣቸው ነው። ፮ኛ፣ ፯ኛ፣ እና ፰ኛ አንቀፅን ተመልከቱ። የአንገቷም እስራት ያለባት የእግዚአብሔር እርግማን፣ ወይም በአህዛብ መካከል የእስራኤል ቅሪቶች በመበተናቸው የደረሰባቸው ጉዳት ነው።

ክፍል ፻፲፬

በሚያዝያ ፲፩፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.)፣ በፋር ዌስት ሚዙሪ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ።

፻፲፫ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. እሴይ።
፬ ሀ ዘፍጥ. ፵፩፥፶–፶፪፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፴–፴፬።
ቅ.መ.መ. ኤፍሬም።
ለ ቅ.መ.መ. ሀይል።
፮ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ ት. እና ቃ. ፵፭፥፱።
ቅ.መ.መ. ምልክት።
ሐ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲፬።
ሐ ቅ.መ.መ. በኩር።
፲ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የተበተኑት እስራኤል።
ለ ሆሴ. ፫፥፬–፭፤
፪ ኔፊ ፮፥፲፩።

፩–፪፡ ታማኝ ባለሆኑት የተያዙት የቤተ ክርስቲያን ስልጣናት ለሌሎች ይሰጣሉ።

፩ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፥ አገልጋዬ ዴቭድ ደብሊው ፓትን በሚመጣው ጸደይ ከሌሎች ጋር፣ እንዲሁም እርሱን ጨምሮ አስራ ሁለት ከሆኑት ጋር፣ ስሜን ለመመስከር እና ለአለም ሁሉ የምስራች ለመውሰድ በተልዕኮ ይሰራልኝ ዘንድ፣ ጉዳዮቹን ሁሉ በቶሎ እንዲያከናውንና የሚሸጡ እቃዎቹን ይሸጥ ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፪ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላልና፣ ስሜን የሚክዱ በመካከላችሁ እስካሉ ድረስ፣ በእነርሱ [ሀ]ምትክ [ለ]የሚተከሉና የኤጺስ ቆጶስ አመራሩን የሚቀበሉ ሌሎች ይኖራሉ። አሜን።

ክፍል ፻፲፭

በሚያዝያ ፳፮፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) በፋር ዌስት ሚዞሪ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠውን የእዚያን ስፍራና የጌታን ቤት መገንባት በሚመለከት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያሳውቅ ራዕይ። ይህ ራዕይ ለቤተክርስቲያኗ አመራር ሀላፊዎች እና አባላት የተሰጠ ንግግር ነው።

፩–፬፡ ጌታ ቤተክርስቲያኑን የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ብሎ ጠራ፤ ፭–፮፡ ፅዮን እና ስቴኳ የቅዱሳን መጠበቂያ እና መሸሸጊያ ናቸው፤ ፯–፲፮፡ ቅዱሳን በፋር ዌስት ላይ የጌታን ቤት እንዲገነቡ ታዝዘዋል፤ ፲፯–፲፱፡ ጆሴፍ ስሚዝ የእግዚአብሔርን መንግስትን ቁልፍ በምድር ይዟል።

፩ ለአገልጋዬ [ሀ]ጆሴፍ ስሚዝ ዳግማዊ እና ደግሞም ለአገልጋዬ [ለ]ስድኒ ሪግደን፣ እና ደግሞም ለአገልጋዬ [ሐ]ሀይረም ስሚዝ፣ እና ለተመደቡት ከዚህም በኋላ ለሚመደቡት አማካሪዎቻችሁ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፤

፪ ደግሞም ለአንተ፣ ለአገልጋዬ [ሀ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ እና ለአማካሪዎቹ፤

፫ ደግሞም በፅዮን ውስጥ በቤተክርስቲያኔ ከፍተኛ ሸንጎ አባል ለሆናችሁ ታማኝ አገልጋዮቼ፣ እንዲህም ተብሎ ይጠራልና፣ እና በአለም ሁሉ በውጪ ለተበተኑት ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች እና ህዝብ ሁሉ።

፬ በመጨረሻዎቹ ቀናትም [ሀ]ቤተክርስቲያኔ የምትጠራው በዚህ፣ እንዲሁም በየኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ [ለ]ቤተክርስቲያን ስም ነው።

፭ ለሁላችሁም እውነት እላችኋለሁ፥ ለህዝቦች [ሀ]መመሪያ ትሆኑ ዘንድ [ለ]ተነሱ እና አብሩ፤

፮ እና [ሀ]በፅዮን ምድርና [ለ]በካስማዎቿ ላይ አብሮ [ሐ]መሰብሰቡ ከአውሎ ነፋስ፣ እና ቁጣም ሳይቀላቀል በምድር ሁሉ ላይ [መ]ከሚፈሰው መጠበቂያ እና [ሠ]መሸሸጊያ ይሆን ዘንድ ተነሱ እናም አብሩ።

፯ ከተማው፣ ፋር ዌስት፣ [ሀ]ቅዱስና ለእኔ

፻፲፬ ፪ሀ ት. እና ቃ. ፷፬፥፴።
ለ ት. እና ቃ. ፻፲፰፥፩፣ ፮።
፻፲፭ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ።
ለ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
ሐ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሀይረም።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣ ኤድዋርድ።
፬ሀ ፫ ኔፊ ፳፯፥፬–፰።
ለ ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
፭ሀ ኢሳ. ፲፩፥፲፪።
ቅ.መ.መ. ምልክት።
ለ ኢሳ. ፷፥፩–፫።
፮ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
ለ ት. እና ቃ. ፻፩፥፳፩።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
ሐ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
መ ራዕ. ፲፬፥፲፤
ት. እና ቃ. ፩፥፲፫–፲፬።
ሠ ኢሳ. ፳፭፥፩፣ ፬፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥፷፮–፸፩።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።

የተቀደሰ ምድር ይሁን፤ እና ከሁሉም በላይ ቅዱስ ይባላል፣ እናንተ የቆማችሁ በት ምድር ቅዱስ ነውና።

፰ ስለዚህ፣ [ሀ]የመልኩኝ ዘንድ ለቅዱሳኔ መሰብሰቢያ እንዲሆን፣ ቤትን [ለ]ትገነቡልኝ ዘንድ አዝዛችኋለሁ።

፱ እና ለዚህም ስራ መጀመሪያ፣ እና መሰረት፣ እና የማዘጋጀውም ስራ በሚቀጥለው በጋ ይሁን፤

፲ እና መጀመሪያውም በሚቀጥለው ሀምሌ ፬ ቀን ላይ ይሁን፤ እና ከዚያም ጊዜ በኋላ ህዝቤ በስሜ ቤት ይገነቡልኝ ዘንድ በቅንነት ይስሩ፤

፲፩ እና ከዚህ ቀን [ሀ]አንድ አመት በኋላ [ለ]ለቤቴ መሰረትን መገንባት ዳግም ይጀምሩ።

፲፪ በዚህም ከዚያ ቀን ጀምሮ፣ ከማዕዘን ድንጋዩ እስከ ላይኛው ያለው እስከሚፈጸም፣ ምንም ነገር ሳይቀር ሁሉም እስከሚፈጸም ድረስ በቅንነት ይስሩ።

፲፫ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ ወይም አገልጋዬ ስድኒ፣ ወይም አገልጋዬ ሀይረም በስሜ ቤት ለመገንባት ተጨማሪ እዳ አይግቡ፤

፲፬ ነገር ግን ለእነርሱ በማሳያቸው [ሀ]ምሳሌ መሰረት ለስሜ ቤት ይሰራ።

፲፭ እና ህዝቤ ለአመራሮቻቸው በማሳየው ምሳሌ መሰረት ባይገነቡት፣ ከእጆቻቸው ይህን አልቀበልም።

፲፮ ነገር ግን ህዝቤ ለአመራሮቻቸው፣ እንዲሁም ለአገልጋዬ ጆሴፍ እና አማካሪዎቹ፣ በማሳያቸው ምሳሌ መሰረት ቢገነቡ፣ ከዚያም ከህዝቤ እጆች ይህን እቀበላለሁ።

፲፯ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ቅዱሳኔ በተሰበሰቡበት የፋር ዌስት ከተማ በፍጥነት መገንባቱ ፍቃዴ ነው።

፲፰ ደግሞም በአካባቢው በሚገኙት ስፍራዎችም፣ ከጊዜ ወደጊዜ በአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ በሚገለጹበት፣ [ሀ]ለካስማዎች ሌሎች ስፍራዎችም ይመደባሉ።

፲፱ እነሆ፣ እኔ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፣ እናም ከህዝቡም ፊት እቀድሰዋለሁና፤ የዚህን መንግስትና አገልግሎት [ሀ]ቁልፎች ሰጥቼዋለሁና። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፲፮

በግንቦት ፲፱፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) በስፕሪንግ ሂል፣ በዴቪስ የግዛት ክፍል፣ ሚዙሪ ውስጥ በራይት ማመላለሻ ጀልባ አጠገብ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ።

፩ ስፕሪንግ ሂል በጌታ እንደ [ሀ]አዳም-ኦንዳይ-አማን ተጠርቷል፣ ምክንያቱም፣ እንዲህም ይላል፣ ይህም [ለ]አዳም ህዝቡን ለመጎብኘት የሚመጣበት ወይም፣ በነቢዩ ዳንኤል እንደተነገረው፣ [ሐ]በዘመናት የሸመገለውም የሚቀመጥበት ስፍራ ነው።

ክፍል ፻፲፯

በሀምሌ ፰፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) በፋር ዌስት ሚዙሪ ውስጥ የውልያም ማርክስ፣

፰ ሀ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፻፲፱፤ ፺፭፥፰።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፰፥፭።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፴፩–፵፬።
፲፬ ሀ ዕብ. ፰፥፭፤ ት. እና ቃ. ፺፯፥፲።
፲፰ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፳፩። ቅ.መ.መ. ካስማ።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፻፲፮ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፲፭። ቅ.መ.መ. አዳም-ኦንዳይ-አማን።
ለ ቅ.መ.መ. አዳም።
ሐ ዳን. ፯፥፲፫–፲፬፤ ፳፪።

የኒዌል ኬ ዊትኒ፣ እና የኦሊቨር ክሬንጀርን ሀላፊነት በሚመለከት ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ።

፩–፱፣ የጌታ አገልጋዮች ምድራዊ ነገሮችን መመኘት የለባቸውም፣ “ለጌታ ንብረት ምኑ ነውና?”፤ ፲–፲፮፣ የነፍስን አሳንሶ ማየትን ይተዉ፣ እና መስዋዕታቸውም ለጌታ የተቀደሰ ይሆናል።

፩ ለአገልጋዬ ዊልያም ማርክስ፣ እና ለአገልጋዬ ኒዌል ኬ ዊትኒ ጌታ እንዲህ ይላል፣ ጉዳዮቻቸውን በፍጥነት ይፈፅሙ እና እኔ ጌታ በምድር ላይ በረዶ ከመላኬ በፊት ከከርትላንድ ምድር ይጓዙ።

፪ ንቁ፣ እና ተነሱ፣ እና ኑ፣ እናም አትዘግዩ፣ እኔ ጌታ ይህን አዝዤአለሁና።

፫ ስለዚህ ቢዘገዩ ከሆኑ መልካም አይሆንላቸውም።

፬ ለኃጢአታቸው ሁሉ፣ እና ለምኞቶቻቸው ሁሉ በፊቴ ንስሀ ይግቡ ይላል ጌታ፤ ለእኔ [ሀ]ንብረት ምኔ ነው? ይላል ጌታ።

፭ የከርትላንድ ንብረቶችም [ሀ]ለእዳ ይተው፣ ይላል ጌታ። ተዉአቸው፣ ይላል ጌታ፣ እና የሚቀረው ማንኛውም በእጆቻችሁ ይቆይ፣ ይላል ጌታ።

፮ የሰማይን አዕዋፋት፣ እና የባህርን አሶች፣ እና የተራራዎቹ እንስሳት የሉኝ ምን? ምድርን አልሰራሁምን? የአለም ህዝብ ሰራዊት [ሀ]እጣ ፈንታ አልያዝኩምን?

፯ ስለዚህ፣ [ሀ]ብቸኛ ስፍራዎችን እንዲፈኩ እና እንዲያብቡ፣ እና ብዙም እንዲያፈሩ አላደርግምን? ይላል ጌታ።

፰ [ሀ]በአዳም-ኦንዳይ-አማን ተራራ ላይ፣ እና በኦሌያ [ለ]ሺኔህ ሜዳ ላይ፣ ወይም አዳም በኖረበት [ሐ]ምድር ብቁ ስፍራ ስለሌለ ነው ጠብታ የሆነውን የምትመኙት፣ እና ከፍተኛ ተፅዕኖ ያላቸውን ጉዳዮች ችላ የምትሉት?

፱ ስለዚህ፣ ወደዚህ ወደ ህዝቤ ምድር፣ እንዲሁም ወደ ፅዮን ኑ።

፲ አገልጋዬ ውልያም ማርክስ በትንሽ ነገሮች [ሀ]ታማኝ ይሁን፣ እና እርሱም በብዙ ነገሮች መሪ ይሆናል። በፋር ዌስት ከተማ ውስጥ በህዝቤ መካከል ይምራ፣ እና በህዝቤ በረከቶችም ይባረክ።

፲፩ አገልጋዬ ኒውል ኬ ዊትኒ ስለ [ሀ]ኒቆላውያንን ስራ እና ስለ [ለ]ስውር ርኩሰታቸው ሁሉ፣ እና በፊቴ ነፍስን አሳንሶ ማየትን ሁሉ ይፈር፣ ይላል ጌታ፣ እና ወደ አዳም-ኦንዳይ-አማን ምድር ና፣ እና የህዝቤም [ሐ]ኤጲስ ቆጶስ ሁን፣ ይላል ጌታ፣ በስም ብቻ ሳይሆን በተግባር ይሁን፣ ይላል ጌታ።

፲፪ ደግሞም እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ [ሀ]ኦሊቨር ግሬንጀርን አስታውሳለሁ፤ እነሆ፣ እውነት እለዋለሁ ስሙ ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ለዘለአለም በቅዱስ መታሰቢያ ይያዛል፣ ይላል ጌታ።

፲፫ ስለዚህ፣ ለቤተክርስቲያኔ ቀዳሚ አመራር ደህንነት በቅንነት ይስራ፣ ይላል ጌታ፤ እና ቢወድቅ ዳግም ይነሳል፣ [ሀ]መስዋዕቱ ለእኔ ከፍሬው በላይ ቅዱስ ነው፣ ይላል ጌታ።

፲፬ ስለዚህ፣ ፈጥኖም ወደዚህ፣ ወደ ፅዮን ምድር ይምጣ፤ እና በጊዜውም ለህዝቤ ጥቅም በስሜ የሚያተርፍ ይሆናል፣ ይላል ጌታ።

፲፭ ስለዚህ፣ ማንም ሰው አገልጋዬ ኦሊቨር ግሬንጀርን አይጥላው፣ ነገር ግን የህዝቤ በረከቶች በእርሱ ላይ ለዘለአለም ይሁኑ።

፻፲፯ ፬ሀ ት. እና ቃ. ፻፬፥፲፬።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፻፬፥፸፰።
፮ሀ የሐዋ. ፲፯፥፳፮፤
፩ ኔፊ ፲፯፥፴፮–፴፱።
፯ሀ ኢሳ. ፴፭፥፩፤
ት. እና ቃ. ፵፱፥፳፬–፳፭።
፰ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፮።
ቅ.መ.መ. አዳም-ኦንዳይ-አማን።
ለ አብር. ፫፥፲፫።
ሐ ቅ.መ.መ. ዔድን።
፲ሀ ማቴ. ፳፭፥፳፫።
፲፩ሀ ራዕ. ፪፥፮፣ ፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. የሚስጥር ስብሰባ።
ሐ ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፲፪ሀ ይህም ነቢዩ በከርትላንድ ጉዳዮቹን እንዲፈጽሙ ሀላፊነት ሰጥቷቸው የነበሩ ወኪሎች ማለት ነው።
፲፫ሀ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።

፲፮ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በከርትላንድ ምድር ውስጥ ያሉት አገልጋዮቹ ጌታ አምላካቸውን፣ እና ደግሞም ቤቴን እንዲቀድሱ እና እንዲጠብቁ፣ እና የገንዘብ ለዋጮችን በጊዜዬ ይሽሩ ዘንድ ያስታውሱ፣ ይላል ጌታ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፲፰

በሀምሌ ፰፣ ፲፰፻፴፰፣ በፋር ዌስት ሚዙሪ ውስጥ፣ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል “ጌታ ሆይ፣ አስራ ሁለቱን በሚመለከት ፈቃድህን አሳየን” በሚለው ልመና መልስ የተሰጠበት ራዕይ።

፩–፫፣ ለአስራ ሁለቱ ቤተሰቦች ጌታ ያቀርብላቸዋል፤ ፬–፮፣ በአስራ ሁለቱ ውስጥ ያሉት ክፍት ስፍራዎች ተሞልተዋል።

፩ በእውነት፣ እንዲህ ይላል ጌታ፥ ጉባኤ ወዲያው ይሰብሰብ፤ አስራ ሁለቱም ይደራጁ፤ እና እነዚያን የወደቁትን ክፍተቶች [ሀ]ለሙላት ሰዎች ይመደቡ።

፪ አገልጋዬ [ሀ]ቶማስ ቃሌን ለማተም በፅዮን ለጥቂት ጊዜ ይቆይ።

፫ ከእዚያ ሰአት ጀምሮ የሚቀሩትም በመስበክ ይቀጥሉ፣ እና ይህንንም በልብ ርህራሄ፣ በየዋህነት፣ [ሀ]በትህትና፣ እና [ለ]በትዕግስት ሁሉ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ቢያደርጉ፣ እኔ ጌታ ለቤተሰቦቻቸው እርዳታ እንደምሰጥ፣ እና ከዚህም ጊዜ የበረከት በር እንደሚከፈትላቸው ቃል እገባላቸዋለሁ።

፬ እና በሚቀጥለውም ጸደይ በታላቅ ውሀዎች ተሻግረው ይሂዱ፣ እና በዚያም ወንጌሌን፣ የእርሱንም ሙላት ያውጁ፣ እና ስለስሜም ምስክርነትን ይስጡ።

፭ በፋር ዌስት ከተማም በሚያዝያ ሀያ ስድስት ቀን ላይ በቤቴ መገንቢያ ስፍራ ላይ ከቅዱሳኔ ተለይተው ይሂዱ፣ ይላል ጌታ።

፮ አገልጋዬ ጆን ቴይለር፣ እና ደግሞም አገልጋዬ ጆን ኢ. ፔጅ፣ እና ደግሞም አገልጋዬ ዊልፈርድ ዉድረፍ፣ እና ደግሞም አገልጋዬ ዊለርድ ሪቻርድስ የወደቁትን በእነዚያ ቦታ ክፍተቶቹን እንዲሞሉ ይመደቡ፣ እና መመደባቸውም በህጋዊ መንገድ ይነገራቸው።

ክፍል ፻፲፱

በሐምሌ ፰፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) በፋር ዌስት ሚዙሪ፣ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ “ጌታ ሆይ፣ የህዝብህን ንብረቶች ለአስራት እንዴት እንዲሆን እንደምትሻ ለአገልጋዮችህ አሳይ” በማለት ለለመነው መልስ የተሰጠ ራዕይ። የአስራት ህግ፣ በዚህ ጊዜ እንደተረዳነው፣ ከዚህ ራዕይ በፊት ለቤተክርስቲያኗ አልተሰጣትም ነበር። በተጠቀሰው ጸሎት እና ከዚህ በፊት በነበሩት ራዕዮች (፵፪፥፴፫፤ ፶፩፥፲፫፤ ፶፰፥፴፮) ውስጥ አስራት አንድ አስረኛ ማለት ብቻ አልነበረም፣ ነገር ግን ለቤተክርስቲያኗ ገንዘብ በፈቃድ የሚሰጥበትን ወይም የሚያዋጡት ሁሉ ማለት ነበር። ከዚህ በፊት ጌታ ለቤተክርስቲያኗ አባላት (ዋና መሪ ሽማግሌዎች) ለዘለአለም የሚሆ

፻፲፰ ፩ሀ የሐዋ. ፩፥፲፫፤ ፲፮–፲፯፤ ፳፩–፳፮።

፪ሀ ቅ.መ.መ. ማርሽ፣ ቶማስ ቢ።

፫ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።

ለ ቅ.መ.መ. መፅናት።

ነውን ቃል ኪዳን የገቡበት የቅድስና እና የንብረት መጋቢነት ህግጋትን ሰጥቷቸው ነበር። ብዙዎች በዚህ ቃል ኪዳን መሰረት ለመኖር ስለአዳገታቸው፣ ጌታ ይህን ለጊዜው ወሰደው እና በዚህ ምትክ ለቤተክርስቲያኗ ሁሉ የአስራት ህግን ሰጠ። ነቢዩ ጌታን ከንብረታቸው ምን ያኽሉን ለዚህ ቅዱስ አላማ እንደሚፈልግባቸው ጠየቀ። መልሱም ይህ ራዕይ ነበር።

፩–፭፣ ቅዱሳን ትርፍ ንብረቶቻቸውን ያበርክቱ እና ከዚያም እንደ አስራት በየአመቱ የወለዳቸውን አንድ አስረኛውን ይስጡ፤ ፮–፯፣ እንደዚህ አይነት ድርጊት የፅዮንን ምድር ይቀድሳል።

፩ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ በፅዮን ውስጥ ባለው በቤተክርስቲያኔ ኤጲስ ቆጶስ እጆች ውስጥ የሚገኙትን [ሀ]የትርፍ ንብረቶቻቸውን ሁሉ እንዲሰጡ እጠይቃቸዋለሁ፣

፪ [ሀ]ቤቴን ለመገንባት፣ እና የፅዮንን መሰረት ለማዘጋጀት እና ለክህነት ስልጣን፣ እና ለቤተክርስቲያኔ አመራር እዳዎችም እንዲሰጡ እጠይቃቸዋለሁ።

፫ እና ይህም የህዝቤ [ሀ]አስራት መጀመሪያ ይሆናል።

፬ እና ከዚህ በኋላ፣ እንደዚህ አስራት የከፈሉት በየአመቱ የገቢያቸውን ሁሉ አንድ አስረኛውን ይስጡ፤ እና ይህም ለዘለአለም ለእነርሱ፣ ለቅዱስ ክህነቴ ቋሚ ህግ ይሆንላቸዋል፣ ይላል ጌታ።

፭ እውነት እላችኋለሁ፣ እንዲህም ይሆናል፣ [ሀ]በፅዮን ምድር ውስጥ የተሰበሰቡት ሁሉ በትርፍ ንብረቶቻቸው ላይ አስራት ይከፍላሉ፣ እና ይህን ህግም ይከተላሉ፣ አለበለዚያ በመሀከላችሁ ለመኖር ብቁ አይሆኑም።

፮ እና እላችኋለሁ፣ ህዝቤ ይህን ህግ በቅድስና በመጠበቅ የማይከተሉ ቢሆን፣ እና ህጌን እና ውሳኔዬን በእንዲህም ይጠበቁ ዘንድ፣ ከሁሉም በላይ ቅዱስም ይሆን ዘንድ በዚህ ህግ [ሀ]የፅዮንን ምድርን የሚቀድሱልኝ ባይሆን፣ እነሆ እውነት እላችኋለሁ፣ ለእናንተ የፅዮን ምድር አይሆንላችሁም።

፯ እና ይህም ለሁሉም የፅዮን [ሀ]ካስማዎች ምሳሌ ይሁን። እንዲህም ይሁን። አሜን።

ክፍል ፻፳

በሐምሌ ፰፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) በፋር ዌስት ሚዙሪ ከቀደመው ራዕይ፣ ክፍል ፻፲፱፣ የተጠቀሱት በአስራት የተሰጡትን ንብረቶችን ምን እንደሚደረግባቸው ለማሳወቅ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ።

፩ በእውነት እንዲህ ይላል ጌታ፣ ለቤተክርስቲያኔ ቀዳሚ አመራር፣ እናለ ኤጲስ ቆጶስ እና ለሸንጎው፣ እና ለከፍተኛ ሸንጎዬ፣ እና በምሰጣቸውም በራሴ ድምጽ፣ [ሀ]ይህም በሸንጎው በጥቅም ላይ የሚውልበት ጊዜ አሁን ነው፣ ይላል ጌታ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፲፱ ፩ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥፴፫–፴፬፤
፶፭፤ ፶፩፥፲፫፤
፹፪፥፲፯–፲፱።
፪ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፭፥፰።
፫ሀ ሚል. ፫፥፰–፲፪፤
ት. እና ቃ. ፷፬፥፳፫።
ቅ.መ.መ. አስራት፤
አስራት መክፈል።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፶፯፥፩–፫።
፮ሀ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ካስማ።
፻፳ ፩ሀ ይህም አስራት
ማለት ነው።

ክፍል ፻፳፩

በመጋቢት ፳፣ ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) በልብረቲ ሚዙሪ በእስር ቤት ውስጥ እስረኛ ሆኖ እያለ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ለቤተክርስቲያኗ በተሰጠ ደብዳቤ ውስጥ የተጻፉ ጸሎት እና ትንቢቶች። ነቢዩ እና አያሌ ባልንጀሮቹ በእስር ቤት ውስጥ ብዙ ወራትን አሳልፈው ነበር። ወደ ውሳኔ ሰጪ ዋና ሰዎችና ወደ ፍርድ ቤቶች የላኩት አቤቱታቸው እና ልመናቸው ምንም እርዳታ አላመጡላቸውም።

፩–፮፣ ነቢዩ ስለቅዱሳን ስቃይ ጌታን ለመነ፤ ፯–፲፣ ጌታም ለእርሱም ሰላምን ተናገረ፤ ፲፩–፲፯፣ በጌታ ህዝብ ላይ በሀሰት መተላለፍ ክስን የሚከሷቸው ሁሉ የተረገሙ ናቸው፤ ፲፰–፳፭፣ ለክህነት ስልጣን መብትም አይኖራቸውም እና ይኮነናሉ፤ ፳፮–፴፪፣ በብርታት ለሚጸኑትም የክብር ራዕዮች ቃል ተገብተውላቸዋል፤ ፴፫–፵፣ ለምን ብዙዎችም እንደተጠሩ እና ጥቂቶችም እንደተመረጡ፤ ፵፩–፵፮፣ ክህነትን በፅድቅ ብቻ ሊጠቀሙበት እንደሚገባ።

፩ እግዚአብሔር ሆይ፣ የት ነህ? እና [ሀ]የተሰወርክበትን ስፍራ የሚሸፍነው ድንኳን የት ነው?

፪ [ሀ]እስከመቼ እጅህ፤ አይንህ አዎን ንጹህ አይኖችህ ከዘለአለማዊው ሰማይ በህዝብህ እና በአገልጋዮችህ ላይ የሚደረጉትን ክፋቶች እያዩ ለቅሶአቸውም ወደ ጆሮህ እያስተጋባ ትታገሳለህ?

፫ አዎን፣ ጌታ ሆይ፣ ልብህ ለእነርሱ ከመለሳለሱ በፊት፣ እና ለእነርሱም አንጀትህ በርህራሄ እስከሚሞላ ድረስ [ሀ]ለስንት ጊዜ እነዚህን ክፋቶችን እና ህጋዊ ያልሆኑትን ጭቆናዎችን ይሰቃዩ።

፬ ሰማይን፣ እና ምድርን፣ እና ባህሮችን፣ እና በውስጣቸው ያሉትን ነገሮችን ሁሉ ፈጣሪው፣ እና ዲያብሎስን እና ጥቁር እና ያጨለመውን የሲኦል ግዛት የምትቆጣጠር እና በቁጥጥር ስር የምታደርግ [ሀ]ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ—እጅህን ዘርጋ፤ አይንህም በትኩረት ይመልከት፤ ድንኳንህም ይነቀል፤ [ለ]የተሰወርክበትም ስፍራ አይሸፈን፤ ጆሮህም ያዘንብል፤ ልብህም ይለሳለስ፣ እና አንጀትህም በርህራሄ ወደ እኛ ይሞላ።

፭ ቁጣህም በጠላቶቻችን ላይ ይቀጣጠል፤ እና በልብህ ቁጣ፣ በጎራዴህ ክፉት ስለተደረጉብን [ሀ]ተበቀልልን።

፮ አምላካችን ሆይ፣ የሚሰቃዩትን ቅዱሳንህን አስታውስ እና አገልጋዮችህም በስምህ ለዘለአለም ይደሰታሉ።

፯ ልጄ፣ ለነፍስህ ሰላም ይኑርህ፤ [ሀ]ጭንቀትህ እና ስቃይህ ለጥቂት ጊዜ ቢሆን ነው፤

፰ ከዚያም፣ በመልካም ይህን [ሀ]ብትጸና፣ እግዚአብሔርም ወደ ላይ ዘለአለማዊ ክብር ይሰጥሀል፤ ጠላቶችህንም በሙሉ ታሸንፋቸዋለህ።

፱ [ሀ]ባልንጀሮችህ በአጠገብህ ቆመዋል፣ እና በሞቀ ልብ እና በጓደኝነት እጆች እንደገናም ሰላምታ ይሰጡሀል።

፲ እንደ [ሀ]ኢያብም ገና አይደለህም፤ ባልንጀሮችህ በኢያብ እንዳደረጉትም በአንተም ላይ በተቃራኒነት አይጣሉህም፣ ወይም በመተላለፍ አይከሱህም።

፲፩ እና በመተላለፍ የሚከሱህም፣ ተስፋቸው ይከስማል፣ እና በምትወጣው ጸሀይ በሚያነድ ጨረር እንደሚቀልጥ [ሀ]በረዶም፣ ተስፋ ያደረጉበትም ነገር ይጠፋል፤

፲፪ ደግሞም እግዚአብሔር እጁም ተገ

፻፳፩ ፩ሀ መዝ. ፲፫፥፩–፪፤ ፻፪፥፩–፪።
፪ሀ እንባ. ፩፥፪።
፫ሀ ት. እና ቃ. ፻፱፥፵፱።
፬ሀ ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚገዛ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፫፥፮።
፭ሀ ሉቃ. ፲፰፥፯–፰።
፯ሀ ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፰ሀ ፩ ጴጥ. ፪፥፲፱–፳፫።
ቅ.መ.መ. መፅናት።
፱ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፪፥፫።
፲ሀ ቅ.መ.መ. ኢዮብ።
፲፩ሀ ዘፀአ. ፲፮፥፲፬።

ልጧል እና ድንቅ ስራዎቹ እንዳይገቧቸው ዘንድ [ሀ]ጊዜያትን እና ዘመናትን ለመቀየርና አዕምሮዎቻቸውን ያጨልም ዘንድ፤ ደግሞም እንዲያረጋግጥላቸውም እና በአታላይነታቸው ይይዛቸው ዘንድ አትሟል፤

፲፫ ደግሞም ልቦቻቸው የረከሱ ስለሆኑ፣ እና በሌሎች ላይ ክፉ ነገሮች እንዲወድቅባቸው ፈቃደኛ ስለሆኑ፣ እና ሌሎች እንዲሰቃዩ ለማድረግ ስለሚወዱ፣ ይህም [ሀ]በእነርሱ ላይ በሚበልጥ መጠን ይመጣባቸዋል፤

፲፬ ተስፋ ያጡ ዘንድ፣ እና ተስፋቸውም እንዲቆረጥ፤

፲፭ እና ከዚህ ጊዜ አያሌ አመታት ሳያልፉም፣ እነርሱ እና መጪዎቹ ትውልዶቻቸው ከሰማይ በታች ይጠረጋሉ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ ማናቸውም በግድግዳው ቆመው አይቀሩም።

፲፮ በእኔ [ሀ]በተቀቡት ላይ ተረከዛቸውን የሚያነሱት፣ ይላል ጌታ፣ እና ምንም እንኳን በአይኖቼ ብቁ የሆኑትን እና ያዘዝኳቸውን የሚያደርጉትን፣ በፊቴ ኃጢአትን ያልሰሩት [ለ]ኃጢአት ሰርተዋል በማለት የሚጮሁት ሁሉ የተረገሙ ናቸው፣ ይላል ጌታ።

፲፯ ነገር ግን ስለመተላለፍ የሚጮሁት ይህን የሚያደርጉት የኃጢአት አገልጋዮች እና ራሳቸውም የአመጸኞች [ሀ]ልጆች ስለሆኑ ነው።

፲፰ እና ወደባርነት እና ወደ ሞት ያመጧቸው ዘንድ በአገልጋዮቼ ላይ በሀሰት የሚመሰክሩትም—

፲፱ ወዮላቸው፤ ታናናሾቼን [ሀ]ስለሚያሰናክሉ ከቤቴ [ለ]ስርዓቶች ይቆረጣሉ።

፳ [ሀ]ቅርጫታቸውም አይሞላም፣ ቤታቸውና ጎተራዎቻቸውም ይጠፋሉ፣ እና እራሳቸውም በሚያባብሏቸው ይጠላሉ።

፳፩ እነርሱ ወይም መጪዎቹ ትውልዶቻቸውም ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ [ሀ]ለክህነት ስልጣንም መብት አይኖራቸውም

፳፪ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቶቻቸው ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስመጥ [ሀ]በተሻላቸው ነበር።

፳፫ ህዝቤን እንዳይመቻቸው ለሚያደርጉም፣ እና ለሚያሳድዷቸው፣ እና ለሚገድሏቸው፣ እና በእነርሱም ላይ ለሚመሰክሩባቸው ሁሉ ወዮላቸው ይላል የሰራዊት ጌታ፤ [ሀ]የእፉኝት ልጆች ከገሀነም ፍርድ አያመልጡም።

፳፬ እነሆ፣ አይኖቼ [ሀ]ያያሉ እና ስራቸውን ሁሉ አውቃለሁ፣ እና ለሁሉም በጊዜውም ፈጣን [ለ]ፍርድም አኑሬላቸዋለሁ፤

፳፭ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ [ሀ]ስራው የተመደበለት [ለ]ጊዜ አለውና።

፳፮ እግዚአብሔር [ሀ]እውቀቱን [ለ]በቅዱስ መንፈሱ፣ አዎን አለም ከነበረበት እስከ አሁንም ድረስ ባልተገለጠውን፣ ለመናገርም የማይቻለውን የመንፈስ ቅዱስ [ሐ]ስጦታውን ይሰጣችኋል፤

፳፯ በመጨረሻዎቹ ዘመናት እንዲገለጡ የቀደሙት አባቶቻችን በጉጉት የጠበቋቸውን፣ ለክብራቸው ሙላት በኋላም የተጠበቁትን በመላዕክት ሀሳብ የተመሩበትን እውቀት ይሰጣችኋል፤

፳፰ እነርሱ ስለሚገለጡ፣ አንድ አምላክም ይኑር ብዙ [ሀ]አማልክት፣ ይህም [ለ]ማንኛውም ነገር የማይሰወርበት ጊዜ ነው።

፲፪ ሀ ዳን. ፪፥ ፳፩።
፲፫ ሀ ምሳ. ፳፰፥ ፲፤
፩ ኔፊ ፲፬፥ ፫።
፲፮ ሀ ፩ ሳሙ. ፳፮፥ ፱፤
መዝ. ፻፭፥ ፲፭።
ለ ፪ ኔፊ ፲፭፥ ፳፤
ሞሮኒ ፯፥ ፲፬፤ ፲፰።
፲፯ ሀ ኤፌ. ፭፥ ፮።
፲፱ ሀ ማቴ. ፲፰፥ ፮።
ቅ.መ.መ. መበደል።
ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
፳ ሀ ዘዳግ. ፳፰፥ ፲፭–፳።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ክህነት።
፳፪ ሀ ማቴ. ፲፰፥ ፮፤
ት. እና ቃ. ፶፬፥ ፭።
፳፫ ሀ ማቴ. ፲፪፥ ፴፬።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ሁሉን የሚያውቅ።
ለ ሔለ. ፰፥ ፳፭።
ቅ.መ.መ. ዳኛ፣ ፍርድ።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ለ ኢዮብ ፯፥ ፩፤
ት. እና ቃ. ፻፳፪፥ ፱።
፳፮ ሀ ዳን. ፪፥ ፳–፳፪፤
እ.አ. ፩፥ ፱።
ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ት. እና ቃ. ፰፥ ፪–፫።
ሐ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።
፳፰ ሀ መዝ. ፹፪፥ ፩፣ ፮፤
ዮሐ. ፲፥ ፴፬–፴፮፤
፩ ቆሮ. ፰፥ ፭–፮፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፶፰፤
፻፴፪፥ ፳፤
አብር. ፬፥ ፩፤ ፭፥ ፩–፪።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፷፩፤
፸፮፥ ፯–፰፤ ፺፰፥ ፲፪።

፳፱ ዙፋናት ቢሆኑ እና ጌትነት እና አለቅነት እና ሥልጣናት ሁሉ [ሀ]ይገለጣሉ እና ለኢየሱስ ክርስቶስም ወንጌል በብርታት ለጸኑት ሁሉ ይሰጧቸዋል።

፴ ደግሞም፣ ለሰማያት ወይም ለባህሮች፣ ወይም ለደረቅ መሬት፣ ወይም ለጸሀይ፣ ጨረቃ፣ ወይም ለከዋክብት [ሀ]ገደብ ቢሆን—

፴፩ የሚዞሩባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ በተመደቡላቸው ቀናት፣ ወራት፣ እና አመታት ሁሉ፣ እና በየቀናቶቻቸው ቀናት፣ ወራት፣ እና አመታት ሁሉ፣ እና በክብሮቻቸው፣ በህግጋታቸው፣ እና በተወሰኑት ጊዜያቶቻቸው ሁሉ፣ [ሀ]በዘመን ፍጻሜ ቀናት ሁሉ ይገለጣሉ—

፴፪ ሁሉም ሰው ወደ [ሀ]ዘለአለማዊነቱ እና ወደ ህያው [ለ]እረፍቱ ሲገቡ፣ እስከመጨረሻው እና ለዚህ መጨረሻም ይጠበቅ ዘንድ፣ ከዚህ አለም በፊት በሌሎች አማልክት ዘለአለማዊ [ሐ]አምላክ [መ]ሸንጎ መካከል በተመደበው መሰረት ያም ሊሆን ይገባዋል።

፴፫ እስከመቼ ጊዜ የሚደበላለቀው ውሀ ንጹህ ሆኖ ሊቆይ ይቻለዋል? የትኛውስ ሀይል ሰማያትን ሊያቆም ይችላል? በኋለኛው ቀን ቅዱሳን ራሶች ላይ ሁሉን የሚገዛው ከሰማይ [ሀ]እውቀቶችን ማፍሰሱን ከሚያቆም፣ ሰው ደካማ ክንዶቹን ዘርግቶ የሚዞሪን ወንዝ ከተወሰነለት መንገዱ ያቆም ዘንድ ወይም ተቃራኒው እንዲዞር ለማድረግ ቢሞክር ይቀለዋል።

፴፬ እነሆ፣ ብዙዎች [ሀ]ተጠርተዋል፣ ነገር ግን [ለ]የተመረጡት ጥቂቶች ናቸው። እና ያልተመረጡትስ ለምንድን ነው?

፴፭ ምክንያቱም ልባቸውን [ሀ]በአለም ነገሮች ላይ ስለሚያደርጉ እና በሰዎች [ለ]ይሞገሱ ዘንድ ስለሚነሳሱ፣ ይህን አንድ ትምህርት አይማሩም—

፴፮ የክህነት [ሀ]መብቶች እና የሰማይ ሀይላት የማይነጣጠሉ ናቸው፣ እና የሰማይ [ለ]ሀይላት [ሐ]በፅድቅ መሰረታዊ መርሆች የሚካሄድ ካልሆነ በስተቀር ሊቆጣጠሯቸው እና ሊጠቀሙባቸውም ዘንድ አይቻልም።

፴፯ ለእኛ ሊሰጡን መቻሉ እውነት ነው፤ ነገር ግን [ሀ]ኃጢአታችንን [ለ]ለመሸፈን፣ ወይም [ሐ]ኩራታችንን እንዲሁም ከንቱ ፍላጎታችንን ለማርካት፣ ወይም በማንኛውም የፅድቅ ባልሆነ መንገድ በሰዎች ልጆች ነፍሳት ላይ ቁጥጥር ወይም የበላይነትን ወይም ግዴታን ለማድረግ ብንሞክር፣ እነሆ፣ ሰማያት ራሳቸውን [መ]ያገልላሉ፤ የጌታም መንፈስም ያዝናል፤ እና ይህ ሲወሰድም፣ የሰው ክህነት ወይም ስልጣን ፍጻሜ ይሆናል።

፴፰ እነሆ፣ ይህን ከማወቁም በፊት፣ የመውጊያውን ብረት [ሀ]ይቃወም ዘንድ፣ ቅዱሳንን [ለ]ያሳድድ፣ እና ከእግዚአብሔርም ጋር ይዋጋ ዘንድ ብቻውን ይተዋል።

፴፱ ወዲያውኑም ትንሽ ስልጣን ያገኙ ሲመስላቸው፣ ፈጥነው ጻድቅ ባልሆነ ሁኔታ በበላይነት ስልጣናቸውን ሲጠቀሙበት፣ ይህም የሰው ሁሉ [ሀ]ተፈጥሮ እና ባህርይ መሆኑንም ከአሳዛኝ አጋጣሚዎች ተምረናል።

፵ ስለዚህ፣ ብዙዎች ተጠርተዋል፣ ግን የተመረጡት ጥቂቶች ናቸው።

፵፩ [ሀ]በማሳመን፣ [ለ]በትእግስት፣ በደግነት፣ እና በትህትና፣ እና ግብዝነት በሌ

፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፴፪።
፴ ሀ ኢዮብ ፳፮፥፯–፲፬፤
መዝ. ፻፬፥፭–፱፤
የሐዋ. ፲፯፥፳፮።
፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ዘመን።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
ለ ዘዳግ. ፲፥፲፯።
ሐ ቅ.መ.መ. እረፍት።
መ ቅ.መ.መ. የሰማይ ሸንጎ።
፴፫ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፱።
ቅ.መ.መ. እውቀት።
፴፬ ሀ ማቴ. ፳፥፲፮፤ ፳፪፥፩–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፺፭፥፭–፮።
ቅ.መ.መ. ጥሪ፣ በእግዚአብሔር መጠራት፣ የተጠራበት።
ለ ቅ.መ.መ. መምረጥ፣ መረጠ፣ የተመረጠ (ግስ)።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. አለማዊነት።
ለ ማቴ. ፮፥፪፤ ፪ ኔፊ ፳፮፥፳፱።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ስልጣን፤ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. ሀይል።
ሐ ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ኃጢያት።
ለ ምሳ. ፳፰፥፲፫።
ሐ ቅ.መ.መ. ኩራት።
መ ት. እና ቃ. ፩፥፴፫።
፴፰ ሀ የሐዋ. ፱፥፭።
ለ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ፍጥረታዊ ሰው።
፵፩ ሀ ፩ ጴጥ. ፭፥፩–፫።
ለ ፪ ቆሮ. ፮፥፬–፮።

ለው ፍቅር ካልሆነ በስተቀር፣ ምንም ሀይል ወይም ተጽዕኖ በክህነት ስልጣን ዘዴ ሊደገፍ አይቻልም ወይም አይገባውም፤

፵፪ ይህም በርህራሄ፣ እና [ሀ]ያለግብዝነትና [ለ]ያለተንኮል መንፈስን በታላቅ በሚያሳድግ ንጹህ እውቀት ብቻ ነው ሊደገፍ የሚችለው፤

፵፫ መንፈስ ቅዱስ በሚነሳሳበት በትክክለኛው ጊዜ በሀያልነት [ሀ]በመቆጣት፤ ከዚያም በኋላ እንደጠላት እንዳያይህ፣ ለተቆጣኸውም ተጨማሪ [ለ]ፍቅር አሳይ፤

፵፬ በእዚህም እምነትህ ከሞት ሀይል በላይ እንደሆነ ይወቅ።

፵፭ አንጀትህም ለሁሉም ሰው እና ለእምነት ቤተ ሰዎች በልግስና ይሞላ፣ እና [ሀ]ምግባረ በጎነትም ሳያቋርጥ [ለ]አስተሳሰብህን ያሳምር፤ ከዚያም ልበ ሙሉነትህ በእግዚአብሔር ፊት እየጠነከረ ይሄዳል፤ እና የክህነት ትምህርትም በነፍስህ ላይ እንደ ሰማይ [ሐ]ጠል ትንጠባጠብልሀለች።

፵፮ [ሀ]መንፈስ ቅዱስም የዘወትር ባልንጀራህ ይሆናል፣ እና በትርህም የማይቀየር የፅድቅ እና የእውነት በትር ይሆናል፤ እና [ለ]ስልጣንህም ዘለአለማዊ ስልጣን ይሆናል፣ እና በማያስገድድ ዘዴም ይህም ወደ አንተ ለዘለአለም ይፈሳል።

ክፍል ፻፳፪

በመጋቢት ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) በልብርቲ እስር ቤት፣ ሚዙሪ ውስጥ ታስሮ እያለ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የመጣ የጌታ ቃል። ይህ ክፍል በመጋቢት ፳፣ ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) ለቤተክርስቲያኗ ከተጻፈ ደብዳቤ ውስጥ የተወሰደ ነው (ክፍል ፻፳፩ ርዕስን ተመልከቱ)።

፩–፬፣ የምድር ዳር ሁሉ ስለጆሴፍ ስሚዝ ስም ይጠይቃሉ፤ ፭–፯፣ እርሱ ያጋጠሙት የአደጋ ሁኔታዎች እና ስቃዮች ልምድን ይሰጡታል እና ለእርሱም ጥቅም ይሆናሉ፤ ፰–፱፣ የሰው ልጅ ከሁሉም በታች ወርዷል።

፩ የምድር ዳርቻዎች ሁሉ [ሀ]ስለስምህ ይጠይቃሉ፣ እና ሞኞችም በአንተ ይሣለቁብሀል፣ እና ገሀነምም በአንተ ላይ ይቆጣል፤

፪ ንጹህ ልብ ያለው እና ጥበበኛው፣ እና ልኡሉ፣ እና ምግባረ መልካሙ ከእጆችህ [ሀ]ምክርን፣ እና ስልጣንን፣ እና በረከትን ዘወትር ይሻል።

፫ እና ህዝብህም በከዳተኛ ምስክር ምክንያት ከአንተ ላይ ድጋፉቸውን አይቀይሩም።

፬ እና ምንም እንኳን የእነርሱ ተጽዕኖ ወደ ችግርና ወደ አጥሮች እና ግድግዳዎች ቢጥልህም፣ ትከብራለህ፤ እና ይህም ለጥቂት [ሀ]ጊዜ እና በፅድቅህም ምክንያት ድምፅህም በጠላቶችህ መካከል ከአደገኛ [ለ]አምበሳ በላይ የሚያስፈራ ይሆናል፤ እናም አምላክህም በአጠገብህ ለዘለአለም ይቆማል።

፭ በፈተናዎች እንድታልፍ ከተጠራህ፤ በሀሰተኛ ወንድሞች መካከል በአደጋ ሁኔታዎች ውስጥ ካለህ፤ በዘራፊዎች መካከል በአደጋ ሁኔታዎች ውስጥም ብትሆን፤ በምድር ወይም በባህር በአደጋ ሁኔታዎች ውስጥ ብትሆን፤

፵፪ ሀ ያዕ. ፫፥፲፯።
ለ ቅ.መ.መ. ተንኮል።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
ለ ቅ.መ.መ. ልግስና፤ ፍቅር።
፵፭ ሀ ቅ.መ.መ. በጎነት።
ለ ቅ.መ.መ. ሀሳቦች።
ሐ ዘዳግ. ፴፪፥፩–፪፤ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፱።
፵፮ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
ለ ዳን. ፯፥፲፫–፲፬።
፻፳፪ ፩ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፫።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፯–፰።
ለ ፫ ኔፊ ፳፥፲፮–፳፩፤ ፳፩፥፲፪።

፮ በሀሰት ክሶች ብትከሰስ፤ ጠላቶችህም ቢያጠቁህ፤ ከአባትህና እናትህ እና ከወንድሞችህና እህቶችህ ህብረት ነጥለው ቢወሰዱህ፤ እና በተመዘዘ ጎራዴ ጠላቶችህ ከሚስትህ እቅፍ እና የስድስት አመት እድሜ ያለው ልጅህም፣ ልብስህንም አጥብቆ በመያዝ፣ አባዬ አባዬ ለምን ከእኛ ጋር ለመቆየት አትችልም? አባዬ ሆይ፣ ሰዎቹ ምን ሊያደርጉብህ ነው? ብሎ ከሚል ከታላቅ ልጅህ ነጥለው ቢወስዱህ፤ እና ከዚያም እርሱ ከአንተ በጎራዴ ተገፍቶ፣ እና አንተም ወደ እስር ቤት ብትጎተት፣ እና ጠላቶችህም በዙሪያህ ለጥቦው ደም እንደሚያንግብቡ [ሀ]ተኩላ ቢሆኑም፤

፯ እና ወደ ጉድጓድ ወይም በገዳዮች እጅም ብትጣል፣ እና የሞት ፍርድ ቢተላለፍብህ፤ ወደ [ሀ]ጥልቁም ብትጣል፤ ወደፊት እና ወደኋላ የሚገፋው ውሀ በአንተ ላይ ቢያድም፤ አደገኛው ነፋሶስም ጠላትህ ቢሆን፤ ሰማያትም ጭለማን ቢሰበስቡ፣ እና ንጥረ-ነገሮች ሁሉ መንገድህን ለማሰናከል ቢጣመሩ፤ እና ከሁሉም በላይ፣ [ለ]የሲኦል መንጋጋም አፍዋን በሰፊው ብትከፍትብህ፣ ልጄ ሆይ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለአንተ [ሐ]ልምድ እንደሚሰጡህ እና ለአንተ ጥቅም እንደሆኑም እወቅ።

፰ [ሀ]የሰው ልጅ ከሁሉም በታች [ለ]ወርዷል። አንተ ከእርሱ ታላቅ ነህ?

፱ ስለዚህ፣ ባለህበት መንገድ ቆይ፣ እና ክህነትም ከአንተ ጋር [ሀ]ይቆያል፤ [ለ]ገደቦቻቸው ተወስነዋል፣ ሊያልፉትም አይችሉም። [ሐ]ቀናትህ የታወቁ ናቸው እና አመታትህም ከዚህ በታች አይቀነሱም፤ ስለዚህ፣ ሰው ማድረግ የሚችለውን [መ]አትፍራ፣ እግዚአብሔር ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ከአንተ ጋር ነውና።

ክፍል ፻፳፫

በልብርቲ እስር ቤት ውስጥ እንደታሰረ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ቅዱሳን ከሚያሳድዷቸው ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት እንዲታወቅ የጻፈው። ይህ ክፍል በመጋቢት ፳፣ ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.) ለቤተክርስቲያኗ ከተጻፈ ደብዳቤ ውስጥ የተወሰደ ነው (ክፍል ፻፳፩ ርዕስን ተመልከቱ)።

፩–፮፣ ቅዱሳን የተሰቃዩበትንና የተሰደዱበትን ታሪካቸውን ሰብስበው ያትሙ፤ ፯–፲፣ የሀሰት እምነትን የመሰረተው መንፈስ ቅዱሳንን እንዲሰደዱም ያደርጋል፤ ፲፩–፲፯፣ ከሁሉም እምነቶች መካከል ብዙዎች እውነትን ይቀበላሉ።

፩ ደግሞም፣ ሁሉም ቅዱሳን በዚህ ስቴት ህዝብ የተሰቃዩባቸውን እና የተጎሳቀሉባቸውን ተጨባጭ ነገሮች እውቀት ሁሉ የመሰብሰባቸውን ትክክለኛነት እንድታስቡበት ሀሳብ እናቀርባለን፤

፪ ደግሞም ንብረቶችን ሁሉ እና የደረሰባቸውን የጉዳት መጠን፣ የስም እና የግለሰብ ጉዳቶች እና የእውነተኛ ንብረቶች ጉዳት፤

፫ ደግሞም፣ እስካገኟቸው እና ለይተውም እስከሚወጧቸው ድረስ፣ በዚህ ጭቆናቸው

፮ሀ ሉቃ. ፲፥፫።
፯ሀ ዮና. ፪፥፫–፯።
ለ ፪ ሳሙ. ፳፪፥፭–፯፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፲፭–፲፮።
ሐ ፪ ቆሮ. ፬፥፲፯፤
ዕብ. ፲፪፥፲–፲፩፤
፪ ኔፊ ፪፥፲፩።
፰ሀ ቅ.መ.መ. የሰው ልጅ።
ለ ዕብ. ፪፥፱፣ ፲፯–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፯፤
፹፰፥፮።
፱ሀ ት. እና ቃ. ፺፥፫።
ለ የሐዋ. ፲፯፥፳፮።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፳፭።
መ ነህ. ፬፥፲፬፤
መዝ. ፶፮፥፬፤ ፻፲፰፥፮፤
ምሳ. ፫፥፭–፮፤
ኢሳ. ፶፩፥፯፤
ሉቃ. ፲፪፥፬–፭፤
፪ ኔፊ ፰፥፯፤
ት. እና ቃ. ፫፥፯፤ ፺፰፥፲፬።

ወቅት ተሳታፊነት የነበሩ ግለሰቦችን ሁሉ ስም እናቀርባለን።

፬ እና ምናልባት እነዚህን ነገሮች እንዲያገኙ፣ ደግሞም የምስክር ቃል እና የመሀላ ቃል እንዲወሰዱ፤ እና ደግሞም ስምን ለማጥፋት የተሰራጩትን ህትመቶችን ለመሰብሰብ ኮሚቴን መመደብ ይቻላል፤

፭ እና በመጽሄቶች ውስጥ፣ እና በኢንሳይክሎፒዲያዎችም ውስጥ ሁሉ፣ እና የታተሙትን እና የሚጻፉትን ስም የሚያጠፉ ታሪኮችን ሁሉ፣ እና የጻፉትንም ሰዎች ስም ለመሰብሰብ፣ እና በእነዚህ ህዝብ ላይ የደረሱትን በዲያብሎስ በመነሳሳት የተደረጉትን ክፋቶች እና ተንኮል በግድ ህይወት የሚያጠፉትንም በሙሉ በማቅረብ—

፮ ለአለም ሁሉ እንድናትመው ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን [ሀ]ከተሰወረበት ስፍራ የሚጠራውን ቃል ኪዳን በሙሉ እና ፈጽመንም ለመውሰድ ከመቻላችን በፊት፣ እንደመጨረሻ ጥረት በሰማይ አባታችን እንደታዘዝነው፣ ለመንግስት መሪዎች ከጨለመ እና ከረከሰ አመለካከታቸው ጋር እንድናቀርባቸው፤ ደግሞም ሀያሉን ክንዱን ከመላኩ በፊት ህዝብ ሁሉ ምንም ምክንያት እንዳይኖራቸው እነዚህን ነገሮች ለመሰብሰብ ኮሚቴን ለመመደብ ይቻላል።

፯ ለእግዚአብሔር፣ በፊቱ አብረውንም ለሚቆሙ መላእክት፣ እና ደግሞም ለራሳችን፣ እና ሀሰትን የወረሱትን የአባቶችን እምነት በልጆቻቸው ልብ ላይ አጥብቆ ባሰረው እና አለምን ግራ በመጋባት በሞላው፣ እና እየበረታም ባለው፣ እና የርኩሰት ሁሉ ዋና ምንጭ በሆነው፣ እና [ሀ]ምድርም ሁሉ በኃጢአቱ ሸክም በሚቃስቱበት መንፈስ በተደገፉት በህይወትን በሚያጠፉ፣ በጨካኝ፣ እና በሚያሰቃዩ የኩነኔ ሀይላት ምክንያት በጥልቅ ሀዘን፣ በሀዘን፣ እና በሀሳብ ለተሰቃዩት ለሚስቶቻችን እና ልጆቻችን ባለእዳ መሆናችን አስፈላጊ ሀላፊነታችን ነው።

፰ ይህም የብረት [ሀ]ቀንበር ነው፣ ይህም ጠንካራ ማስሪያ ነው፤ እነዚህም የሲኦል የእጅ ካቴናዎች፣ ሰንሰለቶችና የእግር ብረቶች፣ እና የእግር ብረት ሰንሰለቶች ናቸው።

፱ ስለዚህ ይህም ለሚስቶቻችን እና ለልጆቻችን ብቻ ሳይሆን ለባልቴቶች እና አባት ለሌላቸው፣ ባሎቻቸው እና አባቶቻቸው ከብረት እጆች በታች [ሀ]ለተገደሉባቸው ያለብን አስፈላጊ የሀላፊነት እዳ ነው፤

፲ እነዚህ ጥቁር እና የሚያጨልሙ ስራዎች ሲኦልም እንድትንቀጥቀጥ፣ እና በድንጋጤም እንድትዋጥ ደብዝዛም እንድትቆም፣ የዲያብሎስ እጆችም እንዲንቀጠቀጡ ለማድረግ ብቁ ናቸው።

፲፩ ደግሞም፣ ይህ ለሚመጡት ትውልዶች ሁሉ፣ እና ልባቸው ንጹህ ለሆኑት ሁሉ ያለብን አስፈላጊ የሀላፊነት እዳ ነው—

፲፪ በሁሉም ሀይማኖቶች፣ ቡድኖች፣ እና በሀይማኖት ክፍሎች ሁሉ መካከል ሰዎችን ለማታለል በሚደበቁበት የብልጠት ማጭበርበሪያዎች ምክንያት አይኖቻቸው [ሀ]የታወሩ፣ እና የት እንደሚያገኙትም [ለ]ባለማወቃቸው ምክንያት እውነትን እንዳያገኙ የተደረጉ ብዙዎችም አሉ—

፲፫ ስለዚህ፣ ባወቅነው መጠን በጨለማ [ሀ]የተሰወሩትን ነገሮች ደግሞ ወደ ብርሀን ለማውጣት ህይወታችንን እናባክን እና ዋጋም እናሳጣ፤ እና እነዚህም በእውነት ከሰማይ የተገለጡ ናቸው—

፲፬ እነዚህም በትጋት ይከናወኑ።

፲፭ ማንም ሰው እነዚህን እንደትንሽ ነገሮች አይቁጠራቸው፤ ቅዱሳኑን በሚመለከት፣ በእነዚህ ላይ የሚመኩ፣ በወደፊት የሚኖሩ ብዙዎች አሉና።

፲፮ ወንድሞች፣ በጣም ግዙፍ መርከብ በማእበል ወቅት በደህንነት በነፋሱ እና በማ

፻፳፫ ፮ሀ ት. እና ቃ. ፻፩፥፹፱፤
፻፳፩፥፩፣ ፬።
፯ሀ ሙሴ ፯፥፵፰–፵፱።
፰ሀ ቅ.መ.መ. ቀንበር።

፱ሀ ት. እና ቃ. ፺፰፥፲፫፤
፻፳፬፥፶፬።
፲፪ሀ ቈላ. ፪፥፰፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፭።

ለ ፩ ኔፊ ፰፥፳፩–፳፫።
፲፫ሀ ፩ ቆሮ. ፬፥፭።

እበሉ መካከል ይሄድ ዘንድ በጣም ጥቂት በሆነ የመርከብ መሪ [ሀ]ጥቅም እንደሚያገኝ ታውቃላችሁ።

፲፯ ስለዚህ፣ ውድ ወንድሞች፣ በሀይላችን ያሉትን ነገሮች ሁሉ [ሀ]በደስታ እናድርግ፤ ከዚያም በእርግጠኝነት የእግዚአብሔር የሚያደርገውን [ለ]ማዳን ለማየት እንቁም እና የክንዱንም መገለጥ እንጠባበቅ።

ክፍል ፻፳፬

በጥር ፲፱፣ ፲፰፻፵፩ (እ.አ.አ.) በናቩ ኢሊኖይ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። በእነርሱ ላይ በመንግስት ባለስልጣናት በተደረጉባቸው ተጨማሪ ስደቶችና ህገ ወጥ ስራዎች ምክንያት፣ ቅዱሳን ሚዙሪን ለቅቀው ለመውጣት ተገድደው ነበር። በጥቅምት ፳፯፣ ፲፰፻፴፰ (እ.አ.አ.) በሚዙሪ አስተዳዳሪ ሊበርን ደብሊው ቧግስ በተሰጠው ዘር የማጥፋት ትእዛዝ ምንም ሌላ ምርጫ አልሰጣቸውም። በ፲፰፻፴፱ (እ.አ.አ.)፣ ይህ ራዕይ ሲሰጥ፣ በቀድሞ ኮመርስ መንደር፣ ኢሊኖይ ስፍራ ላይ የተመሰረተው የናቩ ከተማ በቅዱሳኑ ተገንብቶ ነበር፣ እና በዚህም የቤተክርስቲያኗ ጠቅላይ መምሪያ ተመስርቶ ነበር።

፩–፲፬፣ ጆሴፍ ስሚዝ ለዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዘደንት፣ ለአስተዳዳሪዎች፣ እና ለሁሉም ሀገሮች መሪዎች ወንጌልን እንዲያውጅ ታዘዘ፤ ፲፭–፳፩፣ በህይወት ከሚኖሩትና ከሞቱት መካከል ሀይረም ስሚዝ፣ ዴቪድ ደብሊው ፓትተን፣ ጆሴፍ ስሚዝ ቀዳማዊ፣ እና ሌሎች ለቅንነታቸው እና ለምግባረ መልካምነታቸው ተባርከዋል፤ ፳፪–፳፰፣ ቅዱሳን እንግዳዎችን የሚቀበሉበትን ቤት እና ቤተመቅደስን እንዲገነቡ ታዝዘዋል፣ ፳፱–፴፮፣ የሙታን ጥምቀት በቤተመቅደስ ውስጥ ይፈጸም፤ ፴፯–፵፬፣ የጌታ ህዝብ ለቅዱስ ስርዓቶች ማከናወኛ ዘወትር ቤተመቅደስን ይገነባሉ፤ ፵፭–፶፭፣ ቅዱሳን በጠላቶቻቸው ክፋት ምክንያት በጃክሰን የግዛት ክፍል ቤተመቅደስን ባለመገንባታቸው ይሁንታን አግኝተዋል፤ ፶፮–፹፫፣ ለናቩ ቤት መገንቢያ መመሪያዎች ተሰጥተዋል፤ ፹፬–፺፮፣ ሀይረም ስሚዝ ፔትሪያርክ እንዲሆን፣ ቁልፎችን እንዲቀበል፣ እና በኦሊቨር ካውድሪ ስፍራ እንዲቆም ተጠርቷል፤ ፺፯–፻፳፪፣ ውልያም ሏው እና ሌሎች በአገልግሎታቸው ተመክረዋል፤ ፻፳፫–፻፵፭፣ አጠቃላይ እና የአካባቢ ባለስልጣናት ከሀላፊነታቸው እና ተባባሪ ግንኙነት ካላቸው ቡድኖች ጋር ተጠርተዋል።

፩ በእውነት፣ ጌታ ለአንተ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ፣ እንዲህ ይላል፣ አንተ ባደረካቸው መስዋዕት እና እውቅናዎች በተቀበልክባቸው ተደስቼአለሁ፤ በምድር [ሀ]ደካማ ነገሮች ጥበቤን አሳይ ዘንድ፣ ለዚህም ምክንያት ነው ያስነሳሁህ።

፪ ጸሎቶችህ በፊቴ ተቀብዬአቸዋለሁ፤ እና ለእነዚህም መልስ በመስጠት እንዲህ እልሀለሁ፣ አሁንም ወዲያው ወንጌሌን፣ እና በቤተመንግስት ምሳሌነት በመንጠር የምትብረቀረቀው የፅዮን የማዕዘን ራስ ድንጋይ እንድትሆን ስለተከልኳት [ሀ]ካስማ በቅድስና እንድታውጅ ተጠርተሀል።

፫ ይህም እወጃ ለአለም [ሀ]ነገስታት ሁሉ፣

፲፮ ሀ ያዕ. ፫፥፬፤
አልማ ፴፯፥፮–፯፤
ት. እና ቃ. ፷፬፥፴፫።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፶፱፥፲፭።
ለ ዘፀአ. ፲፬፥፲፫።
፻፳፬ ፩ ሀ ፩ ቆሮ. ፩፥፳፮–፳፰፤
ት. እና ቃ. ፩፥፲፱፤
፴፭፥፲፫።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ካስማ።
፫ ሀ መዝ. ፻፲፱፥፵፮፤
ማቴ. ፲፥፲፰፤
ት. እና ቃ. ፩፥፳፫።

በዚህም አራት ማዕዘናት፣ ለተከበረው እንደ ፕሬዘደንት ለተመረጠው፣ እና ለተከበሩት ለምትኖርበት አገር እና በውጪ ለተበተኑት የምድር አገሮች አስተዳዳሪዎች ሁሉ ይደረግ።

፬ ይህንም [ሀ]በትህትና መንፈስ እና፣ ይህን በምትፅፍበት ጊዜ በውስጥህ በሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ይጻፍ፤

፭ ስለእነዚያ ነገስታት እና ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ወደፊት በሚመጣው ጊዜ ስለሚደርስባቸው፣ ያለኝን ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ታውቅ ዘንድ ይሰጥሀል።

፮ እነሆ፣ የፅዮንን ብርሀን እና ክብር እንዲመለከቱ ልጠራቸው ነውና፣ የመሞገሷ ዘመንም ቀርቧልና።

፯ ስለዚህ በጎላ ድምፅ እወጃ፣ እና በምስክርህ ጥራቸው፣ እና አትፍራቸው፣ ደግሞም ያለምክንያት ይተዉ ዘንድ፣ እነርሱ እንደ [ሀ]ሣር ናቸው እና ክብራቸውም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ይረግፋልና—

፰ እና አገልጋዮቼን እና የገለጥኩላቸውን ምስክሬን ቢቃወሙ፣ ጥርስ [ሀ]ማፋጨት በሚኖርበት የክፉዎችንም እድል ፈንታ ከግብዞች ጋር በማደርግበት ጊዜ፣ የፊቴንም መጋረጃ ሳወልቅ፣ በጉብኝት ቀን ይጎበኛሉ።

፱ ደግሞም፣ ብዙዎቹንም ለእናንተ ጥቅም፣ ወደ እውነትም [ሀ]ብርሀን እና አህዛብም ወደ ዘለአለማዊነት ወይም ወደ ፅዮን ወደ ዘለአለማዊ ክብር ይመጡ ዘንድ በአይኖቻቸውም ፊት ጸጋን ታገኙ ዘንድ፣ እጎበኛቸዋለሁ እናም ልቦቻቸውንም አለሰልሳለሁ።

፲ በማታስቡበት [ሀ]ሰዓት፣ የጉብኝቴ ቀን ፈጥኖ ይመጣል፤ እና የህዝቤ ደህንነት እና ከእነርሱም የሚቀሩት መሸሸጊያቸው የት ይሆናል?

፲፩ ተነሱ፣ የምድር ነገስታት ሆይ! ከወርቃችሁና ከብራችሁ ጋር ህዝቤን ወደ መርዳት፣ ወደፅዮን ሴት ልጆች ቤት ኑ።

፲፪ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ሮበርት ቢ ቶምሰን ይህን እወጃ ለመጻፍ ይርዳህ፣ እና ከአንተ ጋር ይሁን፣ በእርሱ ተደስቻለሁና፤

፲፫ ስለዚህ፣ ምክርህን ያድምጥ፣ እና በሚበዙ በረከቶች እባርከዋለሁ፤ ከዚህ ጀምሮ በሁሉም ነገሮች ታማኝ እና እውነተኛ ይሁን፣ እና በአይኖቼም ታላቅ ይሆናል።

፲፬ ነገር ግን በእጆቹ ስለምጠብቅበት [ሀ]መጋቢነትም ያስታውስ።

፲፭ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ [ሀ]ሀይረም ስሚዝ የተባረከ ነው፤ እኔ ጌታ በልቡ [ለ]ቅንነት፣ እና በፊቴ ትክክል የሆነውን ስለሚወድ እወደዋለሁና፣ ይላል ጌታ።

፲፮ እንደገናም፣ አገልጋዬ ጆን ሲ በነት፣ ቃሌን ለነገስታት እና ለምድር ህዝቦች በመላክ ስራህ ይርዳህ፤ እንዲሁም ከአንተ ከአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝም ጋር በስቃይህ ሰአት ከጎንህ ይቁም እና [ሀ]ምክርንም የሚቀበል ቢሆን ዋጋው አይወድቅም።

፲፯ እና ፍቅሩም ታላቅ ይሆናልና፣ ይህንም ቢያደርግ የእኔ ይሆናልና፣ ይላል ጌታ። ቢቀጥልም የምቀበለውን፣ የሰራውን ስራ ተመልክቻለሁ፣ እና በበረከቶችን እና ታላቅን የክብር አክሊል እጭንለታለሁ።

፲፰ ደግሞም፣ አገልጋዬ ላይመን ዋይት በፅዮን በትሁትነት መንፈስ፣ በአለም ፊት እየመሰከረልኝ በመስበክ እንዲቀጥል ፍቃዴ እንደሆነ ይህን እልሀለሁ፤ እና [ሀ]በንስርም ክንፍ ላይ እንደሚሆንም እሸከመዋለሁ፤ እና ግርማ እና ክብርንም ለእራሱ እና ለስሜ ያገኛል።

፬ ሀ ቅ.መ.መ. ገር፣ ገርነት።
፯ ሀ መዝ. ፻፫፥፲፭–፲፯፤
ኢሳ. ፵፥፮–፰፤
፩ ጴጥ. ፩፥፳፬–፳፭።
፰ ሀ ማቴ. ፰፥፲፪፤ አልማ ፵፥፲፫፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥፺፩፤
፻፲፪፥፳፬።
፱ ሀ ኢሳ. ፰፥፩–፬።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
፲ ሀ ማቴ. ፳፬፥፵፬፤
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፵፰።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣
መጋቢነት።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሀይረም።
ለ ቅ.መ.መ. ቅንነት።
፲፮ ሀ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፲፰ ሀ ዘፀአ. ፲፱፥፬፤ ኢሳ. ፵፥፴፩።

፲፱ ስራውንም ሲጨርስ፣ በዚህ ጊዜ ከእኔ ጋር እንዳለው እንደ አገልጋዬ [ሀ]ዴቪድ ፓትተን እና ደግሞም እንደ አገልጋዬ [ለ]ኤድዋርድ ፓርትሪጅ፣ እና ደግሞም፣ እርሱም የእኔ ነውና፣ በአብርሐም [ሐ]ጋር ቀኝ እንደተቀመጠው፣ የተባረከው እና በቅድስና ያረጀው አገልጋዬ [መ]ጆሴፍ ስሚዝ፣ ቀዳማዊ ወደ እኔም ዘንድ እቀበለዋለሁ።

፳ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ አገልጋዬ ጆርጅ ሚለር [ሀ]አታላይ አይደለም፤ በልቡ ቅንነትም ሊታመን ይቻላል፤ እና ለእኔ፣ ለጌታ፣ ለምስክሬ ባለው ፍቅር ምክንያትም እወደዋለሁ።

፳፩ ስለዚህ እልሀለሁ፣ እንደ አገልጋዬ ኤድዋርድ ፓርትሪጅ፣ የቤቴን ቅድስና ይቀበል ዘንድ፣ በድሀ ህዝቤ ራዕይ ላይ በረከቶችን ይሰጥ ዘንድ [ሀ]የኤጲስ ቆጶስ አመራር ሀላፊነትንም በራሱ ላይ አትምለታለሁ፣ ይላል ጌታ። አገልጋዬ ጆርጅን ማንም ሰው አይጥላው፣ እኔን ያከብረኛልና።

፳፪ አገልጋዬ ጆርጅ፣ እና አገልጋዬ ላይመን፣ እና አገልጋዬ ጆን ስናይደር፣ እና ሌሎችም አገልጋዬ ጆሴፍ እንደሚያሳያቸው አይነት፣ ደግሞም ለእነርሱ በሚያሳያቸው ስፍራ ለስሜ [ሀ]ቤት ይገንቡ።

፳፫ እና ይህም ለማረፊያ ቤት፣ እንግዶች ከሩቅ ስፍራ መጥተው የሚያርፉበት ይሁን፤ ስለዚህ የደከመው [ሀ]ተጓዥ የጌታን ቃል፣ እና ለፅዮን የመደብኩትን [ለ]የማዕዘን ራስ ድንጋይ ሲያሰላስል ጤና እና ደህንነትን ያገኝ ዘንድ መልካም፣ ለተቀባይነትም ያለው ብቁ ቤት ይሁን።

፳፬ ይህ ቤት በስሜ ቢገነባ እና የተመደበበት አስተዳዳሪ ምንም የሚያረክሰውን ነገር እንዲገባበት እስካልፈቀደ ድረስ የጤና መኖሪያ ይሆናል። ቅዱስ ይሆናል፣ አለዚያ ጌታ አምላካችሁ አይኖርበትም።

፳፭ ደግሞም፣ እውነት እልሀለሁ፣ ቅዱሳኔ ከእሩቅ ስፍራዎች ይምጡ።

፳፮ እና ፈጣን መልእክተኞች ላኩ፣ አዎን፣ ምርጥ መልእክተኞችንም፣ እና እንዲህም በሏቸው፥ ከሁሉም ወርቆቻችሁ እና ከብሮቻችሁ፣ እና ከውድ ድንጋዮቻችሁ፣ እና ከሁሉም ጥንታዊ ንብረታችሁ ጋር ኑ፤ እና እውቀት ካላቸውም ከጥንቶቹ ጋር የሚመጡትም ይምጡ፣ እና የባርሰነቱን ዛፍ፣ እና የጥዱን ዛፍ፣ እና የአስታውን ዛፍ ከምድር ውድ ዛፎች ሁሉ ጋር አምጡ፤

፳፯ እና ከብረት፣ ከመዳብ፣ እና ከነሀስ፣ እና ከዚንክ፣ እና ከምድር ውድ ነገሮች ሁሉ ጋር፤ እና ከሁሉም በላይ ልዑል [ሀ]እንዲኖርበት፣ በስሜም [ለ]ቤት ስሩ።

፳፰ ከእናንተ የጠፋውን ወይም የወሰደውን፣ እንዲሁም የክህነት ሙላትን፣ [ሀ]ደግሞ የሚመልስበት እና የሚመጣበት በምድር ላይ ምንም ስፍራ የለምና።

፳፱ እነርሱ፣ ቅዱሳኔ፣ ለሙታን [ሀ]ይጠመቁ ዘንድ፣ በምድርም ላይ [ለ]የማጥመቂያ ገንዳ የለምና—

፴ ይህ ስነ ስርዓት በቤቴ ውስጥ ተገቢ ነውና፣ እና ቤት ለእኔ ለመገንባት በማትችሉበት በድህነታችሁ ቀናቶች በስተቀር፣ እኔ ልቀበልበት አልችልም።

፴፩ ነገር ግን ቅዱሳኔ ሁሉ በስሜ [ሀ]ቤት እንድትገነቡ አዛችኋለሁ፤ እና ለእኔ ቤት የምትገነቡበት ብቁ ጊዜም እሰጣችኋለሁ፤ እና በዚህም ጊዜ ጥምቀቶቻችሁ በእኔ ተቀባይ ይሆናሉ።

፲፱ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፴።
ቅ.መ.መ. ፓተን፣ ዴቪድ ደብሊው።
ለ ቅ.መ.መ. ፓርትሪጅ፣ ኤድዋርድ።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፴፯፥፭።
መ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ቀዳማዊ።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ተንኮል።
፳፩ ሀ ት. እና ቃ. ፵፩፥፱።
ቅ.መ.መ. ኤጲስ ቆጶስ።
፳፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፶፮–፷።
፳፫ ሀ ዘዳግ. ፴፩፥፲፪፤
ማቴ. ፳፭፥፴፭፣ ፴፰።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፪።
፳፯ ሀ ዘፀአ. ፳፭፥፰፤
ት. እና ቃ. ፺፯፥፲፭–፲፯።
ለ ት. እና ቃ. ፻፱፥፭።
ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣
የጌታ ቤት።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. የወንጌል
ዳግም መመለስ።
፳፱ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፱፤
ት. እና ቃ. ፻፳፯፥፮፤
፻፴፰፥፴፫።
ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት፤
ጥምቀት፣ መጥመቅ—
ለሙታን መጠመቅ።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፫።
፴፩ ሀ ት. እና ቃ. ፺፯፥፲።

፴፪ ነገር ግን፣ እነሆ፣ ከዚህ ምደባ በኋላ ለሙታን የምታደርጉት ጥምቀት በእኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም፤ እና እነዚህንም ነገሮች በተመደበላቸው ጊዜ መጨረሻ ላይ ባታደጉት ከሙታኖቻችሁ ጋር እንደ ቤተ ክርስቲያን ትወገዳላችሁ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፴፫ እውነት እላችኋለሁ፣ ለሙታን የጥምቀት ስርዓት የሚገባበት፣ እና አለም ከመመስረቷ በፊት ጀምሮ ለዚህም አላማ የዋለውን ቤቴን ለመገንባት ብቁ ጊዜ ካገኛችሁ በኋላ፣ ለሙታኖቻችሁ የምትጠመቁት በእኔ ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም።

፴፬ ክብር እና ግርማ ትቀበሉ ዘንድ፣ ለቅዱስ ክህነት ስልጣን [ሀ]ቁልፎች የሚሾሙት በዚህም ውስጥ ነውና።

፴፭ ከዚህ ጊዜም በኋላ፣ በመካከላችሁ በየአካማቢው የተበተኑት የሙታን ጥምቀቶቻችሁ በእኔ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው አይደሉም፣ ይላል ጌታ።

፴፮ በፅዮን እና ካስማዎቼ፣ እና በኢየሩሳሌም፣ [ሀ]ለመሸሸጊያነት በመደብኳቸው በእነዚያ ስፍራዎች ውስጥም ለሙታኖቻችሁ ጥምቀት ስፍራ እንዲሆኑ ተመድበዋል።

፴፯ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በስሜ በተሰራው ቤት ውስጥ ካልፈጸማችሁት በስተቀር፣ [ሀ]መታጠባችሁንስ ለእኔ ዘንድ እንዴት ተቀባይነት ይሆራቸዋል?

፴፰ በዱር ተሸክመው ይወስዱት ዘንድ ነው ሙሴን [ሀ]ታቦት እንዲሰራ ያዘዝኩት፣ እና ከአለም ፍጥረት በፊት ተደብቀው የነበሩት ስርዓቶችን ይገልጥም ዘንድ ነው በቃል ኪዳን ምድርም [ለ]ቤት እንዲሰራ ያዘዝኩት።

፴፱ ስለዚህ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]መቀባታችሁ፣ እና መታጠባችሁ፣ እና ለሙታን [ለ]መጠመቃችሁ፣ እና [ሐ]የክብር ስብሰባዎቻችሁ፣ እና ለሌዊ ልጆች [መ]መስዋዕት እና ንግግርን በምትቀበሉበት [ሠ]ቅዱስ ስፍራዎቻችሁ ውስጥ ለሚኖራችሁ የእግዚአብሔር ቃላት መታሰቢያ፣ እና ለደንቦቻችሁ እና ለፍርዶቻችሁ፣ ለራዕያት መጀመሪያ እና ለፅዮን መመስረት፣ እና ለእርሷም ማዘጋጃ ቤት ግርማ፣ ክብር፣ እና መንፈሳዊ ስጦታ፣ ለቅዱስ ስሜ ህዝቤ ሁልጊዜ እንዲገነቡ በሚታዘዙበት በቅዱስ ቤቴ ስነ ስርዓት የተሾሙ ናቸው።

፵ እና እውነት እላችኋለሁ፣ ስነ ስርዓቶቼን ለህዝቤ በዚህ ውስጥ እገልጥ ዘንድ፣ ይህም ቤት በስሜ ይሰራ፤

፵፩ ከአለም መመስረት በፊት [ሀ]ተሰውረው የነበሩትን ነገሮች፣ [ለ]ስለዘመን ፍጻሜ የሚመለከቱትን ነገሮች፣ ለቤተክርስቲያኔ [ሐ]እገልጥ ዘንድ አላማ አለኝና።

፵፪ እና ለአገልጋዬ ጆሴፍ ይህን ቤት፣ እና በዚህም ክህነትን፣ እና ይህም የሚገነባበትን ስፍራ በሚመለከት ሁሉንም ነገሮች [ሀ]አሳየዋለሁ።

፵፫ እና ለመገንባት ስታሰላስሉበት በነበረው ስፍራም ትገነቡታላችሁ፣ እናንተ እንድትገነቡበት የመረጥኩት ስፍራ ነውና።

፵፬ በሙሉ ሀይላችሁ ታገለግሉ ዘንድ፣ ይህም [ሀ]ቅዱስ ይሆን ዘንድ ስፍራውን እቀድሰዋለሁ።

፵፭ እና ህዝቤ ድምጼን እና ህዝቤን እንዲመሩ የመደብኳቸውን [ሀ]የአገልጋዮቼን ድምፅ ቢያደምጡ፣ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከስፍራቸውም አይወጡም።

፵፮ ነገር ግን ድምጼን ወይም እነዚህን

፴፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፥ ፲፬–፲፮።
ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፴፮ ሀ ኢሳ. ፬፥ ፭–፮።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ማጠብ፤
የታጠበ፤ የሚታጠቡ።
፴፰ ሀ ዘፀአ. ፳፭፥ ፩–፱፤ ፴፫፥ ፯።
ቅ.መ.መ. ታቦት።
ለ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፤
የጌታ ቤት።
፴፱ ሀ ዘፀአ. ፳፱፥ ፯።
ቅ.መ.መ. መቀባት።
ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች—
የወኪል ስነስርዓት።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፰፥ ፻፲፱።
መ ት. እና ቃ. ፲፫፤ ፹፬፥ ፴፩፤
፻፳፰፥ ፳፬፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፷፱።
ሠ ሕዝ. ፵፩፥ ፬፤
ት. እና ቃ. ፵፭፥ ፴፪፤
፹፯፥ ፰፤ ፻፩፥ ፳፪።
፵፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥ ፳፮–፴፪።
ለ ኤፌ. ፩፥ ፱–፲፤
ት. እና ቃ. ፳፯፥ ፲፫፤
፻፲፪፥ ፴።
ሐ ኢ.አ. ፩፥ ፱።
፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፺፭፥ ፲፬–፲፯።
፵፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ።
፵፭ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥ ፴፰።
ቅ.መ.መ. ነቢይ።

የመደብኳቸውን የአገልጋዮቼን ድምፅ ባያደምጡ፣ ቅዱስ መሬቴን፣ እና ቅዱስ ስርዓቶቼን፣ እና ህገ መንግስቴን፣ እና የሰጠኋቸውን ቅዱስ ቃላቴን ስለሚያረክሱ አይባረኩም።

፴፯ እና እንዲህም ይሆናል በስሜ ቤቴን ብትሰሩ፣ እና ያልኳቸውንም ነገሮች ባታደርጉ፣ ለእናንተ የገባሁትን [ሀ]መሀላ አልፈፅምም፣ ከእጄም የምትጠብቁትን ቃል ኪዳንም አላሟላም፣ ይላል ጌታ።

፴፰ እናንት በስራችሁ [ሀ]በረከቶች ሳይሆን፣ በሞኝነታችሁና በፊቴ በምታደርጉት በአጸያፊ ስራዎቻችሁ እርግማንን፣ ቁጣን፣ ንዴትን፣ እና ፍርድን በራሳችሁ ላይ ታመጣላችሁና፣ ይላል ጌታ።

፴፱ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ለስሜ ስራን እንዲሰሩ ለየትኞቹም የሰዎች ልጆች ትእዛዝን ስሰጥ፣ እነዚያም የሰዎች ልጆች ሁሉ በሙሉ ሀይላቸውና ባላቸው ሁሉ ያንን ስራ ቢፈጽሙ፣ እና [ሀ]ቅንነታቸውን ባያጎድሉ፣ እና ጠላቶቻቸው ቢመጡባቸው እና ያንንም ስራ እንዳያከናውኑ እንቅፋት ቢሆኑባቸው፣ እነሆ፣ ከእነዚያ የሰዎች ልጆች እጆች ላይ ያንንም ስራ በተጨማሪም [ለ]ላለመጠየቅ፣ ነገር ግን መስዋዕታቸውን እቀበል ዘንድ ፍቃዴ ነው።

፵ እና [ሀ]ንስህ እስካልገቡ እና እስከጠሉኝም ድረስ፣ ክፋትን እና የቅዱስ ህግጋቴን እና ትእዛዛቴን ስራ የሚያደናቅፉትን፣ እስከ ሶስት እና አራት [ለ]ትውልዶች፣ [ሐ]እጎበኛቸዋለሁ፣ ይላል ጌታ አምላክ።

፵፩ ስለዚህ፣ [ሀ]በጃክሰን የግዛት ክፍል ሚዙሪ ውስጥ ከተማ እና [ለ]ቤት በስሜ እንዲገነቡ ካዘዝኳቸው፣ እና በጠላቶቻቸውም ከተደናቀፉት መካከል መስዋዕታቸውን የተቀበልኩት በዚህ ምክንያት ነው፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፵፪ እና ንስህ እስካልገቡ እና እስከጠሉኝ ድረስ፣ [ሀ]ፍርድን፣ ቁጣን፣ ንዴትን፣ ልቅሶን፣ እና ስቃይን፣ እና ጥርስ ማፏጨትን በራሳቸው ላይ፣ እስከ ሶስት እና አራት ትውልድ እመልስላቸዋለሁ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፵፫ እና እነዚያ ስራ እንዲሰሩ ታዝዘው እና በጠላቶቻቸው እጆች እና በግፍ ተደናቅፈው የነበሩትን ሁሉ በሚመለከት ትፅናኑበት ዘንድ ይህን ለእናንተ ምሳሌ አደርጋለሁ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፵፬ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝና፣ እና በልባቸው [ሀ]ንጹህ የሆኑትን፣ እና በሚዙሪ ምድር ውስጥ [ለ]የተገደሉትን ወንድሞቻችሁንም አድናለሁ፣ ይላል ጌታ።

፵፭ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በማዝዛችሁ ማንኛቸውም ነገሮች እናንተ ታማኝ መሆናችሁን ለእኔ [ሀ]ታረጋግጡ ዘንድ፣ እና እኔም እባርካችሁ እና በክብር፣ ህያውነት፣ እና በዘለአለማዊ ህይወትንም አጎናጽፋችሁ ዘንድ በስሜ [ለ]ቤትን እንድትገነቡ፣ በዚህም ስፍራ ይህን ታደርጉ ዘንድ፣ ደግሜ አዛችኋለሁ።

፵፮ አሁንም ለእንግዶች ማረፊያ እንድትገነቡት ያዘዝኳችሁ ማረፊያ [ሀ]ቤትን በሚመለከት እላችኋለሁ፣ በስሜም ይሰራ፣ ስሜም በእርሱ ላይ ይሁን፣ እና አገልጋዬ ጆሴፍ እና ቤቱም በዚህ ውስጥ ከትውልድ እስከ ትውልድ ስፍራ ይኑራቸው።

፵፯ ለዚህም ራሱን ቀብቼዋለሁ፣ ከእርሱ በኋላ ያለው ትውልድ የእርሱን በረከት በላያቸው ይቀበላሉ።

፵፰ እና [ሀ]ለአብርሐም ስለምድር ነገዶች

፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. መህላ።
፴፰ ሀ ዘዳግ. ፳፰፥ ፲፭።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ት. እና ቃ. ፶፮፥ ፬፤ ፻፴፯፥ ፱።
፵ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
ለ ዘዳግ. ፭፥ ፱፤ ት. እና ቃ. ፺፰፥ ፵፮–፵፯።
ሐ ሞዛያ ፲፪፥ ፩።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. የጃክሰን አውራጃ፣ ምዙሪ (ዮኤስኤ)።
ለ ት. እና ቃ. ፻፲፭፥ ፲፩።
፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፩፥ ፲፩–፳፫።
፵፬ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ለ ት. እና ቃ. ፺፰፥ ፲፫፤ ፻፫፥ ፳፯–፳፰።
፵፭ ሀ አብር. ፫፥ ፳፭።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፯፥ ፬።
፵፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥ ፳፪–፳፬።
፵፰ ሀ ዘፍጥ. ፲፪፥ ፫፤ ፳፪፥ ፲፰፤ አብር. ፪፥ ፲፩። ቅ.መ.መ. አብርሐም።

እንዳልኩትም፣ ለአገልጋዬ ጆሴፍም እንዲሁም እለዋለሁ፥ በአንተ እና [ለ]በዘርህ የምድር ነገዶች ይባረካሉ።

፶፱ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ እና ከእርሱም በኋላ ዘሮቹ በዚያ ቤት ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ ለዘለአለም ስፍራ ይኑራቸው፣ ይላል ጌታ።

፷ የቤቱም ስም የናቩ ቤት በመባል ይታወቅ፤ እና ለሰውም የሚያስደስት መኖሪያ እና የፅዮንን ክብር እና የዚህ የማዕዘን ድንጋይ ክብርን ያሰላስል ዘንድ ለደከመውም ተጓዢ ማረፊያ ስፍራ ይሁን፤

፷፩ እንደዝነኛ [ሀ]አትክልት እና እንደ [ለ]ጠባቂዎች በግድግዳዋ ላይ ካስቀመጥኳቸው ምክር ደግሞም ይቀበል ዘንድ።

፷፪ እነሆ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ጆርገ ሚለር እና አገልጋዬ ላይመን ዌይት፣ እና አገልጋዬ ጆን ስናይደር፣ እና አገልጋዬ ፒተር ሀውስ ራሳቸውን ያደራጁ እና ቤቱን ለመገንባትም ባላቸው አላማም በመካከላቸው አንዱን እንደ ቡድናቸው ፕሬዘደንት ይመድቡ።

፷፫ እና እነርሱም ያን ቤት ለመስራትም ሸቀጥ የሚቀበሉበት ህገ መንግስትን ይመስርቱ።

፷፬ እና በዚያ ቤት ውስጥ የድርሻቸውን ሸቀጥ ከሀምሳ ዶላር በላይ አይቀበሉ፣ እና ለዚያ ቤት ሸቀጥም ከእያንዳንዱ ሰው አስራ አምስት ሺህ ዶላሮች እንዲቀበሉ ይፈቀድላቸው።

፷፭ ነገር ግን ከማንም አንድ ሰው ከአስራ አምስት ሺህ ዶላሮች በላይ እንዲቀበሉ አይፈቀድላቸውም።

፷፮ እና ከማንም ሰው ለዚያ ቤት ሸቀጥ የድርሻውን ከአስራ አምስት ሺህ ዶላሮች በታች እንዲቀበሉ አይፈቀድላቸውም።

፷፯ እና ሸቀጡን በሚቀበልበት ጊዜ ለሸቀጡ ካልከፈለ በስተቀር፣ ማንንም ሰው እንደዚህ ቤት ሸቀጥ ድርሻ ያዥ ለመቀበል አይፈቀድላቸውም።

፷፰ በእጆቻቸው በሚከፍለው የሸቀጡ ክፍያው በዚያ ቤት ውስጥ ሸቀጥን ይቀበል፤ ነገር ግን በእጆቻቸው ምንም ካልከፈለ በእዚያ ቤት ውስጥ ምንም ሸቀጥ አይቀበል።

፷፱ እና ማንም ሸቀጥን በእጆቻቸው ቢከፈል በቤቱ ውስጥ እና ለእርሱና ከእርሱ በኋላ ለመጡት ትውልዶችም፣ ከትውልድ እስከትውልድ፣ እርሱ እና የእርሱ ወራሾች ሸቀጡን እስከያዙ ድረስ እና በራሳቸው ነጻ ፈቃድ ወይም ስራ ሸቀጡን ከእጆቻቸው አውጥቶ ካላስተላለፈ ወይም ካልሸጠው በስተቀር፣ ፈቃዴን ብታደርጉ ለሸቀጥ ይሆንለታል፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፸ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ጆርጀ ሚለር እና አገልጋዬ ላይመን ዋይት እና አገልጋዬ ጆን ስናይደር፣ እና አገልጋዬ ፒተር ሀውስ በገንዘቦች ወይም የእውነት ዋጋ ያለው ገንዘብ በሚቀበሉበት ንብረቶች ምንም ሸቀጥ በእጆቻቸው ቢቀበሉ፣ በቤቱ ውስጥ እንጂ ያንን ሸቀጥ የትኛውንም ክፍል ለምንም አላማ አይመድቡ።

፸፩ እና ከቤቱ ላይ በስተቀር የሸቀጡን ማንኛውንም ክፍል በሌላ ስፍራ ሸቀጡን ከያዙት ሳይፈቅዱ ከመደቡት እና በየትኛውም ስፍራ የመደቡትን ሸቀጥ በአራት እጥፍ መልሰው ባይከፍሉ፣ ይረገማሉ፣ እና ከስፍራቸውም ይወጣሉ፣ ይላል ጌታ አምላክ፤ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝ እና በእነዚህ በማንኛቸውም ነገሮች [ሀ]አይዘበትብኝምና።

፸፪ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ጆሴፍ፣ መልካም እንደሚመስለው፣ ቤቱ ከመገንባቱ በፊት ለሸቀጡ በእጆቻቸው ይክፈል፤ ነገር ግን አገልጋዬ ጆሴፍ ለዚያ ቤት ሸቀጥ ከአስራ አምስት ሺህ በላይ ወይም ከአምስት ሺህ በታች መክፈል አይ

፶፰ ለ ት. እና ቃ. ፻፲፥ ፲፪።
ቅ.መ.መ. የአብርሐም ቃል ኪዳን።

፷፩ ሀ ኢሳ. ፷፩፥ ፫፤
ሕዝ. ፴፬፥ ፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. መጠበቅ፣ ጠባቂ።

፸፩ ሀ ገላ. ፮፥ ፯።

ችልም፤ ወይም ሌላም ሰው ይህን ማድረግ አይችልም፣ ይላል ጌታ።

፸፫ እና ፈቃዴን ለማወቅ ፈቃድ ያላቸው ሌሎችም አሉ፣ ከእጆቼ ጠይቀውታልና።

፸፬ ስለዚህ፣ ስለአገልጋዬ ቪንሰን ናይት እላችኋለሁ፣ ፈቃዴን ቢያደርግ በዚያ ቤት ላይ ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጡ ትውልዶቹ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ ሽቀጥን ያስገባ።

፸፭ እና በህዝብ መካከል፣ የድሆች እና እርዳታን ለሚሹ ሀለመለመን፣ ድምጹን ረጅም እና ጉልህ በማድረግ ያንሳ፤ አይውደቅ፣ ወይም ልቡም ተስፋ አይቁረጥ፤ እና መስዋዕቶቹን ለእቀበላቸዋለሁ፣ እንደ ቃየን መስዋእቶች አይደሉምና፣ እርሱም የእኔ ይሆናልና፣ ይላል ጌታ።

፸፮ ቤተሰቡም ይደሰቱ እና ከስቃይም ልባቸውን ይመልሱ፤ እኔ መርጬው እና ቀብቼዋለሁና፣ እና በቤቱም መካከልም ይከብራል፣ ለኃጢአቶቹ ሁሉ ምህረትን እሰጠዋለሁና፣ ይላል ጌታ። አሜን።

፸፯ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ለእራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጡት ትውልዶች፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ መልካም እንደሚመስለው በቤቱ ላይ ሽቀጥን ያስቀምጥ።

፸፰ አገልጋዬ አይዛክ ጋላንድ በቤቱ ላይ ሽቀጥ ያስገባ፤ እኔ ጌታ ለሰራው ስራም እወደዋለሁና እና ለኃጢአቶቹ በሙሉ ምህረትን እሰጠዋለሁና፤ ስለዚህ፣ በዚህም ቤት ውስጥ ሽቀጥ እንዳለውም ከትውልድ እስከ ትውልድ ይታወስ።

፸፱ አገልጋዬ አይዛክ ጋለንድም በመካከላችሁ ይመደብ፣ እና ከአገልጋዬ ሀይረም ስሚዝ ጋር አገልጋዬ ጆሴፍ የሚጠቁምላቸውን ስራ ለማከናወን በአገልጋዬ ዊልያም ማርክስም ይሾም፣ እና በእርሱም ይባረክ፣ እና እነርሱም በታላቅ በረከትም ይባረካሉ።

፹ አገልጋዬ ውልያም ማርክስም መልካም እንደሚመስለው ለራሱ እና ለትውልዱ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ በቤቱ ላይ ለሽቀጥ ይክፈል።

፹፩ አገልጋዬ ሄንሪ ጂ ሸርውድ መልካም እንደሚመስለው ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ በቤቱ ላይ ለሽቀጥ ይክፈል።

፹፪ አገልጋዬ ውልያም ሎው መልካም እንደሚመስለው ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለዘሩ፣ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ በቤቱ ላይ ለሽቀጥ ይክፈል።

፹፫ ፈቃዴን የሚያደርግ ቢሆን፣ ቤተሰቡን ወደ ምስራቅ ምድር፣ እንዲሁም ወደ ከርትላንድ አይውሰድ፤ ይህ ቢሆን፣ እኔ ጌታ ከርትላድን እገነባለሁ፣ እና እኔ ጌታ በዚያ ለሚኖሩትም የሚመቱበትን ጅራፍ አዘጋጅቼላቸዋለሁ።

፹፬ እና ከአገልጋዬ አልሞን ባቢት ያልተደሰትኩበት ብዙ ነገሮች አሉ፤ እነሆ፣ ከመደብኩለት ምክር፣ እንዲሁም ከቤተክርስቲያኔ አመራር በላይ የእራሱን ምክር ለመመስረት ተነሳስቷል፤ እና ህዝቤም ያመልኩት ዘንድ ሀየወርቅ ጥጃን ያቆማል።

፹፭ ትእዛዛቴን በመሻት የመጣ ማንም ሰው ከዚህ ስፍራ ሀአይሂድ።

፹፮ እዚህም የሚኖሩ ቢሆን፣ በእኔ ይኑሩ፤ እና ቢሞቱም፣ በእኔ ይሙቱ፤ ከስራዎቻቸው ሁሉ በዚህ ሀያርፋሉና፣ እና ስራዎቻቸውንም ይቀጥላሉና።

፹፯ ስለዚህ፣ አገልጋዬ ውልያም እምነቱን በእኔ ላይ ያድርግ፣ እና በምድሩ ላይ ባለው ህመም ምክንያትም ስለቤተሰቡ መፍራቱን ያቁም። ሀብትወዱኝ ትእዛዛቴን ጠብቁ፤ እና የምድሩም ህመም ለክብራችሁ ለይቀየራል።

፹፰ አገልጋዬ ውልያም ይሂድ እና በጎላ ድምፅም እና በታላቅ ደስታ፣ ሀበመንፈሴም

፸፭ ሀ ምሳ. ፴፩፥ ፱።
ለ ዘፍጥ. ፬፥ ፬–፭፤
ሙሴ ፭፥ ፲፰–፳፫።
፹፬ ሀ ዘፀአ. ፴፪፥ ፪–፬።
፹፭ ሀ ሉቃ. ፱፥ ፷፪።
፹፮ ሀ ራዕ. ፲፬፥ ፲፫።
ቅ.መ.መ. እረፍት፤
ገነት።
፹፯ ሀ ዮሐ. ፲፬፥ ፲፭።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፮፥ ፫፤
፻፳፬፥ ፯።
፹፰ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣
አምላክ—እግዚአብሔር
መንፈስ ቅዱስ።

እንደተነሳሳ፣ ዘለአለማዊውን ወንጌሌን ለዋርሶ ነዋሪዎች፣ እና ደግሞም ለካርቴጅ ነዋሪዎች፣ እና ደግሞም ለበርሊንግተን ነዋሪዎች፣ እና ደግሞም ለማድሰን ነዋሪዎች፣ ያውጅ፣ እና በትእግስትና በቅንነት በአጠቃላይ ጉባኤ ላይ መመሪያን ይጠብቅ፣ ይላል ጌታ።

፹፱ ፈቃዴን የሚያደርግ ቢሆን፣ የአገልጋዩ ጆሴፍን ምክር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያድምጥ፣ በችሎታውም [ሀ]ድሆችን ይርዳ፣ እና ለምድርም ነዋሪዎች ቅዱስ ቃሌን [ለ]አዲስ ትርጉም ያውጅ።

፺ እና ይህንንም ቢያደርግ በሚበዙ በረከቶች [ሀ]እባርከዋለሁ፣ እርሱ አይተውም፣ ወይም ዘሩም ዳቦ [ለ]እየለመኑ አይገኙም።

፺፩ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዩ ሀይረም በአባቱ እና በበረከት፣ እና ደግሞም በመብት የተመደበለትን ክህነት እና [ሀ]የፓትሪያርክ ሀላፊነት ይወስድ ዘንድ፣ አገልጋዩ ውልያም በአገልጋዩ ሀይረም ምትክ ለአገልጋዩ ጆሴፍ አማካሪ እንዲሆን ይመደብ፣ ይሾም፣ እናም ይቀባ፤

፺፪ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በህዝቤ ሁሉ ላይ [ሀ]የፓትሪያርክ በረከት ቁልፎችን ይያዝ፣

፺፫ ማንም እርሱም የሚባርክ ይባረካል፣ እና ማንም የሚረግመውም [ሀ]ይረገማል፤ በምድር [ለ]የሚያስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የሚፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።

፺፬ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለአገልጋዩ ጆሴፍ ለቤተክርስቲያኔ ነቢይ፣ [ሀ]ባለራዕይ፣ እናም ገላጭ እንዲሆን መድቤዋለሁ፤

፺፭ ከአገልጋዩ ጆሴፍ ጋር በአንድነት ይሰራም ዘንድ፤ እና የሚጠይቀውን እና የሚቀበልበትን [ሀ]ቁልፎች የሚያሳየውን የአገልጋዬን የጆሴፍን ምክር ይቀበል፣ እና በዚህም አይነት በረከት፣ እና አገልጋዩ በነበረው [ለ]ኦሊቨር ካውድሪ ላይ ተጭኖ የነበረውን ግርማ፣ እና ክብር፣ እና ክህነት፣ እና የክህነት ስጦታም ይጎናጸፋል፤

፺፮ አገልጋዩ ሀይረምም ስለማሳየው ነገሮች ምስክነትን ይሰጥ ዘንድ፣ ስሙም በክብር ማስታወሻ ከትውልድ እስከ ትውልድ፣ ለዘለአለም ይሆን ዘንድ መድቤዋለሁ።

፺፯ አገልጋዩ ውልያም ሎውም በረከቶችን በመጠየቅ የሚቀበልበትን ቁልፎች ይቀበል፤ በፊቴም [ሀ]ትሁት፣ እና [ለ]ያለ ነቀፋም ይሁን፣ እና የሁሉንም ነገር እውነትነት የሚገልፅ፣ እና በዚያችም ሰዓት እንዴት እንዲናገር የሚሰጠው መንፈሴን፣ እንዲሁም [ሐ]አፅናኝን ይቀበል።

፺፰ እና እነዚህም [ሀ]ምልክቶች ይከተሉታል—የታመሙትን [ለ]ይፈውሳል፣ አጋንንትን ያወጣል፣ ገዳይ መርዝንም ከሚሰጡትም ከእነርሱም ይድናል፤

፺፱ እና [ሀ]መርዛማም እባብ ተረከዙን በማይነክስበት መንገድ ይመራል፣ እና በሀሳቡም [ለ]አይነ ህሊናው የንስር ክንፍ እንደሚበር ወደላይ ይብረር።

፻ እና የሞተውን እንዲያነሳ ብፈቅድ፣ ድምጹን አይሰብስብ።

፻፩ ስለዚህ፣ አገልጋዩ ውልያምም በደስታ እና በሀሴት በዙፋኑ ላይ ለዘለአለም ለተቀመጠው ሆሳዕና በማለት፣ በታላቅ ድምጽ ይጬህ እናም አይከልከል፣ ይላል ጌታ አምላክህ።

፻፪ እነሆ፣ እላችኋለሁ፣ ለአገልጋዩ ውልያም እና ለአገልጋዩ ሀይረም፣ እና ለእርሱም

፹፱ ሀ ት. እና ቃ. ፸፰፥፫።
ለ ይህም የጆሴፍ ስሚዝ የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ማለት ነው።
፺ ሀ ቅ.መ.መ. መባረክ፤ የተባረከ፤ በረከት።
ለ መዝ. ፴፯፥፳፭።
፺፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፴፱–፵።
ቅ.መ.መ. የአባቶች አለቃ፤ ፓትሪያርክ።
፺፪ ሀ ቅ.መ.መ. የፓትሪያርክ በረከቶች።
፺፫ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፵፮–፵፯።
ለ ማቴ. ፲፮፥፲፱።
ቅ.መ.መ. ማተም፤ ማስተሳሰር።
፺፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፩–፺፪።
ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
፺፭ ሀ ት. እና ቃ. ፮፥፳፰።
ለ ቅ.መ.መ. ካውደሪ፤ ኦልቨር።
፺፯ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፤ ትሕትና።
ለ ቅ.መ.መ. ተንኮል።
ሐ ቅ.መ.መ. አፅናኝ።
፺፰ ሀ ማር. ፲፮፥፲፯–፲፰።
ቅ.መ.መ. የመንፈስ ስጦታዎች።
ለ ቅ.መ.መ. መፈወስ፤ ፈውሶች።
፺፱ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፸፩–፸፫።
ለ ዘፀአ. ፲፱፥፬፤
ኢሳ. ፵፥፴፩።

ብቻ ተልዕኮን አዘጋጅቼላቸዋለሁ፤ እና አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝም በቤት ይቆይ፣ ይፈለጋልና። የሚቀረውን ከዚህ በኋላ አሳያችኋለሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፫ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ [ሀ]ስድኒ ቢያገለግለኝ እና ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ አማካሪ ቢሆን፣ ይነሳ እና ወደፊትም ይምጣ እና በተጠራበት ሀላፊነትም ይቁም፣ እና በፊቴም ትሁት ይሁን።

፻፬ እና ተቀባይነት ያለውን መስዋዕትና እውቀትን ቢያቀርብልኝ፣ እና ከህዝቤም ጋር ቢቆይ፣ እነሆ እኔ ጌታ አምላክህ የሚፈወሰውን እፈውሳለሁ፤ እና በተራሮችም ላይ ድምጹን ከፍ ያደርጋል፣ እና በፊቴም [ሀ]የሚናገርልኝ ይሆናል።

፻፭ ይምጣ እና አገልጋዬ ጆሴፍ በሚኖርበት አካባቢም ቤተሰቡንም በዚያ ያኑር።

፻፮ እና በጉዞዎቹም ሁሉ እንደመለከት ድምጽ ድምጹን ከፍ ያድርግ፣ እና የምድር ነዋሪዎችንም ስለሚመጣው ከሚመጣው ቍጣ እንዲሸሹ ያስጠንቅቃቸው።

፻፯ አገልጋዬ ጆሴፍን ይርዳ፣ እና አገልጋዬ ውልያም ሎውም ከዚህ በፊት እንዳልኳችሁ ለምድር ነገስታት የክብር [ሀ]አዋጅን በማድረግ አገልጋዬ ጆሴፍን ይርዳ።

፻፰ አገልጋዬ ስድኒ ፈቃዴን ቢያደርግ፣ ቤተሰቡን ወደ [ሀ]ምስራቅ ምድር አይውሰዳቸው፣ ነገር ግን እንዳልኩት መኖሪያቸውን ይቀይር።

፻፱ እነሆ፣ ለእናንተ ከመደብኩላችሁ ከተማ፣ እንዲሁም [ሀ]ከናቩ ከተማ፣ ውጪ ደህንነትን እና መሸሸጊያን ለማግኘት መሻቱ ፍቃዴ አይደለም።

፻፲ እውነት እላችኋለሁ፣ አሁንም ድምጼን ብታደምጡ፣ መልካም ይሆንላችኋል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፲፩ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ኤመስ ዴቪስ የማረፊያ ቤት፣ እንዲሁም የናቩን ቤት፣ እንዲገነቡ ለመደብኳቸው ሰዎች በእጆቻቸው ላይ ሸቀጥ ይክፈል።

፻፲፪ ፍላጎቱም ቢሆን ይህንን ያድርግ፤ እና የአገልጋዬ ጆሴፍን ምክር ያድምጥ፣ እና የሰዎችንም እምነት ያገኝ ዘንድ በእጆቹ ይስራ።

፻፲፫ እና እንዲንከባከባቸው በተሰጡት ነገሮች ሁሉ፣ አዎን እንዲሁም በጥቃቅን ነገሮች፣ ታማኝ እንደሆነ ራሱን ሲያረጋግጥ፣ በብዙ ነገሮች [ሀ]አስተዳዳሪ ይሆናል።

፻፲፬ ስለዚህ፣ የላቀ ክብር ይኖረውም ዘንድ እራሱን [ሀ]ያዋርድ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፲፭ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ ሮበርት ዲ ፎስተር ድምጼን ቢታዘዝ፣ ከእርሱ ጋርም በገባው ስምምነት መሰረት ለአገልጋዬ ጆሴፍ ቤት ይስራ፣ ከጊዜ ወደጊዜም በሮች ይከፈቱለታልና።

፻፲፮ እና ለሞኝነት ስራውም ንስሀ ይግባ፣ እና [ሀ]በልግስና እራሱን ያልብስ፤ እና ክፉ ማድረግንም ያቁም፣ እና የክፉ ንግግሮቹንም ያቁም።

፻፲፯ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ለራሱ እና ከእርሱ በኋላ ለሚመጡት ትውልዶች፣ ለናቩ ቤት ቡድኖችም ሸቀጥን ይክፈል፤

፻፲፰ እና አገልጋዮቼን የጆሴፍን፣ እና ሀይረምን፣ እና የውልያም ሎው፣ እና የፅዮንንም መሰረት ይገነቡ ዘንድ የጠራኋቸውን ባለስልጣናት ምክሮችንም ያድምጥ፤ እና ለዘለአለም መልካም ይሆንለታል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፲፱ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በመፅሐፈ ሞርሞን፣ እና በሰጠኋችሁ ራዕዮች የሚያምን ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው ለናቩ ቤት ቡድኖች ሸቀጥን አይክፈል፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፤

፻፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሪግደን፣ ስድኒ።
፻፬ ሀ ዘፀአ. ፬፥ ፲፬–፲፮፤
፪ ኔፊ ፫፥ ፲፯–፲፰፤
ት. እና ቃ. ፩፥ ፱–፲፩።
፻፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥ ፪–፬።
፻፰ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥ ፹፪–፹፫።
፻፱ ሀ ቅ.መ.መ. ናቩ፣ ኢሊኖይ (ዮ.ኤስ.ኤ.)።
፻፲፫ ሀ ማቴ. ፳፭፥ ፲፬–፴።
፻፲፬ ሀ ማቴ. ፳፫፥ ፲፪፤
ት. እና ቃ. ፻፩፥ ፵፪።
፻፲፮ ሀ ቆላ. ፫፥ ፲፬።
ቅ.መ.መ. ልግስና።

፻፳ ከእነዚህም [ሀ]የበዛ ወይም ያነሰ ከክፉው የሚመጣ ነውና፣ እና በበረከቶች ሳይሆን እርግማኖች ይከተሏቸዋልና፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፳፩ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የናቩ ቤት ቡድኖች የናቩ ቤትን ለመገንባት ለሚያደርጉት አገልግሎታቸው ሁሉ በቂ ደመወዝ ይከፈላቸው፤ እና ደሞዛቸውም፣ ስለዋጋው በሚመለከት፣ በመካከላቸው የሚስማሙበት ይሁን።

፻፳፪ እና እያንዳንዱ ሸቀጥን የሚከፍለው የድርሻ ደሞዙን፣ አስፈላጊም ከሆነ የሚደገፉበትን ይክፈል፣ ይላል ጌታ፤ አለበለዚያም፣ አገልግሎታቸው በዚያ ቤት እንደ ሸቀጥ ይቆጠርላቸዋል። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፳፫ እውነት እላችኋለሁ፣ ለእናንተ ለክህነት ስልጣኔ አባል ለሆናችሁት [ሀ]ባለስልጣናት፣ [ለ]ቁልፎቹንም ትይዙ ዘንድ፣ እንዲሁም በአንድያ ልጅ ስርዓት የሆነውን [ሐ]የመልከ ጼዴቅን ስርዓት ክህነት አሁን እሰጣችኋለሁ።

፻፳፬ መጀመሪያ፣ ሀይረም ስሚዝን ለእናንተ [ሀ]ፓትሪያርክ እንዲሆን፣ የሚመጡባችሁን፣ የፈተና [ለ]ስአታትን በመቋቋም እንዳትወድቁ ለቤዛም ቀን [ሐ]የምትታተሙባቸውን የቤተክርስቲያኔን [መ]ማስተሳሰሪያ በረከቶችን፣ እንዲሁም ቅዱስ [ሠ]የተስፋ መንፈስን እንዲይዝ እሰጠዋለሁ።

፻፳፭ አገልጋዬ ጆሴፍ በቤተክርስቲያኔ ሁሉ አስተዳዳሪ ሽማግሌ፣ ተርጓሚ፣ [ሀ]ገላጭ፣ ባለራዕይ፣ እና ነቢይ እንዲሆን እሰጣችኋለሁ።

፻፳፮ ለእርሱም አገልጋዬን ስድኒ ሪግደንን እና አገልጋዬን ውልያም ሎውን እንደ አማካሪዎቹ እሰጠዋለሁ፣ እነዚህም ለቤተክርስቲያኗ [ሀ]የእግዚአብሔርን ቃላት ለመቀበል ቡድንን እና ቀዳሚ አመራርን ያቋቁማሉ።

፻፳፯ አገልጋዬ [ሀ]ብሪገም ያንግን የአስራ ሁለቱ ተጓዥ ሸንጎ ፕሬዘደንት እንዲሆን እሰጣችኋለሁ፤

፻፳፰ [ሀ]አስራ ሁለቱም በምድር አራቱ ማዕዘናት ላይ የመንግስቴን ስልጣን ለመክፈት፣ እና ከዚያም በኋላ ቃሌን ለሁሉም ፍጥረቶች [ለ]ይልኩ ዘንድ ቁልፎችን ይዘዋል።

፻፳፱ እነዚህም ሂበር ሲ ኪምባል፣ ፓርሊ ፒ ፕራት፣ ኦርሰን ፕራት፣ ኦርሰን ሀይድ፣ ውልያም ስሚዝ፣ ጆን ቴይለር፣ ጆን ኢ ፔጅ፣ ዊልፈርድ ዉድረፍ፣ ዊለርድ ርቻርድስ፣ ጆርጅ ኤ ስሚዝ ናቸው፤

፻፴ [ሀ]ዴቪድ ፓትንን ወደ እኔም ዘንድ [ለ]ወስጄዋለሁ፤ እነሆ፣ የእርሱን ክህነት ማንም ሰው አይወስድበትም፤ ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፣ በዚያ ጥሪ ሌላ ሊመደብ ይቻላል።

፻፴፩ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ ለፅዮን የማእዘን ራስ ድንጋይ እንዲሆን [ሀ]ከፍተኛ ሸንጎን ሰጠኋችሁ—

፻፴፪ በስምም፣ ሳሙኤል ቤንት፣ ሔንሪ ጂ ሸርውድ፣ ጆርጅ ደብሊው ሀሪስ፣ ቻርልስ ሲ ሪች፣ ቶማስ ግሮቨር፣ ኒወል ኒይት፣ ዴቪድ ዶርት፣ ዱንባር ዊልሰን—ሲሞር ብረንሰንን ወደ እኔ ወስጃለሁ፤ የእርሱን ክህነት ማንም ሰው አይወስድበትም፤ ነገር ግን በዚያ ክህነት ስልጣን ላይ ሌላ በእርሱ ምትክ ሊመደብ ይቻላል፣ እና እውነት እላችኋለሁ፣ አገልጋዬ አሮን ጆንሰን በእርሱ ምትክ ለዚህ

፻፳ ሀ ማቴ. ፭፥፴፯፤
ት. እና ቃ. ፺፰፥፯።
፻፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. ሀላፊነት፣ ሀላፊ።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ሐ ቅ.መ.መ. የመልከ ጼዴቅ ክህነት።
፻፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. የአባቶች አለቃ፣ ፓትሪያርክ።
ለ ራዕ. ፫፥፲።
ሐ ኤፌ. ፬፥፴።
መ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
ሠ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶፫፤ ፹፰፥፫–፬።
ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
፻፳፭ ሀ ት. እና ቃ. ፳፩፥፩።
ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
፻፳፮ ሀ ት. እና ቃ. ፺፥፬–፭።
፻፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ያንግ፣ ብሪገም።
፻፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።
ለ ማር. ፲፮፥፲፭።
፻፴ ሀ ቅ.መ.መ. ፓተን፣ ዴቪድ ደብሊው።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፲፱።
፻፴፩ ሀ ቅ.መ.መ. ከፍተኛ ሸንጎ።

ጥሪ ይሾም—ዴቪድ ፉልመር፣ አልፊየስ ከትለር፣ ውልያም ሀንቲንግተን።

፻፴፫ ደግሞም፣ ዶን ሲ ስሚዝን በሊቀ ካህናት ቡድን ላይ ፕሬዘደንት እንዲሆን እሰጣችኋለሁ፤

፻፴፬ ይህም ስርዓት የማይጓዙ ፕሬዘደንቶች ወይም በውጪ በተበተኑት በተለያዩ [ሀ]ካስማዎች አገልጋዮች እንዲሆኑ የተመደቡ ብቁ ለሚሆኑበት አላማ የተመሰረተ ነው፤

፻፴፭ እና ቢፈለጉም መጓዝ ይችላሉ፣ ነገር ግን በአንድ ስፍራ እንደሚያገለግሉ ፕሬዘደንቶች ይሾሙ፤ ይህም የጥሪአቸው ሀላፊነት ነው፣ ይላል ጌታ አመላካችሁ።

፻፴፮ በቤተክርስቲያኔ ሊቀ ካህናት ቡድኖችን ያስተዳድሩ ዘንድ አማሳ ላይማንን እና ኖዋ ፓከርድን እንደአማካሪዎቹ እሰጠዋለሁ፣ ይላል ጌታ።

፻፴፯ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ የክህነት ስልጣናቸው [ሀ]የሽማግሌዎች ቡድኖችን እንዲያስተዳድሩ የሆነውን ጆን ኤ ሂክስን፣ ሳሙኤል ዊልያምስን፣ እና ጀሲ ቤከርን እሰጣችኋለሁ፣ ያም ቡድን የተመሰረተው ለማይጓዙ አገልጋዮች ነው፤ ይህም ቢሆን መጓዝ ይችላሉ፣ ነገር ግን የተሾሙት በቤተክርስቲያኗ የማይጓዙ አገልጋዮች እንዲሆኑ ነው፣ ይላል ጌታ።

፻፴፰ ደግሞም፣ ጆሴፍ ያንግን፣ ጆሳያ በተርፊእልድን፣ ዳንኤል ማይልስን፣ ሄንሪ ሀሪማንን፣ ዜራ ፑልሲፈርን፣ ሊቫይ ሀንኮክን፣ ጄምስ ፎስተርን [ሀ]የሰባዎቹን ቡድን እንዲያስተዳድሩ እሰጣችኋለሁ።

፻፴፱ ይህም ቡድን የተመሰረተው የሚጓዙ ሽማግሌዎች በአለም ሁሉ፣ የሚጓዙ ከፍተኛ ሸንጎ፣ ሐዋሪያቴ በፊቴ መንገዶችን ለማዘጋጀት በሚልኳቸው በማናቸውም ስፍራዎች ስለ ስሜ እንዲመሰክሩ ነው።

፻፵ በዚህ ቡድን እና በሽማግሌዎች ቡድን ልዩነት ቢኖር አንዱ ዘወትር ይጓዛል እና ሌላው በቤተክርስቲያኔ ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያስተዳድር ነው፤ አንዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ የማስተዳደር ሀላፊነት አለው፣ እና ሌላውም የማስተዳደር ምንም ሀላፊነት የለውም፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፻፵፩ ደግሞም፣ እላችኋለሁ፣ ቪንሰን ናይትን፣ ሳሙኤል ኤች ስሚዝን፣ እና የሚቀበለው ቢሆን ሻድራክ ራውንዲን የኤጲስ ቆጶስ አመራርን እንዲያስተዳድር እሰጣችኋለሁ፤ የዚህ [ሀ]ኤጲስ ቆጶስ አመራር እውቀት [ለ]በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች መፅሀፍ ውስጥ ተሰጥቷችኋል።

፻፵፪ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሳሙኤል ሮልፍ እና አማካሪዎቹ እንደ ቄሶቹ ፕሬዘደንት፣ እና የመምህራን ፕሬዘደንት እና አማካሪዎች፣ እና ደግሞም የዲያቆናት ፕሬዘደንትና አማካሪዎች፣ እና ደግሞም የካስማ ፕሬዘደንቶችና አማካሪዎች እንዲሆኑ እሰጣችኋለሁ።

፻፵፫ የበላይ ሀላፊዎችን እና እነዚህን ቁልፎች ለእርዳታ እና ለማስተዳደር፣ ለአገልግሎቱ ስራዎችና ለቅዱሳኔ [ሀ]ፍጹምነት ሰጥቻችኋለሁ።

፻፵፬ እና እነዚህን ሀላፊነቶች በሙሉ እና የጠቀስኳቸውን ስሞች በአጠቃላይ ጉባኤዬም ላይ [ሀ]ታሟሏቸው እና ታጸድቋቸው ዘንድ ትእዛዝን እሰጣችኋለሁ፣ አለበለዚያም በአጠቃላይ ጉባኤዬም ላይ አታፅድቋቸውም።

፻፵፭ እና በቤቴ ውስጥም ለስሜ ስትገነቡት ለእነዚህ ሀላፊነቶች ክፍሎች አዘጋጁላቸው፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ። እንዲህም ይሁን። አሜን።

፻፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ካስማ።

፻፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፲፩–፲፪፣
፹፱–፺።
ቅ.መ.መ. ሽማግሌ፤
ቡድን።

፻፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሰባ።

፻፵፩ ሀ ት. እና ቃ. ፷፰፥፲፬፤
፻፯፥፲፭።
ለ ቅ.መ.መ. ትምህርት
እና ቃል ኪዳኖች።

፻፵፫ ሀ ኤፌ. ፬፥፲፩–፲፬።

፻፵፬ ሀ ት. እና ቃ. ፳፮፥፪።
ቅ.መ.መ. የጋራ ስምምነት።

ክፍል ፻፳፭

በመጋቢት ፲፰፻፵፩ (እ.አ.አ.)፣ በናቩ ኢለኖይ ውስጥ በአየዋ ክልል ውስጥ ያሉትን ቅዱሳን በሚመለከት ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ።

፩–፬፣ ቅዱሳን ከተማዎችን ይስሩ እና የፅዮን ካስማዎችንም ይሰብስቡ።

፩ በአየዋ ክልል ያሉትን ቅዱሳን በሚመለከት የጌታ ፈቃድ ምንድን ነው?

፪ ጌታ እንዲህ ይላል፣ እውነት እላችኋለሁ [ሀ]በስሜ ራሳቸውን የሚጠሩና ቅዱሳኔ ለመሆን የሚጥሩ፣ የምፈልገውን ቢያደርጉ እና እነርሱን የሚመለከቱ ትእዛዛቴን ቢያከብሩ፣ በአገልጋዬ ጆሴፍ በምመድብላቸው ስፍራዎች ራሳቸውን አብረው ይሰብስቡ፣ እና ለሚመጣው ዘመንም ይዘጋጁ ዘንድ በስሜም ከተማዎችን ይስሩ።

፫ ከናቩ ከተማ የተለየ ከተማ በስሜ ይስሩ፣ እና ስሙም [ሀ]ዛራሔምላ ይሁን።

፬ እና በዚህ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ ኖሮአቸው ከምስራቅ፣ እና ከምዕራብ፣ እና ከሰሜን፣ እና ከደቡብ የመጡት ሁሉ፣ ከዚህ፣ እና [ሀ]ከናሽቪል ከተማ፣ ወይም ከናቩ ከተማ፣ ከመደብኳቸው [ለ]ካስማዎች ሁሉ ውርሶቻቸውን ያግኙ፣ ይላል ጌታ።

ክፍል ፻፳፮

በሐምሌ ፱፣ ፲፰፻፵፩ (እ.አ.አ.) በብሪገም ያንግ ቤት ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። በዚህ ጊዜ ብሪገም ያንግ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን ፕሬዘደንት ነበር።

፩–፫፣ ብሪገም ያንግ ለአገልግሎቱ ተሞግሷል እና ወደፊትም ወደውጪ ከመጓዝ ፋታን አገኘ።

፩ ውድ እና ተወዳጅ ወንድም [ሀ]ብሪገም ያንግ፣ እውነት ጌታ እንዲህ ይልሀል፥ አገልጋዬ ብሪገም፣ እንዳለፉት ጊዜያት ቤተሰብህን እንድትተው አይጠበቅብህም፣ መስዋዕትህ በእኔ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቷልና።

፪ ስለስሜም በጉዞዎችህ ከባድ ስራህን እና [ሀ]አገልግሎትህን አይቻለሁ።

፫ ስለዚህ ቃሌን ወደውጪ እንድትልክ፣ እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘለአለም [ሀ]ቤተሰብህን በልዩ ሁኔታ እንድትንከባከባቸው አዝሀለሁ። አሜን።

ክፍል ፻፳፯

ከነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ለናቩ ኢለኖይ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ስለሙታን መጠመቅ መመሪያን የያዘ፣ በመስከረም ፩፣ ፲፰፻፵፪ (እ.አ.አ.) በናቩ የተጻፈ ደብዳቤ።

፻፳፭ ፪ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስን ስም በራሳችን ላይ መውሰድ።

፫ሀ ቅ.መ.መ. ዛራሔምላ።

፬ሀ ይህም ናሽቪል፣ ሊ አውራጃ፣ አየዋ ማለት ነው።

ለ ቅ.መ.መ. ካስማ።

፻፳፮ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ያንግ፣ ብሪገም።

፪ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።

፫ሀ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ።

፩–፬፣ ጆሴፍ ስሚዝ በስደት እና በመከራ መካከል ይደሰታል፤ ፭–፲፪፣ ስለሙታን ጥምቀቶችን በሚመለከት መዛግብት መጠበቅ አለባቸው።

፩ ጌታ ለእኔ በገለጠልኝ መጠን ጠላቶቼ በሚዙሪ እና በዚህ ስቴት ውስጥ ዳግም እየፈለጉኝ ናቸው፤ እና [ሀ]ያለምክንያትም እየፈለጉኝ እስከሆነ ድረስ፣ እና በእኔ ላይ በሚያመጡት ክስ በጎናቸው ጥቂት የሆነ የፍትህ ወይም የትክክለኛነት ጥላ ወይም ቀለም የላቸውም፤ እና ጥያቄዎቻቸው በጨለመ ሀሰት ላይ የተመሰረቱ እስከሆኑ ድረስ፣ ለራሴ ደህንነት እና ለዚህ ህዝብም ደህንነት ለአጭር ዘመን ይህን ስፍራ ትቼ መሄዴ አስፈላጊ እና ጥበባዊ እንደሆነም አስቤአለሁ። ጉዳዮቻችን በአንድነት ስላሉት ሁሉ ይህን እላለሁ፣ ጉዳዮችን ሁሉ በፍጥነት እና በትክክለኛው አኳኋን በሚያከናውኑ እና ንብረቶችን በመሸጥ ወይም ጉዳዩ አስፈላጊ በሚሆንበት ወይም ጉዳዩ እንደሚፈቅደው በጊዜውም እዳዎቼን ሁሉ እንዲሰረዙ ለሚያደርጉ ወኪሎች እና ጸሀፊዎች ጉዳዮቼን ትቼአቸዋለሁ። ማእበሉ እንዳለፈ ባወቅሁ ጊዜ፣ ከዚያም ወደ እናንተ ዳግሞ እመለሳለሁ።

፪ እንዳልፍባቸው ስለተጠራሁባቸው [ሀ]አደገኛ ነገሮችም፣ ለእኔ እንደ ጥቂት ነገር ነው የሚመስሉኝ፣ የሰው [ለ]ቅናት እና ቁጣ በህይወቴ ቀናት ሁሉ የየጊዜው እድሌ ነበርና፤ እና እናንተም ልትጠሩት በምትመርጡት ከምድር መመስረት በፊት ለመልካም ወይም ለመጥፎ አላማ [ሐ]የተሾምኩኝ ካልሆነ በስተቀር፣ ይህ በምን እንደሚከሰት ሚስጥር ይመስላል። ለራሳችሁም ፍረዱ። መልካምም ይሁን መጥፎ፣ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያውቃል። ይህም ቢሆን ግን፣ ለመዋኘት የምፈልግበት ጥልቅ ውሀ ነው። ለእኔ ሁለተኛ ህይወት ሆኖልኛል፤ እና እንደ ጳውሎስ [መ]በመከራዎች እደሰታለሁ፤ እስከዚህም ቀን ድረስ የአባቶቼ አምላክ ከሁሉም አድኖኛልና፣ እና ከዚህም በኋላ ያድነኛልና፤ እነሆ እናም አስተውሉ፣ ጠላቶቼን ሁሉ አሸንፋለሁ፣ ጌታ አምላክ ተናግሮታልና።

፫ ቅዱሳን ሁሉ ይደሰቱ፣ እና ከመጠንም በላይም ይደሰቱ፤ የእስራኤል [ሀ]አምላክ አምላካቸው ነውና፣ እና በሚጨቁኗቸው ራሶች ላይ ሁሉ የጽድቅን ብድራት መዝኖ ይሰጣቸዋል።

፬ ደግሞም፣ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፥ [ሀ]የቤተመቅደሴ ስራ፣ እና የመደብኩላችሁ ስራ ሁሉ ይቀጥሉ እና አያቁሙ፤ እና [ለ]ትጋታችሁ እና የፅናት ስራዎቻችሁ፣ እና ትእግስታችሁ፣ እና ስራዎቻችሁ ይጠንክሩ፣ እና ዋጋችሁን አታጡም ይላል የሰራዊት ጌታ። እና [ሐ]ከጨቆኗችሁም፣ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እና ጻድቅ ሰዎችን ጨቁነው ነበር። ለዚህም ሁሉ በሰማይ ደመወዝ አለና።

፭ ደግሞም፣ [ሀ]ስለሙታናችሁ [ለ]ጥምቀት በሚመለከት መልእክትን እሰጣችኋለሁ።

፮ በእውነት ስለሙታናችሁ በሚመለከት ጌታ እንዲህ ይላል፥ ማንኛችሁም ለሙታናችሁ [ሀ]ስትጠመቁ፣ [ለ]ዘጋቢ ይኑር፣ እና እርሱም ለጥምቀቶቻችሁ የአይን ምስክር ይሁን፤ ስለእውነት ይመስክር ዘንድ በጆሮዎቼም ይስማ፣ ይላል ጌታ፤

፯ [ሀ]መዛግብቶቻችሁን በሚመለከትም በሰማይ ውስጥ ይመዘገባሉ፤ በምድር

፻፳፯ ፩ ሀ ኢዮብ ፪፥፫፤
ማቴ. ፭፥፲–፲፪፤
፩ ጴጥ. ፪፥፳–፳፫።
፪ ሀ መዝ. ፳፫።
ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅናት።
ሐ ቅ.መ.መ. ቀድሞ መመረጥ።
መ ፪ ቆሮ. ፮፥፬–፭።
ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩፥፲፪–፲፬።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፶፭።
ለ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ሐ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣ መሳደድ።
፭ ሀ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
ለ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—ለሙታን መጠመቅ።
፮ ሀ ፩ ቆሮ. ፲፭፥፳፱፤
ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፲፫፣ ፲፰።
ለ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፪–፬፣ ፯።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።

[ለ]የሚታሰረው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የሚፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል፤

፰ [ሀ]ክህነትን በሚመለከት፣ በምድር ላይ ብዙ ነገሮችን [ለ]ዳግም ልመልስ ነውና፣ ይላል የሰራዊት ጌታ።

፱ ደግሞም፣ በቅዱስ ቤተመቅደሴ [ሀ]የመዝገብ ማከማቻ ውስጥ እንዲቀመጡ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድም በማስታወሻነት ይቀመጡ ዘንድ መዛግብት በስርዓት ይጠበቁ፣ ይላል የሰራዊት ጌታ።

፲ ለቅዱሳን ሁሉ እላለሁ፣ በሚቀጥለው ሰንበት ስለሙታን የመጠመቅን ርዕስ በመስበኪያው ቆሜ እነርሱን ለማነጋገር በጣም ታላቅ የሆነ ፈቃድ አለኝ። ነገር ግን ይህ ከእኔ ሀይል ውጪ ሆኖ ሲገኝ፣ ስለዚህ ርዕስ እና ስለሌሎች ብዙ ነገሮችም፣ የጌታን ቃል ከጊዜ ወደጊዜ እፅፋለሁ፣ እና በፖስታም እልክላችኋለሁ።

፲፩ ጊዜ ስለሌለኝ፣ አሁን ለጊዜው ደብዳቤዬን በዚሁ እፈፅማለሁ፤ ጠላት ዝግጁ ነውና፣ እና አዳኞችን እንዳለውም፣ የዚህ አለም [ሀ]ገዢ ይመጣል፣ ነገር ግን በእኔ ላይ አንዳች የለውም።

፲፪ እነሆ፣ ለእግዚአብሔር የምጸልየው እናንተ ትድኑ ዘንድ ነው። እና እንደ ጌታ አገልጋይ፣ እንደ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነቢይ እና [ሀ]ባለራዕይ ራሴን አቀርባለሁ።

ጆሴፍ ስሚዝ።

ክፍል ፻፳፰

ከነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ለየኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ስለሙታን ጥምቀት ተጨማሪ መመሪያን የያዘ፣ በመስከረም ፮፣ ፲፰፻፵፪ (እ.አ.አ.) በናቩ የተጻፈ ደብዳቤ።

፩–፭፣ የአካባቢ እና አጠቃላይ መዛግብት ስለሙታን መጠመቅ መከናወን ማረጋገጥ አለባቸው፤ ፮–፱፣ ዘገባዎቹም የሚያስተሳስሩ ናቸው እና በምድር እናም በሰማይ የተመዘገቡ ናቸው፤ ፲–፲፬፣ የማጥመቂያ ገንዳው የመቃብር ተምሳሌት ነው፤ ፲፭–፲፯፣ ኤልያስ ከሙታን ጥምቀት ጋር ተዛማጅነት ያለውን ሀይልን ዳግም መለሰ፤ ፲፰–፳፩፣ ያለፉት ዘመናት ቁልፎች፣ ሀይላት፣ እና ስልጣናት ሁሉ ዳግም ተመልሰዋል፤ ፳፪–፳፭፣ አስደሳች እና የከበረ ምስራች ለህያው እና ለሙታን ታውጇል።

፩ ስፍራዬን ትቼ ከመሄዴ በፊት ከጊዜ ወደጊዜ እንደምፅፍላችሁ እና ብዙ ርዕሶችን በሚመለከት መግለጫዎች እንደምሰጣችሁ እንዳመለከትኳችሁ፣ በጠላቶቼ እየተሰደድኩኝ እያለሁ፣ ርእሱ በአዕምሮዬ ውስጥ ስላለ እና በስሜቴ ላይ በብርቱም ስለሚገፋፋኝ፣ ስለሙታን [ሀ]መጠመቅ ርዕስ እቀጥላለሁ።

፪ ዘጋቢውን በሚመለከት ጥቂት የራዕይ ቃላትን ፅፌላችኋለሁ። ይህን ርዕስ በሚመለከት አሁን የማረጋግጣቸው ጥቂት ተጨማሪ አስተያየቶች አሉኝ። ያም፣ ከዚህ በፊት በደብዳቤዬ እንደገለፅኩት፣ የአይን ምስክር የሚሆን፣ እና በጆሮዎቹ ሰምቶ

፯ ለ ቅ.መ.መ. ማተም፣
ማስተሳሰር።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. የመልከ
ጼዴቅ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. የወንጌል
ዳግም መመለስ።
፱ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥፳፬።
፲፩ ሀ ዮሐ. ፲፬፥፴፤
ጆ.ስ.ት. ዮሐ. ፲፬፥፴
(ተጨማሪ)።
ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፻፳፭።
ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
፻፳፰ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ—ለሙታን
መጠመቅ።

በጌታ ፊት እውነትን ይመዝገብ ዘንድ [ሀ]ዘጋቢ ማስፈለጉን ነው።

፫ አሁን፣ ከዚህ ጉዳይ ጋር በሚገናኝም፣ ለአንድ ዘጋቢ በሁሉም ጊዜያት ለመገኘት እና ሁሉንም ስራዎች ያከናውን ዘንድ አዳጋች መሆኑን ነው ይህን ችግር ለማስወገድ፣ በእያንዳንዱ ከተማው ዎርዶች የስብሰባ መዛግብትን ያለስህተት ለመጻፍ ብቁ የሆነ ዘጋቢ ለመመደብ ይቻላል፤ እና ቃል ጉባኤውን ለመጻፍም፣ በአይኑ እንዳያቸውና በጆሮዎቹ እንደሰማቸው፣ ቀናትን፣ ስሞችን፣ እና ሌሎችን፣ እና የጉዳይን ሁሉ ታሪኮችን በመመዝገብ፣ መዝገቡን በማረጋገጥ በጣም ጥንቁቅ እና ትክክለኛ ይሁን፤ እሰጣችኋለው፤ በሁለት ወይም በሶስት አንደበት [ሀ]ምስክርነት ሁሉም ቃል ይጸና ዘንድ በዚያ ከነበሩም፣ በሚጠሩበት በማንኛውም ጊዜ ይህን ለማረጋገጥ የሚችሉ የነበሩትን ሶስት ግለሰቦችን ስም ይጻፍም።

፬ ከዚያም፣ ዘገባው እውነት እንደሆነ የሚያስረዳ የፈረመባቸውን የምስክር ወረቀቶች የሚቀበል አጠቃላይ ዘጋቢም ይኑር። ከዚያም የ ቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ዘጋቢ በአጠቃላይ በ ቤተክርስቲያኗ መፅሀፍ ውስጥ ከምስክር ወረቀቶች እና ከነበሩት ምስክሮች ጋር በቤተክርስቲያኗ የተመደቡትን ሰዎች አጠቃላይ ጸባይ እውቀቱን በመጠቀም የተጻፈውን መዝገብ እውነትኛነት እና መዛግብቱም እውነት እንደሆኑ እንደሚያምንም ሊፅፋቸው ይችላል። እና ይህም በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኗ መፅሀፍ ውስጥ ሲደረግ፣ መዝገቡም ቅዱስ ይሆናል፣ እና ስነስርዓቱም ልክ በአይኖቹ እንዳያቸው፣ በጆሮዎቹ እንደሰማቸው፣ እና በአጠቃላይ በቤተክርስቲያኗ መፅሀፍ ውስጥም እንደመዘገባቸው ይሆናል።

፭ የእነዚህን ነገሮች ስርዓት በጣም የተለየ ነው በማለት ታስቡ ይሆናል፤ ነገር ግን ይህም የወንጌሉ [ሀ]እውቀት ሳይኖራቸው ለሞቱት ለሙታን [ለ]ደህንነት ጌታ ከአለም መመስረት በፊት የሾመውን እና ያዘጋጀውን ስርዓት እና ዝግጅትን በመከተል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማሟላት ብቻ እንደሆነ ልንገራችሁ።

፮ በተጨማሪም፣ በራዕይ ፳፥፲፪ ውስጥ ተመዝግቦ እንደምታገኙት፣ ባለራዕዩ ዮሐንስ ስለሙታን ርዕስ ሲያሰላስል እንዲህ ነበር ያወጀው—*ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በእግዚአብሔር ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ።*

፯ በዚህ ጥቅስ ውስጥም መፅሀፍት ተከፍተው እንደነበርም ታገኛላችሁ፤ እና ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም [ሀ]የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባቸው፤ በዚህም ምክንያት፣ የተነገረላቸውም መፅሀፍት ስራዎቻቸውን ዘገባ የያዙ መሆን አለባቸው፣ እና በምድር ላይ ተጠብቀው ያሉትን [ለ]መዛግብት የሚጠቅስ ነው። እና የህይወት መፅሀፍ የሆነው መፅሀፍም በሰማይ ውስጥ የተጻፈው መዝገብ ነው፤ ይህም መሰረታዊ መርህ ስፍራዬን ትቼ ከመሄዴ በፊት በላኩላችሁ ደብዳቤ ውስጥ የነበረው ትእዛዝ ከሰጣችሁ ራዕይ ጋር በግልፅም ይስማማል—መዛግብቶቻችሁ ሁሉ በሰማይ የተመዘገቡ ናቸው።

፰ አሁን፣ ለዚህ ስነስርዓት መሰረት የሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ አማካይነት የሚገኘው የክህነት [ሀ]ሀይል ነው፣ በዚህም በምድር [ለ]የምታስሩት ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ እና በምድርም የፈታችሁ ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል። ወይም፣

፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፯፥፮።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. ምስክር።
፭ ሀ ፩ ጴጥ. ፬፥፮።
ለ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
፯ ሀ ራዕ. ፳፥፲፪፤ ት. እና ቃ. ፻፳፯፥፮–፯። ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
ለ ት. እና ቃ. ፳፩፥፩።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. ሀይል፤ ክህነት።
ለ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።

በሌላ ቃላት፣ የትርጉሙን ሌላ አስተያየት በመውሰድ፣ በምድር የመዘገባችሁት ሁሉ በሰማይ የተመዘገበ ይሆናል፣ እና በምድርም የማትመዘግቡትም ሁሉ በሰማያት አይመዘገብም፤ [ሐ]ለደህንነታቸው እግዚአብሔር አለም ከመፈጠሩ በፊት ባዘጋጀው [መ]ስርዓት መሰረት፣ ስለሙታናቸው በተጠበቁት መዛግብቶቻቸው መሰረት እነዚህን ስነስርዓቶች ለራሳቸው ወይም በወኪላቸው ቢያከናውኑትም፣ ከመጻህፍቱ መሰረት፣ ሙታናችሁ እንደ ስራቸው ይፈረድባቸዋል።

፱ የተነጋገርንበት—በምድር የሚመዘገበው ወይም የሚያስረው እና በሰማይ የሚያስረው ሀይል ለአንዳንዱ በጣም ደፋር የሆነ ትምህርት ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ በአለም ዘመናት ሁሉ፣ ጌታ ለማንም ሰው፣ ወይም ለተለያዩ ሰዎች፣ በእውነት ራዕይ የክህነት [ሀ]ዘመንን በሚሰጥበት በማንኛውም ጊዜ ይህ ሀይል ዘወትር ይሰጣል። ከዚህ በኋላ፣ [ለ]በስልጣን፣ በጌታ ስም፣ እነዚህ ሰዎች ምንም ቢያደርጉ፣ እና በእውነት እና በታማኝነት ቢያደርጉት፣ እና የእነዚህን ትክክለኛ እና የታመኑ መዛግብትን ቢጠብቁ፣ በምድር ላይ እና በሰማያት ውስጥ ህግ ይሆናል፣ እና በታላቁ [ሐ]ያህዌህ ህግጋት መሰረት ሊሰረዝም አይችልም። ይህም የታመነ አባባል ነው። ማን ይሰማዋል?

፲ ደግሞም፣ አስቀድሞ ስለተፈጸመው፣ ማቴዎስ ፲፮፥፲፰፣ ፲፱፥ *እኔም እልሀለሁ፣ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፣ የሲዖል ደጆችም አያሸንፏትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሀለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፣ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።*

፲፩ አሁን የዚህ ጉዳይ ታላቅ እና የከበረው ሚስጥር፣ እና በፊታችን የተዘረጋው እጅግ የላቀው መልካም ነገር የቅዱስ ክህነት ሀይላትን በማግኘት ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህ [ሀ]ቁልፎች ለተሰጡትም ለእርሱ ስለሰው ልጆች፣ ስለሙታን እና ህያዋን [ለ]ደህንነት በሚመለከት ተጨባጭ እውቀትን ለማግኘት ችግር አይኖርም።

፲፪ በዚህም ውስጥ [ሀ]ግርማ እና [ለ]ክብር፣ [ሐ]ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት አለ—የውሀ ጥምቀት ስነስርዓት፣ በዚህም በሞት ምሳሌነት [መ]መጥለቅ፣ አንዱ መሰረታዊ መርህ ከሌላው ጋር እንዲስማማ፤ በውሀ ውስጥ መጠለቅና ከውሀው መውጣት እንደ ሟች ከመቃብር በትንሳኤ በሚነሱበት ምሳሌ ነው፤ ከዚህ በኋላም፣ ይህ ስነስርዓት የተመሰረተውም እንደ ሞት አምሳል የሆነው የሙታን ጥምቀት ስነስርዓትን ግንኙነት ለመስራት ነው።

፲፫ በዚህም ምክንያት፣ [ሀ]የማጥመቂያ ገንዳው የተመሰረተው በመቃብር [ለ]አምሳል ሲሆን በዝቅተኛ ስፍራም የሚቀመጥ ሆኖ፣ እና አንዱም ከሌላው ጋር ይወያይ ዘንድ ለህያዋንም ሆነ ለሙታን ሁሉም ነገር አምሳያ እንዳለው ለማሳየት ህያዋን እንዲሰበሰቡ የታዘዙበት ስፍራ ነው—ጳውሎስ እንዳወጀውም፣ ምድራዊው ከሰማያዊ ጋር ይስማማ ዘንድ ነው፣ ፩ ቆሮንቶስ ፲፭፥፵፮፣ ፵፯፣ እና ፵፰፥

፲፬ *ነገር ግን አስቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያ አይደለም። የፊተኛው ሰው ከምድር ምድራዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ የመጣ ጌታ ነው። ምድራዊው እንደ ሆነ ምድራዊ የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው፥ ሰማያዊው እንደ ሆነ ሰማያዊ የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው።* በእው

፰ ሐ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
መ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
፱ ሀ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ለ ቅ.መ.መ. ስልጣን።
ሐ ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. ክብር።
ለ ቅ.መ.መ. ክብር።
ሐ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
መ ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣ መጥመቅ—በማጥለቅ መጥመቅ።
፲፫ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፳፱።
ለ ቅ.መ.መ. ምሳሌዎች።

ነትም የተመዘገቡት፣ የዚያንም ሙታናችሁን በሚመለከትም ምድራዊ መዛግብት እንዳሉ ሁሉ፣ የሰማያዊ መዛግብትም ይኖራሉ። ስለዚህ ይህም [ሀ]የሚያትም እና የሚያስተሳስር ሀይል ነው፣ እና ቃሉም በአንድ ትርጉም፣ [ለ]በእውቀት [ሐ]ቁልፍ ላይ የተመሰረቱ የመንግስት ቁልፎች ናቸው።

፲፭ አሁንም፣ ውድ ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ [ሀ]ደህንነታችንን በሚመለከትም፣ እነዚህ ሙታንንና ህያዋንን የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆች በቀላል እንደማይታለፉ ላረጋግጥላችሁ። ደህንነታቸውም ለእኛ ደህንነት አስፈላጊ እና መሰረታዊ ነው፣ ጳውሎስ ስለአባቶች እንዳለው—ያለ እኛ ፍጹማን ሊሆኑ አይችሉም—ወይም እኛ ያለሙታኖቻችን [ለ]ፍጹም ልንሆን አንችልም።

፲፮ አሁንም፣ የሙታን ጥምቀት በሚመለከት፣ ሌላ የጳውሎስን ጥቅስ እሰጣችኋለሁ፣ ፩ ቆሮንቶስ ፲፭፥፳፱፥ *እንዲያማ ካልሆነ፣ ስለ ሙታን የሚጠመቁ ምን ያደርጋሉ? ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ፣ ስለ እነርሱ የሚጠመቁ ስለ ምንድር ነው?*

፲፯ ደግሞም፣ ከዚህ ጥቅስ ጋር በተገናኘ አይኑን በክህነት ስልጣን [ሀ]ዳግም መመለስ ላይ፣ በመጨረሻዎቹ ቀናት ላይ ለሚገለጡት ክብሮች፣ እና ከሁሉም ርእሶች በላይ የከበረው ይህ፣ እንዲሁም ለሙታን መጠመቅ በዘለአለም ወንጌል ክፍል ስለሆነው ትኩረትን ሰጥቶት ከነበረው ከነብያቱ የአንዱን ጥቅስ እሰጣችኋለሁ፤ በመጨረሻው ምዕራፍ፣ አንቀፅ ፭ እና ፮ ውስጥ ሚልክያስ እንዳለው፥ *እነሆ፣ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን [ለ]ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፣ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።*

፲፰ ለዚህም [ሀ]ግልጽ የሆነ ትርጉም ለመስጠት በቻልኩ ነበር፣ ነገር ግን እንዳለም አላማዬን ያሟላ ዘንድ ይህ በቂ ነው። በዚህ ጉዳይ፣ በአባቶች እና ልጆች መካከል በአንድ በተወሰነ ርዕስ ወይም በሌላ፤ አንድ ወይም ሌላ የሚያስተሳስር [ለ]ግንኙነት ከሌለ ምድር በእርግማን እንደምትመታ ማወቁ በቂ ነው—እና እነሆ ያ ርዕስ ምንድን ነው? ይህም ለሙታን [ሐ]መጠመቅ ነው። ያለእነርሱ ፍጹም ልንሆን አንችልም፤ ወይም እነርሱም ያለእኛ ፍጹማን ሊሆኑ አይችሉም። እነርሱም ይሁን እኛ በወንጌሉ ካልሞቱት በስተቀር ፍጹም ልንሆን አንችልም፤ አሁን መግባት በጀመረው [መ]የዘመን ፍጻሜ መግቢያ ውስጥ ሙላት እና የተፈጸመ እና ፍጹም አንድነት፣ እና ከአዳም ቀናት እስከ አሁን የተገለጡት የዘመናት፣ ቁልፎች፣ እና ሀይላት፣ እና ክብሮች መተሳሰራቸው አስፈላጊ ነውና። እና ይህም ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ከዚህ ምድር [ሠ]መመስረት ጀምሮ ያልተገለጡት፣ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ተሰውረው የነበሩት፣ እነዚያ ነገሮች [ረ]ለህጻናት እና ለሚጠቡት በዚህ በዘመን ፍጻሜ ይገለጣሉ።

፲፱ አሁን፣ በተቀበልነው ወንጌል ውስጥ ምን እንሰማለን? የደስታ ድምፅ! የምህረት ድምፅ ከሰማይ፤ እና ከምድር ውስጥም [ሀ]የእውነትን ድምፅ፤ የምስራች ዜና ለሙታን፤ ከህያውና ከሙታን የደስታ ድምፅ፤ የታላቅ ደስታን [ለ]የምስራች ነው። የምስራች የሚናገር፣ ሠላምን የሚያወራ፣ የመልካምን ወሬ የምስራች የሚናገር፣ ስለመ

፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
ለ ጆ.ስ.ት. ሉቃ. ፲፩፥፶፫ (ተጨማሪ)።
ሐ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፲፭ ሀ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
ለ ዕብ. ፲፩፥፵። ቅ.መ.መ. ፍጹም።
፲፯ ሀ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
ለ ፫ ኔፊ ፳፭፥፭–፮፤ ት. እና ቃ. ፪፤ ፻፲፥፲፫–፲፮። ቅ.መ.መ. ኤልያስ።
፲፰ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፮–፴፱።
ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች—የወኪል ስነስርዓት፤ የትውልድ ሐረግ።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፳፰–፴፮፤ ፻፳፯፥፮–፯።
መ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ሠ ት. እና ቃ. ፴፰፥፲፫።
ረ ማቴ. ፲፩፥፳፭፤ ሉቃ. ፲፥፳፩፤ አልማ ፴፪፥፳፫።
፲፱ ሀ መዝ. ፹፭፥፲–፲፩።
ለ ሉቃ. ፪፥፲።

ዳን የሚያወራ፣ ፅዮንንም አምላክሽ ነግሶ አል! የሚል ሰው [ሐ]እግሮቹ በተራሮች ላይ እጅግ እንዴት ያማሩ ናቸው። እንደ ቀር ሜሎስ [መ]ጠል፣ እንደዚህም የእግዚአብሔር እውቀት በእነርሱ ላይ ያርፋል!

፳ ደግሞም፣ ምን እንሰማለን? [ሀ]ከከሞራ የደስታ ዜና! የሰማይ መልአክ [ለ]ሞሮኒ የነቢያትን ፍጻሜ—የሚገለጠውን [ሐ]መፅሀፍ ሲያውጅ። የጌታም ድምፅ [መ]በፈየት፣ በሰነካ የግዛት ክፍል ዱር ውስጥ ሶስቱ ምስክሮች ስለመፅሐፉ [ሠ]እንዲመሰክሩ ሲያውጅ! [ረ]የሚካኤል ድምፅም በሰስኳሀና ወንዝ ዳር ዲያብሎስን እንደ [ሰ]ብርሀን መልአክ ሲቀርብ በማየት ሲመረምር! [ሸ]የጴጥሮስ፣ የያዕቆብ፣ እና የዮሐንስ ድምፅ በበረሀ ውስጥ በሀርመኒ፣ ሰስኳሀና የግዛት ክፍል ውስጥ እና በኮልስቪል፣ ብሩም የግዛት ክፍል ውስጥ በሰስኳሀና ወንዝ ላይ ራሳቸውን እንደ መንግስት እና እንደ ዘመን ፍጻሜ [ቀ]ቁልፎች ያዡ በመግለፅ ሲያውጁ!

፳፩ ደግሞም፣ በአረጋዊው [ሀ]አባት ዊትመር ቤት ውስጥ በፈየት፣ ሰነካ የግዛት ክፍል ውስጥ እና በተለያዩ ጊዜያት፣ እና በተለያዩ ስፍራዎች በየኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጉዞዎች እና ፈተናዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ድምፅ! እና ሚካኤል የመላእክት አለቃ ድምፅ፤ [ለ]የገብርኤል፣ [ሐ]የሩፋኤል፣ እና የተለያዩ [መ]መላዕክት፣ ከሚካኤል ወይም [ሠ]ከአዳም እስከ አሁን [ረ]ዘመን ድረስ፣ በትዕዛዝ ላይ ትዕዛዝ፣ [ሰ]በስርዐት ላይ ስርዐትን፣ ጥቂት በዚህ፣ ጥቂት በዚያ በመስጠት፤ ወደፊት የሚመጣውን በማወጅ፣ [ሸ]ተስፋችንን በማረጋገጥ፣ ማፅናኛ በመስጠት፣ ሁሉም ዘመኖቻቸውን፣ መብቶቻቸውን፣ ቁልፎቻቸውን፣ ክብሮቻቸውን፣ ምስጋናዎቻቸውን፣ እና ክብሮቻቸውን፣ እና የክህነት ሀይሎቻቸውን ሲያውጁ ነው!

፳፪ ወንድሞች፣ ለዚህ ታላቅ ስራ ወደፊት አንሄድምን? ወደኋላ ሳይሆን ወደፊት ሂዱ። በርቱ፣ ወንድሞች፤ እና ወደ ድል ሂዱ! ልባችሁ ይደሰቱ፣ እና በጣምም ተደሰቱ። ምድርም በድንገት [ሀ]ትዘምር። ሙታንም ከአለም ፍጥረት በፊት ለተመደበው፣ [ለ]ከወህኒም [ሐ]እንድናድናቸው ስላስቻለን ለንጉስ [መ]አማኑኤል የዘለአለማዊ ምስጋና መዝሙርን ይናገሩ፤ እስረኞቹ በነጻ ይሄዳሉና።

፳፫ [ሀ]ተራሮችም በደስታ ይጮሁ፣ እና ሸለቆዎች ሁሉ በጎላ ድምፅ አልቅሱ፤ እና እናንተ ባህሮች እና ደረቅ ምድራት ሁሉ የዘለአለም ንጉሳችሁን አስደናቂነት ተናገሩ! እና እናንተ ወንዞች፣ እና ጅረቶች፣ እና ትንንሽ ወንዞችም በደስታም ፍሰሱ። የሜዳው ጫካዎች እና ዛፎች ሁሉ ጌታን ያመስግኑ! እና እናንተ ጠንካራ [ለ]አለቶችም በደስታ አልቅሱ። እና ጸሀይ፣ ጨረቅ፣ እና [ሐ]የአጥቢያ ኮከቦችም በአንድነት ዘምሩ፣ እና የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በደስታ እልል በሉ። እና ዘለአለማዊ ፍጥረቶችም ስሙን ለዘለአለም ያውጁ። ደግሞም እላለሁ፣ በጆሮዎቻችን ስለክብር፣ እና ደህን

፲፱ ሐ ኢሳ. ፶፪፥፯–፲፤
ሞዛያ ፲፭፥፲፫–፲፰፤
፫ ኔፊ ፳፥፵።
መ ዘዳግ. ፴፪፥፪፤
ት. እና ቃ. ፻፳፩፥፵፭።
፳ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፶፩–፶፪።
ቅ.መ.መ. የከሞራ ኮረብታ።
ለ ቅ.መ.መ. ሞሮኒ፣
የሞርሞን ልጅ።
ሐ ኢሳ. ፳፱፥፬፣ ፲፩–፲፬፤
፪ ኔፊ ፳፯፥፮–፳፱።
ቅ.መ.መ. መፅሐፈ ሞርሞን።
መ ቅ.መ.መ. ፈየት፣ ኒው
ዮርክ (ዮ.ኤስ.ኤ.)።
ሠ ት. እና ቃ. ፲፯፥፩–፫።
ረ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፩።
ቅ.መ.መ. አዳም።
ሰ ፪ ቆሮ. ፲፩፥፲፬።
ሸ ት. እና ቃ. ፳፯፥፲፪።
ቀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፳፩ ሀ ይህም ፒተር ዊትመር
ቀዳማዊ ማለት ነው።
ለ ቅ.መ.መ. ገብርኤል።
ሐ ቅ.መ.መ. ራፋኤል።
መ ቅ.መ.መ. መላእክት።
ሠ ት. እና ቃ. ፻፯፥፶፫–፶፮።
ረ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ሰ ኢሳ. ፳፰፥፲።
ሸ ቅ.መ.መ. ተስፋ።
፳፪ ሀ ኢሳ. ፵፱፥፲፫።
ለ ኢሳ. ፳፬፥፳፪፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፪–፸፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣
ማዳን፣ ቤዛነት።
መ ኢሳ. ፯፥፲፬፤
አልማ ፭፥፶።
ቅ.መ.መ. አማኑኤል።
፳፫ ሀ ኢሳ. ፵፬፥፳፫።
ለ ሉቃ. ፲፱፥፵።
ሐ ኢዮብ ፴፰፥፯።

ነት፣ እና [መ]ህያውነት፣ እና [ሠ]ስለዘለአለማዊ ህይወት፤ ስለመንግስታት፤ አለቅነትና ስልጣናት የሚያውጀው ከሰማያት የምንሰማው ድምጽ እንዴት የከበረ ነው!

፳፬ እነሆ፣ የጌታ ታላቅ [ሀ]ቀን ቀርቧል፤ እና ነገር ግን እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ነውና የሚመጣበትን ቀን [ለ]መታገሥ የሚችል ማን ነው? እርሱስ በተገለጠ ጊዜ የሚቆም ማን ነው? ለእግዚአብሔር በጽድቅ ቍርባንን ያቀርቡ ዘንድ፣ እርሱም ብርን [ሐ]እንደሚያነጥርና እንደሚያጠራ ሰው ይቀመጣል፥ [መ]የሌዊንም ልጆች ያጠራል፥ እንደ ወርቅና እንደ ብርም [ሠ]ያነጥራቸዋል። ስለዚህ፣ እንደ ቤተክርስቲያንና እንደ ህዝብ እና እንደ የኋለኛውም ቀን ቅዱሳን የፅድቅ ለጌታ [ረ]መጽዋዕትን እናቅርብ፤ እና በመጨረሻም በቅዱስ ቤተመቅደሱ ውስጥ፣ ለተቀባይነት ሁሉ ብቁ የሆነውን የሙታናችንን [ሰ]መዛግብት የያዘውን መፅሀፍ እናቅርብ።

፳፭ ወንድሞች፣ በዚህ ርዕስ ላይ የምላችሁ ብዙ ነገሮች አሉኝ፤ ነገር ግን ለጊዜው አበቃለሁ፣ እና ርዕሱንም በሌላ ጊዜ እቀጥላለሁ። እኔ፣ እንደ ወትሮው ሁሉ፣ ትሁት አገልጋያችሁ እና የማይቀየር ባልንጀራችሁ ነኝ፣

ጆሴፍ ስሚዝ።

ክፍል ፻፳፱

በየካቲት ፱፣ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) የአገልጋይ መላዕክት እና የመናፍስትን ትክክለኛ ተፈጥሮን ለመለየት የሚቻልበትን ሶስት ታላላቅ ቁልፎች ለማሳወቅ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የሰጣቸው መመሪያዎች።

፩–፫፣ ከሞት የተነሱ እና የመንፈስ አካላት በሰማያት ውስጥ አሉ፤ ፬–፱፣ ከመጋረጃው አልፈው የሚመጡ መልእክተኞችን ለይቶ የማወቂያ ቁልፎች ተሰጥተዋል።

፩ ሁለት አይነት [ሀ]የሰማይ ፍጥረታት አሉ፣ እነርሱም፥ [ለ]ከሞት የተነሱ ሰዎች፣ የስጋ እና የአጥንት አካል ያሏቸው [ሐ]መላዕክት—

፪ ለምሳሌ፣ ኢየሱስ፥ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ [ሀ]ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው።

፫ ሁለተኛ፥ ከሞት ያልተነሱ፣ ነገር ግን ያንን አይነት ክብር የሚወረሱ፣ ፍጹም የሆኑ [ሀ]የጻድቅ ሰዎች [ለ]መናፍስት።

፬ ከእግዚአብሔር መልእክት አለኝ ብሎ መልእክተኛ ሲመጣ፣ እጆቻችሁን ስጡት እና ከእናንተም እጆች ጋር እንዲጨባበጥ ጠይቁት።

፭ መልአክ ከሆነ ይህን ያደርጋል፣ እና እጁንም በመዳደስ ይሰማችኋል።

፮ ፍጹም የሆነ የጻድቅ ሰው መንፈስ ከሆነ በክብሩ ይመጣል፤ ሊመጣም የሚችልበት መንገድ ይህ ብቻ ነውና—

፯ ከእጆቻችሁም ጋር እንዲጨባበጥ ጠይቁት፣ ነገር ግን አይንቀሳቀስም፣ ምክንያቱም ይህ ፍጹም የሆነው ሰው ይታለል ዘንድ ከሰማይ ስርዓት ጋር የሚቃረን ነውና፤ ነገር ግን መልዕክቱን ያበስራል።

፳፫ መ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሚችነት።
ሠ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ሚል. ፫፥፩–፫።
ሐ ፫ ኔፊ ፳፬፥፪–፫።
ቅ.መ.መ. ምድር— ምድርን ማፅዳት።
መ ዘዳግ. ፲፥፰፤
ት. እና ቃ. ፲፫፤ ፻፳፬፥፴፱።
ሠ ዘካ. ፲፫፥፱።
ረ ት. እና ቃ. ፹፬፥፴፩።
ቅ.መ.መ. በኲራት።
ሰ ት. እና ቃ. ፻፳፯፥፱።
ቅ.መ.መ. የትውልድ ሐረግ።
፻፳፱ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ሰማይ።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሐ ቅ.መ.መ. መላእክት።
፪ ሀ ሉቃ. ፳፬፥፴፱።
፫ ሀ ዕብ. ፲፪፥፳፫፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፷፱።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈስ።

፰ [ሀ]ዲያብሎስ በብርሀን መልአክ አምሳል ቢሆን፣ እጆቻችሁንም እንዲጨብጥ ብትጠይቁት እጁንም ይሰጣችኋል፣ እና ምንም ነገር አይሰማችሁም፤ በዚህም ልታውቁት ትችላላችሁ።

፱ እነዚህም ከእግዚአብሔር የመጡ አገልግሎቶች እንደሆኑ ለማወቅ የምትችሉባቸው ሶስት ታላቅ ቁልፎች ናቸው።

ክፍል ፻፴

በሚያዝያ ፪፣ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) በራመስ ኢለኖይ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጡ የመመሪያ ነገሮች።

፩–፫፣ አብና ወልድ ለሰዎች በግል ሊገለጡ ይችላሉ፤ ፬–፯፣ መላዕክት በሰለስቲያል አለም ውስጥ ይኖራሉ፤ ፰–፱፣ ሰለስቲያላዊ ምድር ታላቅ ኡሪምና ቱሚም ትሆናለች፤ ፲–፲፩፣ ወደ ሰለስቲያል አለም ለሚገቡት ሁሉ ነጭ ድንጋይ ተሰጥቷል፤ ፲፪–፲፯፣ የዳግም ምፅዓት ጊዜ ከነቢያት ተሰውሯል፤ ፲፰–፲፱፣ በዚህ ህይወት የተገኘው የመረዳት ችሎታ በትንሳኤ ጊዜ አብሮን ይነሳል፤ ፳–፳፩፣ ሁሉም በረከቶች ህግን በማክበር ይመጣሉ፤ ፳፪–፳፫፣ አብና ወልድ የስጋ እና አጥንት አካል አላቸው።

፩ አዳኛችን በሚገለጥበት ጊዜ እርሱ እንዳለ [ሀ]እናየዋለን። እርሱም እንደ እኛው [ለ]ሰው እንደሆነም እናያለን።

፪ እና በዚህ በመካከላችን የሚገኘው ማህበራዊ ግንኙነት፣ አሁን የማናገኘውን ነገር ግን [ሀ]ዘለአለማዊ ክብር ተጨምሮበት፣ በዚያም እናገኘዋለን።

፫ ዮሐንስ ፲፬፥፳፫—በዚያ አንቀፅ ውስጥ [ሀ]የአብ እና [ለ]የወልድ መገለጥ፣ በተናጠል [ሐ]የታዩበት ነው፤ እና አብ እና ወልድ በሰው ልብ ውስጥ [መ]ያድራሉ የሚለው አስተሳሰብ የድሮ የሀይማኖት ቡድኖች ሀሳብ ነው፣ እና ሀሰትም ነው።

፬ የእግዚአብሔር [ሀ]ጊዜ፣ የመላዕክት ጊዜ፣ የነቢያት ጊዜ፣ እና የሰው ጊዜ አቆጣጠር እንደየሚኖሩበት ፕላኔት መሰረት አይደለም?—የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ

፭ አዎን ብዬም እመልሳለሁ። ነገር ግን ከዚህ ምድር የሆኑ ወይም የነበሩ ካልሆኑ በስተቀር፣ የሚያገለግሉ [ሀ]መላዕክት አይኖሩም።

፮ መላእክት ይህን ምድር በሚመስል ፕላኔት አይኖሩም።

፯ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት፣ በመስታወት እና [ሀ]እሳት [ለ]ባህር አለም ላይ፣ ሁሉም ነገሮች ጥንት፣ አሁን፣ እና ወደፊት ለክብራቸው በሚገለጥበት፣ እና ይህም በጌታ ፊት በሚቀጥልበት ሁኔታ ይኖራሉ።

፰ እግዚአብሔር የሚኖርበት ስፍራ ታላቅ [ሀ]ኡሪምና ቱሚም ነው።

፱ [ሀ]ምድር፣ በተቀደሰበት እና ዘለአለማዊ ሁኔታ በጥራት ትሰራለች እና በው

፰ ሀ ፪ ቆሮ. ፲፩፥፲፬፤ ፪ ኔፊ ፱፥፱።

፻፴ ፩ ሀ ፩ ዮሐ. ፫፥፪፤ ሞሮኒ ፯፥፵፰። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።

ለ ሉቃ. ፳፬፥፴፮–፵።

፪ ሀ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።

፫ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።

ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።

ሐ ት. እና ቃ. ፺፫፥፩።

መ ት. እና ቃ. ፻፴፥፳፪። ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።

፬ ሀ ፪ ጴጥ. ፫፥፰፤ አብር. ፫፥፬–፲፤ ደግሞም በአብር. ቅርፅ ፪፣ ስዕል ፩ን ተመልከቱ።

፭ ሀ ቅ.መ.መ. መላእክት።

፯ ሀ ኢሳ. ፴፫፥፲፬።

ለ ራዕ. ፬፥፮፤ ፲፭፥፪።

፰ ሀ ቅ.መ.መ. ኡሪም እና ቱሚም።

፱ ሀ ት. እና ቃ. ፸፯፥፩። ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር የመጨረሻ ሁኔታ።

ስጧም ለሚኖሩት እንደ ኡሪምና ቱሚም ትሆናለች፣ በዚህም የዝቅተኛውን መንግስት፣ ወይም የታችኛው ስርዓት መንግስታትን ሁሉ በሚመለከት ነገሮች ሁሉ በእዚያ ለሚኖሩበት ይገለጥላቸዋል፤ እና ይህች ምድርም የክርስቶስ ትሆናለች።

፲ ከዚያም በራዕይ ፪፥፲፯ ውስጥ የተጠቀሰው ነጭ ድንጋይም አንድ ለሚቀበለው ለእያንዳንዱ ሰው የመንግስት ከፍተኛውን ስርዓትን የሚመለከቱ ነገሮችን እንዲያው ቁባቸው የሚደረግበት ኡሪምና ቱሚም ይሆናል፤

፲፩ እና ወደ ሰለስቲያል መንግስት ለሚመጡትም ከሚቀበሉት በስተቀር ማንም የማያውቀው አዲስ [ሀ]ስም የሚጻፍበት [ለ]ነጭ ድንጋይ ለእያንዳንዱ ተሰጥቷል። አዲሱ ስምም እንደቁልፍ የሆነ ቃል ነው።

፲፪ የሰው ልጅ ከመምጣቱ በፊት ብዙ ደም መፋሰስን የሚያስከትሉ [ሀ]ችግሮች የሚጀምሩት [ለ]በደቡብ ኬሮላይና እንደሆነ በጌታ አምላክ ስም እተነብያለሁ።

፲፫ ይህም ምናልባት በባሪያ ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። በታህሳስ ፳፭፣ ፲፰፻፴፪ (እ.አ.አ.) ስለዚህ ርዕስ በቅንነት እየጸለይኩ ሳለሁ፣ ይህን ድምፅ አወጀልኝ።

፲፬ በአንድ ወቅት የሰውን ልጅ [ሀ]የምጻት ጊዜ ለማወቅ በቅንነት ስጸልይ ነበር፣ ድምፅም የሚከተለውን ሲደጋግም የሰማሁት፥

፲፭ ልጄ ጆሴፍ፣ ሰማንያ አምስት አመት እስኪሆንህ ብትኖር፣ የሰውን ልጅ ፊት ለማየት ትችላለህ፤ ስለዚህ ይህ ይብቃህ፣ እናም በዚህም ጉዳይ ከዚህ በላይ አታስቸግረኝ።

፲፮ ይህ የተጠቀሰው ምጽአት ስለአንድ ሺህ ዘመን መጀመሪያ ይሁን ወይም ከዚህ በፊት የሆነ መገለጥ ወይም መሞት እንዳለብኝ እና በዚህም ፊቱን የማይ እንደሆነም ለመወሰን ባለመቻል እንደዚህም ተትቼ ነበር።

፲፯ የሰው ልጅ መምጫ ከዚህ ጊዜ በፊት ቀድሞም እንደማይሆን አምናለሁ።

፲፰ በዚህ ህይወት የምናገኘው ማንኛውም [ሀ]የመረዳት ችሎታ መሰረታዊ መርህ፣ ይህም [ለ]ከሞት ስንነሳ አብሮን ይነሳል።

፲፱ እና አንድ ሰው [ሀ]በትጋቱ እና [ለ]በታዛዥነቱ ከሌላው ሰው በላይ ተጨማሪ [ሐ]እውቀትን እና የመረዳት ችሎታን በዚህ ህይወት ቢያገኝ፣ በሚመጣው አለምም ውስጥ በበለጠ [መ]የተሻለ ሁኔታ ይኖረዋል።

፳ ይህ አለም ከመመስረቱ [ሀ]አስቀድሞ ሁሉም [ለ]በረከቶች የሚመረኮዙበት በሰማያት ውስጥ ሊሻር የማይችል የታወጀ [ሐ]ህግ አለ—

፳፩ እና የትኛውንም በረከት ከእግዚአብሔር ስናገኝ፣ ሁሉም ነገር በተመረኮዘበት ለዚያ ህግ ታዛዥ በመሆን ነው።

፳፪ [ሀ]አብ እንደ ሰው ሊዳሰስ እና ሊጨበጥ የሚችል የስጋ እና አጥንት [ለ]አካል አለው፤ ወልድም ደግሞ እንዲሁ ነው፣ ነገር ግን [ሐ]መንፈስ ቅዱስ የስጋ እና አጥንት አካል የለውም፣ ነገር ግን የመንፈስ አካል ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ለመኖር ባልቻለ ነበር።

፳፫ ሰው [ሀ]መንፈስ ቅዱስን ሊቀበል ይችላል፤ እና በላዩም ሊወርድበትና አብሮትም ላይቆይ ይችላል።

፲፩ ሀ ኢሳ. ፷፪፥፪።
ለ ራዕ. ፪፥፲፯።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፳፱፤ ፵፭፥፷፫።
ለ ት. እና ቃ. ፹፯፥፩–፮።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፲፰ ሀ ቅ.መ.መ. እውቀተኛነት፣ እውቀተኛዎች።
ለ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
ሐ ቅ.መ.መ. እውቀት።
መ አልማ ፲፪፥፱–፲፩።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ቅድመ ምድራዊ ህይወት።
ለ ዘዳግ. ፲፩፥፳፮–፳፰፤ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፭። ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።
ሐ ት. እና ቃ. ፹፪፥፲።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ።
ለ የሐዋ. ፲፯፥፳፱።
ሐ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።

ክፍል ፻፴፩

በግንቦት ፲፮ እና ፲፯፣ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) በራመስ ኢሊኖይ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጡ መመሪያዎች።

፩–፬፣ የሰለስቲያል ጋብቻ ከፍ ባለው ሰማይ ዘለአለማዊ ክብር ለማግኘት አስፈላጊ ነው፤ ፭–፮፣ ሰዎች ለዘለአለም ህይወት እንዴት እንደታተሙ ተገልጿል፤ ፯–፰፣ መንፈስ ሁሉ ግዝፈት ያለው ነው።

፩ [ሀ]በሰለስቲያል ክብር ውስጥ ሶስት ሰማያት ወይም ደረጃዎች አሉ፤

፪ [ሀ]ከፍተኛውን ለማግኘት፣ ሰው ወደ እዚህ የክህነት ስርዓት መግባት አለበት [ይህም [ለ]አዲስ እና ዘለአለማዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን ማለት ነው]፤

፫ እና ይህን ባያደርግ፣ ሊያገኘው አይችልም።

፬ ወደሌሎቹ ለመግባት ይችላል፣ ነገር ግን ያም የሚያደርገው መጨረሻው መንግስቱ ነው፤ [ሀ]ተጨማሪም ሊያገኝ አይችልም።

፭ [ግንቦት ፲፯፣ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.)]። በተጨማሪ እርግጠኛ [ሀ]የትንቢት ቃል ማለት በራዕይ እና በትንቢት መንፈስ፣ በቅዱስ የክህነት ሀይል አማካይነት፣ ሰው [ለ]ለዘለአለም ህይወት [ሐ]እንደታተመ አውቋል ማለት ነው።

፮ ሰው [ሀ]በድንቁርና [ለ]ይድን ዘንድ አይችልም።

፯ ስለዚህ፣ ህልውና የሌለው ህልው ነገር የሚባል ነገር የለም። [ሀ]መንፈስ ሁሉ ህልውና ያለው ነው፣ ነገር ግን ይህም የጠራ እና ንጹህ ነው፣ እና ሰውም ሊለየው የሚችለው [ለ]በነጹ አይኖች ብቻ ነው፤

፰ እናየውም ዘንድ አይቻለንም፤ ነገር ግን ሰውነቶቻችን ሲነጹ ግዝፈት ያለው እንደሆነ ሁሉ እናያለን።

ክፍል ፻፴፪

በናቩ ኢሊኖይ ውስጥ በሐምሌ ፲፪፣ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) የተመዘገበው፣ ስለአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን፣ በተጨማሪም የጋብቻ ቃል ኪዳን ዘለአለማዊነትን እና ደግሞም ከአንድ በላይ ሚስቶችን ስለማግባት መሰረታዊ መርሆ በሚመለከት በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ምንም እንኳን ይህ ራዕይ በ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) የተመዘገበ ቢሆንም፣ ከዚህ ራዕይ ጋር የተገናኙ አንዳንድ መርሆች ለነቢዩ ከ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) መጀመሪያ ጀምሮ ታውቀው ነበር። አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩ን ተመልከቱ።

፩–፮፣ ዘለአለማዊ ክብር የሚገኘው በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ነው፤ ፯–፲፬፣ የዚህ ቃል ኪዳን ምልክት እና ቅድመ ሁኔታዎች ተሰጥተዋል፤ ፲፭–፳፣ ሰለስቲ

፻፴፩ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፸፮፥፸።
ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፭–፳፩።
ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
ለ ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—አዲስ እና ዘለአለማዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን።
፬ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፲፮–፲፯።
፭ ሀ ፪ ጴጥ. ፩፥፲፱።
ቅ.መ.መ. መጠራት እና መመረጥ።
ለ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
ሐ ት. እና ቃ. ፷፰፥፲፪፤ ፹፰፥፬።
ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፯፥፺፱–፻።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት።
፯ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፲፪፤ ፺፯፥፲፮፤ ሙሴ ፩፥፲፩።

ያል ጋብቻ እና የቤተሰብ ስብስብ ቀጣይነት ሰዎች አማልክት እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፤ ፳፩–፳፭፣ ቀጭኑ እና ጠባቡ መንገድ ወደዘለአለም ህይወት ይመራል፤ ፳፮–፳፯፣ መንፈስ ቅዱስን መስደብ በሚመለከት ህግ ተሰጠ፤ ፳፰–፴፱፣ የዘለአለማዊ እድገት እና ዘለአለማዊ ክብር ቃል ኪዳን ለሁሉም ዘመን ነቢያት እና ቅዱሳን ተደርገዋል፤ ፵–፵፯፣ ጆሴፍ ስሚዝ በምድር ላይ እና በሰማይ ውስጥ ለማሰር እና ለማተም ሀይል ተሰጠው፤ ፵፰–፶፣ ጌታ በእርሱ ላይ ዘለአለማዊ ክብር አተመበት፤ ፶፩–፶፯፣ ኤማ ስሚዝ ታማኝ እና እውነተኛ እንድትሆን ተመከረች፤ ፶፰–፷፮፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ሚስቶችን ስለማግባት የሚመሩ ህግጋት ተሰጥተዋል።

፩ በእውነትም ለአንተ አገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ ጌታ እንዲህ ይላል፣ እኔ ጌታ አገልጋዮቼን አብርሐምን፣ ይስሀቅን፣ እና ያዕቆብን፣ ደግሞም ሙሴን፣ ዳዊትን፣ እና ሰለሞንን ብዙ [ሀ]ሚስቶችና ዕቁባቶች የነበሯቸውን መሰረታዊ መርሆች እና ትምህርቶችን በሚመለከት እንዴት ከጥፋት ነጻ እንዳደረኳቸው እንዲገባህ እና ለማወቅ ከእጄ እንደጠየከኝ—

፪ እነሆ፣ እና አስተውል፣ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እና ይህን ጉዳይ በሚነካም መልስን እሰጥሀልሁ።

፫ ስለዚህ፣ ልሰጥህ ያሉትን መመሪያዎች ለመቀበል እና ለማክበር ልብህን [ሀ]አዘጋጅ፤ ይህ ህግ ለተገለጠላቸው ሁሉ ይህን ማክበር አለባቸውና።

፬ እነሆ፣ አዲስ እና ዘለአለማዊ [ሀ]ቃል ኪዳን ገልጬላችኋለሁና፤ እና ይህን ቃል ኪዳን ካልኖራችሁበት፣ ከዚያ [ለ]የተኮነናችሁ ናችሁ፣ ማንም ይህን ቃል ኪዳን [ሐ]ሊቃወምና እና ወደ ክብሬ ይገባ ዘንድ አይችልምና።

፭ ከእጄ በረከት የሚያገኙም ለዚያ [ሀ]በረከት የተመደበውን [ለ]ህግና አለም ከመመስረቷም በፊት በስራ ላይ የዋሉትን ቅድመ ሁኔታ ሊኖሩባቸው ያስፈልጋቸዋልና።

፮ እና [ሀ]አዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳንን በሚመለከት፣ በስራ ላይ የዋለው [ለ]ለክብሬ ሙላት ነበር፤ እና ይህን ሙላት የሚቀበል በህጉ ይኑር እና መኖርም አለበት፣ ወይም ይኮነናል፣ ይላል ጌታ አምላክ።

፯ እና እውነት እላችኋለሁ፣ የዚህ ህግ ቅድመ [ሀ]ሁኔታዎች እነዚህ ናቸው፥ በተቀባው፣ ለጊዜ እና ለዘለአለም፣ በዚህ ምድር ይህን ሀይል እንዲይዝ በመደብኩት (እና አገልጋዬ ጆሴፍን ይህን ሀይል በመጨረሻ ቀናት እንዲይዝ መድቤአለሁ እና የዚህ ክህነት ሀይል እና [ለ]ቁልፎች ይሰጠው ዘንድ የተገባ ከአንድ በላይ የለም) በእኔ በተቀባው በኩል [ሐ]በራዕይ እና በትዕዛዝ እና ከሁሉም በላይ በሆን [መ]የቅዱስ ተስፋ መንፈስ ያልተሰሩ፣ ያልገቡና [ሠ]ያልታተሙ ቃል ኪዳናት፣ ስምምነቶች፣ የተፈረመባቸው መረጃዎች፣ ግዴታዎች፣ [ረ]መሀላዎች፣ ስዕለቶች፣ ግንኙነቶች፣ ተባባሪነቶች፣ ወይም የሚጠበቅባቸው፣ በሙታን ትንሳኤ እና በኋላም ሁሉም ፍቱንነት፣ መልካምነት፣ ወይም ሀይል አይኖራቸውም፤ ለዚህም ውጤት ያልተገቡ ስምምነቶች ሰዎች በሞቱ ጊዜ መጨረሻው ይሆናል።

፰ እነሆ፣ ቤቴ የስርዓት ቤት ነው፣ ይላል ጌታ አምላክ፣ እና የግራ መግባት ቤት አይደለም።

፻፴፪ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፴፬፣ ፴፯–፴፱።
ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፳፱፥፰፤ ፶፰፥፮፤ ፸፰፥፯።
፬ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።
ለ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፴፩፥፩–፬።
፭ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፥፳–፳፩።
ለ ቅ.መ.መ. ህግ።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፷፮፥፪።
ቅ.መ.መ. አዲስ እና የዘለአለም ቃል ኪዳን።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፣ ፺፪–፺፮።
ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
፯ ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፴፰–፴፱።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ሐ ቅ.መ.መ. ራዕይ።
መ ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
ሠ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
ረ ቅ.መ.መ. መሀላ።

፱ በስሜ ያልተደረጉትን [ሀ]መስዋዕቶችን እቀበላለሁን? ይላል ጌታ።

፲ ወይም [ሀ]ያልመደብኩትን ከእጆቻችሁ እቀበላለሁን?

፲፩ እና እንዲሁም እኔ እና አባቴ ለእናንተ ከዚህ አለም በፊት [ሀ]እንደሾምነው፣ በህግ ካልሆነ በስተቀር፣ ይላል ጌታ፣ እመድብላችኋለሁን?

፲፪ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝ፤ እና ይህን ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ—በእኔ እና ህጌ በሆነው በቃሌ በቀር ወደ አብ [ሀ]የሚመጣ የለም፣ ይላል ጌታ።

፲፫ እና በአለም ያለው ሁሉም ነገር፣ በሰዎችም፣ ዙፋናት ወይም በጌትነት ወይም በአለቅነት ወይም በሥልጣናት ስም ባላቸው ነገሮች የተመደበ ቢሆንም፣ ምንም ቢሆኑ፣ በእኔ ወይም በቃሌ ካልሆኑ ይጣላሉ፣ ይላል ጌታ፣ እና ሰዎች ከሞቱም በኋላ፣ ወይም በትንሳኤ ወይም በኋላም እንዲሁ [ሀ]አይቀሩም፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፲፬ የሚቀሩትም ማናቸውም ነገሮች በእኔ ናቸው፤ እና በእኔ ያልሆኑትም ማናቸውም ነገሮች ይናወጣሉ እናም ይደመሰሳሉ።

፲፭ ስለዚህ፣ ሰው በአለም ውስጥ ሚስት [ሀ]ቢያገባ፣ እና በእኔ ወይም በቃሌ ባያገባት፣ እና በአለም እስካለም ድረስ ከእርሷ ጋር እና እርሷም ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ቢገቡ፣ ሲሞቱና ከአለም ሲለዩ ቃል ኪዳናቸውና ጋብቻቸው ሀይል አይኖራቸውም፤ ስለዚህ፣ ከአለም ሲለዩ በምንም ህግ አይታሰሩም።

፲፮ ስለዚህ፣ ከአለም ሲለዩ [ሀ]አያገቡም ወይም አይጋቡምም፤ ነገር ግን በሰማይ ውስጥ እንደ [ለ]መላእክት ይመደባሉ፣ እነዚህም መላእክት ከዚህም በላይ፣ እና በክብርን በዘለአለም እድገት ከሁሉ ይልቅ ብቁ ለሆኑት ረጂ አገልጋዮች ናቸው።

፲፯ እነዚህ መላእክት በህጋቴ አልኖሩምና፤ ስለዚህ፣ ሊያድጉ አይችሉም፣ ነገር ግን ተለያይተው እና በብቸኝነት፣ ከፍ ሳይደረጉ፣ በዳኑበት ሁኔታ ዘለአለማዊ ክብር ሳይኖራቸው ይቆያሉ፤ እና ከዚያም ጊዜ ጀምሮ አማልክት አይደሉም፣ ነገር ግን ለዘለአለም የእግዚአብሔር መላእክት ናቸው።

፲፰ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሰው ሚስት ቢያገባ፣ እና ለጊዜ እና ለዘለአለም ቃል ኪዳን ቢያደርግ፣ ያም ቃል ኪዳን በእኔ ወይም ህጌ በሆነው በቃሌ ባይጸና እና ለዚህ ሀይል በቀባሁት እና በመደብኩት በኩል በቅዱስ የተስፋ መንፈስ ያልታተመ ቢሆን፣ ከዚያም ከዚህ አለም ሲለዩ ጋብቻቸው ተቀባይነት ወይም ሀይል የለውም፣ ምክንያቱም በእኔ ወይም በቃሌ አልተሳሰሩምና፣ ይላል ጌታ፤ ከአለም ሲለዩም በዚያም ተቀባይነት አያገኝም ምክንያቱም በዚያ ሊያልፏቸው የማይችሉ መላእክት እና አማልክት ተመድበዋልና፤ ስለዚህ ክብሬን መውረስ አይችሉም፤ ቤቴ የስርዓት ቤት ነውና፣ ይላል ጌታ አምላክ።

፲፱ ደግሞም፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ህጌ በሆነው በቃሌ እንዲሁም [ሀ]በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ሰው ሚስትን ቢያገባ፣ እና ይህም በተቀባው፣ የዚህን ሀይል እና የዚህን ክህነት [ለ]ቁልፎች በመደብኩለት አማካይነት፣ በቅዱስ [ሐ]የተስፋ መንፈስ [መ]ይታተማል፤ እናም ለእነርሱም እንዲህ ይባላል—እናንተ በመጀመሪያው ትንሳኤ ትመጣላችሁ፤ እና ከመጀመሪያው ትንሳኤ በኋላም ቢሆን፣ በሚቀጥለው ትንሳኤ፤ እና [ሠ]ዙፋናት፣ መንግስታት፣ ጌትነቶች፣

፱ [ሀ] ሞሮኒ ፯፥ ፭–፮።
ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
፲ [ሀ] ዘሌዋ. ፳፪፥ ፳–፳፭፤
ሙሴ ፭፥ ፲፱–፳፫።
፲፩ [ሀ] ት. እና ቃ. ፻፴፪፥ ፭።
፲፪ [ሀ] ዮሐ. ፲፬፥ ፮።
፲፫ [ሀ] ፫ ኔፊ ፳፯፥ ፲–፲፩።
፲፭ [ሀ] ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት።
፲፮ [ሀ] ማቴ. ፳፪፥ ፳፫–፴፫፤
ማር. ፲፪፥ ፲፰–፳፭፤
ሉቃ. ፳፥ ፳፯–፴፮።
[ለ] ቅ.መ.መ. መላእክት።
፲፱ [ሀ] ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣ መጋባት—አዲስ እና ዘለአለማዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን።
[ለ] ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
[ሐ] ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፶፪–፶፫፤
፹፰፥ ፫–፬።
[መ] ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር።
[ሠ] ዘፀአ. ፲፱፥ ፭–፮፤
ራዕ. ፭፥ ፲፤ ፳፥ ፮፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፶፮፤
፸፰፥ ፲፭፣ ፲፰።

እና ሀይላት፣ አለቅነት፣ ሁሉንም ከፍታና ዝቅታን ይወርሳሉ—ከዚያም በበጉ [ረ]የህይወት መፅሀፍ ውስጥ ንጹህ ደም የማይፈስበት ግድያን እንደማይፈፅም ይጻፋል፤ እና በቃል ኪዳኔ ብትኖሩ፣ እና ንጹህ ደም የሚያፈስበትን ግድያ ባትፈጸሙ፣ በጊዜ እና በዘለአለም ሁሉ አገልጋዬ በእነርሱ ላይ የሚኖረው ማንኛውም ነገሮች ሁሉ ይደረጉላቸዋል፤ እና ከዚህ አለም ሲለዩም ሙሉ ሀይል ያለው ይሆናል፤ እና በዚያ በተቀመጡት በመላእክት እና አማልክት አልፈው፣ በራሳቸው ላይ እንደታተሙት በሁሉም ነገሮች ወደ [ሰ]ዘለአለማዊ ክብር እና ወደ ክብራቸው ይሄዳሉ፣ ይህም ክብር ለዘለአለም የሙላት እና ለዘራቸውም ቀጣይነት ያለው ይሆናል።

፳ ከዚያም እነርሱም አማልክት ይሆናሉ፣ ምክንያቱም መጨረሻ የላቸውምና፤ ስለሚቀጥሉም፣ በዚህም ከዘለአለም ወደዘለአለም የሚኖሩ ይሆናሉ፤ ከዚያም ሁሉም ነገሮች ለእነርሱ ተገዢ ስለሚሆኑ፣ ከሁሉም በላይ ይሆናሉ። ከዚያም [ሀ]ሁሉም ሀይል ስለሚኖራቸው፣ [ለ]አማልክት ይሆናሉ፣ እና መላእክትም ተገዢ ይሆኑላቸዋል።

፳፩ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ [ሀ]በህጌ ካልኖራችሁ በስተቀር ይህን ክብር አታገኙም።

፳፪ ወደ ዘለአለማዊ ክብር እና ወደ ቀጣይ [ሀ]ህይወት መቀጠል የሚወስደው ደጅ [ለ]የጠበበ፣ [ሐ]መንገዱም የቀጠነ ነውና፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፣ በዚህ አለም ስላልተቀበላችሁኝ አታውቁኝም።

፳፫ ነገር ግን በዚህ አለም ብትቀበሉኝ፣ ከዚያም ታውቁኛላችሁ፣ እና ዘለአለማዊ ክብራችሁንም ትቀበላላችሁ፤ እኔ [ሀ]ባለሁበት እናንተም ደግሞ ትሆናላችሁ።

፳፬ እውነተኛ እና የጥበብ አምላክ ብቻ የሆነውንና [ሀ]የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች [ለ]የዘለአለም ሕይወት ናት። እኔም እርሱ ነኝ። ስለዚህ ህጌን ትቀበላላችሁ።

፳፭ ወደ [ሀ]ሞት የሚመራው ደጅ [ለ]ሰፊ፣ እናም መንገዱም የሰፋ ነውና፤ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፣ ምክንያቱም [ሐ]አይቀበሉኝም ወይም በህጌም አይኖሩምና።

፳፮ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ሰው በቃሌ መሰረት ሚስት ቢያገባ፣ እና እኔም በመደብኩት መሰረት [ሀ]በቅዱስ የተስፋ መንፈስ ቢታተሙ፣ እና እርሱ ወይም እርሷ በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ላይ ምንም ኃጢአት ወይም መተላለፍ እና ሁሉንም አይነት መተላለፍ ባያደርጉ እና ንጹህንም ደም ለማፍሰስ [ለ]ባይገድሉ፣ በመጀመሪያው ትንሳኤ ይመጣሉ፣ እና ወደ ዘለአለማዊ ክብራቸውም ይገባሉ፤ ነገር ግን በስጋቸው የወደቁ ይሆናሉ፣ እና እስከ ቤዛም ቀን [ሐ]በሰይጣን እንዲጎሰሙ [መ]ይሰጣሉ፣ ይላል ጌታ።

፳፯ መንፈስ ቅዱስን [ሀ]መሳደብ ግን በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው [ለ]ስርየት የለውም፣ በዚያም አዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳኔን ከተቀበላችሁ በኋላ ንጹ

፲፱ ረ ቅ.መ.መ. የሕይወት መፅሐፍ።
ሰ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
፳ ሀ ት. እና ቃ. ፶፥ ፳፮–፳፱፤ ፸፮፥ ፺፬–፺፭፤ ፹፬፥ ፴፫–፴፱።
ለ ማቴ. ፳፭፥ ፳፩፤ ት. እና ቃ. ፳፱፥ ፲፪–፲፫፤ ፻፴፪፥ ፴፯። ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—የሰው እንደ እግዚአብሔር አይነት ለመሆን ያለው ችሎታ።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ህግ።
፳፪ ሀ ማቴ. ፯፥ ፲፫–፲፬፥ ፳፫፤ ፪ ኔፊ ፱፥ ፵፩፤ ፴፩፥ ፲፯–፳፩።
ለ ሉቃ. ፲፫፥ ፳፬፤ ፪ ኔፊ ፴፫፥ ፱፤ ሔለ. ፫፥ ፳፱–፴።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥ ፴–፴፩።
፳፫ ሀ ዮሐ. ፲፬፥ ፪–፫።
፳፬ ሀ ዮሐ. ፫፥ ፲፮–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፹፱፥ ፭።
ለ ዮሐ. ፲፯፥ ፫። ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ሞት።
ለ ማቴ. ፯፥ ፲፫–፲፬፤ ፫ ኔፊ ፲፬፥ ፲፫–፲፭።
ሐ ዮሐ. ፭፥ ፵፫።
፳፮ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱስ የተስፋ መንፈስ።
ለ አልማ ፴፱፥ ፭–፮።
ሐ ቅ.መ.መ. ዲያብሎስ።
መ ት. እና ቃ. ፹፪፥ ፳፩፤ ፻፬፥ ፱–፲።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. መስደብ፤ ይቅርታ የሌለው ኃጢያት።
ለ ማቴ. ፲፪፥ ፴፩–፴፪፤ ዕብ. ፮፥ ፬–፮፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፴፩–፴፭። ቅ.መ.መ. የጥፋት ልጆች።

ህን ደም በማፍሰስ የምትገድሉበት፣ እና በሞቴም የምትስማሙበት ነው፤ እና በዚህ ህግ የማይኖር ማንም ወደ ክብሬ ሊገባ አይችልም፣ ነገር ግን [ሐ]ይኮነናል፣ ይላል ጌታ።

፳፰ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እና ለአንተም ከአለም ፍጥረት በፊት በእኔ እና በአባቴ እንደተመደበ፣ የቅዱስ ክህነቴን ህግ እሰጥሀለሁ።

፳፱ [ሀ]አብርሐም በራዕይ እና ትእዛዝ፣ በቃሌ የተቀበለውን ሁሉንም ነገሮች ተቀበለ፣ እና ወደ ዘለአለማዊ ክብሩም ገብቷል እና በዙፋኑም ተቀምጧል ይላል ጌታ።

፴ አብርሐም ስለዘሩ እና ስለወገብም ፍሬው በሚመለከት [ሀ]ቃል ኪዳንን ተቀበለ—ከእርሱም [ለ]ወገብ፣ በስምም ከአገልጋዬ ዮሴፍ የመጣህ ነህ—እነዚህም በአለም ውስጥ እስከሚገኙ ድረስ ይቀጥላሉ፤ እና አብርሐምን እና ዘሩን በሚመለከት፣ ከአለም ውጪም ይቀጥላሉ፤ በአለም ውስጥ እና ከአለም ውጪም እንደ [ሐ]ከዋክብት በዝተውም ይቀጥላሉ፤ ወይም፣ በባህር ዳር ያለን አሸዋ ብትቆጥርም እነርሱን ልትቆጥራቸው አትችልም።

፴፩ ይህም ቃል ኪዳን ያንተም ነው፣ ምክንያቱም አንተ [ሀ]ከአብርሐም ነህና፣ እና ቃል ኪዳኑም ለአብርሐም ተሰርቶ ነበርና፤ እና በዚህ ህግም የአባቴ ስራ ይቀጥል ዘንድ፣ በዚህም እራሱን ያከብር ዘንድ ነው።

፴፪ ስለዚህ ሂድ እና የአብርሐምን [ሀ]ስራዎች አድርግ፤ ወደህጌም ግባ እናም ትድናለህ።

፴፫ ነገር ግን ወደ ህጌ ባትገባ ለአብርሐም የተገባውን የአባቴን ቃል ኪዳን አትቀበልም።

፴፬ እግዚአብሔር አብርሐምን [ሀ]አዘዘው እና [ለ]ሳራ ለአብርሐም [ሐ]አጋርን ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው። እና ይህን ለምን አደረገች? ምክንያቱም ይህም ህግ ነበር፤ እና ከአጋርም ብዙ ህዝብ ወጣ። ስለዚህ ይህም፣ ከሌሎች ነገሮች ጋር፣ ቃል ኪዳኖችን ያሟላ ነበር።

፴፭ ስለዚህ አብርሐም በኩነኔ ላይ ነበር? እውነት እላችኋለሁ፣ አልነበረም፤ እኔ ጌታ ይህን [ሀ]አዝዤአለሁና።

፴፮ አብርሐም ልጁን [ሀ]ይስሀቅን ለመስዋዕት እንዲያቀርብ [ለ]ታዝዞ ነበር፤ ይሁንእንጂ፣ [ሐ]አትግደል ተብሎ ተፅፎ ነበር። አብርሐም ግን እምቢ አላለም፣ እና ይህም [መ]እንደፅድቅ ተቆጠረለት።

፴፯ አብርሐም [ሀ]እቁባቶችን ተቀበለ፣ እና እነርሱም ልጆችን ወለዱለት፤ እና ይህም ለእርሱ እንደፅድቅ ተቆጥሮለታል፣ ምክንያቱም ለእርሱ ተሰጥተዋልና፣ እና በህጌም ኖሯል፤ ይስሀቅ እና [ለ]ያዕቆብም ከታዘዟቸው ነገሮች በስተቀር ምንም ሌላ ነገርን አላደረጉም፤ እና ከታዘዙትም ነገር ውጪ ምንም ሌላ ነገርን ስላላደረጉ፣ በቃል ኪዳኖች መሰረት [ሐ]ወደ ዘለአለማዊ ክብራቸው ገብተዋል፣ እና በዙፋናትም ተቀምጠዋል፣ እና መላእክት ሳይሆኑ አማልክት ናቸው።

፴፰ [ሀ]ዳዊትም [ለ]ብዙ ሚስቶች እና እቁባቶችን ተቀበለ፣ እና ከፍጥረት መጀመሪያ እስከዚህ ጊዜ ድረስ አገልጋዮቼም ሰለሞን እና ሙሴ፣ እና ብዙ ሌሎች አገልጋዮቼም

፳፯ሐ ቅ.መ.መ. ኩነኔ።
፳፱ ሀ ቅ.መ.መ. አብርሐም።
፴ ሀ ዘፍጥ. ፲፪፥፩–፫፤ ፲፫፥፲፮።
ቅ.መ.መ. አብርሐም—
የአብርሐም ዘር፤
የአብርሐም ቃል ኪዳን።
ለ ፪ ኔፊ ፫፥፮–፲፮።
ሐ ዘፍጥ. ፲፭፥፭፤ ፳፪፥፲፯።
፴፩ ሀ ት. እና ቃ. ፹፮፥፰–
፲፩፤ ፻፲፥፲፪።
፴፪ ሀ ዮሐ. ፰፥፴፱፤
አልማ ፭፥፳፬–፳፭።
፴፬ ሀ ዘፍጥ. ፲፮፥፩–፫።
ለ ቅ.መ.መ. ሳራ።
ሐ ዘፍጥ. ፳፭፥፲፪–፲፰።
ቅ.መ.መ. አጋር።
፴፭ ሀ ያዕቆ. ፪፥፳፬–፴።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. ይስሐቅ።
ለ ዘፍጥ. ፳፪፥፪–፲፪።
ሐ ዘፀአ. ፳፥፲፫።
መ ያዕቆ. ፬፥፭።
ቅ.መ.መ. ጻድቅ፣ ጽድቅ።
፴፯ ሀ ይህም ሌሎች ሚስቶች ማለት
ነው። ዘፍጥ. ፳፭፥፭–፮።
ለ ዘፍጥ. ፴፥፩–፬፤
ት. እና ቃ. ፻፴፫፥፶፭።
ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣
የይስሐቅ ልጅ።
ሐ ቅ.መ.መ. ሰው፣ ሰዎች—
የሰው እንደ እግዚአብሔር
አይነት ለመሆን ያለው
ችሎታ፤
ከፍተኛነት።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. ዳዊት።
ለ ፩ ሳሙ. ፳፭፥፵፪–፵፫፤
፪ ሳሙ. ፭፥፲፫፤
፩ ነገሥ. ፲፩፥፩–፫።

ደግመው ተቀበሉ፤ እና ከእኔም ዘንድ ካል ተቀበሏቸው ነገሮች በስተቀር፣ በምንም ኃጢአትን አልሰሩም።

፴፱ የዳዊት ሚስቶች እና እቁባቶች በአገልጋዬ በናታን እጅ እጅ እና የዚህ ሀይል [ሀ]ቁልፍ በተሰጣቸው በሌሎች ነቢያት እጅ አማካይነት ለእርሱ [ለ]የተሰጡት ከእኔ ዘንድ ነበር፤ እና [ሐ]ከኦርዮ እና ሚስቱ ጉዳይ በስተቀር በእነዚህ ነገሮች በእኔ ላይ ምንም ኃጢአት አልሰራም፤ ስለዚህ ከዘለአለማዊ ክብሩም ወድቋል፣ እና የድርሻውንም ተቀብሏል፤ እና እነዚህንም ከዚህ አለም ውጪ አይወርሳቸውም፣ ለሌላ [መ]ሰጥቻቸዋለሁና፣ ይላል ጌታ።

፵ እኔ ጌታ አምላካችሁ ነኝ፣ እና ለአንተ ኣገልጋዩ ጆሴፍ ስሚዝ ሁሉንም ነገሮች [ሀ]ዳግም ትመልስ ዘንድ ሀላፊነት ሰጥቼህለሁ። ያሻህንን ጠይቅ፣ እና በቃሌም መሰረት ይሰጥሀል።

፵፩ እና ስለ ማመንዘር ስለጠየቅህ፣ እውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣ ሰው በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ሚስትን ቢቀበል፣ እና እርሷም በቅዱስ ቅባት ካልመደብኩላት ከሌላ ሰው ጋር ብትገኝ፣ አመንዝራለች፣ እና ትጠፋለች።

፵፪ በአዲስ እና ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን ውስጥ ካልሆነች፣ እና ከሌላ ሰውም ጋር ብትሆን፣ [ሀ]አመንዝራለች።

፵፫ እና ባሏ ከሌላ ሴት ጋር ቢሆን፣ እና [ሀ]በመሀላም ላይ ቢሆን፣ መሀላውን ሰብሯል እና አመንዝሯል።

፵፬ እና እርሷ ካላመነዘረች፣ ነገር ግን ንጹህ ብትሆንና መሀላዋን ባትሰብር፣ እና ብታውቅም፣ እና እኔም ለአንተ ለአገልጋዩ ጆሴፍ ብትገልጥልህ፣ ከዚያም በቅዱስ ክህነት ስልጣን ሀይል መሰረት እርሷን ለመውሰድ እና ላላመነዘረው፣ ነገር ግን [ሀ]ታማኝ ለሆነው ትሰጥ ዘንድ ሀይል አለህ፤ እርሱ በብዙዎች ላይ ገዢ ይሆናልና።

፵፭ የክህነትን [ሀ]ቁልፎችና ሀይል በላይህ አድርጌአለሁ፤ በዚህም ሁሉንም ነገሮች [ለ]ዳግም እመልሳለሁ፤ በጊዜውም ሁሉንም ነገሮች አሳውቅሀለሁ።

፵፮ እና እውነት፣ እውነት እልሀለሁ፣ በምድር [ሀ]የምታትመው ሁሉ በሰማይ ይታተማል፤ እና በስሜ እና በቃሌ በምድር የምታሰረው ሁሉ በሰማያት ለዘለአለም ይታሰራል፣ ይላል ጌታ፤ በምድር ላይ [ለ]የምትሰርዘው ኃጢአት ሁሉ በሰማይ ለዘለአለም ይሰረዛል፤ እና በምድር ላይ የምትይዘው ኃጢአት ሁሉ በሰማይ ለዘለአለም ይያዛል።

፵፯ ደግሜም፣ እውነት እላለሁ፣ የምትባርከውን ማንኛውንም እባርካለሁ፣ እና የምትረግመውን ማንኛውንም [ሀ]እረግማለሁ፣ ይላል ጌታ፤ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝና።

፵፰ ደግሞም፣ አገልጋዩ ጆሴ እውነት እልሀለሁ፣ በምድር የምትሰጠው ማንኛውም ነገር፣ እና ለማንም በቃሌ እና በህጌ መሰረት ማንንም በምድር ላይ ምንም ብትሰጥ፣ ይህንም በእርግማን ሳይሆን በበረከት በሀይሌ እጎበኝዋለሁ፣ ይላል ጌታ፣ እና በምድር እና በሰማይ ያለኩነኔ ይሆናል።

፵፱ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እና እስከ አለም [ሀ]መጨረሻ ድረስ እና ለዘለአለም ሁሉ ከአንተ ጋር እሆናለሁና፤ በእውነትም [ለ]ዘለአለማዊ ክብርህን [ሐ]አትምብሀለሁ፣ እና በአባቴ መንግስት ውስጥ [መ]ከአባትህ አብርሐም ጋር ዙፋንን አዘጋጅልሀለሁና።

፴፱ ሀ ፪ ሳሙ. ፲፪፥ ፯–፰።
ለ ፪ ሳሙ. ፲፩፥ ፬፣ ፳፯፤ ፲፪፥ ፱፤
፩ ነገሥ. ፲፭፥፭።
ቅ.መ.መ. ማመንዘር፤ ግድያ።
ሐ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
መ ኤር. ፰፥ ፲።
፵ ሀ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፴፫።
ቅ.መ.መ. የወንጌል
ዳግም መመለስ።
፵፪ ሀ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፳፪–፳፮።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን፤
ጋብቻ፣ መጋባት።
፵፬ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህነት።
፵፭ ሀ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
ለ የሐዋ. ፫፥ ፳፩፤
ት. እና ቃ. ፹፮፥ ፲።
ቅ.መ.መ. የወንጌል
ዳግም መመለስ።
፵፮ ሀ ቅ.መ.መ. ማተም፣
ማስተሳሰር።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
፵፯ ሀ ዘፍጥ. ፲፪፥ ፩–፫፤
ት. እና ቃ. ፻፳፬፥ ፺፫።
፵፱ ሀ ማቴ. ፳፰፥ ፳።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥ ፳፪።
ቅ.መ.መ. መጠራት
እና መመረጥ።
ሐ ት. እና ቃ. ፷፰፥ ፲፪።
መ ዘፍጥ. ፲፯፥ ፩–፰፤
፪ ኔፊ ፰፥ ፪።

፶ እነሆ፣ [ሀ]መስዋዕቶችህን አይቻለሁ፣ እና ኃጢአቶችህንም ሁሉ እሰርያለሁ፤ ለነገርኩህ ለዚያ ታዛዥ በመሆን ያደረግኸውን መስዋዕትነት አይቻለሁ። ስለዚህ ሂድ፣ እና አብርሐም ልጁን ይስሀቅን ለመስዋዕት ያቀረበውን [ለ]እንደተቀበልኩኝ፣ የምታመልጥ በትንም መንገድ አዘጋጅቼአለሁ።

፶፩ እውነት እልሀለሁ፥ ለአንተ ለሚስትነት የሰጠሁህን ባሪያዬ ኤማ ስሚዝ ትረጋጋ ዘንድ እና እንድትሰጣትም ካዘዝኩህ በላይ እንዳትቀበል ትእዛዝን እሰጣታለሁ፤ ለአብርሐም እንዳደረግሁት፣ ለሁላችሁንም ለማረጋገጥ፣ እና ከእጆቻችሁ በቃል ኪዳን እና በመስዋዕት መስዋዕትን ለመጠየቅ ይህን አድርጌአለሁና ይላል ጌታ።

፶፪ እና አገልጋዬ [ሀ]ኤማ ስሚዝ ለአገልጋዬ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጡትን፣ በፊቴ ሰጋ ያላቸውና ንጹህ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ትቀበል፤ እና ንጹህ ያልሆኑት፣ እና ንጹህ ነን የሚሉት፣ ይጠፉሉ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፶፫ እኔ ጌታ አምላክሽ ነኝና፣ እና ድምጼንም አክብሪ፤ እና ለአገልጋዬ ጆሴፍም በብዙ ነገሮች ገዢ ይሆን ዘንድ ሰጥቼዋለሁ፤ በትንሽ ነገሮች [ሀ]ታማኝ ሆኗልና፣ እና ከዚህም ጊዜ ጀምሮ አበረታዋለሁ።

፶፬ እና ባሪያዬን ኤማ ስሚዝን ከአገልጋዬ ጆሴፍ ጋር እንድትኖር እና ከአገልጋዬ ጆሴፍ በስተቀር ከማንም ጋር እንዳትጣመር አዝዣታለሁ። ነገር ግን በዚህ ትእዛዝ ባትኖር ትጠፋለች፣ ይላል ጌታ፤ እኔ አምላክሽ ነኝ፣ እና በህጌም ባትኖር አጠፋታለሁ።

፶፭ ነገር ግን በዚህ ህግ ባትኖር፣ ከዚያም አገልጋዬ ጆሴፍ ሁሉንም ነገሮች፣ እንዲሁም እንዳለው፣ ለእርሷ ያድርግ፤ እና እኔም እባርከዋለሁ እናም አባዛዋለሁም እና ለእርሱም በዚህ አለም አባቶችና እናቶች፣ ወንድሞችና እህቶች፣ ቤቶችና መሬቶች፣ ሚስቶችና ልጆች [ሀ]በመቶ እጥፍ፣ እና በዘለአለምም አለማት [ለ]የዘለአለም ህይወትን አክሊል እሰጠዋለሁ።

፶፮ ደግሞም፣ እውነት እላለሁ፣ ገረዴ አገልጋዬን ጆሴፍ ለተላለፋቸው ይቅርታ ትስጠው፤ እና ከዚያም በእኔ ላይ በመተላለፍ ለተላለፈችው [ሀ]ይቅርታ ይሰጣታል፤ እና እኔ ጌታ አምላካችሁ እባርካታለሁ፣ እናም አባዛታለሁ፣ እና ልቧንም እንዲደሰት አደርጋለሁ።

፶፯ ደግሞም፣ እላለሁ፣ ጠላት መጥቶ እናም እንዳያጠፋውም፣ አገልጋዬ ጆሴፍ ንብረቱን ከእጆቹ አያውጣ፣ ሰይጣን ለማጥፋት [ሀ]ይፈልጋልና፤ እኔ ጌታ አምላክህ ነኝ፣ እና እርሱም አገልጋዬ ነውና፤ እና እነሆ፣ አስተውሉም፣ እኔ ከአባታችሁ አብርሐም ጋር፣ [ለ]እስከ ዘለአለማዊ ክብሩ እንደነበርኩኝ፣ ከእርሱም ጋር ነኝ።

፶፰ አሁን፣ [ሀ]የክህነት ህግን በሚመለከት፣ ይህን የሚመለከቱ ብዙ ነገሮች አሉ።

፶፱ እውነት፣ ሰው በአባቴ እንደ [ሀ]አሮን በድምጼ፣ እና በላከኝም ድምፅ፣ ቢጠራ እና እነዚህንም የክህነት [ለ]ቁልፎች ባበረክትለት፣ በስሜ፣ በህጌና በቃሌ ምንም ነገንር ቢያደርግ፣ ምንም ኃጢአትን አይሰራም፣ እና እኔም ከጥፋት ነጻ አደርገዋለሁ።

፷ ስለዚህ ማንም አገልጋዬ ጆሴፍን አያጥቃ፤ እኔ ከጥፋት ነጻ አደርገዋለሁና፤ ለተላለፋቸው ከእጆቹ የምጠብቃቸውን መስዋዕቶች ያደርጋልና፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ።

፷፩ ደግሞም፣ የክህነት ህግን በሚመለከት—ማንም ሰው [ሀ]ድንግልን ቢያገባ፣ እና [ለ]ሌላን ለማግባት ፍላጎት ቢኖረው፣ እና የመጀመሪያዋም ፈቃዷን ብትሰጥ፣

፶ ሀ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ለ ዘፍጥ. ፳፪፥፲–፲፬፤
ት. እና ቃ. ፺፯፥፰።
፶፪ ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ኤማ ሄል።
፶፫ ሀ ማቴ. ፳፭፥፳፩፤
ት. እና ቃ. ፶፪፥፲፫።
፶፭ ሀ ማር. ፲፥፳፰–፴፩።
ለ ቅ.መ.መ. ቤተሰብ—
ዘለአለማዊ ቤተሰብ፤
የዘለዓለም ህይወት።
፶፮ ሀ ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
፶፯ ሀ ማቴ. ፲፥፳፰።
ለ ቅ.መ.መ. ከፍተኛነት።
፶፰ ሀ ት. እና ቃ. ፹፬፥፲፱–፳፯።
ቅ.መ.መ. ክህነት።
፶፱ ሀ ዕብ. ፭፥፬።
ቅ.መ.መ. አሮን፣
የሙሴ ወንድም።
ለ ቅ.መ.መ. የክህነት ቁልፎች።
፷፩ ሀ ቅ.መ.መ. ድንግል።
ለ አ.አ. ፩።
ቅ.መ.መ. ጋብቻ፣
መጋባት—ከአንድ
ሚስት በላይ ማግባት።

እና ሁለተኛይቱን ቢያገባ፣ እና እነርሱም ድንግል ቢሆኑ፣ እና ለሌላም ሰው መሀላ ባይገቡ፣ እርሱም አያጠፋም፤ እርሱም አያመነዝርም ምክንያቱም ለእርሱ ተሰጥተውታልና፤ ከእርሱ በቀር ለማንም ካልሆኑት ጋር አያመነዝርምና።

፷፪ በዚህ ህግ አስር ድናግል ቢሰጡትም፣ ሊያመነዝር አይችልም፣ የእርሱ ናቸውና፣ እና ለእርሱም ተሰጥተውታልና፤ ስለዚህ አይጠፋም።

፷፫ ነገር ግን አንድ ወይም ከአስር ደናግላን አንዷ ካገባች በኋላ ከሌላም ወንድ ጋር ብትሆን፣ አመንዝራለች እና ትጠፋለችም፤ እነርሱም የሰው በትእዛዜ መሰረት ነፍሳትን እንዲወልዱ፣ እና ከአለም መመስረት በፊት በአባቴ የተሰጠውን ቃል ኪዳን ለማሚላት፣ እና በዘለአለሙም አለማት ዘለአለማዊ ክብራቸው [ሀ]እንዲበዛና ምድርን እንዲሞላ የተሰጡት ናቸውና፤ ይህም ይከበር ዘንድ የአባቴ [ለ]ስራ የሚቀጥልበት ነውና።

፷፬ ደግሞም፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የዚህን ሀይል ቁልፍ የያዘ ማንም ሰው ሚስት ቢኖረው፣ እና እነዚህን ነገሮች በሚመለከት የክህነቴን ህግ ቢያስተምራት፣ ከዚያም እርሷም ትመነው እናም ትደግፈው፣ ወይም ትጠፋለች፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፤ እኔ አጠፋታለሁና፤ ህጌን የሚቀበሉ እና በህጌም የሚኖሩትን ሁሉ አጎላቸዋለሁና።

፷፭ ስለዚህ፣ ስላላመነች እና በቃሌ መሰረት ስላልረዳችው፣ ይህን ህግ ባትቀበል፣ እኔ ጌታ የምሰጠውን ማንኛዎቹን ነገሮች ሁሉ ለመቀበል ይህም በእኔ ዘንድ እንደ ህግ ይሆናል፤ እና ከዚያም እርሷም ህግ ተላላፊ ትሆናለች፤ እና እርሱም አብርሐም አጋርን እንዲያገባ ባዘዝኩት ጊዜ ለአብራም በህጉ መሰረት ከደገፈችው ከሳራ የህግ ግዴታ ነጻ ነው።

፷፮ አሁንም፣ ይህን ህግ በሚመለከት፣ እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ከዚህ በኋላ ተጨማሪን ነገር እገልጥላችኋለሁ፤ ስለዚህ፣ ለጊዜው ይህ ይብቃ። እነሆ፣ እኔ አልፋና ኦሜጋ ነኝ። አሜን።

ክፍል ፻፴፫

በህዳር ፫፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.) በሀይረም ኦሀዮ ውስጥ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል የተሰጠ ራዕይ። ይህን ራዕይ በማስተዋወቅ የጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ እንደሚገልጸው፥ “በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎች ወንጌሉን ለምድር ነዋሪዎች ስለመስበክ፣ እና መሰብሰብን በሚመለከት ብዙ ነገሮችን ለማወቅ ፈልገው ነበር፤ እና በእውነት ብርሀን ለመራመድ፣ እና ከበላይም ለመመራት፣ በህዳር ፫፣ ፲፰፻፴፩ (እ.አ.አ.)፣ ጌታን ጠየቅሁ እና ይህን አስፈላጊ ራዕይ ተቀበልኩ።” ይህም ክፍል በትምህርት እና ቃል ኪዳን መፅሐፍ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ተጨማሪ ሆኖ ነበር እና በኋላም የክፍል ቁጥር ተመደበለት።

፩–፮፣ ቅዱሳን ለዳግም ምፅዓት እንዲዘጋጁ ታዝዘዋል፤ ፯–፲፮፣ ሁሉም ሰዎች ከባቢሎን እንዲሸሹ፣ ወደ ፅዮን እንዲመጡ፣ እና ለጌታም ታላቅ ቀን እንዲዘጋጁ ታዝዘዋል፤ ፲፯–፴፭፣ እርሱ በፅዮን ተራራ ላይ ይቆማል፣ ክፍለ አህጉራትም አንድ ምድር ይሆናሉ፣ እና የጠፉት የእስራኤል ነገዶች ይመለሳሉ፤ ፴፮–፵፣ ወንጌሉ በአለም እንዲሰበክ በጆሴፍ ስሚዝ በኩል ዳግም ተመልሷል፤ ፵፩–፶፩፣ ጌታ

፷፫ ሀ ዘፍጥ. ፩፥፳፮–፳፰፤ ያዕቆ. ፪፥፴።

ለ ሙሴ ፩፥፴፱።

በክፉዎች ላይ ለበቀል ይወርዳል፤ ፶፪–፶፮፣ የቤዛነቱም አመት ይሆናል፤ ፶፯–፸፬፣ ወንጌል ቅዱሳንን ለማዳን እና ክፉዎችንም ያጠፉ ዘንድ ተልኳል።

፩ የቤተክርስቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ አድምጡ፣ ይላል ጌታ አምላካችሁ፣ እና እናንተን በሚመለከት የጌታን ቃል ስሙ—

፪ ወደ [ሀ]ቤተመቅደሱ በድንገት የሚመጣው ጌታ፤ አዎን፣ እግዚአብሔርን በእርሱ ህዝብ ላይ፣ እና በመካከላችሁ ላሉ ኃጢአተኞች ላይ ሁሉ [ለ]ለፍርድ እርግማን ይዞ በምድር ላይ የሚወርደው ጌታን አድምጡ።

፫ እግዚአብሔር የተቀደሰውን ክንዱን በአሕዛብ ሁሉ ፊት [ሀ]ይገልጣልና፣ እና በምድር ዳርቻ የሚኖሩትም ሁሉ የአምላካቸውን [ለ]መድኃኒት ያያሉ።

፬ ስለዚህ ህዝቤ ሆይ፣ ተዘጋጁ፣ ተዘጋጁ፤ ራሳችሁን ቀድሱ፤ የቤተክርስቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ እንድትቆዩ ያልታዘዛችሁት ሁሉ አብራችሁ በፅዮን ምድር ውስጥ ተሰብሰቡ።

፭ [ሀ]ከባቢሎንም ውጡ። የጌታን ዕቃ የምትሸከሙ [ለ]ንፁህን ሁኑ።

፮ የክብር ስብሰባችሁን ጥሩ፣ እና አንዳችሁ ከሌላችሁ በየጊዜው [ሀ]ተነጋገሩ። እና እያንዳንዱም ሰው የጌታን ስም ይጥራ።

፯ አዎን፣ ደግሞም እውነት እላችኋለሁ፣ የጌታ ድምፅ ለእናንተ የሚሆንበት ጊዜ መጥቷል፥ ከባቢሎን ውጡ፤ [ሀ]ከአራቱ ነፋሳት፣ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከሀገሮች መካከል [ለ]ተሰብስባችሁ ውጡ።

፰ መጀመሪያ ወደ [ሀ]አህዛብ እና ከዚያም ወደ [ለ]አይሁድ፣ ሁሉንም ሀገሮች እንዲጠሯቸው የቤተክርስቲያኔን ሽማግሌዎች ወደ ራቅ ሀገሮች፣ ወደ ባህር [ሐ]ደሴቶች [መ]ላኳቸው፤ ወደ ባዕድ ሀገሮችም ላኳቸው።

፱ እናም እነሆ እና አስተውሉ፣ ይህም ጩኸታቸው እና ለሁሉም ህዝብ የጌታ ድምፅ ነው፥ የህዝቤ ድንበር ይሰፋ ዘንድ፣ እና [ሀ]ካስማዎቿም ይጠናከሩ ዘንድ፣ እና ፅዮንም በአካባቢው ባሉ ሀገራት ትጎለብት ዘንድ ወደ [ለ]ፅዮን ምድር ሂዱ።

፲ አዎን፣ ከሁሉም ህዝብ መካከል ጩኸቱ ይውጣ፥ ንቁ፣ እና ተነሱ እና ሙሽራውንም ለመገናኘት ሂዱ፤ እነሆ እና አስተውሉ፣ [ሀ]ሙሽራው ይመጣል፣ ትቀበሉትም ዘንድ ውጡ። ለጌታ [ለ]ታላቅ ቀንም ራሳችሁን አዘጋጁ።

፲፩ ቀኒቱንና ሰዓቲቱን [ሀ]አታውቁምና እንግዲህ [ለ]ንቁ።

፲፪ ከአህዛብ [ሀ]መካከል ያሉትም ወደ [ለ]ፅዮን ይሽሹ።

፲፫ እና [ሀ]የይሁዳ የሆኑትም ወደጌታ [ለ]ቤት [ሐ]ተራራዎች ወደ [መ]ኢየሩሳሌም ይሽሹ።

፲፬ ከሀገሮች መካከል፣ እንዲሁም ከባቢሎን፣ መንፈሳዊ ባቢሎን ከሆነው ከክፋት መካከል ውጡ።

፻፴፫ ፪ ሀ ሚል. ፫፥፩፤
ት. እና ቃ. ፴፮፥፰።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፴፮።
ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—ዳኛ።
፫ ሀ ኢሳ. ፶፪፥፲።
ለ ኢሳ. ፲፪፥፪፤ ፶፪፥፲።
ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ፤ ደህንነት።
፭ ሀ አልማ ፭፥፶፯፤
ት. እና ቃ. ፩፥፲፮።
ቅ.መ.መ. ባቢሎን፤ አለማዊነት።
ለ ፪ ጢሞ. ፪፥፳፩፤
፫ ኔፊ ፳፥፵፩፤
ት. እና ቃ. ፴፰፥፵፪።
ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
፮ ሀ ሚል. ፫፥፲፮–፲፰።
፯ ሀ ዘካ. ፪፥፮–፯፤
ማር. ፲፫፥፳፯።
ለ ት. እና ቃ. ፳፱፥፰።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል መሰብሰብ።
፰ ሀ ቅ.መ.መ. አህዛቦች።
ለ ቅ.መ.መ. አይሁዶች።
ሐ ኢሳ. ፲፩፥፲፩፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፬፤
፪ ኔፊ ፲፥፰፣ ፳።
መ ቅ.መ.መ. የሚስዮን ስራ።
፱ ሀ ኢሳ. ፶፬፥፪።
ቅ.መ.መ. ካስማ።
ለ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፲ ሀ ማቴ. ፳፭፥፮፤
ት. እና ቃ. ፴፫፥፲፯–፲፰፤
፹፭፥፶፬–፶፱።
ቅ.መ.መ. ሙሽራ።
ለ ት. እና ቃ. ፩፥፲፪–፲፬።
፲፩ ሀ ት. እና ቃ. ፵፱፥፯።
ለ ማር. ፲፫፥፴፪–፴፯፤
ጆ.ስ.—ማቴ. ፩፥፵፮፣ ፵፰።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፴፰፥፴፩፣ ፵፪።
ለ ቅ.መ.መ. ፅዮን።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ።
ለ መዝ. ፻፳፪።
ሐ ኢሳ. ፪፥፩–፫፤
ሕዝ. ፴፰፥፰።
መ ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም።

፲፭ ነገር ግን በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ ሽሽታችሁ [ሀ]በችኮላ አይሁን፣ ነገር ግን ሁሉም ነገሮች በፊታችሁ ይዘጋጁ፤ እና የሚሄደውም፣ ድንገተኛ ጥፋትም እንዳይደርስበት ወደኋላ [ለ]አይመልከት።

፲፮ የምድር ነዋሪዎች ሁሉ፣ [ሀ]አድምጡ እና ስሙ። የቤተክርስቲያኔ ሽማግሌዎች የሆናችሁ በአንድነት አብራችሁ አድምጡ፣ እና የጌታንም ድምፅ ስሙ፤ ሁሉንም ሰዎች ይጣራልና፣ እና በየትኛውም ስፍራ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ [ለ]ንስሀ ይገቡ ዘንድያዝዛቸዋል።

፲፯ እነሆም፣ ጌታ አምላክ በሰማያት መካከል እንዲህ በማለት በመጮህ መልአክ [ሀ]ልኳል፥ የጌታን መንገድ አዘጋጁ፣ እና ጥርጊያውንም [ለ]ቀና አድርጉ፣ [ሐ]የመምጣቱም ጊዜ ቀርቦአልና—

፲፰ [ሀ]በጉ [ለ]በፅዮን ተራራ ሲቆም፣ እና ከእርሱም ጋር የአባቱ ስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው [ሐ]መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።

፲፱ ስለዚህ፣ [ሀ]ለሙሽራው [ለ]ምጻት ተዘጋጁ፤ ሂዱ፣ ከእርሱም ጋር ለመገናኘት ሂዱ።

፳ እነሆም፣ በደብረ ዘይት ተራራና በታላቋ ባህር ላይ፣ እንዲሁም በታላቁ ጥልቅ፣ እና በባህር ደሴት ላይ፣ እና በፅዮን ምድር ላይ [ሀ]ይቆማል።

፳፩ እና [ሀ]በፅዮንም ሆኖ ድምፁን [ለ]ከፍ አድርጎ ይጮኻል፣ እና ከኢየሩሳሌምም ይናገራል፣ እና ድምጹም በሁሉም ህዝብ መካከል ይሰማል፤

፳፪ ይህም ተራሮችን [ሀ]በሚሰብር፣ እና ሸለቆዎችን እንደሚለያይ በሚያደርግ እንደ ብዙ ውህዎች [ለ]ድምፅና እንደ ታላቅ [ሐ]ነጐድጓድ ድምፅ ይሰማል።

፳፫ ታላቁን ጥልቅ ያዝዘዋል፣ እና ይህም ወደ ሰሜን አገሮችም ይገፋል፣ እና [ሀ]ደሴቶችም አንድ ምድር ይሆናሉ፤

፳፬ እና [ሀ]የኢየሩሳሌም ምድር እና የፅዮን ምድር ወደስፍራቸው ይመለሳሉ፣ እና ምድርም [ለ]ከመከፋፈልዋ ቀን አስቀድሞ እንደነበረችበትም አይነት ትሆናለች።

፳፭ እና ጌታ፣ እንዲሁም አዳኝ፣ በህዝቡ መካከል ይቆማል፣ እና ስጋ ለባሽ ሁሉ መካከል [ሀ]ይነግሳል።

፳፮ እና [ሀ]በሰሜን ሀገሮች ያሉትም ጌታን ያስታውሳሉ፤ እና ነቢያቶቻቸውም ድምጹን ይሰማሉ፣ እና ራሳቸውን ከዚህም በኋላ የሚታገሱ አይሆኑም፤ እና ድንጋይን ይመታሉ፣ እና በፊታቸውም በረዶዎች ይፈሳሉ።

፳፯ እና [ሀ]አውራ መንገድም በታላቁ ጥልቅ መካከል ይዘረጋል።

፳፰ ጠላቶቻቸውም ለእነርሱ እንደ አደን ይሆናሉ፣

፳፱ እና ፍሬ በማያፈራ [ሀ]በረሀ ውስጥም የህይወት ውሀ ምንጭ ይፈልቃል፤ እና

፲፭ ሀ ኢሳ. ፶፪፥ ፲–፲፪፤ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፶፮።
ለ ዘፍጥ. ፲፱፥ ፲፯፤ ፳፮፤ ሉቃ. ፱፥ ፷፪።
፲፮ ሀ ት. እና ቃ. ፩፥ ፩–፮።
ለ ቅ.መ.መ. መጸጸት፤ ንስሀ መግባት።
፲፯ ሀ ት. እና ቃ. ፲፫፤ ፳፯፥ ፯–፰፤ ፹፰፥ ፺፪።
ለ ኢሳ. ፵፥ ፫–፭።
ሐ ሚል. ፫፥ ፩።
፲፰ ሀ ራዕ. ፲፬፥ ፩። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።
ለ ት. እና ቃ. ፹፬፥ ፪።
ሐ ራዕ. ፯፥ ፩–፬።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ሙሽራ።
ለ ማቴ. ፳፭፥ ፩–፲፫፤ ት. እና ቃ. ፴፫፥ ፲፯–፲፰፤ ፹፰፥ ፺፪። ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፳ ሀ ዘካ. ፲፬፥ ፬፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥ ፵፰–፶፫።
፳፩ ሀ ኢሳ. ፪፥ ፪–፬።
ለ ኢዩ. ፫፥ ፲፮፤ ዓሞ. ፩፥ ፪።
፳፪ ሀ መዝ. ፸፯፥ ፲፰፤ ራዕ. ፲፬፥ ፪።
ለ ሕዝ. ፵፫፥ ፪፤ ራዕ. ፩፥ ፲፭፤ ት. እና ቃ. ፻፲፥ ፫።
ሐ መሳ. ፭፥ ፭፤ ኢሳ. ፵፥ ፬፤ ፳፬፥ ፩፤ ራዕ. ፲፮፥ ፳፤ ት. እና ቃ. ፵፱፥ ፳፫፤ ፻፱፥ ፸፬።
፳፫ ሀ ራዕ. ፮፥ ፲፬።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሩሳሌም።
ለ ዘፍጥ. ፲፥ ፳፭። ቅ.መ.መ. ምድር—የምድር መከፋፈል።
፳፭ ሀ ቅ.መ.መ. ኢየሱስ ክርስቶስ—የክርስቶስ የአንድ ሺህ አመት ግዛት።
፳፮ ሀ ኤር. ፲፮፥ ፲፬–፲፭፤ ት. እና ቃ. ፻፲፥ ፲፩። ቅ.መ.መ. እስራኤል—የጠፉት የእስራኤል አስር ጎሳዎች።
፳፯ ሀ ኢሳ. ፲፩፥ ፲፭–፲፮፤ ፪ ኔፊ ፳፩፥ ፲፮።
፳፱ ሀ ኢሳ. ፴፭፥ ፮–፯።

በጸሀይ የደረቀውም መሬት ዳግም የተጠማ ምድር አይሆንም።

፴ እና የከበረ ሀብታቸውንም ወደ አገልጋዬ [ሀ]ኤፍሬም ልጆች ያመጣሉ።

፴፩ እና የዘለአለም [ሀ]ኮረብቶች ድንበሮችም በፊታቸው ይንቀጠቀጣሉ።

፴፪ እና በዚያ፣ እንዲሁም በፅዮን ውስጥ፣ ይወድቃሉ እና በጌታ አገልጋዮች እጆችም፣ እንዲሁም በኤፍሬም ልጆች፣ የክብር አክሊል ይጎነጸፋሉ።

፴፫ እና እነርሱም በዘለአለም የደስታ [ሀ]መዝሙር ይሞላሉ።

፴፬ እነሆ፣ ይህም በእስራኤል [ሀ]ጎሳዎች ላይ የዘለአለማዊው እግዚአብሔር በረከት፣ እና [ለ]በኤፍሬም እና በባልንጀሮቹ ራስ ላይ ዋጋ ያለው በረከት ነው።

፴፭ እና [ሀ]የይሁዳ ጎሳ ለሆኑትም፣ ከስቃያቸው በኋላ [ለ]በቅድስና በጌታ ፊት፣ በቀን እና በማታ፣ ለዘለአለም፣ በፊቱ እንዲኖሩ ይቀደሳሉ።

፴፮ አሁንም፣ በእውነት ጌታ እንዲህ ይላል፣ የምድር ነዋሪዎች ሆይ፣ እነዚህ ነገሮች በእናንተ መካከል የታወቁ ይሆኑ ዘንድ የዘለአለም [ሀ]ወንጌል ያለው፣ ለአንዳንዶች የታየ እና ለሰውም ይህን የሰጠ፣ እና በምድር ላይ ለሚኖሩት ለብዙዎች የሚታየው [ለ]መልአክ ከሰማይ መካከል እንዲበር ልኬአለሁ።

፴፯ እና ይህም [ሀ]ወንጌል [ለ]ለእያንዳንዱ ሕዝብ፣ ለነገድ፣ ቋንቋ፣ እና ወገንም ሁሉ [ሐ]ይሰበካል።

፴፰ እና የእግዚአብሔርም አገልጋዮች በታላቅ ድምፅ፥ የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት በማለት ይሄዳሉ፤

፴፱ እና ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው [ሀ]ስገዱለት—

፵ በቀን እና በማታ የጌታን ስም በመጥራት፥ ሰማያትን [ሀ]ቀድደህ ብትወርድስ፣ ተራሮችም በፊትህ ቢናወጡስ በማለትም።

፵፩ እናም በራሳቸው ላይ መልስ ይሰጣል፤ የጌታ መገኘት እሳት እንደሚያቀልጥ እሳት፣ እና ውኃንም [ሀ]እንደሚያፈላ እሳት ይሆናል።

፵፪ ጌታ ሆይ፣ ስምህ ለጠላቶችህ ይገለጥ ዘንድ፣ እና አሕዛብም በፊትህ ይንቀጠቀጡ ዘንድ ትወርዳለህ—

፵፫ ያልጠበቁትን የሚያስፈራውን ነገር ባደረግህም ጊዜ፤

፵፬ አዎን፣ ወረድህ፣ እና ተራሮችም በፊትህ ተንቀጠቀጡ፣ የሚደሰተውንና ጽድቅን የሚያደርገውን በመንገዶችህም የሚያስቡህን [ሀ]ትገናኛቸዋለህ።

፵፭ እግዚአብሔር ሆይ፣ ሰዎች ከጥንት ጀምሮ [ሀ]ለሚጠብቁህ [ለ]ከምትሠራላቸው ከአንተ በቀር ሌላ አምላክን አልሰሙም፣ በጆሮአቸውም አልተቀበሉም፣ ዓይንም አላየችም።

፵፮ እና እንዲህም ይባላል፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ የወረደው፣ ልብሱም የቀላ፣ ከባሶራ [ሀ]የሚመጣ አለባበሱም ያማረ፣ በጉልበቱስ ጽናት የሚራመድ ይህ [ለ]ማን ነው?

፵፯ እርሱም ይላል፥ በጽድቅ የምናገር ለማዳንም የምበረታ እኔ ነኝ።

፴ ሀ ዘካ. ፲፥ ፯–፲፪።
ቅ.መ.መ. ኤፍሬም—የኤፍሬም ጎሳ።
፴፩ ሀ ዘፍጥ. ፵፱፥ ፳፮።
፴፫ ሀ ኢሳ. ፴፭፥ ፲፤ ፶፩፥ ፲፩፤ ት. እና ቃ. ፷፮፥ ፲፩።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. እስራኤል—የእስራኤል አስራ ሁለት ጎሳዎች።
ለ ዘፍጥ. ፵፰፥ ፲፬–፳፤ ፩ ዜና ፭፥ ፩–፪፤ ኤተር ፲፫፥ ፯–፲።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. ይሁዳ፣ የያዕቆብ ልጅ—የይሁዳ ጎሳ።
ለ ቅ.መ.መ. ቅድስና።
፴፮ ሀ ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
ለ ራዕ. ፲፬፥ ፮–፯፤ ት. እና ቃ. ፳፥ ፭–፲፪።
፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፶፰።
ሐ ቅ.መ.መ. መስበክ፤ የሚስዮን ስራ።
፴፱ ሀ ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፵ ሀ ኢሳ. ፷፬፥ ፩–፪።
፵፩ ሀ ኢዮብ ፵፩፥ ፴፩።
፵፬ ሀ ፩ ተሰ. ፬፥ ፲፮–፲፰።
፵፭ ሀ ሰቆ. ፫፥ ፳፭፤ ፪ ኔፊ ፮፥ ፯፣ ፲፫።
ለ ኢሳ. ፷፬፥ ፬፤ ፩ ቆሮ. ፪፥ ፱።
፵፮ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
ለ ኢሳ. ፷፫፥ ፩–፪።

፵፰ እና ጌታም በልብሱ [ሀ]ቀይ፣ እና ልብሱም ወይን በመጥመቂያ እንደሚረግጥ ሰው ልብስ ይሆናል።

፵፱ እና ከፊቱም ክብር ታላቅነት የተነሳ [ሀ]ጸሀይ በእፍረት ፊቱን ይሸፍናል፣ እና ጨረቃም ብርሀኗን ትከለክላለች፣ እና ከዋክብትም ከስፍራቸው ይወረወራሉ።

፶ እና ድምጹም ይሰማል፥ ወይን መጭመቂያን ብቻዬን [ሀ]ረግጫለሁ፥ እና በሁሉም ህዝብ ላይ ፍርድ አምጥቻለሁ፤ እና ማንም ሰው ከእኔ ጋር አልነበረም፤

፶፩ በቍጣዬ ረገጥኋቸው በመዓቴም ቀጠቀጥኋቸው፣ ደማቸውም በልብሴ ላይ [ሀ]ተረጭቶአል፣ ልብሴንም ሁሉ አሣድፌአለሁ፤ ይህም በልቤ የነበረው የምበቀልበት ቀን ነውና።

፶፪ አሁንም የምቤዥበትም ዓመት ደርሶአል፤ እና የጌታቸውን አፍቃሪ ደግነትን እና በመልካምነቱም መሰረት፣ እናም በአፍቃሪ ደግነቱ መሰረት፣ በእነርሱ ላይ ስላፈሰሰው ሁሉ ለዘለአለም ይናገራሉ።

፶፫ [ሀ]በጭንቃቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ። የፊቱን መልአክ አዳናቸው፤ [ለ]በፍቅሩና በርኅራኄውም [ሐ]ተቤዣቸው፣ በቀደመውም ዘመን ሁሉ አንሥቶ ተሸከማቸው፤

፶፬ አዎን፣ እና [ሀ]ሔኖክ ደግሞም፣ እና ከእርሱም ጋር የነበሩት፤ ከእርሱ በፊት የነበሩት ነቢያት፤ እና [ለ]ኖህም ደግሞ፣ እና ከእርሱም በፊት የነበሩት፤ እና [ሐ]ሙሴም፣ እና ከእርሱ በፊት የነበሩት፤

፶፭ ከሙሴ እስከ ኤልያስ፣ እና ከኤልያስ [ሀ]በትንሳኤው ከክርስቶስ ጋር እስከ ነበረው ዮሐንስ፣ እና ቅዱስ ሐዋርያት፣ ከአብርሐም፣ ይስሀቅ፣ እና ያዕቆብ ጋር በበጉ ፊት ይሆናሉ።

፶፮ [ሀ]የቅዱሳን [ለ]መቃብሮችም [ሐ]ይከፈታሉ፤ እና [መ]በፅዮን ተራራ ላይ፣ እና በቅዱስቲቱ ከተማ [ሠ]አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ላይ ሲቆምም፣ እነርሱም ይመጣሉ እና በበጉም [ረ]ቀኝ ይቆማሉ፤ እና በቀን እና በማታ ለዘለአለም [ሰ]የበጉን [ሸ]መዝሙሮች ይዘምራሉ።

፶፯ እና ለዚህም ምክንያት ሰዎች የሚገለጡትን [ሀ]ክብሮች ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ፣ ጌታ [ለ]የወንጌሉን ሙላት፣ ዘለአለማዊ ቃልኪዳኑን፣ በግልጽ እና በቀላል ምክንያቱን ላከ—

፶፰ በምድር ላይ ለሚመጡት ነገሮች [ሀ]ደካማዎችን ለማዘጋጀት፣ እና ጥበበኞችን በሚያሳፍሩበት ቀን ለጌታ መልእክት፣ እና [ለ]አነስተኛው ብርቱ ሕዝብ ይሆናል፣ እና [ሐ]ሁለቱ አሥሩን ሺህ ያሸሻሉ።

፶፱ እና በመንፈሱ ኃይል ጌታ በአለም ደካማ ነገሮች አህዛብን [ሀ]ይወቃል።

፷ እና ለዚህም ምክንያት እነዚህ ትእዛዛት ተሰጥተው ነበር፤ በተሰጧቸውም ቀን ከአለም ይሰውሯቸው ዘንድ ታዝዛው ነበር፣ ነገር ግን አሁን ወደ ሁሉም [ሀ]ስጋ ለባሾች [ለ]ይሂዱ—

፷፩ እና ይህም ሁሉንም ስጋ ለባሽ በሚገዛው በጌታ አዕምሮ እና ፈቃድ መሰረት ነው።

፵፰ [ሀ] ዘፍጥ. ፵፱፥፲፩–፲፪፤ ሉቃ. ፳፪፥፵፬፤ ራዕ. ፲፱፥፲፫–፲፭፤ ጆ.ስ.ት. ራዕ. ፲፱፥፲፭ (ተጨማሪ)፤ ሞዛያ ፫፥፯፤ ት. እና ቃ. ፲፱፥፲፰።

፵፱ [ሀ] ኢሳ. ፲፫፥፲፤ ፳፬፥፳፫፤ ት. እና ቃ. ፵፭፥፵፪፤ ፹፰፥፹፯።

፶ [ሀ] ኢሳ. ፷፫፥፪–፫፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፻፯፤ ፹፰፥፻፮።

፶፪ [ሀ] ዘሌዋ. ፳፭፥፲።

፶፫ [ሀ] ኢሳ. ፷፫፥፰–፱።

[ለ] ቅ.መ.መ. ልግስና።

[ሐ] ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።

፶፬ [ሀ] ቅ.መ.መ. ሔኖክ።

[ለ] ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ።

[ሐ] ቅ.መ.መ. ሙሴ።

፶፭ [ሀ] ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።

፶፮ [ሀ] ቅ.መ.መ. ቅዱሳን።

[ለ] ት. እና ቃ. ፳፱፥፲፫።

[ሐ] ት. እና ቃ. ፵፭፥፵፭–፵፮፤ ፹፰፥፺፮–፺፯።

[መ] ኢሳ. ፳፬፥፳፫፤ ራዕ. ፲፬፥፩፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፷፮፤ ፹፬፥፪፣ ፺፰–፻፪።

[ሠ] ቅ.መ.መ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም።

[ረ] ማቴ. ፳፭፥፴፫–፴፬።

[ሰ] ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር በግ።

[ሸ] ራዕ. ፲፭፥፫፤ ት. እና ቃ. ፹፬፥፺፰–፻፪።

፶፯ [ሀ] ቅ.መ.መ. የክብር ደረጃዎች።

[ለ] ቅ.መ.መ. ወንጌል።

፶፰ [ሀ] ማቴ. ፲፩፥፳፭፤ ፩ ቆሮ. ፩፥፳፯፤ አልማ ፴፪፥፳፫፤ ፴፯፥፮–፯።

[ለ] ኢሳ. ፷፥፳፪።

[ሐ] ዘዳግ. ፴፪፥፳፱–፴።

፶፱ [ሀ] ሚክ. ፬፥፲፩–፲፫።

፷ [ሀ] ት. እና ቃ. ፩፥፪።

[ለ] ት. እና ቃ. ፻፬፥፶፰–፶፱።

፷፪ እና [ሀ]ንስህ ለሚገባው እና በጌታ ፊት ራሱን [ለ]ለሚቀድስም [ሐ]የዘለአለም ህይወትን ይሰጣል።

፷፫ እና የጌታን ድምፅ [ሀ]ለማያደምጡም፣ ከህዝብ መካከል [ለ]ይቆረጡ ዘንድ፣ በነቢዩ ሙሴ የተጻፈውም ይፈጸማል።

፷፬ እና በነቢዩ [ሀ]ሚልክያስ እንደተጻፈውም፥ እነሆ፣ እንደ ምድጃ እሳት የሚነድድ [ለ]ቀን ይመጣል፤ ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፤ የሚመጣውም ቀን [ሐ]ያቃጥላቸዋልና፥ ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።

፷፭ ስለዚህ፣ ይህም ለእነርሱ የጌታ መልስ ይሆናል፥

፷፮ በዚያም ቀን ወደ ራሴ ስመጣ፣ በመካከላችሁ ማንም [ሀ]አልተቀበለኝም፣ እና ተሰድዳችሁም ነበር።

፷፯ በጠራሁስ ጊዜ የሚመልስ ማንም አልነበረም፤ ነገር ግን መታደግ እንዳልችል [ሀ]እጄ አጭር አልሆነችም፣ ወይስ ለማዳን [ለ]ኃይል የለኝም።

፷፰ እነሆ፣ በገሥጽሁ ጊዜ ባሕርን [ሀ]አደርቃለሁ። ወንዞችንም ምድረበዳ አደርጋቸዋለሁ፤ ዓሦቻቸውም ይገማሉ በጥማትም ይሞታሉ።

፷፱ ሰማያትን ጥቍረት አለብሳቸዋለሁ፥ መጋረጃቸውንም ማቅ አደርጋለሁ።

፸ እና [ሀ]ይህ ከእጄ ይሆንባችኋል—በኀዘን ትተኛላችሁ።

፸፩ እነሆ እና አስተውሉ፣ የሚያድናችሁ ማንም የለም፤ ከሰማያት ስጠራችሁ ድምጼን አልታዘዛችሁበትምና፤ በአገልጋዮቼ አላመናችሁም፣ እና ወደ እናንተም [ሀ]ሲላኩ አልተቀበሏቸውም።

፸፪ ስለዚህ፣ ምስክሩን [ሀ]ያትማሉ እና ህግንም ያስራሉ፣ እና ወደ ድቅድቅ ጭለማም ትጣላላችሁ።

፸፫ እነዚህም በድቅድቅ ጨለማ ይሄዳሉ፣ በዚያ [ሀ]ልቅሶ፣ ሀዘንና፣ ጥርስ ማፏጨት ይሆናል።

፸፬ እነሆ ጌታ አምላካችሁ ይህን ተናግሯል። አሜን።

ክፍል ፻፴፬

በነሀሴ ፲፯፣ ፲፰፻፴፭ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ ኦሀዮ ውስጥ በነበረው በቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ ስብሰባ ላይ በአንድ ድምፅ ምርጫ የተቀበሉት ስለመንግስት እና በአጠቃላይም ስለህግጋት የሚመለከት የእምነት እወጃ። ብዙ ቅዱሳን የትምህርት እና ቃል ኪዳን የመጀመሪያው ቅጂ ውስጥ እንዲኖር የቀረበውን ለማመዛዘን ተሰብስበው ነበር። በዚያም ጊዜ፣ የሚቀጥለው መግቢያ ለዚህ እወጃ ተሰጠው፥ “የምድር መንግስታትን እና አጠቃላይ ህግጋትን በሚመለከት ያለን እምነት የስ

፷፪ ሀ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣
ንስሀ መግባት።
ለ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፬።
ቅ.መ.መ. ቅድስና።
ሐ ቅ.መ.መ. የዘለዓለም
ህይወት።
፷፫ ሀ ቅ.መ.መ. ማዳመጥ።
ለ የሐዋ. ፫፥፳፪–፳፫፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፳–፳፩፤
፫ ኔፊ ፳፥፳፫፤ ፳፩፥፲፩፤
ት. እና ቃ. ፩፥፲፬፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፵።
፷፬ ሀ ሚል. ፬፥፩።
ቅ.መ.መ. ሚልክያስ።
ለ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፮–፴፱።
ሐ ኢሳ. ፷፮፥፲፭–፲፮፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፲፭፤
፫ ኔፊ ፳፭፥፩፤
ት. እና ቃ. ፳፱፥፱፤ ፷፬፥፳፬።
ቅ.መ.መ. ምድር—
ምድርን ማፅዳት።
፷፮ ሀ ዮሐ. ፩፥፲፩።
፷፯ ሀ ፪ ኔፊ ፳፰፥፴፪።
ለ ኢሳ. ፶፥፪፤
፪ ኔፊ ፯፥፪።
፷፰ ሀ ዘፀአ. ፲፬፥፳፩፤
ኢያ. ፫፥፲፬–፲፯።
፸ ሀ ኢሳ. ፶፥፲፩።
፸፩ ሀ ፪ ዜና ፴፮፥፲፭–፲፮፤
ኤር. ፵፬፥፬–፭።
፸፪ ሀ ኢሳ. ፰፥፲፮–፳።
፸፫ ሀ ማቴ. ፰፥፲፩–፲፪፤
ሉቃ. ፲፫፥፳፰፤
ት. እና ቃ. ፲፱፥፭።
ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ፤
ሲዖል።

ህተት ትርጉም ወይም የስህተት መረጃ እንዳይሆን፣ በዚህ መፅሀፍ መዝጊያ ላይ ይህን በሚመለከት አስተሳሰባችንን ማቅረብ ትክክለኛ እንደሆነ አስበናል።”

፩–፬፣ መንግስታት የህሊናን ነጻነት እና አምልኮን ይጠብቁ፤ ፭–፰፣ ሁሉም ሰዎች መንግስታቸውን መደገፍ እና ለህግም ታዛዥነት እና አክብሮት ሊኖራቸው ይገባል፤ ፱–፲፣ የሀይማኖት ህብረተሰቦች የህዝባዊ ሀይላት አይኑራቸው፤ ፲፩–፲፪፣ ሰዎች ራሳቸውን እና ንብረቶቻቸውን በመጠበቅ ከጥፋት ነጻ ይሆናሉ።

፩ [ሀ]መንግስታት እግዚአብሔር ለሰው [ለ]ጥቅም የመሰረታቸው እንደሆኑ እናምናለን፤ እና እነዚህን በሚመለከትም፣ ለህብረተሰብ ጥቅም እና ደህንነት በሚሰሩት አማካይነት ህግጋትን እና እነርሱንም በሚያስተዳድሩ ሰዎችን በተጠያቂነት ይይዟቸዋል።

፪ ህግጋት ለእያንዳንዱ [ሀ]የህሊና [ለ]ነጻነት ጥቅም፣ የንብረት መብትና ቁጥጥር፣ እና የህይወት [ሐ]ጥበቃን ለማግኘት ካልተመሰረቱ እና ተጥሰውም ካልተገኙ በስተቀር ምንም መንግስት በሰላም ለመኖር እንደማይችል እምነት አለን።

፫ መንግስታት ሁሉ እነዚህን ህግጋት ለማስከበር ህዝባዊ [ሀ]ባለስልጣናት እና ዳኞዎች እንደሚያስፈልጋቸው እናምናለን፤ እና ህጉን በእኩልነት እና በፍትህዊነት የሚያስተዳድሩም ሪፐብሊክ ከሆነ በህዝብ ድምፅ፣ ወይም በነገስታት ይፈለጉ፣ ይደገፉም።

፬ ሀይማኖት በእግዚአብሔር እንዲመሰረት እናምናለን፤ እና የሀይማኖታቸው አስተያየት የሌሎችን መብት እና ነጻነት እስካልጣሰ ድረስ፣ ይህን ለመጠቀምም ሰዎች ለእርሱ እና ለእርሱ ብቻ መልስን ይስጡ፤ ነገር ግን የሰዎች ህግ የሰዎችን ህሊና በማስተሳሰር የማምለክን ደንብ በማዘዝ ጣልቃ ለመግባት፣ ወይም የህዝባዊ ወይም የግል [ሀ]የአምልኮ መንገድን ለማዘዝ መብት እንዳላቸው አናምንም፤ ዳኞች ወንጀሎችን ያስቁሙ፣ ነገር ግን ህሊናን አይቆጣጠሩ፤ ወንጀለኛነትን ይቅጡ፣ ነገር ግን የነፍስን ነጻነት አይጨቁኑ።

፭ ሁሉም ሰዎች በሚኖሩባቸው መንግስታት ህግጋት የወረሱትን እና የማይነጠለውን መብቶቻቸውን የሚጠብቁላቸውን መንግስታት ለመቀበል እና ለመደገፍ ግዴታ እንዳላቸው እናምናለን፤ እና በእንደዚህ ከተጠበቁ ዜጎች ህዝብን [ሀ]ማሳመጽ እና መቃወም የሚጠበቅባቸው አይደለም፣ እና መቀጣትም ይገባቸዋል፤ እና መንግስታት ሁሉ የህዝብን ጥቅም በጥብቅ ለመያዝ የራሳቸውን ፍርድ በመልካምነት እንደሚያስቡት እንደዚህ አይነት ህግጋትን ለመስራት መብት አላቸው፤ በዚህም ጊዜ ግን፣ የህሊና ነጻነትን በቅድስና ይጠበቁ።

፮ እያንዳንዱም ሰው በተመደበለት ስፍራ ውስጥ መከበር እንደሚገባው፣ የዋሆችን ለመጠበቅ እና ወንጀለኞችን ለመቅጣት የተመደቡት መሪዎች እና ዳኞዎችም እንደዚህ መከበር እንደሚገባቸው እናምናለን፤ እና [ሀ]ለህግጋትም ሁሉም ሰዎች ክብር እና አክብሮትን ይስጡ፣ ካለእርሱም ስርዓት የለሽነት እና ሽብር ሰላምንና ስምምነትን ይሰጣሉ፤ የሰዎች ህግጋት የሚመሰረቱት እንደግለሰቦች እና እንደህዝቦች፣ በሰዎች እና ሰው መካከል፣ የምንፈልገውን ለመቆጣጠር በሚኖር አላማ ነው፤ እና ከሰማይ የተሰጡት መለኮታዊ ህግጋትም በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ መመሪያዎችን ለመጠቀም፣

፻፴፬ ፩ ሀ ት. እና ቃ. ፺፰፥ ፬–፲፤
እ.አ. ፩፥ ፲፪።
ለ ቅ.መ.መ. መልስ መስጠት፣ ሂሳብ፣ ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. ህሊና።
ለ ቅ.መ.መ. ነጻ ምርጫ።
ሐ ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፲፰–፲፱።
፫ ሀ ት. እና ቃ. ፺፰፥ ፰–፲።
፬ ሀ አልማ ፳፩፥ ፳፩–፳፪፤
እ.አ. ፩፥ ፲፩።
ቅ.መ.መ. ማምለክ።
፭ ሀ እ.አ. ፩፥ ፲፪።
ቅ.መ.መ. አመጽ።
፮ ሀ ት. እና ቃ. ፶፰፥ ፳፩፤
፹፰፥ ፴፬።

ለእምነትና ለአምልኮ፣ ሁለቱም በሰው እና በፈጣሪው ይመለሱ ዘንድ ነው።

፯ ገዢዎች፣ ስቴቶች፣ እና መንግስታት መብት እንዳላቸው፣ እና ዜጎች የሀይማኖት እምነታቸውን በነጻነት ለማምለክ እንዲጠብቋቸው ህግጋትን ለማሳለፍ የሚገባቸው እንደሆኑ እናምናለን፤ ነገር ግን ለህግጋት ትኩረትና ክብር እስከ ተሰጠ ድረስ እና እንደዚህ አይነቶቹ የሀይማኖት አስተያየቶች ህዝብን ማሳመጽንና አድማን እንደ ጥፋት የማያዩ እስካልሆነ ድረስ በፍትህ ይህን መብት ለመውሰድ፣ ወይም በአስተያየታቸው እነዚህን ከህግ ውጪ ለማድረግ መብት እንዳላቸው አናምንም።

፰ ወንጀል መስራት እንደ ጥፋቱ መሰረት [ሀ]መቀጣት እንደሚገባው እናምናለን፤ መግደል፣ አገር መክዳት፣ መዝረፍ፣ መስረቅ፣ እና ሰላምን ማፍረስ፣ በሁሉም ሁኔታዎች፣ በወንጀልነታቸው መሰረት እና በሰዎች መካከል ጥፋት ለማድረግ ባላቸው ፍላጎት መሰረት ጥፋቱ በተደረገበት መንግስት ህግጋት ይቀጡ፤ እና ለህዝባዊ ሰላም እና እርጋታ ሁሉም ሰዎች ወደፊት በመሄድ በመልካም ህግጋት ላይ የሚያጠፉትን ለቅጣት ለማምጣት ችሎታቸውን ይጠቀሙበት።

፱ የሀይማኖት ተፅእኖ ከህዝባዊ መንግስት ጋር በመቀላቀል አንድ የሀይማኖት ህብረተሰብን በማበረታታት እና ሌላን በመንፈሳዊ መብት ከህግ ወጪ በማድረግ፣ እና የእያንዳንዱ አባላት መብቶችም እንደ ዜጋ መካዳቸው ትክክል እንደሆነ አናምንም።

፲ የፅድቅ ህብረተሰቦች ሁሉ አባሎቻቸው በሚረብሹበት ጊዜ በህብረተሰቦች መመሪያዎችና መቆጣጠሪያዎች መሰረት ለመቅጣት መብት እንዳላቸው እናምናለን፤ እነዚህ ቅጣቶች ለማህበርተኛነት እና ለመልካም አቋም እስከሆነ ድረስ፤ ነገር ግን ምንም የሀይማኖት ህብረተሰብ ሰዎችን በንብረት ወይም በህይወት መብት ላይ፣ የዚህ አለም ቁሳቁሶችን ሊወስዱባቸው፣ ወይም በህይወታቸው ይሁን በሰውነታቸው ላይ አደጋን ሊያደርሱባቸው፣ ወይም ምንም የሰውነት ቅጣት በእነርሱ ላይ ለማድረግ ስልጣን እንዳላቸው አናምንም። ከህብረተሰቦቻቸው [ሀ]ይወገዙ ዘንድ ህብረታቸውን ለመውሰድ ብቻ ነው የሚችሉት።

፲፩ ሰዎች በህዝባዊ ህግ ለደረሰባቸው አግባብ ላልሆኑ ነገሮች እና ለቅሬታ፣ ለግል መጎሳቆልን፣ ወይም የንብረት ወይም የህሊና መብት መጣስን፣ እና እነዚህን ለመጠበቅ ህግጋት ባሉበት ይግባኝ መጠየቅ እንደሚገባቸው እናምናለን፤ ነገር ግን መንግስትን ከህጋዊ ካልሆነ ወረራ እና ሁሉንም ሰዎች በአስቸኳይ ሁኔታ የመብትን መጣስ እና በህግጋት ይግባኝ ለመጠየቅ በማይቻልበት ጊዜ ርጋታን ለማግኘት ሁሉም ሰዎች ራሳቸውን፣ ባልንጀሮቻቸውን፣ እና ንብረቶቻቸውን በመጠበቅ ጥፋተኞች እንደማይሆኑ እናምናለን።

፲፪ ወንጌልን ለምድር ህዝቦች [ሀ]መስበክ፣ እና በፅድቅ ራሳቸውን ከአለም ክፉት እንዲያድኑ ማስጠንቀቅ ትክክል እንደሆነ እናምናለን፤ ነገር ግን በባሪያዎች ላይ ጣልቃ በመግባት፣ ወይም ለእነርሱ የአለቆቻቸው ፈቃድ ባለማክበር ወንጌልን መስበክ ወይም ማጥመቅ፣ ወይም ጣልቃ በመግባት ወይም ተጽእኖ በማድረግ በዚህ ህይወት ሁኔታቸው እንዳይደሰቱ ማድረግ፣ በዚህም የሰዎችን ህይወት አደጋ ላይ መጣል ትክክለኛ እንደሆነ አናምንም፤ እንደዚህ አይነት ጣልቃ መግባት ህጋዊ ያልሆነ እና ፍትሀዊ እንዳልሆነ እንደሆነ፣ እና በአገልጋይነት ሰዎች በግድ እንዲያዙ ለሚፈቅደው መንግስት ሰላም አደገኛ እንደሆነም እናምናለን።

፰ ሀ አልማ ፴፥ ፯–፲፩፤
ት. እና ቃ. ፵፪፥ ፹፬–፹፯።

፲ ሀ ቅ.መ.መ. ውግዘት።

፲፪ ሀ ቅ.መ.መ. መስበክ፤
የሚስዮን ስራ።

ክፍል ፻፴፭

በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) በካርቴጅ ኢሊኖይ ውስጥ የነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ እና የወንድሙ ፔትሪያርክ ሀይረም ስሚዝ ሰማዕትነትን ይፋ የሆነበት። ይህ መረጃ በ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ቅጂ ውስጥ መጨረሻ ላይ ተጨምሮ ነበር፣ ይህም ጆሴፍ እና ሀይረም ስሚዝ በተገደሉበት ጊዜ ለመታተም ተዘጋጅቶ ነበር።

፩–፪፣ ጆሴፍ እና ሀይረም በካርቴጅ እስር ቤት ሰማእት ሆኑ፤ ፫፣ የነቢዩ ከሁሉም በላይ የሆነው አቋም ተደነቀ፤ ፬–፯፣ ንጹህ ደማቸው የስራውን እውነትነት እና መለኮታዊነት ይመሰክራል።

፩ የዚህን መፅሐፍ እና የመፅሐፈ ሞርሞንን ምስክር ለማተም፣ የነቢዩ [ሀ]ጆሴፍ ስሚዝ እና የፔትሪያርክ ሀይረም ስሚዝ [ለ]ሰማዕትነትን እናሳውቃለን። በሰኔ ፳፯፣ ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) ከሰአት በኋላ በአምስት ሰአት፣ ጥቁር የተቀቡ ከ፻፶ እስከ ፪፻ በሆኑ መሳሪያ በታጠቀ አመጸኛ ቡድን ሰዎች [ሐ]በካርቴጅ እስር ቤት ውስጥ በጥይት ተገደሉ። [መ]ሀይረም ነበር በመጀመሪያ በጥይት የተመታው እና በጸጥታም ሲወድቅ፣ *የምትኩኝ ሰው ነኝ!* ብሎ በሀይል ተናገረ። ጆሴፍ ከመስኮት ዘለለ፣ እና ይህን ሲሞክርም በጥይት ተመታ፣ *አቤቱ ጌታ አምላኬ!* ብሎ በሀይል ተናገረ። ከሞቱም በኋላ በጥይቶችም ተመትተው ነበር፣ እና ሁለቱም በጭካኔ በአራት ጥይቶች ተመትተው ነበር።

፪ በዚያን ጊዜ በክፍሉ ውስጥ የነበሩት ከአስራ ሁለቱት አባላት ሁለቱ፣ [ሀ]ጆን ቴይለር እና ዊለርድ ሪቻርድ ብቻ ነበሩ፤ የመጀመሪያውም በጭካኔ በአራት ጥይቶች ተመትቶ ነበር፣ ነገር ግን ከዚህ በኋላም ድኗል፤ የኋለኛው በእግዚአብሔር ጥበቃ በልብሱም ላይ ቀዳዳ ሳይገኝ አመለጠ።

፫ የጌታ [ሀ]ነቢይ እና [ለ]ባለራዕይ ጆሴፍ ስሚዝ፣ ከኢየሱስ በስተቀር፣ በዚህ አለም ውስጥ ለሰዎች ደህንነት ከኖሩ ሌሎች ሰዎች ሁሉ በላይ አድርጎታል። በአጭር በሆነ በሀያ አመት ጊዜ ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ስጦታ እና ሀይል የተረጎመውን መፅሐፈ ሞርሞንን አምጥቷል፣ እና በሁለት አህጉራት ላይ ይህን ለማተምም ምክንያት ሆኗል፤ ይህም የያዘውን የዘለአለም ወንጌል [ሐ]ሙላትን ወደ ምድር አራት ማዕዘናት ልኳል፤ ራዕያት እና ትእዛዛት የተቀናበሩበትን የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች መፅሀፍን፣ እና ሌሎች ብዙ ብልህ መረጃዎችን እና መመሪያዎችንም ለሰዎች ልጆች ጥቅም አምጥቷል፤ ብዙ ሺህ የኋለኛ ቀን ቅዱሳንን ሰብስቧል፣ ታላቅ [መ]ከተማን መስርቷል፣ እና ሊሞት የማይችልን ታዋቂነትን እና ስምን ትቷል። በታላቅነት ኖሯል፣ እና በእግዚአብሔር እና በህዝቡ አይኖች ውስጥም በታላቅነት ሞቷል፤ እና እንደ ጥንቱም ጊዜ በጌታ እንደተቀቡ ብዙዎችም ተልዕኮውን እና ስራዎቹን [ሠ]በደሙ አስሯል፤ እና ወንድሙ ሀይረምም ይህንኑ አድርጓል። በህይወት አልተለያዩም ነበር፣ እና በሞትም አልተለያዩም!

፬ ጆሴፍ ለህግ ጥያቄ ራሱን አሳልፎ ለመስጠት ወደካርቴጅ ሲሄድ፣ ከመገደሉ ሁለት ወይም ሶስት ቀናት በፊት፣ እንዲህ ብሏል፥ “ለመታረድ እንደሚሄድ

፻፴፭ ፩ሀ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ጆሴፍ ዳግማዊ።
ለ ት. እና ቃ. ፭፥፳፪፤ ፮፥፴። ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
ሐ ቅ.መ.መ. የካርቴጅ እስር ቤት (ዩ.ኤስ.ኤ.)።
መ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣ ሀይረም።
፪ሀ ቅ.መ.መ. ቴይለር፣ ጆን።
፫ሀ ቅ.መ.መ. ነቢይ።
ለ ቅ.መ.መ. ባለራዕይ።
ሐ ት. እና ቃ. ፴፭፥፲፯፤ ፵፪፥፲፪። ቅ.መ.መ. የወንጌል ዳግም መመለስ።
መ ቅ.መ.መ. ናቩ፣ ኢሊኖይ (ዮ.ኤስ.ኤ.)።
ሠ ዕብ. ፱፥፲፮–፲፯፤ ት. እና ቃ. ፻፴፮፥፴፱።

[ሀ]በግ እሄዳለሁ፤ ነገር ግን እንደ በጋ ማለዳ የረጋሁ ነኝ፤ እግዚአብሔርን እና ለሁሉም ሰዎች ከማይጎዳ ንጹ ህሊናም አለኝ። በንፅህና እሞታለሁ፣ እና ስለ እኔ ግን እንዲህ ይባላል—ግድያ በታለመበት ተገደለ።”—በዚያም ማለዳ፣ ሀይረም ለመሄድ ከተዘጋጀ በኋላ—ወደ መታረድ ሊባል ይቻላልን? አዎን፣ ነበርና—በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ በኤተር አስራ ሁለተኛ ምዕራፍ መጨረሻ አጠገብ ያለውን የሚቀጥለውን አንቀፅ አነበበ፣ እና ገጹንም አጠፈ፥

፭ *እናም እንዲህ ሆነ አህዛብ የጌታ ልግስና ይኖራቸው ዘንድ የመንፈስ ጥንካሬም እንዲያገኙ ወደ ጌታ ፀለዩ። እናም እንዲህ ሆነ ጌታም እንዲህ ሲል ተናገረኝ፥ ልግስና ከሌላቸው አንተ ታማኝ ስለሆንክ ላንተ ምንም አይደለም፤ ስለዚህ፣ ልብስህ [ሀ]ይነፃል። እናም ድካምህን በማየትህ በአባቴ ቤት ባዘጋጀሁልህ ስፍራ እንድትቀመጥ ብርቱ ተደርገሀል። እናም አሁን . . . አህዛብን አዎን እናም ደግሞ የምወዳቸው ወንድሞቼን በክርስቶስ [ለ]የፍርድ ወንበር ፊት እስካገኛቸው ተሰናበትኳቸው፤ ሰዎችም ሁሉ ልብሶቼ በእናንተ ደም እንዳልተበከሉ ያውቃሉ።* [ሐ]መስካሪዎቹ ሞተዋል፣ እና ምስክራቸውም ተፅዕኖ አለው።

፮ ሀይረም ስሚዝ በሚያዝያ ፲፰፻፵፬ (እ.አ.አ.) አርባ አራት አመቱ ነበር፣ እና ጆሴፍ ስሚዝ በታህሳስ ፲፰፻፵፫ (እ.አ.አ.) ሰላሳ ስምንት አመቱ ነበር፤ እና ከዚህም በኋላ ስሞቻቸው ከሀይማኖት ሰማዕታት ጋር የተመደቡ ሆኑ፤ እና መፅሐፈ ሞርሞንን በሁሉም ሀገሮች ውስጥ የሚያነቡትም፣ እና ይህን የቤተክርስቲያኗ የትምህርት እና ቃል ኪዳኖች መፅሐፍ የተበላሸውን አለም ወደ ደህንነት ለማምጣት በአስራ ዘጠነኛው መቶ አመት ከሁሉም የሚልቅ ደም እንደ ተከፈለበት ያስታውሱ፤ እና እሳት ለእግዚአብሔር ክብር [ሀ]አረንጓዴን ዛፍ የሚጎዳ ከሆነ፣ የተበላሸውን የወይን ስፍራ ለማፅዳት እንዴት በቀላል የደረቀውን ዛፍ ያነዳል። ለክብር ኖሩ፤ ለክብርም ሞቱ፤ እና ክብርም የዘለአለም ደመወዛቸው ነው። ከዘመን ወደ ዘመን እስከ ትውልድ ድረስ ስሞቻቸው ለተቀደሱት ዕንቁ ይሆናሉ።

፯ ከዚህ በፊት እንዳረጋገጡት፣ በምንም ወንጀል ንጹህ ነበሩ፣ እና በከሀዲዎች እና በክፉ ሰዎች አድማ ብቻ ነበር የታሰሩት፤ እና በካርቴጅ እስር ቤት ወለል ላይ *ንጹህ ደማቸው* “በሞርሞንነት” ላይ በምድር ፍርድ ቤት ውስጥ ሊወገድ በማይቻል ማህተም የታተመ ነው፣ እና በስቴቱ አስተዳዳሪ የተገባው እምነት በመስበር፣ *ንጹህ ደማቸውም* ለኢሊኖይ ስቴት ህጋዊ አልማም ነው፣ አለም ሁሉ ሊከሰው የማይችለው የዘለአለማዊ ወንጌል እውነትነት ምስክርም ነው፤ እና በነጻነት አርማ እና በዩናይትድ ስቴትስ ማግና ካርታ ላይ *ንጹህ ደማቸው* በሁሉም ሀገሮች መካከል ለሚገኙት የዋህ ሰዎች ለኢየሱስ ክርስቶስ ሀይማኖት አምባሳደር ነው፤ እና *ንጹህ ደማቸውም* ዮሐንስ [ሀ]ከመሰዊያው በታች ካያቸው ሰማዕታት ንጹህ ደም ጋር ወደ ሰራዊት ጌታ ያን ደም በምድር ላይ እስኪያበቅል ድረስ ይጮሀሉ። አሜን።

ክፍል ፻፴፮

በዊንተር ኮርተርስ፣ በእስራኤል ስፍራ፣ በኦማሀ ኔሽን ውስጥ፣ በሚዙሪ ወንዝ ምዕራብ ዳርቻ ላይ፣ በካውንስል ብላፍ አየዋ አጠገብ በፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ በኩል የተሰጠ የጌታ ቃል እና ፈቃድ።

፬ሀ ኢሳ. ፶፫፥፯።
፭ሀ ት. እና ቃ. ፹፰፥፸፬–፸፭።
ለ ኤተር ፲፪፥፴፮–፴፰።
ሐ ዕብ. ፱፥፲፮–፲፯።
፮ሀ ሉቃ. ፳፫፥፴፩።
፯ሀ ራዕ. ፮፥፱።

፩–፲፮፣ የእስራኤል ስፍራ ለምዕራቡ ጉዞ እንዴት እንደሚደራጅ ተገልጿል፤ ፲፯–፳፯፣ ቅዱሳን በብዙዎቹ የወንጌል መሰረቶች እንዲኖሩ ታዘዙ፤ ፳፰–፴፫፣ ቅዱሳን ይዘምሩ፣ እልልታንም ያድርጉ፣ ይጸልዩ፣ እና ጥበብን ይማሩ፤ ፴፬–፵፪፣ ነቢያት የሚገደሉት ይከበሩ እና ጥፋተኞችም ይኮነኑ ዘንድ ነው።

፩ የእስራኤል ስፍራ ለምዕራቡ ጉዞአቸውን የተመልከተ የጌታ ቃል እና ፈቃድ፥

፪ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ [ሀ]ቤተክርስቲያን ህዝብ ሁሉ፣ እና ከእነርሱ ጋር የሚጓዙት በቡድን የጌታ አምላካችንን ትእዛዛት እና ደንብ ለመከተል ቃል ኪዳን እና የተስፋ ቃል በመግባት ይደራጁ።

፫ ቡድኖችም [ሀ]በአንድ መቶዎች አለቃዎች፣ በሀምሳዎች አለቃዎች፣ እና በአስሮች አለቃዎች፣ በሚመሯቸው ፕሬዘደንት እና ሁለት አማካሪዎች፣ በአስራ ሁለት [ለ]ሐዋርያት አመራር መሰረት ይደራጁ።

፬ እና ይህም [ሀ]ቃል ኪዳናችን ይሆናል፣ በጌታ [ለ]ስርዓቶች ሁሉ [ሐ]እንሄዳለን።

፭ ሁሉም ቡድኖች የተጣመዱ እንስሣትን፣ ጋሪዎችን፣ የሚያስፈልጓቸውን፣ ልብሶችን፣ እና ሌላ ለጉዞ የሚያስፈልጉትን፣ ቢቻሉም፣ ራሳቸውን ያዘጋጁ።

፮ ቡድኖች ከተደራጁ በኋላ ለሚቀሩት ለመዘጋጀት ለመስራት በሚችሉት ይሂዱ።

፯ እያንዳንዱም ቡድን ከአለቆቻቸውና ከፕሬዘደንቶቻቸው ጋር በሚቀጥለው ጸደይ ምን ያህል ለመሄድ እንደሚችሉ ይወስኑ፤ ከዚያም ብቁ ሰውነት ያላቸው እና ችሎታ ያላቸው ሰዎች የተጠመዱ እንስሣሳትን፣ ዘሮችን፣ እና የማረሻ እቃዎችን ይዘው የጸደይ አትክልቶችን ለመትከል እንዲሄዱ ፈርቀዳጆች የሚሆኑ ብቁ ቁጥሮችን ምረጡ።

፰ የባልቴት እና አባት የሌላቸው ለቅሶዎች ወደጌታ ጆሮዎች በህዝብ ላይ እንዳይመጣ፣ እያንዳድኑም ቡድን በንብረቶቻቸውን በተከፋፈሉበት መጠን፣ [ሀ]ድሆችን፣ [ለ]ባልቴቶች፣ [ሐ]አባቶች የሌላቸውን፣ እና ወደ ጦር ሰራዊነት የሄዱትን ቤተሰቦችን በመውሰድ በእኩል ድርሻን ይሸከሙ።

፱ እያንዳንዱም ቡድን ለዚህ ዘመን ለሚቀሩትም ቤቶች፣ እና እህልን ለመትከልም መሬቶችን ያዘጋጁ፤ እና ይህም ህዝቦቹን በሚመለከት የጌታ ፈቃድ ነው።

፲ እያንዳንዱም ሰው የእራሱን ተፅዕኖ እና ንብረት ይህን ህዝቡ የፅዮንን [ሀ]ካስማ ጌታ ወደሚወስደው ስፍራ ለመውሰድ ይጠቀም።

፲፩ እና ይህን በንጹህ ልብ፣ በሙሉ ታማኝነት ብታደርጉ፣ [ሀ]ትባረካላችሁ፤ በመንጋዎቻችሁም፣ እና በመሬቶቻችሁ፣ እና በቤቶቻችሁ እና በቤተሰቦቻችሁ ትባረካላችሁ።

፲፪ አገልጋዮቼ ኤዝራ ቲ ቤንሰን እና ኢራስተስ ስኖው ቡድንን ያደራጁ።

፲፫ እና አገልጋዮቼ ኦርሰን ፕራት እና ዊልፈርድ ዉድረፍ ቡድንን ያደራጁ።

፲፬ ደግሞም፣ አገልጋዮቼ አማሳ ላይመን እና ጆርጅ ኤ ስሚዝ ቡድንን ያደራጁ።

፲፭ እና ፕሬዘደንቶችንና የመቶዎችን፣ የሀምሳዎች፣ እና የአስሮች አለቃዎችን ይመድቡ።

፲፮ እና የተመደቡትም ይሂዱ እና ወደ ሰላም ምድርም ለመሄድ ይዘጋጁ ዘንድ ይህን ፈቃዴን ለቅዱሳን ያስተምሩ።

፲፯ ሂዱ እና እንደ ነገርኳችሁም አድርጉ፣ እና ጠላቶቻችሁን አትፍሩ፤ ስራዬን ለማቆም ምንም ሀይል የላቸውምና።

፲፰ ፅዮንም በጊዜዬ [ሀ]ትድናለች።

፲፱ ማንም ሰው እራሱን ከፍ ለማድረግ

፻፴፮ ፪ሀ ቅ.መ.መ. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።

፫ሀ ዘፀአ. ፲፰፥፳፩–፳፮።

ለ ቅ.መ.መ. ሐዋሪያ።

፬ሀ ቅ.መ.መ. ቃል ኪዳን።

ለ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።

ሐ ቅ.መ.መ. መራመድ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መራመድ (መሄድ)።

፰ሀ ቅ.መ.መ. ደሀ።

ለ ቅ.መ.መ. ባል የሞተባት።

ሐ ያዕ. ፩፥፳፯፤ ፫ ኔፊ ፳፬፥፭።

፲ሀ ቅ.መ.መ. ካስማ።

፲፩ሀ ዘዳግ. ፳፰፥፩–፲፬። ቅ.መ.መ. መባረክ፣ የተባረከ፣ በረከት።

፲፰ሀ ት. እና ቃ. ፱፥፲፫።

ቢፈልግ እና [ሀ]ምክሬን ባይፈልግ፣ ምንም ሀይል አይኖረውም እና ሞኝነቱም ግልጽ ይደረጋሉ።

፳ ፈልጉ፤ እና የእርስ በርሳችሁን ቃል ኪዳኖች ሁሉ [ሀ]ጠብቁ፤ እና የወንድማች ሁንም [ለ]አትመኙ።

፳፩ የእግዚአብሔርን የአምላካችሁን ስም በከንቱ የመጥራትን ክፉት ከራሳችሁ [ሀ]አስወግዱ፤ እኔ ጌታ አምላካችሁ፣ የአባቶቻችሁ [ለ]አምላክ፣ የአብርሐምና የይስሀቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝና።

፳፪ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ምድር መርቼ ያወጣኋቸው [ሀ]እኔ ነኝ፤ እና በመጨረሻዎቹም ቀናት እጆቼ የእስራኤልን ህዝብ [ለ]ለማዳን ተዘርግተዋል።

፳፫ እርስ በራስም [ሀ]መጣላትን አቁሙ፤ እርስ በራስም [ለ]ክፉት መነጋገርን አቁሙ።

፳፬ [ሀ]ሰካርን አቁሙ፤ እና ቃላቶቻችሁም እርስ በራሳችሁ [ለ]የሚያንጹ ይሁኑ።

፳፭ ከባልንጀራችሁ ከተበደራችሁ፣ [ሀ]የተበረዳችሁን መልሱ፤ እና ለመክፈል ባትችሉም ወዲያው በመሄድ ለባንጀራችሁ ንገሩ፣ አለበለዚያም ይፈርድባችኋልና።

፳፮ ባልንጀሮቻችሁ [ሀ]ያጡትን ነገር ብታገኙ፣ ዳግሞም መልሳችሁ እስከምትሰጡም ድረስ በትጋት ፈልጉት።

፳፯ ጥበብ ያለው መጋቢም እንድትሆኑ ዘንድ፣ ያላችሁን ለመጠበቅ [ሀ]ትጉ ሁኑ፤ ይህም የጌታ አምላካችሁ የነጻ ስጦታ ነውና፣ እና እናንተም የእርሱ [ለ]መጋቢ ናችሁና።

፳፰ ደስተኛ ብትሆኑ፣ ጌታን [ሀ]በዝማሬ፣ በሙዚቃ፣ በእልልታ፣ እና በምስጋና [ለ]ጸሎት እና [ሐ]በምስጋና አምልኩ።

፳፱ [ሀ]የከፉችሁ ብትሆኑም፣ ነፍሶቻችሁ [ለ]ይደሰቱ ዘንድ፣ ጌታ አምላካችሁን በልመና ጥሩ።

፴ ጠላቶቻችሁን አትፍሩ፣ እነርሱ በእጆቼ ውስጥ ናቸው እና እንደፈቃዴም አደርግባቸዋለሁና።

፴፩ ለእነርሱ ያለኝን [ሀ]ክብር፣ እንዲሁም የፅዮንን ክብር፣ ለመቀበል ይዘጋጁ ዘንድ፣ ህዝቤ በሁሉም ነገሮች [ለ]መሞከር አለባቸው፤ እና [ሐ]መገሰፅን ለመቀበል የማይችል ለመንግስቴ ብቁ አይደለም።

፴፪ ደንቆሮውም አይኖቹ ይከፈቱ ዘንድ እና እንዲያይ፣ እና ጆሮዎቹም ተከፍተው ይሰማ ዘንድ፣ ራሱን [ሀ]ትሁት በማድረግ እና ጌታ አምላኩን በመጥራት [ለ]ጥበብን ይማር፤

፴፫ ትሁቱን እና የተዋረደውን አበራላቸው እና አምላክ የሌላቸውን እኮንን ዘንድ [ሀ]መንፈሴን ልኬአለሁና።

፴፬ ወንድሞቻችሁ፣ እንዲሁም ያሰደዷችሁ ህዝብ፣ እናንተን እና ምስክሮቻችሁን [ሀ]አስወግደዋል፤

፴፭ አሁንም በምጥ እንደተያዘች ሴት የሚያሳቅቃቸው ቀን፣ እንዲሁም የሀዘን

፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ምክር (ስም)።
፳ ሀ ቅ.መ.መ. ታማኝ፣
ታማኝነት።
ለ ቅ.መ.መ. መመኘት።
፳፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማራከስ።
ለ ዘፀአ. ፫÷፯፤
፩ ኔፊ ፲፱÷፲።
፳፪ ሀ ዘፀአ. ፲፫÷፲፰፤
ኤር. ፬÷፭–፯፤
፩ ኔፊ ፭÷፲፭፤
አልማ ፴፯÷፳፰።
ቅ.መ.መ. ያህዌህ።
ለ ኤር. ፴÷፲፤
ሕዝ. ፳÷፴፫–፴፬፤
ት. እና ቃ. ፴፰÷፴፫።
፳፫ ሀ ፫ ኔፊ ፲፩÷፳፱–፴።
ቅ.መ.መ. ጸብ።
ለ ት. እና ቃ. ፳÷፶፬።
ቅ.መ.መ. ክፉ መናገር።
፳፬ ሀ ቅ.መ.መ. የጥበብ ቃል።
ለ ት. እና ቃ. ፻፰÷፯።
፳፭ ሀ መዝ. ፴፯÷፳፩፤
ሞዛያ ፬÷፳፰።
ቅ.መ.መ. ታማኝ፣
ታማኝነት፤
እዳ።
፳፮ ሀ ዘሌዋ. ፮÷፬፤
ዘዳግ. ፳፪÷፫።
፳፯ ሀ ቅ.መ.መ. ትጋት።
ለ ቅ.መ.መ. መጋቢ፣
መጋቢነት።
፳፰ ሀ ቅ.መ.መ. መዘመር።
ለ ቅ.መ.መ. ጸሎት።
ሐ ፬ ዜና ፭÷፲፫፤
ት. እና ቃ. ፶፱÷፲፭–፲፮።
ቅ.መ.መ. አመስጋኝ፣
ምስጋናን፣ ምስጋና
መስጠት።
፳፱ ሀ ፬ ሳሙ. ፳፬÷፯።
ለ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፴፩ ሀ ሮሜ ፰÷፲፰፤
ት. እና ቃ. ፶፰÷፫–፬።
ቅ.መ.መ. ክብር።
ለ ት. እና ቃ. ፻፩÷፬።
ቅ.መ.መ. ጭንቀት።
ሐ ቅ.መ.መ. መገሰጽ፣ ተግሳጽ።
፴፪ ሀ ቅ.መ.መ. ትሁት፣ ትሕትና።
ለ ቅ.መ.መ. ጥበብ።
፴፫ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ ቅዱስ።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ማሳደድ፣
መሳደድ።

ቀናት፣ ይመጣል፤ እና ወዲያው፣ አዎን፣ በጣም ፈጥነውም፣ ንስሀ ባይገቡ ሀዘናቸውም ታላቅ ይሆናል።

፴፮ ነቢያትንና ወደ እነርሱ የተላኩትን ገድለዋልና፤ እና ከምድር በእነርሱ ላይ የሚጮሁትንም ንጹህ ደም አፍሥሠዋል።

፴፯ ስለዚህ፣ በእነዚህ ነገሮች አትደነቁ፣ እናንት [ሀ]ንጹህ አይደላችሁምና፤ ክብሬን ለመቀበል ገና አትችሉም፤ ነገር ግን ከአዳም እስከ አብርሐም፣ ከአብርሐም እስከ ሙሴ፣ ከሙሴ እስከ ኢየሱስና ሐዋርያት፣ እና ከኢየሱስና ሐዋሪያቱ በሚያገለግሉኝ አገልጋዮቼ [ለ]በመላእክቴ፣ እና ከሰማያት በድምጼ ስራዬን እንዲያመጣ በጠራሁት፣ እስከ ጆሴፍ ስሚዝ [ሐ]የሰጠኋችሁን ቃላቴን ለማክበር ታማኝ ከሆናችሁ፣ ይህንንም ታዩታላችሁ፤

፴፰ ይህን መሰረትም መሰረተ፣ እና ታማኝም ነበር፤ እና ወደ እኔም ወሰድኩት።

፴፱ ብዙዎች በሞቱ ምክንያት ተደንቀው ነበር፤ ነገር ግን እንዲከብር እና ክፉዎችም ይኮነኑ ዘንድ [ሀ]ምስክሩን [ለ]በደሙ [ሐ]ማተሙ አስፈላጊ ነበር።

፵ በዚህም የስሜን ምስክር በመተው ብቻ፣ [ሀ]ከጠላቶቻችሁ አላዳንኳችሁም?

፵፩ አሁን፣ ስለዚህ፣ [ሀ]የቤተክርስቲያኔ ህዝብ ሆይ፣ አድምጡ፤ እና እናንት ሽማግሌዎችም አብራችሁ ስሙ፤ [ለ]መንግስቴን ተቀብላችኋል።

፵፪ ፍርድ እንዳይመጣባችሁ እና እምነታችሁም እንዳይወድቅባችሁ፣ እና ጠላቶቻችሁ እንዳያሸንፉችሁ ዘንድ፣ ትእዛዛቴን ሁሉ በማክበር ትጉ ሁኑ። በዚህ ጊዜ ተጨማሪ አልገልፅም። አሜን እና አሜን።

ክፍል ፻፴፯

በጥር ፳፩፣ ፲፰፻፴፮ (እ.አ.አ.) በከርትላንድ በቤተመቅደስ ውስጥ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። ጊዜውም በዚያ ጊዜ ቤተመቅደስን ለመምረቅ በመዘጋጀት ስርዓቶችን በሚያስተዳድርበት ጊዜ ነበር።

፩–፮፣ ነቢዩ ወንድሙን አልቭንን በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ አየ፤ ፯–፱፣ የሙታን ደህንነት ትምህርት ተገለጠ፤ ፲፣ ሁሉም ልጆች በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ይድናሉ።

፩ [ሀ]ሰማያት ተከፈቱልን፣ እና የእግዚአብሔርን [ለ]ሰለስቲያል መንግስትን እና የእዚያን ክብር አየሁ፣ [ሐ]በሰውነት ይሁን ከዚያ ውጪ አላወቅሁም።

፪ በእሳት [ሀ]ነበልባል የተከበበው፣ የዚያ መንግስት ወራሾች የሚገቡበት [ለ]በር በጣም ታላቅ ውበት እንዳለውም አየሁ።

፫ ደግሞም [ሀ]አብና [ለ]ወልድ የሚቀመጡበ

፴፯ ሀ ቅ.መ.መ. ንጹህ፣ ንጹህነት።
ለ ራዕ. ፲፬፥ ፮፤ ት. እና ቃ. ፻፲፥ ፲፩–፲፮፤ ፻፳፰፥ ፲፱–፳፩፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፴–፵፯።
ሐ ሔለ. ፰፥ ፲፰።
፴፱ ሀ ሞዛያ ፲፯፥ ፳፤ ት. እና ቃ. ፻፴፭፥ ፫።
ለ ቅ.መ.መ. ምስክርነት።
ሐ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣ ሰማዕትነት።
፵ ሀ ዘፀአ. ፳፫፥ ፳፪፤ ት. እና ቃ. ፰፥ ፬፤ ፻፭፥ ፲፭።
፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።
ለ ዳን. ፯፥ ፳፯።
፻፴፯ ፩ ሀ የሐዋ. ፯፥ ፶፭–፶፮፤ ፩ ኔፊ ፩፥ ፰፤ ሔለ. ፭፥ ፵፭–፵፱፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥ ፵፫።
ለ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል ክብር።
ሐ ፪ ቆሮ. ፲፪፥ ፪–፬፤ ፩ ኔፊ ፲፩፥ ፩፤ ሙሴ ፩፥ ፲፩።
፪ ሀ ዘፀአ. ፳፬፥ ፲፯፤ ኢሳ. ፴፫፥ ፲፬–፲፭፤ ሔለ. ፭፥ ፳፫፤ ት. እና ቃ. ፻፴፥ ፯።
ለ ፪ ኔፊ ፱፥ ፵፩፤ ፴፩፥ ፲፯።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር ወልድ።

ትን በጣም ብሩህ የሆነውን የእግዚአብሔር [ሐ]የክብር ዙፋንንም ተመለከትኩ።

፬ [ሀ]በወርቅ ምንጣፍ አምሳል የሆኑትን የመንግስቱን ውብ መንገዶችንም አየሁ።

፭ አባት [ሀ]አዳምን እና [ለ]አብርሐምንም፤ እና [ሐ]አባቴና [መ]እናቴንም፤ ለብዙ ጊዜ ሞቶ የነበረው ወንድሜ [ሠ]አልቭንንም አየሁ።

፮ እና ጌታ እስራኤልን [ሀ]ዳግም ለመሰብሰብ እጁን ከመዘርጋቱ በፊት ከዚህ ህይወት ሄዶ ስለነበረ፣ እና ለኃጢአት ስርየት [ለ]ስላልተጠመቀ፣ በዚያ መንግስት ውስጥ እንዴት [ሐ]ውርስ እንዳገኘም ተደነቅሁኝ።

፯ እንዲህም ሲል የጌታ [ሀ]ድምፅ ወደ እኔ መጣ፥ ለመቆየት ቢፈቀድላቸው ይቀበሉት የነበሩት፣ ይህን ወንጌል [ለ]ባለማወቅ የሞቱት ሁሉ የእግዚአብሔር [ሐ]ሰለስቲያል መንግስት [መ]ወራሾች ይሆናሉ።

፰ ደግሞም በሙሉ ልባቸው ይህን [ሀ]ይቀበሉ የነበሩ፣ ካለዚህ እውቀት ከዚህ በኋላ የሞቱት ሁሉ የዚያ መንግስቱ ወራሾች ይሆናሉ፤

፱ እኔ ጌታ ሁሉንም ሰዎች [ሀ]በስራዎቻቸው መሰረት፣ እንደልባቸውም [ለ]ምኞት [ሐ]እፈርድባቸዋለሁና።

፲ እና በተጠያቂነት [ሀ]እድሜም ከመድረሳቸው በፊት የሞቱትን ልጆች ሁሉ በሰማይ ሰለስቲያል መንግስት ውስጥ [ለ]እንደዳኑም ተመለከትኩኝ።

ክፍል ፻፴፰

በጥቅምት ፫፣ ፲፱፻፲፰ (እ.አ.አ.) በሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ ውስጥ ለፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ የተሰጠ ራዕይ። በጥቅምት ፬፣ ፲፱፻፲፰ (እ.አ.አ.) በ፹፱ነኛው የቤተክርስቲያኗ የግማሽ አመት አጠቃላይ ጉባኤ መክፈቻ ንግግራቸው ላይ፣ ፕሬዘደንት ስሚዝ ባለፉት ወራት የተለያዩ መለኮታዊ መልእክቶችን እንደተቀበሉ ገለጹ። ፕሬዘደንት ስሚዝ ባለፈው ቀን ከተቀበሏቸው ከእነዚህ አንዱ አዳኝ ሰውነቱ በመቃብር ውስጥ እያለ የሙታንን መንፈስ መጎብኘቱን በሚመለከት ነበር። በጉባኤው መዝጊያ ወዲያውም ተፅፎ ነበር። በጥቅምት ፴፩፣ ፲፰፻፲፰ (እ.አ.አ.) ይህም ለቀዳሚ አመራር አማካሪዎች፣ ለአስራ ሑለቱ ቡድን፣ እና ለፔትሪያርክ ቀረበ፣ እና እነርሱም በአንድ ድምፅ ተቀብለውት ነበር።

፩–፲፣ ፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ ስለ ጴጥሮስ ፅሁፎች እና ጌታ የመንፈስ አለምን ስለመጎብኘቱ ያሰላስሉ ነበር፤ ፲፩–፳፬፣ ፕሬዘደንት ስሚዝ የሞቱት ጻድ

፫ሐ ኢሳ. ፮፥፩፤
ሕዝ. ፩፥፳፮–፳፰።
፬ሀ ራዕ. ፳፩፥፳፩፤
ት. እና ቃ. ፻፲፥፪።
፭ሀ ቅ.መ.መ. አዳም።
ለ ት. እና ቃ. ፻፴፪፥፳፱።
ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ሐ ት. እና ቃ. ፻፳፬፥፲፱።
ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ጆሴፍ ቀዳማዊ።
መ ቅ.መ.መ. ስሚዝ፣
ሉሲ ማክ።
ሠ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፬።
፮ሀ ዮሐ. ፫፥፫–፭፤
፪ ኔፊ ፱፥፳፫፤
ኤተር ፬፥፲፰–፲፱፤
ት. እና ቃ. ፸፮፥፶–፶፪፤
፹፬፥፸፬።
ቅ.መ.መ. ጥምቀት፣
መጥመቅ።
ለ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
ሐ ኢሳ. ፲፩፥፲፩፤
፩ ኔፊ ፳፪፥፲–፲፪፤
ያዕቆ. ፮፥፪።
ቅ.መ.መ. እስራኤል—
የእስራኤል መሰብሰብ።
፯ሀ ሔለ. ፭፥፴።
ቅ.መ.መ. ራዕይ።
ለ ጆ.ስ.ት. ፩ ጴጥ. ፬፥፮
(ተጨማሪ)፤
፪ ኔፊ ፱፥፳፭–፳፮፤
ሞዛያ ፲፭፥፳፬።
ሐ ቅ.መ.መ. የሰለስቲያል
ክብር።
መ ት. እና ቃ. ፸፮፥፶–፸።
፰ሀ አልማ ፲፰፥፴፪፤
ት. እና ቃ. ፮፥፲፮።
፱ሀ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
ለ ት. እና ቃ. ፷፬፥፴፬።
ቅ.መ.መ. ልብ።
ሐ ራዕ. ፳፥፲፪–፲፫።
ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
፲ሀ ቅ.መ.መ. መልስ
መስጠት፣ ሂሳብ፣
ተጠያቂነት፣ ሀላፊነት።
ለ ቅ.መ.መ. ደህንነት—
የልጆች ደህንነት።

ቃን በገነት ውስጥ ተሰብስበው እና ክርስቶስም በመካከላቸው ያገለገለበትን አዩ፤ ፳፭–፴፯፣ በመናፍስትም መካከል ወንጌልን ለመስበክ እንዴት እንደተደራጀም ተመለከቱ፤ ፴፰–፶፪፣ ከሞት ከመነሳታቸው በፊት የመንፈስ ሁኔታቸውን እንደ ባርነት የሚመለከቱትን አዳምን፣ ሔዋንን፣ እና ብዙ ቅዱሳን ነቢያትን በመንፈስ አለም ውስጥ አዩአቸው፤ ፶፫–፷፣ ዛሬ በፅድቅ የሚሞቱ በመንፈስ አለም ውስጥ አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ።

፩ በጥቅምት ሶስተኛው ቀን፣ በአስራ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት አመተ ምህረት ውስጥ፣ ቅዱሳን መጻህፍትን በክፍሌ ቁጭ ብዬ [ሀ]አሰላስል ነበር፤

፪ እና ለአለም [ሀ]ቤዛነት፣ የእግዚአብሔር ልጅ ያደረገውን ታላቅ [ለ]የኃጢአት ክፍያ እያሰብኩ ነበር፤

፫ እና [ሀ]የቤዛው ወደአለም መምጣት አብ እና ወልድ ያሳዩትን ታላቅ እና አስደናቂ [ለ]ፍቅርም፤

፬ በእርሱ [ሀ]የኃጢአት ክፍያ፣ እና በወንጌሉ መሰረታዊ መርሆች [ለ]ታዛዥነት፣ የሰው ዘር ይድን ዘንድ እንደ ሆነ አሰላስል ነበር።

፭ በዚህ ተይዤ እያለሁ፣ ከጌታ መሰቀል በኋላ ወንጌሉ ተሰብኮላቸው ለነበሩት [ሀ]በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጶዶቅያም፣ እና በሌሎች የእስያ ክፍሎች ውስጥ ለተበተኑት [ለ]የጥንት ቅዱሳን ሐዋሪያው ጴጥሮስ ወደጻፈው አዕምሮዬ ተመለሰ።

፮ መፅሐፍ ቅዱስን ከፈትኩ እና የጴጥሮስን የመጀመሪያ መልእክት ሶስተኛ እና አራተኛውን ምዕራፎች አነበብኩኝ፣ እና ሳነብም ቀድሞ ከነበሩት በላይ በሚቀጥሉት ምንባቦች በጣም ተነካሁ፥

፯ “ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶ አልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥

፰ “በእርሱም ደግሞ ሄዶ [ሀ]በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤

፱ “ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም።” (፩ ጴጥሮስ ፫፥፲፰–፳)።

፲ “እንደሰዎች በሥጋ እንዲፈረድባቸው በመንፈስ ግን እንደ እግዚአብሔር እንዲኖሩ ስለዚህ ምክንያት ወንጌል ለሙታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበርና።” (፩ ጴጥሮስ ፬፥፮)።

፲፩ ስለእነዚህ [ሀ]ስለተጻፉት ነገሮች ሳሰላስል፣ የመረዳት [ለ]አይኖቼ ተከፈቱ፣ እና የጌታ መንፈስ [ሐ]አረፈብኝ፣ እና ታላቁንና ታናሹን [መ]የሙታን ሰራዊትን አየሁ።

፲፪ እና በዚያም በአንድ ስፍራም አብረው የተሰበሰቡ፣ በስጋ ሲኖሩ በኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር [ሀ]ታማኝ የነበሩ፣ ቁጥራቸው ታላቅ የሆኑ [ለ]የጻድቃን የመንፈስ ቡድኖች ነበሩ፤

፲፫ እና እንደ እግዚአብሔር ልጅ አይነት ታላቅ [ሀ]መስዋዕት ያቀረቡ፣ እና በቤዛው ስምም [ለ]ስቃይንም የተቀበሉ ነበሩ።

፲፬ እነዚህ ሁሉ [ሀ]በአብ እግዚአብሔር እና [ለ]በአንድያ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ

፻፴፰ ፩ ሀ ቅ.መ.መ. ማሰላሰል።
፪ ሀ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ለ ማቴ. ፳፥፳፰። ቅ.መ.መ. የኃጢያት ዋጋን መክፈል፤ የኃጢያት ክፍያ።
፫ ሀ ቅ.መ.መ. መድኃኒት።
ለ ዮሐ. ፫፥፲፮። ቅ.መ.መ. ፍቅር።
፬ ሀ እ.አ. ፩፥፫።
ለ ማቴ. ፯፥፳፩። ቅ.መ.መ. ታዛዥነት፣ ታዛዥ፣ መታዘዝ።
፭ ሀ ፩ ጴጥ. ፩፥፩።
ለ ይህም በፊት የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የነበሩማለት ነው።
፰ ሀ ኢሳ. ፷፩፥፩፤ ሉቃ. ፬፥፲፰፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፫–፸፬፤ ፹፰፥፺፱።
፲፩ ሀ ቅ.መ.መ. ቅዱሳት መጻህፍት—የቅዱሣት መጻህፍት ዋጋዎች።
ለ ኤፌ. ፩፥፲፰፤ ት. እና ቃ. ፸፮፥፲፣ ፲፪፣ ፲፱።
ሐ ኢሳ. ፲፩፥፪።
መ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
፲፪ ሀ ት. እና ቃ. ፮፥፲፫፤ ፶፩፥፲፱፤ ፸፮፥፶፩–፶፫።
ለ ት. እና ቃ. ፸፮፥፷፱–፸።
፲፫ ሀ ቅ.መ.መ. መስዋዕት።
ለ ማቴ. ፭፥፲–፲፪።
፲፬ ሀ ቅ.መ.መ. እግዚአብሔር፣ አምላክ—እግዚአብሔር አብ።
ለ ቅ.መ.መ. አንድያ ልጅ።

[ሐ]ጸጋ አማካይነት ለክብሩ [መ]ትንሳኤ ፅኑ [ሠ]ተስፋ ኖሮአቸው ከስጋ ህይወት ተለይተው ነበር።

፲፭ [ሀ]በደስታ እና በተድላ ተሞልተው እንደነበሩም አየሁ፣ እና የሚድኑበት ቀን ስለመጣ አብረው ተደስተው ነበር።

፲፮ ከሞት [ሀ]እስራት ቤዛነታቸውን ይገለጽ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ [ለ]መንፈስ አለም መምጣትን ተሰብስበው ይጠባበቁ ነበር።

፲፯ ያንቀላፋውም ትቢያ የሆነው አካላቸው ወደ ፍጹም ትክክለኛው መልክ፣ [ሀ]አጥንትም ከአጥንቱ፣ እና ጅማትና ስጋ በእነርሱም ላይ [ለ]በዳግም እንዲመለስ፣ እና [ሐ]መንፈስም ከሰውነት ጋር ደግሞም እንዳይለያዩ፣ [መ]የደስታ ሙላትን ይቀበሉ ዘንድ ነበር።

፲፰ ብዙዎች ከሞት ሰንሰለት በሚድኑበት ሰአት እየተደሰቱ፣ እየጠበቁ ሲነጋገሩም፣ የእግዚአብሔር ልጅ ታማኝ ለነበሩት ለታሰሩት [ሀ]ነጻነትን በማወጅ መጣ፤

፲፱ እና እዛም ዘለአለማዊ [ሀ]ወንጌልን፣ የትንሳኤን እና የሰው ዘር [ለ]ከውድቀትና ከግል ኃጢአት [ሐ]ንስሀ ስለመግባት የቤዛነትን ትምህርት [መ]ሰበከላቸው።

፳ ነገር ግን [ሀ]ለክፉዎቹ አልሄደም፣ እና እግዚአብሔርን በሚጠሉት መካከል እና በስጋ እያሉ ንስሀ ላልገቡ ራሳቸውን [ለ]ወዳበላሹትም ድምጹ አለተነሳም።

፳፩ ወይም የጥንት ነቢያትን ምስክሮች እና ማስጠንቀቂያዎችን ያስወገዱት አመጸኞችም ፊቱን አላዩትም፣ ወይም ፊቱንም አልተመለከቱም።

፳፪ እነዚህም በነበሩበት [ሀ]ጭለማ ነገሰ፣ ነገር ግን በጻድቃን መካከል [ለ]ሰላም ነበር፤

፳፫ እና ቅዱሳንም [ሀ]በቤዛነታቸው ተደሰቱ፣ እናም [ለ]በጉልበታቸው ተንበርክከው የእግዚአብሔርን ልጅ እንደቤዛቸው እና ከሞት እና ከገሀነም [ሐ]ሰንሰለት ያዳናቸው እንደሆነም አምነው ተቀበሉ።

፳፬ መልካቸውም በራ፣ እና የጌታ [ሀ]ድምቀትም በእነርሱ ላይ አረፈ፣ እና ለቅዱስ ስሙም ምስጋናን [ለ]ዘመሩ።

፳፭ አዳኝ በአይሁድና በእስራኤል ቤት መካከል በአገልግሎቱ፣ ዘለአለማዊ ወንጌልን ሊያስተምራቸው እንደተጋ እና ለንስሀም ለመጥራት ሶስት አመታትን እንዳሳለፈ ስለገባኝ ተደነቅሁኝም፤

፳፮ እና ግን፣ ምንም እንኳን በታላቅ [ሀ]ሀይል እና ስልጣን ታላቅ ስራዎች፣ እና ተዕምራትን ቢሰራም እውነትንም ቢያውጅ፣ ከጥቂቶች በስተቀር ድምጹን ያደመጡና በመገኘቱም የተደሰቱ፣ እና ከእጆቹም ደህንነትን የተቀበሉ ብዙ አልነበሩም።

፳፯ ነገር ግን ከሞቱት መካከል የነበረው አገልግሎቱ በተሰቀለበት እና በትንሳኤው መካከል በነበረው [ሀ]ጥቂት ጊዜ የተወሰነ ነበር፤

፳፰ ስለጴጥሮስ ቃላትም አሰብኩ—በዚህም ውስጥ እንዲህ አለ የእግዚአብሔር ልጅ ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበ

፲፬ ሐ ቅ.መ.መ. ጸጋ።
መ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ሠ ኤተር ፲፪፥፬፤
ሞሮኒ ፯፥፫፣ ፵–፵፬።
ቅ.መ.መ. ተስፋ።
፲፭ ሀ ኢሳ. ፶፩፥፲፩፤
አልማ ፵፥፲፪።
፲፮ ሀ ሞር. ፱፥፲፫።
ለ ሉቃ. ፳፫፥፵፫፤
አልማ ፵፥፲፩–፲፬።
ቅ.መ.መ. ገነት።
፲፯ ሀ ሕዝ. ፴፯፥፩–፲፬።
ለ ፪ ኔፊ ፱፥፲–፲፫።
ሐ ት. እና ቃ. ፺፫፥፴፫–፴፬።
መ ቅ.መ.መ. ደስታ።
፲፰ ሀ ኢሳ. ፷፩፥፩።
ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
፲፱ ሀ ቅ.መ.መ. ወንጌል።
ለ ቅ.መ.መ. የአዳም እና የሔዋን ውድቀት።
ሐ ቅ.መ.መ. መጸጸት፣ ንስሀ መግባት።
መ ት. እና ቃ. ፸፮፥፸፪–፸፬።
፳ ሀ አልማ ፵፥፲፫–፲፬።
ቅ.መ.መ. ሲዖል፤ ክፉ፣ ክፋት።
ለ ፩ ኔፊ ፲፥፳፩።
፳፪ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ለ ቅ.መ.መ. ሰላም።
፳፫ ሀ ቅ.መ.መ. የቤዛነት ዕቅድ።
ለ ሮሜ ፲፬፥፲፩፤
ሞዛያ ፳፯፥፴፩።
ሐ ፪ ኔፊ ፩፥፲፫፤
አልማ ፲፪፥፲፩።
፳፬ ሀ መዝ. ፻፬፥፩–፪፤
ኢሳ. ፷፥፲፱፤
ራዕ. ፳፪፥፭፤
ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፲፯።
ቅ.መ.መ. ብርሀን፣
የክርስቶስ ብርሀን።
ለ ቅ.መ.መ. መዘመር።
፳፮ ሀ ፩ ኔፊ ፲፩፥፳፰።
፳፯ ሀ ማር. ፰፥፴፩።

ከላቸው፤ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ ላልታዘዙትም— እና ከእነርሱ ጋር በነበረው አጭር ጊዜ ለእነዚያ መንፈሶች ለመስበክ እና አስፈላጊ የሆነውን አገልግሎት ለመፈጸም እንዴት ነበር የቻለው።

፳፱ እና ስለዚህም ሳስብ፣ አይኖቼ ተከፈቱ፣ እና [ሀ]ተረዳሁኝም፣ እና በክፉዎች እና ታዛዥ ባልሆኑት እውነትንም በካዱት መካከል እንዲያስተምራቸው ጌታ እንዳልሄደም ታየኝ፤

፴ ነገር ግን እነሆ፣ ከጻድቃን መካከል ሀይሎቹን አደራጀ እና [ሀ]ሀይል እና ስልጣንን የተላበሱ መልእክተኞቹን መደበ፣ እና እንዲሄዱና የወንጌሉን ብርሀን [ለ]በጭለማ ላሉት፣ እንዲሁም [ሐ]ለሁሉም የሰዎች መንፈሶች እንዲወስዱ ሀላፊነትን ሰጣቸው፤ እና በዚህም ወንጌሉ ለሙታን ተሰብኮ ነበር።

፴፩ እና የተመረጡት መልእክተኞችም ጌታን [ሀ]የመቀበልን ቀን በማወጅ እና ለታሰሩት፣ እንዲሁም ለኃጢአታቸው ንስሀ በመግባት ወንጌሉን ለሚቀበሉት [ለ]ነጻነትን በመግለጥ ሄዱ።

፴፪ እንደዚህም ነበር በኃጢአታቸው፣ እውነትን [ሀ]ያለማወቅ ወይም በመተላለፍ፣ ነቢያትን አስወግደው [ለ]ለሞቱት ወንጌሉ የተሰበከው።

፴፫ እነዚህም በእግዚአብሔር [ሀ]እምነትን፣ ለኃጢአት ንስሀ መግባትን፣ ለኃጢአት [ለ]ስርየት [ሐ]የውክልና ጥምቀትን፣ እጆችን በመጫን የመንፈስ ቅዱስ [መ]ስጦታን ተምረው ነበር።

፴፬ እና እንደሰዎች በሥጋ [ሀ]እንዲፈረድባቸው በመንፈስ ግን እንደ እግዚአብሔር ይኖሩ ዘንድ ራሳቸውን ብቁ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን የወንጌል መሰረታዊ መርሆችን ሁሉ ተምረው ነበር።

፴፭ እና ስለዚህ በታናሹና በታላቁ፣ ጻድቅ ባልሆነው እና በታማኙ፣ ቤዛነት በእግዚአብሔር ልጅ [ሀ]በመስቀል ላይ ባቀረበው [ለ]መስዋዕት በኩል እንደመጣ በሙታኑ መካከል ታወቀ።

፴፮ እንደዚህም አዳኛችን በመንፈስ አለም በቆየበት ጊዜ በስጋቸው ስለእርሱ የመሰከሩትን ታማኝ [ሀ]ነቢያት መናፍስትን በማስተማር እና በማዘጋጀት ጊዜውን አንዳሳለፈ ታውቋል፤

፴፯ [ሀ]በአመጻቸው እና በመተላለፋቸው ምክንያት ራሱ በግል ሊሄድላቸው ለማይችለው፣ እነርሱም በአገልጋዮቹ አገልግሎት በኩል ቃላቶቹን ይሰሙ ዘንድ፣ የቤዛነት መልእክትን ለሙታን ሁሉ እንዲወስዱ ታውቋል።

፴፰ በዚህ ታላቅ የጻድቃን ስብሰባ ከተሰበሰቡት ታላቅ እና ሀያል ከሆኑት መካከል በዘመናት የሸመገለውና የሁሉም አባት፣ አባት [ሀ]አዳም ነበር፣

፴፱ እና የክብርም እናት [ሀ]ሔዋን፣ በዘመናት ውስጥ የኖሩት እና እውነት እና ህያው እግዚአብሔርን ካመለኩ ከብዙዎቹ ታማኝ ሴት ልጆቿ ጋር።

፵ የመጀመሪያው [ሀ]ሰማዕት [ለ]አቤል እና አባቱን አዳምን [ሐ]የሚመስለው ከሀይለኞቹ አንዱ ወንድሙ [መ]ሴትም በዚያ ነበሩ።

፳፱ ሀ ት. እና ቃ. ፸፮፥ ፲፪።
፴ ሀ ሉቃ. ፳፬፥ ፵፱።
ለ ቅ.መ.መ. መንፈሳዊ ጭለማ።
ሐ ት. እና ቃ. ፩፥ ፪።
፴፩ ሀ ኢሳ. ፷፩፥ ፪፤
ሉቃ. ፬፥ ፲፯–፲፱።
ለ ቅ.መ.መ. መብት።
፴፪ ሀ ት. እና ቃ. ፻፳፰፥ ፭።
ቅ.መ.መ. እውቀት።
ለ ዮሐ. ፰፥ ፳፩–፳፬።
፴፫ ሀ እ.አ. ፩፥ ፬።
ቅ.መ.መ. እምነት፣ ማመን።
ለ ቅ.መ.መ. የኃጢያት ስርየት።
ሐ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች—
የወኪል ስነስርዓት፤
ጥምቀት፣ መጥመቅ—
ለሙታን መጠመቅ።
መ ቅ.መ.መ. የመንፈስ
ቅዱስ ስጦታ።
፴፬ ሀ ቅ.መ.መ. ፍርድ፣
የመጨረሻው።
፴፭ ሀ ቅ.መ.መ. መስቀል፤
መስቀል።
ለ አልማ ፴፬፥ ፱–፲፮።
ቅ.መ.መ. መስዋዕት፤
የኃጢያት ዋጋን መክፈል፣
የኃጢያት ክፍያ።
፴፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥ ፶፯።
፴፯ ሀ ት. እና ቃ. ፻፴፰፥ ፳።
ቅ.መ.መ. አመጽ።
፴፰ ሀ ቅ.መ.መ. አዳም።
፴፱ ሀ ሙሴ ፬፥ ፳፮።
ቅ.መ.መ. ሔዋን።
፵ ሀ ቅ.መ.መ. ሰማዕት፣
ሰማዕትነት።
ለ ቅ.መ.መ. አቤል።
ሐ ዘፍጥ. ፭፥ ፫፤
ሙሴ ፮፥ ፲።
መ ቅ.መ.መ. ሴት።

፵፩ ስለጎርፉ ማስጠንቀቂያ የሰጠው [ሀ]ኖኅ፤ ታላቁ [ለ]ሊቀ ካህን [ሐ]ሴም፤ የታማኞቹ አባት [መ]አብርሐም፤ [ሠ]ይስሀቅ፣ [ረ]ያዕቆብ፣ እና የእስራኤል ታላቅ ህግ ሰጪ [ሰ]ሙሴ፤

፵፪ እና በትንቢትም አዳኙ ልባቸው የተሰበረውን ይጠግን ዘንድ፣ [ሀ]ለተማረኩትም ነጻነትን [ለ]ለታሰሩትም መፈታትን ይናገር ዘንድ ተቀብቷል ያለው [ሐ]ኢሳይያስም በዚያ ነበሩ።

፵፫ በተጨማሪም፣ በራዕይ እንደ ህያው ነፍሳት ሙታን [ሀ]በትንሳኤ እንደገና ሲመጡ ወደፊትም በስጋ የሚሸፈኑትን [ለ]የደረቁ አጥንቶች የተሞሉበት ታላቅ ሸለቆ ያየው [ሐ]ሕዝቅኤል፤

፵፬ ደግሞም የማይጠፋው ወይም ለሌሎች ሰዎች የማይሰጠው የእግዚአብሔር [ሀ]መንግስት በኋለኞቹ ቀናት መመስረትን ቀድሞ አይቶ እና ቀድሞ ነግሮ የነበረው [ለ]ዳንኤልም፤

፵፭ ከሙሴ ጋር [ሀ]በክብር የመለወጥ ተራራ ላይ የነበረው [ለ]ኢልያ፤

፵፮ እና [ሀ]ስለኤልያስ መምጣት የመሰከረው ነቢዩ [ለ]ሚልክያስ—ስለዚህም ሞሮኒ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝና የሚያስፈራው [ሐ]የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ይመጣል በማለት ያወጀው ሞሮኒም—በዚያ ነበሩ።

፵፯ ነቢዩ ኤልያስ በልጆች [ሀ]ልብ ውስጥ የአባቶቻቸውን ቃል ኪዳኖች ይተክላል፣

፵፰ ለሙታን ቤዛነት፣ እና ልጆችን ከወላጆቻቸው ጋር [ሀ]ለማስተሳሰር፣ መላው ምድር በምጽአቱ እንዳይረገሙ እና እንዳይጠፉ ዘንድ፣ [ለ]በዘመን ፍጻሜ በጌታ [ሐ]ቤተመቅደሶች ውስጥ የሚደረገውን ታላቅ [መ]ስራ ቀድሞ ለማሳየት።

፵፱ እነዚህ ሁሉ እና ብዙ ተጨማሪዎች፣ እንዲሁም በኔፋውያን መካከል የኖሩት እና ስለእግዚአብሔር ልጅ መምጣት የመሰከሩት [ሀ]ነቢያት፣ በታላቁ ስብሰባ ውስጥ በመደባለቅ እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ፣

፶ ሙታን ሰውነታቸው [ሀ]ከመንፈሳቸው ለረዥም ጊዜ መለየቱን እንደ [ለ]ባርነት ተመልክተውታልና።

፶፩ እነዚህንም ጌታ አስተማረ፣ እና ከትንሳኤው በኋላ ወደ አባቱ መንግስት በመግባት፣ [ሀ]በህያውነት እና [ለ]በዘለአለም ህይወት አክሊል ይጫንላቸው ዘንድም እንዲመጡ [ሐ]ሀይልን ሰጣቸው፣

፶፪ እና ከዚህም በኋላ በጌታ ቃል እንደተገባው በአገልግሎታቸው እንዲቀጥሉ፣ እና ለሚወዱትም ተጠብቀው የነበሩትን [ሀ]በረከቶች ሁሉ ተካፋይ እንዲሆኑ።

፶፫ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ፣ እና አባቴ ሀይረም ስሚዝ፣ ብሪገም ያንግ፣ ጆን ቴይለር፣ ዊልፈርድ ዉድረፍ፣ እና በዘመን ሙላት በታላቁ የኋለኛ ቀን ስራዎች [ሀ]መሰረትን

፵፩ ሀ ቅ.መ.መ. ኖኅ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ የአባቶች አለቃ።
ለ ቅ.መ.መ. ሊቀ ካህን።
ሐ ቅ.መ.መ. ሴም።
መ ዘፍጥ. ፲፯፥፩–፰። ቅ.መ.መ. አብርሐም።
ሠ ዘፍጥ. ፳፩፥፩–፭። ቅ.መ.መ. ይስሐቅ።
ረ ዘፍጥ. ፴፭፥፱–፲፭። ቅ.መ.መ. ያዕቆብ፣ የይስሐቅ ልጅ።
ሰ ቅ.መ.መ. ሙሴ።
፵፪ ሀ ኢሳ. ፷፩፥፩–፪።
ለ ቅ.መ.መ. ሲዖል።
ሐ ቅ.መ.መ. ኢሳይያስ።
፵፫ ሀ ቅ.መ.መ. ትንሳኤ።
ለ ሕዝ. ፴፯፥፩–፲፬።
ሐ ቅ.መ.መ. ሕዝቅኤል።
፵፬ ሀ ዳን. ፪፥፵፬–፵፭። ቅ.መ.መ. የእግዚአብሔር መንግስት ወይም መንግስተ ሰማያት።
ለ ቅ.መ.መ. ዳንኤል።
፵፭ ሀ ቅ.መ.መ. መለወጥ።
ለ ቅ.መ.መ. ኢልያ።
፵፮ ሀ ት. እና ቃ. ፻፲፥፲፫–፲፭። ቅ.መ.መ. ኤልያስ።
ለ ሚል. ፬፥፭–፮፤ ጆ.ስ.—ታ. ፩፥፴፮–፴፱። ቅ.መ.መ. ሚልክያስ።
ሐ ቅ.መ.መ. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት።
፵፯ ሀ ት. እና ቃ. ፪፥፲፮–፲፯።
፵፰ ሀ ቅ.መ.መ. ማተም፣ ማስተሳሰር፤ ቤተሰብ—ዘለአለማዊ ቤተሰብ።
ለ ቅ.መ.መ. ዘመን።
ሐ ቅ.መ.መ. ቤተመቅደስ፣ የጌታ ቤት።
መ ቅ.መ.መ. ለሙታን ደህንነት።
፵፱ ሀ ሔለ. ፰፥፲፱–፳፪።
፶ ሀ ቅ.መ.መ. መንፈስ።
ለ ት. እና ቃ. ፵፭፥፲፯።
፶፩ ሀ ቅ.መ.መ. የማይሞት፣ አለሟችነት።
ለ ት. እና ቃ. ፳፱፥፵፫። ቅ.መ.መ. የዘለዓለም ህይወት።
ሐ ፩ ቆሮ. ፮፥፲፬፤ አልማ ፵፥፲፱–፳፭።
፶፪ ሀ ኢሳ. ፷፬፥፬፤ ፩ ቆሮ. ፪፥፱፤ ት. እና ቃ. ፲፬፥፯።
፶፫ ሀ ት. እና ቃ. ፷፬፥፴፫።

ለመመስረት እንዲመጡ [ለ]የጠበቁት ሌሎች ምርጥ መናፍስት፣

፶፬ በተጨማሪም ቤተመቅደሶችን ለመገንባት እና በእነዚያም ውስጥ [ሀ]ለሙታን ቤዛነት ስነስርዓቶችን ለማከናወን የጠበቁት ምርጥ መናፍስትም በመንፈስ አለም ውስጥ ነበሩ።

፶፭ እነርሱም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ መሪዎች እንዲሆኑ [ሀ]የተመረጡት [ለ]በተከበሩትና በታላቆቹ መካከል እንደነበሩም አየሁ።

፶፮ ከመወለዳቸውም በፊት ከብዙ ሌሎች ጋር የመጀመሪያ ትምህርታቸውን በመንፈስ አለም ውስጥ የተቀበሉት እና በጌታ [ሀ]ጊዜ [ለ]በወይን ስፍራው ለሰዎች የነፍስ ደህንነት እንዲያገለግሉ ለመምጣት [ሐ]ተዘጋጅተውም ነበር።

፶፯ የዚህ ዘመን ታማኝ [ሀ]ሽማግሌዎችም ከዚህ ህይወት ሲሄዱ የንስሀ መግባት እና በእግዚአብሔር አንድያ ልጅ መስዋዕት በኩል የቤዛነት ወንጌልን [ለ]በጭለማ ውስጥ እና በሙታን መንፈሶች ታላቅ አለማት ውስጥ በኃጢአት ባርነት ላሉት በመስበክ አገልግሎታቸውን እንደሚቀጥሉ አየሁ።

፶፰ ንስሀ የገቡ ሙታንም የእግዚአብሔር ቤት [ሀ]ስርዓቶችን በማክበር [ለ]ይድናሉ፣

፶፱ እና የተላለፉት ቅጣታቸውን ከተቀበሉና [ሀ]ለመንጻትም ከታጠቡ በኋላ፣ [ለ]በስራዎቻቸው መሰረት ደመወዛቸውን ይቀበላሉ፣ የደህንነት ወራሾች ናቸውና።

፷ እንደዚህም ነበር የሙታን ቤዛነት የተገለጠልኝ፣ እና እመሰክራለሁም፣ እና በጌታ እና አዳኝ በሆነው፣ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በረከት በኩል ይህ መዝገብ [ሀ]እውነት እንደሆነ አውቃለሁ፣ እንዲህም ይሁን። አሜን።

፶፫ ለ ቅ.መ.መ. ቀድሞ መመረጥ።
፶፬ ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች—የወኪል ስነስርዓት።
፶፭ ሀ ቅ.መ.መ. ቀድሞ መመረጥ።
ለ አብር. ፫፥፳፪–፳፫።
፶፮ ሀ የሐዋ. ፲፯፥፳፮–፳፯።
ለ ያዕቆ. ፭፥፪–፫። ቅ.መ.መ. የጌታ የወይን አትክልት ስፍራ።
ሐ ኢዮብ ፴፰፥፬–፯፤ አልማ ፲፫፥፫–፯።
፶፯ ሀ ቅ.መ.መ. ሽማግሌ።
ለ ቅ.መ.መ. ሲዖል።
፶፰ ሀ ቅ.መ.መ. ስነስርዓቶች።
ለ ቅ.መ.መ. ቤዛ፣ ማዳን፣ ቤዛነት።
፶፱ ሀ አልማ ፭፥፲፯–፳፬። ቅ.መ.መ. ይቅርታ ማድረግ።
ለ ቅ.መ.መ. ስራዎች።
፷ ሀ ቅ.መ.መ. እውነት።

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፩

መፅሐፍ ቅዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞን እንደሚያስተምሩት፣ እርሱ ካላወጀበት በስተቀር አንድ ሚስት ብቻ ማግባት የእግዚአብሔር መሰረታዊ መርሆ እንደሆነ ያስተምራሉ (፪ ሳሙኤል ፲፪፥፯–፰ እና ያዕቆብ ፪፥፳፯፣ ፴ ተመልከቱ)። ለጆሴፍ ስሚዝ ከተሰጠ ረዕይ በኋላ፣ የብዛት ሚስቶች ማግባት ልምድ በቤተክርስቲያኗ በ፲፰፻፵ (እ.አ.አ.) አመታት መጀመሪያ ላይ ተመስርቶ ነበር (ክፍል ፻፴፪ን ተመልከቱ)። ከ፲፰፻፷ እስከ ፲፰፻፹ (እ.አ.አ.) አመታት፣ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ይህን የሀይማኖት ልምድ ህገ ወጥ የሚያደርጉ ህግጋትን መሰረተ። በመጨረሻም ህግጋቱ ትክክለኛ እንደሆኑ የዩ.ኤስ. ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋገጠ። ራዕይን ከተቀበሉ በኋላ፣ ፕሬዘደንት ዊልፈርድ ዉድረፍ የሚቀጥለውን መግለጫ ሰጡ፣ ይህም በቤተክርስቲያኗ እንደ ስልጣንና እንደሚያስተሳስር በጥቅምት ፮፣ ፲፰፻፺ (እ.አ.አ.) ተቀባይነትን አገኘ። ይህም ለቤተክርስቲያኗ የብዛት ሚስቶች የማግባት ልምድ መጨረሻ ሆነ።

ለሚመለከተው ሁሉ፥

የዩታ ኮሚሲዮን በቅርቡ በአገር ውስጥ ጸሀፊ መግለጫ ውስጥ የብዙ ጋብቻ ስርዓቶች እንደሚፈጸሙ እና ባለፈው ሰኔ ወይም ባለፈው አመት አርባ ተመሳሳይ ጋብቻዎች በዩታ ውስጥ እንደተደረጉ፣ ደግሞም በህዝባዊ ንግግሮች የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ካንድ ሚስት በላይ የማግባት ልምድ እንዲቀጥል አስተምረዋል፣ አበረታትተዋል፣ እና ገፋፍተዋል የሚል ለፖለቲካ አላማዎች በብዛት የታተሙ ወረቀቶች ከሶልት ሌክ ስቲ ተልከው ነበር—

እኔ፣ ስለዚህ፣ እንደ ኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት በአፅኖት፣ እነዚህ ክሶች ሀሰት እንደሆኑ እገልጻለሁ። ከአንድ ሚስት በላይ ማግባትን ወይም ጋብቻን ማብዛትን እያስተማርን ወይም ማንም ሰው ወደዚህ ልምድ እንዲገባም እየፈቀድን አይደለም፣ እና አርባ ወይም ማንኛቸውም የብዙ የጋብቻ ስርዓቶች በዚህ ጊዜ በቤተመቅደሳችን ውስጥ ወይም በግዛቱ ማንኛውም ስፍራ እየተከናወነ እንዳልሆነም እመሰክራለሁ።

በጸደይ ፲፰፻፹፱ (እ.አ.አ.) በሶልት ሌክ ስቲ መንፈሳዊ ስጦታ ቤት ውስጥ ጋብቻ እንደተፈጸመ የሚባልበት አንድ ጉዳይ ተመዝግቦ ነበር፣ ነገር ግን ያንን ስነ ስርዓት ማን እንደፈጸመው ለማወቅ አልቻልኩም፤ በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረገው ምንም ነገር እኔ በማላውቅበት ነበር። በመንፈሳዊ ስጦታ ቤት ውስጥ ተደረገ ስለተባለውም ያለመዘግየት በእኔ ትእዛዜ ፈርሷል።

እነዚህም ህግጋት በመጨረሻው አማራጭ ፍርድ ቤት ህገ መንግስታዊ እንደሆነ የፈረዱበት፣ ብዙ ሚስቶችን ስለማግባት ኮንግረሥ ባሳለፋቸው ህግጋት መሰረት፣ እነዚህን ህግጋት ለማክበርና በምመራቸው ከቤተክርስቲያኗ አባላት ጋር ያለኝን ተፅዕኖ በመጠቀም እንደእኔ እንዲያደርጉ ለማድረግ ያለኝን ፈቃድ በዚህ እገልጻለሁ።

በተጠቀሰው ጊዜ በቤተክርስቲያኗ እኔ ወይም አብሬአቸው ከምሰራው በምናስተምራቸው ውስጥ ብዙ ሚስቶችን ማግባትን የሚያበረታታ ወይም እንደሚያዳብር ሊተረጎም የሚችል ምንም የለም፤ እና የቤተክርስቲያኗ ማንም ሽማግሌ እንደዚህ አይነት ትምህርትን እንደሚሰጥ የሚመስል ቋንቋዎችን በተጠቀመ ጊዜ፣ ወዲያው ተገስጿል። አሁንም ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ምክሬ በምድር ህግ የተወገደውን ምንም ጋብቻ ውል ማስገባትን እንዲያቆሙ እንደሆነ በህዝብ ዘንድ አውጃለሁ።

ዊልፈርድ ዉድረፍ
የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ
ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት።

ፕሬዘደንት ሎሬንዞ ስኖው የሚቀጥሉትን አቀረቡ፥

"ዊልፈርድ ዉድረፍን እንደ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት፣ እና በዚህ ጊዜ የማተም ስነስርዓቶችን ቁልፎች በምድር ላይ እንደያዘ ሰው በመቀበል፣ በመስከረም ፳፬ ቀን ፲፰፻፺ (እ.አ.አ.) ቀን እንድንሰማው የተነበበውን ህዝባዊ መግለጫን ለመስጠት ሙሉ ስልጣን እንዳላቸው በመቀበል፣ በአጠቃላይ ጉባኤ እንደተሰበሰብነው ቤተክርስትያን ይህን ብዙ ሚስቶች ማግባትን በሚመለከት ያወጁት አስገዳጅ እና በስልጣን እንደሆነም እንቀበላለን።"

ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ፣ ጥቅምት ፮፣ ፲፰፻፺ (እ.አ.አ.)።

ከፕሬዘደንት ዊልፈርድ ዉድረፍ
ስለህዝባዊ መግለጫ ከሰጡት
ሶስት ንግግሮች የተወሰደ ምንባብ

ጌታ እኔን ወይም በዚህች ቤተክርስቲያን እንደ ፕሬዘደንት የሚቆም ማንንም ሰው እናንተን ወደ ስህተት እንዲመራ አይፈቅድም። ይህም በአላማው ውስጥ አይደለም። ይህም በእግዚአብሔር ልብ አይደለም። ይህን ብሞክር፣ ጌታ ከስፍራዬ ያስወጣኛል፣ እና የሰዎች ልጆችን ከእግዚአብሔር ቃላት እና ከሀላፊነታቸው እንዲሳሳቱ የሚጥረውንም እንዲሁ ያደርጋል። (የቤተክርስቲያኗ ሰላሳ አንደኛው የአጠቃላይ ጉባኤ፣ ጥቅምት ፮ ቀን ፲፰፻፺ [እ.አ.አ.]፣ ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ። በ*Deseret Evening News* [ደዘረት የምሽት ኮኮብ ዜና] ሀተታ፣ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፰፻፺፣ ገፅ ፪።)

ማንም ይኑር ወይም ይሙት፣ ወይም ማንም ይህችን ቤተክርስቲያን ለመምራት መጠራቱ አስፈላጊ አይደለም፣ በሁሉም ገዝ እግዚአብሔር መነሳሳት መምራት አለባቸው። ይህን በዚህ መንገድ ባያደርጉ፣ ሊያደርጉትም አይችሉም. . .።

አንዳንድ፣ እና በጣም አስፈላጊ የሆኑትንም፣ ራዕዮችን ባለፉት ጊዜያት አግኝቻለሁ፣ እና ጌታ ምን እንዳለኝም እነግራችኋለሁ። ህዝባዊ መግለጫ ስለተባለው ታስቡበት ዘንድ ላድርግ. . .።

ጌታ የኋለኛውን ቀን ቅዱሳንን ጥያቄ እንድጠይቅ ነገረኝ፣ እና የምላቸውን ቢሰሙና የምጠይቃቸውንም ቢመልሱ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ እና ሀይል ሁሉም እንደ አንድ ይመልሳሉ፣ እና ስለዚህ ጉዳይም በአንድነት ያምናሉ በማለትም ነገረኝ።

ጥያቄውም ይህ ነው፥ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን መከታተል ያለባቸው የጥበብ መንገድ የትኛው ነው—የቤተመቅደሶችን ሁሉ ማጣትን እና መወረስን፣ እና በእነርሱም ውስጥ ለህያው እና ለሙታን የሚደረጉትን ስርዓቶችን ማቆምን፣ እና የቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራርና አስራ ሑለት፣ እና የቤተሰብ መሪዎች መታሰርን፣ እና የህዝብ (ይህን ልምድ የሚያቆሙትን ሁሉ) የግለሰብ ንብረቶች መወሰድን ክፍያ በማድረግ የሀገር ህግጋትና ስልሳ ሚልዮን የሚቃወሙትን ብዙ ሚስት የማግባት ልምድን ለመቀጠል መሞከርን፤ ወይም ይህን መሰረታዊ መርሆ በማክበር ከደረሰብን እና ከተሰቃየናቸው በኋላ፣ በህጉ ታዛዥ በመሆን እና ይህን ልምድ በማቆም፣ እና ይህን በማድረግም ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ እና አባቶችን ህዝብን እንዲያስተምሩ እና የቤተክርስቲያኗን ሀላፊነታቸውን እንዲያከናውኑ በቤት በማቆየት፣ እና ደግሞም የወንጌልን ስርዓቶችን ለህያው እና ለሙታን ለማድረግ እንዲችሉ ቤተመቅደሶችን በቅዱሳን እጆች ውስጥ እንዲቀሩ በማድረግ ነውን?

ጌታ በመግለጫ እና በራዕይ ይህን ልምድ ባናቆም ምን እንደሚደርስ አሳይቶኛል። ይህንን ካላቆምን፣ ማናችሁም በዚህ በሎጋን ቤተመቅደስ ላሉት ለማንኛውም ሰው ምንም ጥቅም ባልሰጣችሁ ነበር፤ በፅዮን ምድር ውስጥ ሁሉም ስነ ስርዓቶች በቆሙ ነበር። በእስራኤልም ግራ መግባት በነገሰ ነበር፣ እና ብዙ ሰዎችም እስረኞች በሆኑ ነበር። ይህም ችግር በቤተክርስቲያኗ ሙላት ላይ ይመጣ ነበር፣ እና ይህን ልምድ ለማቆምም እንገደድ ነበር። አሁን፣ ጥያቄውም በዚህ መንገድ ይቁም፣ ወይስ ጌታ በገለጸልን መንገድ፣ እና ነብያቶቻችንን እና ሐዋሪያቶቻችንን እና አባቶችን በነጻነት እንተዋቸው እና ሙታን እንዲድኑም ቤተመቅደሳችንን በህዝብ እጆች ውስጥ እንተዋቸው ነው። በዚህ ህዝብ አማካይነት በመንፈስ አለም ውስጥ ካለው የእስር ቤት ታላቅ ቁጥር ያላቸው ድነዋል፣ እና ስራው ይቀጥል ወይስ ይቁም? ይህን ጥያቄ በኋለኛው ቀን ቅዱሳን ፊት አስቀምጣለሁ። ለራሳችሁ መፍረድ አለባችሁ። ለራሳችሁ እንድትመልሱበት እፈልጋችኋለሁ። እኔ አልመልሰውም፤ ነገር ግን የወሰድነውን መንገድ ባንወስድ ኖሮ ይህም እንደ ህዝብ ልንገኝበት የምንችልበት ሁኔታ ነው እላችኋለሁ።

. . .አንድ ነገር ባይደረግ ኖሮ ምን ሊሆን እንደሚችልም አይቼ ነበር። ይህም መንፈስ በእኔ ላይ ለረዥም ጊዜ ኖሮኝም ነበር። ነገር ግን ይህን ለማለት እፈልጋለሁ፥ የእግዚአብሔር ሰማይ ያደረግሁትን እንዳደርግ ባያዘኝ ኖሮ፣ ቤተመቅደሶችን ሁሉ ከእጆቻችን አስወጣ ነበር፤ ራሴም ወደ እስር ቤት፣ እና እያንዳንዱንም ሰው ወደዚያ እንዲሄድ አደርግ ነበር፤ እና ያን እንዳደርግ የታዘዝኩበት ሰዓት ሲመጣ፣ ይህም ለእኔ ግልፅ ነበር። ከጌታም ፊት ሄድኩ፣ እና ጌታ እንድፅፍ የነገረኝን ጻፍኩ. . .።

ይህን ከእናንተው ዘንድ የምተወው እናንት እንድታሰላስሉበት እና እንድታስቡበት ነው። ጌታ ከእኛ ጋር እየሰራ ነው። [ካሽ ካስማ ጉባኤ፣ ሎገን፣ ዩታ፣ እሁድ፣ ህዳር ፩ ቀን ፲፰፻፺፩ (እ.አ.አ.)። በ*Deseret Weekly* [የደዘረት ሳምንታዊ ዜና] ሀተታ ውስጥ፣ ህዳር ፲፬ ቀን ፲፰፻፺፩ (እ.አ.አ.)።]

አሁን የተገለጸልኝን እና በዚህ ነገር የእግዚአብሔር ልጅ ምን እንደፈጸመ እነግራችኋለሁ. . .። ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ፣ ህዝባዊ መግለጫው ባይሰጥ ኖሮ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሆኑ ነበር። ስለዚህ፣ በአዕምሮው ውስጥ ላሉት አላማዎች የእግዚአብሔር ልጅ ያንን ነገር ለቤተክርስቲያኗ እና ለአለም እንዲቀርቡ ፈቃዱ ነበር። ጌታ የፅዮንን መመስረት አውጇል። የዚህ ቤተመቅደስ መፈጸምን አውጇል። የህያው እና የሙታን ደህንነት በእነዚህ ተራሮች ሸለቆዎችም ውስጥ መሰጠት እንዳለባቸውም አውጇል። እና ሁሉን

የሚገዛ እግዚአብሔር ያወጀውን ዲያብሎስ ሊያሰናክል አይችልም። ያንን ለመረዳት ከቻላችሁ፣ ያም ለዚህ ቁልፍ ነው። (በሚያዝያ ፲፰፻፺፫ [እ.አ.አ.] በሶልት ሌክ ቤተመቅደስ መመረቂያ ስድስተኛ ስብሰባ ላይ ከተሰጠው ንግግር። የመመረቂያው ስብሰባ የተተነበየበት ፅሑፍ፣ ፅሑፋዊ ሰነዶች፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ ዲፓርትመንት፣ ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ።)

አስተዳደሪያዊ አዋጅ ፪

መፅሐፈ ሞርሞን እንደሚገልጸው፣ “ሁሉም ለእግዚአብሔር አንድ ናቸው፣” እንዲሁም “ጥቁርም ነጭም፣ ባሪያውና ነፃው፤ ሴትና ወንድ” (፪ ኔፊ ፳፮፥፴፫)። በቤተክርስቲያኗ ታሪክ በሙሉ፣ የእያንዳንዱ ዘረ አባል የሆኑ የብዙ ሀገሮች ሰዎች ተጠምቀዋል እናም እንደ ቤተክርስቲያኗ ታማኝ አባላት ኖረዋል። በጆሴፍ ስሚዝ ህይወት ውስጥ፣ አንዳንድ ጥቁር ወንድ አባላት በክህነት ተሾመው ነበር። በታሪኳ መጀመሪያ፣ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ከአፍሪካ ትውልድ ለሆኑ ወንድ አባላት ክህነትን መስጠት አቆሙ። የቤተክርስቲያኗ መዝገቦች የዚህ ልምድን መጀመሪያ ምን እንደሆነ ምንም አስተያየት አይሰጡም። የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ይህን ልምድ ለመቀየር የእግዚአብሔር ራዕይ አስፈላጊ መሆኑን አምነው ነበር እናም በጸሎት መመሪያን ፈለጉ። ራዕይም ለፕሬዘደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል መጣ እናም በሰኔ ፩፣ ፲፱፻፸፰ (እ.አ.አ.) ለሌሎች የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ይህም ተረጋግጦ ነበር። ራዕዩም በክህነት ላይ በዘር ምክንያት የሚገድበውን በሙሉ እንዲወገድ አደረገ።

ለሚመለከተው ሁሉ፥

በመስከረም ፴፣ ፲፱፻፸፰ (እ.አ.አ.)፣ በ፻፵፰ኛው የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የአመቱ ግማሽ አጠቃላይ ጉባኤ ላይ በቤተክርስቲያኗ ቀዳሚ አመራር የመጀመሪያ አማካሪ ፕሬዘደንት ኤን ኤልደን ታነር የሚቀጥለው ቀረበ፥

በዚህ አመት ሰኔ መጀመሪያ ላይ፣ ክህነትን እና የቤተመቅደስ በረከቶችን ለሁሉም ብቁ የቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ ስለመስጠት ፕሬዘደንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል ራዕይ ተቀብለው እንደነበር ቀዳሚ አመራር አስታወቁ። በቅዱስ ቤተመቅደስ በተቀደሰ ክፍሎች ውስጥ ከረጅም ጥልቅ ሀሳብ እና ጸሎት በኋላ የመጡላቸውን ይህን ራዕይ ከተቀበሉ በኋላ፣ ይህን ለተቀበሉት እና ለተስማሙት አማካሪዎቻቸው እንዳቀረቡ ለጉባኤው እንድነግር ፕሬዘደንት ኪምባል ጠይቀውኝ ነበር። ከዚያም ይህ ለአስራ ሑለቱ ሐዋርያት ቡድን ቀረበ፣ እነርሱም በአንድ ድምፅ ተስማሙበት፣ እና በኋላም ለሁሉም አጠቃላይ ባለስልጣናት ቀረበ፣ እነርሱም በተመሳሳይ ሁኔታ በአንድ ድምፅ ተስማሙበት።

ፕሬዘደንት ኪምባል አሁን ይህን ደብዳቤ እንዳነብ ጠይቀውኛል፥

ሰኔ ፰ ቀን ፲፺፻፸፰
በአለም አቀፍ ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አጠቃላይ እና የአካባቢ የክህነት ሀላፊዎች ሁሉ፥

ውድ ወንድሞች፥

የጌታ ስራ በምድር ላይ ሲያድግ በምስክርነቱን ስናይ፣ የብዙ ሀገሮች ህዝብ ዳግም የተመለሰውን የወንጌል መልእክት ስለተቀበሉ፣ እና ዘወትር በሚያድግ ቁጥሮች በቤተክርስቲያኗ አባል ስለሆኑ ምስጋና አለን። ይህም በተራው ወንጌሉ የሚያቀርባቸውን ሁሉንም መብቶች እና በረከቶች ለእያንዳንዱ ብቁ የቤተክርስቲያን አባላት ለማቅረብ ያለንን ፍላጎት አነሳስቶናል።

አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘለአለማዊ አላማ ብቁ የሆኑት ወንድሞቻችን ሁሉ ክህነትን እንደሚቀበሉ ከእኛ በፊት የነበሩት የቤተክርስቲያኗ ነቢያት እና ፕሬዘደንቶች የሰጡትን የተስፋ ቃል እያወቅን፣ እና ከክህነት ስልጣን ተወግደው የነበሩትን ታማኝነት ምስክር በመሆን፣ ብዙ ሰዓቶችን በቤተመቅደሱ ታላቅ አዳራሽ ውስጥ ጌታን ለመለኮታዊ አመራር በመለመን ለረጅም ጊዜ እና በቅንነት ለእነዚህ ታማኝ ወንድሞቻችን ለምነን ነበር።

ጸሎታችንን ሰምቷል፣ እና በራዕይም እያንዳንዱ ታማኝ፣ ብቁ ወንድ ሰው በቤተክርስቲያኗ ውስጥ፣ መለኮታዊ ስልጣኑን ለመጠቀም ካለው ሀይል ጋር፣ ቅዱስ ክህነትን ለመቀበል እና ከቤተመቅደስ በረከት በተጨማሪ፣ ከሚወዳቸው ጋር ከዚያ የሚፈሱትን እያንዳንዱን በረከት እንዲደሰቱ ለረጅም ጊዜ ቃል የተገባለት ቀንም እንደደረሰ አረጋግጧል። በዚህም መሰረት፣ የቤተክርስቲያኗ ብቁ ወንድ አባላት ለዘር ወይም ቀለም ትኩረት ሳይሰጥ ወደክህነት ስልጣን ሊሾሙ ይችላሉ። የክህነት መሪዎችም ለዚህ ለአሮናዊ ወይም ለመልከ ጼዴቅ ክህነት ሹመት ተመራጭ ለሆኑት ሁሉ ለብቁነት የተመሰረተውን መሰረቶች እንደሚያሟሉ ለማረጋገጥ የጥንቃቄ ቃል ጥያቄ አመራርን እንዲከተሉ ታዝዘዋል።

ጌታ በአለም ውስጥ ሁሉ ያሉትን የባለስልጣን አገልጋዮቹን ድምፅ የሚያዳምጡትን እና የወንጌል እያንዳንዱ በረከቶችን ለመቀበል ራሳቸውን የሚያዘጋጁ ልጆቹን ለመባረክ ያለውን ፍላጎት እንዳስታወቀ በትጋት እናውጃለን።

በቅንነት የእናንተው፣

ስፔንሰር ደብሊው ኪምባል
ኤን ኤልደን ታነር
ሜሪዮን ጂ ሮምኒ

ቀዳሚ አመራር

ስፔንሰር ደብሊው ኪምባልን እንደ ነቢይ፣ ገላጭ፣ እና ባለራዕይ፣ እና እንደኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዘደንት በመቀበል፣ እኛ እንደ አባል ተሰብሳቢዎች ይህን ራዕይ እንደ ጌታ ቃል እና ፈቃድ እንድንቀበል ቀርቦልናል። ይህን የሚቀበሉ ቀኝ እጃቸውን በማንሳት ያሳዩ። የሚቃወሙም በዚህ አይነት ምልክት።

ይህ የቀረበው ሀሳብ በአንድ ድምፅ ምርጫ በአዎንታዊነት ተደግፏል።

ሶልት ሌክ ስቲ፣ ዩታ፣ መስከረም ፴ ቀን ፲፱፻፸፰ (እ.አ.አ.)።